
የጠብታ ፍንጣቂ!*

(ገ.ነ.ብልጣሶር)



ከመከራ ለብራክና ከሥቃያት ማህፀን ተፈልቅተው የወጡ፣ የለሥራ ለምስት ጥቁር ለመታት፣ ያላዛሞቹ ኢትዮጵያውያን ታሪካዊ ውልዶች።

የጠፍ. ቁ. 2—12

* በተከታታይ የሚወጡ ያጫጭር ልቦ-ወለድ ታሪኮች ማኅደር ገጽታ ይህ ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF

Yeshigigir Deba
(G.N. Biltasor)
Författares Bokmaskin, Stockholm 1990
ISBN 91 7328 675 3
July 1989
STOCKHOLM — SWEDEN

t.me/OLDBOOKSPDF

የምንገኝበት መጠቆምያ

ሥያሜያችን		አድራሻችን
1.	የአርእስተ ግጽ	1
2.	የምንኖበት መጠቆሚያ	3
3.	የእርስዎ እስካልሆነ ድረስ	5
4.	መዘክሩ ትውንልኝ	7
5.	እንተዋወቅ	9
6.	የሽግር ደባ	65
7.	አዋልደ-ወንዴ	79
8.	የተጣሰ አጥር	103
9.	ሞኝ ባኮ	137
10.	ሩብያ	169
11	ዘሊባኖስ	203
12.	እየመረረ የሚጣፍጥ	239
13.	ሠመነ	269
14.	እናቴን ለመቅበር	303
15.	ብድር በምድር	327

የርስም እስካልሆነ ድረስ

" ጎሊና ያለው ሰው " ማለት የሞራል ሕግ የሚገዛው ነው። እንደዚያ ዓይነቱን ሰው ደግሞ የገዛ ራሱ ያልሆነ ነገር ሁሉ አይማርከውም። በመሆኑም የሌሎችን " አትመኝ፣ አትንካ፣ አትስረቅ....." ብለው አይነግሩትም። የዚህች ቀጎንጽል መጣፍ ባለቤትነት የርስም እስካልሆነ ድረስ፣ ያለደራሲው ፈቃድ በፈለ ጉት ሁኔታ ለመጠቀም እንደማያስቡ በባለጎሊና ሰውነ ትም ደራሲው ተስፋ ያደርጋል።

t.me/OLDBOOKSPDF

የጠለቀ ምሥጋና

ይህ መጽሐፍ፣በዚህ መልኩ ታትሞ እንዲወጣ ግማሹን ያህል ርዳታ ለሰጠኝ፣ አንድ መንግሥታዊ ድርጅት፣ስሙ ተጠቅሶ መመሥገን ባለመፈለጉ ተውኩት እንጅ፣መጽሐፉን አግኝተው የማንበብ ዕድል በሚያጋጥማቸው ወገኖች ስም፣ የጠለቀ ምሥጋና (djupa tacksamhet) ለማቅረብ ወስኜ ነበር።

ሌላው እንኳ ቢቀር፣ "ሞያ በልብ ነው" እንደሚባለው፣ ድርጅቱ "አታመሥግኑኝ" ማለቱ ብቻ፣ ሊያስመሠግነው ይገባም ነበር። በዚህ አጋጣሚ፣ ይህ ድርጅት የሚመራበት ታላቅና ክቡር ዓላማ፣ገና በማደግ ላይ ለሚገኙ ለየብሔረ-ሰቡ ሥነ-ጽሑፍ አምራች ደራስያን ሁሉ፣ ርዳታዊ ተልእኮው፣"በርቱ!" የሚል ማነቃቂያ በመሆኑ፣በይፋና ባደባባይ ሊያደንቁት የሚገባ ነው።

ይህን እትም ከሌሎቹ እትሞች ሁሉ ልዩ የሚያደርገው፣ የማሳተሚያውን ግማሽ ወጭ የሸፈነው፣በ"ጠረጋ ሥራ"(ተግባረ-ጽዳት) የተገኘ አበል መሆኑ ነው። ምናልባትም ጉድፉ መካን ባለመሆኑ፣ገና ብዙ አስደርሶ ያሳትምልኝ ይሆናል።

t.me/OLDBOOKSPDF

መዘክሩ ትሁንልኝ



መምህር ጣሰው ቸርነት

(19?? - 19??)

(ያልኖረበትን ሕይወት መመዝገቤ ምን ይጠቅመዋል?)

ይህ ዓለም ለሰው ልጅ ሲባል እንጅ፣ በተቃራኒው የሰው ልጅ ለዓለም ሲባል አልተፈጠረም። በመሆኑም፣ የዓለማችን ዓቢይ ቁም ነገር፣ የሰው ልጅ ነው። ይህ እስከሆነም ድረስ፣ ጠቅላላው ዓለም ለሰው ልጆች ፍስሐና ተድላ ሊያረጋግጥለት ይገባል እንጅ በግልብጡ፣ የሰው ልጆች ለዓለም ምርኮኛ ሊያደገድጉለት አይገባም። ዓለም በባሕርዩም ሆነ በተፈጥሮአዊ መዋቅሩ፣ ለሰው ልጆች ርካታ ተስማሚና አመች ሆኖ መዘጋጀቱን እናውቃለን። የሰው ልጅ ጎሊናዊ ጡንቻው በጐለበተ መጠን፣ ዓለምን እንደ ወላድ ጥገት የፍላጎቱን ያህል፣

ሲሳያዊ ወተቱን ሊያልብ ይችላል። በሕዋና በየብስ፣ በባሕርና በውቅያኖስ፣ ዓለም አርግዞት ያለው የሚሳይ ድልብ፣ ይህን ያህላል ብሎ ለመናገር ያስቸግራል። ዝና ያልተነካው የሕዋ ውስጥ ጠቋር መካናት (Black Spots) ብቻ፣ አርግዞት ያለው ኃይለ-ጉልበት፣ ፍፁም ድንግል ነው። በየብስ ውስጥም ተሠ ውረው ያሉ ልዩ ልዩ ማዕድናትም፣ ለዘመናት የሚዛቁ የጠቅላ ላው የሰው ልጅ ድልባዊ ቅርሶች ናቸው። የታላላቆቹ ውቅያ ኖሶች ወለሎች ብቻ፣ አፍነው በያዙት ሀብት አንባር፣ የሰውን ልጅ ከሀላዌ ቀቢፀ ተስፋ፣ ነፃ የሚያወጡ ጽንፍ የሌላቸው የሕይወት አለኝታዎች ናቸው።

ይሁን እንጅ፣ እንደ ኣጋጣሚ ሆኖ፣ እፍኝ በማይሞሉ የስግብግቦች ዕቡይ አርአያነት ተፅዕኖ የተነሣ፣ የሰው ልጆች ያለ ተፈጥሮአዊ ተልእኮአቸውና ያለ ዓለማችንም ነባር ባሕርይ፣ ለዓ ለሙ ሲያረግዱለትና ሲያብዱለት እናያለን። በአንፃሩም፣ ይህ ዐይነቱ ኢሰብኣዊ ዝንባሌ የማይሰማቸው፣ ብዙ ግሑሳን ሰዎች በየሀገሩ ማኅበረ-ሰብ ውስጥ ይገኛሉ። የነዚህ ሰዎች ምድራዊ ሕላዌ ግብ የተነደፈው፣ ለዓለሙ መብለጭለጭ ሳይሆን፣ ለሰው ልጆች ጤናማ ሕይወት ዋስትና ላይ ነው። የነዚህ ሰዎች አጠቃላይ ተጋድሎና መሥዋዕትነት፣ ለሰው ልጅ መሠረ ታዊ ሕይወት የጋርዮሽ ሕጋዊ ርካታ ማግኘት ነው። ስለዚ ህም፣ የራሳቸው ግለኛ ኑሮና ሕይወት፣ ዶጋመድ ቢሆንና አፈር ድሜ ቢግጥ፣ ጨርሶ ደንታቸው አይደለም። ዝምበር ሠርቃ እስክታርብ ድረስ፣ የየቀኑ ተግባራቸው፣ የሰውን ልጅ በሚችሉት ሁሉ ማገልገል ነው። ለግላቸው ጥቅምም ሆነ ዝና፣ ለራሳቸው ምቾትም ሆነ ብልፅግና በፍፁም አያልሙም። ለታ መመው መድኃኒት፣ ለመሐይምኑ እውቀት፣ ለተራበው ምግብ፣ ለታረዘው ልብስ፣ ለሚበሳጨው መጽናናት፣..... ሆነው

t.me/OLDBOOKSPDF

በማገልገላቸው ብቻ ራሳቸውን እንዳገለገሉ ያህል ይሰማቸዋል። ሞራላቸውና ሥነ-ምግባራቸው፣ ሰውን ባለ አቅማቸው በማገ ልገል ላይ የተመሠረተ ነው። ከዚህ ሰብዓዊ ልግሥናና በጎምግ ባር ውጭ፣ እነዚህን ሰዎች ሌላ ነገር አይታያቸውም። ባስተሳ ሰባቸው ክልል ውስጥ " ለኔ- ለግሌ " የሚል ስሜትና ዝንባሌ አልሠረፀባቸውም። እነዚህን የመሰሉ ሰዎች፣ ቁጥራቸው ኣይ ብዛ እንጅ፣ በየዘመኑ ጣቢያዎች ላይ ብቅ ብቅ እያሉ አልፈ ዋል። እጅግ በጣም የሚደንቀኝ ግን፣ እነዚህን መሳይ ሰዎች ዓለምም ሆነ ሕዝብ በሥርዓት ሳያውቃቸው ማለፋቸው ነው። ተደብቀው ተወልደው፣ ተደብቀው ኖረው፣ ተደብቀው ያልፋሉ።

ከነዚህ መሰል ሰዎች አንዱ መምህር ጣሰው ነበር። የዚህን ወንድም፣ ክቡር ሰብዕናና ግሑስ ባሕርይ፣ ኣሟልቶ ለመግለፅ እጅግ በጣም ያስቸግራል። ምንም ዓይነት የብዕር ኃይል ሊገልጸው የማችልም ሆኖ ይሰማኛል። እንደ ማንኛ ውም ሰው ሁሉ ከሰው የተገኘ በመሆኑ፣ የደረጁ ወላጆች አሉት። ይሁን እንጅ፣ መምህር ጣሰው ኣዘውትሮ አያገኛ ቸውም ነበር። ለተሰለፈበት ማኅበራዊ ተግባር፣ አብዛኛው ጊዜውን የሠዋ በመሆኑ፣ የቅርብ ወላጆቹን እንኳ ለመሳብኘት በቂ ጊዜ አልነበረውም። ልጅነቱ፣ የማኅበረ-ሰቡ ነበር።

መምህር ጣሰው፣ እንደኛ ላለው ሕዝብ፣ መዳኛ መድ ኃኒቱ ትምህርት ብቻ መሆኑን ቀደም ብለው ከተረዱት ጥቂት ወገኖች ውስጥ አንዱ በመሆኑ ብዙ ሲሳይ ሊያስገኝለት ከሚች ለው የሠዓሊነት ሙያው ኣፈንግጦ በመውጣት፣ መምህራን ለመሆን ከሚዘጋጁ ወጣቶች ኢንስቲትዩት ተሠማርቶ በፍፁም ቅንነት ያስተምር ነበር። ከምድብ የመምህርነት ሥራው ውጭ ትምህርት ቤቱን እንደ ግል ቤተ-ሰቡ በመቍጠር፣ ሌላው

ቀርቶ እዚያው ትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚያድርበት ቀናት ጥቂት አልነበረም። ከሥራው መመሠጥ የተነሳ፣ የምግብ ሰዓቶ ችን ሳይቀር ይዘነጋቸው ነበር። ተማሪዎቹን እንደግል ልጆቹ ስለሚቆጥራቸው፣ እጅግ ይሳሳላቸው ነበር። ታዲያ ያን ሁሉ የሚያደርገው፣ የራሱ ሕፃናትና የግሉ ቤተሰብ ሳይኖረው ቀርቶ አይደለም። እነሱንም ቢሆን አንዳንድ ጊዜ ለሣምንት ያህል፣ እስከ መኖራቸው ድረስ ይረሳቸው ነበር። በመምህር ጣሰው ንጎሊና ውስጥ ምንጊዜም የሰፈነው፣ እንደ ዐይኑ ብሌን የሚሳ ሳለት ብዙኃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ እድገትና መሻሻል ነበር። የሚያስበውን ያህል፣ የወገኑ እድገት እጅግ ባለመራመዱ፣ የመ ንፈስ ብስጭት እያደረበት፣ ጤናው ይረበሽ ነበር።

ምድብ የስነ-ጥበብ ትምህርቱን በሚያስተምርበት ወቅት፣ በተማሪዎቹ ዘንድ ብቻ ሳይሆን፣ በሌሎች መምህራንም ጭምር ከፍተኛ አድናቆትን አትርፎለታል። በመረጃነት የሚያቀ ርባቸው የተለያዩ ናሙናዎች ሳይቀሩ፣ እጅግ የሚያስደንቁና ከዚያው ካካባቢው የሚሰበስባቸው ነበሩ። ከሌሎች መምህራን ጋርም የነበረው መግባባትና የሚያደርጋቸውም ውይይቶች፣ ጎሊናን ሠንጥቀው የሚገቡ ቁም ነገሮች ነበሩ። ከሁሉም ደግሞ፣ ከዚያ ሁሉ ችሎታውና ተሰጥዎው ውጭ የሚታይበት ትህትና የፍፁምነት ሰብዕናውን የሚያንፀባርቅ ልዩ ምልክት ነው። በዚያ የእጩ መምህራን፣ መሠልጠኛ መናኸርያ ውስጥ፣ የእንደ መምህር ጣሰው ዓይነት ሰው መኖር ከሚሰ ጠው ምድብ ትምህርት ይልቅ፣ አርአያነቱ ከፍተኛ ዕሴት አለው። አንዳንድ ተማሪዎችን ለመሳብኘት መምህር ጣሰውን ቅዳሜና እሁድ ጭምር ዶማና አካፋውን ይዞ ሲያይ፣ የትምህርት ቤቱ አትክልተኛ እንጅ የቀለም መምህር አይመስላቸውም ነበር። ጊቢውን በጽጌያትና በተክሎች አሸብ

t.me/OLDBOOKSPDF

ርቆት፣ ግንተ-ጽጌ ምሥጋን ይንሣው። እንዲውም ካለበት ትውልድ አልፎ ለመጭው ትውልድ ጭምር የሚያስብ ሰው መሆኑን የተከላቸው ዕፀዋት ጭምር ሳይቀሩ ይመሰክሩለታል። ዘመናት ቆጥረው የሚያፈሩ ተክሎች ሳይቀሩ በጊቢው ውስጥ ነበሩት። " ጅል ሰው የመጨረሻዪቱን ድንች ሲበላት፣ ጠቢብ ሰው ግን ይተክላታል " እንዲሉ፣ መምህር ጣሰውም፣ የባለ ዘጠና ዓመቱ አረጋዊ፣ የብርቱካን ችግኝ ተክሎ ውሃ ሲያጠጣ ያየው አንድ ሞኝ " ምን ትፋሽካለህ መቶ ደርሶልህ ለመብላት ነው? " ሲል በማፌዝ ቢጠይቀው " መጪው ትውልዴ ይመ ገብልኛል " እንዳለው ሰው ዓይነት ነበር፣ አትክልታዊ ተግ ባሩ። እንዲህ ዓይነቱ የመምህር ጣሰው የየቀኑ ተግባር፣ ጥቂቱ ክፍል ብቻ ሲጠቀስ ነው። ይህ ተግባሩም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ብቻ የሚታየው ሲሆን፣ ከትምህርት ቤቱ ውጭ የሚያ ከናውናቸው ልዩ ልዩ ሥነ ምግባሮቹን መዘርዘር ያስቸግራል።

እንደ እድር ባሉት የማኅበረ-ሰቡ ባሕላዊ ማኅበራት ውስጥ፣ መምህር ጣሰው ዓይነተኛው ቁልፍ ነበር። በአጭ እምነስ ከሚያዘጋጃቸው የኪነት ውጤት ሽያጭ ገንዘቡ ውስጥ፣ አብዛኛውን የሚያውሰው፣ ባካባቢው የሚገኙትን ችግረኞች፣ ሕመምተኞች፣ ሽማግሌዎችና ባልቴቶች፣ እንሰ-ግውታንና የመ ሳሰሉትን በመርዳት ነበር። የከሞት ወጣት እንደመሆኑ ሁሉ፣ ሰዎችስለሰዎ በሌላም መንቀርቀር ሲችል፣ መምህር ጣሰው ግን ለአገልግሎ ያለው ርካሽና ግብዝ ባሕሪ ተሸሮ ባለመሆኑ፣ መዋቅ የጎደለ ልብሱን እንኳ ሳይለውጥ፣ ደሞዙንም ሆነ የኪነት ተግባሩት ገቢውን፣ ለተቸገሩ ወገኖቹ መድሀ በመቸሩ፣ እጅግ ቀልባቹ አርኅት የጀል። እስከ አውሮፓ ድረስ ሔዶ ከተማ ሰው የኪነት ትምህርት ይልቅ፣ ከዚያው ከሀገሩ ሕዝብ የቀሰ መው ትምህርት ይበልጥ እንደሚጥመው ለዘውትሮ ደናገር ነበር። ከአገደበት የሚወጡት ቃላት ሁሉ፣ የወለላ ማር ያህል ጣዕም ነበራቸው። የቁም ነገር ባለአንደበት የሆነውንም ያህል ጨዋታ አየቁም ነበር።

መምህር ጣሰው የሕፃንነቱን ዓመታት በትምህርት ያሳለፈው፣ በዜተ-ክህነት አካባቢ በመሆኑም፣ ትምህርት- ሃይማ ኖቱን በሚገባ ጠንቅቆ ያውቃል። ግውትም ብቻ ሳይሆን ሠርተ ዬታል። ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው በየቤተ-ክርስቲያናቱ የትም ህርት መድረክ ላይ ሳይቀር በመገኘት፣ በዚያ ነደ አሳት አንደ በቱ፣ ለሞራልና ለኢቲክስ፣ ባጠቃላይም ለሥነ-ምግባራት መሠረቱ ትምህርት ስለሆነው፣ የወንጌሉን " በአንተ ላይ አን ደ ለነቀፉ ከመኑ የሶዘል ጭብጠሚ እውነታ ጋር እያዛመደ ሰለጓጅም ሊተረትረው ሰሰግው ሰው፣ አዳግጩ ሳይቀር የራ ሱን ጆሮ አያምነውም ነበር። የበለበቶ መንጠልያውን አጣፍቶ፣ በዚያ አደባባይ ላይ እየተንጠራራ፣ ሥነ ምግባርን በኪብ ሲያ ወርደው፣ ለተመልካቹ ምድራዊ መሆኑን ያዘነን ነበር። የሰው ልጅ ለመሰሉ ፍጡር በርኅራኄ ስሜት መተሳሰሙና መራራቱ ሊጠቅመው እንጅ ሊጎዳው እንደማይችል በሎዥክ ጭምር ሲያረዳ ላዳመጠው፣ እንደ ጴጥሮስና ላውሎስ ያስተካከለው ነበር።

ልግሉ ሆኖበት፣ ዓለማቸን ብዙ ብሩሃንና በጎ የሥን -ምግባር ሰዎችን፣ ከነመፈጠራቸው ለሕዝብ ሳያሳውት፣ እንዳ ልነበሩ አድርጎ፣ ባጭር እየቀጨ፣ በሞት-ሠረገላ ይሸኛቸዋል። ተደብቀው ቲወልዳው፣ ተደብቀው ናረው፣ ተደብቀው የሚ ያልፉ ገርና ቅን ወገኖች ቁጥር ጥቂት አይደለም። በተለይም የሥነ-ምግባር ሰዎች ሁሉ፣ በተፈጥሮ ባሕርያቸውና ዝንባ ሌአቸው፣ ትሁትና ግሑስ በመሆናቸው፣ አብዛኛውን ጊዜ ባደ ባደ ጉልተው አይታወቁም። ራሳቸውን በራሳቸው ሊያስተ ዋውቁ ቀርቶ፣ ሌሎችም ሊያስተዋውቋቸው ደስ አይላቸ ውም። በእንግሩ፣ ለስሙና ሰዝናው የሚጋስፈሰፈው የማኅበረ -ሰቡ ክፍል፣ በሚፈጥረው ግርግር ውስጥ ስለሚዋጡ፣ እነዚህ የዋህ ሰዎችም ሆኑ፣ በጎ ምግባራቸው፣ በሰፈው ሕብዝ ዘንድ በሥርዓት ሳይታወቅ ይቀራል። በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎችም ቢሆኑ፣ የእንደዚህ ያሉ ሰዎች መታወቅ፣ የራሳ ቸውን የክብር ደረጃ የሚጎረብቸው እየመሰላቸው፣ ሊያስተሩ ባቸውም፣ ከሕዝብም ጋር እንዲተዋወቁ ሊያደርጉም። የሞ ራል ሰዎች፣ በመሠረተ-ባሕርያቸው ፀረ-ሥልጣን በመሆና ቸው፣ ይህ ዐይነቱ የመንግሥት ባለሥልጣናች ማስተዋወቅ፣ የሚጠበቅ አይደለም። ተራግጫና ንቁው የማኅበረ-ሰቡ ክፍል ግን፣ ሥነ ምግባራቸውን ብቻ እንሸቶ ይደርስና፣ ባለው

አትሙ ሁሉ ያከብራቸዋል። ራሱ ጉቁው ክፍል ግን ቁጥሩ ውሱን በመሆኑ፣ የሥነ ምግባር ሰዎችም መታወቅ መጠን፣ ያንኑ ያህል ውሱን ነው።

የአበላ ባይና ያድር ባይ ቡድን በሚያወናብደው ዓለም ውስጥ፣ የማሔሳን ሐዋርያት፣ በሠፈውና በደፋ በሕ ዝብ ዘንድ አለመታወቅ፣ ብዙ አያስደንቅም። ዝናና መታወቅ በዓለማችን አንፃራዊ ይዘት ሲመዝን፣ ያወናባጆችና ያጭበርባሪዎች ገዋያዊ ውጤት ነውና።

" ይህ ዓለም ከብር ከዚህ ዓለም አትም አይበልጥም " እንደሚባለው፣ ዓለማዊውን ክብር የሚያቅርሱ ሁሉ፣ አትግ ቸውን ከዓለሙ አትም ጋር የሚያስተካክሉ ብቻ ናቸው። የግ ብዙ ዓለም ክብርና ዝና ደግሞ ገዋይና አፍቅሮ ርዕስ ነው። ፍፁም ግብዝነት!!

የሁሉ ወንድም ´የሰረው፣ ወንድሜ ጣለው በመም ህርነት ጉራ እንድነት ተሰልፈን በቆየንበት ዓመታት ሁሉ፣ እጅግ ይጠላቸው የነበሩት አፍቅሮ-ገዋይና አፍቅሮ-ርእስ እንደነበሩ፣ በሚገባ አውቅሰታለሁ። ያንድን ሰው ባሕርይና ዝንባሌ በሥ ርዓት ሠቅሰቶ ለማወቅ የሚቻለው በየዕለቱ ከሚፈጽማቸው ድርጊቶችና ከሚያሳያቸው ግብሮች ስለሆነ፣ በዚህ ሳዳን ላይ ጣለውን አስቀምጠ መመዘን አስቸጋሪ አይደለም። በቤቱ ፣ በጐረቤቱ፣በቀበሌው፣ በማኅበረ-ሰቡና በትምህርት ቤቱ ውስጥ ይሠራቸው የነበሩትን ቁምነገሮች ሁሉ፣ በቅርቡ ሆኔ የተመለ ከትሁ ስለሆነ፣ ስለማንነቱ ስመመሥክር አትም የሚያጋሰኝ አይደ ለሁም። የነጠረ የሞራል አቢጋዝ ነበረ። ሊሳው ቀርቶ፣ መም ህር ጣለው፣ በማኅበረ-ሰቡ ተግባራዊ ባሕሮች ውስጥ የተዋጠ ሰው ሰለነበረ፣ ለግለሰ ቤቱና ትዳሩ የሚያስብና የሚጨነቅ አልነበረም። በቤቱ ውስዋ የሚገኙ ንብረታዊ ቆሳቁሶች እንኳ፣ የዓይነታቸው ሁኔታ የጣለውን ሰዓለሰ ባሕሪ ያሳያሉ። ከተራ ከርኅሳ የእንጨት ወንበሮች በስተቀር የተሰየ ምቾታም መቀመ ጫና መቀኛ አልነበረውም። የሚያገኘው ደሞዝ መጠን እንኳ፣ ሊሳው ቤቱር መናኛ ቢጤ ዳግመኛ እጅ ሶፋ ሊገዛለት የማይችል ሆና አይደለም። ወይም በዚያች ኩንትሽ የትኩል ቤት በኪራይ መኖሩ፣ ደሞዙና እሞገለ በሚሸጣቸው ሥዕሎች እንጩራ ፕንዙሱ መሰለተኛ የራሱ ሂኪጋ መቀሰስ አትቶት አይደ ለም። ጣለው በተፈጥሮው እንደዚያ ያለ፣ ግለ-እሱነቱን ብቻ የሚያዝናና ነገር የሚዋጥለት ሰው አልነበረም። የግል ባህንብ ረትነት ስሜት ደንታ የሚሰጠው ምሁር አልነበረም። የደስታ ምንጩ የነበረው፣ ጣለው ነገር ሁሉ የማኅበረ-ሰቡን ችግሮች መቋቋሙ ብቻ ነው። ጣለው በርግጥ በቅርንት ረገድ ውሱን አልነበረም። አልባሌ ሰብሎ፣ አልባሌ ተጫምቶ፣ አልባሌ በልቶ... ሰለው ሲል ተቸግሮ የኖረ ሰው ነበረ። በቅርብ የሚያ ውቁት ሁሉ፣ በሚታይበት ሞራሉና ሥነ-ምግባሩ፣ በከፍተኛ ሰብዕናው በመንፈስ ሲኩሩበትና እጅግም ሲመኩበት፣ በኑሮው ጉስቍልናና ገበትተኛነት ግን እጅግ ያዝኑለት ነበር። ያም ሆኖ ግን፣ ጣለውም ከዚያ ጠንቀኛ ሞት አለመሰጠም። እንደግን ኖውም ተራ ሰው፣ ተራውን አልፏል። እጅግ የሚያሰትለው ግን ከነዚያ በጎ ምግባሮቹ ጋር፣ በወጣትነት እድሜው መቀጨቱ ነው። <u>የዘመናችን ጀርሻራ የፖሰቲካ ሁኔታ ለጣለው፣ ያለዕ ድሜው መቀጨት፣ በርቱዕም ሆነ በሊርቱዕ ተጠያቂ ነው።</u>

እንደሩት ምሥራት ነበር ባሕል ቢታሰብ ኖሮ፣ የሞራል መምህሩ ጣለው፣ የሞራል አርአያዊ ናሙና (ሞዴል) ተደርጎ በመቁው ትውልድ ሁሉ "ከጣለው ተማር! እንደ ጣለው ሁን" እየተባለ ይኖር ነበር። ጣለው ግን ኢትዮጵያዊ ሆነና፣ እንደ ዘመኑ ብሒራዊ ሰብዕና ከንሞራሉ ተቀብሮ ቀረ።

ግን ምን ይሆናል፣ እንደ መምህር ጣለው ያሉትን ሰዎች፣ ዓለምም ሆነ ሕዝቦቿ፣ እስከ መፈጠራቸው ሲዋውቋቸው በድ ብቅ ተወልደው፣ በድብቅ ኖረው፣ በድብቅ ያልፋሉ። እንደዚያ ያሉትን ግሩግን ሰዎች፣ ዓለምም ሆነች ሕዝቦቿ በሚገባ ለማ ወቅና ለማስተዋወቅ ባሕሉም ሆነ ልግዱ የላቸውም። ስለ ሆነም ጣለው፣ ከዚያ ችሎታውና ከዚያ ትውት ሰብዕናው ጋር እንደተደበቀ ኖሮ እንደተደበቀ አልፏል። እንደሱ ያሉ ሰዎች ሁሉ፣ ለከሠረ እታው ግጣሪያ እንዲሆንለት ለሸቀጣ ሸቀጡ ማስታወቂያ እንደሚያስራጨው የዲታ ሪክለም የማይደልጉና የማይመኙ በመሆናቸው፣ ራብቸውን ሳያስተዋውቁ፣ የልብ መታ ቸውን ቢሥውርና በሰሆሳስ አክርውነው ይሞታሉ። መምህር ጣለውን ከዚህ ለዮት የሚያደርገው ቢናር ምን ጊዜም ግንኙቱን የማይረሱለት እጩ መምህራንን፣ የአርአያነቱ ቅርስ አርጎ ግስፉ ነው። በበኩሉም እንደ መምህር ጣለው ቸርነት ያሱ ትንና የሥነ ምግባር ሐዋርያት፣ አደር ስለተጫነባቸው ብቻ ተረስ ተው መቅረት እንደሌለባቸው ለግስገንዘብ፣ ይቺን መጠሐፍ መዘከሩ እንድትሆንለት አበረከቻለሁ።

(ጊኒ ብልጣሶር)



t.me/OLDBOOKSPDF

እንተዋወቅ

ስሜ " የጠብታ ፍንጣቂ" * ይባላል። ያወጣልኝ የግል " አስገኝዬ " ነው። በይዘት ባህርዬ " ፈጠራ " መሆኔን ባውቅም፣ አስገኝዬን " ፈጣሪዬ " ልለው አልፈልግም። ስያሜዬ በይዘቴ አንጻር ሲታይ የ "ጥቅል" እንጅ የ " ተፀውኦ ስም " አይደለም። በዚህኛው ቀዳማይ እትሜ ብቻ፣ ከአስር በላይ የየራሳቸው የተፀውኦ ስም ያላቸው አጫጭር ታሪኮችን አቅፌ መያዜ፣ ለጥቅል ስምነቴ፣ ብቁ ማስረጃዬ ነው። አስገኝዬ በራሱ ልዩ ግላዊ አጠራረሩ፣ በእኔ ታቅፈው ያሉትን አጫጭር ታሪኮች ሁሉ፣ " ቆናፅል ድርሣናት " ይላቸዋል። " ቁራጭ ታሪኮች " ለማለት ነው። ይሁን እንጅ፣ "ቁራጭነታቸው" የመጠን እንጅ የሐሳብ እንዳይደለ አውቃለሁ። እንደ ሐሳብ ረዥምነታቸው የማይዳሰሱት ጉዳይ የለምና!!

ከሠፊው ባሕረ-ሥነ ጽሑፍ ውስጥ፣ በመጠነ-ሕሊና ተጨልፋ ከወጣችው ማየ-ድርሰት፣ አንዲታ ጠብታ ተድበልብላ ስትወድቅ፣ የተገኘችን ብዙኃን ፍንጣቂዎች አስመልክቶ፣ ይህን ስያሜ እንደሰጠኝ አስገኝዬ ይናገራል። " ፈጠራ " ብርቅ ላልሆነበት ጣፊ፣ እንዲህ መሰሉን ስያሜ ማውጣቴ፣ ውቅያኖ ሳዊው ሥነ-ጽሑፍ፣ ምን ያህል ዕመቅና ስፋት እንዳለው አገናዝቦ ይዘቴ ገና ያልተቆነጠረ ድልብ መሆኑን በትህትና ቃና

* ይህ እትም " የጠብታ ፍንጣቂ " ገማደ-አክል ቢሆንም፣ በተሰደ " የዝግር ደብ "የሚለውን ሥያሜ ይዞ እንዲወጣ የተደረገው፣ የሠፈሩት ታጭር ታሪኮች ይዘቶች፣ የወርሀ-ግእዞት ነፀብራቆች በመሆናቸው ነው።

ለመጠቆም በማሰብና፣ እግረ መንገዱንም ለአንባብያን ጉዳዩን ለማስረዳት ሲል፣ የዘየደው መላ ጭምር እንደሆነ እገም ታለሁ።

በዚህ ቀዳማይ እትሜ ውስጥ ታቅፈው የሚገኙትን አጫጭር ታሪኮች፣ አስገኝዬ ካዘጋጃቸው ዓመታት አልፈዋል። በየምክንያቱ በየሣንዱታቸው ውስጥ ተዘርረው ከርመዋል። አብዛኛዎቹ ታሪኮች " ፈጠራዎች " ናቸው። ይሁን እንጅ፣ ሥርወ-ምንጫቸው ግን፣ ግዙፋዊው ጭብጥ ዓለም ነው። በተለምር ከሰማያት በርቀው የወረዱ አይደሉም። የማኅበረ ሰብ ፍጭት የወለዳቸው ሃኒቶች ናቸው። እንዲውም የልደታቸው ወቅት፣ ከድኅረ የካቲት ኢትዮጵያ በኅበሩት ዓመታት ውስጥ መሆኑን አስገኝዬ ገልጸ፣ በዚያው ዘመን አርጋጅ አንጋጅነት፣ ተጥደውና ፈልተው፣ ነፍረውና ተንተክትከው፣ በዚያው ዘመን ውስጥ በቅታቸው የሠከኑ ጥዶሽች ሳይሆኑ፣ እስከ ዚህኛው ወቅት ድረስ ንፍረታቸው በመንተክተክ የቀጠለና፣ በስሎም ያልለየለት ሥሪታዊ ትንግርት እንደሆኑ ይጠቁማል። በርግጥም፣ የታሪኮቹ ባሕርያት የሚያተኩት ጠረን፣ ድኅረ የካቲት ድኅረ የካቲት ይሸታል። መዓዛቸውም የተጨነቁ ሰምችን ዐይነት ያውዳል። እኔ ራሴ በግላዊ አባባሌ፣ እንድገልፃቸው ቢፈቀድልኝና፣ ግራና ቀኝ ወይም ላይና ታች ሳልል፣ ፊት ለፊት በቀጥታ ስለአጠቃላይ ይዘቱ ብናገር፣ " ያለፉት አሥራ አራት ጥቁር ዓመታት፣ ኢትዮጵያዊው ማኅበረ-ሰብ የደረሰበት አሣርና መከራ፣ በደልና ፍዳ፣ ደባና ቍስቍልና፣ በመለስተኛ የጨረፍታ ጭላንጭል የሚንፀባረቅብኝ መስተዋትና፣ ይህም ጭንቀት የፈጠረው ብሶትና ስቆታው፣ እሪታና

t.me/OLDBOOKSPDF

ዋይታ የሚያስተጋባው የሥቃያት ገደል ማሚቶ ነኝ " እላለሁ።

ማንኔቴን አካተቼ ለመግለጽ፣ ከላይ የሠፈረውን አጭር መግለጫ ካቀረብኩ፣ በበኩሌ ይበቃኛል። ዝርዝሩን ሐተታ ግን፣ አዘጋጅዬ ራሱ፣ በሚከተለው ሁኔታ አቅርቦታልና፣ የእትማዊ ይዘቴን ምንነት ማወቅ ለሚፈልጉ አንባቢዎች ሁሉ ሊረኩበት እንደሚችሉ ስለማምን፣ ልብ ብላችሁ እንድታነቡለት እያስታወስኩ፣ እኔ ከዚህ ምክሬ ጋር እሰናበታለሁ። ቸስስ!!

የጠብታ ፍንጣቂ ነኝ!
መልካም ንባብ እመኝላችኋለሁ።

ጥቅል አባባል ቢሆንም፣ የማንኛውም ሀገር ሕዝብ፣ ሥነ ጽሑፍ አለው። የኔ፣ የግሌ የሚለው ሥነ-ጽሑፍ። ይህም ሥነ-ጽሑፍ፣ የየሀገሩ ሕዝባዊ አስተሳሰብ ነፀብራቅ ነው። ብሶቱን፣ ተድላውን፣ ሐዘኑን፣ ዕሴቱን፣ ፍቅሩን፣ ጥላቻውን፣ መከራውን፣ ምኞቱን፣ ተስፋውን፣ ሥቃዩን..... የሚገልጽበትና የሚያሳይበት ሕዝባዊ ሠነዱ ነው። ሲለው አክርሮ፣ ሲያሻውም አርግቦ ያቀርበዋል።

ሥነ- ጽሑፍ፣ የየኅብረተሰቡ አስተሳሰብ ኑሮና ሕይወት ነፀብራቅ ነው ሲባል የዘመን ክልል የለውም። ነበረ፣ አለ፣ ይኖራልም። ቅርፁና ዐይነቱ ቢለያይ የየዘመኑ ሕዝብ፣ የኢኮኖሚና ያስተሳሰብ እርከኖች የሚፈጥሩበት፣ የእድገት ትዕምርት ሆኖ ነው። ማኅበረ-ሰባዊ ነፀብራቅነቱ ግን፣ ሁሰንተና ነው። በባሕርዩ ጠብ ስለሌለው፣ ሁሉንም፣ የተም፣ ምንጊዜም ሕይወትን በየመልኳ ቀርየ ያቀርባል። ያቀራረብ ስልቶቹም የተለያዩ ሲሆኑ፣ በተለይም፣ ዐቢይ ልቦለድና ንዑስ ልቦለድ፣ ቅኔና

ግጥም፣ ቲአትርና ድራማ፣ ሒቲትና መጣጥፍ.... የተባሉ ልዩ ልዩ ዘርፋዊ ዐይነቶች አሉት። እነዚህ ሁሉ የሥነ-ጽሑፍ ዐይነቶች፣ የየራሳቸው የሆነ ያቀራረብ ስልትና ቅርፅ አላቸው። የየሥነ-ጽሑፉን ዓይነታዊ ቅርፅ የሚወልደው፣ እንደእናቱ የሆነው የየሥነ-ጽሑፉ ዐይነታዊ ይዘት ነው። ቅርፅ በባሕርዩ፣ ከይዘት ይሠርፃልና።

በተለይም ቅኔና ግጥም የተባሉት የሥነ-ጽሑፍ ዐይነቶች፣ ልዩ ጣዕምና ውበት፣ ጥልቀትና ምጥቀት፣ ስልታዊ ባሕርያትም ስላሏቸው፣ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትና ተቀባይነት አግኝተዋል። አብዛኛውንም ጊዜ አቀራረባቸው በንፃሬ የተምሳሌት፣ በርቅቀት፣ በስልትና በሕገ-ቋንቋ የበለፀጉ በመሆናቸው፣ ሁኔታውያንን ሁሉ፣ እንደ ደራሲው ፍላጐትና እንደ አንባብያንም ዝንባሌ የመታዘዝና የመግለጽ ችሎታና ተሰጥዎ ይታይባቸዋል። ጮሌ ደራሲያንም፣ ተልእኮአዊ ሒሳባቸውን ለመግለጽ እነዚህን መንታ የሥነ-ጽሑፍ ዘርፎች አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው፣ በነዚህ ባሕርያቸው መንሥ ኤነት ነው። በተለይም፣ ምዝብሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በመከራ አጣብቂኝ ውስጥ የኖረ፣ ነፃና ልቅ ጎብረተሰብ ባለመሆኑ፣ ቅኔና ግጥምን እንደጥልቅ ሒሳብ መግለጫና የልቡን ተናግሮ ሳይወነጀል ማምለጫ አድርጐ ሲጠቀምባቸው በመኖሩ፣ ስልታቸው ደርዝ ይዞ የጭንጫ ድንጋይ ያህል ጠንክረውና ደርጅተው ይገኛሉ። ከዚህም የተነሳ፣ የሕዝባችን ግጥማዊና ቅኔያዊ ቅርስ፣ ከየትኛውም ሕዝብ ይልቅ የበለጸገና የዳበረ ይዘትና ቅርፅ አለው ማለት ይቻላል።

ሕዝባዊ የመንፈስ ቅርስ የሆነው ኢትዮጵያዊ ቅኔ

ወይም ግጥም፣ ባብሕርዩ፣ ያሚያዝናና፣ የሚያስተምር፣ የሚያስጠነቅቅ፣ የሚተርክ፣ የሚያጋልጥ፣ የሚያፈላስፍ፣ የሚያስመጥቅ፣ የሚያሸብር፣ የሚያስቀልድ፣ የሚያፖላትክ ወዘተ.. ኃይል ስላለው፣ በብዙዎች ዘንድ መፈቀሩና መወደዱ የሚበዛበት አይሆንም። ስለቅኔና ግጥም መዝግቤ ያሰፈርኩት ዝርዝር ሒሳብ በሚቀጥለው ባለ አሥር ግጥሞች እትሜ ላይ (ዛር ነው በሽታዋ) እንዲያነቡልኝ እያስታወስኩ፣ በቅድሚያ ግብኣቱን አቀርባለሁ።

ከቅኔና ከግጥም በስተጐን ደግሞ፣ ባጠቃላይ ይዘታቸውና ቅርፃቸው የተለዩ ዝርው (ብትን) የሆኑ የድርሰት ዐይነቶች አሉ። እነዚህ የሥነ-ጽሑፍ ዘርፎች የበኩላቸው ቅርጽና መዋቅር አላቸው። በስልታቸው አንፃርም፣ ራሱን የቻለ መዋቅራዊ ይዘት አላቸው። ከዝርው ድርሰቶች ውስጥ ዋናዎቹ "ዐቢይ ልቦለድ" (ረዥም ልቦለድ) እና "ንዑስ ልቦለድ" (አጭር ልቦለድ) የሚባሉት ናቸው። ሁለቱም በይዘታቸው ብዛትና ስፋት መጠን ይለያዩ እንጅ፣ አጠቃላይ ውቅረታቸው፣ ከሞላ ጐደል ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም የሚነድፏቸው የባለ ታሪክ ባሕርያት አሏቸው። የባሕርያት ወኪሎች የሚሆኑቱ ተዋንያን ግን፣ በቁጥራቸው አይመሳሰሉም። የዐቢይ ልቦለድ ተዋንያን ሲበዙ፣ የንዑስ ልቦለድ ግን አንድ ወይም የጥላ ያህል ውል ውል የሚሉ አጫፋሪ ይኖሩታል። ሁለቱም፣ በማኅበረ-ሰብ የሚከናወኑትን የየዘመን እውነተኛ ድርጊቶች በፈጠራ መልክ ያቀርባሉ። . . . በየወቅቱ የሚከናወኑትን የማኅበረ-ሰብ ድርጊቶች፣ በግለ-ሰብ ባሕርይ ላይ አስታክው ይተርካሉ። ገጠመኙ፣ ችግር፣ መከራ፣ ግፍ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ድክመት፣ ድቀት..... ከሆነ፣ አሳዛኝ ገፁን አጉልተው ሲያቀርቡ በአንባሩም፣ ገጠመኙ፣ ፍስሐ፣ ዕሴት፣ ፍቅር፣ ብሩህ ምኞት፣ ብሩህ ተስፋ፣ ብልፅግና... ከሆነ፣ አስደሳች ገፁን አብራርተው ይጽፋሉ። "ትራዠዲና ኮመዲ" የሚሏቸውም ከዚህ በመነሳት ነው። አብዛኛዎቹም መጻሕፍት እንደ አጠቃላይ መምሪያና ግብ አርገው የሚጠቀሙበት፣ አጓዳኝና ማዕከላዊ መርሐአቸው፣ የትሑት ሰብዕናን ምንነት ቀርፆ ለማሳየት ነው። ስለዚህም እንደትህትና፣ ቅንነት፣ ገርነት፣ ጨዋነት ያሉትን በጎ ባሕርያት፣ እንደባሕርይ መግለጫ ለፈጠሩት አቀንቃኝ ፈትለውና ሸምነው ያለብሱታል። እንደነሞራል፣ ኤቲክስ፣ በጎ ሥርዓት፣ ሉዓላዊ ልቦና፣ ራማዊ መንፈስ ያሉትን መድኃኒተ-መንፈስ ባቀንቃኙ ተዋናይ ላይ ይሥሉበታል፣ ይኩሉበታል። በዚህም ድርጊታቸው በግጎበረ-ሰብ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ግለ-ሰብ የነጠረ ሥነ-ምግባር ሊኖረው እንደሚገባ ያስተምራሉ። ወይም ደግሞ፣ የበደልንና የግፍን አፀያፊነት ለማጋለጥ፣ የአንቃኛቸውን ባሕርይ እንደጭራቅ አርገው ያቀርቡና፣ ኢሰብአዊ ግብሩን ያጋልጣሉ፣ ይኮንናሉ። በተመክሮ ደረጃም ትምህርት እንዲሆን፣ ባለዕኩይ ምግባርን ግለ-ሰባዊ ባሕርይ፣ እርቃነ-መንፈሱን ቅልጥጥ አርገው ያሳያሉ። ግለ-ሰቦችን እንደባሕርያቸው አቅርበው፣ በጐም ሆነ እኩይ ምግባራቸውን በማንፀባረቅ፣ የማኅበረ-ሰቡን የጐበጠ አስተሳሰብ ያርቃሉ። የሰውን ልጅ መማረክ የሚቻለው፣ በስሜቱ በኩል መሆኑ ቢታወቅም፣ ከስሜቱ ይልቅ ጎሊናውን ለማሸብረክ፣ የብዙዎች ልቦለድ መጻሕፍት ጥረት ነው።

ያቀራረብ ስልቱ፣ መተረክና ማተት የሆነውን፣ የዐቢይ

ልቦለድ መጣፍ ጉዳይ ከዚሁ ላይ ልተውና፣ የዚህ እትም ወደ አቀፋቸው " አጫጭር ታሪኮች " ሐተታ ላቅና።

" ያጫጭር ታሪኮች " መሠረት፣ በአፍ የሚነገሩ ተረቶችና ታሪኮች ናቸው። አቀራረባቸው፣ አብዛኛዎቹ ግልጽና ፊት ለፊት ይሁን እንጅ፣ ምፀትና አሽሙር፣ ስቅጭሽና ምስ ጭሽ አለባቸው። አብዛኛውን ጊዜ በግለሰቦች ባሕርያት ተዋቅ ረውና ተጎድፈው፣ ነጠላ ገጠመኝ ይተረክባቸዋል፣ ይንፀባረቅ ባቸዋል። አጭር ታሪክ በመሠረታዊ ይዘቱ፣ የገጠመኝ ሁኔታዎች መስተዋት ነው። በጽሑፋዊ አቀራረቡም ገላጭ ዘዬ ይበዛበታል። ስለዚህም ነው፣ መስተዋታዊ መሰኘቱ።

የገጠመኙ ሐሳባዊ እንብርት፣ መገለፅ ያለበት ቢሆንም ገላጭነቱ አይንዛዛም። እጥር ምጥን፣ ቁልጭ ቅልብጭ ብሎ የተከሸነ ነው። ምንም ጊዜም ቢሆን፣ የወጠነውን አቀንቃኝ ሐሳብ፣ በታሪኩ መጨረሻ ላይ፣ አሟልቶ ማካተት ይኖርበታል። መነሻ ውን በማሳመር የወጠነውን ያህል መድረሻውንም በመቅድመ ሐሳቡ መሠረት፣ መደምደም ግዴታው ነው።

አብዛኛውን ጊዜ፣ ያጭር ታሪክ ንድፋዊ ውቅረት፣ የነባር እውነታን ሐቃዊ ሁኔታ፣ የሚያስተርክ ነው። የሐሳብም ሆነ የቋንቋ ድግግሞሽን፣ ይህ ባሕርዩ ይከላከልለታል። ሐቃዊ እውነታውን ለመግለጽ፣ የቃላትና የሐሳብ ድግግሞሽ ሳይሆን፣ የተሰያዩ አገላለጾች ይበልጥ ያገለግሉታል። ነባር ሁኔታን በመግለጽ ረገድም፣ ከድርቀት ይልቅ ልስላሴ ይስማማዋል። ማለትም፣ ነባሩን ሁኔታ እንዳለ ድርቅ አድርጐ ከማቅረብ ይልቅ " ይሆነኝ " ብሎ እንደሚስማማ ማቅረቡ ይመረጣል።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲህም አቀናብሮ ለማቅረብ፣ የደራሲውን ልዩ ጥበብ ይጠይቃል። ስለዚህም ነው፣ ከደራሲ መምሪያዎች አንዱ መርሐ-ሙያ፣ " ደራሲ እንደ ካሜራኛ ፎቶ አንሺ ሳይሆን፣ እንደ እውቅ ሠዓሊ መሆን አለበት" በማለት ያቀረበው። በተለይም፣ ስለ አጭር ታሪክ አፃፃፍ ዘዴ የሚተርክ አንድ ንድፈ ሐሳብ፣ " The importance of realism lies not in subject matter, but in the writer's attitude toward his material ....." ስለሚል፣ የሚጠቀስና እጅግ የሚተኰርበት ሐሳብ ነው። በዚህ እትም ውስጥ ሠፍረው የሚገኙት አሥር ድሁር ታሪኰች፣ ይህን መመሪያ ተከትለው የተጎደፉ፣ የተዋቀሩና የተፃፉ በመሆናቸው፣ " ካሜራኛንና ብሩሽኛን " በመጠኑም ቢሆን፣ ሰፋ አድርጐ ማብራራት ጠቃሚ ይመስለኛል።

" ደራሲ ነው በርግጥ፣ ግብሩ እንደሰዓሊ፣
እንዳሻው የሚሥል፣ ጭብጥ ይዞ ደባሊ፣
ያ ጋዜጠኛ ግን፣ እንደ ፎቶ አንሺ ነው፣
የሚያየውን ብቻ እንዳለ ገልባጭ ሰው። "

በዚህ አንድ ሥነ-ጽሑፍ ጠቀስ የግጥሜ አርኬ ላይ፣ ሁለት ነገሮች ይታወሳሉ። የካሜራኛ ፎቶና፣ የሰዓሊ ሥዕል ናቸው። አንዱ ግዑዝ ወጥ ሲሆን ሌላው ደግሞ፣ ባለ ሕይወት የወለደው ነው። ፎቶግራፍ፣ ያንዳንድ ሰው ዐካላዊ ገጽታ ሲያነሳ፣ የፊት ላይ ጭረትን ሳይቀር እንዳለ ገልብጦ አንስቶ የሚመዘግብ ሲሆን፣ የእጅ ሥዕል ግን፣ ሠዓሊው እንደሚታየውና ጎሊናውም እንዳሰኘው፣ ወይም ምናቡም ሆነ ቀልቡ እንደመራው ወይም ደግሞ ሊሆን ይገባዋል ብሎ እንዳመነበት ነድፎ የሚስለው ነው። ሠዓሊው የነባራዊ አካሉን

t.me/OLDBOOKSPDF

ጭብጥ ሳይለቅ፣ ከሚታየው አካላዊ ገጽታ አልፎ፣ ወደ ተሣሊው ልቦናና ጎሊና ጠልቆ በመግባት መንፈሱን ጭምር በሥዕሉ ላይ ያንፀባርቃል። አንዱ የነባሩን ሁኔታ በጥሬው እንዳለ ገልብጦ የሚያሳይ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ፣ ነባሩን ጥሬ ሁኔታ ደጀን በማድረግ ከዛ በላይ ደግሞ ደባል ሐሳብን በአሳልነት በመቀንስ ወይም በመጨመር፣ የደራሲው ነፀብራቅ ጎሊና የሚታከልበት ነው። የጭብጡ ትክክለኛ ቅጅ ወይም የነባሩ ጥሬ ሁኔታ ነፀብራቅ፣ ፎቶግራፉ ሲሆን፣ እጅ ወለዱ ሥዕል ግን፣ ነባሩን ሁኔታ መነሻ በማድረግ፣ የሠዓሊው ግላዊ አስተያየት ጭምር የሚነደፍበት ነው። ስለዚህም ነው ጋዜጠኛና ደራሲ፣ እንደ ካሜራኛና እንደ ሠዓሊ ተመስለው የቀረቡት።

የካሜራን ድክመት፣ ሌላ ማሰሪጃ ልጥቀስ። ፎቶ የሰውን ልጅ ምናብ አያሳይም። በአስማት ኃይል መጫኛ እናቆ ማለን የሚሉ መተተኞች አጋጥመውኝ፣ ድርጊታቸውን በካሜራ ለማንሳት ሞክሬ ነበር። ባይገርማችሁ፣ በቆመው መጫኛ ላይ አስማተኛው ሳይቀር እንደጠጣ ፊጥ ብሎ ሲወጣ በዓይኔ አይቼም ነበር። ካሜራዬ ያነሳው ፎቶ ግን ሁለቱንም ሲሆን ሁለቱንም አልመዘገበም ነበር። ምሥጢሩ ምትሐተ-ዓይን ብቻ ነው ማለት ይሆናል።

በቀቀኑ ጋዜጠኛ በጀሮ የሰማውንና እንደአስተዋለው በአካላዊ ዓይኑ ያየውን ብቻ እንዳለ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት የሙያው ኤቲክ ያግረዋል። በአንፃሩ፣ ደራሲ ግን፣ ከዚህም አልፎ፣ የራሱን ግላዊ አስተያየትና ፍልስፍና ያክል በታል። የተለያዩ ደራሲዎች እንደመኖራቸውም መጠን፣

የሚያክሉት አስተያየትም ይለያያል። አንዳንዱ የተነሳበትን ጭብጥ መሠረት አድርጐ፣ በሀገሩ ወይም በዓለም ማኅበረ-ሰቦች መካከል የሚንሸራሸሩትን ጊዚያዊ ዝንባሌዎች ያመላክታል፣ ይጠቁማል። አንዳንዱ በሰዎች መካከል ስለሚገኙ የባሕል፣ የፖሊቲካ፣ የእምነት አስተሳሰቦችና ግጭቶች አንስቶ፣ ድክመታቸውን ወይንም ተፅዕኖነታቸውን በተለያዩ መልኮች ያቀርባል። አንዳንዱ ደራሲ፣ በግላዊ አስተያየቱ ተማምኖ፣ ሌላውን ያወግዛል ወይም ያወድሳል። አንዳንዱ፣ ካንዱ ጠንካራ ጐራ ተዳብሎ ድጋፉን በመስጠት ያደንቃል፣ ያራግባል፣ ያጨበጭባል። አንዳንዱ ደግሞ፣ የራሱን " ይሆነኝ " ብሎ ያመነበትን ሐቅ ያራምዳል። ወይም ግላዊ ስሜት-ወለድ ዝንባሌውን ይሰብካል።

በነዚህ ደራሲያን ልዩ ልዩ ያስተሳሰብ ልዩነቶች የተነሳ፣ የድርሰትም የአፃፃፍ ፈሊጦች የተለያዩ መልኮች እንዲኖራቸው ግድ ሆኖአል። ስለዚህም ልዩ ልዩ ያፃፃፍ ዘዴዎች ተፈጥረዋል። በምዕራባውያን አባባል " ሪአሊዝም፣ ኢምፕሬ ሽንዝም፣ ሹሪአሊዝም፣ አብሶልዩትዝም፣ አብስትራክሽንዝም፣ ክላሲዝም፣ ሬዩቸሪዝም፣ ራሺናሊዝም፣ አካዴሚሲዝም፣ ..... በመባል፣ በዘመናችን የሥነ-ጽሑፍና ባጠቃላይም፣ ለሥነ ኪነት ቤተ-ሰብ ፈርጥና ሐመልማል በመሆን፣ የተለያዩ ውበት ፈንጣቂዎች ተደርገው ይገኛሉ። እንዲውም፣ እንደ ትምህርተ ቀመር፣ መርሐ-ነቢብ ሆነው፣ " ይህ ዐይነት የድርሰት ሐሳብ፣ በዚህ ዐይነት የድርሰት አፃፃፍ መቅረብ አለበት " እስከመባል ተደርሶ፣ እያንዳንዱ ያፃፃፍ ዘዬአዊ ዐይነቶች፣ ለተለያዩ የድርሰት ሐሳባዊ ይዘቶች ተመድበዋል። ዝርዝሩ ውስጥ ገብቼ

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ ጉዳይ ላይ መንቦጫረቅ አልፈልግም እንጅ፣ የትኛው ዐይነት የድርሰት ሐሳባዊ ይዘት፣ በየትኛው ዐይነት ያፃፃፍ ዘዴ እንደተፃፈ፣ አንዳንድ መጻሕፍትን እየጠቀስኩ እንደምሳሌ በማቅረብ ባሳየሁ ነበር።

በዘመናችን፣ በድርሰት አቀራረባቸውና ባፃፃፍ ዘዴያቸውም እጅግ የተደነቁቱ ደራሲያን፣ በተለይ በግለ-ሰቦች ቅንጭብ ታሪክ ላይ ተነስተው፣ የሕይወትንልዩ ልዩ ገጽታ በማስታከክ፣ የየማኅበረ-ሰቡን ደካማ ሆነ በጐ ጐን አጠቃለው ለማሳየት የሞከሩቱ ወገኖች ናቸው። በተለይም፣ ጭብጣቸውን ከመንታ አንፃር እያገናዘቡ፣ ኑሩን እውነታ፣ ሊሆን ከነበረበትና ከሚገባውም አንፃር እያስተያዩ፣ በልዩ ውሕደታዊ ሥምረት የሚያቀርቡ ደራሲያን፣ ወደር የማይገኝላቸው የሥነ ጽሑፍ ጠቢባን ተብለዋል።

ለዚህም ዐይነቱ ድርሰታዊ አቀራረብ፣ " ያጭር ታሪክ " መዋቅር፣ ልክ እንደ ሠንጋ ፈረስ ገሥግሦ የሚያደርስ ነው። ተስማሚ ቃላትን፣ ዐረፍተ-ነገሮችን፣ ዘይቤዎችን መርጦ ብቻ በመጫን፣ ቸቸቸ እያሉ መኰልኰል ነው። ከፈለጉትና ከተ መኙት ግብ ፈጥኖ ያደርሳል።

ከፍተኛ መጠበብ የሚያስፈልገው " ያጭር ታሪክ " አፃፃፍ፣ በተለይ አነጣጣሪ ቃላትን፣ አመርቂ ሐረጐችን፣ አርኪ ዐረፍተ ነገሮችን፣ መሳጭ ዘይቤዎችን፣ ግራኪ አንቀጾችን..... ማቀነባበር ይጠይቃል። በውሕደት፣ በሥምረት፣ በሥልጠት፣ መቆላለፍ ብቻ ሳይሆን ሠምና ፈትል ጭምር መሆን አለባቸው። ሥነ-ጽሑፋዊ መቅረዝና ፋና፣ ከዚያ ዓይነት የውህደት ሥሪት ላይ ፍንትው ብሎ ይሠርፃል። ስለዚህም፣ በአጭር

ታሪክ ህልውና ላይ፣ ነገረ-ድሪቶ ቦታ የለውም። የዐረፍተ ሐሳቦቹ መጠነ ርዝመት መንዛዛት አይኖርበትም። ጉልሀና ግልፅ፣ ቀላልና ልቅ መሆን አለባቸው። የሐሳቦችን ረድፋዊና ዘርፋዊ ቅደም ተከተል፣ ውሕደታዊ ፍፁምነትን ይጠይቃል። ቀዳማዊውን ከዳግማዊው ማዛነፍ የለብንም። ለዚህም አሠራር የሚረዳን፣ የታሪኩን ጭብጥ አስቀድሞ በሚገባ ማመንዠክና ማጣጣም ነው። ይህ ከሆነ የታሪኩን መዋቅር በሥርዓት ለመቀየስ ችግር አይፈጥርም። ጭብጡና መዋቅሩ ደርዝ ከያዘ፣ ድርሰቱ አጥንትና ሥጋን ተዋሕዶ፣ በአካል ገዘፈ ይሏል። አካላዊ ግዝፈትን ካገኘ በኋላ፣ ደመ-ነፍሱ፣ ከተዋቡ የቃላት፣ የሐረጐች፣ የዓረፍተ-ነገሮች፣ የዘይቤዎች፣ የአንቀጾች "ሴሎች" ላይ ይነግሳል። ከዚያ በኋላ፣ ግውዝና ምውት የነበረው፣ የአ ጭር ታሪክ በደን፣ ሕይወት ዘርቶ፣ መንቀሳቀስ ጀመረ ማለት ነው።

በተለያዩ ሀገሮችና፣ በተለያዩ የሥነ-ጽሑፍ ዘመናት፣ ብቅ ጥልቅ ሲሉ የኖሩ የ "ቀጐፅል ድርሣን " ደራሲያን ብዙ ናቸው። ደራሲያትም አሉበት። ያዳዳፍ ስልታቸውና የባሕርያት አወቃቀራቸው ከሞላ ጐደል ይመሰሰላል እንጅ፣ እንደሚኖሩበት ማንበረ-ሰብ ዐይነትና እንደባሕላቸውም ይዘት የታሪኩን ጭብጥ በሚመለከተው ነቀጥ ላይ ይለያያሉ። የሚያግራቸው አያሌ ገደቦች በመኖራቸው፣ ዋናው ወሣኝ፣ የሚኖሩበት ማኅበረ-ሰብ ዐይነት ነው። የጭብጡ ይዘትም የጽሑፉን ቅርጽ ይወስናል። የመልክዐ-ምድር የፖለቲካ አስተ ሳሰብ፣ የኢኮኖሚ እርከን፣ የየታሪካቸው ቅርስ፣ ባሕላቸውና ልምዳቸው፣ ለታሪካቸው ጭብጥ ቅርፅ ያወጣለታል። በአቀራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ረባቸው ረገድ፣ የአንድን ግለ-ሰብ፣ ወይም የአንድን ድረጊት ገጠመኝ ይዘው ይነሱና፣ ከአንድ ግባዊ ውጤት ላይ ደርሰው፣ ያልባሉ። ድርሰቱን ለመፃፍ ያነቃቃቸውና የገፋፋቸውን ገጠመኝ፣ እንደሁኔታው የመለያየቱን ያህል፣ ተፍፃሜተ ታሪኩም፣ እንደየደራሲው ያስተሳሰብ ዝንባሌ፣ ልዩነቱን ጠብቆ፣ በተለያየ መልእክታዊ ቁልፍ ይከረቸማል። በጀመረበት ፈር የማይጨርስ ታሪክ ግን፣ ያዳዳፉን ሕጋዊ ውል እንዳ ላከበረ ይቆጠራል። የደራሲያኑ ጭብጥ ታሪክ፣ ግላዊ አስተሳ ሰባቸው፣ ያዳዳፍ ዘዴአቸው፣ መድረሻ ስልታቸው፣ ይለያይ እንጅ፣ ሁሉም ከአንዳች ገጠመኝ ላይ ተንስተው፣ ግብ ካለው አንድ መደምደሚያ የሚደርሱ በመሆናቸው፣ ይህ ነጥብ ያጐዳኛቸዋል።

ማንኛውም ደራሲ፣ የገዛ ፍጡሩ በሆነው ምናባዊ የድርሰት ሕይወት ውስጥ፣ የፈለገውን ያገናል፣ የጠላውን ይገድላል፣ የወደደውን ያድናል፣ ያፋታል፣ ይድራል። የታ ሪኩን ዋና ባሕርይ፣ ሲፈልገው ሠይጣን፣ ሳይፈልገው መልአክ አርጐ ያቀርበዋል። እንደዚያ በሐሰብ የመዝናናት ነፃነት ቢኖረ ውም ቅሉ፣ በተቻለው መጠን ታሪኩ የሚነገርበትን መካን፣ ጨርሶ መልቀቅ የለበትም። ፈረንጆቹ እኒህን ገደቦች " Local colour and Regional life " ይሏቸዋል። በአንድ ቦታና ወቅት ላይ በግብር የተፈፀሙ ድንቅና ታሪካዊ ድርጊቶችን፣ በፈጠራ መልክ ማቅረብ፣ ያጫጭር ታሪኮች ዐይነተኛ ባሕርይና ተግባር ነው ስለሚባል፣ ገጠመኙ የተከናወነበትን ቦታና ወቅት አግናዝቦ፣ አጠቃላይ ሁኔታውን ማንፀባረቅ ግዴታ ነው።

ወግ ለመጠረቅና፣ ተረብ ለመዘብዘብ ካልሆነ በስተቀር፣

ተፈላጊ መልእክትን ሁሉ በሚገባ ለማስተላለፍ፤ " አጭር ታሪክ " ሊያካትት እንደሚችል፤ ብዙዎች አምነውበታል። ለዚህም ይመስላል፤ የዘመናቸው የሩሲያ እውቅ ደራሲያን የነበሩ፤ የወቢይ ልቦለድ (ኖቬል) ፀሐፊዎች፤ እነ ጐጐል፤ ፑሽኪን፤ ቼኮቭ..... በአንድ ወቅት ትልቅ ልቦለድ መጻፋቸውን ትተው፤ በንውስ ልቦለድ ድርሰት ላይ ተሽቆልቀሉው ተለቀውበት ነበር። በርግጥም፤ እጥር ምጥን፤ ምጥን ብጥር፤ ቅምም ያለ ማንኛውም ነገር በሙሉ፤ ጣዕምና ለዛ እንዳለው ሁሉ፤ አጭር ልቦለድም ያዘለውን ንጥር ሐሳብ፤ ከተነሳበት ጭብጥ ወለም ዘለም ሳይል አለቅጥ ሳይንዛዛና ሳይበርዝ፤ በአንድ መጥ ሐሳብ እንደጀመረ፤ በአንድ ወጥ ሐሳብ የሚያስ ጨርስ በመሆኑ፤ ለድርሰት አባባፍ፤ ተመራጭነቱን አሌ የሚል አይኖርም።

ያጭር ታሪኮች መጠን የማያፈናፍን በመሆኑ፤ በሚጠ ቀምባቸው ቃላት ጥጥርነት የተነሣ፤ የቋንቋ ችሎታን በመጠ ኑም ቢሆን ያንዝር ይሆናል። ክርር፤ ጥብቅ፤ ጥርንቅ፤ ውጥ ርጥር... ያሉ ቃላት እንደ ሽቦ ቀጥነው በየአንጹ ውስጥ ይሠግሠጉ እንጅ፤ በጥቅማቸው አንባር፤ የአንዲቱ ቃል ጉልበት ብቻ፤ ሐሳብን በመግለጥ ችሎታዋ፤ አሥር ጥርቅም ቃላትን ታስከነዳለች። ማለትም፤ የብዙ ቃላት ጋጋታ የማይገልጠውን ጥርንቅ ሐሳብ፤ አንዲቷ ብቻዋን ታመረቅነዋለች። ደራሲ ቼኮቭ፤ የፃፈባቸውን ያጭር ታሪክ ባሕርያትን ሕይወታዊ ቅፅበቶች፤ በተለዩ እምቦቃቅላ ቃላት ተጠቅሞ፤ ከተደበቁበት ፈልቅቆ አውጥቶአቸዋል። በተለይም ውስጣዊ የመንፈስ ትግል ያላቸውን የግለ-ሰቦች ሕይወት፤ በቃላት አግዝፎ፤

ረቂቅነታቸውን በማጋለጥ፤ ቅርፅና መልክ በመስጠት፤ ባጭር ታሪክ አማካይነት ሐሳባቸውን ለመግለጽ የሞከሩ ብዙ ደራሲያን ተጠቅመውበታል።

" አጫጭር ታሪኮች " በቀልጣፋነታቸው አንባር፤ በአንድ እፍታና ትንፋሽ፤ ተነበው የሚያልቁ መሆን አለባቸው። አቀራረባቸውም፤ ይሆነኝ ተብሎ መነሻና መድረሻ (cause and effect) ሐሳቦች የአሏቸው ስለሆኑ፤ ጋማቸውን ይዞ እንደፈረስ ለማጋለብ ያመቻሉ። ሌላው ጥቅማቸው ደግሞ፤ በዚህ አጣዳፊ በሆነው በዘመነ-ጥድፊት ወቅት፤ እጅግ ተጣዳፊ የሆነው የዘመናችን ሰው፤ በሚያዋክበው ኑሮው ውስጥ የጊዜ እጥረት ስላለበት የድርሰቶች ባጫጭር ሆኖ መቅረብ ደቂቃዎቹን ይቆጥቡለታል።

ይህን " ያጫጭር ታሪኮች " ጥቅም፤ በሚገባ የተረ ዳው፤ ፈረንጁ ጮሌ፤ በብዛት ይጠቀምባቸዋል። ስለዚህም " ያጭር ታሪክ " ሥነ-ጽሑፋዊ ቅርስነት በፈረንጆች ሥነ ጽሑፋዊ ይዘት ውስጥ እጅግ የደራና ራሱንም የቻለ ታሪክ አለው። በሥነ-ጽሑፋዊ ሠነድነቱም፤ የከበረ ቦታ አለው። በረዥም ታሪኩ አማካይነትም፤ ለዘመናት ካሳየው ባሕርያቱ አንዱ፤ በእድገቱ ለውጥ ማሳየቱ ነው። በሕገ-ተፈጥሮ እንደምናየው ከሆነ፤ በነባርነት ያለና የነበረ ወደፊትም የሚኖር ራሱ " ለውጥ " ብቻ ስለሆነ፤ አጫጭር ታሪኮችም፤ በለቀነባበራቸው አንባር፤ ይህንን የለውጥ ሕግ አክብረው ኖረ ዋል። " ለውጥ " ነባር ባሕርያቸው መሆኑን፤ በየዘመናቱ ባሳዩት እድገቶች አስመስክረዋል። በየምዕት ዓመታቱ፤ ባሕርየ ይዘታቸውንና ንድፋዊ ቅርፃቸውን ሲለዋውጡ ኖረዋል።

ይህን ለውጣዊ ኪደቱን ልናይበት የሚያስችሉን፤ በዚህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዓይነት አፃፃፍ፣ ሰፋ ያለ ልምድና ቅርስ ካላቸው ብዙ ሀገሮች ውስጥ ቻይና፣ ሩሲያ ፣ ፈረንሳይ፣ ብሪታንያና አሜሪካ ይህኔበታል። ከዋና ዋናዎቹም ደራሲያን ውስጥ፣ እነ ሹሹን፣ ቱርጌኖቭ፣ ቼኮቭ፣ ጎጎል፣ ዶስቶቪስኪ፣ ፑሽኪን፣ ቶልቶይስ፣ ፖ፣ ኢርቪንግ፣ ሐርቴ፣ ሔሚንግዌይ፣ ሎወረንስ፣ ኮንራድ፣ ካፍካ፣ ቾሰር፣ ባካሲዮ፣ ሬኔ፣ ሲሊ፣ ማውፓንሳት..... ጥቂቶቹ ዕውቅ ደራሲያን ይገኙበታል። ያጭር ታሪክን ሥነ-ጽሑፋዊ ጥቅምና፣ በሱም አማካይነት፣ የፈለጉትን ተልእኮ ባቋራች ለማቅረብ መቻሉን በማስመልከት፣ ሁሉም በየበኩ ላቸው ያነገቡት አንድ የጋራ መርሀ አላቸው። ይኸውም ..... " The human spirit could best be cought at close range through short stories! " የሚለው ነው። ይህን አርማዊ መርሀአቸውን አንግበው፣ ባደባባይ ያስተጋቡበትን ያጭር ታሪክ ሥነ-ጽሑፋዊ ጠቃሜታ፣ ምሳሌ እየሰጠሁ፣ በሰፊው ብዘረዝር እጅግ ደስ ባለኝ ነበር። በተለይም፣ በሐቃዊ እውነታ ጭብጥ ላይ የተመሠረተን ያጭር ታሪክ ድርሰት፣ ባገላለጹ ረገድ፣ ስሜት ወለድና ቀልብ ጠቀስ መግለጫ (ኢምፕሬሽኒዝም) ይበልጥ ሊያመረቅነው እንደሚችልና፣ ሌሎቹንም ልዩ ልዩ ፅንሰ-ሐሳቦች በምን በምን ዓይነይ አገላለጽ ስልት መቅረብ እንዳለባቸው መጠቆም በተገባኝ ነበር። ግን ሐተታው ስለሚበዛ በዚህች ትንሽ እትም ለመተንተን አልሞክርም።

በሃገራችንም ደራሲያን ዘንድ፣ በጣም የሠረገ አይሁን እንጅ፣ " የአጭር ታሪኮችን " ህልውና ለማስተዋወቅ ተሞክሯል። በተለይም በጥንታውያኑ መጻሕፍት " በመዝሙረ ዳዊትና በአራቱ ወንጌሎች " ውስጥ ሠፍነው የሚገኙት፣ የአን

ድምታ ግብራርያ አጫጭር ታሪኮች፣ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። የየቅኔ ትምህርት ቤቶቹ መቅድመ ዘረፋ ታሪክ ሊላው ነው። በየዘመኑ የተነሱ ኢትዮጵያውያን ደራሲያንም የከተቧቸው አጫጭር ታሪኮች አሉ። ይህ ያሰንበት ትውልድ የደረሳቸውን ብንጠቅስ፣ የእነ በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት " የእንስሳት ኮሜዲያ " እና፣ የነአቶ ሀዲስ አለማየሁ " ተረት ተረት የመሠረት " ይገኙበታል። በተለይም፣ ከላለ " ድግሞሹና ድርብርቦሹ " መድበለ አካል፣ ሦስት ያቶ ሀዲስ ልቦለድ መጻሕፍት ይልቅ፣ በበኩሌ ፣ በመልእክታቸው ባቀራረባቸው፣ በመዋቅራቸው፣ ባገላለጻቸው፣ በጭብጣዊ ይዘታቸው አንጻር ኩልልና ጥልል፣ ያለችውን ትንሽቱን " ተረት ተረት የመ ሠረት " መጽሐፋቸውን፣ በአንክሮ ጭምር አደንቃለሁ። መሰሏንም ደጋግመው ጽፈው ቢሆን ኖሮ፣ ምንኛ ደስ ባሰኘኝ ነበር። የሚያሳዝነው፣ እነዚያን መሳይ ድርሰቶች፣ የመጣፈ ጣቸውን ያህል፣ ብልጭ ብሎው ድርግም ማለታቸው ነው። ላንባቢያን ምን ያህል ፍሬያማና አርኪ እንደነበሩ፣ ያያቸው ሁሉ ይመሰክራል። በተለይም፣ ተረት መስለው በመቀየዳቸው፣ ተልእኮአቸው ሞራላዊና ትምህርታዊ በመሆኑ፣ በቀረቡበት ዘመንም ሆነ ዛሬ፣ሊሰጡ የቻሉትን ከፍተኛ ሞራላዊና ኤቲካዊ ተመክሮ ማንም ሰው መገመት ይችላል።

በቅርቡም እነአቶ መሥፍን ሀብተማርያም (የቡና ቤት ወሳች) እነአብዱ ንጉሤ (ሙሽራው) የጫጫሩአቸው ሐቲቶችና አጫጭር ልቦለዶች ሥነ ጽሑፋዊ ዋጋ የሚነፈጋቸው አይደሉም። ያገራችን የዘመኑ ደራሲያን እነኛን መሰል መጻሕፍት በሰፊው ማምረት ያልቻሉበት ምክንያት ግን፣ በጭ

t.me/OLDBOOKSPDF

ራሽ አይገባኝም።በተለይም የሀራችን ጊዚያዊ ሁኔታ፣ እንደ ነዚያ ያሉትን ታሪኮች ለማምረት ምቹና ያዝመራውም ወቅት ነበር።

ዛሬ፣ ሀገራችን ከደራስያኗ ብዙ ትጠብቃለች። ጥርስ የለሹ ረሀብ ብቻ፣ ሚልዮን ልጆቿን በዓመት እድሜ ውስጥ ቆርጥሞና ሠልቅጦ የበላባት ሀገር በመሆኗ፣ ሌላው ቢቀር፣ ይኸ ትንግርት ብቻ የስንክሳር ቅዶች ያጽፋል። የየቀኑ የወታደሩ አፈሙዝና፣ የካድሬው ደባ፣ ኖቭሎች ያስደርሳል።

ዛሬ ኢትዮጵያ፣ በሶሻልና በኤኮኖሚ፣ በፖለቲካና በባሕሏ ዘርፋዊ አውታሮቿ ሁሉ ተወጥራ፣ እታች እመቅ ዘቅጣ፣ ዳዴ ይል የነበረው እግራዊ መልሕቋ አዘቅት ወርዶ ባሕረ-ወለል የረገጠበት ዘመን ነው። በውስጥም ሆነ በውጭ ያሉ ልጆቿ መዛበቻና መሣለቂያ የሆኑበት ልዩ ቀውጢ ጊዜ ነው። አንዳንድ ለ " ብቃት " የደረሱ ደራስያን ይህን ስቃያዊ ምንነቷን በተምሳሊት ለማሳየት ሞክረዋል። አንዳንዶቹ የዘመኑ ደራስያንማ... " አንባቢ እኔ እንደምሠራው ሠርቶ ወደኔ ደረጃ መወጣጣት ይኖርበታል። እኔ እሱን ፍለጋ ወደ ታች ካዘቀዘቅሁና ከወረድሁ እድገት አይኖርም" እያሉ ከመመጻደቅ አልፈው ያሾፋሉ። " ድንቄም እድገት እቴ!! ከወለል ላይ ይልቅ ጣራ ላይ መደነስ ያስደስተኛል እንዳለው፣ ዘፋኝ " መኮኑ እኮ ነው። ፊው!!

በተምሳሊት ለማሳየት የሞከሩት እንደ " አፅቋ የለመ ለመች ተክል አስመስለው ያቀረቧት ባለቅኔዎችም አሉ። - ችግኝ አፍልተው፣ ተክለው፣ ኰትኩተው፣ ፍግ አልብሰው፣ ወፃ አጠጥተው፣ ተቀፅላዋን ገርዘው፣ ካሳደጉ በኋላ፣ ተክሏ

ማቆጥቆጥ ስትጀምር፣ ቆፅል አውጥቶ፣ ቀንበጥ አብቅሎ፣ ቅጠል አለምልሞ፣ ቅርንጫፎች ዘንጥፎ፣ እንቡጥ አሞልምሎ፣ አብቦ፣ አኮርቶ፣ አጐምርቶ፣ ፍሬ አምርቶ..... የደረጃ በደረጃ እድገቱን ኩሳበ በኋላ በስተመጨረሻው ገደማ በማዕበላዊ ዶፍ አዘል ዝናብ፣ ከንፈድጓዱና ከነመብረቁ ጋር ወርዶ፣ አፈር በማስጋጥ፣ ልምላሜ-ተክሉን አራቍቶ መለመላ ግንዱን ብቻ መቅረቱን ጠቁሞ በማሳየት፣ ቅኔውን ያልባል። የገጣሚው ደራሲ ሐሳብ ጽሑፋዊ ተልእኮው እዚህ ላይ ይቁም እንጅ፣ ጠልቆና መጥቆ እንዲነበብለት፣ ካንባብያን ሁሉ ይጠብቃል። አንባብያን ግን የባለቅኔውን ተክላዊ አምሳል ተልእኮ፣ ባራዛሚ መነጥር ሳያዩ ለተራው ተክል ልምላሜና ድርቀት ብቻ ሰጥ ፈው ትንሽም ፈቀቅ ሳይሉ ይተውታል። ይህ ጉዳይ በደራሲው አንፃር ሲታይ፣ የወታደሩ አፈሙዝ የፈጠረበት ፍራቻ ያስጠበበው ዘዴ ሲሆን፣ ባንባቢው በኩል ግን የራሱንና የህገሩን ሁኔታ ሳያዛምድበት፣ እንዲው እንዳለ በደፈናው፣ ተክሉን ብቻ አርጐ መቀበሉ፣ የጊዚያችንን ኢትዮጵያ ሁኔታ ረስቶታል ወይም ከምሬቱ ብዛት ሊያስታውሰው አይፈልግም ማለት ነው።

የቻይናም ደራስያን በዚሁ ዘዴ ተጠቅመዋል። በምሥራታዊቷ ቻይና፣ አንዲት ታንኪረኛ ወፍ አለች። " ቺን ዌይ-ኑዎ " ብለው የህገሬው ሰዎች ይጠሯታል። የመልኳ ብሩህነት የወተትን ንጣት ያስንቃል። ፍፁም በረዶ ትመስላለች። ይቺ ወፍ፣ በየዕለቱ፣ ዝምበር ከሰረቀችበት ማለዳ አንስቶ እስከ እምታርብበት ምሽት ድረስ፣ በምትኖርበት አካባቢ ካለ አንድ ሰፊ ባሕር ውስጥ፣ ያገኘችውን ጭራሮና ጠጠር እያጋዘች

t.me/OLDBOOKSPDF

ስትጨምር ትውላለች። ያገራው ከበረኞች እንደሚሉት ከሆነ፣ ዓላማዋ ባሕሩን በምታግዘው ነገር ለመሙላት ነው። ምክንያቱንም ሲዘረዝሩ፣ " ወራቱ ከዘመናት በፊት፣ ከባሕሩ ዳር የሚኖር ያንድ ቤተሰብ ልጅ አገረድ ነበረች። ወላጆቿ ሳያዩአት ከባሀሩ ውስጥ ገብታ ስትዋኝ በመሞቷ፣ ነፍሷ ወደ ወፍነት ተሰውጣለች" ብለው ይተርካሉ። " እስከዛሬ ውሃውን ለመሙላት የምታደርገው ጥረት፣ በቀል ለመወጣት፣ ወይም ባሕሩ በየቄሳቀሱ ተሞልቶ ሲጠፋ፣ ጥንት የሞተችዋን ልጅ አገረድ፣ የገዛ ነፍሷን፣ ከነሕይወቷ የምታገኛ እየመሰላት ነው " ይላሉ። ምሣሌያዊ ታሪክ ሊወጣው የሚችል ግሩም "ገድል" ነው። በንጽጽርም መዋቅራዊ አቀራረብ ታሪኩን ከሀገር፣ ከታጋይ፣ ከትግብርት.... ማዛመድና ማቅረብ የሚያስችል ታሪክ ነው።

እንዲህ መሰሉ ታሪክ፣ ለጊዚያችን አንባብያን፣ ለነፅሮ ቢቀርብ፣ ምን ተብሎ እንደሚተረጐም፣ አስቀድሞ መገመት ይቻላል። ትዕምርት (ሲምቦሊዝም) በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው። እንደ አንዳንዶቹ ከያንያን "አብስትራክት" አይደለም። ረቂቅንና ጥልቅን ሐሳብ፣ ይበልጥ ግልጽና ጉልህ አድርጐ ለማቅረብ የሚረዳ ደጀን ነው።

ደራሲያን እንደየፈሊጣቸው፣ በተለያየ አቀራረብና፣ ለተለያየ አቅጣጫ ይጽፋሉ። ከሞላ ጐደል፣ ያቀራረባቸውን ዐይነት፣ በ " አጭር ታሪክ " አግባፍ፣ አስመልክቼ ጠቅሻለሁ። የሚጽፉበት አቅጣጫዊ ዒላማ እንደየችሎታቸው ይለያይ እንጅ ዋናዎቹ ግን ሁለት ናቸው።

አንደኛው ያንባብያን ስሜት ምርኮ አስገብቶ፣ ተልእኮ አቸውን በቀላሉ መንገድ እንዲቀበሉ ለማድረግ፣ በቀጥታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለልቦና አነጣጥረው የሚተኩሱት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ጎሊናን በምርምር ወጥሮ በማስተዋል እንዲቀበለው፣ በቀጥታ ወደ አእምሮ የሚለጋው ነው። ግልፅ ሆኖ አይታይም እንጅ፣ የሚጽፉ ደራሲያን ሁሉ፣ እነዚህን ኢላማዎች ይዘው ነው። እነዚህን የደራሲያን ሥውር ኢላማዎች በሚመለከት " ትርጁማን ብትሆኑኝ " በሚል አንድ ግጥሜ ውስጥ የሚከ ተሰው አርኬ ሠፍሯል።

" ለይተህ አስረዳኝ፣ ልብን ከጎሊና፣
ሁለቱን ለመለየት አቅቶኛልና!!
እንዳንዴ እንላለን፣ ጠቅሰን አንድ ደራሲ፣
ልንተቸው አስበን፣ በዓይነ ሒያሲ!
'እገሌኮ ይጽፋል፣ ለሰዎች ልቦና፣
ያ ደራሲ ደግሞ፣ ለዚያ ለጎሊና።'
ሲሉ እሰማለሁ፣ ልቦናን ያን ስሜት፣
ሌሎችም ሲያደርጉት፣ ጎሊናን ምክንያት!!
የሚፃፈው ሐቅ ግን፣ አንድ እስከ ሆነ ድረስ
ለምን ይሆን ከቶ፣ የሚሰጡት ልባስ?
አንዱን ሐቅ ለሥጋ፣ ሌላውን ለመንፈስ!
አፍጥጠ ችግሩ፣ እየታየ ሲያምስ!!... "

የዘመናችን ደራሲያን፣ በተምሳሌትም ሆነ በገድል ሽፋን ያቅርቡ፣ ወይም እንዳሻቸው ለልቦናም ሆነ ለጎሊና አልመው ይድረሱ፣ ከመቸውም ዘመን ይልቅ፣ ስላለንበት አሠርታት ወቅት፣ መጻሕፍት መጻፍ የግዴታ ኃላፊነት አለባቸው። የዘመናችንን ጉስቁልና ምዝብር ኢትዮጵያ፣ በሆነው መልክ ሥለው ማቅረብ፣ ከየትኛቹም ባለሙያዎች ይልቅ ከደራሲያን

ይጠበቃል። ለልቦናም ይጻፉት ወይም ለጎሊና፣ የኢትዮጵያ ውያን መራራ ብሶት፣ በሐቅነቱ አንድ ዓይነት ስለሆነ፣ ደባን፣ በደልን፣ ግፍን፣ ሥቃይን፣ ቸነፈርን፣ ረሀብን. ..... ማወቅ የማይችል ልቦናም ሆነ ጎሊና ይኖራል ብሎ የሚገምት አይኖርምና! ብቻ ይጻፍ!!

አንድ ጥንታዊ የግዕዝ ብራና መጣፍ (የመዝሙረ ዳዊት አንድምታ) ውስጥ፣ ያነበብኩት፣ አንድ ከባድ ብሒል፣ የሀገሬን ሕዝብ ሥቃይ ባስታውስኩ ቍጥር ዛሬም ትዝ ይለኛል። እንዲህ ይላል።

" ኢይመውት ዘእንበለ ዘአሐየ " የሚል ነው። ቀጥተኛ ትርጉሙ ሕያው ሆኖ ለተፈጠረ ሁሉ የሚጠቀስ ነው። ከባድ ሐሳብ ያዘለ ኃይለ ቃል ነው። አጭር ትርጉሙ ለመኖር የተፈጠረ ፍጡር ሳይኖር እንዴት ይሞታል? (ሳልኖር አልሞትም እንደማለት)

ዛሬ ኢትዮጵያ፣ የሚሠቃዩ ሕዝቦች የሚታዩባት፣ የትራጀዲያ " መድረክ ናት። መዓዛዋ ሁሉ በሁለንተናው፣ መከራ መከራ ሸትቷል። የውጭና የውስጥ አድኃርያን በፈጠሩት የምሥጢር ደባ፣ የዋሃኑ ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ሲጠበሱ ኖረዋል። በእንዲቷ ምድራችን ላይ፣ በተፈጥሮ ያገኘችው የመልከዐ-ምድር ድርሻ፣ በብዙ አንባር ማራኪ በመሆኑ፣ ልምላሜዋም ሆነ ከበሐውርት ወደ በሐውርት ድልድይነቷ፣ የኃያላን መንግሥታትን ቀልብ አሳብዶ መራኰቻ አርገዋታል። በተለይም ለአውሮፓውያን የደም ስር የሆነው ቤንዚን የሚመነጭበት አካባቢ በመሆኑና፣ እንዲሁም ውሃ ለውሃ ተንሰፎ ከታላላቅ ውቅያኖሶች መዳረሻ አቋራጭ ጉዳና

t.me/OLDBOOKSPDF

በመሆኗ፣ የጥንት ኮሎኒያሊስቶችንና የዘመናይ ኢምፔሪያሊስቶችን የምኞት ልባዊ ትርታ እንዳከነፈው አለ። በዚህ የኃያላን ፍላጐት አጣብቂኝ ውስጥ ላካባቢው ታናናሽ መንግሥታት፣ በሰላም የመኖር ጉዳይ የማይታሰብ መሆኑ ቢታወቅም፣ እንደወረርሽኝ የኢንፍሉዌንዛ በሽታ፣ ውስጥ ውስጡን እንዳማቀቃቸው ናቸው።

በተለይም ኢትዮጵያ፣ ባለፉት ዘመናት በ " አትንኩኝ ባይ " ታሪኳ የታወቀች ገናና ሀገር በመሆኗ፣ በርቱዕ ትግል ያልቻሏትን ያህል፣ በኢርቱዕ ሠርገው ገብተው፣ ለጥንታዊ ሽንፈታቸው በቀል ለመወጣት፣ የማይሸርቡት ሜራ የለም። ዛሬም አንዳንድ የባሕር ማዶ ከበርቴዎችም ይህን የተንኰል ሜራ ለማፋፋም በሚጫረው እሳት ላይ ሁሉ ቤንዚን እንደረጩ ናቸው። ግን ነድዳ እንድትጠፋ የሞከሩት ሁሉ አልተቋጨ ላቸውም። በአንጻሩም በበጎ የሚያስባትን ሁሉ እያቀፈች እስከዛሬ አለች። ለዘመናት በነጻነት ለመኖር ያስቻላት በዓለም የታወቀው የልጆቿ ጀግንነት ብቻ ሳይሆን፣ ሕዝቦቿ ያላቸው ፍጹም የሰብአዊነት ስሜት አውታራዊ ምግባራቸው ጭምር ነው። የጥንት ኢትዮጵያውያን ትህትና፣ ርኅራኄ፣ ትዕግሥት፣ ባጠቃላይም ሞራላዊ ሥነ-ምግባር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ኢትዮጵያውያን ለቆየ ንጥር የመንፈስ ቅርስ ባለቤት በመሆናቸው ሀገራቸውን እንደ ነጻ የሰዎች መንኻርያ ቆጥረው፣ ሌላው ቀርቶ ለእዝሙድ ንግድ፣ ለሐር ሽቀጣ፣ ለገሀን ጥርስ ግቢያ፣ ለአራዊትና ለሌጦ ንግድ፣..... ካለም ዳርቻ ጭምር ይገባ ይወጣ የነበረውን ዓለም አቀፍ ነጋዴ በየዘመኑ በክብር ተቀብለው ሲያስተናግዱ መኖራቸው የዚሁ የነጠረ ሞራላቸው

ልዕልና ነጸብራቅ ነው። የዘመነ አክሱምና የዘመነ አዱሊስ ታሪክ ምስክር ነው። በመስተንግዶ ወደ ሀገራቸው የሚገሰ ግሰው ፍጡር፣ ሰው እስከሆነ ድረስ፣ በዝቅተኛ ደረጃ ስለማ ያዩትም እንደ ነጻ ፍጡርነቱ ተጋብተውታል ተዋልደው ታልም። በዚህም ነጻ ሰብአዊ ድርጊቱ " አልሐበሽ " (ሐበሻ) ..... " ድብልት፣ ብርዝ፣ ዘረ-ብዙኃን " የሚል የተዋረድ ስያሜ ቢሰጡት አያስደንቀውም። እንዲያውም በተዘምዶውም ሆነ በወዳጅነቱ ከሩቅ ምድር ሰዎች ይልቅ ጐረቤቶቹ እንደሚቀርቡት ስለሚያምን ምን ጊዜም የበጎ ፍቃድ በሩን በርግዶ ከፍቶላቸው ኖሯል። ይህ የሰላምና የበጎ ፈቃድ በር የተዘጋባቸው ወቅቶች ቢኖሩ የኢትዮጵያውያንን ነጻ ሕልውና ለመፈታተን " በደረታ ቸው መስቀል፣ በጉያቸው ሾተል፣ ወይም በደረታቸው ጨረቃ፣ በጀርባቸው ጨፈቃ፣ ወይም በደረታቸው ኮከብ በጭናቸው ክላሽኒኮፍ " ይዘው እንደዛር ውላጅ በመንታ አካል ሰርጎ ለመግባት በሞከሩት ላይ ብቻ ነበር። " በቅንነት የመጡትን እንግዶች ሁሉ ኢትዮጵያውያን በክብር ተቀብለው ሙሉ ነጻነት በመስጠት፣ ተልእኮአቸውን እንደፈለጉ ተዘዋው ረው እንዲያሰራጩ መፍቀዳቸውን ለማዘከር፣ የክርስቶስ ሐዋ ርያ የነበረው የሕንደኬው ቶማስ ሌላው ጥሩ ማስረጃ ነው። በአንጻሩ የሮሙ ሻቲካናዊው ሐዋርያ አባ ማስያስ የሠራውን አሻጥር ሁላችንም እናውቃለን። በእንግድነት ገብተው፣ ሴራ የጾለቴትን ሁሉ እዚህ ላይ መዘርዘር አያስፈልግም።

በመሠረቴ እኔ የታሪክ ምሁር አይደለሁም። በሌላ ጥናቴ ስምሪት ወቅት ግን፣ ግላዊ ትምህርቴ እያጣቀሰ ሲነዳኝ፣

ሰራሲ ያህል የሚበቃ የታሪክ መጻሕፍት አንብቤአለሁ። ደግ ሞም በሀገራችን ትምህርታዊ አድጎሮት የተነሳ ከተጻፉት መጻሕ ፍተ ታሪክ ይልቅ ያልተመዘገቡቱ አፈታሪኮች ይበልጥ ጥራ ትም ብዛትም ስላላቸው፣ ክብደታቸው የሚናቅ ባለመሆኑ፣ ያጋጠመኝን አበው ሁሉ አበክሬ ከመጠየቅ የሰነፍኩ ባለመሆኔ፣ ላጣቃሽና ለማገናዘቢያ ያህል የታሪክ ሰነዶች አሉኝ።

ማሳያ ቢያስፈልግ አንዳንድ ድንቃዊ የታሪክ ቅጽበት ድርጊቶችን ልጠቃቅስ። ለምን እንደጠሉት ባላውቅም የኢት ዮጵያ ካህናት አጼ ቴዎድሮስን አይወዷቸውም ነበር። እሳቸ ውም ቢሆኑ፣ " ራሱን ታጣቂ፣ ወገቡን ሰባቂ..... " እያሉ ካህናቱን ያርበደብዱ ነበር። በዘመኑም ከካህናት ጋር መናቆር ቀላል አልነበረም። አምላካቸውን ወንጅለው የሰቀሉ ኃያላን ሴረኞች ካህናት ናቸው። ቴዎድሮስ ግን አልፈራቸውም። የኑ ጠብ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ሊፈጥር የሚችለው ጠባሳ ምን ሊሆን እንደሚችል ማወቁ ነቢይነት ይጠይቃል። ኃይልና ሥልጣን የሕዝብ መሆኑ በማይታወቅበት በዛ የግለ ሰቦች ግናናነት ዘመን፣ ትግላቸው የሚፈጥረውን ብሔራዊ ጠንቅ መገመት ያስቸግር ነበር። የቴዎድሮስ ቁራጥነትና አይምሬነት እየለየለት መምጣቱን ደረጃ በደረጃ የተገነዘቡ ካህናት፣ የበኩላ ቸውን እርምጃ ለመውሰድ አልዘገዩም።

" የቤተ ካህናትን ደወል ፣ ቃጭል፣ ጽዋ፣ ጸናጽል፣ መስቀል፣ ርእሰ-መቋሚያ፣ ጽንሐ..... አቅልጣችሁ መድፍ ሥሩልኝ " ብሎ ያወጀ ጊዜ ነበር በሕይወቱ ላይ የፈረዱት። በየዓውደ ዓመቱ ዕለትና በታላላቅ በዓላት ቀን፣ ይቆርብ የነበረውን ቴዎድሮስ፣ በመሥዋእት ውስጥ መርዝ አድርገው

t.me/OLDBOOKSPDF

ሊገድሉት ወሰኑ። ወዲያውም መርዘኛ የእባብ ጭንቅላት በሚቆርብበት ዕለት አዘጋጅተው፣ ቅዳሴውን ሲያጣድፉ፣ ይህን ተንኰል የተረዳ አፍቃሬ ቴምድሮስ የነበረ አንድ ንፍቅ ቄስ፣ የመጀመርያውን ቁርባን እንዳይቀበል በምሥጢር ይነግረዋል። በስተመጨረሻም ዕርገት ወርደው፣ ሊያቆርቡት ሲሉ፣ አጅሬ ቴምድሮስ " ጥሚሞ አጥዓሞ " ይልብሃልና የመጀመሪያው ላንተ ይልና ዓይኑን አፍጥጦ ገባሬ ሠናይን ካህን ያዘዋል። ካህኑም ወደ ቴምድሮስ አፍ ዘርግቶ የነበረውን መሥዋእት በራሱ አፍ ተቀብሎ ብዙም ሳይሠቃይ ተንፈራፍሮ ይሞታል። ቴምድሮስም ከዛው መሥዋእት ላይ፣ በንፍቅ ካህኑ ቄስ አማካይነት ተቀብሎ ከቆረበ በሁኋላ ወደ ቤተ-መንግሥቱ ይመለሳል። ከዛ ወዲያ ለካህናት ሁሉ፣ ቴምድሮስ ነብር እንጅ ሰው አልሆነ ላቸውም። በተቆጣ ሸካራ ጥፍሩ እያንጠለጠለ ምድረ ካህናትን በየገደሉ እያምዘገዘገ አሰናብቷል። ግን ያኔ የካህናቱ ሜራ ውጤታማ ቢሆን ኖሮ ቴምድሮስ ብሊቱ ኢትዮጵያ ምን ይወጣት ነበር? " ፕሉቶክራሲ ወይስ ቲኦክራሲ? ወይስ ዲሞክራሲ? ..... መተንተን ለሚወደው ለዚህኛው ትውልድ የቀረበ ጥያቄ ይሆናል።

(" በጥቁር ብሌን ትይታ " ከተባለ መጣፌ የተጨለፈ)

ሌላ አንድ ኮሚክ የታሪክ ድርጊት ልጨምር። የ " አበሻ ሀገር ጦርነቶች " ከሚለው ሰነዴ ውስጥ የምቀነጭበው ነው። በዘመናት ባንደኛው ወቅት፣ በጐረቤት ገናና አምባዎች መካከል ከተደረገ ጦርነት የተገኘ፣ የጦር ታክቲክ ዜና ነው። የአንደኛው አምባ መሪ እጅግ ሲበዛ ዘዴኛና ብልህ ነበር። በቂ መሣርያዎች የሌለው በመሆኑ ይመስላል፣ ብልሃቱን የፈጠ

t.me/OLDBOOKSPDF

ረሰት። ጣውንቱ የሌላው ባላምባ መሪ ግን፣ አያሌ ሠራዊትና ብዙ ልዩ ልዩ የጦር መሣርያዎች ያለው ነበር። ለመጋጠም ቦታና ቀን ከወሰኑ በኋላ፣ ብልሁ የጦር መሪ አሥር ባለጋሞች ወታደሮቹን ይዞ አስቀድሞ ከተባለው የጦር ሜዳ በመድረስ፣ ረባዳ ቦታ መርጦ ይመሽጋል። ባለብዙው ሠራዊትም እንደ ሚያሸንፍ ተማምኖ፣ ተዝናንቶ እያቅራራና እየፎከረ ይመጣል። እነዚያ ባለአስር ነፍጠኛ የሆኑቱ የብልሁ መሪ ሠራዊት አባላት ከጠመንጃቸው ሌላ እያንዳንዳቸው አንዳንድ ቀፎ ንብና የንብ መከላከያ የሽቦ ወንፊት አጥልቀው ተዘጋጅተዋል። በተባለው ሰዓት ባለብዙ ሠራዊት ጦር እየተዝናና ሜዳማ ከሆነው የጦር ሜዳ ላይ እንደደረሰ፣ ያ ዘዴኛ የጦር መሪ፣ መልእክተኛ ልኮ " እንታረቅ ያንተን ጦር ትጥቅና የሠራዊቱንም ብዛት ገና ከሩቁ ሳይ ልቤም ጉልበቴም ተማርኳል። ገናናነትህንም አክብሬ ለመቀበሌና እኔም በገዛ ድፍረቴ ለመቅለሌ ገጸ በረከት ይዣ መጥቻለሁና ተቀበለኝ " ብሎ ይልካል።

ያም ባለብዙ ሠራዊት የጦር መሪ እውነት መስሎት " መሸነፉን አምኖ ይገብርልኝ እንጂ ከሰው ደም ማፍሰሱማ እኔ ምን ቆሌ አለኝ " ብሎ ይቀበለዋል። ጦርነቱም መሰረዙን ለሠራዊቱ ይነግርና፣ ምርኮውን እንዲቀበሉ ያለ መሣርያ እንዲሰበሰቡ ያዛል። ያ ዘዴኛ ባለ አሥር ነፍጠኛ ጋሜ ጦር መሪ፣ ካንገት በላይ ያለ የሠራዊቱን ፊት እንደ አባ ገሪማ አጽፍ አከናንቦ ከተፍ ይልና " ገጸ በረከቴ ይሽውልህ! " ይልና እዛ ባዶ እጁን አውላላ ሜዳ ላይ ለተሰጣ ሠራዊት ያሥሮቹን ቀፎዎች የተቆጣ ንብ ይዘረግፍለትና እነዚያን ባለ አሥር ነፍጠኛ ጋሞቹን "በሉ በነፍጣችሁ እመሩኝ" ይላል። ከዛ ወዲያማ ምን

ምን ይጠየቃል። ያ የንብ ሠራዊት፣ እያባረረ የሚጠዘጥዘውን መከላከያ-ቢስ ሠራዊት በጥይቱ ጭምር አንድነት ጠዝጥዞ ጨረሰው። በስተኋላም ከንቡና ከጥይቱ የተረፈውን ሠራዊት ከነጦር መሪው ማርኮ፣ አምባሞቹን ሁሉ ባንድነት የግሉ አድርጎ ለመምራት በቃ።.....”

ይህንን ከመሰለ ያልተጻፈ ታሪኩ፣ የዘመኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ መማር ይችላል። ሌላው ቢቀር፣ ጠላትን ለመቋቋም ለሚደረገው ግብግብ፣ “ የጥራት ” እንጂ “ የብዛት “ ጉዳይ ወሳኝ እንዳይደለ፣ ላለንበት የቀውጢ ዘመን ትውልድ ተመክሮአዊ ትምህርት ሊሆነው ይችላል።

እንደተራ እንሰሳ በዝቅተኛ ደረጃ የሚታዩት የየብሔረ ሰቡ ወገኖች፣ ማለትም እንደ ፋጋ፣ አጋሜ፣ ባርያ፣ ወይጦ፣ ሽጉሌ..... ያሉ ማኅበረሰቦች አባላት፣ ከተጠናወታቸው የተዋ ረድና የሳይኮሎጂ ተጽዕኖ ጭምር ነጻ የሚወጡበትን ዘዴና መላ ማዘጋጀትና መታገል ባለብን በዚህ የትግል ዘመን፣ ነጠላ ፔቲ ቡርዣ የትግሉን ጭብጥ በማሳከርና የመደብ ጠላት ሊመታ የሚችልበትን የተጋድሎ ጎራ ለማወናበድ፣ ጥዋት ማታ ሲፍጨረጨር ይታያል። የባህልም ሆነ የኅሊና ነጻነት መከናውን የሚችለው ትኖቹ የየብሔሩ ምዝብሮችና ጭቁኖች ነጻ ከወጡ በኋላ ነው። ይህ እስካልሆነ ድረስ፣ “ የትልቅ ብሔር ዕቡይ ትምክሕተኝነትን፣ በጠባብ የጭቁን ብሔረተኛ ትግል ለመቋቋም፣ ወይም ጭቁን ጠባብ ብሔረኛነትን በትልቅ ዕቡይ ትምክሕተኛነት ለመታገል፣ ወይም ትልቅ የብሔር ትምክሕተኛነትን በጨቋኝ ጠባብ ብሔረኛነት ለመተካት “ የሚደረግ የጊዜያችን ትግልና ውጣ ውረድ ሁሉ ትከከለኛ

t.me/OLDBOOKSPDF

አማራጭ አይሆንም። ብሔረሰቦች አለትድሚያ ድርድር እኩልነታቸው መረጋገጥ አለበት። በእኩልነትም መኖር የተፈጥሮ መብታቸው ነው። ፍርድ፣ ነጻነትና ብልጽግና፣ ከነሙሉ መብቱ ኖሮት ይመሠረታል ብለን ለምንመኘው የወደፊቱ ብሩህ ማኅበረሰብ፣ ይህ ዓይነቱ የትግል አስተሳሰብ እንቅፋትና ደንቃራ ከመሆን አልፎ፣ አንዳች ጠቀሜታ ሊሰጥ የሚችለው ለሰፊው ጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሆን፣ ከልሒቅ እስከ ደቂቅ ሕጻንና ሽማግሌ፣ ሳይመርጥ በመደዳ በመጨፍጨፍ ላይ ያለውን የምርጥ መኰንኖች ሰው-በላ መንግሥት ብቻ ነው። በተጨ ማሪም፣ እንደ ሶሻል ሳይንስ ትንተና ከሆነም፣ የብሔር ችግር፣ ፍትሕና ዲሞክራሲ ከኢኮኖሚ እድገት ጋር በሚሰፍንበት ወቅት፣ ራሱ በራሱ ቀልጠና ሟምቶ የሚጠፋ የማኅበረ-ሰብ ጨው ነው።

በዘመናችን የኢትዮጵያ ጭብጥ ሁኔታ በግልጽ እንደ እሚያሳየው ከሆነ፣ ማኅበረ-ሰባዊውን እርከን ለማስረዳት ብዙ ስንጠቃና ትንተና አያሻውም። የኃይል አሰላለፍ ረድፎች ከመቸ ውም ይልቅ ቁልጭ ብለው አግጥጠው ይገኛሉ። መጣጨና ተመጣጩ፣ ጨባጭና ተጨባጩ፣ መዝባሪውና ተመዝባሪው፣ ገፊውና ተገፊው፣ እንማን እንደሆኑ ማንነታቸው ባደባባይ ተጋልጦ ይገኛል። የውስጥና የውጭ አድኃርያን ኃይላት ከባንዳዎቻቸውና ከምንደኞቻቸው ጋር፣ ባንድ ጎራ ቦድነው ሲገኙ፣ በሌላው ጎራ ደግሞ ምዝብሩና ጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ከተራማጁና ከአጋር ኃይሎቹ ጋር ተሰልፎለል። ፋታ የለሌው እርቅ አልባው ፍልሚያም በየመልኩና በየረድፉ በመሟሟፍ ላይ ይገኛል። እነዚህ ሁለት ተጻራርያን ኃይሎች

በየጎራው ተፋጥጠው በትግል ላይ ናቸው። ማንኛውም ግለሰብ ኢትዮጵያዊ ሊኖረው የሚችለው ምርጫ፣ ከነዚህ አንደኛው ብቻ ነው። ፈጽሞ የለየለት እብድ ካልሆነ በቀር፣ ከመጀመርያው የመኰንኖች ሰው-በላ መንግሥት ጎራ ለመሜራበት አይሞክርም። አድኃርያን የትም ቦታ ይኑሩ በየትኛውም ወቅት ይኑሩ፣ ዕድሜያቸው ኮንትሽ ነው። ይህን ሐቅ እያወቀ ዓይኑን ጨፍኖ፣ ካድኃርያን ምሽግ የሚገባ አይኖርም። በእንቡዘ-ልብ የሚገባ ቢኖር፣ ወዶ ገባኑቱ የፍርድ በራሴ ደረሰኜ እንደሆነ ይወቅ።

የኢትዮጵያ ምዝብርና ግፉዕ ሕዝብ፣ በራሱ ፍላጎትና ውሳኔ መሠረት፣ የገዛ ድሉን በገዛ ትግሉ እስካገኘ ድረስ፣ ከመላው አድኃርያን ሠራዊት ጋር የተያያዘውን የጦፈና የጋለ ግብግብ ያለፋታ ትጥቁን ሳይፈታ ይቀጥላል። ይህን ሕዝባዊ ትግሉን የሚያወናብዱ ድኩማን ሁሉ፣ ጊዜያቸውን የሚጠብቁ ወላልቀው እንደሚጣሉ የከረከሠ መኪና ቡሎኖች ዓይነት ናቸው። ትንሽ በትንሽ ሲዝጉ ቆይተው በስተመጨረሻ የሚጠ ብቃቸው የውድቀት መራራ ጽዋ ነው።

ይህ ሕዝባዊ የተባበረ ኃይል፣ ውስጥ ውስጡን ተምሞ የሚከሠትበት ዕለት ትንሽ ይዘግይ እንጂ ወቅቱ ሩቅ አይደ ለም። አንድ ቀን ጎልብቶ፣ የውስጡንም ሆነ የውጭን ምንዝር ጠላቶቹን መንጥሮ ድባቅ ይከታል። በዚህ መራራ ትግል ላይ ግማሽ መንገድ የሚጓዙ፣ ግማሽ ታጋዮች ቢኖሩ አያስደንቅም። የትግል ኑባር ባሕርይ ነው። በየጎራው ታይቶአል። " አይነጋ መስሎአት ከቋት አራች " ን ብሂል ያመለክታል እንጅ፣ ጎህ ሲቀድ ተገናንቶ ሁሉን በነጻ ማድረግ ይቻል ነበር። ያ መከረኛ የኢትዮጵያ ምዝብር ሕዝብ፣ ዝንተ ዓለም ፍዳውን ሲቆጥር

t.me/OLDBOOKSPDF

የኖረውን ያህል ወደፊትም ለዘለዓለም የሚቀጥል አይደለም። የጎብረተ-ሰብ እድገታዊ ኪደትም ሕግ፣ በመከራው እንዲቀጥል አይፈቅድለትም። ፍትሕና ነጻነት ከነሙሉ መብቶቹ ጋር ያሰፈነ ሕይወት በእርግጥ አንድ ቀን ይኖረዋል። የብሩህ ተስፋ ባሴበት እንደመሆኑ መጠን የችግርን ተራራዊ አቀበት እየቧጠጠ የወ ጣውን ያህል በስተኋላ ላይ የሚንደረደርበት ቁልቁለት እንደ ሚጠብቀው ያውቃል። የማያወላውል ጽኑ እምነትና የማይ በገር ቆራጥነት ያለው ሕዝብ፣ ምን ጊዜም ከበስተፊቱ ብሩህ ሕይወት እንደሚኖረው ያምናል። ምዝብርና ጭቁን የማኅበረ ሰብ መደቦች ተስፋቸውም እንዳስተሳሰባቸው ተራማጅ ነው። ፍትሕ የሰፈነባት ሕይወት ከንብሩህ ይዞታዋ ጋር እንደ ምትገዝፍለት ጠንቅቆ ያውቃል። ስለዚህም ነው የተያያዘውን ትግል የማያዋዛው።

የኢትዮጵያ ማኅበረ ሕዝብ፣ መሠረተ አቋሙ፣ የሰው ማኅበር እንደመሆኑ መጠን ከሌላው ዓለም ማኅበረ-ሕዝብ በባሕርዩ የሚለይበት ብዙ መለዮ የለውም። በተለይም በመሠረታውያን ሰብአዊ ፍላጎቶቹ አንጻር፣ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ነው። በየዕለቱ ለሕላዌው ማቆያ ምግብ፣ ልብስና ቤት ያስፈልጉታል። እነዚህንም ለሚሟላት የበኩሉን ትግል ያደርጋል። ሌላው ሕዝብ የሚኖረውን ሕይወት እሱ እንዴት መኖር አይችልም?

እንደማንኛውም መደባዊ ወጥ ማኅበረ-ሰብኑቱንም የሚ ያደርገው ትግላዊ እንቅስቃሴ ሁሉ፣ ከሌሎች ሀገር ሕዝቦች የተለየ መሆን አይችልም። ቡርዡዋዊ ነፍጠኞች ለተሳሳተ

ዓላማቸው ሲሉ፣ ይህን ሐቅ ለራሳቸው እንዲስማማ አድር ገው፣ ጠምዝዘውና አጣምመው ቢያቀርቡት፣ ከመሠረታዊ ሐቅነቱ የጋት ያህል ወልፈት አይልም። ስለዚህም እንደ ማንኛውም በመደብ የተከፈለ ማኅበረ-ሰብነቱ ሊያካሒድ የሚ ችለው ሐቀኛ ትግል በመደብ ልዩነት ባሕርይ ብቻ የተመሠረተ መሆን አለበት። ይህ እውነታ በሥነ-ማኅበረ-ሰብ ጥናት የጠረ ሐቅ መሆኑን መካድ አንችልም። የትግልን መሠረታዊ ባሕርይና መንፈስ፣ በማንበጥበጥ፣ የሚፈጠርባቸውን ብዥታ ለሌሎች የሚረጩ ሁሉ፣ ይህ ዓይነቱ ብዥታቸው ዘመን ያለፈ በት ተረት መሆኑን መረዳት ይኖርባቸዋል። በተለይም ሰው በላዎቹ መኰንኖች! ወይም ሌሎቹ!!

አሻፈረን ብለው የፈለጉትን ፕሮፓጋንዳ ያራምዱ እንጂ፣ ሙከራቸው ውሃ መቋጠር እንደማይችል ማወቅ አለ ባቸው። እንዲያውም በዚህ ሴራቸው የሚጠቅሙት ድርጅት ቢኖር፣ ሥልጣንና ጥቅም የጠማውን የውጭና የውስጥ ኢዲ ሞክራሲያዊ ቡድን ብቻ ነው። በዚህም ድርጊታቸው በኢት ዮጵያ ሕዝብ ላይ እንደመቅሰፍት ሲወርድ የኖረውን ያሠርታት ግፍና ደባቸውን እንዳራዘሙት መረዳት ይኖርባቸዋል። የተባበረ ኃይል ሕንጻ ስናኦርን ያህል ጠራራ ግንብ አሠርቶ በጸሐይ ሙቀት ምግብ አብስሎ እስከማብላት ድረስ ማስቻሉን ከታሪክ መማር ይቻላል። ምንም ዓይነት ተአምር ያዘለ ሎጂካዊ ዲያሌ ክትም ቢሆን እንኳ፣ ሰዎችን መበታተን እድገትን ሊፈጥር ይችላል ብሎ በድፍረት መናገር ምንም እርምት የማይገኝለት ድፍን ስሕተት ነው። ካለማችን የተፈጥሮ ሕግ ውጭ መሆኑን በብዙ ማስረጃዎች ማሳመን ይቻላል። ለሌሎች ዘርፋውያን

t.me/OLDBOOKSPDF

ትግሎች ሁሉ ከትልቁ አብዮት በኋላ ተከታትለው የሚመጡ በሕዝቦች መካከል ያሉ ቅራኔዎችና እነሱንም በመፈታቀድና በውይይት አማካይነት የሚፈቱ " የዘመድ ጥል የሥጋ ትል " እንደሚሉት ያሉ ናቸው።

ማንኛውም የሰው ልጅ በምትሐት ወይም በተአምር ከሰማያት በርቆ የወረደ ፍጡር እንዳለመሆኑ ሁሉ በሥርዓት የሚኖርበት ሀገር አለው። ይህም ሀገሩ እንደፍላጎቱ ሊኖርበት የሚገባው መብተ ልደቱ ነው። በገዛ ሀገሩ ላይ የተፈጥሮ ዋልጌ ሆኖ መኖር የሰብአዊነቱን ክብር ይጻረርበታል። የተፈጥሮ መብቱንም ያጐድፍበታል። ሕግ የሚያስከብረው መብታዊ ጥያቄ በመሆኑ የሁሉም የያንዳንዱም ተፈጥሮአዊ አቋሙ ነው። ስለዚህም ነው የዲሞክራሲያዊ ፍትሕ፣ የነጻነት ፍትሕ፣ የመብት ፍትሕ..... ለሁሉም ለያንዳንዱም በእኩልነት እንዲ ሰጠው የምን ጊዜም የሰዎች ትግል ዓላማ የሆነበት። ይህ ትግል ከያንዳንዶችን ለሁላችን፣ ከየሁላችን ለያንዳንዶችን የሚ ጠበቅ ሐቀኛ ትግል ነው።

ተዘውትሮ እንደሚነገረው " የኢትዮጵያን ጉዳይ ለኢትዮጵያውያን ብቻ መተው አለበት" የሚሉ ወገኖች አሉ። በርግጥም ባዕዳን፤ የኢትዮጵያውያንን ያህል ለሀገራቸው ደኅንነት ያስባሉ ብሎ ማመን ያስቸግራል። በተጠቀሰው ነጥብ ላይ የበኩሌ አስየተያየት የተለየ ነው። እንደ ሰው ልጅነታቸው ለማንኛውም ሀገር ሕዝብ ችግር የሚጨነቁ፣ ቍጥራቸው ይነስ እንጂ በየትኛውም ሀገር ይገኛሉ። እነዚህ ለጠቅላላው የሰው ልጅ ቅን አስተያየት ያላቸው ሰዎች፣ በኢትዮጵያ ግላዊ ጉዳይ ላይ ያገባናል ብለው ለእርዳታ ቢመጡ መቃወሙ

እየተዝናና የሚሆነው መላ ቅጥ ጠፍቶታል። ዓለማችን (ምድር) ባለ አንድ ወርድና ስፋት የሆነች አንዲት ነጠላ ሞልሟላ አካል መሆኗ ቢታመንም ሰው ሠራሽ የሆነው የየሀገሩ ድንበር ምድሪቱን በምክንያት ሳይሆን በስሜት ሜትር በየዘመኑ እየሰካ ከልሎ ከልሎ እስከዚህ የአገሌ ሀገር፣ እስከዛ የአገሌ ሀገር እያለ በመደንበር የማያስፈልጉ የሰዎች ልዩነቶች ፈጥሮ፣ ለጦርነቶችና እልቂቶች መነሻ ምክንያት ሆኖ ኖሯል። ይበልጥ የሚያሳዝነውና የሚያሳፍረው ደግሞ፣ ለግላዊ ጥቅም በመንሰፍሰፍ፣ ዓለምን የጦር መሣርያዎች ማምረቻ ያደረጓት ሀገሮች የመርዘኛቹ መሳርያዎቻቸው ማምረቻ ኢንዲስትሪዎችና ፋብሪካዎች የሚተፉት አሰርና የተቃጠለ ካርቦን ክምችት ብዛት የተነሳ፣ ሰዎችን ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን ፍጡራን-ምድር፣ እንስሳትና ዕጸዋት መተንፈሻም ሆነ መድረሻ አሳጥተዋቸዋል። ነዋሪዎችዋ ምንም ዓይነት አማራጭ ሊያገኙ ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ሌላው ደግሞ የሰዎች ተንኰል ከመቸውም ዘመን ይልቅ ጐልብቶ ጠቅላላውን ሥነ-ምግባሮች እያዳሸቃቸው ነው። ድሆች ሕጻናት ከድሀ ሀገሮች ተሸጠው እየተወሰዱ፣ ጤንነቱ ለከዳው የከበርቴ ሰውነት በጤንነት ማሟያነትና መጠገኛነት የሚያገለግሉ ያካል ተለዋጭ ብልቶች ሆነዋል። የሶስተኛው ዓለም ሀገሮችም የኑክለር አሰር ጎልጎታ እየሆኑ ነው። ይህ እንግዲህ ዓለማችን ባጠቃላይ መልኳ ስትታይ የምትፈነጥቀው ብልጭታ ነው።

በቅርብና በዝርዝር ደግሞ በማጎረሰባቸው ሥርዓቶች የሚለያዩ ሁለት የኖርኩባቸውን ሀገሮች ልጥቀስ። ጐረቤቶች አይደሉም። አንዱ በጋርዮሽ ሕይወት የሚመራ ሀገር ሲሆን፣

አግባብ አይመስለኝም። በትንሹ የባዕድ ሀገር ኑሮ ዘመኔ፣ የሰዎች ችግር እጅግ የሚያንገበግባቸው ብዙ ቅን ሰዎች በየሀገሩ መኖራቸውን ተረድቼአለሁ። አብዛኞቹም ከበርቴዎች ሳይሆኑ የመለስተኛ ኑሮ ባለቤቶች ናቸው። በተለይም የኢትዮጵያ ውያን የእልቂት መጠን እጅግ አብጦ በነበረበት ባለፉት ቀውጢ ዓመታት ወቅት፣ የእነዚህ ባዕዳን ሀገሮች ጭንቀትም እኩል አብጦ እንደነበረ በቅርብ ሆኜ አይቻለሁ። እኛ የሩቅ ምሥራቅ ታላቅ መምህር " የጭቁኖች የበደል እንጉርጉሮአዊ ዜማ የትም ምንጊዜም ይዘመር እንጂ ቅላጼውና ምቱ (ሜሎዲውና ሪዝሙ) ተመሳሳይ ነው " እንዳሉት በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ያልተፈታ ችግር የየትኛውም ሀገር ቅን ዜጋ ቢቆረቆርና በጉዳዩ ያገባኛል ቢል ሎጂክ አለው። ተንኰለኞቹ ባዕዳንማ ጣልቃ ቢገቡ ያለውን ችግር ይበልጥ የሚያቀጣጥሉ ጋዞች መሆናቸውን ደጋግመው አሳይተውናል።

ይህ የባዕዳን ጉዳይ መነሳት አንድ ሌላ ነጥብ አስታወሰኝ። እኔ ባለችኝ ትንሽ ዕድሜዬ ውስጥ አራቴን ታላላቅ አህጉራት (በሐወርት) ላጫጭር ወቅቶች ተዘዋውሬ የማየት ዕድል በማግኘቴ፣ ለግሌ ያህል የሚረዳ መለስተኛ ዓለም አቀፋዊ የትዝብት ጭላንጭል ያካበትኩ ይመስለኛል። የምንኖርበት ዓለም ፍጹም ትክክል ነው ማለት ባይቻልም፣ ሰዎች ከሠፈሩበት ወቅት ጀምሮ የተዛባ ሥርዓት ተነጥፎባት የባሰ ችግር ተፈጥሮባታል። ማን እንደመደባቸው ዝርዝሩ ባይታወቅም፣ በትንሽ ሚጢጢ ሀገር ውስጥ፣ ብዙ ሕዝብ ተጣቦና ተጨናንቆ ይኖራል። ባንጻሩ ደግሞ፣ የሰማይ ስባሪ በሚያህል ሰፊ ሀገር ውስጥ፣ ጥቂት ሕዝብ እየተንቀባረረና

t.me/OLDBOOKSPDF

ሌላው ደግሞ በተናጠል ግለኛ ሕይወት የሚያምን ሕዝብ የሚኖርበት ሀገር ነው። አንዱ ብዙ ሕዝብ የሚኖርበት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ጥቂት ሕዝብ የሚገኝበት ነው። ያንደኛው ሕዝብ ለነጻነት ሲንሰፈሰፍ ሌላው ሕዝብ ደግሞ በነጻነት ይጫወታል። አንዱ ለዲሞክራሲ ሲጓጓ፣ ሌላው በዲሞክራሲ ይሞላቀቃል። አንዱ የምድሩን ሲሳይና ጥሪት ለመቆጠብ ሲጨነቅ፣ ሌላው ደግሞ የሀገሩን ሀብት ያላግባብ ሲያባክንና ሲንቀባረርበት ይኖራል። ያንዱ ሀገር ቤተሰብ ባስር ኳድራት ቆጡ ውስጥ ከነልጆቹ ተጨናንቆ ሲግቅት፣ ሌላው ደግሞ ከመቶ ኳድራት ሜትር ስፋት በላይ በሆነ ቪላ ውስጥ እየተንደላቀቀ ይዝናናል። አንዱ የላሙንና የዶሮውን ወተትና እንቁላል ምርት በወር እንኳ አንድ ጊዜ ማግኘት ሲሳነው፣ ሌላው በቀን ከሀያ እጥፍ እያገኘ ለነሰኘ ብሎ ያጉረመርማል። አንዱ ቡናና ስኳር ለቅምሻ ያህል እንኳ ማግኘት ተስኖት ሲንጠራወዝ፣ ሌላው ተርፎት ያመት ስንቅ ያከማቻል። የቤት እንስሳቱንም ይመግብበታል። ..... ታዲያ እነዚህ የሁለቱ ሀገሮች ሕዝቦች፣ ባንዲቷ ምድር ውስጥ፣ አንዲቷን ዝምበር እየሞቁ የሚኖሩ ናቸው። " ኖሩ " የሚለው ቃል ለሁለቱም ሕዝቦች እኩል ማገልገሉ በጣም ይደንቀኛል። ታዲያ ይህን አድላዊ ዓለም ምን ይሉታል? ዳግማይ የመዋቅር ተሐድሶ ሊደርግበት የሚገባ ዓለም ነው። የየሀገሩን ቅን ሰዎች ሐቀኛ ትግል ይጠ ይቃል። የየሀገሩን ስፋትና የየሕዝቡንም መጠን እንደገና ማስ ተካከልና ማካፈል ያስፈልጋል። በበኩሌ በመንታ ተቃርያን ሥርዓት አደር ሀገሮች በመኖሬ፣ ከቀለሙ ትምህርታቸው ይልቅ፣ ያኗኗራቸውን ሁኔታ ማየቱ ብቻ ሰፊ እውቀትና ከፍተኛ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተመክሮ ለግሰውኛል። ትዝብቴን ሳጠቃልለው፣ ያለማችን ጊዚያዊ ችግር፣ የግለ-ሰብ ስግብግብነት (ኢጎይዝም) ስሜት በየሀገሩ ጥቂት ሰዎች መንፈስ ላይ ሰፍኖ፣ አለመጠን መጎል በቱና መደርጀቱ ነው። እነዚህም ጥቂት የየማሕብረ-ሰቡ ከበርቴ ክፍሎችና ገዢ መደቦች በባሕርያቸው የሕዝብ ወገኖች ባለመሆናቸው፣ የብዙኃኑ ጭንቀት አይሰማቸውም። ከሚኖርበት ቪላ ሌላ ትርፍ ቪላዎች የሚጨምርበትን ዘዴ ይፈልጋል እንጅ፣ ሌላው መሰሉ ፍጡር ማደርያ ጉጅ አጥቶ በየበረን ዳውና በየዱሩ ሲንገላታ መኖሩ ጭራሽ አይታሰበውም። ደህ በልቶ ቢያድር ባያድር፣ ደንታው አይደለም። ሲፈጥረው "በቃ ኝን " የማያውቅ በመሆኑ ካለው ላይ ይበልጥ ለመጨመር ምን ጊዜም እንደተንሰፈሰፈ ነው። የሚገርመው ደግሞ እነዚህ ዓይነቶች ሰዎች፣ ራሳቸው ሳያመርቱ የሌሎችን ምርት በመዝ ረፍ የቶጀሩ ፓራሳይቶች ናቸው። እጅግ የሚገርመኝ ባለማችን ያሉ ሥርዓቶችና ዓለሙ ራሱ ለእንደነዚህ ያሉ እበላ ባዮች ፍላጎትና ምኞት ሆነ ብሎ የተቀናጀ መሆኑ ነው። ያደባባይ ዘራፊዎች ሆነው፣ ድርጊታቸው እንደ ትልቅ ሙያ ተቆጥሮ፣ ጮሌ (ስማርት) እስከመባል ድረስ ይደነቁበታል። ይሁን እንጅ ዓለማችን በዚህ ሁኔታ መኖርም ሆነ መቀጠል እንደ ማይችል እሙን ነው። እያደገ የመጣው የሙስና ቅራኔ እልባቱ ላይ ሲደርስ ራሱ እንደሚገታው ግልጽ ነው። ያለሙን ኪደት ወይም ይህን ጥቂቱን ሰፍሳፋ ክፍል፣ በእንቡጡ ቀጭቶ ባጭር ወቅት ውስጥ ለመግታት፣ የየሀገሩ ቅንና ተራማጅ ሕዝባዊ ወገኖች አሁንም በትብብር መሥራት ይኖርባቸዋል። የጊዜና ያስተባባሪ እጦት ሆኖ እንጅ፣ ይህ ውሳኔ ከጸደቀ ከርሟል።

በዓለማችን ላይ ጥቂቶች አልጠግብ ባይ ሰፍሳፎች እስ ካሉ ድረስ፣ በምድር ላይ ሰላም ሊሰፍን አይችልም። በሰዎችም መካከል፣ የጋርዮሽ የሆነ ነጻነት፣ ፍትህ፣ ፍቅር፣ ..... ሊኖር አይችልም።

" ሽምብራ በልቶ የማይፈስ፣ ኮካ ኮላ ጠጥቶ የማያገሳ የለም " እንዲሉ፣ ምድራችን ዕቡዮችንና ተንኰለኞችን፣ ትዕቢተኞችንና ትምክህተኞችን ይዛ እስካለች ድረስ፣ ሰላማዊ ሕይወትና የነጠረ ሥነ ምግባር ይሠፍንበታል ብሎ መጠበቅ፣ መቃዠት ነው። ከእንደዚህ ዓይነቱ ባዶ ምኞትና ተስፋ ይልቅ፣ ለዓለማችን ጠንቅ የሆኑትን ጥቂት ፀረ ሕዝቦችን መመንጠሩ፣ ጥሩ አማራጭ ነው። በተለይም አንዳንድ በመሪነት ደረጃ ጫፍ ላይ ቂጥጥ ብለው ለግል ትልማቸውና ጥቅማቸው ሲሉ ሕዝብን እርስ በርስ በማናከስ የሚያምሱ በመሆናቸው አስቀድሞ መመንጠሩ፣ ተቀዳሚ የማይገኝለት ግዴታ ነው።

ምንም እንኳ፣ የጥልጣሉን፣ የጉጂውን፣ የኩናማውን ኑሮና፣ የጎቢን የካልሃሪን፣ የስሐራን ምድረበዳዎች፣ እንዲሁም የራስ ዳሻንን፣ የቲቤትን፣ የአልፕስን ተራራዎች ..... ምንነት በቅርቡ ሆኖ ዝርዝር ሁኔታቸውን ሠቅሥቆ ያጠና ባይኖርም፣ ዛሬ ዓለም ከመቸውም ይልቅ፣ ወርድና ስፋቷ በሳታላይት ረዳትነት ጭምር ተለክቶና ተቀምሮ፣ በትንሽ ወረቀት ላይ ሠፍሮ ይገኛል። ጤናማ የሆነ የማንኛውም ሰው ጎሊና እንደሚረዳው ከሆነ፣ ምድራችን ቀርታ ጎዋጎው-ሰማያት (ጋላክሲ) ጭምር እጅግ ጠባብና ትንሽ ድምብላል እየሆኑ መጥተዋል። እውቀትና ሥልጣኔ የሰዎችን ጠባብ ያስተሳሰብ አድማስ እያሰፉ በመጡ መጠን፣ የዚያኑ ያህል ለዓለም ያለን

t.me/OLDBOOKSPDF

ዕውቀታዊ ምልዓት በመጥለቁ፣ ዛሬ አድሜ ለብሩሃን ወገኖች እንጂ፣ በፈጣን ሰማያዊ ሠረገላ ተምዘግዝጎ ካንዱ በሐውርት ወደ ሌላው በሐውርት በሰዓቶች እድሜ ውስጥ መድረስ ተችሏል። በዘመናችን አዲስ አበባ ላይ ቀጮርሱን የበላ ቾኳይ መንገደኛ በአክናፋት ተንደርድሮ፣ ለኒው ዮርክ ምሳው ተዝናንቶ ይደርሳል። ዕድሜ ለኮምፒዩተርስና ሪሞት ሴንሰሮች እንጂ፣ ጥንት ሲያስቸግር የኖረው የርቀት ኃይላዊ ጉልበት ተሰብሮ፣ በኬክሮስና በኬንትሮስ ስንባጭ መለካት ግድ ሆነበታል። ዛሬ ካንደኛው ግማደ-መሬት ዋልታ ላይ የሚደረገውን ድርጊት፣ በዛው ቅጽበት ለሌላው ግማደ-መሬት ዋልታ አስተላልፎ ማሳየትና ማናገር ተችሏል። እነዚህ ሁሉ ሳይንሳዊ እሴቶች የሚያስረዱን፣ የምንኖርበት ምድር ትንሽና ያንድ ተፈጥሮ ወጥ ሕዝቦች መኖርያ ዋሕድ ቤት እንደሆነች ነው። ሌላው ታንቲራ ሁሉ ግን በእውቀት ማነስ ምክንያት በየዘመኑ የነበሩ ደካማ ሰዎች የፈጠሩት፣ ኋላ ቀር ልማድ ነው። በዚህም ልማዳዊ አሠራር የተነሳ፣ የዓለሙ ሕዝቦች ሁሉ፣ ያለምድሪቱ ባሕርይ፣ በድንበር ተከፋፍለውና የባሕል አጥር ሠርተው ይኖራሉ። ያለ ዓለማችን ጠባይ ሕዝቦች ተለያይተው እርስ በርሳቸው እንደተናቆሩ አሉ። በየዘመኑ እንደ አሸን የፈሉትም ጦርነቶች፣ ላጠቃላይ እድገት ሊውል የሚችለውን የኢኮኖሚ ምንጭ ጨልጠው እየጠጡ፣ አብዛኛውን የዓለም ሕዝብ በችግር ሲያማቅቁት ኖረዋል።

በየሀገሩ ድንበሮች መጣስ በተጫሩ ጦርነቶች ምክንያት ብቻ፣በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ንጹሐን የሰው ልጆች አልቀዋል። የአንዱ ክልል ሀገር ሕዝብ በሀብቱ ጠግቦ ቁንጣን ሲያማቅቀው፣

በአንጻሩ ደግሞ የሌላው ሀገር ሕዝብ፣ በረሀብ ጠኔ ተጠብሶ ያልቃል። የአንዱ ሀገር ሕዝብ የሌላውን ሀገር ሕዝብ ተንኩሶ ይቀጠቅጠዋል። ሌላው የሦስተኛው ሀገር ሕዝብ በመገላገል ፋንታ፣ ከዳር ቆሞ ያስካካል። ሌላው ደግሞ የሚቀጣቀጡበትን መሣርያ እየቸበቸበ፣ በገንዘቡ ሻምፓኙን ይልፋል። ሌላው ደግሞ በግርግሩ መሐል ገብቶ እያወናበደ ይዘርፋል። ..... ይህ ሁሉ የሚሆነው በተፈጥሮአቸው ተመሳሳይ በሆኑ የሰው ልጆች መካከልና ነጠላና ዋሕድ በሆነችው አንዲት ምድራችን ላይ ነው። ፊው!!! በእግርጥ አለመታደል ነው።

ይህ ዓይነቱ አሳዛኝና አሠቃቂ ክሥተት፣ ከየትኛውም ሀገር ይልቅ በተለይ ከሺ ዓመታት ላላነሰ ጊዜ፣ በኢትዮጵያ ውያን ላይ እጅግ ከፍቶ ታይቷል። የጥንቱ እንኳ፣ በዕውቀት ማነስ የተፈጸመ የድንቍርና ድርጊት ነበር የሚያሰኝ የይቅርታ አስተያየት በመስጠት ሊታለፍ ይችል ይሆናል። ዛሬ በኻያኛው የሥልጣኔ ክፍለ ዘመን ካባውን ቀይሮ በዓለም አቀፍ ወዳጅነት ስም ሲፈፀም መታየቱ ላጠቃላዩ የሰው ልጆች ሞራላዊና ኅሊናዊ አስተሳሰብ የሚቀርብ፣ የዘመናችን ታላቅና ተቀዳሚ ጥያቄ ነው። በሕግጋተ-ዓለም አሻፈረኝ የሚል ደባን ሕገ-ሞራል ይቋቋመው ነበር። ሕገ-ሞራልንም ጭምር ረግጦ የሚ ያልፍ ጋጠ-ወጥና ጀርጃራ ኃይል ሲነሳ የምን ጉልበትና ሥል ጣን ያርቀው ይሆን? የዘመኑን የኃያላን ውንብድና፣ ለታሪክ ፍርድ ብቻ መተው ይሻላል።

በዓለማችን ነባራዊ ባሕርይ ሁኔታ በጣም ከሚያገኙ ሰዎች አንዱ ነኝ። የኢኮኖሚያዊ ፍትሕ ማጣት፣ ነዋሪዎቿን ከረበሸው ዋናውና አንደኛው ችግር ነው። ተከታዩ ደግሞ

t.me/OLDBOOKSPDF

በየሀገሩ፣ የቅን ዜጎች ማነስና መመንመን ነው። ባለማችን የእንደዚህ ያሉ በቀኖዔቶች አለመሟላት ጠብና አለመግባባት እንዲነግሡ ረድቷቸዋል። ስለሆነም፣ በዓለሙ ውስጥ በተፈጥሮ ሕመም ከሚሞቱ ሰዎች ቍጥር ይልቅ፣ በኢተፈጥሮ ሕመም የሚያልፉቱ ይበዛሉ። ይህም አሠቃቂ ሁኔታ መጠኑ እየጨመረ እንጅ እየቀነሰ አልመጣም። ኧረ ለመሆኑ በሕዝቦች ዘንድ ፍቅርን ለማስፈን ምን ዓይነት መፍትሔ ይበጅ ይሆን? መልስ የሚጠብቅ ጥያቄ ነው።

በርግጥ እኮ የሰው ልጆች የርስ በርስ መራራት ባለማችን ቢሰፍን ኖሮ፣ መች ጠላኧና ተጠላኧ፣ መጥማጭና ተመጥማጭ፣ ጨቋኝና ተጨቋኝ..... የሚባሉቱ መንታ መደብ-ሰዎች ይኖሩ ነበር? የርስ በርስ መራራት ባለመኖሩማ፣ ይኸው በደረስንበት የማኅበረ-ሰብ እርከናዊ ደረጃ ላይ፣ የከበርቴው ሥርዓት ምንጪ- ምርቶችን በሥርዓተ-ግለኝነት መመሪያው፣ እንደ መኧገር ለብቻው ተጣብቆ እየመጠመጠ ባስገኘለት ጉል በቱ፣ ተቀናቃኞቹን የሥርዓተ ጋርዮሽ ሶሻሊስቶች ሲከላከል ይታያል። ግን ባይገባው ይሆናል እንጅ፣ የዓለማችን ሕዝባዊ ጉዞ ሁሉ ነገር የጋርዮሽ ወደ እሚሆንበት ካምፕ ነው። የመ ዳረሻ ጉዞውንም ወቅት ለማሳጠር፣ ትግል በየመልኩ በየሀገሩ ይካሔዳል።

በየሃገሩ ያሉ አድኃርያን ኃይሎች ግን፣ ይህን ትግል ለማ ሰናከል እንደጣሩ ናቸው። ከንቱ ጥረት!! ሰው እንዴት ከታሪክ ለመማር እንደማይችል ኣይገባኝም። ያለፉት ዘመናት ታሪክ በሙሉ፣ ሲያሳዩ የኖሩት የለውጥን ያዲስ ልደታዊ ኪደት ነው። ከነበረው ምን ጊዜም ለመሻሻል.....

በጊዜያችን በሀገራችን ሥልጣን ኮሮቻ የተፈናጠጡ ገዢ ምች፣ ይህን ሐቅ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የረሱት ይመስላል። በመሆኑም ከጥንተ-ሥርዓታቸው ጋር ተጣብቀው፣ በመከረኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ፣ በሙስናና በወሲብ ሲባልጉበት ይታ ያሉ። ምንም እንኳ የቆብ አጥላቂነት ዝርያነታቸው ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መሆኑ ቢታወቅም፣ እንደዘመኑ ሰውነ ታቸው ራሳቸውን አርመው ማስተካከል በተገባቸው ነበር። ይህ ዓይነቱን ባሕርይ ምርጥ መኰንኖች የወረሱት ነው ሲባል ያለ ምክንያትና ያለማስረጃ አይደለም። ጥንትም ዛሬም መከረኛውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲለበልቡት የኖሩ የዛሬዎቹ ገዢዎች የሙያ አባቶቹ ለመሆናቸው ካንዲት መጽሐፍ ብቻ ልጥቀስ (ይህ ማለት ሞራል ያላቸው ጥቂት ወታደሮች እንዳሉ በመዘንጋት አይደለም።)

..... " እስከ ትላንት ድረስ በነአጼ ቴዎድሮስና በነአጼ ዮሐንስ ጊዜ፣ የኢትዮጵያ ደህ ለወታደር መጫወቻ ባርያ ነበር። ባርያ በገዛ ራሱ ማዘዝ እንደማይሆንለት የኢትዮጵያ ደህም በገዛ ቤቱ ማዘዝ አይሆንለትም ነበር። የሚያገለበት ቆር ፋፋ ጋሻ ያንገበና፣ አንድ ባለጌ ጦር የያዘ፣ አንድ የመሸበት ደበናንላ የጀራረገውና ተሰገባው በስፍራ ተጣልቶ ፀሐይ የሚሞ ቀው ጐራዴ መሳይ በወገቡ ያገነበጠ ቅማላም ወታደር ነበር። ይኸ ወታደር ግን እሱን ደስ ላይለው የሌላውን ደስታ ሲከላከል ለገዛ ራሱ ላያልፍለት የድህውን ንብረት ሲያፈርስ ይኖር ነበር። ይኸ ወታደር እንኳንስ ተሰሪነት ገብቶ፣ ለቅሶጥ ሒዶም ባደረበት አገር ሳይቀር፣ ድህውን የፊጥኝ አስሮ፣ ነጭ ኑግ፣ ጥቁር ወተት ውለድ ሲልና ባለቤቶቹ ሚስቲቱ እንደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገረድ፣ ባልየው እንደሎሌ እግር አጥበው፣ አልጋ አንጥፈው፣ ትራፊውን በልተው፣ እነሱ ተምድር፣ እሱ ታልጋ ተኝተው ያድሩ ነበር። ከቶም አንዳንድ ጊዜስ መልክ ቅን ምሽት የነበ ረችው በላገር በመከራ ላይ መከራ፣ በግፍ ላይ ግፍ፣ በውርደት ላይ ውርደት ታክሎባት ያድር ነበር። " (ገጽ 2) ..... በነአጤ ቴዎድሮስና በነአጤ ዮሐንስ ጊዜ ከጅብ አምልጦ የቀረ ቆርበት የመሰለ ጨርማዳ ጋሻ በብብቱ ያጣበቀና፣ ባለቋድ ወይም ሲሶ እንጨት ብረት መሳይ በጫንቃው አጋድሞ ብቅ ያለ እንደሆነ አንድ እከካም ነፍጠኛ ብቻውን ሆኖ አንድ መንደር ሲያስር ሲፈታ፣ ሲያስጨንቅ ያድር ነበር..... (ገጽ 4) ..... ወታደሩ ዘመቻ ሲሉት ጐራዴውን መሳል፣ ፈረሱን ማጠጠር፣ ጠበንጃውን መወልወል፣ ተነስም ሲሉት ለውሻ የሥጋ ክምር፣ የርጎ ባሕር አለ ቢሉት ወዴት ነው ሳይል እንደሮጠ ለመዝረፍ፣ ከብት ለመንዳት፣ ተልዕኮ እስካሮጌው ለመፍጀት፣ ተቆንጆ እስከ ባልቴቱ አጋፎ ለባርነት ለማምጣት ይቸኩል ነበር እንጂ....." (ገጽ 45)

(ዳግማዊ ምኒልክ፣ አፈወርቅ ገ.ኢየሱስ 1901 ዓ.ም.)

የወረስነው የማኅበረ-ሰባችን ዋርድያ፣ ጥንተ-ልምዱ፣ ጥንተ-ግብሩ፣ ጥንተ-ባሕሉ፣ እንዲህ መሆኑ ከታወቀ፣ በዘመ ናችን የሚገኘ ዝርያው ሞይልነቱን ቢያንፀባርቅ ከቶ ምን ያስደንቃል? አሁንም የሰው ልጅ ለምን ካለፈ ታሪክ መማርና ተመክሮውንም ለመረዳት እንደማይችል አይገባኝም። የዚህ ትውልድ ትልቁ ተግባር እንዲህ ያለውን ድክመት ተረድቶ ይህ ንን የኛጀ የወታደር ሥርዓት ማናጋትና ማፍረስ በምትኩም አዲስ ዲሞክራታዊ ሥርዓት መገንባት ነው። ጉልበት የሚገ

ዛውን ምንዝር ሕዝብ፣ ጉልበት ያለው የተባበረ ሕዝብ ነጻ ያወጣዋል። ኅብረት የዘመናችን ከበሮ የዕለቱ ታንቡር ነው። ተባበሩ በሚል የጥሪ ድምጽ ይንራል፣ ይነዝራል። በአሁኑ ጊዜ እዝነ ኅሊና አለኝ የሚል ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣ በመስማት ሊጠ ቀምበት የሚገባው ድምጽ ቢኖር ይህንን ጥሪ ብቻ ነው። የሀገራችን ሕዝባዊ ችግሮች ከመቸውም ጊዜ ኅልተውና አፍ ጠው በአደባባይ በሚታዩበት በአሁኑ ዘመን ችግሩ የሚመለከተን ወገኖች ሁሉ የምናቀርበው መፍትሔ ለዘለዓለሙ የሚደነቅ ነው። እንዳንዶቹ መፍትሔዎች በቀረቡበት ዘይቤና በሚገ ለጹበት ይትብህል ቢገመገሙ " ከፍየልና ከበግ ሥጋ የትኛው ይጥማል? " ተብሎ የተጠየቀ አንድ መገለጢጥ ሰው፣ ያልበ ላውን እንደሚያኩለት ጭቷም ሰው፣ ' የዓሳ ሥጋ ያሚል ጫል' " ብሎ እንደመለሰው ዓይነት ናቸው። የማኅበረ-ሰብ ችግር መንስኤዎችና መፍቻም ቀ'ልፎቻቸው በሶሻል ሳይንስ ቀ'ልጭ ተደርገው ንጥረው ቀርበዋል። የችግሩም አጠቃላይ መም'ሪያው " መጣጭን ከተመጣጭ የግድ ገንጥሎ የመጣል ዚቅ ብቻ ነው። " በዘመናችን ዓቅም ያነሳቸው ፈሪ ተገፊዎች እንኳ፣ ዕድሜ ለዘመኑ ሳይንስ በሩቅ የሪሞት ኮንትሮል ፈንጂ ገሬ ኃይሎችን ያጠዛሉ። ..... የኛ ሊቃውንት ግን ልዩ የትግል መፍትሔ ቆፍረው ለማውጣት ግላዊ ሪሞት ኮንትሮላቸውን በአየር ላይ ደግነው የሚያፈነዱት ግዙፍ አካል ሳያገኙ ቆይተ ዋል። ይህም በመሆኑ የሀገራችን ሕዝብ ችግር ከጌዚ ወደ ጌዜ እየባሰበትና እያስመረረ መጥቷል።

እንደሚታወቀው በማዕበለ የካቲት የለውጥ ጭላንጭል በመጠነ ጨረር ፈንጥቆ ነበር። ገና እንደተወጠነ መቀጨቱን

ብዙዎቻችን እናውቃለን። ያ ጅምር ከፍጻሜ መድረስ ያለበት ሕዝባዊ ውጥን ነው። በመደበኛ ደረጃ ያሉ መደበኛ ቅራኔ ዎችን እንዳሉ ወዝፏቸው ጨንግፏል። የትግል ስልት ተሳክሮ ጠላኽ ጠላትን ከሥልጣን ላይ አስቀምጦ አልፏል። ቢቸግ ራቸው የጊዜአችን አንዳንድ ታጋይ ክፍሎች በሁለተኛ ደረጃ የሚገኝ ቅራኔን አስቀድመው፣ አለደረጃው ለመፍታት በመራ ወጥ ላይ ናቸው። የትግል ሥርዓት ግን እንደ መሰላል ያለ በመሆኑ፣ በስተታች ያሉትን ቀዳማይ መወጣጫዎችን ሳያልፉ፣ ከላይኛው መድረስ እንደማይቻል ግልጽ ነው። የደረጃን ቅደም ተከተል ይጠይቃል።

ሉሹን የሚባለው የቻይና እውቅ ደራሲ የመጀመርያ የሙያ መስኩ ሥነ-ጽሑፍ አልነበረም። በዘመኑ፣ ከዚያ ሁሉ መዓት የቻይና ምሁራን ውስጥ የተለየ ዕድል ገጥሞት፣ ጃፓን ቶክዮ፣ ነጻ የትምህርት ዕድል አግኝቶ ሊማር የሔደው ሕክ ምና ነበር። በትምህርቱ ላይ እንዳለ የሰፊው ቻይና ሕዝብ በሽታና ደዌያት መነሻው ራሱ በሽታው ሳይሆን፣ የማኅበረ-ሰቡ በትምህርት ወደ ኋላ መቅረትና ለድንቊርና ተገዢ መሆ ኑን ይገነዘባል። እነዚህን ህዝባዊ ችግሮች መቋቋም የሚቻለው በኪኒንና በመርፌ (መድኃኒት) ሳይሆን በመሰረተ-ትምህርት ነው ብሎ በመወሰን፣ ወዲያው የጀመረውን የሕክምና ትምህ ርት ኣቋርጦ ወደ ሀገሩ ኰብልሎ በመመለስ፣ በደረሰ በማግ ስቴ ባስተማሪነት ተቀጥሮ የመምህርነት ሥራ ጀምሯል። በማና ቸውም የተግባር ስምሪትና መርሐ ግብር ላይ የቅደም ተከተ ልን ሥርዓትና የደረጃ እርከናዊ አሠራርን ዘዴ ማወቅ፣ ለጥሩ ወጤት ወሳኝ ነው። በኢትዮጵያ ትግላዊ ኪደት ላይም፣ ይህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያፈጻጸም ደረጃን ያለመጠበቅ ድክመት ተዘውትሮ ተንጸባ
ርቋል። ለተፈጠረውም ቀውስ አንዱም ምክንያት ይኸው ድክ
መት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተዘፈዘፈበት የክስረት ዝቅጠት ውስጥ መውጣት አልቻለም። የዘመኑን ቀውስ ያባባሰው " ያለኔ የሚያውቅልህ የለም " በሚል ድፍረት ከሥልጣን ኮሮቻ ላይ ተሳፍሮ፣ ከጥንት ጀምሮ በየጊዜው በግፍና በበደል አድራጊነቱ እያደገ የመጣው የወታደሮች መኰንናዊ አምባገ ንንት ነው። ይኸው አድኃሪ ኃይል ላለፉት አስራ አምስት ዓመታት በየዋሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈጸመውን መከራና ሽብር ሥቃይና እልቂት ተናግሮ መጨረስ አይቻልም። በሀገር ውስጥ የሚፐኙ ደራስያን፣ ይህን ግፍና በደል ባጠገቡ ሆነው ማየት ቢችሉም፣ ባለባቸው ተጽዕኖ የተነሳ መዝግበው ሊያሳ ትሙት አይደፍሩም። የደፈሩ ቢኖሩም ከሕይወት መዝገብ ላይ ወዲያው ተፍቀዋል። የጨለማው ዘመን መንግሥት ባለሥ ልጣኖች፣ ደራስያንን በማጥፋት የሚፈጽሙት ግፍና ሙስና ተደብቆ የሚቀር ይመስላቸዋል። በሕዝቦች ላይ የሚፈጸም አስቀያሚ ግፍና በደል ግን እንደተናኘ ጭስ ሽንቁርና ቀደዳ ፈልጎ ሰርስሮ መውጣቱ አይቀርም። በዚህ እትም ላይ የሰፈሩ ታሪኮች፣ የዚህ ሐቅ ክስተት ናቸው።

እነዚህ ቆናጽል ድርሳናት (አጫጭር ልቦለዶች) በይዘት አቀራረባቸውና በመዋቅር ቅርጻቸው ፈጠራ ልቦለድ ይሁኑ እንጂ ጭብጥ ይዘታቸው ያለፈውን አስራ አምስት የጨለመ ጠቂራ ዘመን ከነሰንኮፉ የሚያንፀባርቁ መስተዋቶች ናቸው። አጫጭር መሆናቸው ካላቸው ወርድና ስፋት መለጠጥ ሳይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ችሉ ቀርቶ ሳይሆን፣ በየዘርፉ የተፈጸሙት በደሎች እጅግ ብዙ ስለሆኑ፣ ከየዓይነታቸው ለናሙና ያህል እየቄነጠሩ ለማቅረብ ታስቦ ነው።

እነዚህ ሚጢጢ ልቦለድ ታሪኮች፣ በከረረ አቀራረ ባቸውና ጥርንቅ ይዞታቸው፣ ባለራአምስቱ ዓመታት ውስጥ የተፈጸሙትን መራራ ቅጽበቶች ጥቂቶቹን ብቻ የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ በውሱን ቦታና ወቅት ላይ የተፈጸሙ አስቀያሚ ድርጊ ቶችን በማሳየት ረገድ ወደር የሚገኝላቸው አይደሉም። በተለ ይም የማኅበረ-ሰቡን የመከራ ገጠመኞች ማንፀባረቅ ብቻ ሳይሆን ባቀራረባቸው ረገድ እንዲያብለጨልጩና እንዲያጥ በረብሩ ተደርገው የተዋቀሩ መሆናቸው ሆነ ተብሎ ነው። የማጥበርበርና የማብለጭለጭ ባሕርይ ያለው ወስተዋት የተመ ልካችን ዓይን ይጣላል። ዓይኑ እንዳይቦዝበት የሚፈልግ ተመ ልካች ደግሞ ከብልጭልጩ አካል ዓይኑን ለመከላከልና ለማዳን ተገቢውን ዝግጅት ያደርጋል። ተራው መስተዋት ሁለንተናን እንዳለ ከነጉድፉ ጭምር የሚያሳይ ሲሆን፣ እነዚህኖቹ የማኅበረ-ሰባዊ ሕይወት መስተዋቶች ግን ከዚያም አልፈው ጉድፉን ብቻ በማሳየት ሳይወሰኑ፣ የጉድፉን ማስወገጃ ዘዴ ጭምር ይጠቁማሉ። ከሌሎች መሰል ያጫጭር ልቦለድ ታሪክ ድግሶች የሚለይበት ቅመም ቢኖር፣ ይህ ባሕርያቸው ነው።

ታሪኮቹ በሙሉ የሚተርኩት ስለ ድኅረ የካቲት ኢትዮ ጵያ መቅሰፍት ሲሆን፣ እንዳጋጣሚ እኔ በዚህ ረገጉም ዘመን ወቅት በአካል ኢትዮጵያ ውስጥ አለመኖሬ ግልጽ ነው። በአካል ካልነበረ " ምን አይቶ ከምን አሻሻቶ እንዴትስ ሰምቶ ሊጽፈው ቻለ? " የሚሉ ተራቢዎች ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል። ለደቂቃም

በመንፈስ እንዳልተለየሁ ብናገር የሚያምኑኝ ባይሆኑም፣ ዛሬ ባለንበት ዘመን በአንድ የምድር ጥጋት ላይ ስላለች ሀገር ሁኔታ ለማወቅና ለመጻፍ ለሚፈልግ ሰው፣ ፍላጎቱ እስካለ ድረስ በአካል አገሪቱ ድረስ ሲጎተት መሔድ አይኖርበትም። ሁሉን ዜና ካለበት ሆኖ ማግኘት ይችላልና። ርቀት ተሸንፏል።

በእትሙ ውስጥ የሰፈሩ ታሪኮች ከፊሎቹ የልዩ ልዩ ሰንካላ ሐሳቦች ቀላጤዎች ሲሆኑ፣ ከፊሎቹ ደግሞ የሌላ ባሕርያት ወኪሎች ናቸው። ለማሳያ ያህል አልፈ አልፈ አንዳንዶቹን ላቅርብ።

" የሽሽግግር ደባ "—(ገጽ 65) የሚለው ታሪክ ትእምርታዊ (ሲምቦሊክ) የሆነ የወንዛ ወንዝ ታሪክ ይሣል፣ ይኳል፣ እንጂ እንደው በእንተ ወንዝ ሙላት ብቻ የተጻፈ ከቸሮና ደረቅ ሐቲት አይደለም። ሐቀኛ ትይታው ሦስትና አራት ነቍጦችን ያካትታል። ወንዝ፣ ማዕበል፣ ተሻጋሪ፣ አሻጋሪ። የአንድ ማኅበረ-ሰብ ሕዝብ የሚጓዝበት ሥርዓት ከርክሶ ሲቆም፣ በሆነው ዐይነት ዘዴ ወደ ታዳጊ አዲስ ማኅበረ- ሥርዓት ለመለወጥ ሲሞክር፣ የሚያጋጥመውን የወርሐ ማዕዶት ሁኔታ የሚጠቁም ታሪክ ነው። እንደሚታወቀው ወንዝ ሲሞላ መቸገር ያለ ነው። ወንዙ ከሞላና ተሻጋሪውም ዋና የማይችል ከሆነ፣ አሻጋሪ ማስፈለጉ ያለና ግድም ነው። የዚህኛው ወንዝ ሙላት ግን ማዕበሉና ጎርፉ የተለመደ ቢሆንም፣ ያሻጋሪው ሰው ዓይነት ከወትሮ የተለየ ነው። የውሀ ማዕበል ገጥሞአቸው ተጨንቀው ለነበሩ የሞሃን መንገደኞች ምንም ዓይነት የሞራልና የዲስፕሊን ዝንባሌ አለማሳየቱ ብልግና ነው። የዚህን ታሪክ ይዘት በዚህ ዓይነት ትንተና ጀምሮ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ከታሪኩም ተልእኮአዊ አድማስ ባሻግር የሚኖረውን ምናብ ማዘከሩ፣የአንባቢያን ጉዳይ ነው።

" .... አዋልደ ወንዴ "—(ገጽ 79) የእውነተኛ ታሪክ ሰምና ወርቅ ነው። በወይዘሮ ትምክሕተ የተመሰለች ኢትዮጵያ ከዕብደት ባላነሰ ደዌና ጭንቀት ተሠቃይታለች። ማናቸውም ነገር መነሻ ምክንያትና መድረሻ ውጤት እንዳለው ሁሉ፣ እናት ትምክሕተን ለዚያ ዓይነቱ የጭንቀት በሽታ የጣላቸው፣ ከማሕጸናቸው የወጡ የመንታ ልጆቻቸው እርስ በርስ መናቆር ነው። በባሕላቸው " ይቅርታን፣ ዕርቅን፣ ስሕተት መቀበልን.... " እንደሽንፈት የሚቆጥሩ መንታ ልጆቻቸው እርስ በርሳቸው ተጠፋፍተው እስኪያልቁ ድረስ በየጀመሩት አቋማቸው የጸኑ ይመስላል። እናት ትምክሕተን እየነጀሰ የሚያወፍፋቸውና የሚቀውሳቸው ይኸው የመንታ ልጆቻቸው እርቅ የለሽ አቋም ነው። ታሪኩ ባጭሩ ይህን አውነታ ያንጸባርቃል።

" ሞኝ ባገኘ "—(ገጽ 137) ይህ በአንድ ድኅረ የካቲት ወቅት የተከሰተ የበሽታ ዓይነት ስያሜ ነው። ወረርሽኝ። ያላንዳች ተቀዳሚ ጥናትና ያካባቢ ዝግጅት፣ ተራማጁን ለጋ ወጣት ካጠገባቸው ለማራቅ ብቻ ሲሉ ያቀዱት የገጠር ዘመቻና ያስከተለውን አሠቃቂ ውጤት ለማሳየት የተነደፈ ታሪክ ነው። በሽታው የተላላፊነት ባሕርይ ስለነበረው፣ ታመው በተመለሱ ዘማቾች አማካይነት አዲስ አበባ ሳይቀር ገብቶ ሕዝቡን አምሶት እንደነበር ይታወሳል። በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በህልሙ ያየውን ቅዠት ሁሉ፣ በአዋጅ እያስተላለፈ፣ የሕዝቡን ታዳጊ ልጆች አለምሕረት ይጨፈጭፍ እንደነበር አይዘነጋም። የዚህ ታሪክ ጭብጥ የሚያሳየው ደግሞ፣ የአዋጁ ተንኰል

ከተነቃበት በኋላ ግድያውን በስውር ለመቀጠል የተጠቀመበት ሌላው ዘዴ እንድነበር ነው።

" ዘሲባኖስ "—(ገጽ 203) ገና በወጣትነት ዕድሜው የማኅበረ-ሰቡ አድኃሪ ሥርዓት በፈጠረበት ወንጀል ታስሮ፣ አበባ ዘመኑን ጀህነም በሆነ እስር ቤት ውስጥ፣ የሚያማቅቅ አሳዛኝ ወጣት ሁኔታን የሚያጋልጥ ታሪክ ነው። ቦታው አዲስ አበባ ውስጥ የሚኾነ ዓለም በቃኝ፣ ዘመኑ ድኅረ የካቲት ነው። ቀደም ሲል ራሴ ባይኔ ያየሁት አጋጣሚ ሲሆን፣ የዚያም እስር ቤት ጀሐነማዊ ሁኔታ እስከዚህችኛዋ ቀን ድረስ ያለምንም ለውጥና መሻሻል እንዳለ ነው። ዛሬማ እሰረኛው ጢም ብሎ ሞልቶበታል ይሉ ኖል። እኔ ካገር ቤት ከወጣሁ ጀምሮ፣ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የዓለም አቀፍ ሕዝባዊ ድርጅቶችና ተቋሞች ሁሉ (የተባበሩት መንግሥታት ፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል.....) ስለ ዓለም በቃኙ እስር ቤት ሁኔታ ገልጬ፣ ከሥሩ ተመንግሎ እንዲደመሰስ ብዙ ሙከራዎች አድርጌ ነበር። ሙከራየ ዋጋ እንዳላገኘ በተረዳሁ ጊዜ ነው፣ ባለጉዳዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ እስርቤቱ ውስጣዊ ይዘት እንዲያውቅ በማሰብ ይህን አጭር ታሪክ የጻፍኩት።፣..... ወዘተ.....

እንግዲህ እነዚህን ታሪኮች ለምን ራሳችሁ አታገላብጧቸውም። በወሲብ፣በሙስና፣ በጦርነት፣ በረሀብ..... የማቀቀች ሀገራችሁ፣ የሁላችሁንም ቆራጥ መስዋእትነት ትጠይቃለች። በርግጥ ካንጀታችሁ ካሰባችሁላት፣ ልትረዷት የምትችሉበት ብዙ መንገዶች አሉ። ቢቻል ተባብራችሁ፣ አለያም በየግላችሁ ልታደርጉ የምትችሉትን ከማድረግ ወደ ኋላ አትበሉ። ብዙዎቻችን የግለ-ሰቦችን መልካም ጥረት ስናካኪስና ስናቃልል

t.me/OLDBOOKSPDF


" አንድ ሰንበሌጥ ቢመዘዝ ቤት አያፈስም " እንላለን። ቁምነገሩ በእርግጥ " ከመምዘዙ" ላይ ከሆነ " አንዲት ራስ ክብሪት ተመዛ በመጫሯ አይደል፣ ሀገሩን ምድሩን ለኮሳ የምታቀጣጥል? " ሀገራችንን ራሳችን ልንረዳት ካልቻልን፣ በዓለም ዓቀፍ ወኃጅነት ስም ባዕዳን እየገቡ፣ ወገኖቻችንን እንዴት እንዳመሳቀሏቸው አይተናል፣ ተረድተናልም። የ " ሠመነ " " የተጣሰ አጥር " ..... የተባሉት ታሪኮች በዚህ እትም ውስጥ መሥፈራቸው ይህንን ጥሪ ለማጠንከር ነው።

በስደት ላይ ያለነው ወገኖች ብዙ ፈተናዎች እየገጠሙን ነው። ግንኑታችንን ለማዘናጋትም አያሌ ውጥረቶች እየተፈታተኑን ነው። በእርግጥ የምፈራው የገጠሙን ውጥረቶች በየጊዜው እያደጉና እየከረሩ መጥተው " አባቴን ገድሎ ለአማቹ ይነጭ፣ አማቴን ጋርዶ እናቴን ያስፈጭ " የሚባለውን ብሂል እንዳያስተርቴብን ነው።

በተረፈ እነዚህ ታሪኮች እንደተከማቱ ላስቲኮች ዓይነት ናቸው። በወጠሯቸው መጠን መሳብ ይችላሉ። ለድር ጊቱ ያንባቢያንን ጡንቻ ይጋብዛሉ። ባጠቃላይም ማንኛውም አንባቢ እነዚህን ታሪኮች ካነበበ በኋላ፣ ወገኖቹ ኢትዮጵያውያን በተፈጸመባቸው በደሎች እጅግ ተሰምቶት እንድሚበግን አውቃለሁ። የታሪኮቹ በእንደዚህ ዓይነት መቅረብ ዓላማና ግብ ግን፣ አንባቢያንን ለማብገን ሳይሆን፣ በያሉበት ሆነው፣ ለዚያ ምዝብርና ግፉዕ ሕዝብ፣ አንዳች መፍትሔ እንዲፈልጉለት በምሬት ለማሰብ ብቻ ነው። እንግዲህ ከሌሎች አዳዲስ እትሞቼ ጋር በቅርብ እስክንገናኝ ድረስ እስከዚያው በያላችሁበት ደኅና መሆንን አድርጉልኝ!!

ወንድማችሁ (ገ.ነ. ብልጣሶር)

የሸማር ደባ



ጐርፍን ተገን አርጎ፣ ዕቡይ ዋነተኛ፣
ጨዋ መስሎ ገብቶ፣ ውስጠ-ተንኮለኛ፣

እችላለሁ ብሎ፣ ያሻጋሪ አታላይ!
አርክሶ አጣላ፣ ከኑሮ ሊያለያይ!

ይህ ዐይኑቱስ ታንኳር፣ ደባ አይደለም ወይ?
በወርሀ-ግዕዶት፣ የበቀለ እንጉዳይ!

(የጠፍ. ቁ.2)

t.me/OLDBOOKSPDF

መንደርደርያ

የሰው ልጅ የህይወት ጣቢያዎች ቁጥራቸው ብዙ ቢሆንም፣ ዓበይቶቹ ግን ሦስት ናቸው። ልደት፣ ሰርግ እና ሞት። እነዚህን አብዛኛው ሕዝባችን አምኖ የተቀበላቸው ሲሆኑ፣ በነባር ባህልነትም ሰንጠረዥ ላይ አስፍሯቸዋል። የዚህች ታሪክ ንድፈ ሐሳብ በሠርገኞች ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው። ሠርገኞች ለአዲስ ህይወት የተሰለፉ የረዥም ጉዳና ተጓዦች ናቸው። ዘመቻቸው ውጣ ውረድ ይኖርበታል። ገና ትኩስ የሥርዓተ-ጋብቻ ምልምሎች ቢሆኑ፣ ማሕበረ-ሰቡ ባላቸው ከፍተኛ ዓላማቸው መዝሞ ያከብራቸዋል። ያንድ ማህበረ-ሰብ አቢይ አቋማዊ ድርጅት የሚመሠረተው፣ ከትንሽቱ የቤሰ-ሰብ ሕዋስ ላይ በመጀመር ስለሆነ፣ አክብሮታቸው ምክንያታዊ ነው። ጤናማ ቤተ-ሰብ ከሌለ፣ ጤናማ ማሕበረ-ሰብ ሊኖር አይችልምና።

በዚህች አጭር ልቦለድ ታሪክ ውስጥ የቀረቡት ሙሽሮች ግን፣ ገና በጋብቻቸው ሰሞን ውስጥ፣ ባንድ ወቅት ላይ ፈተና ይገጥማቸዋል። የብሩህ ተስፋቸው ጉዳና ሥክና አሜካላ እንደሞላበት በዚሁ አጋጣሚ አሻግረው ለመመልከት ይረዳቸዋል። ቤሰ-ሰብ በመመሥረታቸው የተደሰቱ ዘመድ ወላጆቻቸው፣ ያገር ልምድ ነውና ቤት ማያ ድግስ ይጠሯቸዋል። አንዱ ጋር ደርሰው ወደ ሌላው ሲያመሩ ውሃ ይሉ የወንዝ ጉርፍ ያግዳቸዋል። ወሃው እስኪያንስ ወይም ጉርፎ እስኪ ሰክን መጠበቅ ቀጠሮ ማበላሸት ይሆንባቸዋል። እንዳይሻገሩ የወንዙ ሙላት ይጐሰብትባቸዋል። በዚህ አጣብቂኝ ውስጥ እንዳሉ፣ ከዚህ መጣ የማይሉት " አሻጋሪ ነኝ ባይ " ዋነተኛ ከፊታቸው ከቸች ይላል። የታሪኩ መሠረተ ጭብጥ በዚሁ ሁኔታ ላይ ይጀምራል።

t.me/OLDBOOKSPDF

አራት ነቀጦችን ማስታወስ ያንባቢዎች ግዴታ ይሆናል። ተሻጋሪዎች፣ አሻጋሪ፣ ማዕበል (ጐርፍ) እና ባሻገር (ማዶን) ናቸው። እነዚህም የሐሳብ መሸከርከርያ ነጥቦች በነዚያ ሙሽሮች ሁኔታ ላይ የሚታዩ እውነታዊ ግኝቶች ይሁኑ እንጂ፣ በሥነ-ጽሑፍ ጥበባዊ አወቃቀር ላይ " ተምሳሊት " ይባላሉ። " ስለዚህኛው " የሚተርኩ መስለው ስለዚያኛው የሚያወሩ ናቸው። " ስለዚህኛው " ጸሐፊው ቢዘረዝም " ስለዚያኛው " ገንግኖ ማየት ያንባቢያኑ ፋንታ ነው። በትምህርተ-ሳይንስ የምና ውቀውን ያህል፣ በጸሐይ ጨረራዊ ኃይል፣ በገጸ-ምድር ላይ ተንጣልለው ያሉ "ውሀዎች" ሞቀውና ግለው በአየርነት ተነው ወደ ሕዋ ያርጋሉ። በሕዋ ላይ ተንሳፎ የሚገኝ ቁር በበኩሉ፣ ቢጋለ አየርነት በመትነን ሸሽቶ በሙጥኝታ የመጣውን አየር አቀዝቅዞ እንደገና ወደ ጥንተ ወሃነት በመቀየር በዝናምነት ወደመጣበት ምድራዊ ቤቱ ይሸኘዋል። ወሃ ሆየ ሲሞቀው ይተናል፣ ሲቀዘቅዘውም ይዘንባል። አንዳንዴም የቁሩ ኃይልና ጉልበት ሲበዛበትና ሲጫነው በረዶ የሚሆንበት ወቅት አለው። ይህ እንግዲህ የውሃ የዝንተ ዓለም " ዑደት " መሆኑ ነው። ወዶ የሚያደርገው ሳይሆን ተገድዶ የሚፈጽመው ነው።

በዝናም መልክ የወረደ ወሃ ረባዳ ቦታዎችን ፈልጎ ወላጅ እናቶቹን ባሕራትና ውቃያኖሶች ለመቀላቀል በየሸለቆ እየ ተሽሎከለከ ይነጐዳል። የውሃውን ጉልበትና ብዛት የሚወስ ንለት፣ የዝናቡ መጠን ነው። ሙሽሮቹን ያጋጠማቸው የውሃ ጐዳና (ወንዝ) የዶፍ ዝናብ የወረደበት ወቅት በመሆኑ እጅግ ጐልብቶ ነው።

እንደሚታወቀው በሃገራችን በተለይም በገጠሩ ክፍል የወ ንዞችን ጉልበት የሚያግሩ ድልድዮች በብዛት የሉም። በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ ተጓጐችን በሥርዓት ለማሻገር ድልድይም

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመሥራት ሆነ ጥበበኛ ዋነተኛን ለማሠልጠን በሚገባ አለ መታሰቡ ነው። እናውቃለን የሚሉ የሕዝብ ጥቅም አስከባሪ የሕዝብ ወገኖች በዚህ ተግባር ላይ በሚገባ አስበውበት አያው ቁም። ለማዘጋጀትም ያሰቡ ቢኖሩ፣ በሚሠራው የድልድይ ዓይነትና ያሻጋሪ ዋነተኛ ምንነት ላይ በሐሳብ ተስማምተው አያ ውቁም። ካንጀታቸው ያላሰቡበት በመሆኑ፣ የሚሠሩት ድል ድይ ተሽላልና ተልካሻ እየሆነ ዋነተኛቸውን አምቡጋርነት ስለ ሚያጠቃው ለመሻገር የመጡትን ብዙ ወገኖች ህይወት በከንቱ አስበልተዋል። አጅሬ ጐርፍ ግን ወቅቱን እየጠበቀ መምጣቱን አላቋረጠም። ድልድዮችን በማነጽ ረገድ አንዱ ባለዋህድ ዓምድ ይሁን ሲል ሌላው ደግሞ ባለመንታ ዋልቶች ያዋጣል ይላል። ያም ተባለ ይኽ እስካለንበት ዘመን ድረስ፣ በተለይም በገጠሩ አገራችን ውስጥ ወንዞች ሁሉ፣ እንበለ ድልድይ በመሆናቸው እየፈለሉ ተሻጋሪውን ሁሉ እንደዋጡ ይገኛሉ። ለተሻጋሪ ወገ ኖችም ምንም የበጀ ነገር አልተገኘም።

አንዳንዴም፣ መንደርና አምባ ያፈራው፣ ራሱን በራሱ፣ አሻጋሪ ዋነተኛ አድርጐ የሠየመ ጎረምሣ፣ እንዳሻው ሲምቦ ራጨቅ ይታያል።

እነዚህም ሙሽሮች ያጋጠማቸው አሻጋሪ ዋነተኛ ይኽው ዓይነት ነው። አካላዊ ሞያው እንኳ ከሞላ ጐደል ባላነሰው ነበር። የማሻገር ሙያ ግን አላካዊ ቅልጥፍና ብቻ አይደለም። ጎሊናንም ይጠይቃል፣ ሞራልም ይመለከታል። ምንም እንኳ ዋነተኛው በተገኘበት ያስተዳደግ አከባቢ ያን ያህል የማይጠበቅ ቢሆንም፣ ሰውን ያህል ክቡር ፍጡር ከበላተኛ ማዕበል አሻግሮ በማዳን፣ ከሚፈልገው ግቡ ለማድረስ፣ ካሻጋሪው ብዙ ነገር ይጠበቃል። ድርጊት ብቻውን አየር የወጠረው ስልቻ መሆን ነው። ትምህርት፣ ችሎታ፣ ከዛ በላይ ደግሞ ሞራል እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። በተለይም ተሻጋሪዎቹ ወገኖች በሰላም

እንዲያሻግራቸው ሙሉ እምነት የሚጥሉበት ስለሆነ፣ የተለየ ጥንቃቄና ጥበብ እንዲኖረው ግዴታ ነው። በተለይም በዛ ሕይወት አድን ተግባር ላይ የሚሰማራ ዋነተኛ፣ ከቅብጠትና ከእብሪት ከብልግናና ከግብዝነት ባጠቃላይም ከማን አለብኝ ባይነት አደገኛ ዝንባሌዎች ነፃ የሆነ ሰው መሆን አለበት። ያን ሁኔታ በመጠቀም፣ የራስን ግላዊ ስሜት ብቻ ከማርካት መቆጠብም ተገቢ ነው። ከሆነማ ከነጠላ አሻጋሪ ዋነተኛ ይልቅ፣ ማኅበረ-ሰቡ ተሰባብሶ የሚሠራው ድልድይ ወሳኝነት አለው። ለዘለቄታም አገልጋይ ሆኖ በየወቅቱ ተሚነርፈውን ማዕበል ሁሉ በቀጥጥሩ ስር ሊያውል የሚችለው በብዙኃን አስተዋፅኦ ተዋቅሮ የሚሠራው ድልድይ ነው። ያም ድልድይ እስካለ ድረስ አንዳን ነጠላ ሞራሊቢስ ዋነተኞች " እናሻግራችሁ " ብለው ከማጭበርበር ይታቀቡም ነበር። የተባለው ድልድይም ታንጾ ግልጋሎት መስጠት እስካልቻለ ድረስ እነዛ ሙሽሮች ያበሳጫቸው ዓይነት ኩታራ ዋነተኛ፣ ወንዞች በሞሉ ቁጥር ብቅ እያለ ፣ ማበሳጨቱን ምንጊዜም አይተውም.....

በዚህች አጭር ልቦለድ ታሪክ ውስጥ አንባቢያን ሊያተኩሩበት የሚገባቸው የመደምደምያ ነጥብ አለ። ይኸውም ከባለ ጌው አሻጋሪ ዋነተኛ ቅጽበታዊ ርካታ በኋላ፣ በፍራቻና በመር በርበድ፣ ሙሺሪትን ከማዶ ላይ ጥሏት ሲሄድ፣ ጅምሩ ታሪክ እንዲያበቃ የተደረገበት ጭብጣዊ መዋቅር ጉዳይ ነው። እንዲያውም ማለቢያው ቃል " ውሻማ " ቃል እንዲሆን የተደረገበት ምክንያት ሁሉ አለ። እኔ ብጥልጥሉን እያወጣሁ ከምተነትነው ይልቅ፣ ለምን አንባቢዬ ራስም በግል አመለካከትም እንዲያጣጥሙት አላደርግም? ምናባቴስ ቆርጦኝ ነው፣ እንደ ፈለጉ የማየት ነጻነትዎንስ የምደፍረው!! ስለዚህ ከማሰብ ነፃነትም ጋር ታሪኪቱ ይቻትልዎ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሽግግር ደባ!

ወቅቱ ወርሃ ክረምት ነው። ሁለት ሙሽሮች ከወንዝ ዳር ተቃቅፈው ቆመዋል። ሠርጋቸው የተፈፀመው ከጥቂት ወራት በፊት፣ በፋሲካው ሰሞን ነበር። የሙሽርነታቸው እንቡጥ አበባ ገና አልጠወለገም። በአፍላ ነዲድ ፍቅራቸው ላይ ነበሩ።

" አይራራ " የሚባለው ወንዝ ከአንኮበር ገመገም ሥር የሚፍለቀለቅ ታላቅ ዥማ ነው። ይህን መሳይ አስፈሪ ስሙን ያገኘው፣ ከዘመናት በፊት በፈጸመው ግፍ ምክንያት ነው። እናት አንድ ልጇን አዝላ ስትሻገር፣ ልጁን ብቻ አስቀርቶ እናትን ነጥሎ በመውሰዱ ነው። " አይራራ " የስን ክሳርን አጠቃላይ ገጾች ሊያስለቅቅ የሚችል ሰፊ የበደል ታሪክ አለው። ልሻገርህ የሚለውን ደካማ ሁሉ ያለምሕረት ሲበላ ኖሯል።

የጫጉላ ወቅታቸውን ያላገባደዱት እሊያ አዲስ ሙሽሮች፣ ከሙሽሪት አጐቶች ባንደኛው ቤት፣ የመልስ ድግስ ላይ ውለው አድረው ወደ ሠፈራቸው በመመለስ ላይ ነበሩ። ሠፈራቸው ለመድረስ " አይራራን" መሻገር ነበረባቸው። ከድግሱ ያጐት ቤት የስድስት ሰዓት ያህል ጉዳና ተጉዘዋል። " አይራራን " ተሻግረው፣ ከሠፈራቸው ለመድረስ ያን ያህል ጊዜ ይቀራቸዋል። አጅሬ " አይራራ " ጉሽ ጠላ የመሰለ ዝናቡን ጠጥቶ፣ ጥምብዝ ብሎ ሰክሮ ባየር ላይ ይጨፍራል። አለወትሮው እስከአፍጢሙ ሞልቶ ድንበሩን ሰቶ በመውጣት፣

የራሱን ጎዳጎች ያስሳል። ከደጋው ላይ ጀምሮ እያጋበሰ ሲውጥ ያመጣውንም ደለል በየዳርቻው ይተፋል። አዲሶቹ ሙሽሮች፣ ያቅማቸውን ያህል ዋና ቢችሉም፣ ያን " የአይ ራራ " ጎርፋማ ሙላት የሚሞክሩት አልነበረም። ያላቸው ምርጫ፣ ተግባራቸው ማሻገር የሆነ፣ በዋና የተካኑ ባለሙ ያዎችን ማግኘት ነበር። እንደዚህ ያሉ ባለሙያዎችም፣ ሥራዬ ብለው ከዠማው ዳርቻ አይታጡም ነበር። በዛ ወቅት ግን አንድም አልነበረም።

ሠርገኞቹ " ምን እናድርግ ?" እያሉ በየርከኑ ዳር ዳር ሲያመነቱ፣ አንድ ከባቴ ዶልዶም፣ ከደረቴ ገምደል፣ ያለ ጠብደል ጎረምሳ፣ ከዚህ መጣ ሳይባል ከወደኋላቸው ድንገት ከቸች ይላል። ጠይምነቱ ቆለኛነቱን ያሳጣበታል። ንዳድ ያጋ የው ጸጉሩና መልኩ ከጸሓይቱ መጐራበቱን ይመሰክራሉ። የሚናገረው ቃል ካንደበቱ ሲወጣ ይተናነቀዋል። ሲቅለሰለስ ደግሞ ትሕትና ያለው ገር ይመስላል። አካሔዱ ከምበል ደፋ ያለ ምታዊ ቅኝት አለው። አለባበሱ እንደነገሩ ነው።

" እንዴት ዋላችሁ! ድልድይ የምትቃኙ ይመስላል " አላቸው።

" ቢኾማ ማን አርጎት! በዚህ ድብልቅልቅ ውስጥ " አለ ሙሽራው፣ የጐረምሳው ጠብደልነት እየቀፈፈው። ሙሽራይቱ ግን የጐረምሳውን የሚገረምም አስተያየቱንና የፈ ረጠመ ሰውነቱን አልወደደችውምና፣ አረመመች። ጐረም ሳው ለተግባር የመጣ ነበርና " ስንት ትከፍላላችሁ? " ሲል ጠየቀ፣ የጀጠባቡን እጀታ እየጠቀለለና ተነፋነፍ ሱሪውን ወደ ላይ እየሰቀሰቀ። ሙሽሪት ቀደም ብላ " የደንቡን ነዋ! "

t.me/OLDBOOKSPDF

አለች። ጐረምሳውም ቀበል አድርጎ " ዛሬ ጅረቱ ተጋፊ ነውና እጥፍ መክፈል አለባችሁ! " አለ።

እንደ መከንከን የጀማመረው ሙሽራ " እጥፉ ስንት ይሆናል?" ሲል ጠየቀ፣ ወንዝወንዙን አሻግሮ እያየ። " ሁለት ሁለት አላድ በየራስ " አለው ጐረምሳው የሙሽሪትን እግሮች አሻግሮ እየመተረ። " ደግሞም ..... " አለ ጐረ ምሳው። " ሁለት ጊዚ ሳይሆን አራት ጊዜ መመላለስ እንዳለብኝ አትዘንጉ "

ይህን እንደተናገረ ሙሽራው ብርክ ያዘውና አቄዘመ። እጅግ ተጨንቆም ያሰላሰ ጀመር አቀርቅሮ። በሓሳቡም ውስጥ ያብሰከሰከው " እሷን አስቀድሞ ቢያሻግር፣ ማዶ ላይ ብቻዋን ያገኛታል። እኔን አስቀድሞ ቢያሻግር አድርሶኝ ሲመለስ፣ ብቻዋን ሊያገኛት ነው።..... " የሚለው ሓሳብ ነው። ጐረምሳውም አቅበጠበጠውና፣ " ቶሎ ወስኑ! አሊያ ዛሬ ' አይራራ' እያበጠና የባሰ እየገነፈለ ነው የሚመጣው! ከወዲያ ባሻገር የሚጥለውን ዝናም አታዩም? " አለና አሻግሮ ማዶውን በጣቱ እየጠቆመ አሳያቸው፣ የዝና ቡምን መምጣት። ጉዳዩ ያሰጋው ሙሽራ ግን፣ የመሸጋገሩን የተናጠል ሁኔታ እያወጣና እያወረደ " ወንድሜ አትቸኮል! የቸኮለ አፍስሶ ለቀመ ሲሉ አልሰማህም! " አለውና በጎሊና ተመስጠ " የሚበጀው ሁለታችንንም ባንዴ ማሻገሩ ይሆናል!" አለና ዋነተኛውን! ጠየቀው።

ጐረምሳውም ወዲያው " ይህ የማይሞከር ነው። እንኳን ዛሬ 'አይራራ' ከመጠን በላይ ሞልቶ ሲጨፍር ይቅ ርና በሌላውም ጊዜ ቢሆን የሚቻል አይደለም" ሲል መለሰ።

" እንግዲያውስ " አለና ሙሽራው የሚያዋጣውን የሽግግር መላ ያሰላ ገባ። " የሚበጀው እሷን አስቀድሞ ቢያ ሻግር ይሆናል። ምክንያቱም የሱ ቤትና የሚከፈለውም ገን ዘብ፣ ከወዲህኛው ማዶ ስለሚቀር፣ ለሁለቱ ጥቅሞቹ ሲል እሷን አሻግሮ ካደረሳት በኋላ ፈጥኖ መመለሱ አይቀርም " በሚለው ሐሳብ ወሰነ። ይህን አስቸጋሪ ውሳኔ ለማድረግ በሓሳብ ተውጦ በሚያውጠነጥንበት ወቅት፣ ፈንጠር ብሎ ቆሞ የነበረው ዋነተኛ ጐረምሳ፣ ሙሽሪትን ደህና አድርጎ በጠበደል ዓይኖቹ እያገላበጠ መተራት። የሱ አለመሆኗ ቆጨው።

ውበቷ " መች ተሻግራልኝ!" እያሰኘ አስቷመጠው። በሩቁ የሚፈነጠቀው ደም ግባቷ አቀኑጠነጠው። በርግጥም ሙሽሪት ውብ ነበረች። ሙሽሪት ሐማራዊ ገርዳሳ በተጐነ ጐነው ሐርማ ፀጉሯ ዳርዳር ላይ፣ ሸብ አርጋለች። በጥልፍ ተሸለምልሞ የቀበጠው ቀሚሷ፣ ያቡነ ሰማላን መስቀል ከደ ረቷ በስተርግርጌ ላይ አስፍኗል። በአልቦ ምትክ በእግሮቿ ላይ የተንቀሰችው ጠልሰም፣ የተመልካቹን ጎሊና ይማታል። የበስተጀርባዋ መለያልይ ቅርፂ፣ ስሜት አልባውን ሳይቀር ይነ ዝራል። ከአንገቷ በስተግርጌ ያንቀላፋው የብር መስቀሏ፣ ክር ስቶስን ሳይሆን ፍቅረኛን የቸነከረ ይመስላል። ከድግስ ቤት መመለሷ ቢሆንም፣ መቀነቷን ያገለደመችበት ሆዷ፣ እህል የገ ባበትም አይመስልም። የወገቧ ቅጥነት ችቦ አይሞላም። ከመ ከዳው ደረቷ ላይ እንደፈርጥ ጉብጉብ ያሉት ዕቶን መሳይ ጡቶቿ፣ ልጇን ባረገኘ ያሰኛሉ። እንደ ቀዘባ ዘንባባ ዘንጠፍ ያለው ዳሌዋ፣ ዐይንማዝ ደዌ ያለበት ሁሉ፣ ገና በሩቁ ሲያ

የው ይፈውሳል!! ስለ ገፅታ ብለው፣ ዋ ላይህ፣ ስለ ዐይኖቿ፣ ስለአፍንጫዋ..... መናገር፣ ቋንቋ ማበላሸት ይሆናል። ..... ዝም ነው። የቃላት አፅናፍም እንኳ አይሸፍነውምና ነው!!

ያ አዲስ ሙሽራ ባሏ፣ አቆዝሞ ሲያሰላስል ከቆየ በኋላ " አጐትሽ ቤት እንደገና ተመልሰን፣ 'አይራራ' ሲጐ ድል ነገ ብንመለስ ይሻላል.." ሲል ሚስቱን አማከረ። " ረሳ ኸው እንዴ! ለምን ቸኩለን መጣንና ነው! ያቺ አክስቴ ደግሳ ብንቀርባት ትቃጠላለች! ሰዎች አታደርገንም! ማታ መገኘት እንዳለብን አስጠንቅቃናለች አይደል? " አለች አበክራ!!

" እሱስ እውነትሽን ነው! ለቤተ ማያው ድግስ የሚ መጡ እንግዶችና ቤተ-ዘመድ ሁሉ፣ ባንደርሳላቸው ሊያስቡና ሊደነግጡ ይችላሉ። ደግሞም በጉን የምታርደው አንተ ነህ ብላለችና አክስትሽ፣ መቅረትስ የለብንም....." አለ እያቅማማ።

ጐረምሣው ዋነተኛ፣ ንግግራቸውን ሲሰማ ቆይቶ እየ ተቆናጠረ፣ " የምታመኑቱ ከሆነ፣ እኔ ሌላጋ እሔዳለሁ። በየ አርከኑ ሁሉ አሻጋሪ ዋነተኛ የሚፈልግ ሰው ሞልቷል!! ዕድሜ ' ላይራራ' ! እንጅ፣ ጠሜን እንደሁ አላድርም! " በማለት ተናገረ።

" በቃ ወስነናል። አራቱን አላድ መጨረሻ ላይ እንከፍልሃለን! በል፣ ባለቤቴን መጀመሪያ አሻግራት " አለ ስለዋነተኛው ባሕሪ እየተጠራጠረና..... ሲፈራ ሲቸር። ከላይ የሚለበሰውን ዋናውን ልብስ በማንጠልጠያ በትሩ ላይ አደረገችና፣ ያቺን ጠምበለል መሳይ ልጅ፣ ክባሏ ነጥሎ ይዟት ወደ " አይራራ " ዥረት ገባ። ገና ከዳርቻው ላይ


t.me/OLDBOOKSPDF

" አይዞሽ አትፍሪ! " ብሎ እየዳሰሰ ሲይዛት ሁኔታውን ማየቱ ባሏ አስጠልቶት ዐይኖቹን ጨፈነ። ዋነተኛው ጉሪምሣ ሆዱ ግን፣ በግላጭ ያገኘውን የትኩስ ሙሽሪት ሚዛይ ይዞና በቀኑ ጥጥሩ ስርም ያዋለውን ውብ ገላዋን እየዳሰሰ፣ ' ያይራራን ' ጉርፍ ሠነጠቀው። በተቀዳሚም ያሻሸ የገባው እነዚያን የተ መኛቸውን የደደሩ አጉጠጉጤ ጡቶቿን ነበር። ከሸሪቱ ዳርቻ እስኪደርስም ድረስ፣ ጠቅላላ አካሏን ሲዳስስ ምኗም ምኗም አልቀረው። ከዳርቻው እርከን እስኪደርስም ድረስ እጅግ ተንሰፈሰፈ። በሞቀው ውሃ ውስጥ፣ የጋለው ሰውነቷ ሙቀቱ ስለገላመጠው፣ በፍትወት ጣመነ። ከወዲያኛው ማዶ በልዩ ፍጥነቱ አንጠልጥሏት እንደደረሰ፣ በውሃ ከራሰው ቀሚሷ ውስጥ ደብቃ ካጐቷ ድግስ ይዛ ያመጣችውን ድፎ ዳቦ፣ ይቦጠቡጠው ገባ።.....

ጊዜው የቀትር በስቲያ በመሆኑ፣ ማዶ ለማዶ ያለ፣ ሁሉ ነገር ወለል ብሎ ይታያል። ባል ሆዱ፣ ከወዲያኛው ማዶ ብቻውን ሆኖ፣ ጉሮሮው ሊያወጣው የሚችለውን ድምፅ ያህል፣ በማውገዝ ጮኸ! ኮነነ! ረገመ! ሊሻገርም ከጅሎት፣ ' አይራራ ' ጉልብቶበት፣ ባቱን እያጠፈ የሚያስተናግደው ሆነ። ከነበረበት ማዶ አንዲት ዲብ ላይ ተቀምጦ፣ እንደ ሕፃን ልጅ እዬዬውን ያቀልጥ ጀመር። ሰውነቱን፣ የማዶው ድርጊት ትይታ ወረረው። ያሚያየው ሁሉ ቅዥት መሰለው። ዋነተኛው ጉሪምሣ፣ የዳቦውን እንቡጥ እንቡጥ ከኰመኰመ በኋላ፣ እንደመጥገብና እንደመርካት ሲሞክረው፣ ያን ባሏን እየጮኸ ጠራውና " ስማ! ገንዘብህን አልፈልግም! ድግሱ ቤት ከበላኸው ዳቦ ትራፊ አግኝቼ፣ እስክጠግብ ከስክሻለሁ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ባለቤትህን ያሻገርኩበት ዋጋም ሆኖልኛል፣ ደህና ክረም !...." አለና፣ የመሠናበቻ ምልክት አሳይቶት፣ ሙሽራዋን ከነልቅሶዋ ጥሎለት፣ ወደ እሚሔድበት እየዘፈነ ነጐደ። ሁለቱም ሙሽ ሮች በያሉበት ማዶ ላይ ሆነው፣ ሲያለቅሱ ከቆዩ በኋላ፣ ቀኑ እየመሸ በሔደ መጠን፣ " አይራራም " ይጐድል ጀመር። ብዙም አልቆየ፣ " አይራራ ሙላትህ ይበቃሃል " ያሉት ይመ ስል፣ ማምሻው ላይ ባፋጣኝ ጐደለ። ወዲያው ማዶ ላይ የነበረው ባሏ፣ ከነእልሁ ዘሎ ወንዙ ውስጥ ገባና፣ በንዴት ፈረሱ ውሃውን እየጋለበ፣ ተጨብጣ ከምታለቅስ ሚስቱ ዘንድ ደረሰ። " ያሁኑ ይባስ! " እንዲሉ፣ እንደደረሰ፣ በያዘው ቆመጡ፣ እያገላበጠ ይጠልዛት ጀመር። ሚስቱም " ምን ላድርግ? አቅም የለኝም! እሱ መረመንድ ግንድ ያህላል! እን ዴት ችየ ራሴን ልከላከል ብለህ ነው? " ብላ በልቅሶዋና በዱ ላው ጣልቃ ነገረችው። ባልዬውም " እሱስ ውነትሽን ነው። እኔንስ ይበልጥ ያናደደኝና ያበሸቀኝ " ስታሸረግጂለት " ማየቴ ነው!" አላት።



አንዳንድ ጮሌ ሰጋሥ፣ላሻግርም ቢል፣ራሱን ብቻ አሻገረ እንጅ፣ ሌሎችን አላሻገረም!


አዋልደ ወንዴ



ያመጣሽው ጠርሙስ፣ አረቄ ነው ብለሽ፣
አዶክሎኝ ሆነ፣ትምክሕተ ምን ነካሽ?

(የጠፍ. ✱.3)

t.me/OLDBOOKSPDF



“ከሁሉም ከሁሉም ፤ ካየሁት በደሌ ፤
እንደ ሬት መራራው ፤ ለኔና ለባሌ ፤
ከውርሱም በኋላ ፤ ብድሩን መክፈሌ!”

(ትምክሕተ)

t.me/OLDBOOKSPDF

መንደርደርያ

አንድ ጎብረተ ሰብ ባሳሰበውና ባልጠበቀው ዓይነት ፤ ከአንድ መራራ የፖለቲካ ፤ የኢኮኖሚና ፤ የሶሻል ቀውስና ክስ ረት ውስጥ ድንገት በተዘፈቀ ጊዜ ፤ በግለሰቦችም ሆነ በማኅበረ ሰቡ ላይ ብዙ አሳዛኝና አስቀያሚ ድርጊቶች ይፈጸማሉ ። በመ ንታ ትውልዶች ያስተሰሰብ ግጭት አንጻር ፤ ወላጅን ከተወ ላጅ ፤ ወንድምን ከወንድም ፤ ወንድን ከሴት ፤ ከተሜን ከገ ጠሬ ፤ በአእምሮ አዳሪውን ከጉልበት አዳሪው ፤ ..... ያጋ ጫል ፤ ያናቁራል ፤ ያናችፋል ። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ፤ አንድ ዓይነት ማኅበረ ሰብ ፤ በአባር የለውጥ ሕግ ተገድዶ ፤ ወደ አዲስ ማኅበረ-ሰብነት ሲለወጥ የሚያጋጥም ፤ የሰው ልጆች በሚኖሩበት አካባቢ ሁሉ ፤ ሲመጣ ሲሔድ ፤ ሲወጣ ሲገባ ፤ ሲያረጅ ሲተካ ፤ ሲዘቅጥ ሲለወጥ ፤ በየዘመኑና በየወቅቱ የሚ ከናወን ቀዋሚ ክስተት ነው ።

የለውጡን ሁኔታና ኪደት ፤ ይዘትና ቅርፅ ፤ የሚወ ስኑት ምክንያቶች ፤ አካባቢና ዘመን ፤ የማኅበረሰቡ የንቃት ደረ ጃና ያደረጃጀት መዋቅር ፤ የትዝምድ-ምርትና አምጻኤ -ምርት ፤.... ዓይነተኞቹ ሲሆኑ ፤ ያለፈው ትውልድ ያስተሳሰብ ቅርስና ይጠቀምበት የነበረው የታዳጊ ሕፃናት ያስተዳደግ ሥርዓት በየበኩላቸው ለሚፈጠረው ለውጥ አስተዋፅኦ አላቸው ። ያን ዘመን-ማዕዶት (የሽግግር ዘመን) በሚገባ ለማስ ተናገድ ያልተዘጋጀ ሕዝብ ፤ አቤት የሚደርስበት ፍዳ!

በዚች ቍንጽል ታሪክ ውስጥ ይህ እውነታ ከድሕረ የካቲት ወዲህ በሰፊው ማኅበረ-ሰብ ውስጥ ቀርቶ ፤ በትንሽዋ አንድ ቤተ-ሰብ ውስጥ እንኳ ፤ እንዴት እንደተንጸባረቀ ያሳ

ያል። የወንድማማቾቼና የወላጆቻቸው ታሪክ የነበረና ያለ እውነታም እንኳ ቢሆንም፣ ጭብጣዊ የታሪኩ ይዘት በሕይወት ያሉ ሕያዋንን ጭምር በተምሳሌት ከመጠቀሙ በስተቀር፣ ማንንም አይመለከትም። በሥነ-ጽሑፍ ታሪካዊ ኪደት ውስጥ፣ ብዙ ጊዜ ተዘውትሮ እንደታየው፣ አንዱ ደራሲ ካም ታትካ ተቀምጦ የጻፈው ድርሰት፣ ከነሙሉ ባሕርያቱ ጋር ሌላ ደራሲ አላስካ ተቀምጦ ከጻፈው ታሪካዊ ይዘት ጋር ያለ ነገር አባትና ያለ ጥሎሽ፣ ያለ አማጭና ረማጭ ተጋብቶ ይገኛል። ፈረንጆቼ ይህን መሰል አጋጣሚ " ኮኢንሲደንስ " ይሉታል። " ተአምራዊ ጥምረት ወይም ሳይገናኙና ሳይተያዩ ተመሳስሎ በመስተጻምርነት መዋሐድ " እንደማለት ነው። እንደዚህም ሁሉ በዚህ ቍንጽል ድርሳን ውስጥ ሰፍረው የሚገኙ ባሕርያት በሙሉ የኮኢንሲደንስ አጋጣሚ ካልሆነ በስ ተቀር፣ " እኔን ይሆናል " የሚለውን ባይ ሁሉ በጭራሽ አይ መለከትም። የኢትዮጵያ ድሕረ-የካቲት ኰድኩዶ ካስወለደው የቀውስ ዱብ ዕዳዎች ውስጥ አንዱ ከሥተት እንደሆነ ግን ሁላችንም እንደምንገነዘበው አምናለሁ። ያንድ ቤተሰብ ልጆች የርስ በርስ መከሰከስ፣ የወላጆቻቸውን ጤንነት እንዳቃወሰው፣ በዚህች አጭር ታሪክ አማካይነት ለማሳየት መሞከሬ፣ የደረሰብን ቀውስና ከስረት ምን ያህል የሚጐመዝዝ መራራ ሠፍነግ መሆኑን እንደሚያስረዳልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚህ አስተሳሰብ ክልል ውጭ ግን የሚሠነዘር ሌላ ትርጉም ቢኖር፣ ትርጕማኑን እንጅ እኔን አይመለከትም።

t.me/OLDBOOKSPDF

" አዋልደ—ወንዴ "

" .... መከረኛ፣ እናት፣ መንታ ልጆች ወልዳ፣
አንዱ፣ ሳት፣ ሌላው ማይ፣ ፅሩራን ዱብ ዕዳ፣
ወግ ደርሷት፣ ሳትጦር፣ ባልሠራችው ፍዳ፣
ሳትኖር፣ ልትሞት፣ ነው፣ ሕይወት ሆኗት፣ ባዳ....."

.....ያለችበት ማኅበረ ሰብ ያወጣለት ሥያሜ " እናት " ነው። እንስፍስፏ እናት-እምዬ። ስምነቱ የወል ስም ይሁን እንጅ፣ የትኛዋም እናት እንደ ግል የተፀውኦ ስሟ ታየዋለች። ስምነቱ፣ የመጀመሪያዋ ሴት በወላጅነት እስከታወቀችበት ወቅት ነበረ፣ አለ፣ ይኖራልም። በዘመናት መካከል ሲንፏፏ የሚኖረውን የትውልድ ዝማ ያስገኘችና የምታስገኛ ምንጭ በመሆኗ፣ በየትኛውም ሕዝብ፣ በማናቸውም ሀገር እንደ ተከበረች ትኖራለች። ለፈፀመችው የተፈጥሮ ሙያዋ፣ ይህ የክብር ስጦታ ቢያንሳት እንጅ አይበዛባትም። ስለዚህም ውለታዋ በሕይወቷ እስ ካለች ድረስ በሰላም፣ በደስታ፣ በምቾት፣ ለመኖር፣ ከሌላው እንኳ ቢቀር፣ የማህፀኗ ፍሬዎች ከሆኑት ልጆቿ የምትጠብቀው ተራ ወሮታ ነው።

በምንኖርበት ሥርዓት ባሕርይ ድክመት የተነሳ ብዙ ዎች ነገሮች እንደሚጠበቁት ሆነው አይገኙም። በዚህ ላይ ደግሞ የጥቂቶች ሰዎች የግብዝነት ጠባይ ሲበረዝበት፣ የባሰውን መራራ ሁኔታዎችን ያሳያሉ። በዘመናችን እንዲህ ያሉ ጐምዛዛ ድርጊቶች፣ ከመቸውም ጊዜ ይልቅ ጐልተው ይገኛሉ።

እንደሚታመንበት ሁሉ፣ ሕገ-ተፈጥሮ የራሱ መመሪ

ያምች አሉት። በዚህም መሠረት ፀሐያችን ሙቀቷንና ፀዳሏን ከመስጠት አልተቈጠበችም። በዚህም ዕለታት ይነጋሉ፣ ይመሻሉ። ዕፀዋት ያብባሉ፣ ያፈራሉ። ክረምትና በጋ ይፈራረቃሉ። ነፋሳት በዘፈቀደ አይነፍሱም። የመንገደ ምዕራብ ስምሪቱ፣ የራሱ ሕገ-አመንክዮ አለው። የስግረቱ መፍጠንና መዘግየት፣ የራሱ የሆነ መርሐ አለው። ግያት ይፈሳሉ። ካል ተገደዱ በስተቀር፣ ፍሰታቸው የተዋረድ ቍልቁሊት ነው። ከዥረት በላይ የሚጠጣን ዥብ፣ ከበታቹ የምትጠጣውን አህያ አደፈረሽብኝ ማለት አያስችልም።... ዓለም ከነተፈጥሮዎቿ በጤነኛ ኪደት ላይ ትገኛለች። የሚያንገዳግዷት እንከኖቿ ግን ጥቂት አይደሉም። አመንጭዎችም ኢሰዎች ናቸው!!

ከሚኖሩባት ደመ ነፍስ ፍጡራን ሁሉ፣ ሰው የተባለው፣ ዓለምን እንደነጀሳት አለ። የሚበላውን ከሚኰሳባትና የሚጠጣውን ከሚሸናባት አልፎ፣ በሠራው መርዙ እየመረዛት ነው። የተነሰነሰባት፣ መርዝም፣ ሲጠዘጥዛትና ሲመዘምዛት ቆይቷል። የሰዎች ዓለምን መድፈርና ማስቸገር፣ ከራሳቸው የእርስ በርስ ግጭት የተፈጠረ ነው። ፍልስፍናቸው እርስ በርስ ይፋጫል። አንዱ ክፍል፣ የሰዎች መሠረት፣ " ግለ-ሰብ! " ነው ብሎ ሲያስተምር ሌላው ደግሞ "ቤተ-ሰብ " ነው እያለ ያስተምራል። የቀረው ክፍል ደግሞ፣ ጠቅላላው " ኅብረተ-ሰብ " ነው ብሎ ይሠብካል። በዚህ በተሣከረ አስተሳሰብ ውስጥ ጮሊዎች ይጠቀማሉ፣ የዋህን ይጐዳሉ። የመንታ ፅንፍ አባሎች በተቆራቆሱ መጠን፣ ዳፋቸውና ጦሳቸው ሌላውን ገር ክፍል እንደረበሸ ነው። ፅንፋውያን ግን፣ ምንጊዜም " ፕሪንስፓል ያድናል፣ ፕሪንስፓል ይገላል " ይላሉ። የነሱ ዓላማ ግብ እስኪመታ ድረስ፣ ዓለም የሆነች

t.me/OLDBOOKSPDF

ውን ብትሆን፣ ደንታ የላቸውም። የነሱ ምኞት ይፈፀም እንጅ፣ አረጋውያን ወላጆቻቸው፣ የዋሁ ሕዝባቸው፣ ጤዛ ቢልስ፣ አፈር ቢምስ፣ ደንታቸው አይደለም። የነሱ የራሳቸው ሐሳብ ብቻ የነጠረ፣ የጠራ፣ ይመስላቸዋል። የሌላውን፣ በፈለገው ዐይነት በቂ አሳማኝ ማሳረጃ ቢቀርብም፣ ይሞታሉ እንጂ አይቀበሉም። ይህ ግትርነታቸው፣ የገመዱት ይመስል፣ እየከረረ ይወጠራል። ጦዞ በሚወጠርበት፣ ደረጃ ሲደርስ፣ ዐይነ ኅሊናቸው ጨርሶ ይታወራል። በዚያን ወቅት የሚሠሩት ሁሉ አይታወቃቸውም። የሚፈስ የሰው ደም፣ ተራ ውሃ ይመስላቸዋል።

ለእንደዚህ ያሉ ልጆች እናት የሆኑ፣ አንድ እመቤት አዲስ አበባ ይኖራሉ። ስማቸው ወይዘሮ ትምክሕተ ይባላል። ተጀምሮ እስኪጨረስ ያዲስ አበባ ነዋሪ ናቸው። ወይዘሮ ትምክሕተ በኖሩበት ማኅበረ-ሰብ ሥርዓት መሠረት እኩያ ቸውን በቁርባን ተድረው ረዥም ጊዜ ኖረዋል። በሕገ-ተፈጥሮ፣ ሥርዓትም፣ ልጆች፣ ወልደው፣ አሳድገዋል። ባለቤታቸው ባላምባራስ ወንዴ ይባላሉ። በዕድሜ ከወይዘሮ ትምክሕተ ጋር ብዙ አይበላለጡም። ንብረታቸው የደራ፣ ትዳራቸው የሞቀ ነበር። በዚያ የረጅም ዘመን የትዳር ዘመናቸው፣ አንድ ጊዜ ብቻ መንታ ወንዶች ወልደው ነበር። ይህም የሆነው የጣልያን ወረራ ካከተመ በኋላ ነው። በስስት፣ በስተኋላ የተገኙ ልጆች ነበሩ። " ወንዴ ወንድ ወለደ " የሚል ዘፈን አስፈልስፈው፣ ወራት አዘፍነዋል።

እሊህ መንታ ልጆቻቸው፣ ለወይዘሮ ትምክሕተና ባላምባራስ ወንዴ የሕይወታቸውን ያህል የሚያስቡላቸው፣ ምትክ የማይገኝላቸው፣ ቅርሳቸው ነበሩ። ያከባቢያቸው ሥል

በየካምፓቸው መሽገው፤ “ ቆይ ባላርድህ! ” በመባባል ይፎ
ካከሩ ገቡ። ይህን ሁኔታ በስተኋላ ላይ የተረዱ ወላጆቻ
ቸው፤ መግቢያ ቀዳዳ፤ መሸሸጊያ ጓዳ፤ መሮጫ ሜዳ፤
ጠፋባቸው። የሚሆኑትን አጡ። የሚመገቡት እስኪያስመ
ልሳቸው ድረስ፤ የመንፈስ ሕመም ተጠናወታቸው። ደረቅ
ጭንቀት! የልጆቻቸው እንዲያ መሆን፤ “ በእንቅርት ላይ
ጀሮደግፍ ” እንዲሉ እንጅ፤ የስም ዐብየተኞች አላግባብ የዘ
ረፉቸው ንብረትና ያወረሳቸው ድህነት፤ ብቻውን፤ ለማናደድ
ይበቃ ነበር። ዘመድ አዝማድ እያጀበ ያሞቅ ያደምቀው
የነበረ፤ ያ ሙሉ ቤታቸው ተበትኖ ጭርታ ዋጠው። የቅጥር
ሠራተኞቻቸው ሣይቀሩ፤ ነፃ ጐጆ ፍለጋ ተሠማርተው አልተ
መለሱም። ያልተለዩአቸው ወዳጆች ቢኖሩ፤ ታማኞች መንታ
ድመቶቻቸው ነበሩ። በዚህ ሁኔታ ሲኖሩ ዐመታት አልፈ
ዋል። “ በማንም የደረሰ ነው ” እያሉ፤ ያሉበትን ሁኔታ አያ
ማርሩም።

በሩቅ ያሉ ልጆቻቸው፤ ከየተሠማሩበት ጐራ አልፈው
አልፈው ደብዳቤ ይጽፉላቸዋል። ባንዳንዱ ደብዳቤ ውስጥ
የሰፈረውን ሐሳብ ሲያነቡ፤ ልጆቻቸው እስከመጨረሻው ባይ
ጽፉላቸው ይመርጣሉ። እጅግ መራራ ነው።

ባላምበራስ አንድ ቀን በረንዳቸው ላይ ቁጭ ብለው
የማታ ፀሐይ ሲሞቁ፤ የድሮ የመንታ ልጆች ጓደኛ፤ ሁለት
ደብዳቤዎች አምጥቶ ይሰጣቸዋል። “ ቤት ግባ! ” የማለቱ
ልምድ ቀርቷልና “ ደብዳቤዎች ከመጡ ሰንብተዋል። በአ
ደራ በሰው እጅ ነው የተላኩት። ሥራ በዝቶብኝ ትንሽ ዘግ
ይተውብኛል!” ብሎ ነበር መልእክተኛው ለወንዴ ሰጥቷቸው
ከደጅ የተመለሰው። ባላምበራስም ደብዳቤዎቹን ይዘው፤ ባለ

ጣኔና ባሕል የፈቀደላቸውን ያህል፤ በሚገባ አሳድገዋቸዋል።
እጅግ ስለሚሳሱላቸው፤ አንዳንዴ በጣም ያሞላቅቋቸው ነበ
ር። በተለይም፤ የማቆላመጫ ስም ሰጥተው ከዋና ስማቸው
ይልቅ በዚሁ ስማቸው እንዲጠሩ አርገዋል። እንደ ውልደ
ታቸው ቅደም ተከተል “ መሩ ” እና “ መራ ” ይባሉ
ነበር። ትምህርት ቤት ውለው እስኪመጡ ድረስ ወላጆ
ቻቸው ልባቸው ተሰቅሎ ይውላል። ተጨንቀው ተጠበው
ነው ያሳደጓቸው። ጉንፋን እንኳ ሲይዛቸው፤ ከልጆቻቸው
ይልቅ ራሳቸው ይታመሙ ነበር። ይሳሱላቸው የነበሩ መንታ
ልጆቻቸውም ቢሆኑ በትምህርት አልሠነፉም ነበር። እንዴ
ውም፤ አይተኙበት ጀንዲ ሆነ እንጂ ዲግሪ እስከማግኘት ደር
ሰዋል። በዚህም ሙያቸው ተሸመውበታል፤ ተሸልመ ውበ
ታል።

“ ልጆቼ ” እያሉ ወላጅ ወይዘሮ ትምክሕተና ባላም
ባራስ ወንዴ ጥሩ ኑሮ በጀመሩበት የተደላደለ ሕይወት ውስ
ጥ፤ ያልጠበቁት ነገር ድንገት ፈነዳ። የየካቲት ሕዝባዊ ግፊት
ያመጣው ዱብ ዕዳ ነበር። አዳዲሶች ሁኔታዎች መጡ። አዳ
ዲሶች ሁኔታዎች ሔዱ። ነገሮች ተመሰቃቀሉ፤ ተሠበጣጠ
ሩም። መከሩን ከእንክርዳድ የሚለየው ሰፌድና ወንፊት ሳይ
ቀር፤ በቀጥቃጭ መራጃ ተተክቶ የማይደረገው ተደረገ። ንፁ
ሐን ያለፍዳቸው ወደቁ። ግለሰቡ በየምርጫው ወገነ። በዚ
ህም ድርጊት ላይ መንታዎቹም፤ መሩ እና መራ ነበሩበት።
የሚደንቀው፤ አሠላለፋቸው ጐራ ለይቶ፤ መሆኑ ነበር። ካር
ባ ዓመታት በላይ በፍቅር ተሣስረው የነበሩ መንቶች፤ የለየ
ላቸው ጠላቶች ሆኑ። አንዱ የማዕከላዊ መንግሥት ተጠሪ
ሹም ሲሆን፤ ሌላው፤ፀረ ማዕከላዊ መንሥት ሆኖ ተሠለፈ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤት ትምክሕተን እየጠሩ፤ “ የልጆችሽ ደብዳቤ መጥቷል! ቶሎ ነይ!” ብለው ማርጀት ወደጀማመረው አሮጌ ሳሎናቸው ያመራሉ። እዚያም እንደደረሱ፤ መንተብ ከሞካከረው ሶፋ ቸው ላይ ጋቢያቸውን አጣፍተው ቁጭ አሉና፤ አዘውትረው የሚያዜሟትን ባለ ልዩ ቅኝትና ቅላፄ እንጉርጉሮ፤ ይዘይሩ ገቡ። ዜማዋ፤ የማንም ልብ አኝካ የምትውጥ ነበረች።

“ የመንትዮች እናት፤ ልቧም ሆኖ መንታ፤
ልብረር ልብረር ይላል፤ ወዳሉበት ቦታ፤
አንዱ ወደ ስሜን፤ ሌላው ሰሜን ዋልታ፤
እንደፈረደበት፤ ሔዶ ሊንገላታ፤
ባልፈፀመው ወንጀል፤ በልጆች ትዝታ!

--- “ ይቺ የዋይታ ዜማህ፤ አትሰለችህ መቼም! ዛሬ ደግሞ ምን ጽፈውልን ይሆን ? ” እያሉ ከባላምባራስ በስተፊት ያለውን የሚዘምር የሳሎን በር ከፍተው፤ ትምክሕተ ይገ ባሉ። ወንዴ፤ ባለቤታቸውን እንዳዩ፤ ዋይታ የተበረዘበት ሣቃቸውን ይለቁታል።

--- “ ዛሬ ደግሞ ኩታውን ቀሚስ አርገሽዋል! ” አሉዋቸው።

በርግጥም፤ ወይዘሮ ትምክሕተ ኩታቸውን አሸር ጠው፤ ቀሚሳቸውን እንደኩታቸው አጣፍተው ለብሰው ታል። የልጆቻቸው ነገር ልባቸውን ሰልቦት፤ ብዙውን ድር ጊት ልዩ ማድረግ፤ የማይገባቸውን አዘውትረው ያደርጋሉ። ይህ ዐይነቱ ድርጊት በዚያ ቤት የተዘወተረ ድርጊት ሆኗል። የማይገባቸውን ሁል ጊዜ ያደርጋሉ። እንዲህ ያለው ነገር በነዚያ የነሁለቶች ቤት መደረጉ አያስደንቅም። በወዲያኛው ወር፤ አንድ የልጆቻቸው የድሮ ጓደኛ ደብዳቤ ይዞላቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

መጥቶ፤ አለወትሮአቸው ምላ ሊጋብዙት አስበው፤ ወይዘሮ ትምክሕተ “ ዛሬ ደግሞ ይህ ደብዳቤአቸው ምን ያሰማኝ ይሆን ?” እያለ በሚጨነት ልቦናቸውና ቀልባቸው እንዳሉ፤ ማእድ ቤት ገብተው ወጥ ሲሠሩ፤ ዘይት መስሎአቸው ጋዝ ጨምረው በማዘጋጀታቸው፤ እስከ ዛሬ ባላምበራስ፤ በባሌቤ ታቸው ትምክሕተ ላይ ጥሩ መቀለጃና መተረቻ አርገውት ቁይቷል። እንዲያውም እንደቅኔ እየሞከራቸው “እመ-ጋዝ” (የጋዝ እናት) የሚል መጠሪያ አውጥተውላቸዋል።

--- “ አንተዬ! እኔ አያስችለኝ! አንተ ትቀልዳለህ! ያንተን ልብ ምናለበት ነበር የኔ ልብ ቢያረገው ኖሮ! በርግጥ የምት ሆነውን እና የምትሠራውን አይ ነበር! ” አሉ ወይዘሮ ትም ክሕተ፤ ያገለደሙትን ኩታ ቀይረው ቀሚሳቸውን እያጠለቁ።

---“ አሁን እሱ ያለው ላይቀር፤ ያላለውም ላይሆን፤ ምን በወጣኝ ነው የምጨነቀው! ቀድሞውንም መንቶች አርጎ ሰጠ! በመንታ አቅጣጫ በታትኖ አሠማራቸው! እርስ በርስ ተፃራርያን! አንዱ ሌላውን ሊያጠፋው እንደሮጠ አለ! ታዲ ያንን የኔ የወንዴ ዓቅም ይህን ውትብትብ ሁኔታ እንዴት ሊፈታውና ሊለውጠው ይችላል ብለሽ ታምኚያለሽ ? ከሆነስ ለምንድነው እንዳንቺ እንድጨነቅ የምትጋብዥኝ! መፍትሔ ቢስ የሆነ ራስ አድርቅ ባዶ ጭንቀት! ” አሉ የተለመደ የዋ ይታ ለበስ ሳቃቸውን ገርገብ ባለ አፋቸው እየለቀቁት።

--- “ የፈሪዎችና የአምቡጋሮች ቁንቁ ብዙና አወዛ ጋቢም ነው! ” አሉ ትምክህተ ብው ብለው እንደ መተቸት።

---“ ይሽማ ለመላው ወንዶች ተብሎላቸው የለ! በተለይ ያዲስ አበባውማ ወንድ “ ነገ ጃን ሜዳ እንዲገኝ፤ አርባ ጅራፍ ትገረፋለህ! ተብሎ ቢታወጅበት፤ ገና ማለዳ ወፍ

ሳይንጫጫ ተነስቶ፣ ለግርፊያው ልብሱን ማውለቅ የሚጀ
ምረው፣ እዚያ ታች ራስ መኰንን ድልድይ ላይ ነው ”
ተብሎ ተተርቶበት የለ! እንደ አባ ገብረሃና ያለ - “ የእንዝ
ልዝል ” - ቀልድ ዓይነት።


---“ አንተዬ! እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅህ ቀልዱን
ተውና! አሁን ያ መሩ አላግባብ ስለ ተፈረደብን የቤት መው
ረስ ጉዳይ ቢሰማ ኖሮ፣ እዚያው አለበት የዱር አምባው
ውስጥ ጧ ብሎ ተቃጥሎ አይሞትም ትላለህ! ” በንዴት
ስሜት በጃቸው ያጨበጭባሉ።

--- “ ያርር እንጂ ትምክሕትዬ! እስቲ ፍትህ መጣ፣
ነፃነት ተገኘ በሚባልበት ዘመን፣ እንዴት ሁለቱንም ክሶች
ባንዴ እናጣለን?” አሉ ባላምበራስ፣ ባለፈው ሰሞን የተረቱ
በትን ክስ እያስታወሱ።

--- “ አንተዬ! እኔንሰ በጣም የገረመኝ የባንኩንም
ብድር እንድንከፍል ሲወስኑብን ነው። እንዴት ያነዳል! ቤቱ
ተወርሷል። እንዲያውም የሚኖርበት ካዲ ይበሉ ካድሪ
ነው። (ስሙ አይያዝ ልኝም) በነፃ ነው የተሰጠው አሉ። ቤቱ
ከተወረሰ የሚጠቀምበት ወራሹ የባንኩን ዕዳ ከነወለዱ መክ
ፈል ሲገባው፣ እኛ እንዴት ለማንጠቀምበት ቤት እንከፍ
ላለን ? ይህንን ጉድ ያ መሩ ቢሰማ፣ አራስ ነብር ነበር የሚሆ
ነው! በእርግጥ አያስችለውም! ” አሉ ትምክሕተ፣ ኮልል
እያለ የሚወርደውን እንባቸውን ከፊታቸው ላይ በመዳ
ፋቸው እየጠረጉ።

--- “ አንችንስ ያንገበገበሽ የባንኩን ብድር መክፈል
ጉዳይ ነው። እኔን ግን እየቁጠቁጠ የሚያቃጥለኝና ጤናም
የነሳኝ፣ በምኑም በምኑም ከኛ የማይሻል፣ አንድ ጋጠወጥ “

t.me/OLDBOOKSPDF



ካናት ተቀምጠ

ሳይሠራ ሳደገዝ፣ በጉልበት ቀምቶ፣
ሳያዕብ ሳያልም፣ በነፃ አግኝቶ፣
ደም ትኖቱን ባነፅነው፣ ሮት ላይ እንፈራጦ፣
እንዳሻው ይዝናናል፣ ካናት ተቀምጦ።
በሚበርፈው ብሩ፣ እያረደ ሙክት፣
ረደሱን ያራግፋል፣ በኛ ላይ ከለናት።
ምን እንደሚጠጣ፣ ባናውቅም ወይነቱን
እንደሸናብን ነው፣ ያን አለጸም ሽንቱን፣
አለትሞ ጠምበሮ፣ የሠከረ ሊታ፣
እገደናደብን ነው፣ የጠርሙስ እሩምታ
ካቅሙ በላይ ውጦ፣ የምግብ አይነቶች፣
ያቀረሽብናል፣ ሸምታኘን ወደታች።
ሁሌ እያጋዘ፣ ያገር ጋለሞታ
ካናት እያስካካ፣ ነስቶናል ዕጥታ።
በገዛ ቤታችን፣ ባይተዋሮች ሆነን፣
ኑሮ ተባለና፣ ይኸው እንኖራለን፣
ይህን ሁሉ መዓት፣ ባናት ተሸክመን፣

ካዲ " (ካድሪ ትምክሕተ ካድሬውን እንደምትጠራው) ካናታችን ላይ ተቀምምጦ፣ ተፈናጦ ማለት ይሻል ይሆን፣ ያገሩን ጋለሞታ ሁሉ በየምሽቱ እያፈራረቀ ዳንኪራ ሲረግ ጥብን፣ በየሰንበቱ የሚያርደውን ሙክት ፈርስ ሲጥልብን፣ በኑጋ በጠባ ሲገባና ሲወጣ እየገላመጠ ሲያፈዝብን ዘወትር ማየቱ ነው።

---" ድሮም ቢሆን ሲያቀብጠን እንጂ፣ ይህን መሳይ ፎቅ ቤት መቸ ያስፈልገን ነበር ? " አሉ ትምክሕተ፣ ውር ደቱን ያመጣባቸው ፎቁ መሆኑን እያማረሩ። ሚዶ መስሏቸው ጸጉራቸው ላይ የሰኩትን ሹካ እየሳቁ በማንሳት። " ወይ ጉዴ! ዛሬ ደግሞ ሹካውን ሚዶ አርጌዋለሁ ለካ! " አሉ ሳቃቸውን እያራዘሙ።

--- " ፎቅ ቤትነቱስ ምንም አልነበረም። የብሱን ላለ ማጥበብና ለሌላውም ወገን እንዲደርሰው ስንል ነበር ወደ ሕዋ የተስፋፋን! እኔን የገረመኝ የአንድ ቁምን መኖርያ ቤት፣ እንደ ትርፍ ቤት ተቁጥሮ፣ ፎቁን ነጥለው መውረሳቸውና ለካዲ መስጠታቸው ነው። " አሉ ራሳቸውን እየነቀነቁ።

---"ምን አለፋህ ወንድዬ! ያ መሩ ይህን በደላችንን ቢሰማ ኖሮ አያስችለውም! መራማ ሁል ጊዜ የሚለው፣ " ከሰው ጋር የመጣውን ሁሉ እንዳመጣጡ መቀበል ነው። " የኛን ጣጣ እሱ አላወቀ። እዚያ ሃች ተቀምጦስ እንዴት ሊያ ውቅልን ይችላል! "

--- " መራንስ ግንድ ቁምነገሩ አክብሬዋለሁ። ሀገር ተቁርሶ እንዳይሔድ ኬላውን በመጠበቁ! " አሉ ባለምባራስ ሻካራ ግንባራ ቸውን እየሰነበሩ።

---" አይ ወንድዬ ቢቸግርህ ነው! ምኑን ይጠብቀ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዋል! ውስጣችን ተራቀሉቶ እርቃነሥጋችንን ብቻ ቀርተን....." እንባቸው እንደተለመደው ካይኖቻቸው ውስጥ ይፍለቀ ለቃል።

---" አዬ ትምክሕተ! ያስችልሽ እንጂ! እኔ የሚገ ርመኝ እነዚህን ጥቁር ዓመታት ሁሉ ስታነቢ እምባሽ አለመ ድረቁ፣ ዓይንሽ አለማለቁ ብቻ ነው። እድሜአችንም ቢሆን ትንሽ አይደለም። ብዙ አይተናል። አላየሽም እንዴ ስንቱ ቀዘባ ወጣት በየፈፋው ወድቆ እንደቀረ ? ተመስገን ማለት ነው! " አሉ ባላምባራስ ትምክሕተን እያባበሉ።

---" ባያድለን ነው እንጂ የምንጠርበት የዕረፍታችን ዘመን ነበር። እንደሌላውም ቤተ-ሰብ፣ የልጅ ልጅ ከቦን፣ ዘመድ አዝማድ አጅቦን የምንዝናናበት ወቅታችን ነበር። በመ ንታ ልጆቻችን ፈንታ፣ መንታ ድመቶቻችን ብቻ ናቸው የቀ ሩን። በሩቅ የሚገኙት ልጆቻችንም ቢሆኑ፣ አይጥና ድመት ሆነው እንዱ ሌላውን ለማጥፋት እንዳቋቁ ናቸው። የዘር እርግማን እንኳ ያለብን አይመስለኝም። ሁላችንም ወላጆ ቻችንን በሚገባ ጠረን ተዝናንተው ነው ያለፉት። ቤታቸው ሁል ጊዜ እንደሞቀ ነው ያለፉት። የኛ ኑሮ ከነሱ ጋር በምኑም አይመሳሰልም። ሌላው ቀርቶ የቅርብ ዘመዶቻችን ሳይቀሩ፣ በልጆቻችን ሁኔታ ምክንያት ከቤታችን ዝር አይሉም። ከዚህስ የበለጠ መከራ ምን አለ ? " .....የማያ ልቀው እንባቸው ይፈሳል።

--- " እንዲያ ቢቸግርሽ እንጂ የሚፈሰው እንባሽ ፏፏቴ ሆኖ ልጆችሽን ከያሉበት ጠራርጎ አያመጣልሽ! " አሉ ወንዴ ባለቤታቸውን ማባበል ሰልችቷቸው።

--- " እሱንስ የኔዋ በዓታ ማርያም ታውቅልኛለች "

አሉ በተማጥኖ ድምፅ።

--- " አይ! እንዴው ቢጨንቅሽ ነው! በዓታማ ራሷን አስወርሳ ዝም ብላ የለ! " እንደመሳቅ እየከጀላቸው ወንዴ ባለቤታቸውን ይተቻሉ።

--- " አንተዬ እሷንስ አትፈታተን! ዝም ያለች አይምሰልህ! ቀኑን እየቀመረች ነው! " አሉ ትምክሕተ የበዓታን ነገር ሲያነሱባቸው አለመውደዳቸውን በመግለጽ።

---" የሷ ነገር ሲነሳብሽ እንደማትወጂ አውቃለሁ! እሷን ለጊዜው እንተውና እስቲ ዛሬ የመጡልን ደብዳቤዎች ደግሞ ምን ይዘው እንደመጡ እንመልከት! " አሉ ወንዴ ደብዳቤዎቹን እያመቻቹ።

--- " እስካሁን እንዴት አስችሎህ አስቀመጥከው?" አሉ ትምክሕተ ለማየት ቸኩለው።

--- " የደንቡን ስጠብቅ ነዋ! የመክፈቻ ጠበል! " አሉ ወንዴ መጠጣት ፈልገው በደብዳቤው ሰበብ። " የገላጭ ይባል የለ በባሕላችን! ትምክሕተዬ! "

--- " እስቲ ለሁሉም የላኩልንን ደብዳቤዎች እንያ ቸውና ይሻላል! መርዶም ሲሆን ይችላል እኮ! " አሉ ትምክሕተ በከፍተኛ የጉጉት ስሜት።

--- " እንዴት ደረቁን እንክፈተው ትምክሕቴ ? ሠቀቀን የሆነብን ደብዳቤ እኮ ነው! የሚጠጣ ጠበል አቅር ቢና ይሻላል፣ ለክፉም ለደጉም! " አሉ ወንዴ እንደጠ ማቸው ለመጠቆም።

---" እኔን ሞት ይርሳኝ! ቀልቤ ከድቶኝ የለ! ከነጋኮ ምንም አልቀመስክም! የጐረንኔም ቢሆን እኮ ያ የትላንቱ ዳግ ም አረቄኮ አለ! " ብለው ሊያመጡ ወደ ሌላ ክፍል ይሔ ዳሉ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ባላምባራስ ወንዴ፣ ትምክሕተ አረቄውን እስኪያመጡ ድረስ ዘወትር ብቻቸውን ሲሆኑ የተለመደች እንጉ ርጉሮአቸውን ያላዝናሉ።

" የመንትዮች እናት፣ ልቧም ሆኖ መንታ፣
ልብረር ልብረር ይላል፣ ወዳሉበት ቦታ፣
አንዱ ወደ ስሜን፣ ሌላው ሰሜን ዋልታ፣
እንደፈረደበት፣ ሔዶ ሲንገላታ፣
ባልፈፀመው ወንጀል፣ በልጆች ትዝታ!..... "

ወይዘሮ ትምክሕተ ከጓዳ ይዘውት የመጡትን ጠር ሙስ ከሳሎን ጠረጴዛ ላይ ያስቀምጣሉ። ጠርሙሱ ጥቁር ስለነበረ ያረቄውን መጠን አያሳይም። ዕለቱን ለማዋል ያህል እንደሚበቃ ለመገመት፣ ትምክሕተ ያመጡትን ጠርሙስ አን ስተው ያነቃንቃሉ።

--- " ለዛሬ ይበቃሃል ወንድዬ - እኔ መቸም ብዙ እንደማልጠጣ ታውቃለህ..... " አሉ፣ የቀረበው መጠጥ ብዙ እንዳ ልሆነ እየገለጹ ትምክሕተ።

--- " እሱስ ይበቃ ነበር! ግን ያመጣሽውን ጠርሙስ አይተሻል! " አሉ ወንዴ ውስጥ ውስጡን ሳቅ አፍኖአቸው።

--- " ምኑን ይሆን ያመጣሁት ? መቸም የኔ ቀልብ ጠፍቷል " አሉ ትምክሕተ ወደ ጠርሙሱ እየተመለከቱ።

--- " የዘይት ጠርሙስ እንኳ ቢሆን ይሻል ነበር! እኔ የገረመኝ የአዶኮሰኜ ጠርሙስ ከምግብ ቤት ክፍል መግባቱ ነው! " አሉ እየሳቁ ወንዴ።

--- " ውይ እኔ በጠፋሁ! ለካ ያመጣሁት አዶኮሎኙን ኖሯል! አሉ ትምክሕተ፣ ራሳቸውን በራሳቸው እየታዘቡ።

---" እኔ የምፈራው እንዴው ጨርሰሽ እንዳትቀው

ሽብኝ ነው! " አሉ የአዶከሎኝ ጠርሙስ፣ ሳሎን መምጣት ጉዳይ አሳስቧቸው ።

--- " እዚያስ አልደርስም! በዓትዬ አለች! ግን እንዲው ስመሆኑ የተሰቀለ ልብ የሚያወርዱበት መድኃኒት፣ ሐኪሞች አይኖራቸው ይሆን ? ብዙውን እየደበቅሁህ ነው እንጂ በየቀኑ የማረገውን ስሕተት ሳስታውሰው፣ ነገሩ አላማ ረኝም !" አሉ እንደመተከዝ አንገታቸውን አቀርቅረው ።

--- " ውነትሽን ነው! ነገሩ አላማረኝም ። አሁንስ የግድ መፍትሔ መፈለግ ከሚያስፈልገን ደረጃ ላይ ደርሰ ናል ። መቸም ዋናውማ መድኃኒትሽ፣ የልጆችሽ በአንድ ማዕከ ላዊ አቋም ላይ ተደራድረው ቢተባበሩና እንደወትሮአቸው ቢፋቀሩ ነበር !--- " አሉ ወንዴ እሳቸውም ተከዘው ።

--- " በዓታ ካለች አንድ ቀን ያደርጉታል! በመሐሉ እኛ ተጐዳን እንጅ....." አሉ ትምክሕተ፣ በምኞት ሰመመን ተውጠው ።

--- " የኛን መጐዳት ተናገሪ እንጅ፣ እነሱስ የሕይ ወት ድብብቆሽ ጨዋታቸውን መቀጠላቸው የማይቀር ነው ። ' በምናምንበት እንሞታለን፣ ' የሚሉ እምቦሶችስ፣ አንዱ ሌላውን ካላጠፋ ሰላም የሚያገኝ አይመስለኝም ። የማዝነው የነሱ ጦስ እኛን እንዲህ ቀልበ-ቢስ በማድረጉ ነው ። "

--- " ወንድዬ፣ ያን ያህል ሔደናል እንዴ ? " አሉ ትምክሕተ ተደናግጠው ።

--- " እንዴታ ከዚህ የባሰ ምን ይመጣል ? " አሉ ወንዴ ፈርጥመው ።

--- " ያዶከሎኜ ጠርሙስ ጉዳይ ነው እንዴ እንዲህ ያስመረረህ! "

t.me/OLDBOOKSPDF

--- " ያዶ ከሎኜ ጉዳይ ቀላል ነው ። በዚያ ሰሞን የሆንሽው ግን ምንጊዜም ቢሆን ከጎሊናዬ አይወጣም! " እያሉ ማሰላሰል ጀመሩ ።

--- " የቱን ይሆን ወንድዬ ? " በከረረ ጉጉት ጠየ ቋቸው ።

--- " ትምክሕቴ ረስተሽው ይሆናል ። በዚያ ሰሞን መንፈቀ ሌሊት ላይ የሆንሽውን ዘወትር ሳስታውሰው ይዘገ ንነኛል ። ድመቶቻችን፣ ረስተን ባልዘጋነው የበስተግርጌ መስ ኰታችን በኩል ካመሹበት ዘለው ሲገቡ፣ በቀሰቀሱን ጊዜ፣ እነ መሩ መጡ ብለሽ በእንቅልፍ ልብሽ መንፈቀ ሌሊት ላይ መስኰቶቹን ሁሉ ከፍተሽ፣ ምግብ ለማምጣት ወደ ማዕድ ቤት ልትሔጂ ስትዪ፣ አከላክዬ ያስቀረሁሽ ትዝ ይልሻል ? በሌሊት ድንገት የሚነቁና ካልጋቸው ላይ ሳያውቁት ተነስ ተው፣ በያጋጣሚው የሞቱ ሰዎች ቍጥራቸው ጥቂት እንዳ ይመስልሽ ትምክሕቴ..... " አሉ ፈርጥመው ።

--- " እንደዚህ ካለውስ አደጋ ትጠብቀኛለች - በዓታ የት ሔዳ! ይልቅስ አሁን ካረቁው ፉት ፉት እንበልና፣ ደብዳ ቤዎቹን እናንብባቸው! " ብለው፣ ካመጡት አረቄ በመለኪያ ይቀዱ ጀመር ።

--- " እስቲ ቸር ያሰማኝ " ብለው የደብዳቤዎቹን ኤንቬሎፕ መክፈት ጀመሩ፣ የድርሻቸውን የመለኪያ አረቄ ባንድ ትንፋሽ ከጨለጡ በኋላ ።

--- " እንግዲህ ረጋ ብለሽ አድምጭ -- መጀመሪያ ከስሜን የመጣውን የመሩን ደብዳቤ አነብልሻለሁ ። በዘመን ማመኑን ትቶታል መሰል፣ ቀኑን አልፃፈበትም ። "....

ምንጊዜም ለምትታሰቡኝ ወላጆቼ
አባቴ ወንዲ
እናቴ ትምክሕተ፤

ይህ ደብዳቤዬ እንደሌላው ጊዜ ሁሉ በሰላም እንደ ሚያገኛችሁ ተስፋዬም እምነቴም ነው። ባለንበት ትውልድ ግዳጅ መሠረት፣ የነበረኝን ንብረትና ሥልጣን፣ በተለይም እናንተን ወላጆቼን ዐቅም ባነሳችሁና መጦርም በሚገባችሁ ወቅት፣ ትቼ እዚህ ትግል ላይ በመሠማሪቴ፣ የፐሪንስፕሌን ከፍተኛነት ያሳስበኛል። ከዚህ ቀደም እንደገለፅሁላችሁ ሁሉ፣ ያን ከሐዲ ወንድሜን ከነግብረ-አበሮቹ ይዘን ለፍርድ ለማቅ ረብ፣ የመጨረሻ ዝግጅት እያደረግን ነው። ይህ ያለሁበት ድርጅት ትግላዊ ውሳኔ ይሁን እንጅ፣ በበኩሌ መራን ባገኝ፣ ርኩስነቴን ይጠየፈዋል እንጅ፣ በጥርሴ ነበር የምዘልዝለው። ይህ ባይሆን ደግሞ፣ በጥይቴ ሳይሆን በጠበንጃዬ ሟንጃ ነው የማርደው። የፈጠሩትን ችግር፣ ከኔ ይልቅ በቅርቡ ሆናችሁ በየዕለቱ የምታዩት እናንተና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀ ዋል። መራ ሞተ ብላችሁ በጭራሽ እንዳታዝኑ። የሕዝብ ጠላቶች መጨረሻቸው አጉል ሞት ነውና። ጊዜው ይርዘም እንጅ፣ በድል አድራጊነት አዲስ አበባ እንገባለን። ይህ ምኞት ሳይሆን ውሣኔ ነው። ፍላጐትም ሳይሆን ግዴታ ነው። ፍትሕ በሚያምንበት እንበቀላለን። ነገሮች ሁሉ እንዲህ እንደተጨማለቁ አይኖሩም። ልጅ አይ በለውና፣ ያንን መራን እንደረገማችሁት በሐሳቤ እገምታለሁ። ርግማን ሲያንሰው ነው። ዛሬ ብዙ አልጽፍላችሁም። የኔን ስም እያጠፋም ይጽ ፍላችሁ ይሆናል። ያን ከሐዲ ለመዘረር ዝግጅት ላይ ነኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደተለመደው ደብዳቤ ይፅፍላችሁ ከሆነ፣ የሚቀጥለው ደብዳቤ ይዘት የራሱን መርዶ እንደሆነ አትጠራጠሩ። ይህ ዕውን ባይሆን፣ ቃል ለምድር ለሰማይ!

ሁልጊዜ ከሐሳቤ የማልለያችሁ
ልጃችሁ፣ መሩ (ኤርማ)

ትምክሕተ፣ ከረጅም እንቅልፍ የተቀሰቀሱ ይመስል፣ ሲያዳ ምጡ ቆይተው፣

--- " እኛ እንደሆነ ደንገዘናል! መርዶም ሆነ ልደት አይሰማንም። የሚያሳዝነን፣ እርስበርሳቸው የተጋደሉ መንቶች እየተባሉ መተረቻ መሆናቸው ነው "

--- " አንቺ ስለኛ መደንዘዝ ነው የምታስቢው። ልጆቻችን ግን በየግላቸው አመለካከት የሚያስቡት ስለወደፊቱ ትውልድ፣ ደኅንነትና ብልፅግና ነው። ሁሉም እንደሚሉት፣ ትግላቸው ለጠቅላላው የሃገራችን ሕዝብ መድኅን ለመሆን ነው። ሞታቸውንም ቢሆን የሚቆጥሩት በመሥዋዕትነት ነው። የትኛው ወገን እንደሚያሸንፍና የትኛውስ ወገን ትክ ክለኛ መስመር እንደያዘ ጊዜ ያሳያል። ላረጋውያኑ እኛ ግን የጠቀመን ፋይዳ የለም። ካዲው አናታችን ላይ ተቀምጦ፣ ይበልጥ እያሰረጀን ነው.... እባክሽን አረቄውን ቅጅልኝ! " ይላሉ ወንዲ።

--- " ደብዳቤውን አንበህ ጨርስ ብዬኮ ነው " አሉና ትምክሕተ አረቄውን ቀዱ።

--- " እውነትሽን ነው! ለብ ካለኝ ወይ እቀንሳለሁ ወይ እጨምራለሁ! እዚያ ደረጃ ሳልደርስ፣ የመራን ደብዳቤ ደግሞ ላንብልሽ " አሉ እየቀለዱ።

ሚያዝያ 30- 79 ዓ.ም.

ሁልጊዜ በልቤ ላላችሁ ወላጆቼ፣
አባቴ ባላምባራስ ወንዴ
እናቴ ወይዘሮ ትምክሕተ

የተለመደ ሰላምታዬን አስቀድማለሁ።

የዐብዮት ግዴታ ሆኖብኝ በተሰጠኝ ኃላፊነት ስባክን፣ ደብዳቤ ሳልጽፍላችሁ ዘገየሁ። ሆኖም ደኅንነታችሁን ካካባቢያችሁ ካሉ ካድሬዎች አሰማለሁ። መቸም ያ ወንበዴ እንደሚጽፍላችሁ አውቃለሁ። ባለፈው ወር ላይ ለጥቂት አመለጠ እንጅ፣ ከዚህ የተላኩ የነበልባል እዞች ሊማርኩት ነበር። እንዲህ በሀገሩና በዐብዮት ላይ ወንብዶ አይቀራተም። አንድ ቀን ዋጋውን ያገኛል። አንድ ቀን ምርኮ ገብቶ፣ እንደ ተለመደው፣ የፍየል ወጠጤ ይዘየርበታል። አብዶ ይሆናል እንጅ፣ በርግጥ በጤናው፣ ሕዝቡንና ሀገሩን አይክዳም ነበር። ሀገራችን በዓለም የለየላት ምስኪን ሆናለች። በለማኝ ነትም የመጀመሪያውን ደረጃ ይዛለች። ለዚህ ሁሉ ያደረሷት፣ እንደ መሩ ያሉ ፀረ ዐብየተኞች የቦደኗቸው የወንበዴ ድርጅቶች ናቸው። በስንት አርበኞች መስዋዕትነት የተገነባች ሀገራችን፣ በደምና አጥንት የታነፀች ድንበራችን እንደነመሩ ባሉ ወንበዴዎች መመዝበር የለባትም። የምናካሔደው ትግል የሞትና የሕይወት ትግል ነው። የመጨረሻዋ ደም ጠብታ ድረስ ለሃገራችን ክብር ልንዋደቅላት ቆርጠናል። ይህን የምጽፍላችሁ፣ ያ ወንበዴ መሩ፣ የኔን ስምና ዓላማ በማርከስ፣ አዘውትሮ እንደሚጽፍላችሁ፣ በመገመት ነው። ጽፎ ላችሁ ከሆነ ሐሰት ነው። እንዲያውም እሱን መሳይ ከሐዲ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከኛ ቤት መወለዱ ዘወትር ያስደንቀኛል። ዘር የሚያሰድብ ወስላታ ነው። ጭራሽ እንዳትሰሙት። ሌላው ደግሞ፣ ማናቸውንም ዓይነት ችግር ለመታገስ ሞክሩ። ሰው እንደ ሆነው ሁሉ ለመሆን ሞክሩ። የድል ቀን ሩቅ አይደለም። ጠቅላላው ሀገር ሁሉ ነፃ ሲሆንና ነባር ሰላም ሲሠፍን፣ እኔም እዚያው አዲስ አበባ መጥቼ አብረን እንኖራለን። የዚያን ወራዳ ወንበዴ ልጅነትና ሕይወት ግን፣ ብዙ ጊዜ እንደ መከርኳችሁ ሁሉ፣ መሠረዝና እስከ መጨረሻም መርሳት ይኖርባችኋል።

ምንጊዜም በመንፈስ የማልለያችሁ
አንዱ ልጃችሁ
መራ (ሔርማ)
ኢትዮጵያ ትቅደም።

--- " ሰማሽው አይደለም ትምክሕትዬ! መንታ ልጆች ቢኖሩን ከመንታ ድመቶቻችን የተሻሉ አልሆኑም። አንዱ ሌላውን ሠርዙ ይላል። *1-1 = 0* ለማለት ነው። ድሮውንስ ቤሆን ' የሰለት ልጅ ' ይባል የለ። አለመታደል ነው! " አሉ ባላምባራስ ወንዴ አለወትሮአቸው እንደመመረር ብለው።

--- " ወንድዬ! ዛሬስ እኔ ነኝ በደንብ መጠጣት ያለብኝ! " አሉና ትምክሕተ መለኪያቸውን እስካፍጢሙ ሞልተው ጭልጥ አረጉት። በዚያው ቢበቃቸው እንኳ ደግ ነበር፣ ደገሙት።

--- " ትምክሕተ በነገር መቃጠሉ አንሶሽ፣ የመጠጡን ቃጠሎ ባትጨምሪበት ደግ ይመስለኛል! " አሉ ወንዴ

በባለቤታቸው ያልተለመደ ድርጊት ተደናግጠው።

--- " ትጠጣ እንደሆን ልቅዳልህ! ድህነታችንን ሳይሆን ልጆቻችንን የሚያስረሳን ሌላ መፍትሔ ያለ አይመስ ለኝም! " አሉ ትምክሕተ፣ አንደበታቸው በመጠጡ እንደ መለፋደድ እየቃጣው።

--- " ለጤናችን! እንኳ ከእንግዲህ ማለቱ አያዋጣም..... ትምክህተ፣ ለሞታችን-ፅዋችንን እናንሳ! " ብለው፣ ያቺ ያረቄ ጠርሙስ ጠብታዋ እስክታልቅ ጠጥተው ጨረሱ። በስተምሽቱ ላይም፣ እንደምንም እየተንገዳገዱ፣ ተያይዘው አልጋቸው ላይ ወደቁ። መንቃታቸውን ያየ አንድም ሰው ባይኖርም፣ እንቅልፍ ሊወስዳቸው ገደማ፣ ባላምባራስ ወንዴ፣ እንደ ' ደጎና አሳድረኝ ፀሎት ' ያቺ የተለመደች እንጉርጉሮአቸውን ሲያላዝኑ ይሰማ ነበር፣

" የመንትዮች እናት ልቧም ሆኖ መንታ፣ ..
ልብረር ልብረር ይላል፣ ወዳሉበት ቦታ፣
አንዱ ወደ ስሜን፣ ሌላው ሰሜን ዋልታ፣
እንደፈረደበት፣ ሐሩ ሊንገላታ፣
ባልፈፀመው ወንጀል፣ በልጆች ትዝታ!.....
መከረኛ፣ እናት፣ መንታ ልጆች ወልዳ፣
አንዱ፣ ሳት፣ ሌላው ማይ፣ ፅሩራን ዱብ ዕዳ፣
ወግ ደርሷት፣ ሳትጦር፣ ባልሠራችው ፍዳ፣
ሳትኖር፣ ልትሞት፣ ነው፣ ሕይወት ሆኗት፣ ባዳ...."

ለጊዜው አበቃ

t.me/OLDBOOKSPDF

የ ተ ጣ ሰ አ ጥ ር



" ወጋ ወጋ አድርጉ እዚያም እዚህ ምድር!
የኔም ሆነ ያንቺ ግዴታኮ ነበር!
ማንም የጣሰውን እንደገና ማጠር! "

(የጠፍ . ቁ . 4)

መንደርደርያ

በገዛ አገራቸውና በገዛ ምድራቸው ላይ እየኖሩ፤ በየዕለቱ የውርደት አተላ የሚጋቱ ወገኖች ቍጥር፤ እየጨመረ መጥቷል። ጥንታውያን ጀግኖች አባቶች፤ ይህን መሳይ ብሔራዊ ውርደትን በመጥላት፣ ለሕዝባቸው ክብርና ለሃገራቸው ነፃነት ሲሉ፤ ከባዕዳን ወራሪዎች ጋር እየመከቱ በየጐራው ሲታገሉ ኖረው ነበር። ዝርዝሮቹን ጐራዎች መጥቀስ ባያስፈልግ እንኳ፤ አድዋንና መተማን ማንሳቱ ይበቃል። የነዚያ ጀግኖች አባቶችን አፅም፤ ገና ያስከበሩት መሬት በልቶ ሳይጨርሰው፤ በአንድ ትውልድ ዕድሜ ውስጥ፤ የሞቱላት ሀገር የባዕዳን ወራሪዎች መፈንጫ፤ የልጆቿ ክብር መረገጫ፤ ለመሆን በቃች።

እነሱ አስቀድሞ ታይቷቸው፤ “ የጠሉት ይወርሳል፤ የፈሩት ይደርሳል ” ብለው ይተርቱ እንደነበር ሁሉ፤ ዛሬ እኛ ትንቢታዊ ንባበ ቃላቸውን፣ በድርጊት አየን። የፈሩት መድረሱ ቢያስደንቀንም፤ የጠሉት መውረሱ ደግሞ ይበልጥ አስገርሞ አስፈጨነቀን። ታዲያ ይህን ትንቢት የነበረ የአባቶች ንግርት፤ ለመጭው ትውልድ መዝግቦ ማቈየቱ፤ ፋይዳ ይኖረው ይሆን? አለያስ፤ በትግል ያለውን ተጋዳይ፤ ብሔራዊ ውርደት ያሳደረበትን ቆራጥነት፤ ይበልጥ እንዲቀጥል መራራ ሐሞቱን ሠፍነግ አድርጐ በትግሉ እንዲጠነክር አይረዳው ይሆን? አለያስ፤ በን ቃት ማነስ ምክንያት የዳበረውን ህዝባዊ ወገን፤ የህገሩን ክብር ለማስደፈርና ህዝባዊ ልዕልናን ለማፍራት፤ ተዳፍሮና ተባብሮ እንዲነሣ ለመገፋፋት፤ ይህ ዐይነቱ የግፍና የውርደት ታሪክ የርዳታ ድርሻ አይኖረው ይሆንን? እነዚህን ተደራራቢ መጠይቆች፤ መጪው ታሪክ ይመልሳቸዋል።

t.me/OLDBOOKSPDF

የተጣሰ አጥር!

(የመናገሻዪቱ ከተማ ጊዜያዊ ሕይወት ብልጭታ)

" ..... ማርጀትዋ በጃት እንጅ አሮጌት እናቴንም አይለቃትም ነበር። ትናንትና በዓታ በዓል ለማክበር ስንሔድ፣ ፊት በር ላይ ጂፒን አቁሞ ሴቴን ሁሉ ሲመትር፣ በናቴ የበስ ተጀርባ ሽንጥ ላይ ዐይኑን ጥሎ ነበር። እኔን ይበልጥ የሚገ ርመኝ በኔ ቤተሰብ ላይ ብቻ ይህን ያህል መቅነዝነዙ ነው። እንደኛውን ምክንያት እንኳ አውቀዋለሁ። የኔ ቤተ-ሰብ የው በት መደብር፣ የቆንጆዎች አድባር መሆኑ ነው። እንዳው ከምን ዐይነቱ ዘመን ላይ ደረስን? ምን ዐይነት የአውሬዎች ጊዜ ላይ ጣለን? ..... " አሉ እንባ እየተናነቃቸው። በሣሎናቸው እንደ ሀዘንተኛ ጋቢያቸውን ተጀቡነው በመቀመጥ ከአ ማቻቸው ጋር የሚወያዩት፣ ስለተጠለፈባቸው ልጅ ጉዳይ ነው። ከበስተፊታቸው ካለች ክብ ጠረጴዛ ላይ ሞኝ አንግሥ በጠርሙስ ቀርቧል። እያንዳንዱን ዐረፍተ ሐሳብ በጨረሱ ቍጥር አንንዳንድ መለኪያ ይጨልጣሉ። ከበስተጀርባቸውም የሚንጠለጠልበት ጉጠት መሳይ ምስማርም በግድግዳው ላይ ይታያል።

" ወይ ነዶ! " አሉ ድንገት ከተቀመጡበት ተነስተው በሣሎኑ ውስጥ እየተንጐራደዱ። " ወይ ነዶ! መንጥር ባትወ ረስብኝ ኖሮ፣ ዘንድሮ ይለይልኝ ነበር! እንዲህ የባዕድ ምናም ንቴ መጫወቻ አሻንጉሊት ከመሆን ታድነኝ ነበር! ወይ ነዶ! " አሉ እጃቸውን ዘርግተው፣ ጠመንጃቸው ይሰቀልበት የነበረውን ምስማር እየዳሰሱ። "ወይ ነዶ! ጠላትን ገድሎ መሞት ክብርኮ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው! በምውትነት ሕያውነት! ውርደትን ቍጭ ብሎ ከመ ጋት፣ ምሬቱንም በግዳጅ ከመ ዋጥ፣ ጠላትን አጥፍቶ መሞት፣ ሞትነቱ ከማር ይልቅ ይጥማል። እንደተከበሩ መሞት በክብር መሞት ያህል ይቆጠራል። አላመቸኝም እንጅ፣ ይህ፣ የጣልያን ፋሽስት አንገት ሲጐምድ የኖረ ጐራዴም በቀሌን ይወጣልኝ ነበር!! " አሉ የሽለላና የቀረርቶ ያህል ስሜታቸው እየሞከራ ቸውና ጐራዴያቸውን መዘው እያወጡ። " ወይ ነዶ! የውር ደት ማኅደር ሆኜ ልቅር! አይደረግም! ግን ያንድ ቀን ጉዳይ ነው! ሲያመቸኝ አርጄው እሞታለሁ!!....." አሉ ብስጭት ናላቸውን በጥብጦት እየተወራጩ።

" አይደለም! እርስም ብዙ ነገር አይተዋል! መታገሥ አለብዎት! የማያልፍ ነገር የለም! የጊዜ ጉዳይ ነው። ትክክልኛ ፍርድ የምናገኝበት ወቅት ይመጣል። ሩቅም አይመስለኝም። መታገሥ ግን ይኖርብናል " አለ አማቻቸው፣ ቆንጆ ሚስቱን ካስጠለፈ ሣምንት ሆኖት፣ ከባለቤቱ አባት ጋር ስለጉዳዩ ለመወ ያየት መጥቶ በትካዜ ስሜት ተዝናንተው የተቀመጡ እግሮቹን እያነዘረ።

" ትዕግሥትኮ ቁና አለው። መጠኑን ሲያልፍ ታጋ ሹን ሊያሳብደው ይችላል። እኔ ግን እስካብድ ድረስ መጠበቅ አይኖርብኝም! ባለቤቴን አርክሶብኛል! የልጆቼን እናት! የእህ ቴን ባል፣ አድኃሪ የሚል ሰበብ ፈጥሮ እሷን እንደልቡ ለማግ ኘት ሲል አሳስሮ፣ ይኸው በእስር ቤት ሲማቅቅ ሦስተኛ ዐመ ቴን ይዟል! ሦስት ሴቶች ልጆች ቢኖሩኝ፣ ሦስቴንም ከናታ ቸውና ከአክስታቸው ጋር እኩል ወሽሞ እንደ ባዝራ ባሰኘው

t.me/OLDBOOKSPDF

ቍጥር ይነዳቸዋል። አንድ ወንድ ልጅ ቢኖረኝ፣ በእህቶቼ፣ በናቴና በአክስቴ መዋረድ፣ በቀላቸውን ለመወጣት በሞከረ ቍጥር፣ ፀረ ዐብዮት እየተባለ እንደጥጃ በየጊዜው ይታሠራል ይፈታል።እንዲውም ሰሞኑን ከዚሁ ሰው ጋር ግጭት ፈጥሮ፣ ሊገድሰው ዝቶበታል! ታዲያ ታገሥ የምትለኝ የቱን ነው? መታገሤሥ ምን ሊፈጥርልኝ ነው? ውርደቴ ያደባባይ ይፋ ከሆነ ሰንብቷል! ....." አሉ በደረሰባቸው ውርደት ተበሳጭተው እዬዬአቸውን ለማቅለጥ እየዳዳቸው።

" ዛሬ ደግሞ ምን ሆኑ? ብዙ ጊዜ ታግሠው የለ ምን? ውርደቴ የመጣው በኛ ብቻ አይደለም። ባገር ላይ የመጣ፣ በየቤቱ የደረሰ ነው። ቆንጆ ሚስቴ ያልተጐሸመች በት፣ ኰረዳ ልጁ ያልተደፈረችበት፣ በክብር የኖረች እናቴ ያልተዋረደችበት እንደሌለ ያውቃሉ። ይህ ዐይነቱ ውርደት በሴቶቹ ወገኖቻችን ላይ የደረሰ ሲሆን፣ በኢኮኖሚያችን መድቀቅ የተነሳ፣ ስንቱ በረሀብ እንዳለቀ፣ ስንቱ በችግር እንደማቀቀ፣ ስንቱ ጤናውን አጥቶ እንዳበደ፣ ስንቱ ቤት ሀገሩን፣ ዘመድ ወጉን ጥሎ እንደተሰደደ፣ ስንቱ ያለወንጀል በየእስር ቤቱ ያለፍርድ እንደሚሠቃይ፣ ስንቱ በየመንገዱ ገላመጥከኝ እየተባለ መከራውን እንደሚያይ፣ እርስዎም ሆኑ ያገሩ ሰው በሙሉ ያውቀዋል። ታዲያ ለምንድር ነው መበሳ ጨትዎ? መበሳጨት ብቻውን፣ ራስን መልሶ ይጐዳል እንጅ ምንም ፋይዳ አይሠራ። ርግጥ በተለይ በኛ ቤተሰብ ሴቶች ላይ የደረሰው ውርደት ወደር አይገኝለትም። ባለቤቴ እንደሚያውቁት ሁሉ፣ ከኔ በስተቀር በሕይወቷ ሙሉ ሌላ ወንድ አታውቅም። ምሥ ክሯ ነኝ! ቀና ብላ እንኳ፣ ወንድ ቀርቶ ሴት አታይም ነበር። ይኸው ዛሬ የውርደት ሸማዋን ለብሳ የመገን ሸላ መተረቻና

መዛበቻ ለመሆን በቃች ---" እንባው በፊቱ ላይ ኩልልል እያለ መንጠብጠብ ሲጀምር፣ መናገር አቅቶት ይንተባተብ ገባ።

" ሴቶቻችን ተዋረዱ ለምን ትለኛለህ! የተዋረድነው እኛ ወንዶቻቸው እንጅ! እነሱማ ምን ዓቅም አላቸው! የምና ስከብራቸው እኛ ነበርን! ጥንታዊ ብሂሉማ፣ ' መሪን በመን ግስቱ፣ ጐልማሳን በሚስቱ' ሲመጡበት ይሞታል እንጅ አሳልፎ አይሰጥም ነው የሚባለው! ታዲያ ሚስቴን፣ እህቴን፣ ሶስት ልጆቼን ለባዕድ ነጣቂ አስረክቤ እንዴት ታገስ ትለኛለህ! በዚህ ጥቁር የውርደት ህይወት ውስጥስ፣ መኖሬ ምን ትርጉም አለው ትላለህ? ሀገር፣ ነጻነት፣ መብት፣ ፍርድ፣ በኔ በዚህ የጨለማ ህይወት ውስጥ ምን ፍቺ አላቸው? ሰዎች ራሳቸውን እያታለሉ ይኑሩ! ሰዎች እኔንም ያታሉ! እኔ ግን ራሴን ማታ ለል አልችልም! በመሸ በነጋ ቁጥር፣ የነዚህ የሴቶች ወገኖቼ ውርደትና ርክሰት እንደ ትልቅ ገዳም ደወል ጆሮ ግንዴ ላይ እየጮኸ ጤና ከሚነሳኝ ይልቅ፣ ትክክለኛ የሆነ ምርጫየን ማዘጋጀት ይኖርብኛል። ታገሥ ብለህ የምታቀርብልኝን ምክር ሀን፣ በውርደቱ ደወል ጩኸት ጆሮየ ስለደነቆረ ልሰማህ ልችልም። ይልቅስ በቀሴን የምወጣበትን ዘዴ ብትመክረኝ ይሻ ላል። እኔ አባትህ እንደሆንኩ ቆርጫለሁ---" ብለው በሚሎኑ ውስጥ እየተንጐራደዱ፣ የያዙትን ጐራዴ እንደ ቀላል ለበቅ ያውለበልቡት ጀመር። ከጐረቤታቸው፣ የታወቀ ካድሬ መኖሩ አላመቻቸውም እንጅ፣ " ገዳይ----ሰው ባገሩ፣ ሰው በወንዙ ቢበላ ሣር ቢበላ መቅመቆ፣ ይከበር የለም ወይ ሰውነቴ ታውቆ--" ብለው ለማቅራራት ነሽጧቸው ነበር። አባትና አማች

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ ሁኔታ እንዳሉ፣ ወንድ ልጃቸው የሚሎኑን በር አንኳክቶ ዘው ይላል። አማችና አባት ያሉበትን ሁኔታ አይቶ ለጊዜው ግር አለው፣-

"ደኅና አይደላችሁም እንዴ?" ሁለቱንም ይጠይቃል።

" አይደለንም! " እየተንጐራደዱ " ደግሞ መቸ ነው ደህና ሆነን የምናውቀው " ለጥያቄው መልስ መሆኑ ነው፣ አባት ተናገሩ።

" የድሮው ትዝ እያላቸው እያወሩኝ ነው " አለ አማች ሁኔታውን ያበረደና፣ ልጁም እንዳያውቅ የሞከረ መስሎት፣

" ኧረ ምን የድሮ፣ የዛሬውን በለው እንጅ! " አሉ ከቁጣ ባላነሰ ተግሳጻዊ አነጋገር።

" እባክህ እንዲታገሡ ምከራቸው " አለ አማች፣ ከመቀመጫው እየተርበተበተ ተነስቶ።

" ስለምን ነበር የምትወያዩት? " አለ በሁኔታው ተደ ናግጦ ልጅ!

" ከቤተ ሰባችን ሴቶች ላይ ስለደረሰው ችግር ነበር " አለ አማች።

" ታዲያ ምን ተወያያችሁ! " ሲል ጠየቀ መነሻውን ለማወቅ።

" ኧረ ተወኝ! እበቀላለሁ ይላሉ " አለ አማች፣ ከመ ቀመጫው እየተርበተበተ ተነስቶ።

" አይ ይሽንንማ ጉዳይ ከኔም ጋር ብዙ ግዜ ተነጋግረን አንድ ሌላ ነጥብ ላይ ደርሰናል! " አለ ረጋ ብሎ ልጅ።

" ምን! የበቀል ርምጃ ለመውሰድ! " አለ አማች ተቻ ኩሎ " ብቻ ሁላችንንም እንዳታስጨርሱን! "

" ማለቅስ አሁንም ቢሆን ሁላችንም አልቀናል " አሉ አባት በሁለቱ መካከል ጣልቃ ገብተው ።

" አይ መጨረሱ የኔ ፋንታ ነው ፣ በኛ በኩል ግን የምናደገውን በደንብ ማወቅ አለብን ። ለማወቅም እንዲረዳን ፣ ችግሩን በጠባቡ ሳይሆን በሰፊው ማየትና መመርመር አለብን ። የችግሩን መሠረታዊ ምክንያት ከሥሩ ሰርስረን መረዳት አለ ብን ። ከአባቴ ጋር እንደተነጋገርነው ከሆነ ፣ በቤተሰባችን ሴቶች ላይ ስለ ደረሰው በደል ፣ በጠባቡ አይተን የምንቀበልበትን ሁኔታ መንገድ ከማሰብ ይልቅ ፣ ለበደሉ መነሻ የሆነውን ዋና ምክንያት ፣ ዐቅማችን በፈቀደን መጠን ማናጋቱ ይበልጥ ዋጋ አለው----" ብሎ ገና የጀመረውን ሐሳብ ሳይጨርስ ፣

" ሥርዓቱ ነው ጠላታችን ይልሃላ ! " አሉ አባቴ እንደ ሥላቅ እየሞከራቸውና ሐሳቡን ለማካሂያስ እየተጣደፉ ።

" ትክክልኛ ነኝ ! አልተሳሳትኩም ! " አለ ልጃቸው ያለ ማመንታት ።

" ይኸውልሃ ሥርዓቱ ነው ሚስትህን ያስጠለፈው ! " አሉ እየሳቁ ።

" አም ርግጠኛ ነኝ ! ምን የሱ ሚስት ብቻ ! በሺና በሚ ልዮን የሚቆጠሩ ሚስቶች ናቸው የተጠለፉት ። ጠምዛዛ ማሸን ገን ያነገና ገዳዳ ባርኔጣ ያሸጠለቀ ተራ ወታደር ሁሉ ፣ ያልተ ነከሰባቸው ሚስቶች ቁጥር እግጅ በጣም ትንሽ ነው ። ድሮም ቢሆን ድንቁርናው ሀገር ሊፈታ ምንም ያህል አልቀረው ነበር ፣ ይኸው ዛሬ ኃይልና ሥልጣን አግኝቶ ፣ በሰፊው ሕዝብ ላይ እየሸናበት ነው " አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

" ሥርዓት የምትሉት የወታደሩን ሥርዓት ይሆን ? " አለ አግቻቸው ፣ በቀረበው አዲስ ሐሳብ ውዥንብር ተመቶ !

" እባክህ እሱ የሚያትተው የሥርዓት ዓይነት ብዙ ነው ! ከቅድመ ታሪክ ፣ ከድኅረ ታሪክ የነበረ ሥርዓት ፣ የባርነት ሥርዓት ፣ የፊውዳል ሥርዓት ፣ የሞናርሺ ሥርዓት ፣ የምናምን ሥርዓት እያለ የማይዘበዝበው የነገር ዝግንትል የለም ! " አሉ አሁንም በብስጭት የተበረዘ ሣቅ እየሳቁ ።

" ታዲያ የዛሬውን ሥርዓት ምን ሥርዓት ነው የሚ ሉት ፣ እንዲህ የሰውን ሚስት ሁሉ የሚያስጠልፍ ? " አለ አግች ፣ አባትና ልጅ ተወያይተው ስላልተግባቡበት ሐሳብ እየጠየቀ ።

" ሊያምኑ አልፈለጉም እንጅ ፣ በየዕለቱ የምንበላውን እንጀራ የየዘመኑ ሰው በእንዴት ያለ ሁኔታ ሊያገኝ እንደ ሚችል ዘርዝሬ በመተንተን በበቂ ማስረጃዎችና ማሳያዎች አስረ ድቻቸው ገብቷቸዋል ፣ እህል በጠቅላላውም ለሰው ልጆች የሚ ያገለግሉ እቃዎች ፣ ቆሳቁሶችም ሆኑ ሸቀጣ ሸቀጦች በምን ዓይ ነት ሁኔታ ተመርተውና ተገኝተው ፣ ምን ዓይነት ኅብረተሰባዊና ተግባራዊ ግንኙነት ሊያስገዝፋቸው እንደቻለ ፣ እነዚህንም ሊያ ስገኙ የቻሉ የየዘመኑ ተግባራዊ መሳሪያዎችና ኃይላተ-ምርት ሁኔታ ምን ዐይነት እንደነበሩና ዐይነታቸውም ከዘመን ወደ ዘመን በመደብ ቅራኔዎች ፍጭት አማካይነት እያደገ እንደመጣ በሚገባ አስረድቻቸው ተቀብለውኛል ። ይሁን እንጅ ሐሳቡን ቢቀበሉኝም አላመኑበትም ። ሊያምኑበት መቀበል ደግሞ ብቻ ውን ፋይዳ የለውም ። ደግሞም--- " ብሎ ሊቀጥል ሲል ፣ አግች የሚስቱን አባት የጋለ ሐሞት ያበረደ መስሎት ፣

" ሰበቀል ብቻ ቆርጦ መነሣቱ ብዙ አያዋጣም። ታግሶ፣ አሁን እሱ እንደሚለው ሁኔታውያን ሁሉ በሰፊው በማየትና ለገጠመን ቤተሰባዊ ችግር ብሔራዊ መፍትሔ ለማግኘት መሞከር ያዋጣል " አለ ሲፈራ ሲቸር፣ አማች የሚስቱን አባት ለማ ብረድ የሚጥርው፣ በሚፈጥሩት ጠንቅ፣ ዳፋው እሱም ላይ ሊደርስ እንደሚችል በመፍራት ነው። በርግጥም የወታደሩ ፋሽስታዊ መንግሥት በእንደዚህ ያለው ጉዳይ ላይ፣ የተለ ምዶ አሠራሩና ተዘውትሮም የሚታየው፣ አንድ ሰው ሲቃረ ነው ያገኘ እንደሆነ፣ ሰውየውን ብቻ ማጥፋት ሳይሆን መላ ዘመዱንና የቅርብ ወዳጆቹን በሙሉ በመደዳ መጥረግ ነው። ጅምላ ጠረጋ እንጅ 'ወንጀለኛ' የሚለውን ብቻ ነጥሎ ማጥቃት አይሆንለትም። ከዚህም አደገኛ ሁኔታ ለጊዜውም ቢሆን የልጃቸው ሐሳብ አዳኝነት መልክ አለውና፣ የሱን ሐሳብ ይግጠናል። "

" ምናልባት የሱ ሐሳብ አጠቃላይ መፍትሔ ሳይሆን አይቀርም! መፍትሔነቱም በሩቅ ሲታይ እንጅ በቅርቡ ላለው ጊዜያዊ ሁኔታ አይደለም " አለ ወለል ወለሉን እየተመለከተ።

" አም የዋሔ! ለሩቁ እንጅ ለዛሬው ችግራችን መፍ ትሔ አይሆንም አልክ! ታዲያማ ምናለ፣ የባዕድ ዲቃላህን እስ ክትታቀፍ ድረስ ዝም ብለህ መጠበቅ ነዋ! እኔስ አይዋጥ ልኝም! የሚስቴና የሦስት ልጆቼ የባዕዳን ዲቃላዎች ቤቴን እስኪሞሉ ድረስ ቁጭ ብዬ ማየቱ አይሆንልኝም። ከክፉ ዘር እርሾ ለማስቀረትም አይጠቅመኝም። እኔ አንድ ነጠላዬን የተዋ ረድኩት አንሶኝ፣ የሚቀጥለውን ትውልዴን ክልስ እያሰኘሁ መኖሩ፣ ሳስበው እንኳን ይዘገንነኛል! ሞትን ለምን ብዬ ነው የምፈራው! በመወለዴ መሞቴንም አውቃለሁ። ታዲያ መሞቴ

t.me/OLDBOOKSPDF

ላይቀር፣ ለምን ትርጉም ያለው ሞት አልሞትም? ለምንስ ሚስ ቴና ሴት ልጄ ለተዋረደችበት ወንድ ሁሉ፣ በሞቴ አርአያና ምሳሌ አልሆነውም። እንዲያው ባታከላክሉኝ ደግ ነው " አሉ አባት ከንዴታቸው ብዛት የተነሳ አረፋ መሣይ ምራቃቸው በከንፈሮቻቸው ዳርዳር እየተንዘረበረበ።

"አይሆንም! የርስዎን ቆራጥነት ብቻ አይደለም ማየት! በሆነው ሁኔታ እስኪያልፍ ድረስ፣ እንደሆነው ሆነው መኖር የሚፈልጉ ዘመዶችዎም ይኖራሉና፣ ለነሱም ማሰብ ይኖርብ ዎታል! " አለ አማች ተዳፍሮ!

" አይ! ቆራጥነቴስ የምንፈልገው ስሜት ነው! ግን የቤ ተሰባችንን ሴቶች ያባለገ አንድ ደንቆሮ ወታደር መግደልና መሞት ዋጋ አይኖረውም። የሚፈጥረው ጥቅም ዘለቂታነት የለ ውም። እሱ ሲሞት ሌላ ፎጠናና ትኩስ ወታደር ሊተካ ይች ላል። የሴቶቻችንም ውርደት፣ ሰው ቀየረ እንጅ አላከተመም ማለት ነው። ስለዚህም ነው እኔ መነሳትም ሆነ መቃወም አለ ብን የምለው፣ ሥርዓቱን እንጅ፣ ሥርዓቱ የወለዳቸውን ጥቂት ግለሰቦች አይሁን! " አለ ልጃቸው አሁንም አቋሙን ለማ ስረዳት እየሞከረ።

" እውነቱና ሐቁ ይኸ ይመስለኛል። ግን ሥርዓቱ ስትል ምን ማለት እንደሆነ ለኔ በመጠኑም እንደገና ብታብራ ራልኝ!! " አማች ጥያቄውን በለዘብታ ያቀርባል።

" በግራና በጉልቱኛው መካከል ያለው መሬት-ጠቀስ ፍልሚያ ገና ገፈቱ እንኳ አልተቀመሰም። በላብ አደሩና በከበር ቴውም መካከል ያለው የፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ተግባ ራዊ ፍልሚያ ገና እፍታው እንኳ አልተነካም። በየረድፋቸው ያሉት መሠረታውያን ቅራኔዎች ገና ጥሬ ናቸው። መፈታት

የሆነው፣ በዘመናችን በዓለም ላይ ልዕልናን ለመቀዳጀት ያሰፈሰፈው፣ የዘመናዊው ሪቪዝኒዥም ባለቤትና፣ ሶሻል ኢምፐሬሪያሊስት በመባል የታወቀው የሶቭየት ኅብረት መንግሥስት ነው። ከኢትዮጵያ ጊዚያዊ ሁኔታ ላይ፣ ባለው መንግሥት አንፃር እነዚህን ሦስት ጠላቶች ነጥሎ ማየት አይቻልም። እስከዚህ ድረስ ከተከታተላችሁልኝ፣ ስላለው ሥርዓት እናገራለሁ።

በበዝባዥ መደብ ደጋፊነት የተመሠረተ ማንኛውም መንግሥት፣ ሕዝባዊነት የለውም። ሰፊው ሕዝብ ከጭቆናውና ከርግጫው በስተቀር ከእንዲህ መሰሉ መንግስት ሥልጣንም ሆነ ጥቅም አይጋራም። ኢሕዝባዊ መንግሥትም በመሆኑ የገዥውን መደብ እንዳይቀናቀንበት ሲል፣ በመሠረቱ የሕዝብ የሆኑትን ዲሞክራሲያዊ ነፃነት፣ ዲሞክራሲያዊ መብት፣ ዲሞክራሲያዊ ፍትህ--- ይነፍጋል። ተጋፍተው የሚመጡትንም ያጠፋል። ይህ በመሆኑ፣ በሰፊው ሕዝብና በገዥው መደብ የማያቋርጥ ትግል ይካሔዳል። የኃይል ሚዛን በሚወስነው መሠረት ይህ ትግል አንዴ ይከራል አንዴ ይረግባል። አንዴ ይጠፋል አንዴ ይከስማል። ግን ጨርሶ ሊጠፋ አይችልም። ከዚህ የትግል ሒደግ ውስጥ አንዲቷን መዘን እስክጫፏ ብንደርስ ያቺ የሒደግ ዘለላ ከኛ ቤተሰብ ውስጥ መርታ ታመጣንና በኛና በጠላቶቻችን መካከል ከሚካሔደው ትግል ላይ ታደርሰናለች።

የኔን እናት አክስትና ሦስት እህቶች በገዛ ሀገራቸው በገዛ ሕዝባቸው መካከል የውርደት ጋቢ አልብሶ የሚጫወት ባቸው ላለው መንግሥት አጋር እሆንህለሁ ብሎ በመግባት የሥልጣንና የጥቅም ሙሉ ተካፋይ የሆነው የባዕድ መንግሥት ቅጥር ወታደር ነው። እናቴንም ሆነ የቀሩት ዘመዶቼን ለስሜቴ ማርኪያ ማድረጉ ከጥቃቅን ጥቅሞቹ እንደአንዱ ሊቆ ጠር ይች

ቀርቶ አለሰለሱም። በጊዜያችን የሁለቱም መንፀባረቂያ ሥልተ-ምርቶች በገጠርና በከተማ ጐልተውና ቅልጥጥ ብለው ይታያሉ። ሞፈር ዘመቱ ገበሬ በጅ አዙር አሁንም ከገባርነት ኑሮው አልተላቀቀም። ሰብሉን በማጭድ አጭዶ፣ ከምሮ ይጐትር እንጅ፣ ባመረተው ምርቱ አላዘዘበትም። በሰበብ አሰባቡ ለባዕዳን ሀገሮች ሳይቀር እየተጋዘበት ነው። ላብ አደሩ ሠራተኛ በፋብሪካ እሳትና በእንዱስትሪ ኮሪንቲ እየተቃጠለ፣ በመዶሻው ቀጥቅጦ ያመረተው እቃ ሁሉ፣ ከበርቴው በፈጠረው ሽርክና ለባዕዳን በርካሽ እየተሸጠ፣ ጉልበቱ ባስገኘለት እቃ ራሱም ሆነ ወገኑ ሊጠቀምበት ካለመቻሉ አልፎ፣ ለላቡ የሚመጣጠን ዋጋ አላገኘበትም። ይህ ሁሉ ምዝበራና ብዝበዛ፣ ጉልተኞችና ከበርቴዎች ተባብረው በዘየዱት መላ፣ በዐብዮት ስም፣ አዲስ ጊዜያዊ መንግሥት፣ በሥውር እንዳሉ፣ መቋቋሙን አስነግረው፣ ብዝበዛቸው በአዲስ መልክና አቀራረብ እየተካሔደ ነው። እንደ እባብ ቆዳ ያረጀው ጉልተኛና ከበርቴ ተገልፍፎ ይውደቅ እንጅ፣ አዲሱና አደገኛው ጉልተኛና ከበርቴ በቦታው ተተክቶ ይገኛል። ምንም እንኳ በአርሶ አደሩ ገበሬና በጉልተኛው፣ እንዲሁም በላብ አደሩ ሠራተኛና በከበርቴው መካከል በመፋተግ ላይ ያሉ ቅራኔዎች እድገታቸውን ጠብቀው አንድ መፍትሔ እንደሚያመጡ ቢታመንም፣ ለጊዜውም ቢሆን የቅራኔዎቹን ግለት ያበርዳል በሚል ግምት ጉልተኞችና ከበርቴዎች ከአጋር ባዕዳን መንግሥት ጋር በመደለት፣ እንደራሴያቸውን ሥልጣን ላይ በማስቀመጥ አዲስ ጊዜያዊ መንግሥት አቋቁመዋል። 'ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትም' ይባል 'ደርግ' በሙሉ ተጠሪነቱ ለአዲሱ የጉልተኛና የከበርቴ መደብ ነው። በመካከላቸውም በወሽመጥ ገብቶ የጥቅምም ሆነ የሥልጣን ተካፋይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ላል። ይህንን የማይገባ ጥቅሙን እንዳያገኝ መቆጣ ጠሩም ሆነ መከላከሉ የኛ ግዴታ ነው። በዚህም ረገድ አባቴ የሚያደርጉት የበቀል ዝግጅት ሁሉ ትክክል ነው። ግን የሐረጉ ግንድ እስካለ ድረስ አንዲቷን ዘለላና ቅርንጫፍ ለመቀጭጥ ማቀዱ ብዙ ረብህ አይኖረውም። ስለሆነም ተባብረን ግንዱን መገዝገዝ ብሎም ቆርጦ መጣል ይኖርብናል። ይህ ግንድ ሥርዓቱ ነው። አምባ ገነን ፋሽስታዊ የወታደር መንግሥት ከአጋር ኃይሎች ጋር (ጉልተኛ፣ ከበርቴ፣ ሶሻል ኢምፔሪያሊስት) ያቋቋመው ኢሕዝ ባዊ ሥርዓት ነው። ባጭሩ ሲካተት፣ በማቆጥቆጥ ላይ የሚገ ኘውን ቡርዡዋን፣ ሙጥኛ ብሎ የተቆራኘ፣ የቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ አጋፋሪ የሆነ የፋሽስት መንግሥት ነው። በነጠላ አምባ ገነን መሪ የሚነዳው ያስተዳደሩ ጋሪ፣ በየአቅጣጫው ለከፈተው ጦርነት፣ በገጠርና በከተማ ባሉ ቢሮክራቶች፣ የየቀበሌ ካድሬ ዎች፣ የሠራተኛ ማኅበራት ሹማምንቶች፣ የገበሬ ድርጅት ተጠ ሪዎች አማካይነትና ቀጥተኛ ወኪልነት፣ በአዋጅ የወረሰውን ሀብት ሁሉ ከቍጥጥር ሥር በማዋል ካፒታል ይሰበስባል፣ ቦም ብና ታንክ ይገዛል። ሕዝብ ይገድላል፣ ያርዳል፣ ያቃጥላል። ቅይር ቋንቋ አምጥቼ፣ " የቀኝ ክንፍ፣ የቡርዡዋ ተቀፅላ ነው" ስላችሁ ግር ይላልና በግራዝያኒ ይመራ የነበረው የጣልያን ወረራ በፈጸመው አሠቃቂ ግፍ አንባር፣ የፋሽስትን ትርጉም ይበልጥ እንደምትረዱት በማመን፣ ከዚያ አሥር ጊዜ የሚከ ፋውን የዛሬውን ፋሽስት፣ ከዚያ የጣልያን ፋሽስት ጋር እንድ ታነፃፅሩት ከመጠቆም ይልቅ ሌላ ያገለለጥ ምርጫ ያለኝ አይመስለኝም። በተጨማሪ ልገልፀው የምፈልገው፣ ይህ ሴቶች ወኖቼን ያዋረደ ባዕድ ወታደር፣ ጉልበት ያጥንበትን መሣሪ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያዎች፣ ጠብመንጃም ሆነ ጅፕ ታንክም ሆነ ሮኬት ከየት ያገ ኘው መሰላችሁ? ፋሽስቶች ባቋቋሙት ሥርዓት አማካይነት ከሕዝባችን በየረድፉና በየመልኩ ከሚዘረፍ ሀብት፣ ከሶሻል ኢምፔሪያሊስቶች የተገዛ ነው። ይህን የሕዝባችንን መዘረፍ ተባብረን ማስቀረት ብንችል፣ እንኳን ሴቶቻችንን ቀርቶ፣ የጊቢ ያችንን ዝንብም እሽ ማለት አይችልም! ትሰሙኛላችሁ ---" አለና ረዥም ዲስኩሩን አበቃ።

" ምነው ይሽን ሳላይ ቀደም ብዬ በሞትኩ! " አሉ አባት በትካዜ ባሕር ሰጥመው። ይህ አባባል፣ ብዙዎች ያገራችን የጊዜው አረጋውያን፣ በየዕለቱ የሚናገሩት ነው። መጦር በሚ ገባቸው ዘመን ብሔራዊ ክብራቸው ተገፎ፣ ሽምግልናቸውም ሆነ ዜግነታቸው ተንቆ፣ ከሠፍነግ የመረረ ኑሮ፣ በህይወታቸው መጨረሻ ዘመን ስሊጋጠማቸው በምሬት የሚናገሩት ነው።

ለባላምበራስ ገብርዬ ግን፣ የፊተኛውም ቅድመ ፋሽስት ዘመን፣ የደስታና የፍስሐ ዘመን አልነበረም። በተፈጥሮአቸው ሕዝባዊ ዝንባሌ ያላቸው በመሆናቸው፣ ካለፉትም ባለሥል ጣኖች ጋር ሳይጣጣሙ የኖሩ ናቸው። ከግዞት ባላነሰ ሹመት በዳር አገር ሲንከራተቱ የኖሩ ነበሩ። መሰል የድሮ ጓደኞቻቸው ቢትወደድ፣ ደጃዝማች፣ ሲባሉ፣ እሳቸው ግን ተጀምሮ እስኪ ጨረስ በባላምባራስነት ደረጃ ነው የኖሩት። የወታደሩ ፋሽስ ታዊ መንግሥት፣ በጡረታ መልክ እስካወረዳቸው ጊዜ ድረስ፣ ያንድ አውራጃ አስተዳዳሪ ነበሩ። በአቆርቋዝነት ድምር መዝ ገብ ውስጥ ያስገባቸው እንጅ፣ ባላምባራስ ገብርዬ ጡረታ ወጡ በተባለ ቀን፣ ያውራጃቸው ከተማ ሕዝብ ተኩስ ከፍቶ፣ " እስቲ ማነው አስተዳዳሪያችንን የሚሸርብን! " እያለ አንድ ቀን ሙሉ ሲያንጣጣ ውሏል። " ለሶሻሊስት ትምህርታዊ ጥም

ቀት እንዲካፈሉ እንጅ፣ ተመልሰው ይመጣሉ " በሚል ዘዴ የተነሳውን ዐመፅ አበረደው እንጅ፣ በአስተዳዳሪነት ተወዳጅነ ታቸው ወደር የማይኖላቸውን ባላምባራስ፣ ከአውራጃው እንዲለይበት ሕዝቡ አልፈለገም። በተለይም ባላምባራስን ይበ ልጥ የሚወዳቸው የየባላባቱና የየትልቁ ሰው አንጋች የሆነ ጐሪምላ ሁሉ፣ ወሬሣ ሊመታ ተስማምቶ ዱር እስከመግባት ወስኖ ነበር። ይህ የጎብረተ-ሰብ ክፍል ባላምባራስን እንደነፍሱ የሚወድበት ዋናው ምክንያት የሰውን መሠረታዊ እኩልነት* ላይ፣ የጌቶቻቸውን በቅሎም ሆነ ፈረስ ልጓም ይዘው ግማሽ ቀን ያህል፣ ጌቶቻቸው በእልፍኝ ውስጥ ጠጥተው እስኪረኩ ድረስ መጠበቅ ነበረባቸው። በዚያ አውራጃ ባላምባራስ ገብርዬ ከገቡ ጀምሮ ይኸ ድርጊት አክትሟል። የባላምባራስ አንዱ የት ርፍ ሰዓት ተግባራቸው፣ እንዚህን የጌቶቻቸውን ፈረስ ጠባቂ ምች፣ በራሳቸው ገንዘብ እየጋበዙ ከጌቶቻቸው እኩል አስቀም ጠው ማስተናገድና፣ በየመጠጥ ቤቱ ደጃፍ ላይ ሁሉ የፈረስና የበቅሎ ማሠሪያ ምሰሶ ማስተከል ነበር። ከዐመት ቆይታም በኋላ፣ ይህ ጌቶችና አሽከር፣ አብረው በእኩልነት የመጠጣቱ ጉዳይ የተለመደ ተራ ነገር መሆን ችሏል። ባላምባራስ፣ ለዚህ ድርጊታቸው ቅመም እንዲሆን በማሰብ፣ በየመጠጡ ቤት ለዚህ ተግባራቸው በተለማሩ ቁጥር የሚያስገቧት አንዲት ዜማ ነበረ ቻቸው፣

" ጌቶችም ቢሆኑ እንደኛው ሰው ናቸው!
እሜቴም ቢሆኑ እንደኛው ሰው ናቸው!
ከኛ የተለየ ምን አግር አላቸው?

* (የተዘለለ)— በጥቃቅን ምክሴምቶ ሳይቀር፣ ስላላየችና ስላስተማሩት ነው። ወትሮ በየጠጡ ቤትና በየመሸታ ቤቱ ደጃፍ.....

t.me/OLDBOOKSPDF

ከኛ የተለየ አራት እጅ የላቸው?
በባሕርይ እንጅ የምናከብራቸው!!" ይሏታል በአራራይ ዜማ።

ባላምባራስ ገብርዬ፣ በሚያስተዳድሩት አውራጃ ሕዝብ በጣም የተወደዱና የተከበሩ በመሆናቸው፣ አንድ ቀን ሕዝቡን ያሣምፅና ያስነሣብናል በሚል ፍራቻ ብቻ በጡረታ ተገልለው እግድ የተጣለባቸው አዛውንት ናቸው። ማእከላዊ እድሜአቸ ውን አገባደው፣ ወደ ሽምግልና ዘመናቸው የገቡ ትክክለኛ ሰው ናቸው።በዚያ ዘመን ሁሉ የሥልጣን ጊዜያቸው፣ የወደሮ መሬት እንኳ በርስትነት የላቸውም። ሌላው ቀርቶ፣ በአውራ ጃው ውስጥ በአስተዳዳሪነት የኖሩት፣ በራሳቸው ገንዘብ በተከራ ዩት መለስተኛ ቤት ውስጥ ነው። መተያያም ሆነ ጉቦ ሲያል ፍም አይነካቸው። የሚያደርጉት ውሳኔ ሁሉ፣ ሕዝቡ መርጦ በሰየማቸው የጉባኤ አባሎች የሚጸድቀውን ብቻ ነበር። ላጠ ቃላይ ስብሰባ ጠቅላላውን ያውራጃ ሕዝብ የጠሩበት ጊዜ ጥቂት አልነበረም። የያኔው ማዕከላዊ መንግሥት ያልፈቀደ ላቸው ሆኖ ነው እንጅ፣ ከበጐ አድራጊ፣ ገለልተኛ መንግ ሥታት እርዳታና ብድር በቀጥታ በአውራጃው ስም በመጠየቅ፣ ያውራጃቸውን ሕዝብ ኑሮ ለማሻሻል ያልሞከሩት መንገድ የለም። አንዱ የሚያበሳጫቸውና ካለፈው መንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር ሲያናቁሯቸው የኖረው የዚሁ ሕዝባዊ እቅዳቸው አለመሣካት ነው። ከማስተዋልና ከኑሮ ከቀሰሙት እውቀት በስተቀር መደበኛ ትምህርት የላቸውም። በጐ ፈቃ ድና ቅን ሐሳብ በባሕርያቸው ላይ የሠፈነ በመሆኑ፣ አለመማር የሚፈጥረው ጥቁር ጠባይ በሳቸው ላይ አልሠረፀም። በሥል ጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ፣ የግል ኑሮአቸውና ትዳራቸው

ትዝም ብሏቸው አያውቅ። ያውራጃ ሕዝባቸው በየረድፉ ሊያድግ የሚችልበትን መንገድ ከማውጠንጠን በስተቀር፣ ሌላ ነገር የሚያስቡበት ጎሊና አልነበራቸውም። ሌላው ቀርቶ፣ በበዓልም ሆነ በተራ ቀናት የሚለብሱት ልብስ ልዩነት የለ ውም። በቅርቡና ባጠገቡ ተገኝቶ፣ የሕዝቡን ችግርና ብሶት ለማቃለል ሲሉ፣ በየሚጢጢዋ ቀበሌና ወረዳ ሲዘዋወሩ፣ በአውራጃ ቤታቸው የሚገኙበት ወቅት በጣም አጭር ነበር። እንደውም ቤተሰባቸው፣ ከመለያየት ቆይታ የተነሳ፣ የሚነፋ ፈቁበት ጊዜ አለ። ለሚያስተዳድሩት ሕዝብ፣ ዘመኑ ከፈቀደ ላቸው የበጉ ፈቃድ መጨረሻ ክልል ድረስ፣ ካንጀታቸው ርዳታ አድርገውለታል። አንዳንዴም ክልሉን እየጣሱ በመገኘ ታቸው፣ በበላይ ባለሥልጣን ተጐሽመዋል፣ ተኰርኩመዋል። ከነበራቸውም ሥልጣን እንዲባረሩ፣ ካንድ ሁለት ጊዜ ያህል ተወስኖ፣ በራስ እምሩ አማላጅነት ታልፈዋል። ከአውራጃ አስተ ዳዳሪነት ምድብ ሥራቸው ሌላና፣ ጠቅላይ ግዛቱና የሀገር ግዛት ሚኒስቴር ከሚሰጠው የሥራ መምሪያ ክልል ውጭ፣ ምንም ዓይነት ተግባር እንዳያከናውኑ፣ ጥብቅ ትእዛዝ በየጊ ዜው ቢተላለፍባቸውም ቅሉ፣ ባለምባራስ ግን ሕዝቡን በየእቅ ጣጫው እያስተባበሩ ለልማትና ለእድገት እንዲሠማራ በማድ ረግ፣ ተዝረክርኮ የኖረውን የአውራጃውን ጎብረታዊ ተግባር ሥርዓት አሲዘውት ነበር።

አውራጃው በራሱ አስተደደር እንዲመራ አዘውትረው በመወትወታቸው፣ ማዕከላዊው መንግሥት በጣም ይፈራቸው ነበር። ለዚህም ፍራቻው ሲል ነው ከሦስት ያላነሱ ምክትል አውራጃ አስተዳዳሪዎች ሾሞ፣ ባለምባራስን እንዲቈጣጠሩ ያደ ረገው። ባለምባራስ ግን፣ በየገጠሩ እተየተዘዋወሩ ከገበሬው

t.me/OLDBOOKSPDF


ቤት በማረፍ የሚበላውን እየበሉ፣ የሚጠጣውን እየጠጡ፣ የቅ ርብ ችግሩን እየተወያዩ ከጭብጥ ሁኔታ በመረዳት፣ የሚመ ጡትን ያህል ሊረዱት ባይችሉም፣ ለችግሩ ጊዜያዊ መፍትሔ ከመስጠት አልተቆጠቡም። የዘለቄታ መፍትሔው ምን መሆን እንዳለበት ቢያውቁም፣ በተግባር ለመግለጽ፣ ካቅማቸው በላይ በመሆኑ ምን ጊዜም ያገሱ ነበር። ሆኖም ያውራጃውን ሕዝብ በጎብረት እርሻ ለማሠራት የቻሉ፣ የመጀመሪያ አስተዳዳሪ ናቸው። ምናልባትም ለዚህ ውጤት መብቃታቸው፣ በሚያስተዳድሩት አውራጃ ውስጥ የነበረው የመሬት ሥሪት የዘር ርስት የሚባለው ዐይነት በመሆኑ፣ እንደሌላው ክፍለ ሀገር፣ የገባርና የጉልተኛ (ጪሰኛና ባላባት) ቁርቋሶ ስለሚያፅዕበት ይሆናል። በዚህና በዚህ መሰል ድርጊታቸው፣ በአውራጃው ሕዝብ ከፍተኛ ተወዳጅነት አፍርተዋል። ከመወ ደዳቸው ብዛት የተነሣ፣ ከሕፃን እስከ ሽማግሌ፣ ለማረጋገጫ የሚጠቀምበት መሐላ ሁሉ የሳቸው ስም ነበር።

በሀገራችን ለውጥ እንዲመጣ ከፍተኛ ምኞት ከነበራ ቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ ባለምባራስ ነበሩ። ራሳቸው መሥ ራት እንኳ ባይችሉ፣ የሚሠሩ ሰዎች ተመርጠው፣ ያዲስ ሕይ ወት አዲስ ልማታዊና እድገታዊ ትርዒት ማየት ደስታቸው ነበር። በወርኀ የካቲት፣ የተመመው ሕዝብ፣ የለውጥ መፈክ ሩን ይዞ ሲነሣና፣ አሮጌ ሥርዓት ሲያናጋ በመመልከታቸው፣ ደስታ ፈንቅሏቸው፣ ታመው የማያውቁትን፣ ሁለት ቀናት ያህል አልጋቸው ላይ አሣልፈዋል። ይህ በሆነ በዓመቱ ነው፣ ከእስረኛነት ባልተሻለ ሁኔታ፣ በጡረታ ተገልለው፣ ያዲስ አበባን ከተማ ክልል እንዳይወጡ ታዘው፣ በሚኖሩበት ቤት እንዳሉ፣ አዲሱ መንግሥት ያመጣውን ግፍ እየኰፈነናቸው በመቅመስ ላይ ያሉት።

በሀገራችን ጥንታዊ ባህል መሠረት፣ በቁርባን ያገቧቸው ሞንዳላ ባለቤታቸው፣ ባላምባራስን በዐለም መገኘታቸው ከሚያስደስታቸው አንዱ ምክንያት ናቸው። ተፈጥሮ፣ በልዩ ጥበባዊ ኪነቷ፣ ውበትን ደርባ ሠልሣ ስትስልባቸው የኖረች ይመስላሉ። ያያቸው ዐይን ሁሉ በውበታቸው ተደናግጦ፣ ላጭርም ጊዜ ቢሆን ይንሸዋረራል። ተፈጥሮ ተጨንቃ ስትሠራቸው ለመኖሯ፣ ደላንታዊ አፍንጫቸው፣ ዋድላዊ ከንፈራቸው፣ ኰረማሽ ጉንጮቻቸው፣ አዘዞ ሽንጣቸው፣ ጉልሀ ምስክሮች ናቸው። ረዥሙ ሐርማ ፀጉራቸው፣ አስር ሺህ የተራቆተ ጐልማሳን፣ ከነስሜቱ ያለብሰል። ስለአቋማቸውና አረማመዳቸው መናገር ከንቱ ነው። ለሰዎች ያልተሰጠ ልዩ ተውህቦ ነው። ባላምባራስ፣ እኝህን መሳይ ባለቤት ለማግኘት የበቁት፣ በጣልያን ጊዜ በፈፀሙት ጀብዱና በአስገኙት ከፍተኛ ዝና አማካይነት ነው። አለያ ወይዘሮ የውብዳርን ማግኘት ቀላል ትግል ብቻውን አይበቃም ነበር። አብረው በኖሩበት ዘመን፣ ፍቅር በቤተሰባቸው ውስጥ ድንኳኗን ጥላ፣ ፍስሓና ደስታን አስፍና ከመኖሯም በላይ፣ ያራት ብርቅዮች ልጆች ባለቤት አርጋቸዋለች። ሲዋደዱና ሲከባበሩ ላያቸው ሰው፣ ምነው እነሱን ባረገኝ እስከማለት ያስቆጫሉ፣ ያስቀናሉም። ሦስት የመጀመሪያ ተከታታይ ልጆቻቸው ሴቶች ሲሆኑ፣ አረተኛውና የመጨረሻ ልጃቸው ወንድ ነው። እነሦስቱን እናታቸውን አይቶ ማየት ነው። ዘመናዊውን ሜክአፕ እየጨመሩበት፣ ከናታቸው አስበልጠው ፍፁም መላእክት አስመስሏቸዋል። ሁሉቱ የተዳሩ ሲሆኑ አንደኛዪቱ ገና ናት። የመካከለኛዪቱ ልጅ ባል፣ ባልታወቀ ምክንያት ተገድሎ ከሞተ ስድስት ወራት አልፎ

t.me/OLDBOOKSPDF

ታል። በፀረ አብዮት ተሳቦበት፣ በባእድ ወታደሮች በጩቤ ተዘክዝኮ፣ አይሞቴ ሞት እንደሞተና በዚያው በሞተበት ምሽት መኪናውም ተቃጥላ መገኘትዋ፣ ላዲስአቦች ያደባባይ ትንግርት ሆኖ እንደታሪክ የሚነገር ግዳይ ተደርጓል። የሞተበት መሠረተ ምክንያት ግን እንደተባለው በፀረ ዐብዮትነት ሳይሆን፣ ውብ ሚስቱን ለማስከበር ባደረገው ቆራጥ ሙከራ ነው። ሚስቱ ሁለተኛዪቱ የባላምሪስ ልጅ ስትሆን፣ የሦስት ውብ ልጆቻቸው ኰከብ ናት። ባሏ ከሞተ ጀምሮ የምትኖረው ከባሏ ገዳይ ጋር ነው። ይህም የውዴታ ሳይሆን የግዴታ ነው። ይኸው አስገዳጁ የባዕድ ወታደር፣ በሷ አሳቦ፣ ጠቅላላ የቤተሰቧን ሴቶች፣ እክስቷንም ሳይቀር ወሽሞ በፈለገው ሚና እየጎዳቸው ነው። ትንሿን ሴት ልጅ ገፈርሳ በሚገኝ ቪላ ውስጥ ቅምጥ አርጓት ዐመታት አልፈዋል። የአክስቷን ባል በፀረዐብዮት ስም አራተኛ ክፍለጦር ውስጥ፣ ያላንዳች ፍርድ አሣስሮ፣ የባል ያህል ካክስቷ ቤት ይወጣል ይገባል። እናታቸውን ሲፈልገው በስልክ፣ ሲያሻውም ከቤታቸው ደጃፍ እየመጣ፣ ያመላልሳቸዋል። አንድ የቀረችው የመጀመርያ ልጃቸው ነበረች፣ እሷንም ከባሏ ላይ ጠልፎ በመውሰድ፣ ነፋስ ስልክ ከሚገኝ ከአንድ ደጃዝማች የተወረሰ ቪላ ውስጥ ካስቀመጣት ሣምንት ሆኗታል። ስለተጠለፈች ሚስቱ ለመወያየት መጥቶ ነው፣ አማች ካባቷ ቤት እንዳለ፣ ቀደም ሲል ሲነጋገሩ ያገኘናቸው። በዚያን ቀን፣ ልጅ፣ አባት አማች ሆነው ባንድነት የጦፈ ውይይት በማካሔድ ላይ እንዳሉ፣ የጅፕ መኪና ጥሩምባ፣ ከውጭ፣ ሦስቱም ይሰማሉ። እንደለመደው እናትን ሊወስድ፣ መጥራቱ ነው። አባትና ልጅ ጥሩምባውን ለምደውታልና፣ ይኸውልህ ሊወስዳት መጣ! ብለው ለአማች ይነግሩታል። አማችም "እስቲ ስለሚስቱ ሁኔታና ደኅንነት ልጠይቀው! መቸም ከሱ ሌላ



ችካል

ተክለው የማይተውት፤ተቸክሎም ላይቀር፤
በነጋ በጠባ፤ መሮጥ ለመቀርቀር፤
ሞራል ኤቲክስ ገድሎ፤ ያን ስሜት ለማክበር፤
ሙስናን አንግሦ፤ ጎሊናን ለመቅበር፤
አለ ሲያደዘድዝ፤ ሲያሽቃብጥ በሀገር፤
አረም በቀል እንጨት፤ ከመራጃው ጭምር፤
ችካሉ ናዚራ፤ የወሲብ ድንብርብር!!

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚደፍረን የለም!" ብሎ፤ ደመ-ነፍሱን የሳሎኑን በር ከፍቶ፤ ወደ ዋናው አጥር በር ያመራል።

" ባትዋረድ ደግ ነው!" አለ የባላምባራስ ልጅ፤ የሳሎኑን መስኮት ከፍቶ ወደ አማቹ እያቀና።

" ደኅንነቷ ብቻ ለመጠየቅ ነው! " አለ አማች የሚስቱን አቃጣይ ፍቅር፤ ውስጥ ውስጡን አንፍሮት ማልቀስ እየቃጣው።

የውጭውን በር ከፍቶ እንደወጣ፤ መረመንድ ግንድ የሚያህል ሰው፤ ጅፒን ተደግፎ ከውጭ ቆሞ ያገኛል። ዐይኑ ላይ ጥቁር መነጥር ገትሯል። በቀኝና በግራው ሽንጡ ላይ ከጠመንጃ የሚስተካከሉ ሁለት ሽጉጦች ታጥቋል። ያደረገው ጫማ ቅልጥሙን በሙሉ ሸፍኖ ከጉልበቱ ሎሚ ይደርሳል። የለበሰው ኧጉርጉር ነብርማ ካኪ ሲሆን፤ ጐፈሬውን የምትሚገት ኰፊያ ራሱ ላይ ጣል አርጓል። ሥንዝር የሚያህል የትንባሆ ሲጋር አፉ ላይ ለጉሞ ጢሱን ያቦናል። ደረቱ ላይ ያለው ፀጉር እመጫት ድመት ከነልጆቿ ይደብቃል። ካንገቱ ሥር፤ ያልተደረደረ የወርቅ፤ የብር፤ የነሓስ ጌጣ ጌጥና ሐብል አይገኝም። ከግራ እጁ ላይ ቋጥኝ የሚያህል ሰዓት አሥሯል። ከሰዓቱም አጠገብ አምባሮች ተደርድረዋል። አስሩም ጣቶቹ በተሸከሙት የቀለቤቶች ብዛትአለመድከማቸው መጥኔውን ይስጣቸው።ደረቱ ላይ፤ ያቡነ ሰላማን ጢምና ሪዝ የሚስተካከለውን የዕንቶኔን ገፅታ የሚያሳይ ምስል ለጥፏል። በዚህ ሁኔታ ከባላምባራስ ደጃፍ ላይ እንዳለ ነው፤ አማች ሆዬ ሲፈራ ሲቸር ለማነጋገር የከጀለው።

" ጉድ ሞርኒንግ ሰር " ይላል እንደባሕሉ እጅ እየነሳ አማች፤

“ የስ ጉድ ሞርኒንግ! ” ይላል ከግልምጫ ጋር፣ ወታደሩ!

“ አይ ሀቭ ኤ ፕሮብሌም ” አለ አማች እየተሽቆጠቆጠ

“ ሁዋት ፕሮብሌም? ” አለ ጥምባሆውን በብዛት እያቦነነ

“ ማይ ዋይፍ ኢዝ ሎስት ” አለ አማች ሚስቴን መልስ ልኝ በማለት ፈንታ።

“ አር ዩ ክሬዚ! ሺት! ” ሲጋሩን አጭሶ ሊጨርስ ነበ ረና፣ ቀሪዋን ቁራጭ ይወረውርበታል። ወደ አማችም ይበልጥ ቀረብ ብሎ “ ጐ አንደ ቴል ቱ ቤንጂስቶ! አይ ዶንተ ኬር!” አማችን አንድ ካልቾ አቅምሶ ካጠገቡ እንዲሄድ ያዘዋል።

አማችም በሁኔታው ተደናግጦ ወደ መጣበት ሊመለስ በሩን ሊከፍት ሲል፣ የባላምባራስ ሚስት ተዘጋጅተው ሲወጡ ያጋጥመዋል። ይህም ሁናቴ ተጨማሪ ማስደንገጫ ሆነበት፣ እናቴ እንደጠፉችበት ሕፃን፣ እሪ ብሎ ሲጮህና፣ ጅፔ አማቴን ጭኖ ይዞ ሲሔድ እኩል ይሆናል። ጩኸቱን የሰሙ አባትና ልጅ ከቤት ሮጠው ቢመጡ፣ አማቻቸው፣ የቀጠቀ ጡትን ያህል ተዝለፍልፎ ደጃፍ በመውደቅ ሲያላዝን ያገኙ ታል፣ ደጋግፈው ከቤት ካገቡት በኋላ፣

“ ነግሬህ ነበርኮ! ” አለ ልጃቸው። አማች ግን ሊያዳ ምጠውም አልቻለም። ትንሽ ቆይቶ ነፍሱን ሲዘራ፣

“ ባላምባራስ ትክክል ናቸው! ” አለ እቅታ እየሞ ከረው።

“ አሁን ገባህ መሰለኝ!” አሉ ባላምባራስ እየተኰራሩ!!

“ እኔና ርስም እንበቃለን። ሐረጉን እንቆርጣለን። ልጅም እንደሚለው፣ እሱም ግንዱን ይቀረጥ! ” አለ ንዴትና ብስጭት በሸፈነው ለቅሶ እየተንሠቀሠቀ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ ጥሩ፣ ሁለታችንን አያቅተንም! አፈር እናስግጠ ዋለን!” አሉ ባላምባራስ፣ በስተኋላ ሐሰባቸውን የደገፈላቸውን አማቻቸውን እያፅናኑ። ታዲያ ማውደም ያለብን እሱን ብቻ ሣይሆን፣በሚረጨው ገንዘቡ ባሪያው ያረጋቸውንና የኛን ቤት ሴቶች ጠቁመው ያሳዩትን ካድሬዎችና የቀበሌ ሹሞች ጭምር ነው ” አሉ ባላምባራስ፣ በንዴት።

“ እርስም እንዳሉ! ቁርጥም ቁርጤ ነው! ” አለና ተስ ማሙ። በዚያንው እለት መንፈቀ ሌሊት ላይ፣ ሚስታቸውን ወደ ቤታቸው ሊመልስ ሲመጣ፣ በጐራዴና በጦር ሊበቀሉት ወስነው፣ ቀኑን ሙሉ ዝግጅት ሲያካሒዱ ዋሉ። እቅዳቸውም እሱን ካረዱ በኋላ፣ ወደ ጠቋሚ ካድሬዎችና የቀበሌ ሹማም ንት ቤት ሌሊቱን ለመሔድና ተመሳሳይ ግዳጅ ለማከናወን ነበር። ግን ምን ይሆናል፣ በዚያን ዕለት ማታ በአማቻቸው ልፍስፍስነት እቅዳቸው ሁሉ ከሸፈ፣ የባላምባራስ ጐራዴ ብቻ፣ የወታደሩን ጆሮ ግንድና ግራ ዓይን ሲበቀል፣ አስከትሎት መጥቶ የነበረው የወታደሩ ጓደኛ፣ ተወልደው ባደጉበት፣ ተድ ረው በወለዱበት፣ በገዛ ሀገራቸው ከተማ፣ በተፈጠሩበት ምድር፣ በኖሩበት ቤት ደጃፍ ላይ፣ ባላምባራስን የሽጉጥ ጥይት አርከፍክፎባቸው ጠላታቸውን ሳይገድሉ ወደቁ። ተገደሉ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም፣ ምድረ ወታደር፣ ምድረ ነጭ ለባሽ ግቢያቸውን ወረረው። አማቻቸው በጥይት ቆስሎ፣ ከነ ጦር ኤግዚቢቱ ተያዘ። የባላምባራስ ሬሳም ለምርመራ ተወ ሰደ። እቤታቸው የነበረ ሰው ሁሉም ሲያዝ፣ ያ ልጃቸው ብቻ፣ በማይሰሳ እቅዳቸው ቀንም ቢሆን አልተስማም ነበርና እምልጧል። እስከዛሬም ይኑር ይሙት አይታወቅም፣ ተፈልጎ አልተገኘም። በማግሥቱም፣ ጋዜጣውም ሬድዮኑም ቴለቪዥ

ኑም በሙሉ ባለምባራስ ባለምባራስ ሽተተ። የለየላቸው አድኃሪ! ታዋቂውን ተራማጅአጋራችንን ሊገድሉ ሲሞክሩ ተገደሉ አለ። በምሽቱም ፕሮግራም ላይ፣ ሊገደል ሙከራ ስለተደረገበት የቅጥሩ ወታደር ዝናና ታሪካዊ ተግባር መግለጫ ተነገረ። ስለ ሶሻሊስት ዲስፕሊኑ፣ ስለ ኢንተርናሽናል ሰብዕናው ወደር የማይገኝለት ተራማጅ ወታደር ስለ መሆኑ ተተረከ።-------

ይህ ወታደር የኢትዮጵያን ዐብዮት ለመጠበቅ ከውጭ የመጣ "ተራማጅ" ነው። የሻለቃነት ማዕርግ አለው። ስሙ ሻለቃ ፔርኖ ይባላል፣ ሻለቃ ፔርኖ በጮሌነቱና በደፋርነቱ በሩሲያውያን ከፍተኛ አማካሪዎች የታወቀና፣ አንጐላ በነበረበትም ዘመን በወሰዳቸው የጨካኝነት ግዳጆቹ ዝና ያተረፈ በመሆኑ፣ በሹመት መልክ ተዛውሮ አዲስ አበባ ከመጣ ዐመታት አልፈውታል። የመናገሻይቱን የአዲስ አበባ ከተማ ፀጥታና ዲስፕሊን የማስከበር ኃላፊነት የተሰጠው፣ ከበላይ ሊቆምበር ቤንጂስቶ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በፈለገው ጊዜ የማድረግ መብትና ሥልጣን ያለው የውስጥ ባለሟል ነው። ለከተማይቱ ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ፣ ያሻውን ሁሉ ሲያደርግ የራሽያ ከፍተኛ አማካሪዎች ሁሉ ሳይቀጥሩ፣ የውሳኔው ተገዥዎች ናቸው። በቀዩ ሽብር ጊዜ ባስገደለው ታጋዮች ቁጥር ብዛት ከበላይ አካል ሊቆምበርና ከብሬዥንቭ እንዲሁም ከሀገሩ ልዩ ልዩ ሽልማቶች ተበርክተውለታል። በየቀበሌው የግሉ ወኪሎች አሉት። በእበላይነት ያሠፈሠፉትን ምድረ ካድሬዎችና የቀበሌ ሹሞች እንደፈለገው ያዛቸዋል። ይነዳቸዋል!

አንዳንድ የዋሐን ያዲስ አበባ ነዋሪዎች ብሶታቸውን ሊያቃልል የሚችል እየመሰላቸው፣ በደላቸውን ለማመልከት

t.me/OLDBOOKSPDF

በሔዱ ቊጥር፣ " አድኃሪ ነህ ይበልህ! አቆርቋዥ ነህ፣ መደብ ደቡ ደግ አርጓል! " የሚል መልስ በመስጠት፣ በጥፊ መልውሎ ይመልሳቸዋል። መጠጥ ቤት ገብቶ ወይም ከሱቅ እቃ ገዝቶ፣ ዋጋውን ቢሞት አይከፍልም። ደፍረው የሚጠይቁት ሲኖሩ " ሔዳችሁ ቤንጂስቶን ጠይቁ! " የሚል በትዕቢት የተወጠረ መልስ ይሰጣቸዋል። ትክክል አለመሆኑን ለመግለጽ የሚሞክር ሰው ባገኘ ቊጥር፣ ቢፈልግ ያስደበድበዋል፣ ከፈለገም ላልተወሰነ ጊዜ ያሣስረዋል። ተናዶ ዐይኑን ያፈጠጠ እንደሆነ፣ ዘሎ ለመዋጥ ያደባ አዞ ምሥጋን ይንሣው። ምን አለፋችሁ፣ ያላመረረውና ያላለቀሰበት፣ ድፍን ያዲስ አበባ ሰው አይኖም። በተለይም ያዲስ አበባ ሴቶች፣ በተለይም ያዲስ አበባ ልጃገረዶች--- በሥጋቸው ብቻ ሳይሆን፣ በነፍሳቸው ጭምር ነው ያላገጠባቸው።

ሻለቃ ፔርኖ፣ የክልስነት መልክ ያለው የስፓንሽ ዲቃላ ነው። ጥሩ ስፓንኛና ፈረንሳይኛ እንግሊዝኛ ካገሩ ቋንቋ ጋር መናገር ይችላል። ባገሩ፣ የኤለመንተሪ ትምህርት የጨረሰና በዘመድ ረዳትነት ሥልጣን አግኝቶ፣ ወደ ውጭ የተጓዘ ነው። አንጐላ ውስጥ በነበረበት ጊዜ ብዙ የመግደል ሙከራዎች ተደርጐበት ነበር። አዲስ አበባም ቢሆን፣ ሥስት ጊዜ ተሞክሮበት ለጥቂት አምልጧል። ለጥበቃ እንዲያመች ተብሎ፣ አራት ቦታዎች እየተዘዋወረ እንዲኖር ጥሩ ጥሩ ቪላዎች ተሰጥተውታል። ዋና መቀመጫ ሔድኳርተሩ ለላይ ኛው ቤተ-መንግሥት ጐረቤት የሆነው ከሒልተን ሆቴል ነው። የፈለገውን ማድረግ እንዲችል፣ ሊቆምበር ነኝ ባዩ፣ ልዩ ሥልጣን ሰጥቶታል። በዚህም ሥልጣኑ፣ ባዲሳቦች ላይ ከሽንት አልፎ አርቶባቸዋል። በእምቢታ ያስቸገሩትን ቆነጃጅት

ሲገል፣ ቍጥሩ ከመቶ ይጠጋል። ሊቋቋሙት የሞከሩትን ሁሉ “ አድኃሪ ኤለመንት ነው! ” እያለ እንዳሻው መንጥሯል። በዚሁ ሰበቡ አማካይነት በመጠቀም፣ በየአሥር ቤቱ የሚያማ ቅታቸው የቆንጃጅት ባሎች ቍጥሩ አይታወቅም። ምን አለፋ ችሁ፣ በአዲስ አበባ ውስጥ፣ ከበላይ አካል ልዩ ሹሞች ይልቅ በጣም የሚፈራው፣ ሻለቃ ፔርኖ ነው።

እንዲውም አንድ ቀን፣ ሁለቱም በለመዲት ሴት ተጋ ጭተው፣ ሻለቃ ፔርኖ፣ ሊቀምበር ን “ ክብርህን ብትጠብቅ ይሻላል! የሥልጣኑ ኃይል ቍልፍ ያለው በኔ እጅ ነው! ብንከባበር ይሻላል! ” የሚል ማስጠንቀቂያ ከሰጠው ወዲህ፣ ባፕኘው ቍጥር ሲሽቆጠቆጠለት ሌላ ነው አሉ። ከቶውንም የቅርብ ጊዜው አነጋገሩ “ ሒድና ለቤንጂስቶ ንገር! እኔ የምፈራው መሰለህ! ” ሆኗል፣ የልቡን ሠርቶ የሚያማርርበት ሰው ባጋጠመው ቍጥር ነው ይህን ማለት የጀመረው፣ ባላም ባራስ ግራ ዐይኑና ግራ ጆሮውን በጐራዴያቸው ከሰሉት ወዲህ፣ ይህ የደረሰበት አደጋ፣ ለአብዮታዊነት ግዳጁ እንደ ከፍተኛ መሥዋዕትነት ተቆጥሮለት፣ ከብሬዥኖቭ በመሪው በኩል በተቀዳጀው ታላቅ የኢሻን ሽልማትና፣ ባፕኘው የኰሎኔልነት ማዕርግ ነው። የደረሰበትንም ከፍተኛ የአካል ጕድለት ለመታ ከም፣ ልዩ የቀዶ ጥገና ስፔሲያሊቶች በብሬዥኖቭ ታዘውለት፣ ለሦስት ወራት ያህል በሞስኮ የታወቀ ሆስፒታል ሲታከም ቆይቷል። ሐኪሞቹም፣ የባላምባራስ ስል ጐራዴ፣ በስላች የጐረዳቸውን ግራ ዐይንና ግራ ጆሮ መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል ብዙ ጥረት ቢያደርጉም ሊሳካላቸው ባለመቻሉ፣ በፍ የል ወጠጤ አዋጅ በዚያን ሰሞን ከተረሸነ ያንድ ተጋይ ራሳ ላይ የተወሰደ፣ ትኩስ ዐይንና ጆሮ በቀዶ ጥገና ጥበብ ተተክ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቶለት ከዳነ በኋላ፣ ሀቫሬ ለወራት ጊዜ ያህል ረፍት ሲያረግ ቆይቶ አዲስ አበባ ተመልሷል። ሥጋው ከሥጋ፣ ነርቩ ከነርቭ ጎብሩ ከጎብር፣ መጠኑ ከመጠን ሊመሳሰልለት ባለመቻሉ፣ በቀዶ ጥገ ናው አማካይነት የተተካለትን የታጋይ ጆሮና ዐይን ለመሸፈን፣ ልዩ ባርኔጣና ልዩ መነፅር ተሠርቶለት፣ መነፅሩ ገት ሮና ባርኔ ጣውን ቀሥሮ፣ መላ አዲስ አበባን፣ ከንጦጦ እስከ ቦሌ፣ ከገፈርሳ እስከ ኰተቤ፣ ከመቸውም በበለጠ ፍጥነት ሲያስስ ይውላል። የሚፈጽመውም ግፍና ጭከና፣ ከወትሮው ከሮ፣ እጥፍ ድርብ ሆኗል። ዛሬ በአዲስ አበባ፣ የኰሎኔል ፔርኖን የግፍ ፅዋ፣ መጠኑ ይለያይ እንጅ፣ ያልቀመሰው ሰው አይኘም። አዲስ አበባም፣ እንደፈለገው የሚምነሸነሽባት አዲስ አበባው ሆናለታለች። ማን አለብኝ ብሎ፣ ልቡ ያበጠበትና ደረቱ የተነፋበት ደንቆሮ የባዕድ ወታደር፣ በዚያ ክቡር ሕዝብ መካከል ተኵሶ፣ ተከብሮ ለዘመናት ያልኖረውን ያህል፣ ብሔራዊ ክብሩን በመድፈር፣ ያልዘለለው፣ የባሕል ዕድሞ፣ ያልተራመደው፣ የኢኮኖሚ ግንብ፣ ያልጣሰው ሰብአዊ የፍትህ፣ የመብት፣ የንግነት፣ የእኩልነት አጥር አይኘም። ይህን ማየት አንችልም ያሉ ኢትዮጵያውያን ልጆቿ ታርደዋል ወይም ተሰደዋል። ሁሉ ያልፋል፣ በማለት ተስፋ ያረጉም እየተረገጡ አሉ። ይህን ብሔራዊ ውርደት ለመቋቋምም ጥቂቶች ጫካ ገብተዋል። አልተቋጨም እንጅ፣ በከተማም ሆነ፣ በገጠር፣ ፔርኖ ና አምላኪዎቹን ባፍ ጢም ለመድፋት፣ ሁልጊዜ ትግላዊ ሙከራ እንዳደረጉ ናቸው። አንድ ቀንም በቀዶ ጥገና የተተካለትን፣ የታጋይ ዐይንና ጆሮ ነዳ ለማውጣት ብቻ ሳይሆን፣ እንዲያ በኢትዮጵያውያን ጭቁን ሕዝቦች ላይ እንዲጫወት የፈቀ ደለትን የፋሽስት ሥርዓት፣ ከነቁንጮው ጭምር፣ ገነጣጥሎ እንደ ሚጥል፣ ታሪክ የሚከስትለት የታጋዩ ኢትዮጵያዊ የትግል

እውነት ነው። ይህ ታሪካዊ ክሥተት ነገ የምናየው ድላዊ ሐቅ ነው።-----

ባላምባራስ ገብርዬ፣ ከጉዛ ደጃቸው ላይ፣ በአረመኔው ጥይት፣ በግፍ ተደብድበው፣ ለሞት ሲያጣጥሩ በነበሩበት ወቅት፣ አንድ ከፍተኛ ኃይለ ቃል ተናግረዋል። ይኸውም የሚከተለው ነበር፣-

" ያለፉት ኢትዮጵያውያን አባቶቼ፣ ያለፈው ትውልድ ያገሬ ሕዝቦች፣ ይህን መሳይ ባዕዳን ወለድ ውርደት እንዳይደርስባቸው በመጠንቀቅ፣ ባላቸው አቅም ሁሉ፣ በደማቸውና ባጥንታቸው ሲከላከሉ ኖረዋል። ዮሐንስ በመተማ፣ ቴዎድሮስ፣ በመቅደላ፣ ምኒልክ በአድዋ የተጋደሉት፣ ይህ የሀገራችን ብሔራዊ ክብር እንዳይጣስ ነበር። የሕዝባችን ብሔራዊ ባሕል እንዳይደፈር ነበር። አዲሱ ትውልድ፣ ዘውድ በመጫናቸው ብቻ ሊያክቸለችላቸው ቢቃጣም፣ ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን ከብሔራዊ ክብሩና ከብሔራዊ ባሕሉ ጋር፣ ታሪክ ባቀረበ ላቸው ግዴታ መሠረት፣ በነበሩበት ዘመን እንዳር፣ እስከዛሬ ጠብቆ በማቆየት፣ የባዕዳንን ወረራ ሁሉ በየአቅጣጫው ለማጨናገፍ፣ የከፈሉትን መሥዋዕትነትና የፈፀሙትን መራራ ተጋድሎ ታሪክ ሊፍቀው አይችልም።ታጋይ ሕዝብም ከጐናቸው ነበር። ዛሬ፣ የዓለም ታናናሽ ሀገሮች፣ ሥልተኛ ምርጫ ባጡበት ዘመን፣ ለምዕራብ ወይም ለምሥራቅ ኃያላን በዝባዥ መንግሥታት፣ በጥገኝነት መንበርከክ፣ ግዴታ መስሎ ቢታይም፣ ይህ የወረርሽኝ ግዴታ፣ ለጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን ዕድል ፈንታ አልነበረም። ይሁን እንጅ እድሜ ደጉ ሁሉን አሳየን። በአንድ ትውልድ እድሜ ውስጥ፣ እኒህ በዝባዥ መንግሥታት በእር

t.me/OLDBOOKSPDF

ዳታና በሥልጣኔ እድገት አማካሪነት ስም፣ በሀገራችን ውስጥ ሠርገው በመግባት፣ ወኪል፣ መሪዎቻቸውን በመንግሥት ሥልጣን ላይ አስቀምጠው፣ የሕዝባችንን ላብና ደም እንደ ጥገት ላም በፈራረቃ ሲያልቡት አየን። ገና አንዱ ጅብ ጓዙን ጠቅሎ በፊት በር ሲወጣ ሲዘጋጅ ሳለ፣ ሌላው ጅብ በጓሮ በር ሲገባ ተመለከትን። ዛሬ ሀገሬ ከሦስት ሺ ዘመናት በኋላ፣ የደርቡሾችን ምጣት ሳይቀር ያልተቋቋመችውን ያህል፣ በዐብዮት ስም ተደፈረች። የውስጧን ብሔራዊ ችግሮችና ድክመቶች ልጆቿ፣ ራሳቸው በራሳቸው፣ በውስጣዊ ትግል፣ ከጊዜ በኋላ ይወጡት ነበር። ይህንንም፣ የራሳችንን ችግር በራስ የመ ወጣት እውነታ፣ የባዕዳኑ ጊዜያዊ ወረራ ከመቸውም ይልቅ፣ ሐቅነቱን እያጐላ አምጥቶታል።

ይህ የዛሬው ትውልድ፣ የተጣሰውን ብሔራዊ አጥር ለማስከበር፣ ከመቸውም የበለጠ ግዴታና ኃላፊነት አለበት። የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ፣ ለባዕዳን ቀርቶ፣ ለሀገሩ ጨቋኝ መሪዎች እንኳ እንደማይተኛ አውቃለሁ። ታሪክም ደጋግሞ መሥክሯል። ያገሬ ሕዝብ የትግል ባሕርዩ እንደኑግ፣ እንደሠሊጥ ያለ ነው። በወቀጡት መጠን፣ የድል ቅባት ያመጣል። ምንጊዜም ቢሆን ይሸነፋል ብዬ አላምንም። ይህን እምነቴንም አጥንቴ ሚይቀር ከሞትኩ በኋላም ይመሠክራል። የጊዜውን መርዘምና ማጠር አላውቅም እንጅ፣ የኋላ ኋላ፣ ይህ ዛሬ፣ ባዕዳን ከብሔራዊ ጭፍሮቻቸው ጋር የጣሱትንና የመነቃቀሩትን ብሔራዊ ክብር፣ ነፃነት፣ መብት፣ ፍትህ፣ ጭቁኑ ያገሬ ሕዝብ፣ ባጥንቴ ሸክላነትና በደሙ ሲሚንቶነት እንድገና ገንብቶ እንደሚያስከብረው፣ ሕያው ትንቢቴ ነው። ብሬዥንቭና ጭራዎቹ፣ በዐብዮታውያን ወታደርነት ስም

የላኳቸውም አለሌ ኰርማዎቻቸው፣ በጋለ የሀገሬ ታጋዮች ብረት፣ የሚኰላሹበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። ያ ልጁ የተናገረ ውም ትክክል ነው። ሕዝባችን ሥርዓቱን በመቃወም ማመፅ ይኖርበታል። ብሔራዊ አጥሩ ተጥሶበት በሶሻሊዝም ስም ሲበዘብዝ የኖረው የምዝብር ሕዝብ፣ የወጠነውን የትግል ጅምር ተግሳሳይ ችግር የደረሰባቸው ኢትዮጵያውያን ያካት ቱታል እንጅ፣ የተጣሰው አጥር እንደተመነቃቀረ አይሰነብትም።

--- ስትሞቂኝ የኖርሽ ያገሬ ፀሐይ፣ ብርሃንሽን ስትለ ግሽልኝ የኖርሽ የሀገሬ ዝንበር፣ አዝርዕቱንና ዕፀዋቱን ስታበረክችኝ የኖርሽ ያገሬ ምድር፣ ስተነፍስህ የኖርኩ ያገሬ ዐየር፣ ስጠጣህ የኖርኩ ያገሬ ውሃ---- ለባዳን ወራሪዎችና ለሀገራችን ፋሽስቶች፣ የተፈጥሮ ልግሥናችሁን እንዳትገብ ሩላቸው ተስፋዬም እምነቴም ነው።" የተጣሰው አጥር፣ " በቅርብ ጊዜ ውስጥ፣ በጭቁን ወገኖቼ አጥንትና ደም ከአዲስ ነፃነቱ፣ ዲሞክራሲው፣ ፍትሁ፣ መብቱ እኩልነቱ፣ ይዘታዊ መልኩ ጋር ይገነባል። የብሔራዊ ክብራችንን አጥር ለመድፈ ርና ለመጣስ ምክንያት የሆኑ ሁሉ፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሕዝ ባዊ ፍርዳቸውን ያገኛሉ!" የባለምባራስ ኑዛዜ መሆኑ ነው።

" ወጋ ወጋ አድርጐ እዚያም እዚህ ምድር!
የኔም ሆነ ያንቺ ግዴታኮ ነበር!
ማንም የጣሰውን እንደገና ማጠር! "

ተፈጸመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሞኝ ባገኝ





ምድረ በዳ-ወለድ፣ ትል ይሉ ወይ ትንኝ፣
ስንቱን ወገን ቀጪ፣ አዲስ ሕይወት ሲመኝ!?
ስንት ለም እያለ፣ የሚታረስ መሬት፣
ለማራቅ ተብሎ፣ ታጋይ ትኩስ ወጣት፣
ሲሣይ ሆኖ ቀረ፣ ለበረሐ ነፍሳት!

(የጠፍ. ቁ.5)

መንደርደሪያ

እበላ ባይ የገሸር መደብ አሠፍስፎ በሚቧግትበት ወቅት፣ የብዙዎች ንፁሐን ሕዝባዊ ሕይወት በጥቃቅን ምክንያቶች መነሻነት ይጠፋል። የሕዝብ ሕይወት፣ በቀላሉ ቍጥጥር ሥር ሊውሉ በሚችሉ ደቂያት ይበከላል። ግቡና ዓላማው የራሱን ግላዊ ፍላጐት ለማርካት ብቻ እስከሆነ ድረስ፣የገሸሩው መደብ፣ ለግል ስሜቱ እርካታ ሲንዘላዘልና፣ ጥንብ እንዳየ አሞራ ጥቅም ባለበት ቦታ ብቻ ሲያንጎብብና ሲያደዘድዝ፣ በመሐሉ “ በሥርዓት አስተዳድረዋለሁ ” ብሎ ቃል ኪዳን የገባለት የሕዝብ ሕይወት መቅኖ ያጣል። መቅኖ ማጣት ብቻ ሳይሆን፣ የመኖር ዋስትናው እየተናጋ፣ ያለዕድሜው እየተቀጨ ያልቃል። ሕይወትን ያህል የምድራችን ትልቅና ክቡር ፀጋ፣ በማይረቡ ጥቃቅን ምክንያቶች ከማጣት የከፋ፣ ሌላ ምንም ነገር አይኖርም።

የገሸር መደቦች፣ ሆነ ብለው የሚፈጥሩአቸው አንዳንድ ረጋ-ሠራሽ ወጥመዶች፣ ለብዙ ሕዝቦች መጥፋት መነሻዎች እንደነበሩ፣ የየጊዜው ታሪክ አሳይቷል። የዘመናችን ፋሽስቶችም በየወቅቱ ያጠመዷቸው የመቅሰፍት ወጥመዶች፣ ምን ያህል አሠቃቂ እንደነበሩ ማሳየት ያደባባይን እውነት ይበልጥ ለማጉላት ይረዳ ይሆናል እንጅ፣ በማንም ዘንድ የታወቀ ነው። ሆኖም፣ ለዝክረ-ነገር መዝግቦ ማቆየቱ፣ መጭውን ትውልድ ከመሰል ሥቃይ ለማዳን ማንጠንቀቂያ እንዲሆንና “ እንዳይ ሞኝም ይረዳዋል ” ተብሎ ይታመናል።

ይህ ሐተታዊ መጣጥፍ ባቀራረቡ ከልብ ወለድ ታሪክ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይለያል። ካጭር ልብ ወለድ፣ ለየት ባለ መልክ በጣልቃነት እዚህ መቅረቡ፣ አንባብያንን በባሕርያት ትረካ ላለማሰልቸት ተብሎ ነው። ጽሑፉ በተናጠል የሚያጤኑት መሪ ባሕርይ የለ ውም። አንባብያን ይህን ነቁጥ አስመልክተው እንዲያነቡት ይጠየቃሉ። ይህን ዐይነት አፃፃፍ ካጫጭር ታሪኮች መካከል ጣልቃ ማስገባቱ፣ ሌላው ምክንያት ደግሞ አንድን ትንግርት በሌላም ያፃፃፍ መልክ ማቅረብ እንደሚቻል ለማሳየትና ባንድ ዐይነት ጽሑፋዊ አቀራረብ ብቻ ላለማሰልቸት ሲባል ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሞኝ ባገኝ

"አጥፍቼው ልጠፋ ከነቃም ሊያጠፋኝ
ደሙን ተዋህጄ ጉልጥምቴን ልል ሙጥኝ
በክሥተቴ ዝፍኩ ለመኖር ካልበጡኝ
ብልጡማ አያስጢጋም ምናልባት ሞኝ ባገኝ! -----"

ቀትር ቀን ላይ ነው። ገ/ምበር ሙሉ ፀዳሏን ፈንጥ ቃለች። ለምልክት ያህል እንኳ፣ ከህዋ ደጃፍ ላይ ደመና አይ ታይም። ደረቱን ገልብጦ ለሰጠው ያዲስ አበባ ከተማ ምድር፣ በፍፁም ለጋሥነት ያቺ ፀሐይ ስጦታዋን ስታበረክት፣ ያ ፀሓ ያማ ቀን የመጀመርያ ቀን ይመስላል። ጉብሎችና ኰረዶች በስ ሪኳርተር መኪና ላይ ተጭነው በማሽንገን ተከበዋል። ቍጥራ ቸው ከአስር በላይ ይሆናል - መኪናዎቹ! የሚያላዝኑ ዐይኖች፣ በሌሎች ያጐረጡ ዐይኖች ይገለመጣሉ። ግማሹ ልጁን፣ ግማሹ ወንድሙንና እህቱን፣ የተቀረውም የዘመዱንና ባልንጀራውን ለመሸኘት፣ ካራተኛ ክፍለ ጦር ደጃፍ ላይ ጢም ብሏል። በስ ሪኳርተር መኪናዎች ላይ ተጭነው የነበሩ ወጣቶች ሁኔታ፣ ተመልካቹን ሁሉ በማሳዘን ላይ እንዳለ፣ ይግረማችሁ ብሎ፣ ወደ ሀምሳ የሚጠጋ የማክ ትሬንታ ቍጥራቸው ይህን ያህላል ብሎ ለመገመት የሚያስቸግር የወጣቶች መዓት ጭኖ ካልተወቀ ሥፍራ እየገሠገሠ መጥቶ ካራተኛ ክፍለ ጦር በር ላይ ተደረ ደረ። የነዚህ ሁሉ ወጣቶች መነሻ ስፍራ ባይታወቅም፣ ለተወ

ሰኑ ዐመታት እስር ቤት የማቀቁ ለመሆናቸው መልካቸው ያስረዳል። ፊታቸው፤ ሆነ ብለው ጭስ ላይ የሠቀሉት ብቅል ይመስላል። ፍዀም ጥቀርሻ ሆነዋል። ያካል ሥጋቸው አልቆ አጥንታቸው ብቻ እርቃኑን ቀርቷል። የፃዕረ ሞት ምስል ይመስላሉ። በገፅ አጥንቶቻቸው መካከል ጨርሰው ያልጠፉ ዐይኖቻቸው፤ ረዳት ጉልበት የሚመኙ ይመስል፤ ክብልል ክብልል ይላሉ። ሽፋሽፍቶአቸውና ቅንድቦቻቸው፤ ለምልክት ያህል እንኳ ከቦታቸው ላይ አይታዩም። ጆሮዎቻቸውና አፍንጫዎቻቸው ቢሆኑም ለወጉ ያህል ጉች ጉች አሉ እንጅ፤ ጐል ተው አይታዩም። መከራና ሥቃይ ያንገላቱዋቸው እነዚህ ወጣቶች፤ በዚያን ዕለት አራተኛ ክፍለ ጦር እንዲመጡ የተደረገው፤ በሦስተኛው የናት ሀገር ጥሪ- " በአረንጓዴው የልማት ዘመቻ " - መሠረት፤ ገጠር ለማልማት እንዲካፈሉ ተወስኖ፤ ለሥምሪቱ እንዲዘጋጁ ታስቦ ነው።

ቀደም ሲል፤ በአሥር ስሪኳርተር መኪናዎች ተጭነው፤ ከክፍለ ጦሩ ግቢ ውስጥ ሠፍረው የነበሩት ወጣቶች ግን በቀበሌዎችና ሴሎች ድርጅቶች አማካይነት ተመንጥረው የታፈሱ፤ ተማሪዎች፤ ሥራ አጦች፤ ሴትኛ አዳሪዎች፤ ረዳት የለሽ ወገኖች ናቸው። የልጆቻቸውን ለዚህ ዘመቻ መታፈስ የሰሙ ወላጆችና ዘመዶች፤ እንባቸውን እያነቡ፤ ከውጭ ሆነው ለዘመቻ የሚነሱበትን ሰዓት ለማየት አኰብኩበው ይጠባበቃሉ። አብዛኛዎቹም እናቶች ነበሩ። የዘመኑ መዓት የጠበሳቸው!!

አንዳንድ ሁኔታው ያላስቻላቸው እናቶች፤ ከክፍለ ጦር ደጃፍ ላይ ተምበርክከው፤ የየግል ሙሾአቸውን መደርደር ጀምረዋል።በዚያ ቀውጢ ዘመን፤ እንኳንስ ተለይተዋቸው ሩቅ ሀገር መሔዳቸው ይቅርና፤ እዚያው እጉያቸው ተደብቀው የነበሩ ልጆቻቸው፤ በየምክንያቱ እየተወሰዱ መረሸናቸውና፤ አንዳንዶቹም ድንገት ወጥተው፤ እውስጥ ይግቡ ስምጥ የት እንደደረሱ ሳይታወቅ የውላ ሽታ ሆነው መቅረታቸው፤ እናቶችን እየታወሳቸው ነበር። ለነዚያ ሩቅ ሀገር ተወስደው፤ ዱር ለመ መንጠር፤ በረሐ ለማልማት ያስገደዷቸው ምስኪን ልጆቻቸው፤ የሚገጥማቸው ሥቃይና መከራ እየታያቸው ነበር የሚያለቅሱት። ያልቅሱ እንጅ፤ ልቅሶአቸውን ቁምነገሬ ያለው የወታደር ባለሥልጣን አልነበረም። እንደውም እዚያ ክፍለ ጦር በር ላይ ተሰብስበው፤ በልጆቻቸው ላይ መጥፎ እድል የሚያሟርቱ እናቶችን ሁሉ፤ በደረጃቸው ፀረ-ዐብዮተኞች ናቸው ተብለው፤ ልጆቻቸው ለሞትም ይሁን ለሕይወት፤ በወጉ ሳይሸኙ፤ በቅፅበት ከዚያ አካባቢ እንዲባረሩ፤ አንድ ዩኒት ጦር ታዘዘ።

ከዚያማ ምኑ ይነገራል ? የታዘዘው ዩኒት፤ ደካማዋን እናት ከብርቱዋ እናት አልመረጠም። ዝም ብሎ መደዳውን በሠደፍ መጥረጊያና በሳንጃ መሠቅሠቂያ፤ እየጠቀጠቀ ጠረጋቸው። የዚያ የታዘዘ ዩኒት ጦር የማምሻው ተግባሩ፤ እነዚያን መከረኞች እናቶች የማጉላላትና የማንገላታት ሥምሪት እንደነበር፤ ካካባቢው የነበረ ወጭ ወራጅ መንገደኛ ሳይቀር ተመለከተ። በዚያ ዕለት ምሽት፤ መሿለኪያ የተባለው ሥፍራ፤ የሽብርና የግርግር ቦታ ሆኖ ከወትሮው ብሶበት ነበር። ደም የተለቀለቀው የናቶች እንባ እንደ ጐርፍ ፈሠሠ። የድሮ የራሔል የእናትነት ታሪካዊ ዋይታና ስለልጆቿም ስትል የመሠቀቂ ትራገዲያዊ ድራማ ፤ በዚያ ምሽቱ ያራተኛ ክፍለጦር ደጃፍ መድረክ ላይ ባዲስ መልክ ቀርቦ ታየ። ተባራሪ ተመልካችም፤ በአንክሮ ሳይሆን፤ በሀዘንና በብስጭት ተመለከተው። ጥይት ባይተኰሰባቸውም፤ በመከረኞቹ እናቶች ላይ የሠደፍና የሣንጃ እሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ምታ ወርዶባቸዋል። በዚያ ምሽት፣ በዚያ ሥፍራ የተገኘች መከረኛ እናት ሁሉ፣ አንድም ቆስላለች፣ አንድም ያበጠ ዐካል አትርፋለች። ከዱላው ፋሽስታዊነት የተነሳሣ መላወስ ያቃታቸው፣ በወሣንሳ እየተነሱ፣ በአንቡላንስ የተወሰዱት ቍጥራቸው ትንሽ አልነበረም። ከሣንጃው አረማዊነት የተነሣ ዐይናቸው ሳይቀር የቈሰሉ እናቶች ብዛታቸው አንስተኛ አልነበረም።

በዚያ ዐይነት የምንጠራ ሥምሪት፣ የታዘዘው ፎኒት ጦር፣ የክፍለ ጦሩን ደጃፍ ካፀዳ በኋላ፣ የዕለቷ ዝንበር ጠልቃ፣ ምሽቱ ጨለምለም ሲል፣ ለዘመቻው የተዘጋጁት የታፈሱና በእፃስር ቤት የቆዩ ወጣቶች መንቀሳቀስ ጀመሩ። የት እንደሚወሰዱና ለምንስ እንደሚጓዙ የማያውቁ፣ እነዚያ አሳዛኝ ወጣቶች፣ ዝምታና ፀጥታ ውጧቸዋል። ብቻ አልፎ አልፎ አን ዳንድ ወጣት፣ ድምፁን ከፍ እያረገ፣ ደኅና ክረሙ! እኛ ወደ እልቂታችን መሔዳችን ነው! ይል ነበር። ከናቶች ዋይታ በስተ ቀር፣ ሊያስጥል የሞከረ ወንድ አልነበረም።

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገደማ ላይ፣ እነዚያ ስሪ ኳርተ ሮችና የማክ ትሬንታዎች፣ የሒትለርን የሥንቅ ማጓጓዣ ይመ ስል፣ ተያይዘው ፣ በዐብዮት አደባባይ፣ በአስመራ መንገድ፣ በየካ፣ በኰተቤ፣ በላምበረት አድርገው ነጐዱ። በላዮቻቸው ላይ እንደሰርዲን ታምቀው የተጫኑት የሚያሳዝኑ ዘማቾችም፣ የሴሊቱን ቍርና የቀኑን ሐሩር መከላከያ ሳይሰጣቸው፣ የደረቀ ሞፎ እየጋጡ፣ ካሥር ቀናት ጉዞ በኋላ፣ እንዲያለሙ ከተወሰ ነላቸው በረሐ ደረሱ። ለምን ያንን በረሐ ለማልማት እንደ ተወሰነ፣ ባይገለፅላቸውም፣ ሰው የሌለባቸው፣ ደጋና ወይና ደጋ ሰፋፊ መሬቶችን እየዩ እንደመጡ፣ በጉዞአቸው ላይ ተመ ልክተዋል።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሠፈሩበት በረሐ፣ ከዚህ በፊት የሰው ልጅ እግሩን ያልረገጠበት ምድረ በዳ ነው። የሱዳን ጠረፍ በሩቅ ይታያል። ከሁመራ አልፎ፣ አብደራፊን ተሻግሮ ጭው ካለው በረሐ ላይ ነው። ከዚህ ቀደም ሰው ያልረገጠውና ያልሠፈረበትም በመ ሆኑ ሥፍራው " ስም የለሽ " ነው። ከዚህ በረሐ ዳርቻ ላይ አንድ ከፍተኛ ዱር አለ። ከሠፈራው ቦታ ወደዚያ ዱር ለመድ ረስ አንደ ቀን ይፈጃል። የበረሀው መለስተኛ የውሃ ምንጭ እስከተገኘበት ቅርብ ጊዜ ድረስ፣ የሠፈረው የልማት ሠራዊት እየተቆነነ ሚሰጠውን ውሃ የሚያገኘው፣ ከዚያ ዱር ውስጥ ከምትገኘ አንዲት ትንሽ ምንጭ ነበር። ምድብ ሥራቸው ውሃ ማመላለስ የነበሩት ዘማቾች፣ ፣ በየሦስት ቀኑ ውስጥ፣ አንድ ቀን ሙሉ መጓዝ ነበረባቸው።

መቸም አንድ ያንን መሰል ትልቅ የልማት ዘመቻ እቅድ ሲታሰብ፣ ማንም እንደሚያውቀውና እንድሚያምንበት ሁሉ፣ በተቀዳሚ መዘጋጀት ያለባቸው ብዙ ተግባሮች፣ ፕሮጀክቶች፣ መሠናዶዎች፣ አሉ። ቢያንስ ቢያንስ፣ ጊዜያዊ መጠለያ ቤቶች የመጀመርያ እርዳታ መስጫ ክሊኒኮች፣ ዶክቶሮችም ባይገኙ ድሬሰሮች ሥንቅና በተለይም ውሃና አስፈላጊ ልብሶች እንዲኖሩ ግዴታ ነው። እነዚህ ከሞላ ጐደል መገኘት አለባቸው። በተ ጨማሪም ፣ ለዘመቻ መሥፈሪያ የሚመረጠው ሥፍራ፣ አስቀ ድሞ በተለያዩ ባለሙያዎችና ኤክስፐርቶች ተጠንቶ፣ አመችነቱ መረጋገጥ አለበት። ሥፍራው ጤነኛ አከባቢ መሆኑ ብቻ እንኳ አይበቃም። መጓጓዣ ሊገባው ይችላል ወይ? ሊመረት የሚችለውን ምርት የሚጠናወት ያካባቢ አውሬ፣ ተውሳክ፣ ፀረ

ምርት ነፍሳት አሉ ወይ? ለሠፈረው ሠራዊትስ፣ አካባቢው የጤንነት ዋስትና ሊኖረው ይችላል ወይ? ለማልማት የታቀዱትን አዝርዕቶች ያካባቢው አፈር ይቀበለው፣ ይስማማው፣ ይዋሐ ደው ይሆን ወይ? የእነዚህ ጥያቄዎች መልሶች ወሣኞች ናቸው።

ልማትን ያህል ትልቅ ፕሮጀክት አቅዶ፣ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መሠናዳዎች በሚገባ ሳያዘጋጁ፣ ባዶ እጁን ያለ፣ ወጣት የልማት ሠራዊት፣ በግዳጅ ወስዶ ጭው ካለ በረሀ ላይ ማፍሰስ፣ "ልማት" ከሚለው ክቡር ዓላማና ግብ፣ በይዘትም ሆነ በቅርፅ የተለየ፣ ሌላ ምክንያት ሊኖረው ይችላል። "ሊበ ሉት ያሰቡትን እሪያ፣ በገ-ሰማይ ይሉታል" እንደሚባለው ያለ - ወጣት ተራማጅ አልባ አዲስአበባ ለመፍጠር?

እነዚያ የፈረደባቸው ምስኪን ወጣት የልማት ዘማቾች ከዚያ ምድረ-በዳ ተጥለው፣ አሣራቸውን ያቦኩ፣ ፍዳቸውም ይዝቁ ጀመር። ሌቱ መሽቶ በነጋ ቊጥር፣ ምሕረት በሌለው መሃይምን ካድሬ መጨቅጨቅና መነረት፣ የዘወትር ምሣቸው ሆነ። ምግብ ይሉ ልብስ በሥርዓት አይሰጣቸውም። ከሥራ ድካምና ከጤንነት ጕድለት የተነሣ፣ መሥራት ሲሳናቸው፣ በዐብዮቱ የሚለግሙ አድኃሪዎች እየተባሉ፣ እዚያው በተሠራ ወንኒ ቤት ተልከው ይማቅቃሉ። ከመድኃኒት ይሉ መድኃኒት፣ ከሐኪም ይሉ ሐኪም ስለሌለ፣ ከጤነኛው ዘማች ይልቅ፣ የሕ መምተኛው ቊጥር ይበልጣል። ለወጉ ያህልማ፣ የሚሰጡትን ክኒን ዐይነትና ምንነት በደንብ ለይተው የማያውቁ፣ አምስት የጤና መኰንኖች አሉ። ለዚያውም ክኒናቸው ቢሆን፣ የዘማ ቹን እጅ ያያሉ።

መጠለያ ተብሎ የተሠራላቸው ቤት ያው እነሱ ከደረሱ በኋላ ያዘጋጁት ጊዜያዊ ማረፍያ ነበር። ከተራ ዳስ አይሻልም።

ጕረቤታቸው ካለው ዱር በሸክም ከመጣ እንጨት የተዋቀረና ግድግዳው ባጋምና ባልታወቁ ቅጠሎች የተሸመጠጠ ሲሆን፣ ጣራው በተጣጣፈ አሮጌ የድንኳን ሽራ የተሸፈነ ነው። ለዚያ ውም ቢሆን፣ ግማሹን ጣራ ሸራውን አላዳርስ ብሎት፣ የበረሀ ሣር ተረብርቦለታል። የበረሀው ሐሩር ቃጠሎው በሚብስበት ወቅት፣ በሣርና በቅጠል ብቻ የተሸፈነው የጣራው ክፍል፣ ሰደድ እሳት የለኰሰበት ይመስል ቢል ብሎ የጎደደበት ወቅት ነበረ። ደግነቱ ያ ወቅት፣ መላው ሠራዊት ለሥራ በሚሠማ ራበት በቀኑ የሥራ ሰዓት መሆኑ በጀ እንጅ፣ ስንት ዘማች በቃ ጠሎው በነደደ ነበር።

የዘማቾቹ መጠለያ የተሠራው፣ ከበረሀው መሐል ላይ ስለነበረ (ለማምለጥ ለሚሞክሩ ዘማቾች እንዳያመች ተዘይዶ ነው!) ቃጠሎው በተነሣ ቊጥር ለማጥፋት በጭራሽ አይሞ ክርም። በመሆኑም ያ ዳሳቸው ብዙ ጊዜ እየተቃጠለ፣ የሚኖ ሩት ኋላ ላይ በመጡ ድንኳኖች ውስጥ ነው። ድንኳኑም በበ ኩሉ ከበረሀው ንዳድና ሐሩር የተነሣ ወበቁና ሙቀቱ አየድርስ ያሰኛል። ትንሽ ቀዝቀዝ ብለው የሚታዩት አንድ ክፍል ወጡቹ ዛኒጋባዎች ናቸው። እነዚህ ዛኒጋባዎች፣ ጣራቸው በደ ርብ እንጨት ተሠርቶ፣ በአሸዋ የለበሱ በመሆናቸው፣ ውስጣ ቸው መለስተኛ ቅዝቃዜ ይሰጣሉ። እንዲውም የበረሐው ሪፍ ሬጀሮች የሚል ስም በዘማቾች ተሰጥቷቸዋል።

ይሁን እንጅ፣ ዕድል አጋጥሞት በውስጣቸው የሚኖር ተራ ዘማች እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። እነዚህም ቢሆኑ ከዘመ ቻው መሪዎች ጋር ልዩ ግኑኝነት ያላቸውና፣ በወራዳ ጠባያ ቸውም የታወቁ እበላ ባዮች ብቻ ናቸው። እንደግል ቤታቸው ቆጥረው አዘውትው የሚወጡባቸውና የሚገቡባቸው፣ ብዙም

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀናት የሚዝናኑባቸው፤ ከዘማቾች ሴቶች ውስጥ በመልክ ቀናነ ታቸው ተመርጠው፤ ለካድሬዎቹ የዘመቻው ሹሞች፤ ያለውል የተዳሩት ቅምጦቻቸው ናቸው። እነሱም ቢሆን የግዴታ "እመ ቤቶች" የተደረጉ ናቸው። እነዚህ የበረሐ ሴት ወይዘሮዎች፤ ለምድብ ሥራቸው እንኳ፤ ከዚያ ቀዝቃዛ ጉዶዎቻቸው ውስጥ ብቅ የሚሉት፤ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነበር። በሥራ ምድባቸውም ቢሆን፤ እንደሌላው ተራ ዘማች፤ የውሃ ጉድጓዶች ቁፈራ ተግ ባር፤ የበረሐ ጉርባዎችና ዲቦችን ሰርሻ የመስተካከል ከባድ ሥራ፤ ወይም ከዚያ ሩቅ ዱር ለሁለትና ለሦስተ ቀናት ዕድሜ ተጉዞ ጫካ መመንጠር ሳይሆን፤ ለዘማቹ ምግብ ማዘጋጀት ብቻ ስለሆነ፤ ባካባቢው የኑሮ ደረጃ አንፃር፤ በኑሮአቸው የሚንቀ ባረሩ ቅምጥሎች ናቸው። በአንጻራቸውም በሔዋንነታቸው ማራኪ ያልሆኑቱ ወገኖች፤ ከወንዶቹ እኩል በሥራ ይማቅ ቃሉ።

በነዚያ ቀዝቃዛ ዛኒጋባዎች ለመኖር፤ዕድል የተሰጣቸው፤ ሌሎች እበላ ባዮች ደግሞ፤ በወራዳ ተግባራቸው የዘመቻ መሪ ዎቹን የሚያገለግሉ ቡችሎቻቸው ናቸው። አብዛኛዎቹ በዘማቹ ሠራዊት ውስጥ በሰላይነት የተሠማሩ፤ ባብሮ ዘመት ጓደኞ ቻቸው ላይ በወራዳ ተግባራቸው ሹመት ያገኙ ዘማቾች ናቸው። እነዚህም የውስጥ ጠላቶች፤ በሚፈሩትና በሚጠሉት ጓደኛቸው ላይ ሳይቀር፤ የውሸት ወንጀል እየፈጠሩ፤ "ሲያ ሳድም አገኘነው! ሊሰደድ ሲዘጋጅ ደረስንበት፤ ፀረ-ዐብዮት ወሬ ሲነዛ ያዝነው---" ከሚለው ክስ እንስቶ እስከ "ፍቅረ ኛዎን ሲያባልግ ሲያጨልግ፤ ሲያባብል ደረስንበት!" እሚለው ወንጀል ድረስ፤ በብዙዎቹ ጓደኞቻቸው ላይ ደባ የሚፈፅሙ ናቸው። እነዚህም እበላ ባይ ንውሣን ሹሞች፤ የሚ

t.me/OLDBOOKSPDF

በሉት ምግብና የሚመገቡበት ሥፍራ ሳይቀር፤ ከተራው ዘማች ሠራዊት የተለየ ነው። ከዋናው ማዕከላዊ የዕድገት መሥሪያ ቤትና የዘመቻ መምሪያ የሚላክ ማንኛውም ዳረጐትና ገፀ በረከት ሳይደርሳቸው አያልፍም። ከበላይ አለቆቻቸውም ጋር አልፎ አልፎ፤ እግር ከጣለው የኮንትሮባንድ ነጋዴ ላይ ከሚወ ረሰው ልዩ ልዩ እቃ ውስጥና እንደውስኪ ያሉት መጠጦች ሲወረሱ፤ እነዚህም እበላ ባይ ጥቃቅን ሹማምንት የመጠጣት ዕድል አላቸው።

በተቀዳሚ ስለ ተራው ዘማች ቤትና ጠቅላላ ኑሮ ሁኔታ ተነገረ እንጅ፤ የዘመቻውን መሪዎች የበረሐ ኑሮ ሁኔታ ቢነሳ፤ ሌላ ሆኖ እናገኘዋለን። ለመጀመሪያው አንድ ወር ያህል ብቻ መለስተኛ የቤት ችግር ደርሶባቸው ነበር። ከዚያ በኋላ ግን፤ ከማዕከላዊ መጪት የተላኩ፤ ተጓዥ ቤቶች ስለደረሰላቸው፤ ከከ ተማ ባላነሰ የኑሮ ሁኔታ ይኖራሉ። ሪፍሬጅረተር ሳይቀር አላ ቸው። ትኩስ በቆርቆሮ የታሸጉ ምግቦች በየጊዜው ይደርሳ ቸዋል። ለነገሩ ያህል "የዘመቻ መሪዎች" ተብለው፤ ምድብ የሥራ ቦታቸው በዚያ በረሐ ይወሰን እንጅ፤ በሥራና በስብሰባ ምክንያቶች እያሳበቡ፤ አብዛኛወን ጊዜ የሚያሳልፉት፤ ጉንደር ከተማ ወይም አዲስ አበባ ነው። ቍጥራቸው አይብዛ እንጅ፤ በምሥራቅ ጀርመን መንግሥት የተሰጡ፤ በረሐ ተጓዥ የሆኑ ልዩ ልዩ ጅፖች አሏቸው። ቅርባቸው ሆነው በአዝማችነት እንዲመሩአቸው የተመደቡትን ዘማቾች ግን፤ ረስተዋቸዋል። ምናልባትም ጠቅላላውን የዘማች ሠራዊት የሚገናኙበት ጊዜ ቢኖር፤ አልፎ አልፎ በየወሩ መጨረሻ ላይ በሚደረገው አጠ ቃላይ ስብሰባ ጊዜ ብቻ ነው። ለዚያውም ቢሆን፤ አንድ የተለየ የበላይ ትእዛዝ ካልመጣና፤ ለሠራዊቱ መንገር ካላስፈለገ በስተ

ቀር፤ ይሽንንም የመገናኛ ወቅት እንዳሻቸው ይሠርዙታል።

ዘማቹ ሠራዊት ከዕለታዊ ሥቃዩ ጋር፤ እነሱም እንደ አዛዥነታቸው ከቅምጥል ኑሮአቸው ጋር እንዳሉ፤ ወራት አለ ፉና የበጋው ጊዜ አልቆ የክረምት ወቅት ገባ። ያ በረሐ ባለው የተፈጥሮ የቆየ ልምዱ ክረምትነቱን የመሰከረው፤ ለግማሽ ወር ያህል፤ ከተራ ማርከፍከፍ አንስቶ ለጥቂት ቀናትም የዶፍ ዝናም ባወረደበት ወቅት ነው። ያ ለረዥም ወራት፤ በሐሩር ብዛት ሲጋይ የቆየ የበረሐ አሸዋ እንኳንስ በዝናሙ ውሃ ሊርስ ቀርቶ፤ ጥማቱንም አላረካ። ብቻ በክረምቱ ዝናም የተነሳ፤ ዘማቹም ሆነ አዝማቹ ከዚያ በፊት በአካባቢው ያላወቁት አንዳች ነገር ተከሠተ።

ለዐይን ጉልተው የማይታዩ ረቂቃን ነፍሳት ርጥበት ከተሰማው የበረሐ አሸዋ ላይ እንደ መዓት ፈሉ። ደግነቱ የበረ ሐውን ሙቀት መቋቋም ባለመቻላቸው ብቻ ይመስላል፤ ፈል ተው በታዩበት በሦስተኛው ቀን ዶጋመድ ሆነው ይጠፉ ነ። ይሁን እንጅ፤ ከእነዚህ ጥቃቅን የበረሐ ነፍሳት ጥቂቶቹ፤ ለዘ ማቹ ሠራዊት ውሃ አመላላሽ በሆኑ በቅሎዎችና አህዮች ኮቴ ስር ተሰጥፈው፤ ከጋለው የበረሐ ሐሩር ወደ ቀዝቃዛው ምንጭ ያለበት ያካባቢው ዱር በመወሰዳቸው፤ ከቅዝቃዜው፤ ነፍስ ዘርተው በሕይወት መትረፋቸው፤ መርዛቸውን ለማጐ ልበት እስከቻሉበት ወቅት ድረስ በምንጩ አካባቢ በማደጋ ቸው፤ ለከፍተኛ ወረራ የተዘጋጁ ሆኑ።

የነዚህን መርዘኛ ነፍሳት አደገኛነት፤ ለግዳይ ከመሠማራ ታቸው በፊት፤ ከዘማቹም ሆነ ከአዝማቹ መካከል፤ የተረዳ አን ድም ሰው አልነበረም። እነዚህ መርዘኛ ነፍሳት፤ በተቀዳሚ መር ዘው የከረበቱት፤ ወሃ አመላላሽ የነበረች አንዲት በቅሎ ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ውሃ ለማምጣት ከሔደችበት የዱር ውስጥ ምንጭ አልተመለ ሰችም። አገልግሎቷን በቅርቧ ሆነው የሚያውቁ፤ የውሃ አመላ ላሽ ምድብ ሠራተኞች፤ አንድ ሰው የሞተ ያህል በመቍጠር ፤ ለበቅሎዋ አልቅሰው በወግ ቀብረዋታል። ይህ በሆነ ባራተኛው ቀን ደግሞ ሦስት አህዮች በዚያው በዱሩ ምንጭ አጠገብ፤ ውሀ ለማምጣት እንደሔዱ ሞቱ። ያንጊዜ ነበር የውሃ አመላ ላሽ ምድብ ሠራተኞች ፍራቻ፤ የተጠነሰሰው።

ከዱሩ እንደተመለሱ፤ ወዲያው በማግስቱ፤ ጉዳዩ ለሚ መለከተው የዘመቻ ባለሥልጣን ሪፖርት አቀረቡ። ጥቆማ ቸውን ሰምተው አስቸኳይ ርምጃ እንዲወሰዱ የሞከሩ፤ የዘመ ቻው ባለሥልጣኖች ግን አልነበሩም። ሁኔታው በዚሁ መልኩ እንዳለ፤ ከውሃ አመላላሽ ምድብ ሠራተኞች ውስጥ አንድ ዘማች፤ሦስት አገልጋይ ከብቶቻቸው በሞቱ ሣምንት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ፤ ከውሃ ማምጣት ተግባሩ በተመለሰ በሁለተኛው ቀን፤ ተኝቶ ካደረበት ከኬሻ መኝታው ላይ መነሳት ሳይችል ቀረ። እነዚያ የጤና መኰንኖች፤ ያሰ የሌለ ኪኒን ቢያቅሙትም መንቀሳቀስ ሳይችል፤ ምን እንደነካው እንኳ መናገር እንዳ ቃተው፤ በሚያሳዝን ሁኔታ ተሠቃይቶ ሞተ። ይህም ዜና በመ ላው የዘማች ሠራዊት ውስጥ ተሰማ። ይሁን እንጅ፤ በየምክ ንያቱ በየጊዜው የሚሞተው ዘማች ቍጥር ትንሽ ስላይደለ፤ ጕዳዩ ብሎ እጅግ የተጨነቀበት አልነበረም።

ያ ዘማች በሞተ በሦስተኛው ቀን አምስት ሌሎች የውሃ አመላላሽ ምድብ ሠራተኞች ታመው ተኙ። ብዙም ቀን አልቆ ይም፤ አምስቱም ዓረፉ። የሠራዊቱን ካምፕ ያናጋው፤ የነዚህ ዘማቾች ባንድ ጊዜ የመሞታቸው ዜና ነበር። ሁሉንም ሽብር ለቀቀበት! ይበልጥም የካምፑን ሠራዊት ያነቃነቀው፤ እነዚያን

በድንገት የሞቱ ጓደኞቻቸውን በሕክምና ለመርዳት ሔደው የነበሩት ሁለት የጤና መኰንኖች፣ በጠና መታመም ነው። እነሱም ብዙ አልቆዩ፣ ተከታትለው ሞቱ። ከዚያ በኋላማ፣ ምን ይወራል፣ ቊጥር የለሽ ዘማቾች እንደቅጠል ረገፉ። በዚያ አጋጣሚ የሚይዙትና የሚጥሉት መላቅጥ የጠፋባቸው፣ የዘመቻው ባለሥልጣኖች ስለተደናገራቸው፣ ብዙ ዘማቾች በቡድን በቡድን እየሆኑ፣ ቊጥጥሩ በላላበት አካባቢ እየመረሹ " እግሬ አውጭኝ " አሉ። ዐይናቸው እያየ ከሚሞቱ ይልቅ፣ የሚሔዱበትን ሳያውቁ መጥፋትን መረጡ። በየሁለት ወር ተረኛነት፣ በፈራረቃ የዘመቻውን ሠራዊት በታማኝነት ለመጠበቅ ይመጡ የነበሩትም ከገበሬውና ከባላገሩ የተመረጡ ሚሊሽያ ዘበኞችም በበኩላቸው፣ " ነፍሴ አውጭኝ " እያሉ መፈርጠጥ ሆነ። ይህም ለዘማቹ ሠራዊት የማምለጫ ሽንቁር ስለቀደደለት፣ በየዕለቱ እየጠፋ የሚሰደደውን ዘማች ቊጥር በጥፍ አሳደገው። ለማምለጥ ያልሆነለትም ቢኖር ሞቱን ይጠብቅ ጀመር።

ከሞት ያመለጡት ሦስት የጤና መኰንኖችም የበሽታውን ምንነት አጥንተውና ተረድተው ሳይሆን፣ ለራሳቸው ሕይወት ጭምር በመፍራት፣ በዘመቻው ካምፕ ውስጥ፣ " ተላላፊ በሽታ " መግባቱን በጽሑፍ በመግለጽ፣ ለዘመቻው ባለሥልጣኖች ካምፑ እንዲዘጋና፣ የቀረውም ሠራዊት ባስቸኳይ ወደ ሌላ እንዲዛወር አመለከቱ። ራሳቸውም የዘመቻው ባለሥልጣኖች ለራሳቸው ጤንነት ሲሉ፣ ሌላ የሚወስዱት የተሻለ ምርጫ ስላልነበራቸው፣ በጤና መኰንኖቹ ውሳኔ ተገደው፣ ዘማቹን ሠራዊት ወደ ሌላ ስፍራ ለማንቃንቅ፣ አስቸኳይ መልእክት አዲስ አበባ ለሚገኘው ማዕከላዊ የዕ

t.me/OLDBOOKSPDF

ድገት መምሪያ መ.ቤት አስተላለፉ። አስፈላጊው ውሳኔና ትዕዛዝ ከዋናው መ.ቤት እስኪመጣ ድረስ፣ የየዕለቱ የሞት ፍጥነት *(death rate)* ከአምስት ወደ አስር አደገ። እንደሠንሠለት ተቆላልፎ የሚርመሰመሰው አጅሬ ቢሮክራሲ፣ "ለበላይ አካል" በሚል ፈሊጡ እየፈተለ ሲያጠነጥንና ሲያስትላልፍ እርስ በርሱ ሲተሻሽ ከረመ። የታች አካል ከበላይ አካል ውሣኔ ለማግኘት አንጋጦ ሲጠብቅ፣ ቀናት ተቃጠሉ።

እንዳጋጣሚም፣ ከአዝማቾቹ አንዱ ተጋደመ። ይህም አስደንጋጭ ሁኔታ በፈጠረው ድፍረት፣ የቀሩት የዘማች ባለሥልጣኖች፣ በረሓውን ለቆ የመውጣት ግላዊ ውሣኔ አስተላልፈው፣ የበላዮቻቸውን ትዕዛዝ ሳይጠብቁ፣ ጉዞውን ባስቸኳይ ጀመሩ። በየመንገዱ እየተንጠባጠበ የቀረውን ሚች ቊጥር ማወቅ ባይቻልም፣ በያቅጣጫው እየጠፉ የተሰደደውን ዘማች መጠን ሳይጨምር፣ ሰው ከሚኖርበት ካቅራቢያው መንደር ነፍሱን ይዞ የደረሰው ዘማች፣ ብዛቱ እጅግ በጣም ትንሽ ነበር።

ከዚህ የተላላፊ በሽታ መዓትና ሞት ቀደም ብለው ካምፑን ጥለው ከሸሹት ዘማቾች ውስጥ፣ ሱዳን ውስጥ ገብተውኖሮ፣ የሰጡት የበረሓ እልቂት ሁኔታ በሬድዮና በጋዜጣ ለዓለም በመሠራጨቱና የማዕከላዊውን መንግሥት የጫፍ ባለሥልጣኖችም ዜናው ያሳሰባቸው በመሆኑ፣ ለሚፈሩት ፕሮፓጋንዳ ብቻ ሲሉ፣ በነፍስ የተረፉትን ዘማቾች ከሚገኙበት ቦታ ላይ፣ በሔሊኮፕተር ሳይቀር ተፈልገው ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ አስቸኳይ ትዕዛዝ አስተላለፉ። (የዚህን ምንጭ ለኔ የጠቆሙት ከሱዳን ስደተኞች አንዱ ነው።) በዚህም ትዕዛዝ መሠረት፣ በሕይወት የተገኙ የዘመቻው ተራፊዎች ሦስት ቀን

ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባ ገቡ። በጣም የሚገርመው ግን፣ እነዚህን የበረሐ ስደተኞች፣ ቢቻል ሆስፒታል ገብተው በምርመራ እንዲቆዩ፣ ወይም የተሰየ ማረፊያ ተመድቦላቸው የጤንነታቸው ሁኔታ እስኪረጋገጥ ድረስ፣ በሐኪሞች ጥበቃ ስር እንዲቆዩ በማድረግ ፈንታ፣ ገና እንደመጡ ለየቤተሰቦቻቸው እንዲሰጡ መደረጉ ነው። በዚህም ውሣኔአቸው የተነሣ፣ ያ የሰሜን በረሐ የወለደው መርዛማ ነፍሳት ያስገኘው ተላላፊ በሽታ፣ ከሀገሪቱ መናገሻ ከተማ፣ ያላንዳች እክል ከአዲስ አበባ ሰተት ብሎ ገባ። በበረሐው ውስጥ ልጆቿን የጨረሰው አንሶት፣ በሀገሪቱ እንብርት ላይ ተገኝቶ፣ ሕዝቡን ያተራምሰው ጀመር። መፍትሔው ታውቆ መከላከል እስከተቻለበት ድረስ የጨረሰውን ወጣት ኢትዮጵያዊ (ት) ቍጥር፣ ቤቱ ይቍጠረው ከማለት በስተቀር መገመት አይቻልም።

ከጊዜ በኋላ የወጣለት ስም " ሞኝ ባገኝ " ይባላል። " የወረርሽኝ በሽታ " ስም ነው። ከተገኘለት መፍትሔ ጋር የተዛመደ ሥያሜው ነው። ይህ በሽታ ቢያዘ በሦስተኛው ቀኑ ለጥብስ እንደሚያደርስ ተነግሮለታል። በነዚያ ሦስት ቀኖች ውስጥ፣ ከግጥወልወል አንስቶ፣ ደረቅ ራስ ምታት በማስከተል፣ ሁለንትናን ቀስፎ በመያዝ፣ ወደ ላይ ያስመልሳል፣ ወደ ታችም ያስቀምጣል። " ሞኞችና የዋህን ይተወናል ብለው ችላ ሲሉ፣ በሦስተኛው ቀን ይዞአቸው ይሔዳል። " ብልጦቹ ግን ሦስት ቀን እንዲቆይ ዕድል አይሰጡትም። ገና በሽታው ሲጀምራቸው፣ ቶሎ ብለው ከግራ እጃቸው በክርናቸው በስተጀርባ ላይ የተጋደመውን የደም ሥር፣ በተገኘው ስለት ያለፍርኀት ይበጡታል። ወዲያው ጥቁር ደም ፊን ብሎ ይፈሳል።

t.me/OLDBOOKSPDF

የዚህ ጥቁር ደም ባስቸኳይ መፍሰስ፣ የበሽታውን ቅጽበታዊ ፈውስ ይዞ ይመጣል። ከዚያም በኋላ፣ ያንን ሰው፣ እርም ብሎ ተመልሶ አይነካውም። ሞኞች ግን በዚህዘዴ፣ በፍራቻም ሆነ በሌላ ምክንያት ስለማይጠቀሙ፣ ተላላፊው በሽታ እነሱን ባገኘ ቍጥር ድል ይመታል። በሽታው ይህን " ሞኝ ባገኘ " የተሰኘ ሥያሜውን ሊያተርፍ የበቃው፣ ባጭር አገላለፅ፣ በተጠቀሰው ምክንያት ነው።

ይህ በሽታ ከነበረው አስደናቂ ጠባዮች አንዱ፣ ለወጣቶች ብቻ ውሱን መሆኑ ነው። የበሽታውን መግባት የሰሙ ቤተ ሰቦች ሁሉ፣ መፍትሔውን በወቅቱ ለማግኘት፣ ያልደረሱበት ቦታ፣ ያልቧጠጡት ኮረብታ፣ ያልቀነጠቡት ዕፀዋት፣ ያልጨለፉት ዥረት፣ አልነበረም። ከነዚህም በተጨማሪ የየሆስፒታሉ ዶክቶሮችና፣ የየመንደሩ ጠንቋዮችና መጣፍ ገላጮች ይገኙበታል። አንዳንድ የሕክምና ሊቃውንትም፣ "ታላላቅ የዘመኑ ቦምቦችና ሮኬቶች የሚፈተኑት ከበረሐ ላይ ነው" የሚለውን ጭብጥ ይዘው፣ ምናልባት የበሽታው ምንጭ " ሬድዮ አክቲቭ" የፈጠረው ጠንቅ ነው ብለው፣ እስከመራቀቅ ደረሱ። አንዳንዶቹም ከዚሁ ባልራቀ ግምገማ፣ በሽታው ከመነጨበት አካባቢ ብዙ ዐይነት ጦርነቶች የተካሔዱበት ስለሆነ፣ የዘመናይ ጦር መሣሪያዎች ያስከተለው አደገኛ መርዝ ነው ያሉ አሉ። የተቀሩትም እንዲያ ያለ " ቫይረስ "፣ ከዚህ ቀደም በዓለም ላይ ያልነበረና ሕክምና ጠበብቶችም ያልደረሱበት በሽታ ነው ሲሉ፣ ገለልተኛ አስተያየታቸውን ሠነዘሩ። ይህ ዐይነቱ የሐኪሞች አስተያየት ትክክለኛነቱ ቢያጠራጥርም እንኳ፣ እንደ

ሙያቸው አስተሳሰብ የተሠነዘረ በመሆኑ፤ ተቀባይነት ባያገኝም "እንኪያ ሰላንቲያ" ይባልበታል። በጣም የሚገርመውና የሚያስቀው ግን የኢትዮጵያ ወታደራዊ ዐብዮት በሚሰጡት ተግባራዊ ድርሻ አምኖ በመቀበል ምንም ዐይነት እርምጃ ያልወሰደባቸው፤ የየመንደሩ ጠንቋዮች፤ ባለውቃቤዎች፤ መጣፍ ገላጮች፤ ስለበሽታው የሰጡት አስተያየት ነው።

መቸም የጨነቀው ሰው፤ የደረሰበትን ጭንቀት ለማስወገድ የማይደርስበት ቦታና የማይሞክረው ዘዴ የለምና፤ በተላላፊው በሽታ ልጆቻቸው የተያዙባቸው ቤተ ሰቦች፤ ልጆቻቸውን ለማዳን ያልደረሱበት ድቢ ደብዳቢ፤ ያልረገጡት የጠንቋይ ደጅ፤ ያልተሳለሙት የመጣፍ ገላጭ በር አልነበረም።

ዛሬም እንደወትሮው፤ የባለውቃቤነት ዝናው በዓብዮታዊት ኢትዮጵያ ጭምር በጣም ገናና ሆኖ የሚገኘው የቄራው ቀበሌ ጠንቋይ፤ ለዚህ ተላላፊ በሽታ መፍትሔ ይሆናል ብሎ የሰጠው መድኃኒት "--- የጥንጁት ቅጠል፤ የሠንሠል ስር፤ የውሻ ኩስ፤ የዝንጆሮ ንፍጥ፤ ባንድ ላይ አድርቆ አድቆና ሠልቆ፤ ወደምሥራቅ በሚፈስ የወንዝ ወሃ በጥብጦ በፍንጃል ማጠጣት ነው" የሚል ነበር። ሌላዋ የዶሮ ማነቂያ ባለ አዶክ ብሬዋ ጫት ቃሚ፤ ለተጠቀሰው ተላላፊ በሽታ የበኩሏን መፍትሔ ስትናገር፤ "ከበረሀ የመጣን እንግዳ፤ ቁጠማ ጐዝጉዛችሁ፤ ጠጅ ሣሩን ነስንሳችሁ፤ አረቄውን ከርክፋችሁ፤ እጣኑን፤ ከርቤውን፤ ሠንደሉን እያጨሳችሁ በመቀበል፤ ያዳልሞቴን፤ የራሔሎን፤ የአውልያን፤ የሌጌዎንን፤ የመጀንን ምሶች በማቅረብ ማስተናገድ ነው። እንግዳው ቂመኛ አይደለምና በሰላም እንደመጣ በሰላም ይመለሳል" በማለት ነበር የመረቀነችው። እንደሌሎቹ ግብረ አበሮቹ ሁሉ የእንጦጦው

t.me/OLDBOOKSPDF

መጣፍ ገላጭም፤ ስለተላላፊው በሽታ ሲፈላሰፍ ያተተው "--- ያለንበት ሐራ ዘመን ወልጋዳ ነው። ዐውደ ወርኁም ዐውደ ፀሐየም ከውሉ ስቶ ያፈነገጠበት ቀውጢ ዘመን ነው። ዑደተ ከዋክብቱም ከኬሮስ ይልቅ ለኬንትሮስ አጋድሏል፤ ከሠሌዳ- ሰማይ እንደሚታየው ከሆነ፤ ቀመሩ ጐደሎ ነው። ከሐሳበ ሕይወት ይልቅ ሐሳበ ሞት ጐልቶ ይነበባል። ከፀጋማይ ይልቅ ለየማናይ ይቀናል። መላውን ሠንጠረዥ አመላክተን በከሠተው ቅምር ሲገደፍና መባጃ ሐመሩ ሲሰላ፤ ለዘመኑ የሚላከውን መቅሠፍት ወለል አርጐ ያሳየናል። ከሐዘሎ በረሐ የመጣው ተላላፊ ደዌ ብዙ ጊዜ አይሰነብትም። በዚያው አጭር ጊዜ ውስጥ ግን ብዙ ይቀጫል። በፊደል ትርጁማን ሲታተት፤ "ሸ" ንና "አ"ን አይደፍርም። " ሕ" ንም አይነካም። የሚረፈርፈው ግን "ወ" ና "ዘ"ን ነው። መዳኛው መፍትሔ አንድ ብቻ ነው። ይኸውም የመብረቅ ከሰል መታጠን። ወዲያው ለቆ ይበናል ይተናል! ---" የሚል ነው።

ሁሉም አዋቂ ነኝ ባይ፤ ጨንቆት ለጠየቀው ሕመምተኛ የየበኩሉን እንደመሰለው ቀባጠረ። ሌላው ቢቀር፤ " ዐብዮታዊው መንግሥት" አምኖበት ለተቀበለው ሙያው፤ በየወሩ ለሚያስከፍለው የሥራ ግብር የሚያሟላበትን ዲናሮች ቀር ጭሟል። በዚህም ተግባራዊ አገልግሎቱ፤ ዐብዮታዊ ግዴታውን እንዳበረከተ፤ ገንዘብ የከፈለበት ካርኔ ሳይቀር ያረጋግጥለታል።

በተግባር ላይ ውሎ፤ ለተባለው ተላላፊ በሽታ ፤ ሙሉ መፍትሔ ሊያስገኝ የቻለውን፤የክንድ ደም ስር የመብጣት ሕክምናዊ ዘዴ፤ ግን እንዳስገኘው፤ በውል ባይታወቅም፤ " ዐብ

ዮታዊው መንግሥት " ፣ የሥራ ግብር የሚያስከፍላቸው አባይ ጠንቋዮች እንዳይደሉ ተረጋግጧል። ምንም እንኳ፣ ያስተካከሙ ዘዴ ከዘመናዊው ሕክምና ቴክኒክ ጋር የጠበቀ ዝምድና የሌለው ቢመስልም፣ እስከፈወሰ ድረስ፣ በሕመም ተኛቹ ዘንድ ተቀባይነትን ካገኘ፣ መድሐኒትነቱን መካድ አይቻ ልም። ምናልባትም፣ ለተላላፊ በሽታዎች መከላከያ እየተባለ ክትባትስ ይደረግ የለ ! የደም ሥር መብጣቱም የዚያ ብጤ ይሆናል። ጥቁር ደም ግን ፊን ብሎ መውጣቱ፣ ታንኪር ሊያ ሰኝ ነው !!

ይህ ተላላፊ በሽታ በተስፋፋበት ሰሞን በሕክምና ሊቃ ውንት አካባቢ ከፍተኛ ጉምጉምታ ተፈጥሮ ነበር። ከቶውንም ስብሰባ ብጤ ተደርጉ፣ ከበሽታው ጠባይ ዐይነት አንስቶ፣ መከ ላከያውን የማጥናትና፣ በመጨረሻም ስለበሽታው ምንጭ ምር ምር ድረስ የጠፈ ውይይትና ክርክር ተካሒዶ ነበር። ያም ስብ ሰባ፣ " የተባለውን ተላላፊ በሽታ ምንነት ለማወቅ፣ ምንጩን መረዳት አማራጭ የሌለው መዳረሻ ዘዴ ነው....." የሚል ውሳኔ አስተላልፎ ነበር። ይህም ውሳኔ፣ የሳበውን ሁሉ ስቦ፣ ከፍተኛ መዘዝ በማስከተሉ አንዳንድ በስብሰባው ላይ ቀንደኛ ተካፋይ የነበሩትን ሐኪሞች እስከማሠር አብቅቷል። ዋናው መነሾ፣ በስብሰባው ላይ የተነሱት ፣ ጥያቄዎች እንደሠንሠለት እየተያያዙ፣ ለበሽታው መፈጠር ምክንያት የሆኑትን ምንጮች በመጠቆማቸው ነው። ስብሰባው ካነሳቸው ጥያቄዎች ውስጥ፣ ሐኪም "በሽታው በአሁኑ ወቅት የትኛው ሥፍራ ላይ ይታያል? "

ኣዝማች_" አዲስ አበባ ከተማ ላይ። "

ሐኪም _" በምን አካባቢ ? "

t.me/OLDBOOKSPDF

ኣዝማች_" በእድገት ዘማች ቤተሰቦች ውስጥ!"

ሐኪም_" እዚያ ቤተ ሰብ ውስጥ ብቻ እንዴት ሊገኝ ቻለ? "

ኣዝማች_" ዘማቾች ይዘውት መጡ። "

ሐኪም_" ከየት ክፍለ ሀገር ? "

ኣዝማች_" ከበረሐ። "

ሐኪም_" ዘማች ለምን በረሐ ሔደ ? "

ኣዝማች_" የልማት ሀገራዊ ጥሪ ግዴታ ለማሟላት። "

ሐኪም_" በረሐው ነዋሪዎች ነበሩበት? "

ኣዝማች_" ምድረ-በዳ ነው። "

ሐኪም_" አካባቢው በተቀዳሚ ተጠንቶ ነበር?

ኣዝማች_" አናውቅም! "

ሐኪም_" ከዘመቻው ተጠሪ፣ ማብራርያ ይቅረብልን !...."

ከዘመቻ ዋና መምሪያ ባሉ የበላይ ባለሥልጣኖች፣ ለቀረቡ ጥያቄዎች፣

የዘመቻ መሪ_" ከተባለው ሥፍራ፣ በተሰጠኝ ትእዛዝ መሠረት አዝምቻለሁ--- "

ተጠሪ ሓኪሞች_" ስለዘመቻው ቦታ አስቀድሞ መጠናት የሚ ያውቁት አለ? ።

የዘመቻው መሪ_" አይመለከተኝም። የበላዮቼን ጠይቁ! "

ተጠሪ ሐኪሞች_" ማን የሚያስረዳን ይመስልዎታል? "

የዘመቻው መሪ_" ምናልባት የመምሪያው ኃላፊዎች!"

ተጠሪ ሐኪሞች_" ስለመልሶችዎ እናመሰግናለን!ይበቃናል!

የመምሪያ ኃላፊ_"ለጥያቄው እንደፈለጋችሁኝ አንድ የመምሪያ አባል ነገረኝ "

ተጠሪ ሐኪሞች_" አዎ አዝማች ስለነበረበት በረሐ፣ አስቀድሞ

መጠናትና አለመጠናቴን ለማወቅ ፈልገን ነበር። እንደሚ ያውቁት የተላላፊ በሽታ ከዚያ----"

የመምሪያ ኃላፊ__"ይህን ጥያቄ እንዳነሳችሁበት አዝማቼም ነግሮኛል። ግን አንድ ያልተነዘባችሁት ነገር አለ። የዐብዮት ጥሪ ቦታ አይመርጥም። ሆኖም ያነሳችሁት ጥያቄ ከኔ ዐቅም በላይ ነውና፣ ለበላይ ባለሥልጣን አስተላልፋለሁ። ማብራ ሪያውን ከሳቸው ታገኙ ይሆናል።"

የበላይ አካል__"የደርግ አባል ነኝ። የማዕከላዊ ኮሚቲም አባል ነኝ። የኢሰፓአኮም አባል ነኝ። ለጥያቄ እንደምፈለግ ተነግሮኝ ነው የመጣሁት።

ሐኪሞች__" በጣም አደገኛ ሆኖ ስለተገኘው፣ የተላላፊ በሽታ፣ መከላለከያ መፍትሔ ለማግኘት ጥናት ላይ ስላለን፣ ለዚሁ ዝግ ጅት እንዲረዳን፣ የዘመቻው ቦታ፣ አስቀድሞ መጠናትና አለመ ጠናቴን ለማወቅ ፈልገን ነበርና ---"።

የበላይ አካል__" መቸም ያን ያህል ቍጥር የያዘ ዐብዮታዊ ዘማች ሠራዊት፣ ካንድ ቦታ ሲላክ ያለጥናት የሚሠማራ አይመ ስለኝም። ይኸ መቸም ዋናው መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ያለጥ ናት የተደረገ በዐብዮታችን አንድም ነገር የለ። አምናለሁ ቦታው ተጠንቷል። ይሁን እንጅ ዝርዝሩ እንዴት እንደሆነ፣ እኔን ስለማይመለከት፣ የበላይ ባለሥልጣን ሊያስረዳ ይችላል። ይህንም የመጠየቅ ፍላጎታችሁን አቀርባለሁ።"

ዋና ፀሓፊ__" ዋና ፀሓፊ ነኝ። ጥያቄያችሁን ሰምቻለሁ። እኛ ብዙ ከፍተኛ አጣዳፊ ጉዳዮች በየቀኑ ስላሉብን፣ እንዲህ ያለውን ዝርዝር ተግባር ለማወቅ፣ ጊዜም ዐቅምም ዕድልም የለንም። ቢሆንም ለንዲህ ያለው ዝርዝር ተግባር አቅድ ሁሉ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

አጠቃላይ መምሪያ ያለ በመሆኑ፣ ዘመቻው ላንድ ቦታ (አካ ባቢ) ጥናት የተወጠነ አይመስለኝም። ለሁሉም ምድብ የየዘርፉ አማካሪዎች ስላሉ፣ የበላዩን ከመጠየቁ በፊት፣ ስለጉዳዩ የሚያ ውቁትን እንዲያብራሩላችሁ፣ ሁለንም በየተራ እልካለሁ-----"

አማካሪ__" በምሕዋር ስሜ ቫራዎቭ እባላለሁ። ሩሲያዊ ያለም አቀፍ ወዳጅነት አማካሪ ነኝ። ጥያቄአችሁንፀሓፊው ነግሮኛል። ግን ስለጉዳዩ ምንም የማውቀው ነገር የለም። በርግጥ ያለ ተቀዳሚ ጥናት ተዘምቶ ከሆነ ከፍተኛ ስሕተት ነው!"

አማካሪ__"ራውል ቫልዲስ ቪቮ እባላለሁ። ኩባዊ ነኝ። የቀረበልኝ ጥያቄ እኔን አይመለከተኝም። እንደማይመለከተኝ ልነግራችሁ ነው የመጣሁት። አማካሪነቴ ለጦር ነው።"

አማካሪ__"ምሥራቅ ጀርመናዊ ነኝ። ሆረሰት ይሁለስ እባላለሁ። በዐብዮት ኪደት ውስጥ ብዙ ስሕተቶች ሊደረጉ ይችላሉ። ይህንንም ሐቅ ባለፉት ዐብዮቶች ታሪክ ውስጥ በየም ዕራፉ ዐይተናል። ግን ዋናው ቁምነገር፣ ከትክክለኛው ተግባር ይልቅ ስሕተቱ ያነሰ መሆነ ነው። ስለዚህም ነው ሕዝቦች ድል የሚያገኙት። ወደ ጥያቄአችሁ ልመጣና፣ ጥያቄው ትክክለኛ ይመስለኛል። ግን እኔን ስለማይመለከተኝ መልሱን ልሰጣችሁ አልችልም። በነገራችሁ ላይ የኔ ሙያየና ሥምሪቴ፣ በፀጥታ ተግባር ላይ ነው። ሌሎቹን አማካሪዎች መጠየቁ ያዋጣል!"

የነዚህ የሥስቱ አማካሪዎች ምላሽ ተሰምቶ እንዳበቃ፣ የሐኪሞቹ ስብሰባ ቀጥሎ ነበር። በዚያው በውይይታቸው ላይ እንዳሉ፣ ድግን መትረየስ በያዙ ወታደሮች ተከበው፣ ዋና ዋና ዎቹ ቀንደኞች ተነቅሰው፣ ወደ ማረፊያ ቤት እንደተወሰዱ፣ ስብሰባው ወዲያው ተበተነ። በቋሚ ተጠሪም የተስተናገዱ

ነበሩ። ስብሰባው ይበተን እንጅ፣ ባልታሠሩት ጥቂት ሓኪ ሞች፣ በጉዳዩ ላይ ግለኛ ትችት ቀጥሎ ነበር። ሁኔታው በጣም ያበሳጫቸው፣ " ዐብዮታዊ ጥሪ እንዴት ቦታ አይመጥርም ይባላል? ያን ያህል ወጣትና የተማሪ ጉልበት የትም በረሐ ያለ ተቀዳሚ ጥናት መስደድ፣ ዐብዮታዊነቱ ከምኑ ላይ ነው? ስንት ደጋና ወይነ ደጋ መሬት፣ ደረቱን ገልብጦ፣ የሠራተኛ ያለህ እያለ ሲጮህ፣ ያን ሁሉ ሠራዊት ንዳድ ከሚፈላበት ምድረ በዳ መስደድ፣ ዐብዮትነቱ ከምን ላይ ነው? ለዚሁ ዐይነት ዘመቻ ' የዐብዮት ጥሪ፣ የቀይ ኮከብ ጥሪ ' እየተባለ በሙገሣ ሲዘፈንለትና ድርሰት ሲደረስለት፣ መስማትም ሆነ ማየት ወንጀል ነው። አስቀድሞ ባልተመረመረና ባልተጠና በረሐ፣ ወጣት ታዳጊዎችን ወስዶ ያለዕድሜአቸው እንዲቀጩና እንዲ ያልቁ ማድረግ ይቅርታ የማያልፈው በደል ነው። ይህንን መሰል አሠቃቂ ኢሰብአዊ በደል የሚፈጽም መንግሥት፣ "ዐብ ዮት " የሚለውን ክቡር ቃል እንኳንስ ሊጠቀምበት ቀርቶ፣ በሕልሙ ሊያየው አይገባም። በዚህ ተላላፊ በሽታ ተለክፈው፣ ያለዕድሜአቸው የተሠዉ ወጣት መገኖቻችንን፣ የህገራችን የወደፊት ተራማጅ ታሪክ ሲያስታውሳቸው ይኖራል።

በዐብዮት ስም ለተፈፀመው አልቂትና ፋሽስታዊ ደባ ግን ምን ጊዜም ቢሆን ተጠያቂዎቹ ፋሽስቶቹ ባለሥልጣኖች ናቸው። በፈፀሟቸው ፋሽስታዊ ግፎች ሁሉ፣ ተጠያቂነታቸው አጋልጧቸው፣ አንድ ቀን ለፍርድ እንደሚቀርቡ፣ በማንኛውም አመዛዛኝ ጎሊና ውስጥ የሚጐላላ እውነታ ነው። የስንት ንፁሓን ለጋ ወጣቶች ሕይወት፣ ሰው ባልደረሰበት ምድረ-በዳ ውስጥ፣ እንደጣሉት ቅራቅንቦ ቆሳቍስ ተንከታክቶ ሲወድም

t.me/OLDBOOKSPDF

ማየት፣ የብዙ መጭ ትውልዶች ታሪክ የሚያስታውሰው የሚዘ ገንን ትዝብት ነው።

ይህ አሰቃቂ ድርጊት ከኛ የሕክምና ሙያ ተግባር ጋር በተዛመደ አጋጣሚ የተከሠተ በመሆኑ፣ ለተላላፊው በሽታ መንሥኤ የሆነውን " ዐብዮታዊ የልማት ዘመቻ " የሚሉትን ፈሊጥ፣ ዐቅማችን የፈቀደልንን ያህል በመቃወም፣ ፋሽስታዊ ባህርዩን ማጋለጥ አለብን። ለዚህም የማጋለጥ ትግላችን የሚረዳን፣ በዐብዮት ስም ተሠልፎ ፋሽስታዊ ደባ የሚፈጽ መውን መንግሥት አንዳንድ እበላ ባዮች፣ በራሳቸው ግላዊ ጥቅም አንግር ተነስተው ሲያሞግሱና ሲቀድሱት፣ ሲዘምሩለትና ሲዘፍኑለት ባየን ቍጥር፣ ሕዝቡ ከመሰበኩ በፊት፣ ተገቢውን ሓቀኛ ጐዳና በማሳየት የሰባኪዎቹን ተንኰል ያጋለጥን እንደ ሆነ ነው።

ይህ በዐብዮት ስም የሚነግድ መንግሥት፣ ፋሽስታዊ ሸፍጡን ጭኖ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ፣ በግዴታ በሕዝቡ ላይ ለማራገፍ፣ ያልተጠቀመበት ዘዴ የለም። በተለይም ደራሲያንና ጋዜጠኞችን፣ ሠዓልያንና ሙዚቀኞችን፣ እንዳሻው አገ ላ ብጦ ተጠቅሞባቸዋል። ከየቦታው የተለቃቀሙ እበላ ባይ ቱኪ ቹም፣ እድሜውን ያስረዘሙለት መሰሏቸው፣ ያልቀባጠሩለት ቱግታና ያልነፉለት እንቢልታ የለም። የፋሽስቱን ሸቀጥ ለማዋደድ፣ አሻሻጭ ቅጥረኞች በመሆናቸውም፣ ያልደረ ደሩለት ሪክለምና ያልጀነጀኑለት ማስታወቂያ አይኖም። ፋሽስ ታዊነቱን፣ በዐብዮታዊነት ለመተካት ያልመቱለት የውሸት ነጋ ሪት፣ ያላስተጋቡለት የውሸት አዋጅ፣ ያልነፉለት የዕድገት ቱል ቱላ አይኖም።

ፋሽስታዊው መንግሥት በየዕለቱ ያርዳል፣ ይረሽናል፣ ያቃጥላል። ፋሽስቱ በየዕለቱ የሚፈፅመውን፣ በተለይም ይህንን ኢሰብኣዊ ግብር፣ ይህንን አመፃዊ በደል፣ ይህንን በዐብዮት ስም ያሚፈፅም ግፍ፣ ይህንን ያደባባይ ፋሽስታዊ ደባ፣ በጽሑፋዊ መጋረጃቸው የሸፈኑለት መስለው፣ አንዳንድ የኪነት ውር ውር ባይ ፋሽስት አደር ደራሲያንና አርቲስቶች እንደቃተቱ አሉ። በተለይምለፈውዳሉ ባለሥልጣኖች ጋሻ ጃግሬ ሆነው፣ ተራማጆችን ነዳፊዎች ሲከላከሉላቸው ኖረው፣ ዛሬ ደግሞ በተራው ለፋሽስት ባለሥልጣኖች ባለሟል ሆነው ሥሉሣቸውን ያዞሩ፣ የኪነት ሰዎች፣ ወላዋይ አቋማቸው የሚያጠያይቅ ከመ ሆን አልፎ፣ ተገቢ ዋጋቸውን እንዲያገኙ አሳሳቢ ከሆነ ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ፋሽስቱ መንግሥት የግፍ ድርጊቱን በሶሻሊ ዝምና በዐብዮት ካባ ሸፍኖ በየዕለቱ የሚፈፅመውን ዳባ፣ "ከ ሀ ሁ ጀምሮ፣ በአቡጊዳ በኩል፣ የቀይ ~ኮከብ ጥሪ " እስከሚለው ድረስ፣ የፋሽስቱን ደባዊ እርምጃዎች ሁሉ፣ ተራማጅ ድርጊት ለማስመሰል ሞክረዋል። ጭብጡንና ሓቀኛውን የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ጊዚያዊ ሁኔታና ኑሮ፣ የሚያውቅ ሁሉ፣ የእነዚህ እበላ ባይ ደራሲዎች እሪታ፣ የገደል ማሚቶ መሆኑን በግልፅ ሊረዳው ይችላል። የነሱ የውሸት ድርሰታዊ አዋጅ፣ የኢትዮጵያን ጊዚያዊ አሳዛኝ ሁኔታ ሊለውጠው አይችልም። በተለይም፣ የፋሽስቱን መንግሥት ለማንበርከክ የሚታገሉትን ተቃዋሚ ኃይሎች ለማዳከምና፣ የሲሰባቸውንም ባሕርይ ለመስ ጠት ከመጠን በላይ፣ በድርሰታቸው ውስጥ ጥረዋል።

ያራምባና የቆቦውን እየቀባጠሩ፣ " በሕይወት ያልነበሩ ሰዎችን " ባሕርይ እንገልፃለን ቢሉም፣ ራሳቸው የሚኖሩበት

የንዑስ ከበርቴነት ወላዋይ ጠባየቸው፣ በውሸታምነት ያጋልጣ ቸዋል። ከሁሉ ይልቅ በጣም የሚያስገርመው፣ በፍጹም ቆራጥ ነት ኢሕዝባዊውን መንግሥት ለመቋቋምና ለመቃወም ባጭሩ ታጥቀው የተሠለፉበትንና፣ ለጭቁኑ ኢትዮጵያዊ ወገናቸው አጋር የሆኑትን ታጋዮች፣ በገዛ ራሳቸው እበላ ባይነት ዐይነ ልቦናቸው ተመልክቶ፣ እበላ ባዮች ለድርጐ ለማሳየት መሞከሩ ነው።

የዘመኑን የስነ-ጽሑፋዊ ይዘት በዐይነሕሊና ብንመረ ምር፣ የፋሽስት መንግሥት ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ እያደገ የመ ጣውን የሥነ ጽሑፍ መጫጫት በጉልህ የሚያሳይ ማስረጃ ነው። ኪነትም በድርሻዋ በወታደር አፈ-ሙዝ ፋሽስታዊ ስለት ተገዝግዛለች። በተረፈ ግን፣ የፋሽስቱን የጉልበትና የደን ደስ ኣገዛዝ፣ " የናት ሀገር ጥሪ፣ የዐብዮት ጥሪ፣ የቀይ ኰኮብ ጥሪ፣ የእድገት ዘመቻ፣ የልማት ዘመቻ-- " እያሉ ሶሻልስታዊ መልክና ስም በመስጠት፣ ለማስመሰል የሚምክሩትን ሁሉ፣ የፈ ጠረውን ልዩ ልዩ፣ የድህነት፣ የድንቍርና፣ የግባርነት፣ የበሽ ታና የእልቂት ጠንቆችን በማስረጃነት በማሳየት፣ ፕሮፓጋ ንዳን፣ በጥልቅ ሁኔታዎች በመመከት፣ ማንኛውም ተራማጅ ወገን ሊቋቋማቸው ግዴታ አለበት። እኛም በበኩላችን፣ ይህን የተላላፊ በሽታ መሠረተ-ምክንያት መነሻ በማድረግ አቋማች ንን በይፋ ለመግለጽ ሠላማዊ ሠልፍ እናደርጋለን!" ብለው ለረዥም ጊዜ ሲወያዩ ከቆዩ በኃላ፣ የሚከተሉትን መርሖዎች ለሠልፋቸው አዘጋጁ።

" ለተላላፊ በሽታ ምክንያት የሆኑ ሰፍርድ ይቅረቡ! "

" ከጭብጥ ሁኔታ የራቀ ፕሮፓጋንዳ ይወገዝ!"

t.me/OLDBOOKSPDF

“ የእበላ ባዮች ደራሲያን መጻሕፍት ባደባባይ ይቃ ጠሉ! ”

“ በሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ ሕዝቡ የመወሰን መብት ይኑረው!”

“ አስመሳይ ሶሻሊስቶች ይውደሙ!”

“ በበረሐ ለተሰዉ ወጣት ወገኖቻችን መታሰቢያ ይቁም! ”

“ ሶሻሊስታዊ እውነት ምንጊዜም ትኑር!--- ”


እነዚህን የመቃወሚያ መርሖዎቻቸውን በሠሌዳ ላይ ፅፈው ካዘጋጁ በኋላ፣ ለሚያደርጉት የመቃወሚያ ሰላማዊ ሠልፍ፣ አጃቢ ደጋፊዎችን ለመሰብሰብ፣ የጥሪ ወረቃታቸውን በድብቅ በተኑ።

ምንም እንኳ ኢሕዝባዊ መንግሥት በጉዳዩ ነቅቶ፣ ሠልፋቸውን በጠመንጃ አፈሙዝ ደግኖ ቢያጨናግፋቸውም፣ በተባለው ቀንና ሰዓት ሰልፉን አካሒደው፣ የጠበቁትን መለስ ተኛ ውጤት ለማግኘት በቅተዋል። ይሁን እንጅ ያን ውጤት ለማግኘት የከፈሉት መሥዋዕትነት ቀላል አልነበረም። በሰላማ ዊው ሠልፍ ላይ የተገደሉም የቆሰሉም ነበሩ። በተለይም፣ በልዩ ዝግጅት “ ድንቄም ሶሻሊዝም ” የተባለ የፀጉር አሠራር በመጠቀም፣ የፋሽስቱን አቋም ለማጋለጥ፣ በየዕለቱ ግንባር ቀደም ላይ ተሠልፈው የነበሩ፣ የተላላፊ በሽታው ልጆቻቸ ውንና ወንድሞቻቸውን የገደለባቸው፣ እናቶችና እህቶች ሞተ ዋል፣ ቆስለዋል፣ ታስረዋል።

ሰላማዊውን ሠልፍ ካዘጋጁት የሕክምና ዶክቶሮች ውስጥ፣ ዋናዎቹ መሪዎች፣ ከዚያ ቀን ጀምረው የት እንደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደረሱ አይታወቅም። የዚያን ከፍተኛ ሰላማዊ ሠልፍ መል እክት ለማድበስበስና፣ ባሕር ማዶ ድረስ አምልጦ የወጣውን የዘማቾች እልቂት ዜናና ያስከተለውንም የፕሮፓጋንዳ ተፅዕኖ ለመቋቋም በታሰበ እቅድ፣ የኢሕዝባዊው መንግሥት ባለሥል ጣኖች የ “ ሞኝ ባሸ ” ን ተላላፊ በሽታ ምንጭላለማሳየትና በዚያም አካባቢ አንድም የዘማች ቡድን እንዳልተሠማራ ለማሳመን፣ ለውጭ ሀገር አምባሣዶሮችና ለታወቁ ጋዜጠኞች ከስፍራው ድረስ ጉዞ አዘጋጅቶ አስተናገደ። በያለበትም በተፈ ለፈሉት የቀበሌ ኪነት አባሎች አማካኝነት፣ “ ተላላፊው በሽታ ጠፍቷል”፣ “ በሶሻሊስት ሀገር ሞኝ የለም! ” የሚሉ የፕሮፓ ጋንዳ መዝሙሮች አዘመረ። ላንዳንድ የተረፉ ዘማቾችም የዐብ ዮት መዳልያ ሸለመ። ከነዚህም ማደናገሪያዎቹ ይበልጥ ያስደ ነቀው፣ ራሱ ለፈጠረው ግዳይ የተጠቀመበትን የበቀል ርምጃ ነው። ይኸውም ለተላላፊው በሽታ መነሻ ምንጭ የሆነችው ያች የበረሐ መርዘኛ ትንኝ፣ መናኻሪያዋ ነው በሚል ግምት፣ ያን የሚያሳዝን የዱር ሀብት፣ ሠደድ እሳት ለቆበት፣ ዘሬም እንደነደደ አለ።



ሩቢያ



ለውጥ አለ ይሉናል ሰማን እንጅ አላየን!
ባላገር እኛ ግን እንዳለነው አለን!
ሙቀጫና ወፍጮ ቁናና እንሥራ እያላገጡብን!

(የጠፍ.*.6)

t.me/OLDBOOKSPDF

መንደርደርያ

ከመጻሕፍት ብቻ ከተቃረሙ ድፍን ንባበ-ቃላት በመመራት፣ የሕዝብን ያካባቢ ጭብጥ ሁኔታዎች፣ በባሕሉ፣ በልምዱ፣ በእምነቱ አንፃሮች ያሉትን ጊዜያዊ ኃይሎችና ድክመቶች፣ በሚገባ ሳያጠኑ፣ እንዲው ዘለው ከኅብረተ-ሰቡ ውስጥ በመግባት፣ ሥር ነቀል ለውጥ እናድርግ ለሚሉና ለሚያተራምሱ የበታች ሹማምንት (ካድሬዎች) ትምህርትና ተመክሮ ይሆናል። በሌላ ጐኑ ደግሞ፣ እነዚህን መሰሎቹ ተምኔታውያን ካድሬዎች፣ በዓብዮት ስም ለሚፈፅሙት ሕዝባዊ በደል፣ የስንቱ ቤት ትዳርና ንብረት መፍረስ እንደቻለ የሚያሳይ፣ የወርኀ ማዕዶት (የሽግግር ዘመን) ችግር ማንፀባረቂያ መስተዋትም ነው።



"ዚአኪ ለዚአየ"፣ እንዳለው ያ መጣፍ፣
ነውሩ ምን ላይ ይሆን? በወል መደጋገፍ!
አጥቤሽ ብታጥቢኝ፣በኩልነት ብናርፍ፣
"አንድ አካል"ስ ማለት፣ነው ወይ ከዚህ የሚያልፍ?

t.me/OLDBOOKSPDF

ሩቢያ

.... ካፈ-ድስት ባላነሰ ትልቅ ማሠሮ ውስጥ ውሀ ጥዳ ለች። እንጨት እንደልብ መቍረጥ ከተከለከለበት ጀምሮ፣ የጮልቻ ላይ ማሠሮዎች በእሳት ነበልባል ከመጠን በላይ መለብለቡ ቀርቶላ ቸው፣ መዝናናት ከጀመሩ ዐመታት አልፏቸዋል። አዘውትራ "ለማ ሰሮዎች እንኳ ጊዜ ይውጣ! " የምትለዋ ሩቢያ፣ እንደልቧ የምት ማግደው እንጨት እንደወትሮው ባለመገኘቱ፣ የምትጥደው ሁሉ ቶሎ አልበስል አልፈላ እያላት በሚያስከትለው ምሬት እየበሸቀች ነው። ማድቤቷ በዚያው በትልቅ ሠቀላ ቤቷ ውስጥ፣ ካንደኛው ጥጋት ላይ ነው። ሲቀመጡ እግር ሊያስቆም የሚያስችል ያህል ክብ መደብ በምድጃው ዙሪያ አለ። በረባዷው ምድጃ ላይ ዘወትር የምትዝቀው የታመቀ አመድ ይገኛል። በመሐሉም ላይ የኰረዳ አጐጠጐጤ ጡቶች የሚመስሉ ሦስት የድንጋይ ጉልቻዎች ጉብ ጉብ ብለዋል። ያ ለባል እግር ማጠብያ እንዲሆን የሚዘጋጀውን ውሃ በማሞቅ ላይ የሚገኘው ማሠሮ ተንዘራፍጦ የተቀመጠው በነ ዚህ ጉልቻዎች ላይ ነው።

ከምድጃው በስተቀኝ ጥግ ጥጉን ይዞ መጠናቸው የተለያየ ጋኖችና ድብኝቶች ተደርድረዋል። የእህል ማከማቻዎቻቸው መሆ

t.me/OLDBOOKSPDF

ናቸው ነው። ከምድጃው በስተግራ፣ ከቤቱ ግድግዳ ጋር ተደግፎ የተተከለ ወፍጮ ቆሟል። ለሩብያ እህል የምትፈጭበት ወፍጮ ቤቷ ብቻ ሳይሆን፣ መንፈቀ ሌሊት በደረሰ ቊጥር፣ ከእንቅልፏ ተነስታ ዝግሬዋን የምታቀልጥበት የምሽት ክበቧ ጭምር ነው። ኑሮዋን የሚያስመለክት ደመ-ነፍስ ሐሳቧን በዜማ የምታን ጐራጉርበት የሙዚቃ አደራሿ ነው። መንፈቀ ሌሊት ላይ መጀን ይዛ ለወፍጮ በምትዘጋጅበት ቊጥር፣ ድንገት የሚፈልቅ ዘፈኗን በቅኝት ስታንጐራጉር፣ ወፍጮና መጅ በበኩላቸው በሚፈጥሩት ጃዛቸው ያጅቧታል። ታዲያ የዘንድሮ እንጕርጕሮዋ ይዘት ከወትሮው ለየት ይላል። በየቀኑ መንፈቀ ሌሊት ላይ ለወፍጮ ተግባሯ በተሠማራች ቊጥር፣መልሳ ቀልጣ፣ ደጋግማ ሠልሳ የምታዜመው

" ለውጥ አለ ይሉናል ሰማን እንጅ አላየን፣
ባላገር እኛ ግን እንዳለነው አለን፣
ሙቀጫና ወፍጮ፣ ቁናና እንሥራ፣ እያላገጡብን። "

የምትለውን ነው። ዜማዋን ለሰማ ልቅሶውን ለመቆጣጠር አይችልም። ሩቢያ ይህንን ይዘት ያዘለ እንጕርጕሮዋን ስታዜም ካን ጀታ ስለሆነ፣ የሰሚውን ማንኛውም ሰው አንጀት ስለሚበላ፣ ከፀፀት ነፃ አይሆንም። ከላኛውም እንጕርጕሮዋ ጋር አያይዛ የምታዜመው ፣

" ምን ዐይነት ለውጥ ነው ያላጠፋ ቅማል፣
ምን ዐይነት ለውጥ ነው የሚያጣላ ከባል፣
ምን ዐይነት ለውጥ ነው፣ ማምጣት ያልሆነለት፣ ከድሮው
የሚሻል

ዝምብሎ ባዶውን ባየር የሚፎልል! " ብላ በዕዝል የምትዘመውን እንጕርጕሮ ወደ ንጋቱ ላይ፣ ያካባቢዋ ወፎች ሳይቀሩ በዝግሬአቸው ያጅቧታል። እንጕርጕሮዋ መሥጫት ሞቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያረጋት ጊዜም፣ መጀን ከደረሰበት ላይ ታቆምና፣ ሽንጦቿን በጆቿ ደግና " እሽክም እስስ! እሽክም እስስ!..." እያለች እስክስታዋን ታስለነካዋለች። አልፎ አልፎም ራቅ ብሎ ደረቅ መደብ ላይ ተኝቶ፣ የንጋት እንቅልፉን ሲለጥጥ ያለ ባሏን፣ በዚሁ እስክስታዋ የምትቀሰቅስበት ጊዜ አለ።

ሩቢያ የሰላሣ ስምንት ዐመት እድሜ ያላት፣ የገበሬ ሚስት ነች። ባሏን ካገባችው አምስት ዐመታት ቢያልፏትም፣ ከአምስት ዐመታት በፊት ከወለደችው ወንድ ልጇ በስተቀር ሌላ ልጅ የላትም። እሱንም ቢሆን ማደጉ ሰጥታዋለች። ተወልዳ እስካሁን የምትኖረው በደቡብ ኢትዮጵያ በሚገኝ፣ በአንድ የክፍለ ሀገር ገጠር ውስጥ ነው። ባሏ ሞፈር ዘመት ገበሬ ሲሆን፣ "በለውጡ " ጊዜ በተላለፈው አዋጅ መሠረት፣ ከጢሰኛነቱ ነፃ ወጥቶ፣ የኩር ማን መሬት ባለርስት ሆኗል። በገዛ ርስትነት ላምስት ዐመታት ቢጠቀምበትም፣ ኩርማኑ መሬት ባስገኘለት ምርቱ ተደስቶ አያውቅም። የምርትነቱ ማነስና መብዛት ሳይሆን፣ የሚያናድደው፣ አዋጅ በሰጠው ሀብት ሊያዝበት አለመቻሉ ነው። የጋራ ጐተራ፣ የመዋጮ፣ የርዳታ.... እየተባለ፣ ላቡ ያስገኘለትን ምርት በሙሉ ሊያገኘው አልቻለም። "ብዝበዛ መልኩንና ባሌበቴን ቀይሮ መጣ" ነው የሚለው የሩቢያ ባል፣ ንዴቱ ገንፍሎ በቃላት እስትንፋሱ ሁኔታውን ለመግለጽ ሲሞክር።

በዚያን ዐመት አንድ ዕለት፣ በጥማድ በሮቹ እርሻ ውሎ ማታ ወደ ቤቱ ይመለሳል። በዚያን ዕለት ከወትሮው የተለየ ድካም ተሰምቶት ነበር። " ቤቴ ቶሎ ደርሼ፣ የጣመነ እግሬን ሚስቴ እንደተለመደው እሽትሽት አርጋ አጥባኝ፣ " እያለ ሲገሠግስ ቤት ይደርሳል። እንዳጋጣሚ በዚያንው ዕለት፣ የገጠር ሴቶች ማኅበር

ስብሰባ አድርጐ ናሮ፤ ከመንግሥት በተላኩ ሴቶች ካድሬዎች አማ
ካይነት " ስለ ሴቶች እኩልነት " ጉዳይ የመጀመሪያው ከፍተኛ
ውይይት ሲደረግ ውሎ፤ ሩብያም በዚህ ስብሰባ የመገኘት ግዴታ
ስለነበረባት፤ እዚያው ውላ፤ ቀደም ሲል ገና ከቤት መድረሷ
ነበር። እሷን ይበልጥ ያደከማት፤ ወደ ስብሰባው ስትሔድና ስት
መለስ የተጓዘችው የሩቅ መንገድ ጣመን ሳይሆን፤ በስብሰባው ላይ
ስትሰማ የዋለችው የካድሬዎች ዲስኩር ነው። ለጆሮዎቿ እንግዳ
የሆኑ አዳዲስ ሐሳቦች ከከተሜዎቹ የሴቶች ሹማምንት ሲንቆረቁሮ
ርላት ውሎ፤ መንፈሷ ተሸብሮ ሰውነቷን እጅግ አዝሎታል።
ይሆናል ብላ የማታስበው፤ ወርቃ ወርቅ ሐሳቦች፤ ሲምቦለቡላት
በመስማቷ፤ መንታ ስሜቶች ባንዴ መንፈሷን ወረዉት፤ አለቅጥ
ስለረበሻት፤ አለወትሮዋ በሐሳብ ሰጥማ ታሰላስል ነበር። " እነሱ
እንዳሉትማ ቢሆን ናሮ፤ ሕይወት ምንኛ በሠመረ! ግን በኑሮአችን
አካባቢ ውስጥ ገዝፈው በየዕለቱ የምናያቸውን ጉልህ ችግሮች፤
እንዴት ልንወጣቸው ችለን ነው፤ ለዚያ ከፍተኛ ተግባራዊ እኩል
ነት የምንበቃው? " እያለች፤ ኰርኩረዋት የማያውቁ አዳዲስ መሠ
ረታውያን ጥያቄዎች በልቧ ውስጥ እያነሣች ትጥላለች። አለወት
ሮዋም የነበራት ንቃት ሁሉ ከሁለንተናዋ ደብዝዞ መጥፋቱ፤ እንደ
ገበሬ ሚስትነቷ የነበሩባትን የምሽት ተግባሮቿን ዘንግታቸው፤ ብቻ
ለባሏ እግር ማጠቢያ የሚሆነውን ውሃ በማሠሮ አድርጋ ከምድ
ጃው ላይ መጣዷ ይታወሳታል።

ባሏ ጥማድ በሬዎቹን እየነዳ፤ " ካሁን አሁን ቤቱ ደርሼ፤
ጣመኔን ተወጥቼ፤ " በሚል ተምኔቱ ሲገሠግሥ ቆይቶ ደጃፍ ላይ
ይደርሳል። እንደደረሰም፤ ባለቤቱን ባካባቢው ለማግኘት በዐይኖቹ
ይመትራል። ለወትሮው፤ ሚስቱ ከደጅ ራቅ ብላ በመሔድ፤ የደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከመ ባሏን ትቀበለው ነበር። ብዙ ጊዜም ከንፈሮቹን ሳይሆን፤
አፈር ሲቅሙ የዋሉ ጉንጮቹን ሙጭጭ አርጋ በመሳም፤ " የደ
ኅና ገባህ " ምኞቷን ትገልጽለት ነበር። ወዲያውም፤ እሱ የተጠ
መዱትን በሬዎች እስኪፈታ ድረስ፤ ጅራፉንና ጠዋት ምሳ የወሰ
ደበትን አገልግልና ቅል ተቀብላ፤ ወደ ቤት ትመለስና፤ እቃዎቹን
በየቦታቸው ታስቀምጣለች። ያላት ለታም እንደገና ተመልሳ፤ ሞፈ
ሩንና ቀንበሩን ቅትርቱንና ወገቡን.. ከባሏ ተቀብላ ከቤት በመው
ሰድ በቤታቸው ውስጥ፤ በተለይ ለእቃዎች መስቀያ በተዘጋጀው፤
በቤቱ እንብርት ላይ በቆመው፤ ባለባላ ምሠሦ ላይ ታስቀምጣ
ቸዋለች። በዚያን ዕለት ግን፤ ሌላው ትርፍ ተግባራዊ ርዳ
ታዋ ቀርቶ፤በተለምዶ ምድብ ሥራዋ የነበረውን፤ ሲያርሱ ለዋሉት
በሬዎች መቀቢያ የሚሆን የድርቆሽ ሣር እንኳ በግርግማቸው
ውስጥ አላስቀመጠችም ነበር።

ባሏ ከቤቱ ደጃፍ ደርሶ፤ መላ ገረገንቡን በዐይኖቹ ሩቢያን
ቢያፈላልግ ሊያገኛት አልቻለም። " ምናልባት ከስብሰባው አልተ
መለሰች ይሆናል " እያለ ጥቂት እንዳመነታ፤ የተጫነው የድካም
ጣመን አላስችል ብሎት፤ ከደጃቸው ላይ ለጥጃዎች ማሰርያ ተብሎ
ከተጋደመው ግንድ ላይ፤ አረፍ ለማለት ቀጭ ይላል። ምንም
ያህል አልቆየ፤ የምሽቱ አጋጣሚ አበሳጭቶት፤ ሚስቱም እንደእሱ
ስብስባውና መንገዱ አድክሟት፤ ቤት ውስጥ ተኝታ ይሆናል
በሚል ጥርጣሬ፤ ድምጹን ከፍ አርጎ፤

" ሩብያ! ሩብያ!..... " ብሎ ይጣራል።

" አቤት! " ከእንቅልፏ የቀሰቀሳትን ያህል ቀኑን ስትሰማው
የዋለችውን ሐሳብ ስታሰላስል ከነበረችበት ምድጃ አጠገብ አፈፍ
ብላ ትነሣለች።

" ሩብያ! ሩብያ! " ደግሞ ይጠራታል፣ በጨረፍታ የሰማው ድምፂ እውን ይሁን አይሁን እየተጠራጠረ።

" መጣሁ! አቤት፣ ጌትዬ! " የላላ መቀነቷን እያጠበቀች፣ ከቤት ባሏ ወዳለበት ቦታ እየሮጠች ትመጣለች።

" ጉባኤው አደከመሽ እንዴ? ደጁም ሆነ ቤቱ በጣም ጭር አለብኝ " እንደለመመን፣ ከቤታቸው ክፍክፉት ላይ ብን ብን የምትለዋን አነስተኛ የምትገለገለግ ጭስ፣ በሩቅ ጣራጣራውን እያየ።

ሩብያ ወዲያው ተፍ ተፍ ብላ፣ ጅራፉንም፣ ጠዋት ይዞት የሔደውን የስንቅ መያዣ አገልግልና ቅል ትቀበለዋለች። ባልየዋ ግን አሁንም ተደናግሮታል። ለወትሮው፣ እርሻ ውሎ ሲመጣ፣ ከቤቱ ደጃፍ ላይ ይጠብቀው የነበረው መቀበያ ሁሉ አልነበረም። ሲኖር ጠላ፣ ሲኖር ትኩስ ወተት፣ አለያም እርጐ፣ እነዚህ ሲጠፉ ደግሞ ቅራሬ ወይም አሬራ ማግኘት ነበረበት። በዚያን ቀን ምሽት ግን፣ ሌላው ሁሉ ቀርቶ፣ ለመኖሩና ለሀላፂው ተስፋና አለኝታ የነበረው የሩብያን ከንፈር ስሚያ አላገኘም። ይህንንም በማጣቱ፣ ሁኔታው ይበልጥ ተጣብሶበት፣ ከመደናገር አልፎ መርበትበት ጀመረ። ሩብያ የስንቅ መያዣዎቹን ከቤት አስቀምጣ ስትመለስ፣ ባሏ ሮጥ ብሎ ጣመን ባብረከረካቸው እጆቹ፣ ሁለት የሩብያ ትክሻ ዎቿን ያዘና፣

"እመቤቴ! ዛሬ ምን ነካብኝ ይሆን! መሳሙንም ረሳሽው!" አለና አፈር ሲቅሙ በዋሉት ከንፈሮቹ፣ የቀኝ ጉንጭዋን እንደቆላ ሎሚ ምጥጥጥጥጥ ሲያደርግ፣ ሰዓት ያዥ ተቆጣጣሪ ባጠገባቸው አልነበረም እንጅ፣ መምጠጡን ሲያቆም አሥር ደቂቃዎች ብሎ በመዘገበ ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

" ጌትዬ!" አለች ሩብያ የተመጠጠው ጉንጭዋ ከፈጠረው ስሜት ጋር፣ መላ ፊቷን ፍም አስመስሎት " ጌትዬ! ዛሬ እንደማ ትቀየመኝ እምናለሁ! " አለች በባሏ ከንፈሮች እንደዋግምት ተሰቦ የወጣው ውስጣዊ ስሜቷ፣ ቁና ቁና ያህል እያስተነፈሳት።

" ታውቂያለሽ ሩብያ፣ እኔ ላንቺ ብቻ ብዬ፣ በዚህ ዐይነቱ ኑሮአችን በሥቃይ እንደምኖር! ታውቂያለሽ! ያላንቺ ጠቅላላው ዐለምና ተፈጥሮ ከንዝግንትሉ፣ ምናምንቴ ዐይነት ነገር መስሎ እንደሚታየኝ! ታውቂያለሽ! እኔ የምመሰከትሽ፣ በተራ መውደድ ሳይሆን፣ በተለየ ፍቅር እንደሆነ! በርግጥም ታውቂያለሽ፣ ብርሃንና ዐየር፣ እፀዋትና አዝርእት ሌሎችም የተፈጥሮ በረከቶች ሁሉ፣ አንቺ በሌለሽበት ወቅት ሁሉ ለኔ ምንም ዐይነት ትርጉም እንደማይሰጡኝ ታድያንን ዛሬ ምን ነካብኝ ይሆን፣ እንዲህ ጣምኜ ስመጣ፣ ነፍስ ትዘራብኛለሽ ብዬ ሳስብ፣ ከደጅ የጠፋሽብኝ! " አለ፣ ፍቅር ባጥላላው አንደበቱ በመንተባተብና በደረቷ ላይ እንደበሰለ ብርቱካን ትምቡክ ትምቡክ የሚሉ መንታ ያጐበሩ ጡቶቿን እየዳሰሰ።

" አንተዬ እንዳትቀየመኝ ብዬሃለሁኮ! ጌታዬ፣ ሁለታችንም ብንሆን፣ ፍቅር አገብሮን እንጅ፣ በእንደዚህ ዐይነቱ ኑሮ መኖር እንደማንችል ብዙ ጊዜ ተነጋግረንበታል። የኔ ፍቅር ምንጊዜም ቢሆን ተከብሮልህ እንደሚኖር መሐላ አያሻውም። በሁለታችን መካከል ያለውን የፍቅር መተማመን፣ ከሁለታችን ሌላ፣ ማንም ሰው እንደማያውቀው ታምናለህ። ሌላው ቀሮቶ፣ ወላጆቻችን እንኳ፣ ውጫዊውን ፍቅራችንን እንጅ ውስጣዊውን የነደደ ስሜታችንን አያውቁትም። እንዲውም... " ብላ ልትቀጥል ስትል፣ አንድ ነገር ትዝ አላትና " በሞትኩት! ጌትዬ አፈር በበላኝ! " ብላ

ይተሻሻት ከነበረው ሰውነቱ ላይ ተመንጥቃ፣ ወደ ቤት እየሮጠች ገባች። አልቆየችም፣ ትልቅ ቅል በሁለት እጆቿ ይዛ ወደ ደጅ እየመጣች " ሞት ይርሳኝና ጌትዬ ረሳሁህ! ለዛሬ የሚደርስ ጉሽ ጠላ ነበረኝኮ! ዛሬ ምን እንደነካኝ አላውቅም፣ ደክመህ ስትመጣ፣ ምንም ሳልልህ ቀረሁ!" ትሰጠዋለች።

ከመቀመጫ የሚያስነሳ ጠላ ኖሯል። ገፈት ገፈቱን አጥልላ፣ ሁለቱም ደጃቸው ላይ በተጋደመው ግንድ ላይ ቁጭ ብለው፣ ተራ በተራ እየተፈራረቁ፣ ያን የቅል ጠላ አሱት። ሁለቱም ጠላይቱን ከቀማመሱ በኋላ፣ በለመዱት ዐይነት መሳሳም፣ እርስ በርስ ተጨረ ማምተው ሲግጠጡ፣ ስልምልም ብለው ቀሩ። ቆይተው ቆይ ተው፣ ፍቅር የደበተው መንፈሳቸው እንደገና ሲመለስ፣

" አንቺዬ! ምንም ነገር ደብቀሽኝ እንደማታውቂ አውቃ ለሁ። ወደፊትም ቢሆን በዚሁ ባሕርይሽ እንደምትቀጥዪ አምና ለሁ። ዛሬ፣ በተለይ ዛሬ፣ የሆንሽው ነገር አለና፣ ሳትደብቂኝ ንገ ሪኝ! " ሲል ተማጠናት።

" አንተዬ! በኔና ባንተ የፍቅር መዝገበ-ቃል ውስጥ፣ ለም ሥጢር ቦታ የለውም። ግን ጌትዬ ቡዳ ነህ! አውቀህብኛል። ስብ ሰባቸው ነገሮኝ ነው የመጣሁት። እኔን ሳይሆን አንዳንድ ሐሳቦቼን ጐሻሽመውብኛል። መለስተኛ ሽብርም ሞክሮኝ ነበር " አለች። የሆነችውን አፍረጥርጣ ልትነግረው እየተዘጋጀች።

" አንቺዬ፣ ለመሆኑ ብዙ ሴቶች ተሰበሰቡላቸው? ለመሆኑ እነዚህ ስብሰባውን የመሩት የሴቶች ካድሬዎች የት የሚኖሩ ናቸው? የትስ የተማሩ ናቸው? " ሲል ጠየቃት፣ ማምሻውን ሻጉራ አድርጓት የቆየውን ምክንያት፣ በስተዙርያ ለማውጣጣትና ለማወቅ ጓጉቶ። እሷም፣ ሲተሻሹ ላልቶ የወደቀውን መቀነት ከመሬት አንስታ እንደገና ወገቧን እያሸመች፣

t.me/OLDBOOKSPDF

" ጌትዬ ዘርዝሬ አጫውትሐለሁ! ቆይ መጀመሪያ ከጠላው ልድገምህ!" አለች። ባዶውን ቅል አንጠልጥላ ወደ ቤት ገባችና፣ ወዲያው ይዛ ከተፍ አለች። ቅሉን ለባሏ እንደሰጠች፣ ካጠገቡ ጠጋ ብላ ቁጭ አለችና የስብሰባውን ዝርዝር ሐተታ ትዘክዝከው ጀመር።

" ያልተሰበሰበ ያካባቢያችን ሴት የለም። ብቻ ሁለት ሴቶች 'ስብሰባው ላይ መገኘት የለብሽም ' በሚል የባሎች ተቃውሞ በተነ ሳው ጠብ ባባወራምቻቸው ተፈንክተው እዚያ ማዶ ካለው የጤና ጣቢያ ተወስደዋል አሉ! " አለች ስትጀምር።

" አንቺየ! ደግ አላረጉም! ምናለ ቢፈቅዱላቸውና ቢሔዱ ኖሮ " አለ ባል።

" አንተም ሳታውቃቸው አትቀር፣ እነግራዝማች ውቤና እነአለቃ ፍስሐ ናቸው አሉ፣ ሚስቶቻቸውን የፈነከቱት " አለች መሣቅ እየሞካከራት።

" ኧሃሃሃ ያደርጋሉ! እነሱስ እንዲህ እንዲህ ያለው፣ የሴቶች ቅሥር ቅሥር ማለት አይዋጥላቸውም " አለ ከት ብሎ እየ ሣቀ። ወዲያው " ዛሬስ አንቺም ጠምቶሻልኮ፣ የስንቶቹን ዲስ ኩር ያለወትሮሽ ስትሰሚ ውለሽ " አለና ከቅሉ ሦስት አራት ጊዜ፣ በጹ እንደያዘ ጠላውን አስጐነጫት። እንደመብቃት ሲቃጣትም ለገታት።

" ለስድስት ወራት ለከፍተኛ ትምህርት መስኩብ ደርሰው የተመለሱ ናቸው አሉ፣ ስብሰባውን የመሩት የሴቶች ሹማምንት " አለች ሩቢያ።

" ስንት ነበሩ? " የሹማምንቱን ብዛት ለማወቅ? ባል ያቀረ በው ጥያቄ ነው።

" አምስት ነበሩ። ግን የሚገርምህ አምስቱም ስለ ባላገሩ

ኑሮ የማያውቁ፣ ከተማ ውስጥ ተወልደው ያደጉ ናቸው አሉ ” አለች።

“ ታዲያ ስለባላገሩ ሴቶች ሁኔታ ምን አውቀው ነው፣ የገጠሩን ሴት ሰብስበው ሊያስተምሩ የመጡት? ” አለ ባል በቁምነገር።

“ አይ እሱስ እንኳ ሹማምንቶቹን ያስተዋወቁን ሴትዮ፣ መጀመሪያ ሲናገሩ፣ አምስቱም ሹማምንቶች በሞስኮብ ያጠኑት ትምህርት የገጠሩን ሴቶች የሚመለከት እንደነበርና፣ በሩሲያ በሚ ፕኑ የገጠር መንደሮችም በመዘዋወር ሁሉን የገጠር ሴት ችግር ያጠኑ መሆናቸውን ገልጸውልናል ” አለች ሩብያ፣ እንደ መቅረፀ-ድምፅ ስትቀዳና ስትጠመጥም የዋለችውን ሁሉ መልሳ እየተረተረችለት።

“ አንቼዬ ታድያማ እንቅብና ሠፌድን ሲያመሳስሉ ውለ ዋል አትይኝም እንዴ!” አለ በስላቅ ውስጥ ውስጡን እየነካካ።

“ ጌትዬ፣ እንቅብና ሠፌድን ደግሞ ምን አገናኝቷቸው ነው፣ የምትጠቅስልኝ ” አለች፣ ሐሳቡ ይበልጥ እንዲብራራላት እየጐመዠች።

“ አም! እንቅብና ሠፌድ፣ እንዳልሽው በጭራሽ አይገ ናኙም። ቅርፃቸውም ሆነ አገልግሎታቸው ለየቅል ነው። ታዲያ የመስኰብ አካባቢ ገጠሮችና የኛዎቹ ገጠሮች ሁኔታ፣ በየመልኩ የሚለያይ ባሕርያት አሏቸው። በዚያ ስለሚኖሩት የገጠር ሴቶችን ሁናቴ አጥንቶ፣ ለዚህኛው ለኛው የገጠር ሴቶች መጠቅጠቅ፣ እንደሠፈዱና እንደ እንቅቡ ሆኔታ አይመሰል ብለሽ? የቆላና የደጋ ወፍ አይመሳሰል፣ ዘፈኑ እንኳ ለየቅሉ ነው! ደግሞምኮ..... ” ብሎ ሊቀጥል ሲል፣ አፉን በጇ እያመቀች

t.me/OLDBOOKSPDF

“ ቆይ ስማኝ እንጅ ጌትዬ! ገና አልጀመርኩምኮ፣ የሰብ ሰባው ዋና እንብርት፣ የሴቶች ግላዊ መብት ጉዳይ ነው ብለው፣ ከሚስቶች የባል እግር ማጠብ አንስተው፣ እስከ ሴት ልጇ በሷ ስም መጠራት አለበት እሚለው ድረስ፣ አምስቱም ተራ በተራ እየ ተነሱ ሲሰብኩን ዋሉ ” አለችው።

“ ሩብያ፣ ይህ ዐይነቱ ጉዳይ ለኔና ላንቺ እንግዳ ነገር አይደለም። ሴቶች እኩልነታዊ ክብራቸው መጠበቅ እንዳለበት በያ ጋጣሚው ሁሉ ስንነጋገርበት ቆይተናል። እነ ግራዝማችንና እነ አለቃን፣ የጉዳዩ አስፈላጊነት ባይገባቸው ሌላ ጉዳይ ነው። እኔ ሓሳቡን ሙሉ በሙሉ እንደምደግፍ ደጋግሜ ነግሬሻለሁ። ታውቂ ዋለሽ። እንኳን በግል ትዳራችን ውስጥ የምናከናውነው ተግባር ሁሉ፣ በሁለታችን የመፈቃቀድና የመከባበር መንፈስ ላይ የተመ ሠረተ እንጅ፣ ባሕላችን የፈጠረው የታላቅነትና የታናሽነት ስሜት ተፅዕኖ እንዳይደለ አምነንበታል። ግን፣ መሠረታዊውን የባለት ዳሮች እኩልነት ለማግዘፍ፣ አስቀድመው መዘጋጀት ያለባቸው የኑሮ ተግባራዊ ድርጅቶች አሉ። እነዚህ ተግባራዊ ድርጅቶች እስካል ተሟሉ ድረስ፣ በዚህ ጉዳይ የሚነሣው ሙከራ ሁሉ፣ ባልና ሚስ ትን ይበልጥ ያሻክራሉ እንጅ፣ መድኀንነት አይኖራቸውም ” አለ።

“ ጌትዬ ልክ ነህ! አንዳንድ ተርብ የሆኑ ሴቶች፣ አሁን አንተ የጠቀስከውን ነጥብ አንስተው፣ በያካባቢው ወፍጮ ቤት ቢቋቋም፣ የውሀ አሸንዳዎች ቢተከሉ፣ የሕፃናት ማሳደጊያ ጣቢያ ዎች፣ ቢቋቋሙ፣ የመሰሰሉትም የኑሮ አስፈላጊ ድርጅቶች ቢዘ ጋጁ፣ እነሱ አበክረው የተናገሩለትን የሴቶች እኩልነት መብት ከሞላ ጐደል በሥራ ላይ ለማዋል በተሞከረ ነበር። ይህም ሁኔታ የተግባራት መፈራረቀን በባልና በሚስት መካከል መፍጠር አስ ችሎ፣ አንድን ተግባር ሴትም ሆነ ወንድ ሊሠራው እንደሚችል

በማረጋገጥ፤ ባሕሉ በዚህ ሳቢያ ያሣደረውን የበታችነትና የበላ ይነት ስሜታዊ ተፅዕኖ በጥቂት ቀኖች ውስጥ፤ ጨርሶ ማጥፋት እንኳ ባይሆን፤ ማሻሻል ይቻላል፤ ብለው ሐሳባቸውን ያቀረቡ ሴቶች ብዙ ነበሩ " አለች ሳታመነታ።

" ልክ ናቸው! በበሬዎቻችን ምትክ ትራክተር፤ በድንጋይ ወፍጮቻችን ምትክ የሞተር ወፍጮ.... በየመስኩም የተሻለ ተግባራዊ የመሣሪያዎች ለውጥ ቢኖር፤ የሚሉት ሁሉ ተግባራዊ ሊሆን በቻለ ነበር። በተረፈ ግን ባል፤ እንጀራ ቢጋግር፤ ወጥ ቢሠራ፤ ጠላ ቢጠምቅ፤ ወፍጮ ቢፈጭ..... እኔ ኣልቃወምም። ችግሩ ባሕላችን የለመደው፤ የቤትና የውጭ ሥራ አከፋፈል ሁኔታ፤ በሥራ ማከናውኛ መሣሪያዎች ሁኔታ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፤ የመሣሪያዎቹ አለመለወጥ ባሕሉን ሊሽረው አለመቻሉ ነው የሚያሳዝነኝ! " አለ ሚስቱን በተቻለ መጠን እኩያው እንደሆነች፤ መን ገድ መንገዱን እያሳያት። " እኛ እንኳ የቤቱ እኩል ኣዛኖች ነን! " ኣለ።

" አንተዬ! እኛ ጠላችንን እየተጐነጨን የቀኑን ወሬ ስን ደልቅ፤ በሬዎቹን ረስተናቸዋል " አለች፤ ልቧ ከበፊቱ ይልቅ ረገብ እያለ።

" አይ ሩብያ! የኛ ነገር ያሳዝናል! በሬዎቹ ኣይናገሩ፤ እን ዲያ ሲደክሙ ውለው በማረፊያቸው ሰዓት፤ ከነቀንበራቸው ኣቁ መን አሠቃይተናቸው ኖሯል " አለና ወዲያው ብድግ ብሎ ይፈ ታታ ገባ። ወዲያውም፤ ሩቢያ እቃዎቹን ኣግብታ ቤት እንዳስ ቀመጠች፤ ከግርግም ውስጥ የሳር ድርቆሽ ለበሬዎቹ እንዳላዘጋጀች ትዝ ኣላትና፤ ስትበር ወደ ሜሩ ክምሮች ሮጠች። ሜሩን በወቅቱ በግርግሙ ውስጥ አለማዘጋጀቷን ባሏ በመመልከቱ፤ ተጨማሪ ቀኑ የፈጠረው ኣዲስ ሁኔታ መሆኑ ተሰማው። " ዕለታዊ ምድብ ተግ

t.me/OLDBOOKSPDF

ባሯን እንዳትሠራ ፤ ስብሰባው ላይ ምን መክረዋት ይሆን? " እያለ እንደገና ያሰላሰል ጀመር። በዚሁ ሐሳብ ላይ ተመሥጠ፤ የዕለቱን ስብሰባ በማስመልከት፤ ሚስቱ ያሳየችውን ጥቂት የተግባር ግድየለሽነት ሁኔታዎች ያወጣ ያወርድ ጀመር። በልቡም እንደ መተከዝ ብሎ " ለወትሮዋ ከርሻ ስመለስ ከደጅ ተገኝታ ትቀበለኝ ነበር፤ ለወትሮዋ የመቀበያ መጠጥ አዘጋጅታ ትጠብቀኝ ነበር፤ ለወትሮዋ ሲያርሱ ለዋሉ በሬዎቻችን፤ ድርቆሽ ሣር በግርግሙ ወስጥ ታዘጋጅ ነበር። ዛሬ ምን ነክቷት ይሆን እነዚህን ተግባሮች ችላ ያለቻቸው? ነገር አለ! እነዚያ ከመስኩብ ተምረው የመጡ የስብሰባው መሪዎች፤ የመስኩብ አከባቢ የገጠር ገበሬዎች ሚስቶች፤ ለባሎቻቸው እንደዚህ ያለውን ተግባር ኣያደርጉምና፤ እናንተም ለባሎቻችሁ ኣታደርጉ፤ ይሆን መሳይ ተግባር ብታከና ውኑ፤ የሴትነት መብታችሁንና፤ ከወንድም ጋር እኩል መሆናችሁን ይፃረርባችኋል ብለው ነግረዋት ይሆን? " እያለ የምሽቱን ሁኔታ እያብላላ ይጨነቃል። ሩብያ ቋጥኛ የሚያህል የሣር ድርቆሽ በኪሻ ጠቅልላ፤ በመጫኛ የጠፈረችውን ኣዝላ ወደ ቤት ለመምጣት ስትዘጋጅ፤ከድርቆሹ ክምር ሳር ላይ ቁጭ ብላ፤ እንደባሏ ውስጥ ውስጧን ጭንቀት ያኝካት ነበር።

" ዛሬ ባሳየሁት የተግባር ቸልተኛነት ታዝቦኝ ይሆናል። ምን ላድርግ! እኔ ራሴ ኣውቄ የፈጠርኩት ኣይደለም። በጆሮየ ሲጠቀጠቅ የዋለው የሴት ሹማምንት ምክር ጤና ነስቶኝ ነው ያመሸሁት። ይቅርታ እንዲያደርግልኝ እጠይቀዋለሁ። እሱ ለኔ ሲል፤ ፍቅር ኣስገድዶት ከሞቀ የከተማ እናት ኣባቱ ቤት ተሰዶ፤ የመምህርነት ሥራውን ትቶ በተራ ገበሬነት ሲቆራመድና ሲማቅቅ ኖሯል። እኔ መሠረተ ምክንያቶቹ በሥርዓት ባልተጠኑ፤ በመስ ኩብ መንፈቅ በተማሩ የሴቶች ሹማምንት የስብሰባ ምክሮች፤ መሸ

በርም ሆነ መነዳት የለብኝም። እሱን የማከብረው ስሰጠኝ ሙሉ ፍቅሩ ስል እንጅ፣ በወንድነቱ ባሕላችን ባስፕኘለት የበላይነቱ ላይደለም። እኔን ብሎ ከኔ ተቈራኝቶ በገጠር ሲማቅቅ የኖረው፣ ፍቅር ባስፕኘልን መተሣሠር እንጅ ከተማ ገብቶ ከዚህ የተሻለ ኑሮ መኖር ኣቅቶት ኣይደለም። እኔን የገጠሪቱን ልጅ ከነሳዱላዩ በማፍቀሩና ሚስቱም እንድሆነው በመወሰኑ፣ ወላጆቹ " ዐይንህ ላፈር " ብለው ረግመው ዳግመኛ ላይገናኙት ከወሰኑ ዐመታት ኣልፈዋል። በፊት ኣስተማሪ ሆኖ ገጠር ሳለ ኣውቆኝ፣ ኋላም ለዘመቻ ሲል መጥቶ ኣግብቶኝ እንኖራለን። እሱም እኔን ሲል፣ የተወለደበትና ያደገበትን ከተማ እርም ብሎ ትቶ፣ ይኸው በገጠር ገበሬነት ሲን ገላታ ዘመናት ኣልፈዋል። ዘመዶቹም በሙሉ፣ " መድኃኒት ኣድር ጋበት ነው፣ ኣስደግማበታለች " እያሉ የማይደረድሩብኝ ሓሜት የለም። እኛ ግን ሁኔታውያን ኣገናኝተውን በእውነተኛ ፍቅር ተሳስበን የምንኖር ነን። ለፍቅረኛ ከእኩልነት ላይ የመነጨ ፍቅርን ከመስጠት የበለጠ ሌላ ስጦታ የለም። በዕለት ተግባርም ሆነ በሌላ ሁኔታ፣ በፍፁም ቅንነት የምንረዳዳው፣ ከዚሁ ከፍቅራችን ላይ በመነጨ መንፈስ ለማካይነትና ለስገዳጅነት ነው። እኔን ከተራ መሐይምነት ሞርዶ ሞርዶ፣ ከኣከባቢዬ ባለው ኣስተሳሰብ ኣንፃር ኣዋቂ ኣድርጎኛል። ፊደል የማላውቀውን ሰው፣ ዛሬ መጻፍና ማንበብ ኣስችሎኛል። ከዚህ ሁሉ ይልቅ፣ ስግብግቦችን ብቻ ኣቅፎና እንደ ላቆ በሚኖር ዐለም ውስጥ፣ ለንዋይ መንሠፍሠፍ ሐሳብና ጭን ቀት በሌለበት ነፃ ሕይወት ውስጥ በገጠር ጐጆኣችን የተደበቀች ኑራኣችንን በሰላም እንኖራለን። ያው ያካባቢን ጭቁን ሕዝብ ያስ መረረውና ጭንቁም ያሠቃየው የኢኮኖሚና የእድገት ኋላ ቀርነት በኛም ላይ ይጫወትብናል እንጅ፣ በሁለታችን መካከል ያለው የባልና ሚስት ሰላም ምን ጊዜም መናጋት የሚችል ኣይደለም። ካቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማችን በላይ በሆነው ባከባቢው የኑሮ ችግር ግን ሕዝቡ እንደ ሆነው እንሆናለን። እኩልነት በሥራ መከፋፈል ላይ የሚመሠረት ከሆነም፣ ሰባኪዎቹ እንዳሉት እኔን ላይመለከት ነው። ጌትዬ፣ ከእንቅልፉ ሌሊት ተነስቶ፣ ወፍጮውን ሳይቀር የሚረዳበት ጊዜ ጥቂት ኣይደለም። ጊዜ ካለው፣ እኔ ጥጥ ስፈትል ሲያይ፣ እሱ ያዳውራል። እኔ ሊጥ ሳቦካ፣ እሱ ውሃ ይጨምራል። እንጀራም ሳስስ፣ ኣክምባሎ ይደፋል። ድስት ጥጄ እንደሆነ እንጨት ይቆሰ ቍሳል። ለሙቀጫውም ከሆነ፣ የምንጠቀመው በሁለት ዘንዘናዎች ነው። ልብስ ኣጠባ ዥረት የወረድን እንደሆነ፣ እኔ ሳሽ፣ እሱ ይረግጣል። እኔ ሳሰጣ እሱ እንዶድ ቆርጦ ይቀጠቅጣል። የምንጠ መዝዘውም፣ የልብሱን ጫፍና ጫፍ ይዘን ነው። የቤታችንን ወለል ኣዛባ ስለቀልቅ፣ እሱ መደብ መደቡን ይዞ እንደሆን፣ እኔ ወለል ወለሉ ይደርሰኛል። እሪ ምን የሚቀረው የቤት ሥራ ኣለ? ..... " በሐሳብ ሰምጣ ድርቆሹን ለበሬዎቹ ማምጣት ዘንግታ ቁጭ ብላለች። ባሏ ሣር ለማምጣት እንደሔደች ጠርጥሮ፣ ወደ ከምሮቹ ሲሮጥ ቢሄድ ድርቆሹን በሚገባ በኬሻ ጠቅልላ ኣዘጋጅታ፣ ካጠገቡ ቁጭ እንዳለች ያገኛታል።

" ምን ሆንሽ ዘገየሽ? " ኣሁንም የዕለቱን ጥርጣሬ ለማውጣጣት ነው።

" እሪ ተወኝ፣ ዛሬ በሐሳቤ የማይወጣ የማይወርድ ነገር የለም! " ኣለች።

" ኣም እኔም ተሰምቶኛል! ነገ ደግመሽ ከስብሰባው ኣት ሔጅም "

"ደግሞ ምን ላደርግ! ዛሬ የረበሸኝ ኣነሰኝ እንዴ! " ደረቱ ላይ ጠጋ ብላ በመለጠፍ " ጌትዬ፣ ዛሬ ይቅርታ እንደም ታደርግልኝ ኣምናለሁ። ለወደፊቱ ግን ኣይለምደኝም! " ትለዋለች

ጉንጮቹን እንደተለመደው እየዳሰሰች።

" ለመሆኑ ምን ዐይነት ስሜት ላሳደሩብሽ ይሆን? " አለ፤ የሆነችውን ለማወቅ።

" ኧረ ድራሽባቸው በጠፋ- ደርሰው የሴት መብት እኩልነት፣ ፍትሕ..... እያሉ ያልተጨማለቁት የለም። በርግጥ ላዲስ ለውጥ መጥቷል የሚሉን ከሆነ፣ ከነዚህ ሁለተኛ ደረጃ ችግሮቻችን ይልቅ፣ በተቀዳሚ ሊደረጉ የሚገቡትን ነገሮች ባዘጋጁልን ነበር! የኩልነቴን ጉዳይ እኛው በየቤታችንና በየላደባባዩ ራሳችን በራሳችን እናስተካክለው ነበር። እሱን ትተው፣ ሲመጠምጡን የሚያድሩትን ቅማሎች፣ ቁንጫዎች፣ ቱሐኖች የምናጠፋበትን መድኃኒት በሰጡን! የተዘራውን እህል ሳይቀር የሚያወድሙብንን አይጦች፣ አይጠ-ሞገጦች፣ ጃርቶች፣ ቁራዎች፣ የምናጠፋበትን ዘዴ ባዘጋጁልን! እንደልብ የምናነደውን ማገዶአችንን ባልከለከሉን! ለራስ ምታት፣ ለጉንፋን በሽታችን መከላከያ ኪኒና በሰጡን! ለገበሬዎች ኑሮ እንደዋልታና ምሠሶ የሆኑትን ሚስቶቻቸውን ከማንሳሳት ይልቅ፣ በግርድና፣ በሴተኛ ኣዳሪነት፣ በዕቁባት ቅምጥነትና በመሳሰሉትም ችግሮች የሚሰቃዩትን እህቶች ነፃ ለማውጣት ተቀዳሚ ርዳታ ባደረጉላቸው ነበር። እነሱ ባቀረቡት ሐሳብ እንኳ ቢሆን፣ በአስፈፃሚነትም ሆነ በመካሪነት፣ ከነሱ ይልቅ የተሻሉና ችግሩንም በቅርብ የሚያውቁ፣ ከዚሁ ከገጠሩ የተመረጡ ሴቶች ይበልጥ፣ ችግሩን ለመፍታት በቻሉ ነበር! .....

" እምቢ! እምቢ! እምቢ! ... " የተራቡ በሬዎች በግርግም ውስጥ ሣር ባለማግኘታቸው አቤቱታ ማቅረባቸው ኖሯል። ባልና ሚስት ተቃቅፈው ከነበሩበት ከድርቆሹ ክምር አጠገብ፣ የበሬ ዎቹን ጩኸት በጨረፍታ ይሰማሉ።

t.me/OLDBOOKSPDF

" ዛሬ በይበልጥ የተበደሉት በሬዎቻችን ናቸው! " አለ ባል፣ ቶሎ እንዲሔዱ ሚስቱን እያጣደፈና በኬሻ የተጠቀለለውንም ሣር በትከሻው እየተሸከመ።

" ምን ዐይነት፣ ሐሳብ የሚሰርቅ ጣጣ ፈጠሩብን? " አለች ሩብያ ሣር ለበሬዎች ልታመጣ ሔዳ፣ አንድ ሰዓት ያህል ከምሩ አጠገብ በሐሳብ ሰጥማ ቁጭ ብላ መዘግየቷን እያስታወሰች። ከቤት እንደደረሱም፣ ምሽቱ ደንገዝገዝ ብሎ ኖሮ፣ ሩብያ ኩራዝ ለመለኮስ ስትጣደፍ፣ ባሏ ለተራቡ በሬዎቹ ያመጣውን ድርቆሽ፣ ከግርግማቸው ውስጥ ያስቀምጥላቸዋል። ሩብያም ኩራዙን ለኩሳ ከመስቀያው ላይ ካስቀመጠች በኋላ፣

" ጌትዬ፣ ዛሬ መቼም ሳትታዘበኝ አልቀረህም!" ትለዋለች።

" አዎ ነካክቶኛል! " ይላታል ሣቅ እያለ።

" ቆይ ዝምበል! የምን ስብሰባ! ሁለተኛ ንክች አላረጋትም! " ትላለችከልቧ መሆኑን፣ በከንፈሮቿ ሳሚያ እያረጋገጠችለት።

" ደግሞ፣ አልተፐኛችም ብለው ችግር እንዳይፈጥሩብን! " ይላል ባሏ እንደማቅማማት እየሞከረው።

" የሚያደርጉትን ያድርጉ! እኔና አንተ እኩል እንደሆንን፣ ከኔና ካንተ ይበልጥ እነሱ አያውቁም!" አለች፣ ከምድጃው አጠገብ ካለው መደብ ላይ፣ ከድርቆሹ ጐዝጉዝ አድርጋ ደላጐ እያነጠፈች። " እነግራዝማችን እነፊታውራሪን እነካብትሺን እነአመቴን " ይምከሩ።

" መጠንቀቅ አለብን እንደሕዝቡ ካልሔድን ሌላ ችግር ሊመጣብን ይችላል " አለ ባል፣በያጋጣሚው የሆነውን እየተረከላት።

" ጌትዬ! ውሃው እንደወትሮው ባይሞቅም፣ እግሮችህን

ላጥብ ነውና ተዘጋጅ!" አለች፣ በጇ የማሰሮውን ውሃ እየፈተሸች።

" ሩቢያ፣ ውነቴን ንገሪኝ! የባሎቻችሁን እግሮች እንዳ ታጥቡ ብለዋችሁ የሰም እንዴ ዛሬ! " እያሾፈ የልቡን መጠየቁ ነበር።

" አንተ ምስጥኮ ነህ! ጌትዬ በምን አወቅኸው! እንዲውም የኩልነታችሁ መፈተኛ ማረጋገጫ ነውና፣ ዛሬ ማታ እንደተመለ ሳችሁ፣ የባሎቻችሁን እግር እንዳታጥቡ ብለው አስጠንቅቀውናል" አለችው በሣቂ እያስካካች።

" አም ጠርጥሬለሁ! ውሃው ዛሬ አለወትሮው በደንብ አልሞቀም አልሽ፣ ምን ውሃው ብቻ፣ ዛሬ አለወትሮው በደንብ ያልሆነው ውሃው ብቻ አይደለም... " ይላታል፣ በነገር እየነካካት።

" በል እግርህን አምጣ " ትለዋለች? ከማሠሮው ውሃ በብረት ድስት ላይ ቀንሳ እያዘጋጀች!

" ሩብያ! ቆይ የመስኰብ መምህሮችሽን ቃል ለማክበር፣ እኔ መጀመርያ አጥብሽና ኋላ ደግሞ አንቺ በተራሽ ታጥቢኛ ለሽ። ተስተካክልን ማለት አይደል? " ይላታል ከነበረችበት ቦታ ታቅፎ አንስቶ ለሱ በተዘጋጀ የመደብ መቀመጫ ላይ እያስቀመ ጠና፣ እግሮቿን ወደ ተዘጋጀው የግር ማጠቢያ ገበቴ እየኰተተ።

" ለኛ ይኸ አዲስ ነገር አይደለም! ሁልጊዜ የምናደርገው ነው!" አለች ሩቢያ መደቧ ላይ እንደተቀመጠች ባሏ ዝቅ ብሎ እግሯን ሲያጥብ።

" ሩብያ! ሩብያ! " ከውጭ የሴት ድምፅ ጥሪ ይሰማል።

" ማነሽ!" ትላለች እንደተቀመጠች ባሏ እግሯን ሲያጥብ።

" ሩብያ! በሩን ክፈችልኝ!እኔ ነኝ! " ይላል የውጭ የሴት ድምፅ።

" አትናገሪም እንዴ! ማነሽ! " ትላለች አንደኛው እግሯ

t.me/OLDBOOKSPDF

መታጠቡ አብቅቶ፣ ሁለተኛው ሊጀምር ሲል፣ ከመቀመጫዋ ላይ እንዳለች ባሏ በሩን ሊከፍት ይሔዳል። ሲከፈት ቢያዩ፣ ከአሱ ማዶ መንደር የምትኖር የሩቢያ ወዳጅ ሆና ያገኟታል። እንግዳዪቱም ገብታ ከሩብያ አጠገብ እንደተቀመጠች፣

" ደኅና አይደለሽም እንዴ፣ በምሽት የመጣሽው? " ሩብያ ትጠይቃለች።

" አንቺ የታደልሽ አለመኛ ነሽ! እንዲውም ይኸው ባልሽ እግርሽን ያጥባል፣ እኔ ዛሬ ለምን ስብሰባ ሔድሽ ብሎ፣ ሊገድለኝ ሲሞክር፣ በታዛ ዘልዬ ነው አምልጬው የመጣሁት። ይኸውልሽ በጉማሬው የገሾለጠኝ! " ብላበጀርባዋ ላይ ያጐረበጠውን የጉማሬ ሠንበር ታሣያታለች።አልቆየም፣ ይህንኑ ጨዋታ ይዘው፣ ጉሽ ጠላ ቸውን እየከሰከሱ ሲያወሩ፣ ሌላ የሴት ድምፅ ከደጅ ይጣራል።

" ሩብያ! ኧረ ሩብያ! ሩብያ! " ትላለች አዲሲቱ እንግዳ።

" ማን ልበል? " ይላል ባሏ ድምፁን ከፍ አድርጎ።

" እኔ ነኝ ክፈቱልኝ!" ትላለች።

" ደኅናም አላመሸሽ " ይላል ባል በሩን እየከፈተ። ለካስ ይህችም እመቤት ተመሣሣይ የዕለቱ አጋጣሚ ደርሶባት ያባወራ ዱላ ቀምሳ ያመለጠች፣ ከማዶው ባሻገር ባለ ዠረት አጠገብ የምት ኖር፣ የሩብያ አብሮ አደግ ጓደኛዋ ኖራለች። ከላይዋ ላይ ያንገት ልብስም ሆነ ነጠላ አልደረበችም። እንዲውም ከምሽቱ ግብ ግብ የተነሣ፣ ባሏ ቀሚሷን ሳይቀር አራት ቦታ ላይ ከላይ እስከታች ተር ትሮባት፣ አዶከብሬ ያሳበዳት ወፈፍቱ መስላ ነው የመጣችው። ቀደም ሲል እነሩብያ ቤት፣ ለሽሽት የመጣችውም አብሮ አደግ ጓደኞች በመሆናቸው፣ ገና በሩን ስትገባ የቀሚሷን መቀዳደድ አይታ ሳቋን ለቀቀችው። የጐንና የጐን ሽንጧ ወለል ብሎ ይታ ያል። የበስተፊቷና የበስተኋላዋማ፣ ሆነ ብሎ የሠሩት ይመስላል።

አፈግጥጿኢና ኩስ አምባዋ " እዮኝ! እዮኝ! " የሚል ሆኖ እንዳ ቀረቡት ትርዒት መስሎ ፈጥጦ ይታያል። ደግነቱ ሁሉም ከልብ የሚተዋወቁ በመሆናቸው፣ የዐካሏን ሁለንተና በሚያሳይ ሁኔታ በመምጣቷ፣ አልተፋፈሩም። ሣቃቸው ግን የቤቷን ጣራ ቀድዶ ሊወጣ ምንም አልቀረውም ነበር።

" በጣም ደበደበሽ እንዴ " ትላለች ሩብያ ሣቃቸው ጋብ ሲል።

" ምንም አላስተረፈኝ! " ትላለች እንግዳይቱ፣ ጥብጣብ በመሰለ መልክ በተቀዳደደው ቀሚሷ ውስጥ የቆሰለችውን እያሣየች።

" እሱ ነብርኮ ነው! ዛሬ ስብሰባው ላይ ስሙም ተነስቶ ነበር " አለች ሌላይቱ ለሽሽት ቀደም ብላ የመጣችው ጓደኛቸው።

" ስብሰባው ላይ እንዳትገኝ አልነገረሽም ነበር? " አለ ባል።

" በጣም ስለፈራ፣ ሒጂም ቅሪም አላለም! ያው ትዕዛዝ በመሆኑ፣ ጠዋት ለጉዞው ስዘገጃጅ፣ ፊቴ ተኰማትሮ፣ አይ መስሉ መስሎ ነበር! " አለች ሁኔታውን እየገለጠች።

" ታዲያ ጠዋት ዝም ብሎ ለቆሽ፣ አሁን ምን ሁኚ ነው የሚልሽ? " አለች ሩብያ፣ ሣቋን እየቀጠለች።

" እግሬን እጠቢኝ! ብሏት ይሆናል! " አለች ሌላዪቱ ሸሽታ የመጣች ጓደኛዋ፣ በራሷ ላይ የደረሰውም ትዝ እያላት።

" አለሽ እንዴ! " አለች ሩብያ እያሚሚቀች።

" ኋላሳ! " አለች እንግዳዪቱ፣ የምሽቱ ሁኔታ እየታያት።

" አጅሪት እምቢ ብለሽው ይሆናል! " አለ የሩቢያ ባል።

" ምን በወጣኝ ንክች አላረገውም!ዛሬ ቀን ወጥቶልናል! ባሪያው አድርጐ እንደፈለገው ሲረግጠኝና ሲነዳኝ ኖሯል!

t.me/OLDBOOKSPDF

ይበቃዋል! እድሜ ለሴቶች ሹማምንት! ዛሬ ሲያስተምሩን ውለ ዋል! የምን አዛዥነት? የምንስ እግር ማጠብ? ነፃ ወጥተናል። ክብሩን ጠብቆ መኖር ባይፈልግ፣ ዋጋውን የገጠር ማኅበር ይሰ ጠዋል፣ አለያም የመፍታት መብቴ የተጠበቀ ነው! የትም ሠርቼ አድራለሁ!....." አለች፣ የምሽቱ ዱላና፣ የባሏ ግብግብ እጅግ አስመ ርሯትና አበሳጭቷት። በርግጥም ባሏ የታወቀ አክብሩኝ ባይ፣ የቀበ ሌያቸው ጉረኛ ሰው ነው። ድሮም ቢሆን አብዛኛው የባላባት ልጅና የነፍጠኛ ውላጅ ቀብራራዎች ናቸው። ተጀምሮ እስኪ ጨረስ፣እንኳንስ ሰሌት፣ ላልመሰላቸውም ወንድ፣ ፊት አይሰ ጡም። የዚያን ዕለቱ የስብሰባ አፈና፣ ያጨለመባቸው ሰዎች ቢኖሩ፣ በእነዚያ መሰሎች ትዕቢተኞችና አብሪተኞች ላይ ነው። ተራውና ጭቁኑ ገበሬ ግን፣ ሚስቱን የሚመለከታትም ሆነ የሚያከብራት፣ ዝቅ ሲል እንደእህቱ፣ እንደሚስቱ፣ ከፍ ሲል እንደ እናቱ ነው። አልፎ አልፎ፣ መጥፎ ባሕሪ የተጣላው፣ ሚስ ቱን ፍፁም ታዛዥ አድርጐ በበላይነት ስሜት ሲያጮላለት የሚገኝ ቢኖር፣ ቁጥሩ እስከዚህም አይደለም። በተረፈ ግን፣ ራሱ የግብ ርናው ዝቅተኛ ኑሮ ተባብሮ መሥራትና መከባበርን የሚጠይቅ በመሆኑ ለመናናቅ ዕድል አይሰጥም። ስለሆነም ፍቅራቸው የእኩ ልነታቸው ምልክት ነው። ሰው ሠራሽና በትዕዛዝ የተገኘ መከባ በር ሳይሆን፣ ከልብ የመነጨ ፍፁምና ተፈጥሮአዊ የሆነ መቀራረብ ነው ያላቸው። በነግራዝማችና በነአለቃ ቤት ያለው የኑሮ መልክ ቅይር ስለሆነ፣ ምናልባት የስብሰባው መብረቅም ሆነ ነጐድጓድ፣ በነሱ አካባቢ ተአምር ይሠራ ይሆናል። የነዚያ መሰሎቹ ባለትዳ ሮች፣ ስለሚስቶቻቸው ያላቸው ስሜት ብቻ ሳይሆን መላ ያስተሰ ሰብ ባሕርያቸው መለወጥ እንዳለበት፣ ህገር የሚያውቀውና የሚያምንበት ነው። ሚስቱን ሲደበድብ ያመሸ አባወራ ሁሉ፣

የነዚያ ምጥን ቤተ-ሰቦች ዝርያና ዘርፍ ያለው ነው። በነዚህ አካባቢዎች ላይ የሚሽከረከሩ ሐሳቦችን፣ አራቱ ሰዎች ቁጭ ብለው፣ ያንን ጉሽ ጠላቸውን እየቀመቀሙና፣ ያጋም እንጨት አሳታቸውን እየከሰከሱ፣ ይደልቁት ጀመር።

" እኛ ደኻዝማች ምን ውጧቸው ይሆን? " አለች ሩብያ፣ ያውራጃው ሕዝብ ባላባት ትዝ እያላት። ከዛያ ያላነሱ የሴት አገል ጋዮች አሏቸው።

" ካብትሼ ነፃ ወጣች አትይኝም እንዴ! እንዲያ የደኻ ዝማች ዘመድ በሞተ ቍጥር፣ ደረቷን ለመቤቷ ገልጣ በመስጠት በየልቅሶው ላይ ስታስደበድብ የምትውለው! " አለች መጀመሪያ ሽሽታ የመጣችው የሩብያ ጓደኛ።

" እንደክብር ነበርኮ የምትቆጥረው! " አለች ሌላይቱ ጓደኛዋ።

" የምን ክብር እቴ! እሜቴም እንግዲህ የራሳቸውን ደረት ገለጥለጥ አርገው መደብደብ ሊኖርባቸው ነው! " አለች ሩብያ።

" እንደነሱ ላሉት ሁሉ፣ ስብሰባው የለብቃ ጠበል ነው። ሌላው ቢቀር ደረታቸውን በሌላ ሰው እጅ የመደብደብ በሽታ ይፈውሳቸው ይሆናል! " አለ ባል፣ ጠላውን እንዲጠጡ፣ የምሽቱን ሁለት ድንገተኛ እንግዶቹን እየጋበዘ። ቀጠልም አድርጐ፣ " ሩብያ ብዙ አላጫወተችኝም። ድው ብሏታል። ስብሰባችሁ እንዴት ነበር? " አለ ባል፣ ሁለቱን እንግዶች፣ ስለቀኑ ሁኔታ ይበልጥ ለማወቅ እየቋመጠ።

" ልቤ ነው የረካው! " አለች ሁለተኛ ላይ የደረሰችው እንግዳ። ዱላው አስደንግጧታል እንጅ፣ ጨዋታ የምትወድ ትመ ስላለች። ስትናገርም ፎለፎል ናት። ልቤ ነው የረካው! ሴትነቴን ካወቅሁበት ጊዜ ጀምሮ እመኘው የነበረውን ሐሳቤን ነው የሰብሰ

t.me/OLDBOOKSPDF

ባው መሪዎች ሲናገሩ የሞሉት። እኛ ሴቶች በገዛ ራሳችን ፍቅር፣ የምንወደውን ፍቅረኛ እንኳ እንደፈለግነው ማነጋገር አንችልም። እኛ ሴቶች፣ ያልተጫነብን የቤት ሙያ የለም። እንፈትላለን- ለማ ልበስ፣ ወለል አዛባ እንለቀልቃለን - ለማናር፣ እንፈጫለን፣ እንወቅጣለን እናልባስን እንጋግራለን - ለመመገብና ሕይወት ለመስጠት። ሌላው ቀርቶ፣ የወንዶች ስሜት ሲነሣ እንጅ፣ ስለኛ ስሜት ምንነት ተነግሮም ሆነ ተከብሮ አያውቅም። የቤት ራስ ወንድ ነው እየተባለ፣ ፈላጩ ቆራጩ፣ አድራጊው ፈጣሪው ባል ብቻ ነው። አስታውሳለሁ አምና፣ ዶሮ የሚያርድ ወንድ ጠፍቶ ፋሲካን በደረቁ አሳልፈናል። እሪ ስንቴ ተነግሮ፣ ሴት ተሳስታ የወንድ ሱሪ አጥልቃ ብትገኝ፣ ያያት ሁሉ ያመናጭቃታል። ከተሜዎች እንኳ በዚህ በዚህ ተለማምደዋል። እኛ ገጠሪዎቹ...." ብላ ልትቀጥል ስትል፣ የሩብያ ባል ነገሯ ከንከኖት አቋረጣትና፣

" የተናገርሽው ትክክል ነው። በተለይም ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን የሚመለከት አንድ ነጥብ አንስተሻል። ከተሜዎችና ገጠሬዎች ያልሽው ነው። ሁለት ፍፁም የተለያዩ ቦታዎች ናቸው። እንደየአካባቢያቸው የሥልጣኔ ከፍታና ዝቅጠት፣ በውስጣቸው የሚርመሰመሰው ሕይወትና የኑሮ ዐይነት ይለያያል። ከተሜዎችኮ፣ ባይንዛዛም ያዲሱን ስልጣኔ ገፈት ቀማምሰዋል። ሳይንስ ባስገኘውም ሚሳይ፣ ባይበዛም ተጠቅመዋል። የሥራቸው ዐይነት፣ የሚሠሩበት መሣሪያ፣ የመጓጓዣው፣ የገበያው፣ ሌሎችም የኑሮ አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ከኛ ከገጠሮቹ ይልቅ ይበልጥ የተሻሻሉና የተሟሉ ናቸው። ይህ ሁኔታ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን ልዩነት ብቻ ሳይሆን፣ በከፍተኛና፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ መካከል ያሉትን ልዩነቶች፣ ከኛ ከገጠሬዎቹ ይልቅ ያጠብላቸዋል። እንዱን የከተማ ደህ፣ ገጠርኮ እንደሀብታም አድርጐ የሚያይበት ጊዜ አለ

ከራሱ የገጠር ኑሮ ሁኔታ ጋር እያስተያየው! ከተሜዎች፣ ‘ ከገጠር ንብ የከተማ ዝንብ ይሻላል ’ እያሉ ይተርቱብንስ የለ? ስለዚህ ነገሩን በየመልኩ ካየነው ይበልጥ ሊገባንና መፍትሔ እኛው ራሳችን ልንፈልግለት እንችላለን። ደግሞም.... ” ብሎ ሲቀጥል ሲል ሌላዋ አቋረጠችው።

“ ምነው እባክህ፣ ጉዳያችንን ወደ ከተማ ትወስድብናለህ? እኛ የምናወራው፣ ስለኛ ራሳችን ጉዳይ፣ ስለባሎቻችን አምባገነንነት፣ ጠዋት ማታ፣ ፋታ ስለነሳን የቤት ሙያ ተግባራችን፣ በፍልጥና በጉማሬ በየቀኑ ስለመደብደባችንና ስለመሳሰለው ነው። ከተማ ምን አስሔደን። የኛን የራሳችንን የቤታችንን መራራ ኑሮና ጉዳት ከተናገርን መች አነሰን! ተሠቃይተናልኮ..... ምነው አንቺየ! ያንን ውሀ ለመቅዳት እንስራችንን አዝለን ወደ ዥረት ስንወርድ የምንዘፍነውን አታመጭልኝም!” ብላ ለሩብያ ባል እንዲያሰሙት ትጐተጉታቸዋለች። ያንን ጉሽ ጠላ፣ ከደረሰባቸው የምሽት ብስጭት ጋር ሁለት ሦስቴን ቅል ጨላልጠው ስለነበር የልባቸውን ለመናገር፣ ማደፋፈሪያ ሆኗቸዋል።

“ ልክ ነሽ! እናሰማዋለን ” አለች ሚስቱም ከሁለቱ እንግዶች ጋር ተደርባ።

“ የማዳውርበት ጭኔ ተመላልጧል፣
ውሃ እምቀዳበት ጀርባዬ ተግጧል፣
የምሸከምበት ትከሻዬ ጐብጧል፣
ሳፈላ፣ ስቀቅል፣ ስቆላ ስጋግር፣ ያ ዐይኔ ሞጭሙጩዋል፣
ባሌ የሚገርፈኝ ሰውነቴ ሟልጧል፣

ይህን ሁሉ ሆኜ እንዳለሁት አለሁ።
ቀን የሚያስጥንውን በተስፋ እየጠበቅሁ።---- ” የሚለውን ዘፈን፣ በዘያ በጉሽ ጠላ ፈረሳቸው ሲያረግዱበት ጊዜ፣ ያ የነሩብያ ሰቀላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤት የሠርግ በዓል የሚከናወንበት ትልቅ ዳስ መስሎ፣ በሴቶቹ እስክስታ አበደ። ሦስቱም ሴቶች ተነስተው፣ የኩራዝ ላምባ ብልጭ ብልጭ እያለ፣ ባበራው ወለል ላይ፣ እስክስታቸውንና ዘፈናቸውን ያቀልጡት ጀመር። ረዣሙን ዘፈናቸውን ባጭር ሙናየ ተኩትና፣

“ አህያ መጣች ተጭና ማር
አባወራዬ በል ደኅና ደር!
አህያ መጣች ተጭና ስኳር፣
ወንድና ሴቶች እንከባበር።
አህያ መጣች ተጭና ከሦ፣
ምን ይዋጣቸው እናስገብር ሲሦ!
አህያ መጣች ተጭና ፈጦ፣
ባልንት ቀረ ዐይንን አፍጦ።.....” እያሉ ይደልቁት ጀመር።

ሩብያም፣ አዛባ የምትለቅምበትን ገረወይና አምጥታ ከበሮዋ በማድረግ፣ ባሎቻቸው ካስመረሯቸው ሁለት ጓደኞቿ ጋር ገጥማ፣ እስክስታውን ታቀልጠው ጀመር። የሩብያ ቤት፣ ባልታሰበ አገጣሚ ተሟሙቆ፣ ጨዋታው እንደደራ፣ መንፈቀ ሌሊት ተገባዶ ኖሯል። እስክስታቸው አድክሟቸው፣ ከመደቡ ላይ ዐረፍ እንዳሉ፣ ቁጭ ብሎ በጥሞና ይመለከታቸው የነበረው፣ የሩብያ ባል፣

“እረ ከውጭ ዑዑታ የሰማሁ መስሎኛል!” አላቸው።

“ የምን ዑዑታ ይሆን ብለው!” አራቱም ተያይዘው ወደ ውጭ ፣ ዑዑታውን ለማዳመጥ ይወጣሉ። ለካስ ከግዶአቸው ባሻገር ላይ ከሚገኝ ቤት ውስጥ ዑዑታ ይቀልጥ ኖሯል።

“ የወንድ ያለህ! ድረሱልኝ! ሊገድለኝ ነው! አድኑኝ! ” የሚል የሴት ድምፅ ከልቅሶ ጋር ይሰማሉ። ሩቅ በመሆኑ ግን፣ ምንም ነገር ማድረግ ስለማይችሉ “ አይ ያቺ ወርቅነሽ ትሆናለች!

" እያሉ ወደቤት ተመልሰው ጪዋታቸውን ቀጠሉ።

" የናንተም አባወራዎች እዚህ ቢመጡኮ፣ እንደወርቅነሽ መሆናችሁ ነው! " አለ የሩብያ ባል እየሣቀ።

" አይ እነሱማ ከቤታቸው አባረውናል! ያውም ደብድበው ነው ያባረሩን! ደግሞ ምን እንሁን ብለው ነው የሚመጡት? " አለች የመጀመሪያዪቱ እንግዳቸው።

" እረ አይቃጣቸውም! " አለች ሁለተኛይቱ።

" መምጣትስ አይመጡም፣ እየቀለድሁ ነው። ግን ጥያቄ ዬን በደንብ አልመለሳችሁልኝም! " ይላል፣ የሩብያ ባል፣ በስብሰ ባው አማካይነት የሠረፀባቸውን ስሜት ለመገምገም እየተመኘ።

" ስንቴን እንነግርህለን! በጣም ሰፊ ነው! ሩብያ አላስ ረዳችህም እንዴ! " አለች ሁለተኛዪቱ እንግዳ።

" እባክሽ እሱ ሰምቶ ሰምቶ አልጠቀመውም! " አለች ሚስት።

" ምን አለፋህ፣ እንደነገሩን ከሆነ ከመሐላችን ውስጥ በቅ ርብ ጊዜ፣ የሴት ፓትርያርክ፣ የሴት ጀኔራል፣ የሴት ሚኒስቴር፣ የሴት ክፍለ ግዛት አስተዳዳሪ ፣..... ባጠቃላይ በሁሉም መስክ የመሠማራት ዕድል ሊኖረን ይችላል። ለሴቶች ተንፍሳ የኖረውን ቤተ-መቅደስ ሳይቀር፣ በቅርብ ጊዜ ገብተን እንቀድስበታለን። ብዙ ሺህ ሠራዊት ሊያዘ የሁለትና ሦስት ባታልዮን ጦር፣ ማርሻልና ጀኔራል የምንሆንበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። እነዚህ ምሳሌዎች ይሁኝ እንጅ፣ ምን አለፋህ፣ በጠቅላላው፣ ወንዶች ከደረሱበት የሥልጣን መሠላል ጫፍ፣ እኛም ሴቶቹ የመውጣትና የመድረስ መብት እንዳለን፣ ባንድ ቀን ትምህርታቸው ብቻ አስረድተው አሣምነውናል " አለች፣ ፎለፈሊቱ ተቀዳሚ እንግዳ።

" እኔን ይበልጥ ደስ ያለኝ " አለች ሁለተኛይቱ እንግዳ "

t.me/OLDBOOKSPDF

እኔን ያስደሰተኝ፣ ማንኛዪቱም ሴት፣ የፈለገችውን ወንድ መርጣ ማግባት ትችላለች ያሉት ነው። የሴቶችም የፍች መብት በሕግ የተጠበቀ መሆኑንም ነግረውናል። አጅሬን ነገ ጠዋት ጤና ይስጥ ልኛ ነዋ! " አለች፣ በምሽቱ ዱላ የተደበደበችበት ሥምበሯ፣ እንደ መቀኖሰል ብሎ ሲጠዘጥዛት እየተሰማት። ሁለቱም የሩብያ የምሽት እንግዶች ለጥቂት ጊዜ ቢሆንም ከተማ ቀመሶች ናቸው።

" የነገሯችሁ ሁሉ በሙሉ ትክክል ነው። ሰሐ አይወጣ ለትም። ለወንዶች የሆነው ሁሉ፣ለሴቶችም የማይደርስበት ምንም ምክንያት የለም። እንዲውም! ሴቶችኮ የወንዶች እናቶች ናቸው! ማበላለጡ አያመችም እንጅ፣ ወንዶችም የሴቶች አባቶች ናቸውና- ለወንዶች ዘንቦ ያጐረፈው፣ ለሴቶችም ቢያርከፈክፍ አይበዛባ ቸውም። ግና አያሌ ትውልዶች ለዘመናት ቆይታ፣ ባሕል በሚሉ መጫሚያቸው ረግጠው ያተሙትን አስተሳሰብ ባዲስ መልክ ለማ ደስ ጊዜና ዘዴ ሳይጠይቅ የሚቀር አይመስለኝም። አንዱ ዘዴ ትምህርት ማሰራጨት ነው፣ በተለይም ለኛ ለገጠሬዎቹ! የጐለመ ስነውንና ያረጀነውን ሰዎች ማደስ እንኳ ባይችል፣ አዲሱን ታዳጊ ትውልድ፣ ከኋላ ቀር ሐሳቦች ተከላክሎ ማዳን ይቻላል። አሁን እነአለቃ ፍስሐ፣ እንዲያ ወልደው፣ ከብደው፣ ያን ሁሉ ማቲያ ቸውን አፍሰው፣ ከሚስታቸው ጋር ሲናቆሩ፣ ለሁለቱም የሚጥም ድርጊት አይመስልም። ባጭርም ጊዜ ውስጥ፣ ይህ ትብትብ ችግር በቀላሉ እንዲፈታ፣ ካስፈለገ፣ " የሀገሩን ሠርዶ በሀገሩ በሬ " እንዲሉ፣ ከዚሁ ከቀበሌ የችግሩን ምንነት ሠቅስቀው በሚያውቁት ገጠሬዎች ቢሞከር ይሻላል እንጅ፣ ስለመስኰብ አካባቢ ገጠሮች ተመሳሳይ ችግር በሚል ዘዴ ለመንፈቅ ዕድሜ ታሸተው በመጡት የሴቶች ሊቃውንት፣ መፍትሔ ማፈላለጉ የሚያዋጣ አይመስለኝም " አለ የሩብያ ባል፣ አራምባና ቆቦ ገብቶ የሚቀባጥረው፣ የሱ

ሚስት በየትኛው ነጥብ ላይ ተነክታ ፣ እንዲያ በአንድ ቀን ውስጥ ሻጉራ የሆነችበትን መነሻ፣ ፈልፍሎ ለማግኘት እየሞከረ ነው።

" ግደላችሁም፣ እነዚህ ሰዎች፣ ሌላም ተልእኮ ይኖራቸው ይሆናል! " አለች ሩብያ ድንገት ሌላ የውስጧ ሐሳብ ብልጭ ብሎባት።

" እረ እባክሽን ተይ! እኛን ነፃ ለማውጣት ካልሆነ በስተቀር ሌላ የተለየ ዐላማም ሆነ ግብ ያላቸው አይመስለኝም አለች " ያቺ ተቀዳሚቱ እንግዳቸው።

" አቀራረባቸው ያስጠረጥራል!" አለ የሩብያ ባል፣ አስተያየት እንዲሰጡት በር እየከፈተና ሐሳባቸውን እንዲሠነዝሩ እየጋበዘ።

" ሌላ ምን ተግባር ይኖራቸዋል ብላችሁ ታስባላችሁ? " አለች ሁለተኛዪቱ እንግዳ።

" ምናልባት፣ በአንደኛ ደረጃ የምንመኛቸውን ፍላጐቶች ለሚሟላት፣ መንግሥት፣ ዐቅምም ሆነ ፈቃደኛነት ስላለሰው፣ እኛ ንና አንድነታችንን፣ በሁለተኛ ደረጃ ፍላጎታችን ላይ ብቻ ትኩረት በማሳረፍ፣ ሊበታትነን ፈልጐ እንደሆነስ ማን ያውቃል? የሴቶች መብት እያለ የዘረጋቸው አውታሮች፣ በቀጥታ በየቤቱ ገብተው የት ዳርን ምሰሦ ለመነቃቀር፣ እየተተበተቡ ናቸው፣ ይሽው እናንተ ዛሬ በኛ ቤት ያለውዴታችሁ ማደራችሁ፣ ያንድ ቀን፣ አንድ ምል ክት ነው።" አለች ሩብያ፣ ከባሏ የተማረችው ይመስላል።

" በአንደኛ ደረጃ የምንመኛቸው ፍላጐቶች የምትዪው፣ እነየትኞቹን ነው? " አለች ያቺ የመጀመሪያዪቱ እንግዳ።

" እዚህ ላይ ሩብያን አኔም እረዳታለሁ። መንግሥት በተቀዳሚ በተለይ ለኛ ለገጠሬዎቹ ሊያደርግልን የሚገባውና፣ እኛም ለብዙ ጊዜ ስንመኘው የኖርነው፣ የተሻለ መጠለያ ቤት፣ የተሻለ

t.me/OLDBOOKSPDF

ልብስ፣ የተሻለ ምግብ የምንላቸውን ነው። እነዚህን ሊያስገኙ የሚችሉ ዘዴዎች ቁጥራቸው ቢበዛም፣ ዐይነተኞቹ ግን ገንዘብና እውቀት ናቸው። መንግሥት በሰጠን መሬት፣ ሌላ እጅ ባይገባበት፣ ከሚያደርግልን ተጨማሪ እርዳታ ጋር (መነሻ ሀብት) ራሳችን ሠርተን ገንዘብ ማግኘት እንችላለን። ካፈር ጋር ለመታገል ደግሞ፣ ጤነኛ ዐካል እንዲኖረን ያስፈልገናልና፣ ሐኪም ቤትና ክሊኒክ ቢያቆምልን አስፈላጊያችን ነው። ከዘመኑ ሥልጣኔ ለመቅሰም ሆነ ጥንታዊ አስተሳሰባችንን ለመለወጥ ደግሞ ዕውቀት ያስፈልገናል። የዕውቀትም ምንጭ ትምህርት ቤትና፣ በተግባር ላይ የምንቀስመው የየቀኑ ልምድ ነው። ስለሆነም እኛ ገጠሮቹ ለአከባቢያችን ጠቃሚ የሆነና ሁሉ-ገብ የሆነ ትምህርት ቤት ቢቋቋምልን፣ ሌላው የመጠለያችን፣ የልብሳችንና የምግባችን ማሻሻያ ዘዴ ነው! ታዲያ! እነዚህ መቸ አሉን? ይህ እንኳ የማይሆንለት ቢሆን፣ እግር አትጠቡ ከማለት ይልቅ ሴቶች ከተሸጐጡበት ቤት ውስጥ ወደ አደባባይ የሚወጡበትን ስር ነቀል ለውጥ ለማስገኘት የሚያስችሉ ፣ ፕሮግራሞች ደረጃ በደረጃ ባዘጋጁ ነበር.... " አለ፣ ከበስተፊቱ ያለውን እሳት እየቆሠቆሠ ።

" ለውጥ አለ ይሉናል ሰማን እንጅ አላየን፣
ባላገር እኛ ግን እንዳለነው አለን፣
ሙቀጫና ወፍጮ፣ ቁናና እንሥራ፣ እያላገጡብን!"...

እያለች ሩብያ ታንጐራጉር ጀመር፣ የባሏን ሐሳብ በመደገፍ።

" ምነዋ ባሎችን ተውሽብን " አለች ሁለተኛዪቱ ሞኛሞኝ ብጤ እንግዳዪቱ። ሩብያ ይህንን ስትሰማ፣ ከመቀመጫዋ ተነስታ፣ ባሏ አንገት ላይ ተጠመጠመችና፣ " የኔ ባል ወተት ነው " እያለች ያ እንደሎሚ መጠጣዋን፣ ሁለት ጓደኞቿ እያዩአት ታስነካው ጀመር። ይህን ትርዒት በማየትና በማሳየት ላይ እንዳሉ፣ ከቤቱ

ጣራ ሥር ባለ ቆጥ ላይ የሠፈሩ የሩብያ አራት አውራ ዶሮዎች ደግመው ደጋግመው " ኩኩሉ! ኩኩሉ! " እያሉ የሰሚዎ ቻቸውን ጆሮዎች እስኪያደነቁሩ ድረስ ጮኹ።

" ዛሬ ወፍጮውም መቅረቱ ነው! ጨዋታችንን ይዘን ስን ደልቅ፣ ለካስ ሌሊቱ ሊነጋ ተቃርቦ ኖሯል! " አለች ሩብያ። ባሏም ከመቀመጫው ተነስቶ ከቤታቸው ውስጥ በስተቀኝ በኩል ካለው ሰፊ የመኝታ ደረቅ መደብ ላይ፣ ድርቆሽ ሣር ይጐዘጉዝ ጀመር።


" እኛ ቤት ይኸውላችሁ፣ የንጨት አልጋ እንኳ የለንም አለ! " እንግዶቹን ይቅርታ እየጠየቀ።

" የሁላችንም ያው መደብ ነው " አለች ሁለተኛዪቱ እን ግዳ። በየቅል የያዙትን ጠላቸውን ሁሉም ጨላለጡና ኬሻ ብቻ በለበሰ የመደብና የድርቆሽ መኝታቸው ላይ ክልትው አሉ።

በማግስቱ ሁለቱ እንግዶቿ ወደ ስብሰባው ሲያመሩ፣ ሩብያ ሌሊት ያለፈበትን ወፍጮዋን ተያያዘችው። በቀበሌያቸውም ስብሰ ባው ባስከተለው ጦስ፣ ብዙ ሰዎች ተጋደሉ፣ ብዙ ሰዎች ተፋቱ፣ ብዙ ሰዎች ታሠሩ። በየት አምልጠው እንደሔዱ አይታወቅም እንጅ፣ እነዚያ የመጀመሪያውን የስብሰባ ዱብ ዕዳ ገፈት የቀመሱ ሁለት የሩብያ እንግዶች፣ ጂቡቲ ገብተው " ሴተኛ አዳሪ " ከሆኑ መንፈቅ አልፏቸዋል። ሩብያና ባሏም፣ " ስብሰባውን ንቆ ባለመ ካፈልና፣ የሴቶችን እኩልነት መብት በማርከስ " በተሰኙ ሁለት የወ ንጀል ዐይነቶች ተከሠው፣ ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ሳይቀርብ፣ ከሚኖ ሩበት ቀበሌያቸው ወደ አውራጃው ዋና እሥር ቤት ተወስደው፣ ያለፍርድ ከታሠሩ፣ ይኸው ሁለት መስቀሎችን ተኩሰዋል።

t.me/OLDBOOKSPDF

" ዘሲግሞስ "



መፈጠሬ ብቻ ፣ አርጎኝ ወንጀለኛ፣
ሰግቶት ኖሬአለሁ ፣ ሆንሰት አሰረኛ!

(የጠፍ. ✱.7)

ጣራ ሥር ባለ ቆጥ ላይ የሠፈሩ የሩብያ አራት አውራ ዶሮዎች ደግመው ደጋግመው “ ኩኩሉ! ኩኩሉ! ” እያሉ የሰሚዎ ቻቸውን ጀሮዎች እስኪያደነቍሩ ድረስ ጮኹ።

“ ዛሬ ወፍጮውም መቅረቱ ነው! ጨዋታችንን ይዘን ስን ደልቅ፤ ለካስ ሌሊቱ ሊነጋ ተቃርቦ ኖሯል! ” አለች ሩብያ። ባሏም ከመቀመጫው ተነስቶ ከቤታቸው ውስጥ በስተቀኝ በኩል ካለው ሰፊ የመኝታ ደረቅ መደብ ላይ፤ ድርቆሽ ሣር ይጐዘጉዝ ጀመር።


“ እኛ ቤት ይኸውላችሁ፤ የንጨት አልጋ እንኳ የለንም አለ! ” እንግዶቹን ይቅርታ እየጠየቀ።

“ የሁላችንም ያው መደብ ነው ” አለች ሁለተኛዪቱ እን ግዳ። በየቅል የያዙትን ጠላቸውን ሁሉም ጨላለጡና ኬሻ ብቻ በለበሰ የመደብና የድርቆሽ መኝታቸው ላይ ክልትው አሉ።

በማግስቱ ሁለቱ እንግዶቿ ወደ ስብሰባው ሲያመሩ፤ ሩብያ ሌሊት ያለፈበትን ወፍጮዋን ተያያዘችው። በቀበሌያቸውም ስብሰ ባው ባለከተለው ጦስ፤ ብዙ ሰዎች ተጋደሉ፤ ብዙ ሰዎች ተፋቱ፤ ብዙ ሰዎች ታሠሩ። በየት አምልጠው እንደሔዱ አይታወቅም እንጅ፤ እነዚያ የመጀመሪያውን የስብሰባ ዱብ ዕዳ ገፈት የቀመሱ ሁለት የሩብያ እንግዶች፤ ጂቡቲ ገብተው ” ሴተኛ አዳሪ ” ከሆኑ መንፈቅ አልፏቸዋል። ሩብያና ባሏም፤ “ ስብሰባውን ንቆ ባለመ ካፈልና፤ የሴቶችን እኩልነት መብት በማርከስ ” በተሰኙ ሁለት የወ ንጀል ዐይነቶች ተከሠው፤ ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ሳይቀርብ፤ ከሚኖ ሩበት ቀበሌያቸው ወደ አውራጃው ዋና እሥር ቤት ተወስደው፤ ያለፍርድ ከታሠሩ፤ ይኸው ሁለት መስቀሎችን ተኩሰዋል።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ ዘሊግሞስ ”



መፈጠሬ ብቻ ፣ አርጎኝ ወንጀለኛ፤
ስግቅት ናሬአለሁ ፣ ሆንለት እስረኛ!

(የጠፍ. ቁ.7)

መንደርደርያ

በዓለማችን፤ እላይ ያለው ወደ ታች ላለመውረድ፤ እታች ያለው ወደ ላይ ለመውጣት ሲሉ፤ ትግል በየመልኩ ይካሔዳል። አንዱ ክፍል ጐልብቶ ድል ያገኘ እንደሆነ፤ ምርኰኛውን በእግሩ ስር ረግጦ አፈር ሲያስግጠው ይኖራል። ተረጋ ጩም ክፍል ተራ ደርሶት ድል ሲመታ፤ ሲረግጠው የኖረውን ድባቅ ይመታል። በነዚህ የትግልና የድል ለውጦች መካከል፤ ምንም ዐይነት ለውጥ ሳይኖረው፤ በነባርነት የሚገኝ፤ በምርኮኛነት የሚማቅቀው ክፍል፤ የሚታሠርበት እሥር ቤት ብቻ ነው። ሰው ነኝ የሚለው ፍጡር፤ ሰብዓዊነት በተለየው የሚያሠቅቅ ሁኔታ፤ ድል በማግኘቱ ብቻ፤ ጠላቴ ነው ብሎ ያመነበትን መሰሉን ፍጡር፤ እንዲያ በሚያሰቅቅ ወህኒ ቤት አሽገው ግፍና ደባ ሲፈጽምበት ከማየት የከፋ ሌላ ነገር አይኖርም። በተለይም የሰው መብትና ክብር እንዲጠበቅ፤ በየትኛውም ክፍለ ዓለም፤ የእሰጥ አገባው ክርክር በጦፈበት ዘመን፤ ያገራችን የዓለም በቃኝ እሥር ቤት በዚያ ሁኔታ ዛሬም መገኘቱ ያስደንቃል። ምናልባት የዓለም በቃኝን ውስጣዊ ሁኔታና አሠቃቂነት የማያውቅ ቢኖር፤ ዘሲባኖስን ያዳምጥ!

t.me/OLDBOOKSPDF

“ (141) (10) (67) (98) (48) ”

“ ዓለም በቃኝ ” ብለው ይጠሩታል። በመላው አፍሪቃ በጠቅላላ ይዘቱ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት፤ የትልቁ ወህኒ ቤት አንደኛው ክፍል ነው። በመናገሻ ከተማይቱ ምዕራባዊ ዳርቻ ላይ ይገኛል። የሕንፃው መሠረት የተጣለው በአፄ ምኒልክ መቅድማዊ ዘመን ላይ ሲሆን፤ እንዲያ አርገው የነደፉትና ያነፁት ግን የፈረንሣይ መሐንዲሶች ናቸው ይባላል። ከውስጡ ገብቶ ያየው ሰው ቍጥር ይነስ እንጅ፤ “ ዓለም- በቃኝ ” የሚል ስሙን የማያውቅ በመላው ምድረ-ኢትዮጵያ አይገኝም። ከቶውንም፤ ይህ ገናና ስሙ፤ የሃገሪቱን ድንበር ቆርጦ፤ የዓለም ታሪክ ፀሐፊዎችና ጋዜጥኞችን ብዕሮች እንዳሠለቸ ይነገር ለታል። ይህ ሕንፃ በመጀመሪያ ላይ ሲታነፅ፤ ለምን አገል ግሎት እንዲውል እስከዛሬ ድረስ ያልተጣራ ቢሆንም፤ ባለፈው ረዥም ዘመኑ፤ “ የነፍሰ ገዳይና የከፍተኛ ወንጀለኞች ” ማጐ ሪያ ጉረኖ ሆኖ ሲያገለግል ኖሯል።

ከአንድ አግጣጫ ላይ ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ አግጣጫ ዎች አንፃር ሲያዩት ተመሳሳይ ቅርፅ አለው። አውቀው የገለበ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጡት በርሜል ይመስላል። ካለአንድ በር በስተቀር፤ መስኮት የሚሉት ነገር ለምልክት ያህል እንኳ አይታይበትም። ልሙጥ ምልምሉን የቆመ ነው። “ አያድርግብዎትና ” እውስጡ ቢገቡ፤ ደመና ከጐረሠ ሰማይ በስተቀር ምንም ነገር ሊያዩ አይችሉም። የሕንፃው ተንቀዋሎ በረኸሙ መሠራት ለተን ቀሳቃሽ ትኩስ አየር ወደ ሕንፃው የመግባት ዕድል አይሰ ጥም። ይህም ቢመሆኑ፤ እውስጡ ያለው መከረኛ ፍጡር፤ ምንጊዜም በተቃጠለ ዐየር እንደታጀለ ነው። ስለዚህም ነው በውስጡ የሚኖሩት እሥረኞች ሁሉ፤ ከመጠን በላይ ገርጥተው ትኰስ ገመምተኛ የሚመስሉት። በተቃጠለ አየር ከመታጀል የተ ነሳ፤ አንዳንዱን እሥረኛ ዘመዶቹ ሳይቀሩ፤ ሊለዩት የማይች ሉበት አጋጣሚ አለ። የዐየሩ አፈና እንደ አራቱ የዐመት ወቅ ቶች የዐየር ጠባይ፤ በሙቀትና በቅዝቃዜ መካከል ቅይር ባሕርይ ስለሚያሳይ፤ አብዛኛውን እሥረኛ ጤና ቢስ ያደርገዋል። ይህ ሕንፃ ባለ አንድ ፎቅ ሆኖ የተሠራ ሲሆን፤ በጣም ጠባብ የሆኑ፤ ከግማሽ መቶ በላይ ክፍሎችን ይዟል። በብረት በሮቻ ቸው የታሸጉት እነዚህ ክፍሎች፤ ሁለት ሰዎች አጣበው ማስቀ መጥ ቢችሉ ነው። ግን ከስድስት በላይ ያጉሩባቸዋል። ፎቁ፤ ዳር ዳሩን የብረት አሸንዳ ያጠረው፤ ባለግማሽ ሜትር ስፋት በረንዳ አለው። ከክቡ ሕንፃ መካከል፤ አንዲት ጨምባሳ ፊን የምትል ውሃና፤ ክብ የሆነች የሲሚንቶ መስክ አለች። ያ ሁሉ እሥረኛ ተራ ሲደርሰው፤ ከሚቆለፈው የክፍል ጉረኖው ውስጥ ወጥቶ ለተወሰኑ ደቂቃዎች የሚዝናናው በዚችው ደረቅ የሲሚንቶ መስክ ላይ ነው። አበባ ቀርቶ፤ ርጥብ ቅጠ ልና ለምለም ተክል እሥረኛውን የሚናፍቁት፤ እነሱን ማግኘት ቀርቶ ማየት እንኳ ከማይችልበት ከዚህ ደረቅ አካባቢ በመኖሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው። ምዕራብም ሆነ ምሥራቅ ወይም ሰሜን ሆነ ደቡብ፤ ተገላምጦም ሆነ ተንጠራርቶ ባለው አቅም ሁሉ ቢሞክር፤ የተስፋና የሕይወት ምልክቶች የሆኑትን ለምለም እፀዋት ማየት አይሆንለትም። ከተራው ፍላጎቶቹ ታግዶ በእሥር ላይ የሚኖር ሁሉ፤ ዐለም በቃኝ ውስጥ እስካለ ድረስ፤ ከፍተኛ ትዝታ ከሚፈ ጥሩበት ነገሮች አንዱ፤ መታየት እንኳ ያልተቻሉት እፀዋት ናቸው። እነዚያ የፈረንሣይ ቅኝ ገዥዎች “ ምን ይሆነን ” ብለው እንደሠሩት ባይረጋገጥም፤ ግዛታቸውን ለሚቃወም የነ ፃነት ታጋይ ማሠቃያ ምሽጋዊ ዋሻ እንደነበረ፤ ሁኔታውን ያየ ሁሉ ይፈርዳል።

ለዚያ ሁሉ እሥረኛና ለዚያ ሁሉ ክፍል፤ ያለው ሽንት ቤት አንድ ብቻ ነው። ተራ ሲጠብቁ የወጠራቸው የሚያመ ልጣቸው ታይተዋል። የሽንት ቤት እንደፈለጉት ለማግኘት፤ የጉቦው ሥርዓት የሞቀ ነው። ሌላውንማ ጥቁር ገበያ አለማ ንሳቱ ይሻላል። እጅግ የጦፈ ነው። በዚሁ የደራ ገበያ፤ ነባር እሥረኞችና ፖሊሶች፤ ሁለትና ሦስት የቪላ ሕንፃዎች አሠር ተው በሺ ብር ያከራያሉ። ሲጋራ ማጨስ ቀርቶ፤ ይዞ መገኘት እንኳ በሚያስቀጣው በዚያ የዓለም በቃኝ ልዩ አካባቢ ውስጥ፤ የተራው ግሥላ አንዲ ቀጠና ሲጋራ እንኳ የምትሸጠው በአ ንድ ብር ነው። እንግዲህ አንዲን በ አስራ አምስት ሳንቲም ገዝቶ ያስገባ ፖሊስ፤ ኻያ ብር ነግዶባት ይወጣል ማለት ነው። ከሌሊት ልብሱና ከቀን ልብሱ በስተቀር፤ ምንም ነገር ይዞ መግ ባት በማይፈቀድበት ዐለም በቃኝ ውስጥ፤ የጥቃቅን ምጢጢ ሬድዮኖች ገበያ ሳይቀር የደራበት በመሆኑ፤ ዐለም በቃኝን የተ ለየ መልክ ከሚሰጠው ባሕርዩ አንዱ ነው። የዚያንው ያህል፤ ብጫቂ ወረቀት የተገኘበት ኩታራ እሥረኛ፤ ወንጀል ሠርተ

ሃል ተብሎ፤ ሲቀጠቀጥ የሚውልበት ቦታ ነው።

ይህ አሠቃይነቱ የተለየና በመከራ ቦታነቱ ከፍተኛ ዝናን ያተረፈ ይህ እሥር ቤት ባጠቃላይ ሥስት የተለያዩ ክፍሎች አሉት። እነዚህም ክፍሎች በሥስት የተመደቡት እንደ እሥረኛው የወንጀል ይዘትና እንደሚበየንበት የፍርድ አፈጻፀም ዐይነት ነው። እነዚህም ክፍሎች፤ ቀጠሮኛ፤ ፍርደኛና ሞት ወይም ዕድሜ ልክ እሥራት በመባል የተሠየሙ ናቸው። የመ ጀመሪያው፤(ቀጠሮኛ ክፍል) አንድ ሰው በፍርድ ቤት ተከሶ፤ ፈፅሟል የተባለው ወንጀል በዋስ የማያስለቅቀው ሲሆን፤ የፍ ርድ ውሣኔ እስኪሰጠው ድረስ፤ በቀጠሮ የሚቆይበት የመታ ሠሪያ ክፍል ነው። ዳኞቹማ የሚጠሩት "ማረፊያ ቤት" ብለው ነው። በጣም የሚገርመውና የሚያሳዝነው፤ እስከ ሰባትና ስም ንት ዐመታት በቀጠሮ ነገሩ ሲጐተት ኖሮ፤ በመጨረሻ ላይ፤ እነዚያ ምናምንቴ ዳኞች "የተከሰስክበት ወንጀል በሚገባ ሲጠና ቈይቶ በቀረበው ማስረጃ ረገድ፤ የተባለውን ወንጀል ያልፈ ጸምክ መሆኑ አሁን ስለተረጋገጠ፤ ፍርድ ቤቱ እስከዛሬ ድረስ የታሠርከው ያላግባብ በመሆኑ እያዘነ ይቅርታ በመጠየቅ፤ በነፃ መለቀቅህን ያረጋግጣል" የሚሉት ቀልድና ፌዝ ነው። ለረኽም ጊዜ ባልፈፀመው ወንጀል ተከሶ፤ በዚያ የሚያሠቃይ እሥር ቤት ውስጥ መከራውን ሲጠብስ ኖሮ፤ በንፁህንት የሚወጣው ወንጀለኛ ቍጥር ብዙ ነው። ገድለሃል ያሉት ሰው፤ መቀበሩ ሣይቀር በሥስት ምስክሮች የተረጋገጠለት ሟች፤ ከሥስት ዐመት በኋላ፤ ከነሙሉ ጤናው በሕይወት እየተገኘለት በነፃ የሚወጣው " ወንጀለኛ " ቍጥር ትንሽ አልነበረም።

ይህ " ቀጠሮኛ ቤት " የሚጠጡት ውሃ እንኳ እንደ ልብ የማይገኝበት የማሠሪያ ክፍል ነው። ከቤቱ መጥበብና ከእ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሥረኛው ብዛት የተነሣ፤ እግር ዘርግቶ ለመቀመጥ እንኳ አይቻ ልም። ለመተኛትማ የማይሞከር ነው። አንድ እሥረኛ ከተወሰ ነለት ሰዓትና ተራ በስተቀር፤ ውጭ ወጥቶ ፀሐይ መሞቅ አይፈ ቀድለትም።አብዛኛውን ጊዜ ግን፤ በዚያ ቅጥ የለሽ ቤት ውስጥ ታፍኖ መቀመጥ ነው። ከሰው ብዛትና ከዓየሩ መቃጠል የተነሣ ትንፋሹ አይጣል ነው። ምሣና ራት ብለው በነፍስወከፍ የሚያ ድሏት ድቡልቡል ቂጣ፤ በዓለም ለታወቀ ከፍተኛ ኤግዚብሽን፤ ለላንቲካ የምትቀርብ ትንግርት ነበረች። ከምን ዐይነት እህል እንደምትሠራ አይታወቅምም። እንክርዳድና ጓያ ያሉባት መሆኑ ግን፤ የበላት ሰው ሁሉ ወዲያውኑ ራስ ምታት ሲለቅበ ትና ሲያዞረው፤ ለመነሣትና ለመቆም የሚሞክረውንም፤ ሲያጥ ወለውለውና ሲያንገዳግደው ማየቱ ምሥክር ይሆናል። የሚ ገርመው ደግሞ፤ እሁድ በመጣ ቍጥር እንጀራና ሥጋ ብለው የሚያድሉት ትርኪ ምርኪ ነው። የጤፍ ነው የሚሉት እንጀራ ገና ግቢውን ሲገባ፤ አፍንጫ ይሰነፍጣል። ከምላስ ጋርማ ሲገ ናኝ አቤት ያለው ምሬት። ገና መልኩን ሲያዩት፤ የሚታይበት ጥቁረት አስቀድሞ የመብላት ፍላጐትን ይዘጋል። የሽመጠረ ምናምን፤ ግግር እንጀራ ነው ብለው ሲሰጡ፤ ይታዘቡናል ብለው አለማሰባቸው ያሳዝናል። ሥጋዋማ የፈገፈጉባት ላጲስ ትመስላለች። ምን መምሰል ብቻ፤ ታህላለችም። ከምን ዐይነት ከብት (እንስሳ) ቆርጠው እንዳመጧት ማን ያውቃል? ከብትኮ ባለቀንዳምም ባለጋማም ነው። የዚያ ቤት አራጅ፤ ሠኰናም አይመለከት ይሆናል። ያ መከረኛ እሥረኛ በዚያ ቀጠሮ ቤት፤ ይህን አይነት ምግብ እየበላ፤ ቀኑን ውሎ በመሸ ቍጥር በነባር እሥረኞች፤ የሻማ ፍራንክ አምጣ እየተባለ በመደብደብ ይኖ ራል። ከዚህም የተነሣ የስኳር አራጣ የሌለበት የለም።

ትንሽ የተሻለ ይዞታ አለው የሚባልለት ሁለተኛው ክፍል ነው። " ፍርደኛ ቤት " ይሉታል። ለዐመታት በቀጠሮ ሲማቅቅ ኖሮ፣ እንደወንጀሉ ዐይነት ፍርድ ተሰጥቶት፣ ለተወሰኑ ዐመታት የሚኖርበት ክፍል ነው። ከዕድሜ ልክ እሥራት በታች ለተወሰኑ ዐመታት የተፈረደባቸው ሰዎች የሚኖሩበት ምድብ ቦታ ነው። በሚምንት ሁለት ቀናት ያህል፣ ከቤተ-ሰቡ ምግብ ሊገባለት ስለሚችል፣ ረዳት ያለው፣ ብዙ የምግብ ችግር አይገጥመውም። እስከዚህ ንፁህ ነው ባይባልም፣ መለስተኛ መሻሻል በመኝታውም ሆነ በቤቱ ይዞታ ላይ ይታያል። እንደ ፈሰሰው ላብ መጠን፣ አይከፈለውም እንጅ፣ እንደሙያው ዐይነት ጊዜ የሚያሳልፍበት የትንሽ ሰዓቶች የሙያ ሥራ ይሰጠዋል። " ጥቁር ገበያ " እጅግ የደራበት ክፍል ይሽኛው ነው። በሕልማቸው የሚመጡባቸውን ሴት ወዳጆች ለማግኘት እስከመቻል ድረስ፣ በልዩ ዘዴ ከተማ ደርሰው የሚመጡ፣ የእሥር ቤት መሣፍንት ቀጥር ጥቂት አልነበረም። ይህን ለማስፈፀም የሚከፈለው የዲናር መጠን ግን የትየለሌ ነው። በእሥር ቤት እንኳ፣ በመደብ መካከል ያለውን የጎብተረ-ሰብ ልዩነት የሚያንፀባርቅ፣ ይህን መሳዩ ላላቸው እሥረኞች ብቻ የሚከናወን ድርጊት፣ ቀጭልጭ ያለ ማሳያ ነው። ሦስት አራተኛው የጠቅላላው የእሥር ቤቱ አስተዳደርና ተግባር የሚመራውም ሆነ የሚከናወነው፣ ከብዙ የእሥር ዘመናቸው፣ ታማኝነት ባተረፉ ዛሬም በእሥር ላይ በሚገኙ፣ ጮሌ እሥረኞች ነው። እነዚህ ብልጣ ብልጥ እሥረኞች " ጥቁር ገበያ " ባስገኘላቸው ከፍተኛ ጥቅም የተነሣ፣ ያን ወህኒ ቤት ለዘለዓለም ሊለቁ አይፈልጉም። ከፍርድ የእሥር ዘመናቸው በኋላም፣ በዚያው በወህኒ ቤት፣ በእሥረኝነት ስም ሙጥኝ ብለው የሚኖሩ አሉ። ሳያስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቡት ያገኙትን ጥቅም ሙጥኝ ብለው፣ እሥረኛው ላይ የሆነ ያልሆነ ምክንያትና ወንጀል በመፍጠር፣ ቤሣ ውለድ እያሉ ሲያሰቃዩት አሉ። እንደነገሩ ላሉት የጊቢው፣ ቤተ ክርስቲያን፣ መስጊድ፣ መጻሕፍት ቤት፣ ለመሐድ እነዚህን አልቅቶች ማስፈቀድ ግዴታ ስለሆነ፣ ለጉቦ መብሊያ ሰፊ ዕድል አፍርቶላቸዋል። በፍርደኛ ክፍል ኪራይ መክፈል ያስፈልጋል እንጅ፣ ለወጉ ያህል የሚጐረብጥ የንጨት ድርብርብ አልጋም አለ። በተላላኪነት የሚያገለግሉ በጊቢው ውስጥ ዝናን ያተረፉ " እስኩፒኛዎች" ም ስላሉ፣ ሻይ ቡናም ማለት ይቻላል። ወንጀል ይበዛ የነበረው ከተማ ውስጥ ሆኖ ሳለ፣ በዚያ እሥር ቤት ውስጥ ከሚገኘው እሥረኛ አብዛኛው፣ ከገጠር የሚመጣ ነበር። ያን መራራ የእሥር ቤት አሠቃቂ ኑሮ ገጠሬዎች በብዛት የሚሠቃዩበት ምክንያት የሚያጠያይቅ ቢሆንም፣ ባጠቃላይ ወህኒ ቤቱ፣የሚመጡትን ሰዎች በዚያ የዘቀጠ የኑሮ ደረጃ በማጉላላቱ፣ እሥረኞቹ "ወንጀለኞች" ቢሆኑም፣ ሰዎች መሆናቸውን የረሳው ይመስላል። በዚህም ኢሰብአዊ ድርጊቱ፣ በታሪክ ይጠየቅበታል።

እንደ አውሮፓ ባሉ ሀገሮች የሚገኙ እሥር ቤቶች፣ ለመኖሪያነት ሳይቀር የሚያጓጉ ናቸው። የሚቀርብላቸው ምግብ፣ እያንዳንዱ የቅመም ዐይነት ሳይቀር በሚዛን እየተመዘነ የሚዘጋጅ ነው። የቤቱን፣ የልብሳቸውን፣ የጊቢያቸውን ጊዜ ያዊ ሁኔታ በየጊዜው እየሔደ የሚቆጣጠር፣ ገለልተኛ የተቆጣጣሪ ቡድን አለ። ለላው ቀርቶ በየበዓላቱ እሥረኞችን ለማስደሰት ሲባል፣ የታወቁ ኦርኬስትራዎች ከእሥር ቤቱ አዳራሽ በመገኘት፣ የዳንስ ምሽት አዘጋጅተው ያዝናኑአቸዋል። በእሥረኞቹም ቀጥር ተመጣጣኝ የሆኑ፣ የበጐ ፈቃድና የኪራይ

የዳንስ አጣማጆች በዕለቱ ምሽት ይቀርቡላቸዋል። ለየበዓላቱም ከተለያዩ ድርጅቶች ልዩ ልዩ ስጦታ ይደረግላቸዋል። የእነዚህ መሰሉ ሀገሮች የማሠር ዓላማና ግብ፤ ከኛው ዐይነት የተለየ ነው። የኛው፤ ወንጀለኛውን ለመቅጣት ሲሆን፤ የነሱ ግን ለማረም ነው። የመቅጣቱና የማረሙ ግብና ዐላማ፤ በሁለቱ የእሥር ቤቶች ይዞታና ድርጊት ስለሚንፀባረቅ፤ በፍትህ ላይ ያላቸውን አቋም ለማሳየት ትርጁማን አያስፈልገውም።

ሦስተኛው አስፈሪው የወህኒ ቤት ክፍል፤ ዐለም በቃኝ የተሰኘው ነው። ምንነቱን አበጥሮ ለማስረዳት፤ ሲያሜው ብቻ ይበቃል። የመነኑ ባሕታውያን፤ የዚህን እሥርቤት ይዞታ ቀደም ብለው አላወቁም እንጅ፤ በርግጥ " ዓለም በቃኝ " ብለው ከአስር ቤቱ ጠቅለው በመግባት፤ እጅግ በጣም ርቀው ከሚገኙ ገዳማት፤ ዱሮች፤ በረሀዎች ዘንድ ለመመነን ባልቻ ጣቸው ነበር። ከዛሬ አሥራ አምስት ዐመት በፊት፤ በዚህ የዐ ለም በቃኝ፤ የማሠሪያ ጉረኖ ውስጥ ቍጥራቸው ከአምስት መቶ በላይ የሆኑ ነፍሰ ገዳይ እሥረኞችና ጥቂት ከፍተኛ የፖለ ቲካ እሥረኞች ታጉረው ይኖሩ ነበር። የሲጋራ ሱስ ያለበት እሥረኛ የግስላ ብጣቂ ጥንባሆ፤ ከላይኛው ከንፈሩ ስር እንደ ሡረት ለግጦ ሦስት አራት ቀናት ያለንግግር የሚውል እሥረኛ ማየት፤ ተራው ትርዒት ነበር። እንዲያ መሆኑ፤ የገጠጠ ችግር ወጥሮ ይዞት ነው። በስንት ሥቃይ በኰንትሮባንድ የሚያገ ኛትን ሲጋራ ለማጨስ ዕድል አልነበረውም። እሳት በጊቢው ድርሽ አይልም። እንዳይተወው የሱሱ ኃይል አቅበጥብጦታል። ታዲያንን ከላኛው ከንፈሩ ስር ጥንባሆውን ለብዶ፤ መናገር እንኳ አይሆንለትም ነበር። " ነገ ይበቅላል " ብሎ ከዚያ ደረቅ የሲሚንቶ መናፈሻ ወለል ላይ፤ ብልቱን ቄርጦ የጣለ ወፈፍቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

እሥረኛ፤ ሌላው አሠቃቂ ትርዒት ነበር። " ሁለተኛ ሞት አይፈረድብኝም " ብሎ፤ እዚያው የእሥር ጓደኛውን አንቆ የገ ደለ እሥረኛም እዚያው ውስጥ ጀግንነቱን እየተረከ፤ ሦስተኛ ለመግደል ይዘጋጅ ነበር። የሥጋ ናፍቆትና አምሮት አስቸ ግሮት፤ የእሥረኛ ጓደኛውን ፍሬዎች ያኰላሸም፤ ወፈፍቱ እሥረኛ ታይቷል። " ወንጀላችሁ ተሻሽሎ፤ ፍርዳችሁ ይቀል ላችኋል " የተባሉ፤ በእሥረኛ ነጭ-ለባሽነት የተመለመሉ ደግሞ፤ ለስለላ ተግባራዊ ውጤት ያሳዩ ለመምሰል፤ ራሳቸው ያዘጋጃጁትን አስወንጃይ ጽሑፍም ሆነ ተንኰል፤ በሌላው የዋህ እሥረኛ ላይ በመለጠፍ፤ ሲያስደበድቡትና፤ እነማሚቶ፤ እነጅቦ በተባሉ ምሕረት የለሽ የእግር ብረቶችና እግረሙቆች ሲያስጠፍሩት ማየት፤ በጠቅላላ መፈጠርን ያስጠላል። ከነገ ዛሬ እገደል ይሆናል እያለ፤ ምግብ መብላት የተሣነው፤ ያ ሁሉ የሞት ፍርድ እሥረኛ ከክሳቱና ከጥቍረቱ የተነሳ፤ ሌላ ፍጡር መስሏል። በተለይም ቍጥር 17 በመባል የታወቀው ያበዱ እሥረኞች መኖርያ ክፍል ውስጥ፤ በየዕለቱ የሚፈፀ መውን አሳዛኝ ድርጊት መስማትም ሆነ ማየት፤ ሰው መሆን ከማስጠላት አልፎ፤ የዚያን እሥር ቤት " ዓለም- በቃኝነት " በርግጥ ያረጋግጣል። ..... በተለይም " የቀይ ሽብር ጊዜ " የተፈፀመውን ግፍ ሌላ ታሪክ ፀሐፊ ያወራዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ይቆይና፤ ያ ሁሉ ሠራዊተ እሥ ረኛ፤ በሥቃዩ አንፃር ምን ተስፋ ነበረው? ምኞቱስ ምን ለመ ሆን ነበር? በየቀኑ በሚፈፀምባቸው ግፍና በደል፤ ሥቃይና መከራ፤ መራራነት የተነሣ፤ እያንዳንዱ እሥረኛ፤ በሃገሪቱ ውስጥ የመንግሥት ለውጥ እንዲመጣ፤ ከፍተኛ ምኞቱ ነበር። ከቶውንም ከእሥር ቤቱ ኑሮ ምሬት የተነሳ፤ ከየትኛውም የኢ

ትዮጵያ ሕዝብ ክፍል በዚያ የነበረ እሥረኛ ሁሉ ስር ነቀል ለውጥ እንዲመጣለት ተስፋ ነበረው። ምኞቱና ተስፋው፤ ለውጡ ሲመጣ፤ ነፃ ለመውጣት አስቦ ሳይሆን፤ ባግባብ ለመታ ሠር ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበረው ነው። (ምፀት ባይሆን!)

ይህ ምኞቱ በየሰዓቱ ያጉላላው የነበረ አንድ የ 19 ዐመት ወጣት፤ በዚያን ጊዜ ወንጀለኛ ተብሎ ዐለም በቃኝ ውስጥ በመግቀቅ ላይ እንዳለና፤ የመጣውም ለውጥ፤ በእሥ ረኛው ላይ የባሰ ሥቃይና ግፍ ይበልጥ የጫነበት መሆኑን የሚገልጽ ምሥጢራዊ ደብዳቤ በዚያው ሰሞን በመገኘቱ፤ የዚህን ደብዳቤ ይዘት መነሻ በማድረግ፤ የጊዜውን የእሥር ቤት ሁኔታ ከሞላ ጐደል በጨረፍታ ይታተታል። ከዚያ ሐተታ በፊት ግን፤ ይህ የ 19 ዐመት ጉብል ወጣት፤ በዚያ ዕድ ሜው፤ እንዴት በዓለም በቃኝ ውስጥ እሥረኛ ሊሆን የቻለ በትን መነሾ ባጭሩ ማስረዳት ይገባል።

ይህ ወጣት፤ ሸንኰራና ምንጃር ተብሎ በሚጠራው ክፍለ ሀገር ተወልዶ ያደገ፤ ያንድ ብርቱ ገበሬ ልጅ ነው። አባቱ እንደጢሰኛ ገበሬ አደርነቱ፤ መሰል የሙያ ባልንጀሮቹን ካንድ ሁለቱ እየሰበሰበ፤ የባለርስቶችን መሬት ለገዛባለቤቱ ለአ ራሹ ገበሬ ለማድረግ፤ አድማ አስመትቶ፤ ከመንግሥትና ከርስት ባለቤቶች ቅጣትና ዛቻ ደርሶበታል። እንዲያውም ከነቤተሰቡ፤ በሳር ቤቱ ውስጥ እንዳለ በተንኰለኞች ሌሊት በተለኰሰ እሳት ተቃጥሎ በመንደድ የሞተው፤ እንደነገ ፍልሚያ ከባላባቶች ጋር ለማድረግ፤ መሰል ገበሬዎችን ባስተባበረበት ዕለት ነው። ይህ ወጣት ልጁ ግን፤ እንዳጋጣሚ ጨውና ላምባ ለመግዛት፤ ናዝሬት ካለው ገበያ ሔዶ አልተመለሰም ነበርና፤ ከቃጠሎው በሕይወቱ አምልጧል። ይሁን እንጅ፤ በተወለደበት አካባቢ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚረዳው ሌላ ሰው ባለማግኘቱ፤ ዘመዶቹ እንደማገዶ የነደዱ በትን መንደሩን ትቶ፤ የቀን ሥራ ወደ እሚለገኝበት ወደ ናዝ ሬት ከተማ ተሰዶ ሲኖር ሁለት ወራት ያህል ሆኖታል። ወን ጀል ሠርተሃል ተብሎ የተያዘው በዚሁ ከተማ ውስጥ ነው።

ራሱ በገዛ አንደበቱ ያስረዳ እንደነበረው ከሆነ፤ በናዝ ሬት ከተማ ይኖር የነበረው፤ በኩሊነት ሥራ ነው። እንዳጋጣሚ ሆኖ አንድ ሰሞን ለአራት ቀናት ያህል ሥራ አጥቶ ይቸገራል። ረሀብ ጊዜ አይሰጥምና፤ ምግብ የሚያገኝበት ሌላ ዘዴ ይፈል ጋል። አንዱ፤ ከመንገደኛም ላይ ሆነ በየቤቱ ተዟዝሮ መለመን ነበር።

" ጤነኛ ነህ! ወጣት ነህ! ሠርተህ አታድርም! " የሚል መልስ ሆነ በልመና ያገኘው ውጤት። ሌላ ነፍሱን ከረሀብ ለማዳን ያለው ምርጫ፤ መሥረቅ ሆኖ ይታየዋል። አልዘገየም፤ አንድ ቀን ማለዳ ላይ፤ በዚሁ ውሳኔው ፀንቶ፤ ማታ ማታ ከሚያድርበት፤ ከማርያም ቤተ ክርስቲያን እድሞ ጥጋት ሥር፤ ለስርቆት ተዘጋጅቶ ይወጣል።

ረፋድ ላይ፤ ከአንድ በሩ ገርበብ ካለ የቤት ደጃፍ ላይ፤ ሁለት አዳዲስ ብርድ ልብሶች በሽቦ ላይ ተሠቅለው ያያል። " ዛሬ የመጣው ይምጣ " ይልና፤ ቶሎ ደርሶ እጁ የያዘለትን አንዱን ብርድ ልብስ ይዞ ይሸመጥጣል። ለካስ ሁለት ትንንሽ ሕፃናት ከቤቱ ደጃፍ ላይ ቁጭ ብለው ይጫወቱ ኖሮ፤ ብርድ ልብሱን ይዞ ሲሄድ አይተውት ኖሯል። ሕፃናቱ ተጣድፈው ወደ ቤት በመግባት፤ የመንደሩ ሰው ሁሉ ተሰብስቦ የተፈ ላውን ቡና በመከስከስ ላይ እንዳለ፤ " ብርድ ልብሱን ሌባ ወሰ ደው! " የሚል ሪፖርት እየጮሁ ያቀርባሉ።

መላው የቡና ተሳታፊ ተጣድፎ ወዲያው በመነሳት

ብርድ ልብሱን የወሰደውን ሰው ይከተላል። ያ መሥረቅ የመ
ጀመሪያ ጊዜው የሆነ ወጣት፣ ብርድ ልብሱን ይዞ ሠከም
ሠከም ሲል፣ ከበስተኋላው መዓት ሕዝብ ሲመጣበት ያይና
በጣም መሮጥ ይጀምራል። ሊይዘው የሚከተለውን ሰው ብዛት
እየተገላመጠ በማየትና በመፍራት፣ " ብርድልብሱን ስተው
ላቸው ይተዉኛል " በሚል ግምት፣ የሠረቀውን ብርድ ልብስ
ጥሎ በተራበ አንጀቱ ሩጫውን ይቀጥላል።

ትንሽ ሮጦ ዞር ብሎ ቢያይ፣ ብርድ ልብሳቸውን ቢያገ
ኙም፣ እሱን እንዳልተዉት ይረዳል። የኋላ ኋላም መሮጥ ስለ
ተሳነው ይወድቃል። ያ ሁሉ " ሌባ! ሌባ! " እያለ የተከተለው
ሕዝብ በሙሉ፣ መንገደኛውም ሳይቀር፣ የተቻለውን ያህል
ይቀጠቅጠዋል።

በመጨረሻም፣ ጐትተው ሙት ሬሣውን ለፖሊስ በመስ
ጠት፣ ፖሊስ ጣቢያ ተወስዶ፣ በሦስተኛው ቀን ወጣቱ ነፍስ
ሲዘራ፣ ለምርመራ ያቀርቡታል። ሌባ መባሉ ኃፍረት ያሳደ
ረበት በመሆኑ፣ ራሱ በፈጠረው ዘዴ፣ ለምርመራ በቀረበበት
ወቅት፣ የዕብደት በሽታ እንዳለበት ሰው ወፈፍቱ ዐይነት ሆኖ
ይቀርባል። መርማሪው ፖሊስ ሲጠይቀው ያልሆነ ነገር ይዘላ
ብዳል። አእምሮው የተነካ እውነተኛ ዕብድ መስሎ በመታየቱ፣
በዚያው በታሠረበት ጣቢያ ሁለት ሳምንት ያህል ቆይቶ፣ በመ
ጨረሻ ላይ መርማሪው ፖሊስ ለጣቢያው አዛዥ ያቀርበዋል።
የጣብያውም አዛዥ የምርመራውን ሪፖርት ከተመለከተ በኋላ፣
" ይሽማ አደገኛ ወጣት ነው። እብደቱ ሲብስበት ከመስረቅ
አልፎ ሰውም ሊገድል ይችላል! " በሚል ውሳኔ ላይ በመ
ድረስ፣ የእብዶች መናኸርያ ወደሆነው፣ አማኑኤል ሆስፒታል
ተወስዶ እንዲታከም አዲስ አበባ እንዲላክ ትዕዛዝ ይሰጣል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ውሳኔው አልዘገየም፣ በማግስቱ የፊጥኝ ታስሮ አማኑ
ኤል ይላካል። እዚያም እንደደረሰ፣ በሆስፒታሉ ሁለት የታ
ወቁ ዶክቶሮች መቅድማዊ ምርመራ ይደረግለታል። ወጣቱም፣
ዶክተሮቹ ላቀረቡለት ጥያቄዎች ጤነኛ መልስ ከሰጠ በኋላ፣
የገጠመውን ሁኔታ በዝርዝር ምንም ሳይደብቅ ይነግራቸዋል።
በረዳትና በሥራ ማጣት፣ የሚቀምሰው ባለማግኘቱ ለመስረቅ
እንደተገደደና ሰዎቹም ሌብነቱን እንዳያምኑበት በማሰብ፣ ልክ
እንደእብድ ሆኖ በመርማሪ ፖሊሶች ዘንድ አውቆ ማድረጉንና፣
በተረፈ ንፁሕና ጤነኛ መሆኑን ጭምር ያስረዳል። ዶክተሮቹ
ግን የወጣቱን ሐቀኛ መግለጫ በመጠራጠር " ይሽማ አደገኛ
እብደት ነው። ሲነሣበት ሕይወት እስከ ማጥፋት አይመለስም፣
ሲበርድለት ደግሞ ሙሉ ጤነኛ ሰው ይመስላል። ከዚህ ቀደ
ምም፣ይህን መሳይ በሽተኛ ብዙ ጊዜ አጋጥሞናል። ጤነኛ ነው
ብለን ብንለቀው፣ በመስረቅ ወንጀሉ መከሠሱ አይቀርምና፣ ኋላ
በሚያመጣው ጠንቅ እኛን ሊያስወቅሰንና ኃላፊነት ውስጥ ሊያ
ስገባን ይችላል። የአእምሮ ሕመም እንዳለበት ብንመሰክር
ደግሞ፣ ፍርድ ቤት አይቀርብምና፣ ለጊዜው ሁኔታው በሰፊው
እስኪጠና፣ ዓለም በቃኝ ቍጥር 17 ይቈይ " ብለው ይወ
ስናሉ።


በዚህም ውሳኔ መሠረት፣ ዓለም በቃኝ ተወስዶ፣ በተመ
ሳሳይ ሁኔታ ከሚኖሩ እብዶች ጋር በክፍል ቍጥር 17 ውስጥ
ሲኖር፣በዚያን ጊዜ ብቻ ሦስት ያህል ዓመታት አድርጐ ነበር።
ይህ ወጣት፣ አንደኛ የት ደረሰ ብሎ የሚከባከበው አንድም
ዘመድና አዝማድ የሌለው በመሆኑ፣ ሁለተኛ በፈፀመው ወን
ጀል እንኳ ቢከሠስ፣ ከዓመት ጊዜ ያልበለጠ የእሥራት ቅጣት
እንደሚበቃው ሲታወቅ፣ ወንጀለኛነቱን የትኛውም ፍርድ ቤት

ስለማያውቅና የፋይል መዝገብም የሌለው በመሆኑ፤ እነዚያ የአማኑኤል ሆስፒታል ዶክቶሮችም፤ “ ልዝብተኛ እብድ ” ብለው፤ ያለፋይል ወደ ዓለም በቃኝ ከላኩት በኋላ ስለለ ረሱት፤ አራተኛ ስለግለ-ሰቦች ሕይወት ጥንቃቄ የሚከታተል ድርጅት በሃገራችን ባለመኖሩና በመሰል ምክንያቶች፤ ያን መሳይ ሎጋ ወጣት፤ በዚያ አሠቃቂ እሥር ቤት ውስጥ፤ ከሐ ቀኛ እብዶች ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ታፍኖ ሲኖር፤ ብዙ ዓመታት አልፈዋል።

ድሮ የዛሬ አሥራ አምስት ዓመት፤በዓለም በቃኝ ውስጥ ያውቀው ለነበረ አንድ የእሥር ጓደኛው፤ ሰሞኑን እድል አጋ ጥሞት፤ በቀይ መስቀል ረዳትነት የሚከተለውን ደብዳቤ ይጽ ፋል። በተለይም ያ የድሮ እሥር ቤት ሁኔታ፤ዛሬ ምን መልክ እንዳለው በሰፊውና በዝርዝር የሚገልጽ በመሆኑ፤ “ ለውጥ አመጣሁ እያለ የሚፎክረውንና የሚደነፋውን የጊዜያዊ አምባ ገነን የፋሽስቶች መንግሥት፤ በሚገባ ሠቅሰቆ የሚያጋልጥ በመ ሆኑ፤ ደብዳቤው እንዳለ ከነሙሉ ይዘቱ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሚያዝያ (ፋሲካ) 1980
ዓለም በቃኝ
ክፍል፤ 17
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

እንደ እንጀራ የምትርበኝ፤
እንደውሃም የምትጠማኝ፤
ምንጊዜም የምትታሰበኝ፤
የዓለም በቃኝ የእስር ጓደ.....
ጓዴ ሆይ፤ ሰላምታየ ይድረስህ ብዬ እንዳልጽፍ፤



ማኾሪያ፡ በር

ዓለም _ በቃኝ

ጀሐነብ (ዩጎ) እንዳለ፤ ግዉት ለሚረልግ፤
ዓለም-በቃኝ ቢሔድ፤ ያጥናዋል በወግ።
የሥቃያት ዐይነት፤ ይረዳል በዝርዝር፤
ብዙ ዘመን ሳይፈጅ፤ በአንዲት ቀን አዳር።
ባስቲል ይሉ ባርካ፤ ሜሪ አብዮቶች፤
አደወዳደሩም፤ ካለም-በቃኝ ገጾች!!
ለቃጥሎ የሚጠብስ፤ የሠቆቃው ዓይነት፤
በዚያ ባለም-በቃኝ፤ መኖሩን ሲያይበት፤
ጀሐነብ መሆኑን፤ ያውቀዋል በትፅበት!

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰላም የለኝም። ሰላምን የት አውቃትና። ደኅና ነኝ እንዳል ልህም፤ ደኅና አይደለሁም። ደኅንነትን የት አውቄው?..... ትመስገን እንዳልልህ፤ ምን ስላደረገችልኝ። አሥራስምንት ዐመታት ሙሉ፤ ረሃቤ በፈጠረው ወንጀሌ በመማቀቄና፤ በዚያ የሳት ቃጠሎ ቤተሰቦቼ ስለነደዱ፤ ሕይወት የሚሉት ነገር ትዝ ታው ጭምር ጠፍቶብኛል። ይህን ደብዳቤ የጻፍኩልህ፤ መድ ረቅ ላይ የተቃረበውን እምባዬን፤ ከዚያች ከምታውቃት ድቡል ቡል ቂጣ ጋር ተሳስቶ የመጣ ከሰል አግኝቼ፤ ከፈጨሁት በኋላ፤ ባቀለምኩት የእምባ ቀለም ነው። ብዕርማ አይፈቀድም። ጓዴ፤ ሰው ሆኖ መፈጠር ትልቅ ዕዳ እንደሆነ፤ የኔ ታሪክ ምስክር ነው። እድል ገጥሞህ፤ እንደገና ልታየኝ ብትችል፤ በጭራስ አትለየኝም። ለትንግርት የምታይ ልዩና ቅይር ፍጡር ወጥቶ ኛል። " Forgetful of the world by whom they are forgotten " እንዳለው ጂቦን፤ የረሳኝን ዓለም እኔም ረስቼዋለሁ።

ከሌላው አንጻር ባይገርምህ፤ እሳት የላሰው ተማሪ ወጥ ቶኛል። ከምሁራን ጓድ እሥረኞች እየተጠጋሁ፤ ያጠናሁት እውቀት፤ ነፃ ወጥቼ አልሠራሁበትም እንጅ፤ ብለቀቅ ኖሮ፤ ለሀገሬ፤ ፀሐይ ዘንድ የሚደርስ ሮኬት ሳይሆን ሲፐር ሮኬት እፈጥርላት ነበር። ቋንቋውንማ ተወው፤ ሊቅ ሆኜልሃለሁ። ከሀገራችን የብሔረሰብ ቋንቆች አንስቶ በዓለም እስከታወቁት እነ እንግሊዝኛን፤ ፈረንሳይኛን፤ ጣልያንኛን በሚገባ በሙሉ አን ደበቴ ልናገርባቸው ችያለሁ። ግን ምን ያደርጋል? ምንስ ፋይዳ አለው? ስለ ሕይወትም ሆነ ስለ ሰው ህላዌ ያለኝ አስተ ሳሰብ በደረሰብኝ ስቃይ ተሞርዶ ተሞርዶ አልቋል። እንደገና ሰው መሆኔ ያጠራጥራል።

ጓዴ ሆይ፤ እንዲህ ያለውን ልተውና፤ ባጠገቤ ያለ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውን " ገብስ ገብሱን " ላውራህ። ያኔ ያ ሁሉ እሥረኛ ሲመ ኘውና ሲያልመው የኖረው፤ የመንግሥት " ለውጥ " እንደ ምኞቱ መጣ። " ለውጡ " መጣ እንጅ ምኞቱና ተስፋው አሁንም በአዲስ መልክ እንዳለ ነው። የመጣው "ለውጥ" ሳይ ሆን " ነውጥ " ነው። ተሳስተው አሳሳቱ እንጅ፤ ቤሣ ሣን ቲም የተሻሻለ ነገር የለም። ስለውጭው ከተማና ገጠር፤ በወሬ ጠግቤዋለሁ። እልፍ አእላፋት እሥረኞች በእሥር ቤታችን ተሞጅረው ታጭቀው፤ ስለሁሉም አስረድተውኛል። በወሬ የሰ ማሁትን አላወራህም። ላንተ ፍላጎት ያህል፤ የዚሁ የግቢያችን መግለጫ ይበቃሃል።

ያ፤ ድሮ የምታውቀው ዓለም በቃኝ፤ እስካፍ ጢሙ በእሥረኞች ጢም ብሎ በመሞላቱ፤ መንቀሳቀሻ እንኳ አጥተ ናል። አብዛኛውም እሥረኞች ምሁራን ናቸው። ከሞት ተር ፈው የታሠሩትንማ፤ ጭቁኖችና የጭቁን መደብ ወገኖች፤ ልቆ ጥርልህ አልችልም። ምን አለፋህ ድሮ፤ ስድስት በዝቶባታል ብለን የምናማርርባት ያቺ ያለም በቃኝ ክፍል፤ ዛሬ ከእጥፍ በላይ ታምቆባት፤ ከአስራ አምስት እሥረኞች በላይ ያጉሩ ባታል። ሠርዲን አይቶ ማየት ነው። ሌላው ቀርቶ፤ ላበዱ እሥረኞች ብቻ ተመድባ የነበረችው ቀጭጥር 17 የኛ ክፍል፤ ዛሬ በጤነኞች እሥረኞች ሣይቀር፤ ጢቅ ብላለች።

ከእሥረኛው ሠራዊት ብዛት የተነሳ፤ ድሮ የቀጠሮኛ፤ የፍርደኛ፤ የእድሜ ልክ እሥራት፤ የሞት ፍርደኛ፤ እየተባለ እንደ እሥራት ዘመኑና እንደ ወንጀሉ፤ እየከፋፈሉ መድቦ ማስቀመጡ ቀርቶ፤ የመጣውን እሥረኛ ሁሉ፤ ካገኙበት ቦታ ዝም ብሎ መሞጀር ሆኗል። ከእሥረኛው ብዛት የተነሣ፤ ያቺ ድሮ በቀን ሁለቴ እናገኛት የነበረችዋ አሎሎ መሣይ ቂጣ

እንኳ፤ ዛሬ በሚምንት አራት ጊዜ ብቻ ስትመጣ፤ እንደብርቅ እናያታለን። ያ እሑድ እሑድ ይሰጠን የነበረው የሾመጠጠ እንጀራና፤ ያቺ ላሲስ ሲጋቸው፤ መቅረት የጀመሩት፤ ገና አብ ዮት ተጀመረ ተብሎ፤ ወታደሩ ሥልጣን መያዝና ሀብት ማስከ በር በወጠነበት ጊዜ ነው።

" ቡና" እየተባለ ጠዋት ጠዋት ይሰጠን የነበረውም ያረረ የገብስ ቅቅል ጭማቂ፤ ከቀረ ብዙ ጊዜ ስለሆነው፤ ጭራስ ከነመኖሩም ረስተነዋል። እሱስ እንኳን የቀረልን። ያኔ አንተ እንኳ በነበርክበት ዘመን፤ ያን ሁሉ እሥረኛ ጥላሸት አለመ ስሎት እንደነበረ አትዘነጋም። ምን አለፋህ፤ በዚያ ግቢአችን ያልቀሩትና፤ በይበልጥም ተባዝተው ያሉት፤ " እነማሚቶና እነጅቦ " (እግረ-ሙቆች) ናቸው። ሁኔታው አላስችል ያለውና መታገስ ያቃተው ታጋይ እሥረኛ፤ በረበሸና በተሳደበ ቍጥር፤ እንደአሸን ከቦን ያለ ወታደር፤ ወዲያው እግሮቹንና እጆቹን እየጠፈረ ሲቀጠቅጠው ይውላል። አንተ ያኔ ያላየኸው፤ አራት አምስቱን እሥረኞች አንድ ላይ ጨብጠ የሚያቆራኝ ግንድ ግንድ የሚያህል ሠንሠለትም፤ ዛሬ ዓለም በቃኝ ውስጥ ሥራ ላይ ውሏል። በነዚህ ሠንሠለቶች የታሠሩ ሁሉ ለመን ቀሳቀስ ምንም ዕድል ስለሌላቸው፤ መብላትም ሆነ መሽናት በጭራሽ አይችሉም። ደግነቱ ይህ ዓይነቱ ቅጣት፤ ለተወሰኑ ቀኖች ብቻ መሆኑ በጀ እንጅ፤ ጊዜው ረዥም ቢሆን ኖሮማ፤ ብዙ ሬሣዎችን በየቀኑ ማየት ይቻል ነበር። ሌላው፤ እሥረኛ በየጥቃቅኑ ምክንያት አጥፍተሃል እየተባለ በጉማሬ መገረፉ ተራ ነገር ሆኗል። በጊቢያችን ውስጥ፤ ከዚያ ሁሉ እሥረኛ፤ ጠባሳ የሌለበት ቢገኝ፤ ቍጥሩ እጅግ በጣም ጥቂት ነው።

" አንዳንድ የኢንተርናሲዮናል ድርጅቶች፤ የኢትዮጵያን

t.me/OLDBOOKSPDF

እሥር ቤቶች ጐበኙ " የሚል ፈጠራ ወሬ ስትሰማ፤ " እሥር ቤቶች ከድሮ ይዞታቸው ተሻሽለዋል " ብለህ ታስብ ይሆናል። ደረቅ ፕሮፓጋንዳ ነው። ሀገራችን ከምትሰጠው ጥቅም ለመ ሻማት አሰፍስፈው ከሚገኙት የሩሲያ፤ የኩባና የምሥራቅ አው ሮፓ የስም ሶሻሊስት ሀገሮች፤ የተውጣጡና እንዲሁም አንዳ ንድ በገንዘብ የተገዙ የአውሮፓና ያሜሪካ ኤጀንቶች፤ ሁለት ጊዜ ያህል ጐብኝተውን ነበር። እነሱ በመጡባቸው ሁለት ቀናት፤ አቤት የበላነው ምግብ፤ የጠጣነው መጠጥ፤ ሌላ ነበር! የፍትፍቱ ሽታ ለስምንት ቀን ያህል፤ መላውን የወህኒ ቤት ክልል ያውድ ነበር።

መጠጡማ ተወኝ ! ካልኮል በስተቀር ያልቀረበልን ለስ ላሳ የመጠጥ ዘር አልነበረም። ጐብኝዎቻችን ከጊቢያችን ሲወጡ፤ ወዲያው እያወለቅን አስረከብን እንጅ፤ ለወቅቱ ተሰጥቶን ለብሰነው የነበረ ጨርቅ፤ ግቢውን ሳይቀር አድምቆት ነበር። ቀለሙ ቀይ የሆነ እጀጉርድ እጀጠባብና፤ ግማሽ ባት ላይ የምትደርስ ሱሪ ተሰጥቶን፤ ለጥቂት ሰዓታትም ቢሆን ሽር ብለን ዋልን። ጐብኝዎቹ ሲመጡ፤ ምንም ዓይነት ጥያቄ እንዳ ናቀርብና በጭራሽም እንዳንነጋገር ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶን ስለነበረ፤ ከጥቂት ቄራጥና ደፋር እሥረኞች በስተቀር፤ በዚያ ቀን የተናገረ እሥረኛ አልነበረም። እነዚያ የተናገሩ ጥቂት እሥረኞችም ቢሆኑ፤ በዚያው እለት ምሽት ለቅጣት ተወስደው እስከ ዛሬ የት እንደደረሱ የሚያውቅ የለም።

በዚያ እለት ብቻ እንዲያ ለብሰን፤ እንዲያ በልተን፤ እንዲያ ጠጥተን ያዩ፤ የኢንተርናሲዮናል ታዛቢዎች፤ ምናል ባት " አዲስ አበባ ያለው ትልቁ እሥር ቤት መንግሥተ ሰማ ያት ነው " ባይሉም፤ ከምድራዊ " ገነት " ጋር አወዳድረው፤

ለዓለም ህዝብ መግለጫ ሰጥተው ይሆናል። ይህም አባባል፣ የነሱ ብዕርና አንደበት የተፋው ምናምንቴ መግለጫ ይሆናል እንጅ፣ የኛ የእሥረኞቹ ሁኔታና የእሥር ቤቱም ተጨባጭ እውነታ ሌላ ነው።

የሚገርምህ፣ ያን ዕለት እንግዶቹ ጐብኝዎች ሊያዩን ሲመጡ፣ አዲሱን ለዚያ ዕለት ብቻ የተዘጋጀውን ልብስ ልበሱ ሲባል፣ አሻፈረኝ ያሉ እሥረኞች በሙሉ ቍጥር 17 ክፍል ውስጥ አግረው፣ ያበዱ ወንጀለኞች ናቸው በማለት፣ ለጐብኝ ዎቹ ካሳዩ በኋላ፣ እነዚያን እሥረኞች ከዚያ ቀን ጀምሮ በልዩ እግረ-ሙቅ ገብተው እስከ ዛሬ ድረስ ሳይፈቱ በመማቀቅ ላይ ይገኛሉ። አንዳንድ አሳዛኝ ሁኔታ ልጥቀስልህ ብዬ ነው እንጅ፣ የሚፈፀምብን ግፍ ይህ ነው አይባልም።

በጣም የሚገርመው ግን፣ ድሮ ባለፈው መንግሥት ጊዜ ለይስሙላም ቢሆን፣ አብዛኛው እሥረኛ ወደ እሥር ቤት የሚላከው፣ ፍርድ ቤት ቀርቦ፣ ዳኞች አይተውት ነበር። ዛሬ ግን፣ በዚህ ጊቢ ከሚገኘው እሥረኛ 90ው እጅ ፍርድ ቤት ከሚባለው፣ ከደጁም ያልደረሰ ነው። አብዛኛውም እሥረኛ በምን ወንጀል እንደተከሠሰም አያውቅም። ብቻ ሰብስበው አምጥተው ይሞጅሩታል። ፍርድ የለ! ቀጠሮ የለ! በዚህ በኛ ዓለም በቃኝ ጊቢ ውስጥ ያሉትን አብዛኛዎቹን እስረኞች አነጋግሬአለሁ። የወጣቱ አጠቃላይ ወንጀል " ፀረ ሕዝብ " ና " አና ርሺነት " የሚል ሲሆን፣ ጠና ጠና ያሉት እሥረኞች ደግሞ " አድኃሪነት " እንደሆነ ነግረውኛል። ባይገርምህ አብዛኛው፣ ወጣትና ገና በአፍላ ዘመኑ የሚገኝ ነው። ጠጋ ብለህ ስታነጋ ግረው፣ መንግሥት ይሠረው እንጅ፣ ስለ ሀገሩ ፍቅርና ስለ ጭቁኑ ሕዝብ አርነት ያለው ስሜት አሁንም እጅግ የጋለና

t.me/OLDBOOKSPDF

ትኩስ ነው። የታሠረበት ምክንያት በዓይነቱ ይለያይ እንጅ፣ የሁሉም እሥረኛ መነሻ ምክንያት የጊዜያዊውን አምባገነን የፋሽስት መንግሥት ጥላቻ፣ የሀገሩ ብሔራዊ ክብር በባዕዳን ሠርጐ ገብ ወራሪዎች መደፈር፣ ለሕዝቡ የመጣለት ዐብዮት መኰላሸት..... ያበሳጨው መሆኑን ያለመጠራጠር ትረዳለህ።

ይሁን እንጅ፣ ያን ሁሉ ታጋይ ጓድ ሲያስሩ፣ የተለያየ ስምና ወንጀል በመስጠት ነው።

" ፀጉርህን ለምን አጐፈርክ?
የቀበሌ ሹም ለምን ሰደብክ?
ጌቶች ሊቀ መንበር በመኪና ሲያልፉ ለምን ገላመጥክ?
ያልሆነ ቃል ለምን ተናገርህ?
በጥናት ጉባዔ ላይ ለምን አልተገኘህም?
"የኢትዮጵያ ትቅደም" ፍልስፍናን ለምን አንጓጠጥህ?
ራሻኖችን ለምን ሪቪዢኒስት አልህ?
የማኦን መጣፍ ለምን ይዘህ ተገኘህ?
የጴንጤዎች አባል ለምን ሆንህ?
የድሮ ነገሥታት ፎቶ ለምን ከቤትህ አስቀመጥህ?
ከድሮ ጢሰኛህ ጋር ለምን ተናገርህ?
ይታጠን ለምን ደገፍክ?
አምስት ኪሎ ቡና ለምን ደብቀህ ተገኘህ?
ውጭ አገር ለሚኖር ዘመድህ ለምን ደብዳቤ ጻፍህ?
የድል በዓል ላይ ለምን አልተገኘህም?
አለፈቃድ ለምን ከሥራህ ላይ ጠፋህ?
ሰዓት እላፊ ለምን ጠጣህ?"?.....እነዚህን የመሳሰሉ ልዩ ልዩ ምክንያቶች ይገኙበታል። በውነቱ እያንዳንዱ ዝርዝር ወንጀል ቀርቶ፣ ጠቅላላው

ወንጀል ባንደት ተጨምቆ እንኳ የሚገኘው የወንጀል ጠብታ አምስትና ስድስት ዐመታት ማሣሠር ቀርቶ፤ አንድ ነጠላ ዓመት እንኳ ማሣሠር አይችልም ነበር። አንድ ሌላ ትንግርታዊ ዜና ላጫውትህ። በጊቢያችን የመጨረሻው ወጣት እሥረኛ አሥራ አምስት ዓመት የሆነው ተማሪ ነው። ፈፅመሐል የተባለው ወንጀል ያስቅሃል።

ሰምተህ ይሆናል፤ ደርግ የሚሉት ምናምንቴ ገና የተቋቋመ ሰሞን፤ ይሆኝኝ ብሎ ያዘጋጀው አንድ የኢትዮጵያ ካርታ አለ። በዚያ ካርታ ላይ እስከ ዛሬ ፍቺው ምን እንደሆነ በግልጽ ያልታወቀ አንድ ዐይን መኻሉ ላይ ተሥሎበታል። ምናልባት፤ አንድ ብር ኖት ላይ በሥውር እንደተጻፈው ያለ ዐይነት አንድ ታንኪረኛ ሰው ያዘጋጀው ሥዕል ይሆናል። ይህ ወጣት እሥረኛ፤ ያን ባለ አንድ ዐይን ካርታ ለመጀመርያ ጊዜ ሲያይ፤ በቅንነትም ይሆናል ወይም በብልህነት፤ " ምነው የናት ኢትዮጵያን አንድ ዐይን ደርግ አጠፋው! ዐይንሁሉ ሁለት አልነበረም እንዴ? " ብሎ በመገረም ይናገራል። ማታ ብዙ ሰዎች ባሉበት፤ ቴሌቪዣርን ሲያይ እንደ ልጅነቱ የመጣለትን የተናገረው ነበር። ግን ከቴሌቪዣርን ተመልካቾቹ ውስጥ ሦስቱ ወታደሮች ስለነበሩ፤ ሪፖርት አርገውበት፤ በማግ ሥ ቱ፤ ይኸው ንግግሩ ብቻ አስወንጅሎት ዓለም በቃኝ ከገባ ሦስት ዐመቱን ይዟል። የዚህን ወጣት ወንጀለኛነት፤ ፍርድ ቤትም ሆነ ፖሊስ ጣቢያ ስለማያውቀው፤ ፋይልም ሆነ ቀጠሮ የለውም። አሁን፤ በዚያ አሠቃቂ ቦታ ላይ በለጋነቱ ዘመን በመግባቱ አልፎ አልፎ ወፈፍ ያደርገዋል። ከየት እንደሰማው አላውቅም እንጅ፤ ራሱን ነካ ያደረገውዕለት፤ እንደሚከተለው እየጮኸ ይዘምራል።

t.me/OLDBOOKSPDF

" ናፖሊ ናፖሊ ያሠለጠናቸው፤
ኰፍያው ገዳዳ ጫማው ምሥማር የለው፤
እነመቶ አለቃ፤ እነሻምበል ናቸው፤
ታምቡር እየመቱ ይሔዳሉ እኛው!"

አጠቃላይ መግለጫ ከየዓይነቱ እየጠቃቀስኩ የምፅፍልህ፤ ዝርዝሩን በማተት እንዳላስለችህ ብዬ ነው። ድሮ እያንዳንዱ ዓለም በቃኝ ክፍል ውስጥ መፀዳጃ እንዲሆን አንዳንድ ገረወይና ይቀመጥ ነበር። ለዚያች ሽንት ቤት ተራ ባልደረሰን ጊዜ፤ ይህን ገረወይና እንጠቀምበት እንደነበር ትዝ ይልሃል። ዛሬ እነዚያ ገረወይናዎች በሙሉ ተወስደዋል።ያለው ምርጫ፤ የክፍሉን አንድ ጥጋት ለገረወይናው አገልግሎት ምትክ አርጐ መጠቀም ስለሆነ፤ ምን አለፋህ እያንዳንዱ እሥረኛ በወር ውስጥ ለተወሰኑ ሣምንታት በጉንፋን መታመም አለበት። ድሮ እንደነገሩም ቢሆን ዶክቶርና ሐኪም ቤት ነበር። ሰምተህ ይሆናል የሰባት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ወጣት ልዕልታትና ልዑላን ሳይቀሩ፤ ከሰው ያልተፈጠሩ ይመስል፤ ከሕዝቡ ጋር እንደ ሕዝቡ እንዳይታሠሩ፤ በተለይ ለይተው በሆስፒታሉ ውስጥ አስረዋቸዋል። ገና ለገና የነገሥታት ዝርያ አላቸው ብሎ፤ ገና ጡት ያልጠገቡ ሕፃናትን ሕዝባዊነት ባሕርይ እንዲሠር ፅባቸው ከሕዝቡ ጋር ደባልቆ በማስተማር ፋንታ፤ በሆስፒታሉ ውስጥ ከርችሞ በማኖሩ፤ መሪዎቻችን ምን ዐይነት የሞራል ዝንባሌ እንዳላቸው የሚያሳይ ያምባገነንነት ፋሽስታዊ ጠባይ ማንፀባረቂያ መስተዋቶች ሆነዋል። ታዲያ ከእንደዚህ ዐይነቱ መንግሥት ምን ዐይነት ተስፋ ትጠብቃለህ? መታከሚያ ሆስፒታልና ሐኪም ባለመኖሩ፤ የሚሞተውም ሆነ የሚታመመው የእሥረኛ ቍጥር ተመጣጣኝ ነው። ባስፈለጋቸውም ጊዜ

የተወሰኑ እስረኞች እየመረጡ ወስደው በመረሸን በጥይት ያነዷቸዋል። የዚያንው ያህል እስረኛ ከሚመጣበት አይታወቅም፤ በማግሥቱ ሞልቶ ጢም ይላል። ከእሥረኛው ብዛት የተነሳ፤ የሚያሰፍሩበት ቤት ቢያጡ፤ ድሮ የሙያ ተግባር መሥሪያ ቤት የነበረውን አዳራሽ ሳይቀር፤ ሞቶሮቹን በሙሉ አውጥተው፤ የእሥረኛ ማጐሪያጉረ አድርገውታል። ምን የሙያ ቤቱን ብቻ፤ ቤተ መስጊዱ፤ ቤተ ክርስትያኑና መጻሕፍት ቤቱ ሳይቀሩ በሙሉ፤ ለእሥረኞች ማፈጊያነት ተሰው ጠዋል። ጉዕኛው ካቦ ፤ ካድሬ በሚል አዲስ ስያሜ፤ ሲያረጠርጥ ብታይ ልዩ ድራማ ነው!

እሑድ በመጣ ቁጥር፤ የዚያ ሁሉ እሥረኛ ቤተሰብ ይመጣ ይመጣና፤ የእሥር ቤቱን ማርገጃ መተናፈሻ ሲያሳጣው፤ መላው የአዲስ አበባ ሕዝብ ተነቅሎ የመጣ ይመስላል። እንደድሮው ገብቶ እሥረኛን መጠየቅ አይፈቀድም። ከስንቅ አቀባዩ ብዛት የተነሣ፤ ስንቁ ሳይቀር እየተሳከረ፤ ያንዱ ስንቅ ለሌላው ሲደርስ፤ ስንቅ ያልተላከለት እሥረኛም በፎርፌ ያንዱ ስንቅ ያንተ ነው ተብሎ የሚሰጥበት ጊዜ ይበዛል። ያ ሁሉ ጠያቂ ሕዝብ በየእሑዱ እየመጣ በወህኒ ቤቱ ደጃፍ ላይ ሲተምና ሲርመሰመስ፤ እኛ ከውስጥ ሆነን ድምፁንና ሁካታውን ስንሰማ፤ የጥ ም ቀት በዓል፤ ወይም ምፅአት የመጣ ይመስለናል። በጣም የሚገርምህ ደግሞ፤ እሥረኛ ዘመዳቸው በሕይወት አለመኖሩን ሳያውቁ፤ በየሣምንቱ እሑድ እሑድ፤ ለሌላ ባይተዋር ወገናቸው ስንቅ የሚያቀብሉ መኖራቸው ነው። ይኸ እንኳ አይከፋም!

ድሮ የወህኒ ቤቱ ዙሪያ የታጠረው በተራ ሽቦ እንደነበር ታስታውሳለህ። ዛሬ ዙሪያው በስሚንቶ እድሞ ታሽጓል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ድሮ አልፎ አልፎ ታያቸው የነበሩ ማማዎች፤ ዛሬ ቍጥራቸው በርክቶ፤ በሮንድነት የሚጠብቁትም ወታደሮች ሦስትና አራት ሆኗል። ስለማይተማመኑ ይመስላል፤ በአንድ ማማ ላይ ሦስት ወታደሮች ካሉ፤ ሦስቱም ከተለላየ ሥፍራ የሚመጡና በተለይም፤ አንዱ ኢትዮጵያዊ ሌላው ኩባዊ፤ የቀረው ደግሞ ምሥራቅ ጀርመናዊ መሆን አለበት። ድሮ የእሥር ቤት ፖሊሶች በመጠበቂያነት ይጠቀሙባቸው የነበሩ መሣሪያዎች፤ እንደ ናስ ናስርና አልቤን የነበሩ ጠብመንጃዎች በሙሉ፤ በአዳዲስና ኡዙ ልዩ ልዩ መሣሪያዎች ተተክተዋል። በአዲስ አበባ የሚገኝ ታንክና መትረየስ ሳይቀር፤ በወህኒ ቤቱ ዙርያ ተደግኖ ይውላል፤ ተደግኖ ያድራል። በዚያንው ልክ፤ እነዚያ የምታውቃቸው ባውዛዎች በሙሉ ተለውጠው፤ በላምባ መሥራቱ ቀርቶ፤ በኤሌትሪክ ከፍተኛ ዋት የሚንቀሳቀሱ፤ ከመቶ ያላነሱ ባውዛዎች በየአቅጣጫው ተተክለው፤ ምሽት በመጣ ቍጥር ባበሯቸው ጊዜ፤ መላውን የወህኒ ቤት ጊቢ፤ የቀኗን ፀሐይ ያህል ወለል አርድጐ በማሳየት፤ ጤፍ ሳይቀር ያስለቅማል።

የእሥር ቤቱ ጠቅላላ የአስተዳደርም ሆነ የኃላፊነት ሥልጣን የተሰጠው፤ የህገሪቱን ጠቅላላ የፀጥታ ቍጥጥር የያዘው፤ የምሥራቅ ጀርመን መንግሥት ቢሆንም፤ የሩሲያና የሌላ መንግሥታትም በአማካሪነት አሉበት። የድሮው የወፍጮ ቤት ትልቅ ሕንፃ ታድሶ፤ ተጨማሪ ያስተዳደር መምሪያ ቢሮ ሆኗል። በነጭ ለባሽነት ያሠሩት የወታደር ቍጥር አይነገርም። የሚገርምህ፤ ወንጀል ሠርተዋል ተብለው፤ ለዚሁ ለስለላ ተግባር የተሠማሩ ፤ባእዳን ጭምር በእሥረኛነት ስም መገኘታቸው ነው።

ድሮ ጅምር የነበረው የጥቁር ገበያ ኮራፕሽን፤ ዛሬ

ከምንጊዜም ይልቅ ጦፎልሃል። ብዙ ብር ጉቦ መስጠት የቻለ፤ በደርግ አባል አማላጅነት፤ ከታሠረበት በቅፅበት መፈታት ይች ላል። እነዚያ የድሮዎቹ ስኩፒኛዎች በሙሉ ጠፍተው፤ ዛሬ፤ በእስኩፒያነት ለሚገኘው ጥቅም ሲል፤ ወታደሩ ራሱ ስኩፒኛ ሆኗል። ገንዘብ እስካለ ድረስ፤ ወታደሮችን በመደለል፤ እሥረኞቹን ሴቶች ለእሥረኞቹ ወንዶች ለተወሰነ ሰዓት ቆይታ ማቃጠር ይቻላል።


በሥልጣን ላይ ያሉ አዲሶቹ የወታደር መሣፍንት፤ በጣም የሚፈሩትና ያሠጋቸው ቦታ ቢኖር፤ የመጀመሪያው ሥፍራ ወህኒ ቤቱ ነው። አብዛኛው ከሞት ያመለጠው ምሁራንና ሊቃውንት፤ ተራማጅ አስተሳሰብ ያለው ወታደሩ ዲሞክራቱ፤ ተማሪው፤ የብሔረ-ሰቡ ታጋይ፤ ታፍኖ የታጐረው በዚሁ ታላቅ ወህኒ ቤት ውስጥ ስለሆነ፤ መንግሥት ያለ የሌለ ኃይሉን በጥበቃ ላይ ያዋለው በዚሁ ሥፍራ ላይ ነው።

አንዳች ነገር አጋጥሞ፤ ከተማው ውስጥ አንድ ድምታ የተሰማ እንደሆነ፤ የጊዜው ባለሥልጣኖች በሙሉ፤ ለወህኒ ቤቱ ከያለበት አቅጣጫ ስልካቸውን ያቅጨለጭላሉ። ወደዱም ጠሉ ግን፤ አንድ ቀን ያ የታፈነ ኃይሉ መፈንዳቱ አይቀርም። እንዲውም አሁን የሚገኝበት ደረጃ ቋፍ ላይ ነው። ያኔ ታስታውስ እንደሆነ፤ በ1953 መንግሥት ለመገልበጥ ሞክረው የነበሩት የነገርማሜ ጭፍሮች በሥር ቤቱ ሲማቅቁ ኖረው፤ ይህ ያሁኑ መንግሥት፤ ለፕሮፓጋንዳውና ለሥልጣን ላይ መወጣጫ እንዲሆነው በዘየደው መላ፤ እሥር ቤቱ ውስጥ ባላቸው ኤክስፔርያንስ ሜራ መተው እንዳያሣምፁ በማሰብ፤ “የፖለቲካ እሥረኞች ሁሉ በነፃ ተለቀዋል” በሚል አዋጅ በየቦታው በታትኖ ነበር። ዛሬ ከነሱ ወስጥ ለዘር ያህል የተረፈ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቢገኝ ያ እበላ ባዩ ሻለቃ ብቻ ነው። እሱንም ቢሆን እስኪ ጠቀሙበት ድረስ እንጅ፤ ኋላ የራሺያ ጥይት ራት ማድረጋቸው አይቀርም። በዚያን ጊዜ ታስረው የነበሩትን እነታደሰ ብሩን፤ እነመኮንን ወሰኑን ታስታውስ የለም? ዛሬ የት ናቸው? ነፃ ተለቃችኋል ባላቸው ባመቱ አይደለም ያስረሸናቸው!! እንግዲህ እኔ፤ በእንደዚህ ዐይነቱ ሕይወቴ ውስጥ ይህንሁሉ አየሁ። ከኔ በዕድሜና በመራራ ኑሮ ይበልጥ የኖሩት ወገኖቼ ስንቱን ትንግርት አይተው ይሆን?

ለዚህ የመጀመሪያም የመጨረሻም ደብዳቤዬ፤ ማለቢያ የሚሆነኝን አንድ ቁም ነገር ያዘለ አረፍተ ሐሳብ ሳልሰጥህ፤ ልዘጋ አልፈልግም። “ፋሽስቶችም ሆኑ መላው አድኃሪ ኃይሎች፤ የሚፈልጉትን ያህል ለተወሰነ ጊዜ የተራማጆችን አካላዊ ሰውነታቸውን ብቻ ሊያሥሩ ይችሉ ይሆናል። ግን አላማቸውንና ትግላቸውን የሚያቀናጁበት ውስጣዊ ልባቸውን ማሠር አይሆንላቸውምና ትግል ይቀጥላል። አነሳሱ ያላማረኝ የፋሽስት መንግሥት፤ አወዳደቁን ለማየት ጓጉቻለሁና፤ የደብዳቤዬን የብዕር ስም እንደሚከተለው ሠይምልኝ። ባንገናኝም ደኅና ሁን።




ያንተው

141 10 67 98 48

(ስመ—ምሥጢር)






ዋርድያሽ ብዛቱ

“ አይ አንቺ እመቤት ፣ ዋርድያሽ ብዛቱ!
ሲሰው አንበሳ ነው ፣ ወይም ንሥር ፣ ዐይነቱ!
ሲወጣ ሲገባ ፣ ሲቀየር ባመቱ።
ኧረ መቸ ይሆን? ራስሽን ችለሽ!
ያን ዐይነት ዋርድያ ፣ የማያስፈልግሽ።
በሬት ጥሎሽ ሔዶ ፣ የገባው ጐረቤት ፣
ጥሞታል መሰለኝ ፣ ያስባል ለመምጣት ፣
እንደገና ሊያድር ፣ ላንቺ ዋርድያነት!!”

t.me/OLDBOOKSPDF



የእብደት አንድምታ


ምንድር ነው ይባላል፣ ደግሞስ ምን ይሉታል?
መሰሉን ሰው ፍጡር፣ መሰል ሰው ሊያጋድል!
ሄረ ምን ይሉታል፣ ይህ ዓይነቴን ድርጊት?
ሰው በሰው ጨከኖ፣ እየለጠ ብረት!
አንድን ሕዝብ ለያይቶ፣ እርስ በርስ ሊያራኩት፣
ሴላ ትርጉም የለው፣ ነው እንጅ ተራ እብደት!!

መሰሉ ሰው ፍጡር፣ አውሬ እየመሰለው፣
እያቀጣቀጠ፣ ድራሹን ካጠፋው፣
ከዚህ የተለየ፣ እብደት ምን ቦታ አለው?!
ካላበደ በቀር፣ ልቡ ካልተነካ፣
ለድቻልም የሰው ልጅ፣ በግዳይ ሊረካ!
ጤነኛ የሆነ፣ ኅሊና ያለው ሰው፣

ለተራበ አንጀት፣ ጥይት ሊለግሠው?
ብናምንም ባናምንም፣ እንዲህ አድርገኖል፣
ባሩድ ነጋዴዎች፣ በሰው ኑፍስ ከብረዋል።
ወደድንም ጠላንም፣ ያለንበት ምድር፣
መሰወጡ አይቀርም፣ "ግሎባሉ አርደር"!
የሚያጋድል ኃይልም፣ ለዘለዓለም አይኖር ።

እስከዚያው ድረስ ግን፣ በጣም የሚገርመው፣
ቆራጡን አጥፍተው፣ ምሁሩን አባረው፣
ስንቴን ሀገር ወዳድ፣ ጎልጎታ ከተው!
እንደወፍ ለከናፋት፣ ትውልዱን ሰባብረው፣
አሁን "ሰላም" አሰሀ፣ "ነፃነት" ጠቅላላው!

"እንደፈለግህ ብረር!" የሚሉት ዕብሪት ነው!



t.me/OLDBOOKSPDF

እየመረረ የሚጣፍጥ



አብርሐት

ዛሬም ትጥቋን አልፈታችም!

የሚያታግለው እስካለ ድረስ ፣ የጠብመንጃዋ

አፈ-ሙዝ ፣ የጠላትን ፋሽስታዊ ጠረን እያነፈነፈ

በመቅጣት ላይ ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF

መንደርደርያ

ዩኒቬርስ ወይም ፅንፈ-ዓለም፣ በመንታ ባሕርያት ይመሠረታል። ውጥኑም ሆነ ጥርሱ ይኸው ነው። "ይን-ያን"። የሥምረትና የፅርረት መሠረቶች ናቸው። አንፃርያንም። ጥምር ሰማይ ስንል መሬት አለ። እሳት ስንልም ውሃ። ከብናኝቱ ዐካለ-አቶም፣ የነዚህ መንታ ዐካላት መፈልቀቅ፣ ይህን ያህላል ብለው የማይገምቱትን ኃይል-ጉልበት ያበረቁትን ያህል፣ በሌላም ገጻቸው ያንኑ ያህል ለተለያዩ ውጤቶችና ምርቶች ምንጮች ናቸው። ዓለማችን ባጠቃላይ፣ ባሕርየ-መልካቸው ይለያይ እንጅ፣ የነዚህ መንታ ግማደ-አካላት (ኤሌመንትስ) ነፀብራቅ ነው። በነሱ መጋባትና በነሱም መፋታት፣ የዓለማችን መንገኒቃዊ ኩነት ይካሔዳል።

ከነዚህ ባሕርያት መግለጫ አንዱ ሰው ነው። የሰው አካላዊ ምንታዌነት፣ ከተገኘበት ወቅት ጀምሮ እውቅ ነው። ምንታዌነቱ ላዲስ ምርታዊ ልደት ምክንያት ነው። አንዱ ያለ ሌላው፣ ሌላውም ያለ አጣማጁ መኖር የሚችል ቢሆንም፣ መባዛትም ሆነ መሰሉን ማምረት አይሆንለትም። ስለዚህም ወንዴና ሴቴ በየራሳቸው ቅርፀ-አካላት እንዲኖሩ ሆነ። በመሆኑም በግንኙነት ይራባሉ። ይህ ነባር ሕግ ሆኗል።

ሌላው የምንታዌ ባሕርያት መግለጫ፣ ጠባይ ነው። እንደማናቸውም ሌሎች ጥምር ባሕርያት ሁሉ፣ ጠባይም በመሠረቱ ሁለት ዐይነት ነው። እነዚህ በየበኩላቸው ደግሞ፣ የየራሳቸው ዘርፎች አሏቸው። ዋናዎቹ ግን፣ ክፋትና በጐነት ናቸው። በተለያዩ መልኰቻቸው ይገዝፋሉ። ክፋት በራስ ወዳድነት ቀርቦ እንደሆነ፣ በጎነት ደግሞ በጋርዮሽ አፍቃሪነት ይከሰታል። እነዚህ ጠባዮች በመሠረተ-ባሕርያቸው፣ በባለ ኅሊናው ሰው የሚገለፀ እንጅ፣ የነጠላ ራሳቸው ግለኛ ሕላዌ የላቸውም። ሰውን ተዋሕደው፣ ሰውን ሙጥኝ ብለው፣ በጥገኝነት የሚኖሩ ናቸው። እንዲያም ሲል፣ በሌሎችም ፍጡራን ላይ አልፎ አልፎ መታየታቸው አልቀረም።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህች አጭር ልቦለድ ታሪክ በነዚህ መንታ የሰዎች ባሕርያት ላይ የተነደፈች ናት። ጭብጡ፣ በሀገራችን የለውጥ ሣኢታ ላይ የበረቀ ነው። ለማኅበረ-ሰባዊ በጐነት የምታስባዋን አብርሒትን፣ ለግሉ ደኅንነት ከሚያስበው ወንድሟ ጋር እየነፃፀረ ማቅረቡ፣ የክፋትንና የበጎነትን እርቃነ-ምንነት ባደባባይ ለማጋለጥ ታስቦ ነው። ይህችን ስንጣሪ ሓሳብ፣ በትልቁ አጉልተን ብንመለከተው፣ በጊዜያችን ያለውን የሥልጣን ቡድንና፣ ለነፃነቱና ለመብቱ፣ ለፍትሕና ለማኅበራዊ ብልፅግናው ከሚታገለው ህዝባዊ ኃይል ጋር ያለውን ሁኔታና ትንቅንቅ ቁልጭ አርጎ ያሳያል። እግረ መንገዱንም ነፃነትን ያህል ክቡር ነገር ለማግኘት፣ ምን ያህል የመረረ ትግልና መሥዋዕትነት እንደሚጠይቅ ለማሳየት፣ ከትግሉ ጎራ ይወስድና ያለውን ቸነፈር፣ መከራ፣ ሥቃይ ያሳያል። የትግሉንም ክቡርነትና ቆራጥነት ለማዘከር ካንድ አብራክና ካንድ ማኅፀን የተገኙትን ያንድ አባትና እናት ልጆች፣ በደም ደረጃ ያታግላል። ድርጊቱ ልቦለድ ይባል እንጅ፣ በዚች በኩንትሿ የትግል ዓመታት ውስጥ፣ በተለያዩ ቦታዎችና በተለያዩ ቤተሰቦች ውስጥ በብዛት የተፈፀመ ነው። የአስተሳሰብ ዝምድና ከሌለ፣ የሥጋ ዝምድና ብቻውን ሰዎችን ማወዳጀት እንደማይችል በማዘከር፣ የሰው ልጆችን የርዕዮተ-ዓለም አንድነት የሚጠይቅ የገድላዊ ታሪክ ትይታ ነው። የገድሉን ታሪካዊ ርዕስ፣ "አብርሒት" ብሎ መሠየሙ አቋራጭ በሆነ ነበር። ግን በተመሳሳይ የገድል ታሪክ ይዘት ላይ፣ ተቀዳሚነት ሊሰጠው የሚገባው፣ የገድሉ ታሪክ አቀንቃኝ ግለ ሰብ ሳይሆን፣ የገድሉ ታሪክ አቀንቃኝ ሐሳብ መሆን ስላለበት፣ ከ "አብርሒት" ርዕስነት ይልቅ የ "እየመረረ የሚጣፍጥ" ርዕስነት ተመረጠ። ትግል በተካሔደባቸው ሀገሮች ውስጥ፣ ይህን መሰል የገድል ታሪክ ሥነ ጽሑፋዊ ዥጣ የሳንሡር ግድቦችን ሳይቀር እየደረመሠ ጉርፍል። በዚህ ታሪክ ውስጥ፣ በጅምላ አነጋገር ሳቢያ፣ ለጭቁን ወገን የሚቆጩ የወታደር ወገኖች ቢኖሩ "ከኑግ የተገኘህ ሠሊጥ፡ አብረህ ተወቀጥ !" እንዲሉ፣ በድምር ተኩንነው ይሆናል። ይሁን እንጂ ያ ክቡር ዝንባሌ ያላቸውን ተራማጅ ወታደሮች፣ ታሪኩ አይመለከታቸውም። የፋሽስት አርጋጅ አንጋጅ የሆኑትን ግን አይምርም። አብርሒት ወንድሟን እንደ አባት እናት

t.me/OLDBOOKSPDF

ልጅነቱ፣ የተፈጥሮ ስሜት ነውና፣ አልጠላችውም ነበር። ግን የወንድሟ የበስተኋላ ኢኩኖሚአዊ ዝንባሌውና፣ ለገዛ ጥቅሙ ብቻ የመንሰፍሰፍ ስሜቱ፣ ያስከተለበት ባሕርዩ ነው፣ ያጣላትና ወንድምነቱንም ያስጠላት። በዓለማችን ላይ፣ ዘርዝረንና መንዝረን ሳናየው እየቀረን ይሆናል እንጅ፣ በየትኛውም ምድርና በማናቸውም ሕዝብ መካከል የሚኖሩ ተቃርኖ ሁሉ አብርሒትን ከወንድሟ ጋር ሊያቃቅራት የቻለው፣ ለግለ-ሰብ ርካታ የሚደረግ የኢኩኖሚ፣ እንሰፍሰፍታ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህን ግለ-ሰብአዊ የኢኮኖሚ እንሰፍሰፍታ፣ እርቅ አይፈታውም። ምናልባት ለተወሰነ ጊዜ ያህል ፋታ ይሰጥ እንጅ፣ እንሰፍሰፍታው ለሚፈጥረው ተቃርኖ፣ እርቅ ብቻውን መሠረታዊ ዋስትናም ሆነ ውጤት ሊወጣው አይችልም። ስለዚህም ነው፣ የኢኮኖሚ እንሰፍሰፍታ ያናከሳቸው ሁሉ፣ ወደዱም ጠሉ፣ ለፍልሚያ የሚቀርቡት። የበዝባዥና የተበዝባዥ መደቦች ትንቅንቅና ፍልሚያ፣ ከዚህ ዓይነቱ የነአብሪሒት ገድል ተለይቶ አይታይም።

በጎነት ከነቤተሰቡ፣የክፋትን ጀሌ ድል ለመምታት፣ የሚጠይቀው መሠዋዕትነትና ቆራጥነት፣ ቀላል እንዳይደለ፣ በጨረፍታም ቢሆን ታሪኩ ያሳያል። ከጠቅላላ ሠንኩፋም ጋር እስከ መጨረሻው በታትኖ ለመጣል፣ የረዥም ጊዜ ትግል እንደሚጠይቅ ይጠቁማል። በረዥም ዘመናት አታጋይነቱ አንፃር ሲታይ፣ መራራነቱ እረፍት ነው። ከበጋና ክረምት፣ ከሞያሌና ተባይ፣ ከቆንጥርና ከአሜከላ፣ ከንዳድና ከበረሐ ... ጭምር ስለሆነ፣ ትግሉ መራራ ነው። የኋላ ኋላ ግን ድል የማይቀር ነውና፣ ጣፋጭነቱ የምሬቱን ያህል ማርማ ነው።

ይህች ልብ-ወለድ ታሪክ፣ በሌላ ገጿ አንድ እውነታ ፍንትው አርጋለች። "ኢትዮጵያውያት በትግሉ ዓለም የሉበትም" በሚለው ሐሜታ አንፃር፣ ቁጥራቸው አይብዛ እንጅ፣ እነ አብርሒትም ከነሞግዜራችው ጋር ዛሬም እንዳሉ ጠቁማለች። በተለይ ደግሞ፣ የጉራው ትግል እየተራዘመ በሔደ ቁጥር፣ በሚያከማቸው ተመክሮ፣ ይበልጥ እየደረጀና እየደመቀ መሆኑ ባይዘነጋም፣ በመጀመርያ ወቅት የነበረውን ችግር አጉልቶ መግለጹ፣ የ "እየመረረ የሚጣፍጥ" እድገታዊ ሁኔታውን ለማብሠር ተብሎ ነው። ለማንኛውም፣ የግል ፍላጐቱን ገድሎ፣ ከሕዝብ ጋር የቦደነ ሁሉ፣ መጨረሻ ግቡ ጣፋጭ እንደሆነ ይረዳል።

እየመረረ የሚጣፍጥ

(በጐራው የትግል ትዝታ ላይ የተመሠረተ ገድል)

"...በተጨማደደችና በቀረፈደች የስልቻ ኮፋዳ ውስጥ፣ ጭብጦ አዝላለች። የገብስ ወይም የስንዴ ቢሆን በበጀ። የጓያ ጭብጦ ነው። ገንፎ ቢሆንማ ኖሮ፣ እግር ያንሻፍፍ ነበር። የአኮፋዳው እንዲያ መቀርፈድ፣ የጭብጦውን ቅባት-አልባነት ያስረዳል። ይህችም ጭብጦ፣ ለወር ዕድሜ የማታወላዳ፣ የወር ስንቅ መሆንዋ ነው። የጥይት ፋጢስና የባሩድ ጠረን ጥቂት ሰክኖ፣ እፎይታ ስታገኝ ጠዋትና ማታ የምትቀምሳት ቁርስና ራት ናት።

ከጭብጦዋ ድርቀት የተነሳ፣ ያለ ውሃ አትቀመስም። ካነገበቻት ኮዳ ውስጥ ባላት ውሃ፣ መዳፍ የምታህለውን ቁራሽ አርሳ፣ በውሃይቱ ጉርጉጭ ታረጋታለች። በየጐራው እሳት አይገኝም እንጅ፣ የነፈረ ውሃ ይበልጥ አርሶ፣ ለጉሮሮዋ እንንዲያመች ባደረገች ነበር። በየጐራው ስትወጣና ስትወርድ፣ "በልቶ መጥገብ" የሚባለውን ሐሳብ፣ ከረሳችው ዓመታት አልፈዋል። አልፎ አልፎ ቢያጋጥማትም ልምዱን ስለረሳችው፣ እምብዛም አትጨነቅለትም። ከቶውንም የጐራውን አባል ጓዶች፣ በምግብ እጦት አንባር፣ አልፎ አልፍ የሚያጋጥማቸውን በማስመልከት፣ ቀደም ሲል የነፃ ማውጣት ትግል በተካሔደባቸው ሀገሮች፣ የቬትናም፣ የቻይናና የሌሎችንም ታጋዮች፣ የደረሱባቸውን መሰል ችግሮችና የተቋቋሙባቸውን ዘዴዎች በመጥቀስ፣ እንደ ተመክሮ በማቅረብ ታፅናናቸዋለች፣ ታጐለብታቸዋለችም። በተልይም አዘውትራ ከምትነግራቸው "የችግር መቋቋም" ታሪክ ውስጥ፤ ፋሽስቱ ሙሶሊኒ ሀገራችንን ሊወር መጥቶ በነበረበት ጊዜ፤ ሀገራችንን በባዕዳን ወራሪዎች ላለማስደፈር፣ በዱር በገደሉ ተሠማርተው ግራዚያኒን ከነሠራዊቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያንበረከኩት ታጋይ አባቶች፣ የከፈሉት መሥዋዕትነት ይገኝበታል። ከዚህም አንዱ ትንግርት፣ ስንቃቸው ቢያልቅባቸው፣ የዘየዱት መላ ነው።

ሕይወታቸውን አራዝመው፣ የጀመሩትን ትግል ከግብ ለማድረስ ሲሉ "ስንቅ የጫኑብትን ስልቻና መጫኛ፣ በውሃ እያራሱ አኝኩ ከመምጠጥ ጀምሮ፣ በመጨረሻም፣ አህያዋን ራሷን ነፍስ-አድን እስከማድረግ ድረስ"፣ ተጠቅመውባታል። እንዲህ መሰሉን ማበረታቻ ተመክሮ፣ ላብሮ ዘመት ጓዶች በማስረዳት፣ ልባቸው ሆነ ቆራጥነታቸው፣ ከብረት የጠነከረ እንዲሆን በማድረግ፣ ለማንኛውም ዐይነት ችግር የማይበገሩ ታጋዮች ለመሆን አብቅታቸዋለች። በበኩሏም፣ ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ያለበትን አብዮታዊ ግዴታ ለመፈጸም ስትል፣ በፍፁም ቆራጥነት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ "ኢሕአሠ" በመባል ለታወቀው የጦር ክንፉ፣ ከአንደኛው የብርጌድ ሠራዊት ውስጥ፣ በአባልነት ተሠልፋ፣ ከግፈኛው የፋሽስት ጦር ጋር ስትፋለም፣ ዐመታት አልፍታል።

ስሟ አብርሒት ይባላል። ኽያ ስድስተኛ ዐመቷን ያገባደደች፣ የዩኒቨርሲቲ ምርቅት ናት። ለነገሩማ፣ ካንድ ኩብንያ ውስጥ ተቀጥራ፣ ብዙ ገንዘብም ትዝቅ ነበር። ረዢም ጊዜ ግን አልሠራችም። አከባቢዋን ለማረጋጋት በማሰብም፣ እንደ ዘመኑ ኩረዳ፣ መኪናም ቤትም ነበራት። ወላጆቿም፣ ደሀም ሀብታምም ያልሆኑ የማዕከላዊ ኑሮ ባለቤቶች ነበሩ። ለቤቶቿ ሁለተኛ ልጅ ናት። "ወንድም ጋሼ" የምትለው ታላቅ ወንድሟ፣ ከሐረር የጦር አካዳሚ የተመረቀ፣ የሺ አለቃ ነው። ወታደር ከሆነበት ወቅት ጀምሮ እስኪጨረስ፣ ከወንድሟ ጋር ተጣጥመው አያውቁም። ገና ድሮ፣ ወታደር ለመሆን የቆረጠለት ነው፣ የከረረ ጠብ ያበቀሉት።

ወላጆቻቸው፣ እንዳህያ ጡት ሁለት ብቻ የሆኑ ልጆቻቸውን፣ በወንድምነትና በእህትነት ደረጃ ለማቀራረብ ያልጣሩበት ጊዜ የለም። ከተውንም በማስታረቁ የረዷቸው መስሏቸው፣ ያልሠገዱለት ጠንቋይ፣ ያልተሣሉለት ታቦት አይገኝም። ሊያስታርቃቸው የሞከረ፣ የወዳጅና የሽማግሌ ጋጋታ፣ ቁጥሩ አይታወቅም። በልጆቻቸው አለመስማማት፣ ቤተ-ሰባቸው ከቆሰለ ዘመናት አልፎታል። ከዚህም የተነሣ፣ ወላጅ አባትና እናት፣ ደስ ብሏቸው የዋሉበትና ያደሩበት ዘመን፣ በቁጥር

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው። አንዴ አብርሒትን፣ አንዴ ሻለቃ ልጃቸውን ለማስታረቅ ሲያባብሉ፣ አፍላ ዘመናቸውን ገፍተው፣ በማዕከላዊ እድሜ ፍፃሜያቸው ላይ ይገኛሉ። በልጆቻቸው መናቆር የተነሣ፣ "ምን አልንህ" እያሉ የቁልቢውን ሳይቀር ያማርራሉ።

አብርሒት፣ ገና ከሕፃንነቷ ጀምሮ፤ ጠሊቅ አስተሳሰብ ያላት፣ በረዢሙ የምታስብ፣ የጎብረተ-ሰብ ችግሮች ዘወትር የሚከነክናት፣ ኋላም በትምህርት ከጉለመሰች አንስቶ፣ ማንኛውንም ሁኔታ፣ ሣይንሳዊ በሆነ ዐይን የምትመለከት፣ ችግሮችን ሁሉ፣ ከጭብጡ ሁኔታ በመነሣት፣ በሳይንስ ይዘት የምትመረምር፣ የሶሻል ፍልስፍና ጠበብቶችን ትምህርት፣ ከአከባቢዋ ሁኔታ ጋር የምታገናዝብ፣ ሀገሯም ሆነ ጠቅላላው ዓለም ቅንና ትሁት በሆነው በሠራተኛው የላብ አደር መደብ የሕዝብን ዲሞክራሲያዊ ትርታ የሚያዳምጥ የበላይነት መተዳደር እንዳለበት የምታምን፣ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ጥቂት መሰል ሔዋንያት ልጆቿ ውስጥ አንዲቱ ናት። በማታምንበት የጎብረተ-ሰብ አድኃሪ ሥርዓት ውስጥ ያለ ውዴታዋ ስትኖር፣ ዓመታት አልፈዋታል። ግን ያን ሁሉ ዓመታት፣ በዝምታ አላቃጠለቻቸውም። ቀዳዳ ባገኘች ቁጥር፣ አድኃሪውን ሥርዓት ስትቦረቡርና ስትገዘግዝ ኖራለች። ይህን ሁሉ ታደርግ የነበር፣ በጎቡዕ ነው።

ታላቅ ወንድሟ፣ ወታደር እስከሆነበት ጊዜ ድረስ፣ ነፍሷ እስኪጠፋ ትወደው ነበር። የሁለቱም ዕድሜ እየጨመረ በሔደ ቁጥር፣ ያስተሳሰብ አድማሳቸው እየሰፋና የኑሮ ምርጫቸው እየጠበበ መጥቶ፣ ከማይጣጣመብት ደረጃ ላይ ደረሱ። ቀደም ሲል ግን፣ በዚያ በሞቀ ወላጆቻቸው ቤት ውስጥ፣ በዚያ ተድላ ደስታ በሰፈነበት ቤት ውስጥ፣ በዚያ ወላጆችና ልጆች እኩል ይናገሩበት፣ ይዝናኑበት በነበረበት ቤት ውስጥ፣ ለሰዓት ዕድሜ እንኳ ሲለያዩ፣ ናፍቆታቸውን አይችሉትም ነበር።

በልጅነታቸው ዘመን ወላጆቿ፣ ለሷ አዲስ ልብስ ገዝተው፣ ለወንድሟ ሳይገዙ ሲቀሩ፣ ታቀልጠው የነበረውን የተቃውሞ እሪታ፣ አሁን አንታረቅም ብለው ላስቸገሯቸው ልጆቻቸው፣ የቀድሞ ፍቅር፣ ትዝታ ሆኖ፣ ውስጥ ውስጡን ይበላቸዋል፣ ይቆጠቁጣቸዋል፣ ወላጆቻቸውን። አብሪሒትና ወንድሟ በትምህርት

ዘመናቸው ጊዜ፣ የነበራቸውን ፍቅር የተመለከተ የጉረቤት ሰው፤እንዲያ ይተሳሰቡ ይረዳዱ በነበሩበት የወጣትነት ውቅት፣ ያጤናቸው የትምህርት ቤት ጓደኛ፣ በወላጆቻቸው ጠለላ ስር፣ ባንድነት ይኖሩ በነበሩበት ዘመን፣ ያስተዋላቸው አዛውንት ሁሉ፣ በነበራቸው ፍቅር፣ በሚያሳዩት መተሳሰብና መረዳዳት፣ አበክሮ ያልቀናባቸው ሰው አይገኝም ነበር። እንዲያው በሰፈራቸው ውስጥ ተንኳሽና በጥባጭ፣ ዓመለኛና ረባሽ የሆነ ልጅ ያለው ወላጅ ሁሉ፣ "ምነው እንደ ነአብረሒት ብትሆን !" እያለ የጥሩ ምግባርና ፀባይ፣ ምሳሌና አርአያ እስኪሆኑ ድርስ፣ በይፋ መስክሮላቸው ነበር። የሠፈራቸው ፋደት ሁሉ ባስቸገረ ቁጥር፣ "ምንው ከነአብርሒት ብትማር !" ያልተባለ አይገኝም። በርግጥም፣ አብርሒትና ወንድሚ፣ ዕለት በዕለት ያሳዩት በነበረው መልካም ምግባርና ጥሩ ጠባይ አንፃር፣በጎ አርአያነታቸው፣ በተመክሮ ደረጃ መቅረቡ አያስደንቅም ነበር። በመንደራቸው ውስጥ፣ በሕመም ወይም በእርጅና ምክንያት መጓዝ ተስኖት በመንገድ ላይ ያገኙትን ሰው ሁሉ፣ ከሚፈልግበት ስፍራ ሳያደርሱት እንደሌሎች አይተው እንዳላየ አያልፉትም።

ባካቢያቸው የሚገኙ አረጋውያንና ባልቴቶች ሁሉ፣ በየመልኩ በነአብርሒት የልተረዳ አይገኝም። የዘመመ ጎጆውን ያላቃኑለት፣ የተቀደደ ልብሱን ያልሠፉለት፣ የሚየንገበግብ ሞያሌውን ያልፈነቀሉለት፣ እንዲያም ሲል የተጠማ ጉሮሮውን፣ የተራበ አንጀቱን ያላረሱለት፣ የመንደሩ ችግተኛ አይገኝም። በዚያ የትምህርት ዘመናቸው ጊዜ፣ የኢኩኖሚ እጥረት አንበርክኳቸው እንጅ፣ እንደምኞታቸውማ ቢሆን ኖሮ፣ ስንቱም ባራመዱ ነበር። ሆኖም በዚያ አቅማቸው እንኳ፣ የማታ ትምህርት ቤት ከፍተው፣ መሠረተ-ትምህርት በነፃ ሰጥተዋል። ለአርአያነት የምታበቃ ትንሽ መጻሕፍት ቤት ከፍተው፣ አንባብያንን ረድተዋል። እግረ መንገዳቸውንም፣ ከጎብረተ-ሰቡ ያስተሳሰብ እድገት ጋር የሚሔድ፣ የንቃት ቅስቀሳ፣ ዐቅማቸውና አካባቢያቸው እስከመጠነ ድረስ፣ በየጊዜው አካሒደዋል። የነሱ ጊዜያዊ ርዳታ በቂ አለመሆኑን በማስረዳት፣ ቀዋሚና መሠረታዊ ለውጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማስፈለጉን፣ ባደባባይ ተናግረዋል። በዚህና በመሰለ ሌላ ድርጊት ተወንጅለውም፣ በዚያ በወጣትነታቸው ዘመን፣ ላጭር ጊዜ ታስረዋል፣ ቸብ ቸብ ተደርገዋልም።

ያ የወጣትነትና አፍላ የትምህርት ዘመናቸው፣ እንዲህ የመሳሰለውን ተግባራት ሲያንፀባርቅ ቆይቶ፣ አንደኛው ጎን በድንገት ሽብረክ አለና፣ ሌላ ያልተጠበቀ መልክና ሁኔታ ማሳየት ጀመረ። ይኸውም፣ ያብርሒት ታላቅ ወንድም፣ የድሮው ተማሪ፣ የዛሬው ሻለቃ፣ የጠባይ አዝማሚያ ጉዳይ ነው።

አብርሒት፣ ገና አሥረኛ ክፍል ሳለች፣ ወንድሚ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ላይ ነበርና፣ የሁለተኛ ደረጃን መልቀቂያ ፈተና መውሰድ ነበረበት። እንዳጋጣሚም፣ ለስድስት ፈተናዎች ተቀምጦ፣ በአራቱ ብቻ ሲያልፍ፣ በቀሩት ወደቀ። በዚህም ውጤቱ ምክንያት፣ ዩኒቬርሲቲ የመማር ምኞቱ፣ ለጊዜው ተቀጨ። ያልጠበቀው አጋጣሚም በመሆኑ፣ እድሜ ልኩን ታይቶበት በማይታወቅ ሁኔታ ተበሳጨ። ይህ በሆነ፣ በመንፈቅ እድሜ ውስጥ፣ ያ፣ በጎ ምግባሩና ተራማጅ ባሕርዩ ሁሉ ነፍተው እንዳስተነፈሱት የላስቲክ ነፋሪት፣ ጨርሶ ሚሸሽ። እንዲያ ይንሠፈሰፍላቸው የነበሩትን ወላጆቹን፣ የመንደሩን ችግተኞችና የነፍሱን ያህል ይወዳት የነበረውን፣ እህቱን አብርሒትን ሳይቀር፣ ርግፍ አርጎ ተዋቸው። የደረሰበትን የመንፈስ ጭንቀት የተቋቋመ መስሎት፣ አንዳንድ ጓደኞቹ እንዳደረጉት ሁሉ፣ ሐረር የጦር አካዳሚ ለመግባት፣ በግሉ ወሰነ። በዚያም ወቅት ይህ ውሳኔው ሌላ አማራጭ የማይገኝለት መሰለው።

ይህን ውሳኔውን የነገራት ለት ነው፣ ከእህቱ ከአብርሒት ጋር፣ እርቅ የለሽ ጸባቸው የተጠነሠሠው። ለወራት ያህል ገሸሽ አርጓት ከቆየ በኋላ አንድ ቀን ማለዳ፣ ቁርሳቸውን በልተው እንደጨረሱ፤

"አብርሒት ! አንድ ውሳኔ አድርጌያለሁ !" አላት፣ እንደምትቆጣው፣ እንደምታዝን፣ እንደማትቀበለው አውቆ፣ ሲፈራ ሲቸር።

"የምን ውሳኔ ?" አለችው እንደመደንገጥም እንደመቆጣትም እየቃጣት፣

"እንደምታውቂው፣" አለ በሸላላ አንደበት እንደመዝናናት ብሎ፣ "ፈተና ከወደቅሁበት ጊዜ ጀምሮ፣ ደስ ብሎኝ እንዳልኖርኩ፣ በቅርብ ሆነው ካዩኝ ሰዎች

ውስጥ፣ አንቺ አንዷ ነሽ። ጭንቀቴ ከጊዜ ወደጊዜ እየባሰና እየከፋ ሔደ እንጂ አልቀነሰም። ከአሁኑ የመቆጣጠሪያ ዘዴ ካላገኘሁ፣ ለሌላ ችግር ይጥለኛል ብዬ ስለሠጋሁ ...” ብሎ ሊናገር ሲቀጥል፤

“እኮ ምን ልትሆን አሰብክ” ሐሳቡን ለማወቅ እየትቅበጠበጠች ጠየቀችው፣

“እንደምታውቂው በአራት የማትሪክ ፈተናዎች አልፈአለሁ። ተመሳሳይ ውጤት አግኝተው እንዳደረጉት ሁሉ፣ ሰሞኑን ሐረር ለመሔድ ወስኛለሁ።” አላት እየተርበተበተ።

“ደኅናም አይደለህ እንዴ ! በዚህ ዐመቱ ማትሪክ መወደቅህ፣ ምንም እንዳይደለ ብዙ ጊዜ ተነጋግረናል። ያንድ ጊዜ ፈተና መወደቅ፣ ያንተን የመማር ዕድል እስከ መጨረሻው የሚወስን እንዳይደለ፣ ተወያይተን አምነህበት፣ ለመጭው እንድትዘጋጅ አድርገናል። አሁን ደግሞ፣ ምን ዓይነት የሐሳብ ማዕበል ነድሎህ ነው ሐረር ልሒድ የምትለው ! ይህ ሐሳብህ፣ እማማና አባባ ጆሮጋ እንዳይደርስ አስብበት ...” ሐሳቡን ችላ ብላና አዋድቃ፣ ለመሔድ ከመቀመጫዋ ልትነሳ ስትከጅል፣ እጇን ያዘና፣ እንባ እየታነቀው፣ ከልቅሶ ባላነሰ አንደበቱ፤

“አብርሒት ! ውሣኔዬ ነው። ወታደር ለመሆን ቆርጫለሁ። የሐረሩ የጦር አካዳሚም ተቀብሎኛል። ይኸውልሽ ደብዳቤያቸው !” ብሎ ደብዳቤውን ሊያሳያት ወደ ኪሱ ሲገባ፤ አብርሒት፣ የቀትር ብራቅ የመታውን ሰው ይመስል፤

“አልሰማም ! ጆሮዬ አይሰማም ! ...” እሪ እያለች፣ እናትና አባቷ ወደ ሥራ ለመሔድ ከሚዘጋጁበት ክፍል ሮጣ ገብታ፣ መርዶውን ነገረቻቸው። በዚያንም ወቅት ነው፣ ወንድሟ ለጉዞ ያዘጋጃትን ትንሽ ሻንጣ ይዞ፣ በሚያስደንቅ ፍጥነት ባጠገቡ ባለ መስኮት ዘሎ፣ ወላጆቹም ሆኑ እህቱ ሳይገናኙትና ሳያማክሩት፣ ወደ ሐረር የመረሸው።

አብርሒትና ወላጆቿም፣ እንደ ዝማ የጐረፈውን እንባቸውን ጠርገው፣ እቅታቸውን ውጠው፣ በድንገት የተለያቸውን የቤተሰብ አባላቸውን፣ በአካል ሥጋ ሳይሆን፣ በልባዊ ተውኔት ተሰነባብተው፣ ከዚያችም ቀንና ሰዓት ጀምሮ፣ ለሁለት ዐመታት ጊዜ ሳይገናኙት ኖሩ። የሚያገኛቸው ሰው፣ ሰለሱ በጠየቃቸው ቁጥር፣

t.me/OLDBOOKSPDF

“አጐቱን ሊጠይቅ ባላገር ሔዷል” እያሉ ይዋሹ ነበር። አብርሒትም፣ የወንድሟን፣ የቀድሞ በጐነት፣ ቅንነት፣ ታታሪነት፣ አርቆ አሳቢነት፣ በጠቅላላውም የነበረውን ተራማጅ አስተሳሰቦች እያስታወሰች፣ ስለ ወንድሟ የነበራት የጋለ ትዝታ፤ ጊዜ፣ ቀስ በቀስ እያለ፣ እስካበረደው ድረስ እየተንሠቀሠቀች ታዝን ነበር።

እንዴውም የምታለቅስበት ዐይኖቿ ጕድጕደው፣ የባሌ ውሃ ማቀር የሚያስችሉ ይመስላሉ። ወንድሟ ትዝ ባላት ቁጥር “ያን መሳይ ተራማጅ ወንድሜ፣ ወታደር ይሁን ! የገዥ መደብ ዋርድያ ! ለሚዘርፉትና ከጭቁን ሕዝብ ለሚበዘብዙት ሀብትና ንብረታቸው፣ ሕጋዊ ዘበኛ ! የጠሉትን ሁሉ ለመረሸን የሚታዘዝ፣ ሕጋዊ ገዳይ ! በጠቅላላው፣ የቦጥቧጭ መደብ፣ ሳይሠራና ሳይደክም ለሚዝቀው ጥቅም፣ ከተራው ውሻ ባላነሰ አገልጋይነት፣ ወታደራቸው ሆኖ ‘ለፓራሳይት’ ሕይወታቸው ሕጋዊ ጠባቂና አስከባሪ ይሁን ! ...” እያለች ሌት ከቀን ታነባዋለች።

አንዳንዴም፣ ቤተሰቡን ጥሎ ከጠፋበት ቀን አንስቶ፣ በዚያ የሐረሩ የጦር አካዳሚ የሚገኝበትን ሁኔታ፣ በዓይነ– ኅሊናዋ ስትመለከተውና በእህትነት ልቦናዋ ስታስበው፣ አንዳንድ ትርሚቶች እየተደቀኑ ይረብሿት ነበር። “ይኸኔ፣ ያን ሳንጃ የተለጐመ ጠበንጃ ተሰጦት፣ ያን ያልታደለ ጭቁን ሕዝብ፣ እንዴት ማረድ እንዳለበት፣ እንዴት ማሰቃየት እንዳለበት፤ በፈንጂ፣ በቦንብ፣ ባዳፍኔ፣ በመትርየስ፣ በታንክ፣ ለነፃነቱ፣ ለዲሞክራሲው፣ ለኢኮኖሚያዊ ፍትሁ፣ ለተስተካከለ ኑሮው፣ አምፆ የሚነሳን ጭቁን ሕዝብ፤ እንዴት አድርጐ ያለርኅራኄ ማጨድና ማጥፋት እንዳለበት፣ ይማራል ! በባዕዳን መንግሥታት ብሔራዊ ክብራችን ተደፈረ፣ ብለው የሚነሱትን ሀገር ወዳዶች፤ አምባገነን መሪ እንፈልግም፣ ብለው የሚነሱትን ዲሞክራቶች፣ በሳይንስ ላይ የተመሠረተ ኅብረተ–ሰብ እንፈልጋለን ብለው፣ የሚታገሉትን ተራማጆችና ሌሎችንም የነፃነት ታጋዮች ሁሉ፤ እንዴት አድርጐ በማያዳግም ሁኔታ፣ ማጥፋት እንዳለበት፤ ይኸኔ በሐረሩ የውትድርና ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት፣ ትምህርቱ እየተሰጠው ነው ! ይኸኔ መሠረታውያን የወታደር ዲሲፕሊንና ግዳጆች ተብለው፣ የሚቀርቡትን፤

እንደ "... የበላይ የሚያዝህን፣ አለአንዳች ተቃውሞ ተቀበል፣ ለበላይህም ሆነ ለቅርብ አለቃህ፣ ፍፁም ታማኝና ታዛዥ ሁን፤ ለግዳጅ ስትጠራ ለምን ብለህ አትጠይቅ፤ ለግዳይ ግዴታህ ምሕረት አታሣይ፣ ለቆምህለት ዓላማ ለሕይወትህ ሳትሣሣ ተሠዋ ..." ያሉትን፣ የሞራል ምናምንቴዎች በሰላ አንደበታቸው በመስበክ፣ ያንን ሕዝባዊ የነበረ አእምሮውን፣ ጠዋት ማታ ቱር አርገው ያጥቡታል። ይኸኔ፣ "ለጭቁን ሕዝብ መሞት አለብኝ" ይል የነበረውን ውሣኔውን "ለመሪህ ክብር ስትል፣ ሞትን አትፍራ" በሚለው ትምህርታቸው እየለወጡት ነው። ..." እያለች፣ አብርሒት ብቻዋን፣ በሐሳብና ባሳዛኝ የትዝታ ባሕር ውስጥ የምትሰጥምባቸው ጊዜያቶች፣ እጥር አልነበሩም። አንዳንድ ቀንማ፣ በብስጭት ተውጣ፣ አንጉሉን ነካ አርጉት እንደወፈፈ ሰው፣ ብቻዋን እየተናገረች በየመንገዱ ትሔድ ነበር። አዘውትራ የምታነበንበው የብቸኛ ንግግሯ፣ እንዲህ የሚል ይዘት ነበረው፤

"...አውቃለሁ፣ ወንድሜ በፊት ተራማጅ አስተሳሰብ ነበረው። ባንዳንድ ነጥቦች ላይ ብስለት እንዳልነበረውም አምናለሁ። አንዳንድ ጊዜም፣ እስኪወጣለት ድረስ፣ በስሕተቶቹ ላይ እንጨቃጨቅ ነበር። ያላሚላቸውን ጥራቶች ወደፊት እንዲዘጋጅባቸው እየተስማማን ያለፍንባቸው፣ የንትርክ ጊዜዎች ጥቂት አልነበሩም። ያስተሳሰብ ብቃት፣ እኔም ቢሆን እንደሌለኝ አምናለሁ። ... ግን ለምንድር ነው ! የፈተናውን መውደቅ አጋጣሚ ይዞ በመነሳት፣ ለዚህ አስደንጋጭና አሳዛኝ ውሳኔ የበቃው ? ይህን ጥያቄ፣ መላልሼ መመርመር ይኖርብኛል !! እንደሚታየኝ ከሆነ፣ ለዚህ ርካሽ ውሣኔው፣ የፈተናውን መውደቅ ሰበብ አርጉ ተነሳ እንጅ፣ በመሠረቱ ሁኔታው ሲተነተን፣ የተደበቀ ባሕርይ ክስተት ይመስለኛል። ፈተናው ሰበቡ ይሁንለት እንጅ፣ ማናው መነሾ፣ የራሱ ባሕርይ ለውጥ ይሆናል።

በርግጥኮ፣ ወንድሜ እንዴት ያለ፣ የጭቁን ሕዝብ ተቆርቋሪ ነበር ! ምናልባት በቅርብ ጊዜ፣ ከዚያች የቱጃር ልጅ ከሆነችው ሦፊያ ጋር፣ እንዲያ ብን ማለት፣ ያስከተለበት የባሕርይ ለውጥ የሆናል። እዎ በመኪናዋ እያዘለች በየ ሲኒማ ቤቱ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ቡና ቤቱ፣ ዳንስ ቤቱ ... ስታዞረው፣ ብዙ ጊዜ ሒስ አቅርቤለት ነበር። ለዚህ ወታደር የመሆን ውሳኔውና፣ ለባሕርዩ መንሸራተት፣ ዋናው ጉዳይና የዚቁ እንብርት፣ ከሦፊያ ጋር መግጠምና፣ በሱዋም በኩል ጭለንጭሉና ብልጭታው ለተያው፣ የካፒታል መሠብሰብና፣ ቱጃር የመሆን ስሜቱና ዝንባሌው ነው። ሌላው ቀርቶ፣ እንዲያ በትምህርት ችሎታው ታውቆ "ብልህ" የተባለው ወንድሜ፤ አድርጉትና ደርሶበት የማያውቀው፣ የፈተና መውደቅ ሁኔታ ያጋጠመው፣ ከዚችው ልጅ ጋር ተያይዞ፣ እፍ እፍ በማለቱ አይደል !

... እኔን ይበልጥ የሚያሳዝነኝ፣ ስንት ከባድ ምስጢር ስንካፈል ኖሮን፣ ስንት የመሠረታዊ ለውጦች እቅድ፣ ስናውጠነጥንና ስናካሔድ ቀይተን፣ አሁን ለጠላት አገልጋይ ለመሆን፣ ወታደርነት መግባቱ ነው። ምስጢሬ ምስጢሩ በመሆኑና፣ በአሁኑ ወቅትም፣ የገዢው ክፍል የጥቅም ጠባቂ ወታደር በመሆኑ፣ ባሳየው፣ የመደብ ባሕርዩን የመክዳት ድርጊት፣ ከእንግዲህ መጠንቀቅ ይኖርብኛል። ማንነቴን፣ ከማንም ሰው ይልቅ ይበልጥ ስለሚያውቅ፣ አንድ ቁጥር ጠላቴ እንደሆነ ማመን አለብኝ። ወንደምነቱንም በጠላትነት መተካቱን ማመን ግዴታዬ ነው። በጣም የደነቀኝ ግን፣ ለብዙ ጊዜ እንዲያ የነበረ ሰው፣ ባንዳናፍታ ቅፅበታዊ ለውጥ ማሳየቱ ነው። ..." እያለች በየመንገዱ ታነበንብ ነበር። ደግነቱ የምትናገረው በለሆሣሥ መሆኑ በጀ እንጅ፣ የሚሰማ ቢሆን ኖሮ፣ ለራሷም ሕይወት ያሰጋት ነበር።

አያልፍ የለምና፣ ጊዜና ወቅት፣ እንደፈሳሽ ዝማ፣ ዘወርዋራ የሕወይት ኪደቶችን እያሳየ ያልፋል። በአብርሒት ቤተሰቦች ላይ፣ የወንድሚ ወታደርነት መግባትና፣ የሱም ወላጆቹን ብቅ ብሎ አለመጠየቅ፣ እንዲያ ሞቆ በኖረው ቤተሰባቸው ላይ፣ የሐዘን ድባብ አጥልቶበት ቆየ። ይሁን እንጅ፣ በዚያ ረዢም የትካዜ ጊዜ ውስጥ፣ ወንድሚ ቤተሰቦቹን ለመጠየቅ ከቤታቸው ባይመጣም፣ ካሉበት ከተማ ብቅ እያለ፣ ከዚያች ቱባ ወዳጁ ከሦፊያ ጋር መታየቱ ታውቋል። በተለይም፣ ባጭር ጊዜ በቀሠመው የሐረሩ ይጦር ትምህርት አማካይነት "በመጀመርያ፣ በደንብ የሚያውቅህንና የቅርብህን ጠላት ባስቸኳይ ማጥፋት

አለብህ !" በሚለው መመሪያ ተሎ፣ ሳሊናው ብቻ ሳይሆን፣ ልቦናው ጭምር ታጥቦ ኖሮ፣ ያቺን ተራማጅ እህቱን አብርሒትን፣ በጅ አዙር ለማስገደል፣ ያልሞከረው ዘዴ አልነበረም።

ዓመት ባልሞላ ጊዜው ውስጥ፣ በሦፍያ ረዳትነት፣ ሦስት ጊዜ በመኪና ሊያስገጫት ሞክሮ፣ ለጥቂት አምልጣለች። ከተላኩ ዳርዬዎች፣ የድብደባ ሙከራ አንስቶ፣ ማንነቷን፣ ለፀጥታ ሰላዮች ሹማምንት እስከማጋለጥ ድረስ፣ እህቱን ለማጥፋት፣ ያልሮጠበት ሙከራ አይገኝም። በዚህም ሙከራው፣ እህቱን ለማጥፋት ባይሣካለትም፣ አብርሒት የሕይወቷን ያህል የምትከባከባቸውን፣ የጭቁን ሕዝብ መረጃ እንቡጥ ድርጅቶቿን፣ ለማዘጋት በቅቷል። አብረው አቋቁመውት የነበረውን፣ የማታውን ትምህርት ቤት፣ መጻሕፍት ቤትና የጥናት መካን፤ የፖለቲካ መልክ በመስጠት፣ ፖሊስ እንዲዘጉ አድርጓል። ለናትና ላባቷ አልነገረቻቸውም እንጅ፣ ሦስት ጊዜ ያህል፣ ከተማ ውስጥ ከሦፍያ ጋር አግኝታው፣ ልኩን ነግራዋለች። እሱም ዝቶባታል።

ከሁለት ዐመታት ቆይታ በኋላ፣ አብርሒት፣ ያስራ ሁለተኛን ክፍል ፈተና በሚያስደንቅ ሁኔታ አለፈች። ሌላውን ትግሏን ሙሉ በሙሉ ባታቋርጥም፣ ለሠላዮች ላለመመቸትና ከወንድሟም ወጥመድ ውስጥ ላለመግባት ስትል በተአቅቦ ይዛው ቆይታለች። በወንድሟና በእህቷ መካከል ይካሔድ የነበረውን የቅራኔ መደባዊ ትግል፣ ወላጆቿ በጥራሽ አያውቁም ነበር። የበለጠ ሐዘን ላይ እንዳይወድቁ በማሰብም፣ ይህን ጉዳይ ላባትና ለናቷ ነግራቸው አታውቅም ነበር። ፈተና የማለፏን ዜና፣ ከነአብሒት ጉረቤት ከሚኖር፣ አንድ የድሮ ጓደኛው ሰምቶ ኖሮ፣ ይህን አጋጣሚ ምክንያት በማድረግ፣ በክረምቱ የዕረፍት ጊዜው፣ የረሳቸውን ቤተሰቦች ለማየት፣ ድንገት ከድሮ ቤቱ ከቸች ይላል። የልጅ ነገር የማያስችላቸው እናትና አባት፣ ያለፈውን በደሉን ሁሉ ረስተው፣ በጋለ ደስታ ተቀበሉት። ከዚያ በፊት ከከተማቸው እየመጣ ይምነሸነሽ ያልነበረውን ያህል፣ "ጊዜ ስላልነበረኝ እስከ ዛሬ ሳልጠይቃችሁ ቆየሁ !" እያለ ወሻከተላቸው። እንዳጋጣሚ እሱ በመጣበት ሰዓት፣ አብርሒት ቤት ስላልነበረችና፤ ከሔደችበትም ስትመለስ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

የወንድሟን መምጣት፣ ገና በውጭ ከጉረቤቶች ስለ ሰማች፣ ላለመገናኘት ወስና ካንድ ጓደኛዋ ቤት ተመልሳ በመሔድ፣ ወንድሟ ተመልሶ እስከሔደበት ቀን ድረስ፣ ተደብቃ ሳትታይ ቆየች። እሊያ ያልታደሉ መከረኛ ወላጆቿ ግን፣ በሱ መገኘት የተደሰቱትን ያህል፣ በሷ መጥፋት ደግሞ፣ ያለመጠን ሲጨነቁ ሰነበቱ። ወንድሟ ለሣምንት ያህል በወላጆቹ ቤት በከረመበት ወቅት፣ ያቺን የዲታ ልጅ ሦፍያን፣ እጮኛው መሆኗን ከማስተዋወቁም በላይ፣ ወሸቱን፣ ከአብርሒት ጋር የሰላምታ ደብዳቤዎች እንደ ሚለዋወጥና፣ ባንዳንድ ነገሮችም እንደማይጣጣሙ ገልፆላቸዋል።

ደቂቃው፣ ለሰዓት፣ ሰዓቱ ለቀን፣ ቀኑ ለሣምንት፣ ሣምንቱ ለወር እያቋጠረ የዚያ አሳዝኝ ቤተሰብ ሁኔታ፣ እንዲያ እንዳለ፣ ዐመታት አለፉ። በዚያም የዘመናት ጉዞ ውስጥ፣ አብርሒት በፖለቲካ ትምህርት ከዩኒቨርሲቲ ተመርቃ፣ የሚያባብል ወፋራም ደሞዝ ያለው ሥራ ተሰጥቷት፣ ባለ መኪና፣ ባለ ቪላ፣ ለመሆን በቅታለች። ያን ዘመን ሁሉ፣ ታደርገው የነበረው የኑሮ መልክ ሁሉ፣ በመምሰል ላይ የተመሠረተ፣ ፍፁም የማታምንበት ረጋ ሠራሽ ድርጊት ነበር። በልዩ ልዩ ፈተናዎች ታጥራ፣ በምሥጢር ተቆጣጣሪዎች ተወጥራ፣ የተያዘች መሆኑን ስለምታውቅ የልቧን ተምኔት፣ ለማንም አሣይታ አታውቅም ነበር። በዚህም ዝንባሌዋ፣ የረኩ ሰዎች ቢኖሩ፣ ተቆጣጣሪዎቿ የመንግሥት ሠላዮቿና፣ እንዲያ እንድትሆን ይመኝላት የነበረው፣ ወንድሟ ብቻ ናቸው። ማንነቷን፣ ቀደም ሲል ያውቋት የነበሩ፣ የጭቁን ሕዝብ ወገኖች ግን፣ "የኛ ተራማጅ" እያሉ ባዩዋት ቁጥር፣ ያሸሟጥጧት ነበር። አብርሒት ግን፣ በበኩሏ የምታምንበትን አቋም፣ ባደባባይ የምትግልጽበትን ጊዜና ቦታ ስትፈልግ የነበረች ናት።

ወንድሟም በበኩሉ፣ በዚያ የረዥም ዘመናት ቆይታ ውስጥ፣ ብዙ ለውጦችን አድርጉ፣ የለየለት ቱጃር ሆኗል። ያቺን የዲታ ልጅ የነበረች ልጅ፣ ሦፊያን መቀራኘቱም፣ ለዚህ የሀብታምነት ግቡ ረድቶታል። ከሐረሩ የጦር አከዳሚ እንደተመረቀ፣ ወዲያው ጋብቻቸው ተፈጽሞ፣ በሦፍያ አባት ረዳትነት፣ የቡና ርሻቸውን ለመቆጣጠር እንዲረዳቸው አስበው፣ ሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ባለ፣ የጦር

ክፍል ተመድቦ፣ የጭቁኑን የኢኮኖሚ ዐካል ሲግጥና ሲቦጭቅ፣ ዐመታት አልፈውታል። የወጣለትም ቱጃር ሆኗል። እንዴት ቱጃር አይሆን፣ ገቢው ባራት ማዕዘን ይጉርፋል። የቡናው እርሻ፣ የቢና ቤቱ ንግድ፣ ኳላም በድንገት በመኪና አደጋ ከሞቱት፣ የሦፊያ አባትና እናት የተወረሰ፣ ጠቅላላ ሀብትና ንብረት፤ (ለሀብታቸው ሲባል፣ መኪናቸው ውስጥ ፊንጅ አስቀምጦ ያስገደላቸውም ራሱ ነው እየተባለ ይጠረጠራል) በሺ አለቃነት ሥልጣኑ፣ ያንድ ክፍለ ጦር አዛዥ በመሆኑ፣ ካካባቢው በየምክንያቱ ከሚያጋፍፈው ሀብት ጋር ተደምሮ፣ ቢጠሩት የማይሰማ፣ የነጠጠ ሀብታም ለመሆን በቅቷል። እየዘረፈ ባገኘው ሀብቱም፣ ድፍን የሲዳሞ ሕዝብ ያውቀዋል። ያከባቢውንም ጭቁን ሕዝብ፣ በፈፀመበት ግፍ የማያዝንበትና የማያማርረው ሰው የለም።

ሁኔታውያን፣ በሁለቱም በኩል፣ ይህን መልክ ይዘው እንዳሉ፣ የየካቲቱ አብዮት እንደ ከባድ የክረምት ነጐድጓድ፣ ግምግም ማለት ጀመረ። አብዮቱ የምዝብሮቹን በቀል ለመወጣት፣ የበዘበዞችን በር ማንኳኳት ጀመረች። እንደ መቅድማዊ አመጣጡ ቢሆን፣ ሕዝባዊ መልክ ስለነበረው፣ ለአብርሒት ደስታ፣ ለወንድሚ ግን ሀዘን ፈነጠቀ። የኳላ መፈክሩ ግን፣ በወታደር አርማ ላይ የተቀየሰ በመሆኑ፣ የወንድሚን ዘራፊነትና ሀብታምነት ሸፍኖለት፣ የሐረር ምሩቅ ወታደርነቱን ብቻ አንፀባርቆ፣ የአብዮቱ ቀኝ እጅ አድርጐ አቀረበው። የአፍለኛው ዐብዮት ሁኔታ ይህን መልክ ከማሳየቱ በፊት ግን፣ ዐብዮቱ የመጣው ለነአብርሒት ነው በሚል ፍራቻ፣ የበቀል በትር ታወርድብኝ ይሆናል ብሎ በማሰብ ተምደርድሮ፣ ላለፈው ይቅርታ ሊጠይቃት፣ በወር ሦስት ጊዜ ያህል ከሲዳሞ፣ አለችብት ከተማ እየሔደ ይፈልጋት ነበር።

በዚህ ሙከራው፣ ባንደኛው ቀን፣ ድንገት ባገኛት ብሎ ከቤተሰቦቹ ዘንድ ቢሔድ፣ እንዳጋጣሚ አገኛት። አብርሒትም፣ መለስተኛ ጊዝያዊ የነፃነት ትንፋሽ፣ በዐብዮቱ መፈንዳት ተሰምቷት ስለነበር እንደሌላው ጊዜ፣ ወንድሚን ለመዝጋት አላሰበችም። እንዲያውም ልኩን ልትነግረው ፈልጋለች። ጥቂት ያሳዘናት፣ እነዚያ መከረኛ ወላጆቿ በመካከላቸው ሆነው፣ የአለመግባባታቸውን መሠረተ-ምክንያት

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመጀመርያ ጊዜ በይፋ ለማወቅ መብቃታቸው ነው። ቢሆንም፣ ጪዋነት ባልተለየው አቀራረብ እንዲህ አለችው፤

"ስማ፣ ያንድ ቤተ-ሰብና ያንድ ወላጆች ልጆች ብንሆንም፣ በመደብ አስተሳሰብ አንገናኝም። ያንድ ሕዝብ ወገን፣ ያንድ ሀገር ዜጋ ብንሆንም፣ ጉራችን ለየቅሉ ነው። ያንድ ወጥ-ባሕል፣ ልምድና አከባቢ ውልዶች ብንሆንም፣ ግባችን የተለያየ ነው። ባንድ መልክ ያደግን ብንሆንም፣ በተዥጐረጐረ ባሕርይ ጉልምሰናል። እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ልዩነቶቻችን፣ ፍላጐታችንን ሁሉ ሳይቀር ለያይተውታል። ስለዚህም፣ ለኔ የሚጣፍጠኝ አንተን ይመርሃል። ለኔ የሚጥመኝ አንተን ያቅርሃል። እኔ አጋም ላይ ብተኛ አይቆረቁረኝም፣ አንተ ግን እብቅ ላይ ብትተኛ ይጐረብጥሃል። እኔ ተጀምሮ እስኪጨረስ ሕዝባዊ ነኝ፣ አንተ ግን የማን ወገን እንደሆንክ፣ የተሰለፍክበት የሙያ ምርጫህ መስክሮብሃል። እኔ ለማምንበትና ለቆየሁብት አቋም ታማኝ ነኝ። አንተ ግን ያደግህበትን ዐላማና ግብ፣ በያጋጣሚው የምትለዋውጥ፣ ወላዋይና ከዳተኛ ነህ።

... ዛሬ የመጨረሻ ዕድል ሰጥቼህ የማነጋግርህ፣ ወላጆቻችን ምንነትህን እንዲያውቁና፣ በተለይም ሁለታችንም፣ ካንድ አብራክና ካንድ ማኅፀን ለመገኘት መቻላችን፣ ብቻውን አንድ ዐይነት ሰዎች ሊያደርገን እንደማይችል እንድታውቀውና፤ ከዛሬም ጀምሮ የናት አባቴ ልጅ የሆነች እህት አለኝ ብለህ እንዳታምንና እንዳታወራ ላስጠነቅቅህ ፈልጌ ነው። በኔ ላይ የፈፀምከውን በደሎችና የጅ አዙር አሳዛኝ ሙከራዎችህን፣ ለወላጆቼ መንገር አልፈልግም። ግን መርሳት የሌለብህ፣ ለነዚህ በደሎችህ፣ ጊዜው ደርዘም እንጅ፣ አንድ ቀን ፍርዳዊ ዋጋህን ታገኛለህ ... " ብላ ንግግሯን እንደጨረሰች፣ ወጥመድ እንዳደናቀፋት ቆቅ ቱር ብላ ወደ ውጭ በረረች። በርግጥም ጪከና ኖሯል፣ ወላጆቿም ሆኑ ወንድሚ ፈልገው አላገኟትም።

እነዚያ ያልታደሉ እናትና አባት "እዩዩአቸውን" ይዘው ከቤታቸው ሲቀመጡ፣ ያ የእህቱ ንግግርና ማስጠንቀቂያ ያናወዘው፣ እሷን ካላጠፉ በሰላም እንደማይኖር ተሰምቶት፣ አሠሣ ገባ። ባስቸኳይም፣ ያዲሱ መንግሥት ቀንደኛ ጠላት መሆኗን፣

ለሚመለከተው ባለሥልጣን አመልክቶ፣ በደንብ እንድትፈለግ አዘዘ። ምድረ ነጭ ለባሽና ሠላይ፣ በዚያን ቀን አብርሒትን ፍለጋ ያልደረሰበት ቦታ አልነበረም። አብርሒት በጠፋች በማግሥቱ፣ ደብረ ብርሃን መዳረሻ ላይ ከምትገኝ፣ ቀላጢ ከምትባል ከተማ አውራ ጉደና ላይ፣ መኪናዋ ተገኘች። እሷ ግን የውኃ ሽታ ሆናባቸው፣ እስከ ዛሬ አላገኟትም። ወንድሟም፣ የገዛ እህቱን የመንግሥት ጠላት መሆኗን በመጠቆሙ፣ ልዩ ሽልማትና ልዩ የደሞዝ አበል በመስጠት፣ ታማኝነቱን አደነቀለት መንግሥት ፤ .

ይህ እንዲህ እንዳለ፣ ዐመታት ተጓዙ። ለካስ አጅሬት አብርሒት፣ ከፋኖ ገዳሟ ገብታ ኖሯል። የሠፈረችበት ጉራ፣ የታጋዮች መናኸሪያ የሆነው፤ ለአሻፈረኝ ባይ፣ ባመኾነቱ የታወቀውና የራሱ የሆነ የተፈጥሮ መከላከያ ያለው አርማጭሆ የሚባለው በረሃ ነው። ያኔ በመኪናዋ ሆና የጠፋች ጊዜ፣ ቤንዚኗ በማለቁ ከደረሰችበት ሥፍራ ተነስታ፣ አርማጭኾ ድረስ ለመጓዝ ወራት ፈጅቶባታል። ያን ጊዜ ከመንገዱ ጣመን የተነሣ፣ ብዙ ሥቃይ ቢደርስባትም፣ ዛሬ በረሃውን ለምዳው ከምንም አትቆጥረውም።

ርግጥ ከበረሃው ንዳድና፣ ከትግሉ ውጣ ውረድ የተነሣ፣ ቀድሞ የነበራት ውብትና ላህይ ተሟጦ ጠፍቷል። ያ ሀር ያስንቅ የነበረ ዞማ ፀጉሯ፣ ዛሬ አለመጠን ጉፍሮ፣ አነር ከነግልገሎቹ መደበቅ የሚችል ዱር መስሏል። እልያ አለንጋ ይመስሉ የነበሩ ጣቶቿ፣ ቁሩና ዐመዳዩ፣ ሐሩሩና ንዳዱ ተፈራርቆባቸው፣ መጋዣ መግረፍ የሠለቸውን ጉማሬ ይመስላሉ። የጣቶቿ ጥፍሮች፣ የጠመንጃዋ ቃታ ሞርዷቸው፣ ካረጀ ያንበሳ መዳፍ ጋር ይነፃፀራሉ። ያ፣ መሸት የጀመረ ወይን ይመስል የነበረው የገጿ ላህይ፣ ድራሽ አባቱ ጠፍቶ፣ በምትኩ በፊቷ ላይ አፍጠው የሚታዩትን አጥንቶች አንድ ሁለት ብሎ መቁጠር የቻላል። ያ ጠንበለል ይመስል የነበረ ማራኪ ቁመናዋ፣ ዛሬ ሽንቅጥ ብሎ፣ ቤቴ ብላ ላለችበት በረሃዋ፣ ነብር አስመስሏታል። አጭር ቁንጣዋን ታጥቃ፣ እጀ ጉርድ ኮቷን አጥልቃ የጠፍር ጫማዋን ተጫምታ፣ ካንገቷ ላይ በጠፍር ተጠልቀው፣ በደረቷ ላይ የሚጨፍሩ፣ መርፌ ቁልፍ፣ ወረንሎ ኩክ ማውጫና አነስተኛ የነተብች የጨርቅ ከረጢት

t.me/OLDBOOKSPDF

አንጠልጥላ፣ ከግራ ትከሻዋ ላይም፣ የሥንቅ ማከቻ አኩፋዳዋንና አንዳዲም ቦምብ የምትይዝበትን ስልቻ አንግባ፣ በስተቀኝ ትከሻዋ ላይም ሌት ከቀን የማይለያትን "መቅጫ" ብላ የሠየመችውን ጠመንጃ ይዛ ላያት ሰው፣ አብርሒት ጀግና ወንድ እንጅ፣ በጭራሽ ሴት አትመስልም።

ትክሳ፣ ትጥቁር እንጅ፣ ወዘናዋ ጨርሶ አልተሟጠጠም። ስትስቅ፣ የጥርሷ ውጋጋን፣ ጨለማ ይገላምጣል። ኩልል እያለ የሚውጣው ድምጿ፣ የበረደውን ሰው ያሞቃል። ጠቅላላ ሰውነቷ ኩምጭጭ ይበል እንጅ፣ ያላት ዐቅምና ብርታት ከብረት ይጠነክራል። ግርማ ሞገሷም ይገላምጣል ፤ አብርሒት በዚህ ሁኔታ ነው፣ ያርማጭኾን አካባቢ፣ ፒያሣዋ፣ ሲነማ ቤቷ፣ ቪላዋ አድርጋ፣ ለአመታት ቆይታ የምትኖርበት። ፀለምት መናኸሪያዋ ሆኗል። ድሮ የለመደችው መጠጡ፣ ፍትፍቱ፣ መኪናው፣ ሣፋው፣ ምናምኑ፣ ዛሬ አርማጭኾን ለምዳ፣ ምንም ትዝ አይላት። አንዳንድ አዲስ መጥ ታጋዮች፣ ከቦታው እንደመጡ ሰሞን እንቅፋት እንኳ በመታቸው ቁጥር፣ ሲበሳጩና ለዚያ ዓላማ ወስነው የመጡበትን ቀን ሲረግሙ ስትሰማ፣ "ጓዶች አይዟችሁ ፤ እያደር ትለምዱታላችሁ" እያለች ታፅናናቸዋለች። እሷም በበኩሏ፣ የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝብ ብሶት ለመበቀልና አዲስ የኅብረተ–ሰብ ሥርዓት ለመመሥረት፣ አርማጭኾን ተለማምዳ ትግል ስታካሒድ ዐመታት አልፍታል። ዛሬማ ትጥቁም፣ ሥንቁም ስላደገ፣ ታጋዮችን ይጋብዛል ॥

አብረሒት፣ በተመደበችበት የኢሕአሠ አንዱ ኮማንዶ ውስጥ፣ ብዙ ጀብዱዎችን የፈፀመችና፣ በከፈለችው መሥዋዕትነትና፣ የሞራል አራአያነት በጠቅላላው ሠራዊት ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትን ያተረፈች ናት። የታጋይነት ሙያዋ በጦር ሜዳ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፣ ያለችበትን የኮማንዶ አባሎች በማነቃቃትና ከፍተኛ የዐብዮት መንፈሣቸውን እንዲጠብቁ ለማድረግ፣ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በማዘጋጃት፣ ያበረከተችው ድርሻ፣ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ሌላው ሌላውን ተግባሮቿን መጥቀስ እንኳ ባይሰፈልግ፣ የሚከተለውን አለማውሳቱ ከበደል ያስቆጥራል።

ከግዳጅ መልስ ማታ ማታ፣ ካርማጭኾ ዋሻቸው፣ ታጋይ ጓዶች በሙሉ ለእረፍት

ሲገናኙ፣ የዕለቱን ሁኔታ ከተወያዩ በኋላ፣ አብርሒት በየቀኑ ትምህርታዊነት ያለው የመዝናኛ ጨዋታ ታቀርባለች። የሚነድ ዕንጨት ያገኙ ለት፣ እሳት አንደው ዙርያውን ከበው፣ ጨዋታው በሷ መሪነት ይቀጥላል። ካሰቂኝ ጨዋታዋ አንዱ እንካ ተጠየቅ ነው።

"እንኪያ ተጠየቅ" ትጀምራለች አብርሒት፡

"በምን ልጠየቅ" ይላል አንዱ ጓድ ይነሣና፡

"በወጪፎ" ትለዋላች አብርሒት ትመልስና።

"ምን አለሽ በወጪፎ" ብሎ ይጠይቃታል አንዱ ጓድ፣

"ብረጌኔሽ ታየኝ ያ ቆዳው ተገፎ" ብላ ትመልሳለች ።

ሌላው ጓድ ወዲያው ተነስቶ፣ እኔ ሌላ መልስ አለኝ ይልና፡

"ያ ወልደ ሒትለር ኖሯል፣ ለካስ ባዶ ቀፎ ነው" የሚል ይሠጣል።

ሌላው ደግሞ ይነሳና፣ እኔ የተለየ መልስ አለኝ ፣

"ያንን ደርግ አየሁት፣ ከንፈሩ ተንሻፎ፣ ነው ሲል ይመልስና፤

በሙሉ ሣቃቸውን ያስነኩታል።

አንዱ ጓድ ይነሳና፣ አብርሒትን ሌላ ተጠየቅ እንድትሰጥ ይጠይቃታል። እሷም ምንጊዜም ዝግጁ ናትና፤

"እንኪያ ተጠየቅ" ትለዋለች

"በምን ልጠየቅ ?" ይላታል፣

"በፋሽስት" ትለዋለች

"ምን አለሽ በፋሽስት ?" ይላታል፤

"የድሮውን ሒትለር፣ ዛሬ አገሬ አየሁት !" ብላ ስትመለስ፣ እያንዳንዱ ታጋይ ጓድ፣ አርማጮኽ ዋሻ ውስጥ መሆኑን እስኪረሳ ድረስ፣ የኩረኩሩትን ያህል ይስቃል።

አብርሒት፣ የጓዶቿ ሣቅ ገና ሳያልቅ ሌላ ጨዋታ ወዲያው ትተካለች። ድምፃዊት በመሆኗ፣ ያቅራራች እንደሆነ፣ የማይነሽጠው ጓድ አይገኝም። የምታዘወትረው፣ "የተው ጉራው" ቀረርቶ ሲሆን በተለይም፤

"ከል ጭኖ፣ በላ ግኖ፣ በል ጭኖ ጓዶች

t.me/OLDBOOKSPDF

ዐብዮት ያመጣል፣ ድልን አንድ ቀን !" የሚለው እንጉርጉሮዋ፣ መተከዥዋ ብቻ ሳይሆን፣ ማነቃቂያዋም ጭምር ነው። አብርሒት ታጋይ ጓዶቿን ለማዝናናት በዚህ ብቻ አትወሰንም። ሣቅ በሣቅ የሚያደርግ የቀልድ ጨዋታም አላት። ከዚህም ውስጥ፣ ጓዶች በሙሉ፣ ሰምተው ሰምተው የማይሰለቹት ቀልድ፣ የሚከተለው ነው።

"አያ ብረጌዥኔሽ፣ ለሁለተኛ ጊዜ በቻውሴስኮ ተጋብዞ ቡዳፔስት ይሄዳል። ጉብኝቱን በጀመረ በሦስተኛው ቀን ካጌት ቻውሲስኮ ጋር እየተዝናኑ የግል ጭውውት ለማድረግ፣ ቡዳፔስት ከታወቀው አንድ ረዥም ሕንፃ ጫፍ ላይ ከሚገኝ አንድ የመዝናኛ ሳሎን ውስጥ፣ ከተማውን ቁልቁል ወደ ታች እያዩ ጭውውታቸውን ይቀጥላሉ። አጌት ቻውሴስኮ ድንገት ትዝ ብሎትና

"ጓድ ብረጌነሽ ! ሕዝቡ ዝንባሌው እንዴት ነው ? አሁን በሙሉ ተረጋጋልህ ? ተቃዋሚዎችህስ በሙሉ ጠፉልህ ?" ሲል ይጠይቀዋል።

"እንዴታ ጓድ ! ሕዝቤ ከመረጋጋት አልፎ፣ ሕዝባዊ መሪ መሆኔን አምኖ በገዛ ፈቃዱ፣ ያለአንዳች አማራጭ በማቅረብ፣ ለኮመንስት ፓርቲ ፅንስ ለሆነው ድርጅት፣ ሊቀ ወንበር እንድሆንለት ከመምረጡም በላይ፣ እያንዳንዱ የህገሬ ዜጋ፣ ከገዛ ነፍሱ አብልጦ ነው የሚወደኝ" ብሎ በኩራት ይመልስለታል።

"አይ፣ ባጭር ጊዜ እንኳ ያን ያህል ላይወድህ ይችላል ! እኔ እንኳ ይህን ያህል ዘመን ገዥቼው፤ ዛሬም ቢሆን ያለኝ የተቃዋሚ ብዛት፣ ከራስ ፀጉሬ ቢበዛ እንጅ አያንስም !" ይለዋል፣ እውነቱን እንዲነግረው በመጋበዝ።

"ምን ማለትህ ነው አጌት ብረጌነሽ እኔ የምነግርህን አታምንም ማለት ነው እንዴ !" ይላል ቻውሴስኮ እንደመሣቅም እንደመቆጣትም ዐይኖቹን እያቁለጨለጨ።

"በጣም በዛ ማለቴ ነው እንጅ፣ ሕዝቡ በጠቅላላው አይውድህም ማለቴ አይደለም ! ግን እንዲህ በሙሉ አንደበትህ፣ ሕዝቡ በሙሉ ይወደኛል ስትል፣ ምን ተጨባጭ ማስረጃ ይዘህ ነው ?" በማለት፣ በዚያ የሚጐመዝዝ ፊቱ የፈገግታ ገጽታ ብልጭ አደረገለት።

“ምን ያህል እንደሚወደኝ፣ ሌላ ማስረጃ ከመዘብዘብ፣ ለምን እዚሁ በዓይንህ አላሳይህም ! እያንዳንዱ ዜጋ በሕዝባዊነት መሪነቴ እምኖ፣ ለኔ ትእዛዛዊ ፍቅር ሲል፣ ለሕይወቱ ሳይሳሳ እንደሚሠዋልኝ እዚሁ አሳይሃለሁ !” ብሎ ከፋከራ ባላነሰ መቀበጥበጥ ተናግሮ፣ አጠገቡ ከነበሩ ፈጣን ጋሻ ጃግሬዎች አንዱን ይጠቅስና፣ “እገሌ፣ እገሌ፣ ባስቸኳይ እዚህ እንዲመጡ ጥራቸው” ብሎ ትእዛዝ አስተላለፈ። ወዲያው ተኩልኩሎው እንደመጡም፣ ካጠገቡ የሚገኝ አንድ መስኩት ከፍቶ በመጠቆም፤

“ቆራጥነታችሁን ለማሳየትና፣ ለኔም ሕዝባዊ መሪነት ፍቅር ስትሉ ለሞት እንኳ ቢሆን ወደኋላ እንደማትሉ፣ ጓድ ብሬዝኔቭ ዐይቶ ለማረጋገጥ ፈልጓልና፤ በል እንግዲህ ጉብዝ ! በዚህ መስኩት አንድ በአንድ እመረኝ !!” ብሎ፣ እንደ አራስ ነብር ዐይኖቹን አጉርጦ፣ እንዳያዋርዱት በማስጠንቀቅ፣ ትዕዛዝ ሰጠ። ተወርውሬ አልከሠከሰም በማለት ለጊዜው አሻፈረኝ ቢልም፣ ኋላ እንደ ማይቀርለት የሚያውቀው፣ ያ ምሥኪን ጀሌው ሁሉ፤ ብድግ እያለ በመስኩቱ ጤና ይስጥልኝ! እየዘለለ፣ በዚያ መስኩት ሶተመሪና ! ሦስቱ ያህል እየተውዘገዘጉ ወርደው ሲከሠከሱ፣ ያይ የነበረው ብሬዝኔቭ በሁኔታው ደነገጠና ከተቀመጠበት አፈፍ ብሎ ተነስቶ፣ አራተኛው ሰው ሊዘል ሲል፣ መላ ዐካሉ ወጥቶ የግራ እግሩ እንደቀረ፣ አፈፍ አድርጉ በመያዝ፣ ከመለሰው በኋላ፣ ወደ ቻውሴስኮ ዞር ብሎ “በተናገርከው ሁሉ አምኛለሁ !! የቀረበው ማስረጃ ይበቃኛል። ግን እነዚህን የቀሩትን ለመዝለል የተዘጋጁ ሰዎች አንድ ጥያቄ እንድጠይቃቸው ፍቀድልኝ” ብሎ ባየው ሁኔታ፣ ተደናግጦና ተሸብሮ፣ ጥያቄ ያቀርባል።

“በደስታ !” ሲል ጓድ ቻውሴስኮ የመጠየቅ ፈቃድ ይሰጠዋል።

“ሳትደብቁ ንገሩኝ ! ለመሆኑ በምን ዐላማና ግብ ተነስታችሁ ነው፣ በዚህ ዐይነት ቆራጥነት ተዘጋጅታችሁ፣ የቻውሴስኩን ትዕዛዝ በማክበር ለሞት መሥዋዕትነት የቀረባችሁት ?” ሲል አድናቆት በዋጠው፣ ያነጋገር ዘዬ ጠየቃቸው። የቀሩት ሦስት ነበሩና፣ ብዙ ጊዜ ተማክረውብትና ተዘጋጅተውበት የመጡበት ይመስል፣ እንደ አንድ ዐካልና እንደ አንድ መንፈስ በመሆን “ከቻውሴስኮ ጋር ለብቻ ከመኖር ይልቅ፣ ሞት ይሻለናል ብለን ነው !!” ሲሉ መለሱለት።

t.me/OLDBOOKSPDF

... አብርሒት ይህን መሰሉን ቀልድ ለጓዶቿ ስታጫውታቸው፣ ያ የበረሀ ሌሊታቸው፣ ሳይታወቅ የሚነጋበት ጊዜ ነበር። ቀልድ ብቻውን እንዳያስለቻቸው በማሰብ፣ አልፎ አልፎ በዚያ ማራኪ ድምጿ፤

“ባርማጮኽ ዋሻ፣ ቅጣው በጄ እስካለች፤

ማንም አይደፍረኝም ነፃነት ከኔ ነች !” እያለች ስታንጉራጉር፣ ያካባቢዋ ያርማጮኽ ገረገንቡና ገደል ማሚቶው ሳይቀር፣ በሚያስተጋባው ጃዙ ያጅባታል።

በዚህ ዐይነት ሁኔታ፣ አብርሒት ከመሰል የበረሀ ጓዶቿ ጋር፣ ትግል ስታካሒድ ረዥም ጊዜ ሆኗታል። ያብርሒት ጣትና፣ የጠመንጃዋ ቃታ፣ በቃል ኪዳን የተጋቡ ይመስል፣ ለደቂቃ ያህል እንኳ ተለያይተው አያውቁም። የጭቁኑን ደም ለመበቀል፣ ባካባቢዋ የሚገኘውን ሠራዊተ-ፋሽስት በየጉራው ስታራውጥ ላያት፣ ወንድ ነኝ ያለ ጉብዝ አይስተካከላትም። በዚህም ዐብዮታዊ ተግባሩዋ በሠራዊቱ ውስጥ፣ ወደር የማይገኝለት ዝናና ትግላዊ ክብር ለመቀዳጀት በቅታለች።

አብርሒት፣ ከምድብ የኩማንዶ ዩኒቷ አሥር አባሎች ጋር ሆና፣ በወዲያኛው ዐመት አንድ ቀን ለግዳጅ ትሠማራለች። ከተሠማሩበትም ጉራ ላይ፣ አንድ የጠላት ባታሊዎን ገጥሚቸው፣ ቁጥራቸው፣ ከጠላት ሠራዊት ያነሰ በመሆኑ በ “አጥቅተህ ተደበቅ” የሽምቅ ውጊያ ዘዴ በመጠቀም፣ ላምስት ተከታታይ ቀናት ሲዋጉ ከቆዩ በኋላ፣ አስፈላጊውን ቅጣት ከሰጡና ከነሱም በኩል መሥዋዕትነት ከፍለው፤ የጠላት ጦር በማየሉ፣ ወደ ሠፈር ለመመለስ፣ መንገዱን ስለዘጋባቸው፣ ወደ ኋላ አፈግፍገው፣ ካንድ በረሀ ውስጥ ለሁለት ወራት ጊዜ ያህል፣ ከዋናው ብርጌዳቸው ተቋርጠው ያለስንቅና ያለትጥቅ፣ ቆይተው ነበር። ያን ጊዜ ነው፣ አብርሒት ከስንቅ መያዣ አኩፋዳዋ ጋር፣ ምን ትመስል እንደነበር፣ ቀደም ሲል የተገለፀችው። አለያ ግን፣ የዐብዮቱ ሠራዊት ያን ያህል ችግረኛ አይደለም። እንደውም፣ የኢሕአሠ ሠራዊት፣ በዚያ ለጋ ዕድሜው ውስጥ ያን ያህል ድርጅታዊ ትጥቅ አሟልቶ በመገኘቱ፣ ያላደነቁት፣ የዓለም ታጋዮችና የተራማጅ ድርጅቶች አይገኙም።

በዚያ የግዳጅ ቀናት፣ የነአብርሒት ሁለት ጓዶቻቸው በጦርነቱ ላይ ቢወድቁም፣

አስከፈናቸውን ሳያስማርኩ፣ ተደብቀው ከከረመብት ያርማጮኽ ዋሻ በክብር አሳርፈዋል፣ ያን ጊዜም ነበር፣ በዚያች አቁፋዳዋ ውስጥ የነበረች፣ የጓያ ጭብጦ ሥንቋን ስትቆረጥም የሰነበተችው። ከሁለት ወራት በኋላ ግን፣ የብርጌዳቸው የኋላ ደጀን፣ የት እንደጠፋ፣ እነ አብርሒትን ለማግኘት አሰሳ ሲያደርግ፣ ያ መንገድ የዘጋባቸውና ላምስ ቀናትም ያህል የተዋጉትን፣ የፋሽስት ጦር፣ ከሠፈረበት ጉራ ይደርሳል።

ጠላት የሰፈረው ክራባዳ ሥፍራ ስለነበር፣ ለሣምንት ጊዜ ያህል መሬት እንቅብ ሆና፣ እስክትንቀጠቀጥ ድረስ፣ ከባድ ጦርነት ሲያካሔዱ ቆይተው፣ እነአብርሒትም በቃፊርነት ካስቀመጡት፣ ያካባቢው ገበሬዎች አንዱ ካሉበት በረሀ ድረስ ሔዶ፣ ስለጦርነቱ ስለነገራቸው፣ ካሉበት ተጉዘው በሁለተኛው ቀን ማታ ምሽቱ ላይ በመድረስ፣ ከጠላት በስተጀርባ የሚገኘውን ኮረብታ ተገንና መከታ አድርገው፣ ሌሊቱን በጠይትና በቦምብ ሲቆሉት አደሩ። ንጋት ላይ ከማዶአቸው ሆኖ፣ ጠላትን ሲያንገረግብ የሰነበተው፣ የደጀን ብርጌዳቸው፣ የነሱን ድጋፍ በማግኘቱ፣ ከመጠን በላይ በጉራው ፍልሚያ ላይ አይሎ፣ የጠላት ሠራዊት ሰፍሮ ወደሚታኮስበት ረባዳ ሥፍራ፣ መገስገስ ጀመረ። ከፋሽስቱም ሠራዊት ወገን፣ ግብግቡን መቋቋም ያቃታቸው፣ አንዳንድ አምልጦ ለመሸሽ ወደ ኋላው ያፈገፍግ የነበረውን ተባራሪ የፋሽስት ወታደር፣ ከበስተጀርባው ሆነው እንደንብ የሚናደፉት፣ አብርሒትና ጓዶቿ፣ የዘለዓለም ምሱን ያቀምሱት ነበር። በዚያም ረባዳ ጉራ ላይ፣ ቀኑን ሙሉ፣ በዚያ የጠራራ ፀሐይና የበረሀ ንዳድ ውስጥ፣ ከምንጊዜውም የጦፈ ጦርነት ሲካሔድ ውሎ፣ ማታውን የጪበጣ ግብ ግብ ተጀመረ።

ወዲያው የጠላት ጦር ተመታና፣ ማታውን ምድረ-ፋሽስት ትጥቁን እየፈታ መለመላውን፣ ወደኋላው እየመረሸ፣ እግሬ አውጭኝ ማለት ጀመረ። ማምለጥ ግን አልሆነለትም። እነአብርሒት፣ ከበስተ ጀርባው መሽገው የሚራወጠውን ባንዳ ሁሉ፣ በቀላሉ መማረክ ጀመሩ። መንፈቀ-ሌሊት ላይ፣ በሩቅ ይሰማ የነበረው የጥይት ጩኸት ሁሉ "ጭጭ በል"፣ ያሉት ይመስል፣ ጉራው ረጭ አለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የነአብርሒት ዩኒት፣ እያንዳንዱ ጓድ፣ ካምስት ያላነሰ የፋሽስት ባንዳ ወታደር ሲማርክ፣ አብርሒት ብቻዋን አሥሩን ትማርካለች። ሌሊቱ በጪረቃ ብርሃን የደመቀ ስለ ነበር፣ ጓዶቹ ከያሉበት ሥምሪታቸው ተጠራርተው፣ ከነ ምርኮቻቸው ጋር፣ አንድ ቦታ ላይ ተሰበሰቡ። በዚያም ሌሊት፣ ከስልሳ ያላነሱ የጠላት ወታደሮችን ማርከው፣ እጅ እጃቸውን በልጥ ጠፍረው፣ በስምንት ጠመንጃቸው አግረው፣ እስኪነጋ ካቆየ በኋላ፣ ጉሕ ቀዶ ማለዳ ላይ ምርኮአቸውን ሲመለከቱ፣ የቆላ መጋዣ ከመሳሰሉት ምርኩኞች ውስጥ፣ ለካስ፣ የአብርሒት ወንድም የነበረው፣ ያ ሻለቃ ከመሐላቸው ኖሯል።

አብርሒት እንደ ወንድ ታጥቃ፣ የድሮ ገጽታዋ ሁሉ፣ በበረሀው ንዳድ ኃይለኛነት ተለውጦ፣ የቀድሞ ማንነቷ ስለማይታወቅ፣ ወንድሟ ምርኩኖው፣ ሊለያት አልቻለም። እሷ ግን ገና ስታየው አውቃዋለች። እሷንማ እንዴት ብሎ ሊለያት ይችላል? ያ፣ ሰብ ረገብ እያለ፣ ታችና ላይ ይል የነበረ ሽንጧ ሚሙቶ አልቋል። ያ ማራኪ ውብ መልኳ፣ ጠበንጃዋን አንግባ ቆላ ደጋ ስትራወጥ፣ ከሐሩሩና ከውርጩ ጋር ለመላመድ፣ ባደረገችው ስምምነት፣ ውብቷንና ወዘናዋን ገብራለች። ተመልካችን ይገረምም የነበረውን፣ ያን ውብቷን፣ በራሷ ፈቃድ ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ አሣልፋ በመስጠት፣ ለቆመችለት አብዮት ለውጣዋለች። ስለዚህም፣ ያ ድንባዥም ሻለቃ ወንድሟ፣ ከማራኪዎቹ ውስጥ፣ አንዷ የገዛ እህቱ የነበረችዋ አብርሒት፣ እንደምትገኝበት፣ ማወቅ ቀርቶ መጠራጠር እንኳ አልቻለም። አብርሒት ግን፣ በጂ እንደወደቀ ካወቀችበት ቅፅበት አንስቶ፤ ይህ ነው በማይባል ፈንጠዝያ፣ ልቧ ተነክቶ፣ ሁኔታውን ለማንም ሳትነግር በምሥጢር ለራሷ ብቻ ጠብቃ፣ ወደ ዋናው ደጀን ጦር ለመቀላቀል ምርኩኞቻቸውን በጠመንጃ እየነዱ፣ ጉዞ ጀመሩ። ከአንድ ሰዓት መንገድ በኋላም፤ ደጀኑ ጦር፣ በበኩሉ ያገኘውን የምርኮ ግዳይ ጥሎ፣ ለፍርድ ሲዘጋጅ ከነበረበት ሥፍራ ድንገት ከቸች አሉ። ስልሳውም የፋሽስት ሙርኩኞቻቸው፤ እንደ ብቅል አውራጅ፣ እጆቹን ወደላይ አንከርፎ እየተነዳ ገባ።

ከዚያም ምን ይነገራል ! በሕይወት መኖራቸውና መገኘታቸው ብቻ ሳይሆን፣

የዚያ የፋሽስቱ ሠራዊት ጦር መሪ፣ የነበረውን ሻለቃ ሳይቀር፣ የነበረበትን የስልሣ ምርኩኞች አጀብ፣ ይዘው በመምጣታቸው፤ በቀጣናው ጦር ሜዳ ከተሠማሩበት ጊዜ አንስቶ፣ በብርጌዳቸው ግዳይ ላይ፣ አጋጥሚቸው የማያውቁት ደስታ ተሰማቸው። ከመጠን በላይ ፈነጠዙ። የፈሽታ ጥይት ሩምታ፣ ማንጣጣትና ማንዲዲት ሆነ። በኋላ ስምንቶቹን የአብርሒት ጓዶች፣ የፍፁም ጀግናነት መግለጫ የሆነ የበረሃ አበባ ሸለሚቸውና፣ ሰላምታ መለዋወጥ ጀመሩ።

በማግሥቱ ቀትር ላይ፣ የተማረከው ሰው 150፣ የተገደለውም 150 መሆኑም ከራሳቸውም 10 ጓዶች መሠዋታቸው፣ ተነገረና፣ ላገኙት ድል የደስታ መግለጫ ንግግር፣ ለወደቁት ጓዶችም የመታሰቢያ ትውስት ተደረገ። የብርጌዱ መርማሪ ጓዶችም፣ የምርኩኞቹን ምርመራ ጨርሶ ስለ ነበር፣ በምሥጢር የሚጠበቀው ተጠብቆ፣ የቀረው ለሠፊው ሠራዊት ባደባባይ ተነበበ። በሪፓርቱ ውስጥም፣ ያ የማረኩት የፋሽስት ጦር፣ በጨካኝነቱ የታወቀው የነበልባል ብርጌድ ቅርንጫፍ ሠራዊት እንደነበርና፣ ብዙ ግፍና በደል በታጋዮችና በስሜን ጭቁን ሕዝብ ላይ ሕፃናት ልጃገረዶችን ከመድፈር አንስቶ፣ ሽማግሌና አሮጊቶችን ቤት እየዘጋ በእሳት እስከማቃጠል ድረስ፣ ወንጀል ይፈጽም እንደነበር፣ ከማስረጃ ጋር ተነገረ። ይህም ግፈኛ የፋሽስት ብርጌድ፣ ከሐረሩ የጦር አካዳሚ ምሩቅ በሆነ፣ አንድ ሻለቃ ይመራ እንደነበረና፣ ያም ሻለቃ ከነሕይወቱ በጓድ አብርሒት አማካይነት እንደተማረከ ሲነገር፤ ጭብጨባው ቀለጠ። ስብሰባው ከመበተኑ በፊትም፣ አብርሒት በስብሰባው ላይ ለመናገር መፈለጓን አስቀድማ ነግራ ኖሮ፣ ከተቀመጠችበት ተነስታ፣ የጭብጨባውን ማዕበል አብርዳ፣ መናገር ጀመረች።

"ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ አርነት የቆማችሁ ጓዶች!

በመራራው ትግላችን ውስጥ፣ ዛሬ ለኔ አዲስ ታሪክ አጋጥሞኛል። ብዙ ሐተታ የሚጠይቀውን ይህን ታሪክ፣ ባጭሩ ለመግለፅ ብሞክር፤ ሊገድለኝ ያሳድድ የነበረው፣ የናቴ የአባቴ ልጅ፣ የጥንቱ አንጀቴ፣ የኋላ ጠላቴ፣ ዛሬ በጄ ወድቋል። እናቴም አባቴም ወንድሜም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ብቻ እንደሆነ አምኜ፣ ለጋራው ትግል ከተሳማራሁበት ወቅት ጀምሮ፣ ብዙ መራራ ቅፅበቶችን አሳልፌ

t.me/OLDBOOKSPDF

አለሁ። ዛሬ ግን፣ የአብዮት መራራዊ ትግል ዋጋ፣ ድል ነውና፣ ይኸው፣ የማረክነው፣ የፋሽስት ጦር አዝማች ሆኖ የተገኘው ሻለቃ፣ የኔው የራሴ ታላቅ ወንድም የነበረ ነው። ለኔ ከዚህ የበለጠ ደስታ አላገኝም። ወደ ትግል ሜዳ ከመሠማራቴ በፊት፣ በየጊዜው ሊያስገድለኝ አስቦ ብዙ ሙከራዎችን አድርጉ ነበር። ዛሬ ግን ከኔ ቀድሞ ራሱ ወድቋል። ይህ ዓይነቱ ልዩ አጋጣሚ፣ ጠቅላላው የፋሽስት መንግሥትና ሠራዊቱ፣ ከጊዜ በኋላ፣ በተራማጅ ኃይሎች የማያቋርጥ ትግል፣ ተንኰታኩቶ እንደሚወድቅ፣ ይህ ዐይነቱ ድላችን ዐይነተኛ ምስክር እንደሚሆን አምናለሁ። የዛሬው አጋጣሚ፣ ራሱን በራሱ የሚገልጥ ልዩ አብዮታዊ ትንግርት በመሆኑ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ልናገር አልፈልግም። አጭሩን ንግግሬን ከመፈፀሜ በፊት ግን፣ ሁለት ነገሮችን እጠይቃለሁ።

የመጀመርያው፣ ዐብዮት "እየመረረ የሚጣፍጥ" አዝጋሚ ኪደት እንደሆነና፣ ታጋይ ጓዶች ሁሉ፣ ምንም ነገር ሳይፈትናቸውና ተስፋ ሳይቆርጡ እስከ መጨረሻዩቱ የድል ዋዜማ ቀን ድረስ፣ ትግላቸውን እንዲቀጥሉና የመራራ ትግላዊ አዝመራቸውን፣ ጣፋጭ ፍሬ በመጨረሻ ላይ ሊያገኙ እንደሚችሉ አስታውሳለሁ።

ሁለተኛው ጥያቄዬ ደግሞ፤ ይህ የተማረከ ግፈኛ ወንድሜ፣ ከሠራዊቱ ፊት ቀርቦ፣ እኔ እህቱ አብርሒት መሆኔ ተገልጾለትና ተነግሮት፣ በኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ላይ ለፈፀመው በደል፣ ራሱ የራሱን ፍርድ በሠራዊቱ ፊት እንዲሠጥ እጠይቃለሁ።" ብላ እንደጨረሰች፣ በጭብጨባና በጥይት እሩምታ፣ ጉራው አስተጋባ። ወዲያውም ሻለቃ ወንድሟ፣ የፊጥኝ ታስሮ፣ ሠራዊቱ ከተሰበሰበበት ቦታ ላይ ቀረበ። የማረከቸው የገዛ እህቱ አብርሒት መሆኗ ከተነገረው በኋላ፣ ሁኔታውን አይቶ እዲያረጋግጥ ተጠየቀ። የተቀለሰ ራሱን አቅንቶ፣ እንባ በሚያዘንቡ ዐይኖቹ ሊመለከት ቢሞክር ማየት አልቻለም። እህቱ መሆን እንዳለባት ግን፣ ለልቅሶ በሚሞክረው ድምፁ "እኔን ያለሷ ማንም ሰው ሊያጠፋኝ እንደማይችል፣ ድሮውን አውቃለሁ!" እያለ ተለፋደደ። በመጨረሻም ላይ፣ የፋሽስት ጦር አዝማች ሆኖ፣ በኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ላይ ለፈፀመው ግፍ፣

ራሱ ለራሱ ፍርድ እንዲሠጥ ተጠየቀ። በሰማው ዜናና ባጋጠመው ልዩ ሁኔታ፣ ሕሊናው ዞሮበት፣ መናገር ስለተሳነው፣ አንዲት ጣቱን ቀስሮ በማሳየት "አንዲት የአብርሐት ጥይት !" ሲል የግዱን እንባ እየተናነቀው ተናገረ። ወዲያውም "የአብርሐት ጥይት የተከበረ ነው። ላንተ ለርካሹ ሰው፣ ለፋሽስቱ ውሻ አይሆንም ! ክቡር ጥይቷን ያረክስባታል !" ሲል የብርጌዱ፣ የፊልድ ኮማንደር ተናገረና፣ ሻለቃው ያ ሁሉ ሠራዊት ፊት እንደቆመ፣ ሁለት ድግን መትረየስ ይዘው በቀረቡ፣ ሁለት ተዋጊ ጓዶች አማካይነት፣ ራሱ በሰጠው "ያንድ ጥይት ፍርድ" ብቻ ሳይሆን ከመቶ በማያንሱ፣ በሚያንገበግቡና በሚቆጠቁጡ የጥይት ጅራፎች ተገረፈ።

(በምሕርት ታልፎ ቢሆን ኖሮ፣ ራሱን በማረም ይሻሻል ነበርን?)

-------- * * * * ---------

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰ መ ነ



እትብቱ ተቆርጦ፣ካረፈበት ምድር፣
የሰው ልጅ ካልኖረ፣ ከራሱ ሕዝብ ጋር፣
ምን መትኖ ያገኛል፣ ያገር ልጅነቱ፣
በተዘጣ ዕድሜው፣ ከራቀ ከናቱ!
ወገኑና ሕዝቡ፣ እንደሆነው ሆኖ፣
ላብርት ካላደገ፣ ምን ያገኛል መትኖ?
ከወላጆቹ ጉያ፣ ካልኖረ በሥርዓት፣
እንዴት ሊል ይችላል፣ ልጅ ነኝ ለናት ላባት?
ምን ትርጉም ሊሰጠው፣ ባሕል ሆነ ሀገር?
ለጋ ልጅ ካደገ፣ በባእዳን ምድር!
በሐት "ተቆረጠ"፣ የሚባለው" እትብት"!
ሕፃን ሲሰት ነው፣ የልደቱን መረት
እንቦታትላውን፣ ያን ተዘጣ ሕፃን፣
ላይመርጥና ላይችል፣ራሱም መወሰን፣
ካገር ጉያ አውጥቶ፣ ለሌላ ባሕል መስጠት፣
ወንጀል ነው ኩነኔ፣ አስተዋጭ አለምሕረት።
ዓለም-አቀፍ መንፈስ፣ ቢሆን ለግጻበር፣
በጉልግላው እንጅ ፣ በጨትላው ባልነበር!
አሱም ይቻል ነበር፣ ግባር ውስጥ ግለተግር
ተዘጣ ልጅ ወሰዶ፣ ባርግዶ ከመንከር!!

መንደርደርያ

ሕፃናት በተፈጥሮአቸው ታቡላ ራዛዎች ናቸው። በጎሊናቸው አነፃር፣ ምንም ያልተፃፈባቸው ሌጣ ብራናዎች ! ማንኛውም ሰው፣ በለጋ ዘመናቸው ወቅት፣ የፈለገውን ቢፅፍባቸው፣ ሌጣ የጎሊና ሠሌዳቸው እንዳለ ይቀበለዋል። ማንም ሰው፣ የፈለገውን ቢኩልባቸው፣ የልቦና መድሔታቸው ያንፀባርቀዋል።

የዘመናችን የሀገራችን ኢሕዝባዊ መንግሥት፣ ለኢትዮጵያ ሕፃናት ተቀዳሚነት የሚሰጥበት አንዳንድ አጋጣሚዎች ቢኖር፣ ይህን የተፈጥሮ ልዩ ምሥጢር በመረዳቱ ነው። በየቀበሌው የኪነት ክበብ አማካይነት፣ የሆነ ያልሆነ ምናምንቴውን ሲለቀልቅባቸው ይውላል። የሕፃናት አምባ ብሎ በሠየመው፣ የእምቦቃቅላ–ሕፃናት ማጉሪያው፣ ፈልቶ ያልወጣለትን የግል ራሱን ጥንስስ ድፍድፍ ሲግታቸው ይውላል። ከዚህም አልፎ፣ ከጌታቸው ሀገር ሞስኮ ልኮ፣ ክለሳን ይበግታቸዋል። በርሊን ልኮ፣ የሰላይነት ኢስብዓዊ ተግባር ያስተምራቸዋል፣ በነዚህ ልዩ ልዩ የንፁሐን ሕፃናት መቅሠፊያዎች አንፃር፣ ወደ ሌላ ወዳጅ ሀገር በብዛት የተላኩትስ ሕፃናት፣ ለምን ዓይነት ግብ ተጠምቀው ሊዘጋጁ ይሆን ?

ዕድሜው እጅግ አጭር እንደሆነ፣ ገና ያልተከሠተለት፣ የኢሕዝባዊ መንግሥት፣ ለረዥም ጊዜ ምኞታዊ እቅዱ፣ የማያዘጋጀው ነገር የለም። ከነዚህ ዝግጅቶቹ ውስጥ፣ እንደ ጭቃ እየጠፈጠፈ፣ በአምሣሉ እየቀረፀ ለማውጣት፣ እንዳሻንጉሊት የሚጫወትባቸው ሠራዊተ–ሕፃናት ይገኙበታል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ፣ ለዚህ ግብ ወደ ውጭ የተላኩት ኢትዮጵያውያን ሕፃናት፣ ወላጃቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጀቱን አቃጥሎበታል። ከሀገሪቱ ውስጥ ያሻቸውን ሁሉ ሀብትና ንብረት እየዛቁ ሲወስዱ ያልቆጨውን ያህል፣ ከአብራኩ ተከፍለው፣ ከማኅፀኑ የወጡትን ልጆቹን፣ ያለወላጅና ያለተወላጅ ግላዊ ፈቃድ፣ በግድ እያንጠለጠለ ሲውስድበት፣ ልቡ እስኪደማ አብግኖታል። ሕፃናቱ ራሳቸው ቢሆኑ፣ ለመከላከል ያልባለቁና አቅም የሌላቸው በመሆናቸው፣ ዝም ብሎ ከመሔድ በስተቀር፣ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። መሔዱንስ ይሒዱ፣ የሆነው ሆኖ፣ በማያውቁት ሀገር፣ በዚያ ለጋ የሕፃናት እድሜያቸው ከተላኩ በኋላ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ያጋጠማቸው ሁኔታ ምን ነበር ? "ሠመነ" ከሔዱት ሕፃናት አንዷ ናት። ይህች እምቦቃቅለ ሕፃን፣ የገጠማት መከራና ፍዳ ሁሉ፣ ሌሎቹንም ሕፃናት የጐሸማቸው ስለሆነ፣ የሠመነ ታሪክ ስለሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ከርታታ ሕፃናት ጭምር የሚናገር ወኪልና ቀላጤ ነው። ወደ ተከታዮቹ ገጾች ሲያመሩ፣ የሕፃናቱን አሳዛኝ ሁኔታ ተመዝግቦ ያገኙታል።

እንደሚታወቀው ሁሉ፣ ማንኛውም ልጅ በተወለደበት ማኅበረ-ሰባዊ ባሕልና አከባቢ ውስጥ ሆኖ፣ ከወላጆቹ፣ ቤተ-ዘመዶቹ ባልንጀሮቹና ባጠቃላይም ወገኖቹ ጋር ሆኖ ቢያድግ፣ ሰብዓዊነትና የሰብዓዊነትም መብት ጭምር ነው። ይህ እስካልሆነም ድረስ፣ በአንድ ሀገር የተወለደ ሕፃን፣ በሌላ ሀገር እስካደገ ድረስ፣ የባዕድ ስሜት ተገዥ የማይሆንበት ምክንያት የለም። ለጋ ጎሊናው፣ ለባዕዳን አከባቢ በቀላሉ ተገዢ ለመሆን በመቻሉም፣ ጥንተ ባሕሉን፣ ቀስ በቀስ አጥፍቶ ልሙጥ ይሆናል።

በተለይም እንደ ኢትዮጵያዊ ያለውን ከባድ ባህል፣ እንኳንስ በባዕድ አከባቢ ተቀምጦ፣ ውስጡም እንኳ ሆኖ መንከባከብ ስለሚያስቸግር፤ እነይሉኝታ፣ እነአክብሮተ- ሰብ፣ እነ-ባሕርየ-ጪዋነት፣ እነጠባየ-ሽጋነት፣ እነትህትና፣ እነማስተዋል፣ ... ድራሽ አባታቸው ይጠፋል። ሕፃኑም፣ ላልተወለደበትና ዘለዓለም ለማይኖርበት ባዕድ ሀገር ባሕል፣ ባሪያ ሆኖ ይቀራል። የኋላ ኋላም፣ ከትውልድ ሀገሩ ቢመለስ፣ የባሕል ግጭት ተፈጥሮበት፣ መላ ሕይወቱ መቅኖ አጥቶ ይኖራል። በሔደበት ቦታ ሁሉም፣ ሁለት ወዥንብር የመታው ባሕል የተጫነ ሠረገላ በመሆኑ፣ መንገዶቹ ቅርቅፍት ይበዙበታል።


የየትኛውም ሕዝብ ቢሆን፣ የማኅበረ-ሰቡ አቋም መላላት ካልሆነ በስተቀር፣ ምንም ያህል ችግረኛ ቢሆን፣ የገዛ ራሱን እምቦቃቅላ ለጋ ሕፃናት፣ በባዕድ ሀገር ሞግዚትነት እንዲያድጉ አያደርግም። እንደ ኢትዮጵያውያን ያለ ባሕለ-ወዳድ ሕዝብ፣ ጪርሶ ካላበደና፣ ጪርቁን ጥሎ ካልወፈፈ በስተቀር፣ እንዲያ የሚሳሳላቸውን ልጆቹን ከጉያው አውጥቶ፣ ለሀገሩ ምድርም ሆነ፣ ለሚንገበገብለት ባሕሉ፣ እጅግ በራቀ ሀገር ውስጥ ልኮ፣ በባዕዳን ሞግዚቶች

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲያድጉ አያደርግም። በርግጥ ነካ አርጐት ካልሆነ በስተቀር፣ ተተኪ የሚሆኑትን ያዲስ ትውልድ ወኪሎች፣ ከባሕር ማዶ ልኮ፣ በባዕዳን ባሕል እንዲበከሉ በጭራሽ አያደርግም። የትኛውም ሕዝብ፣ ከገዛ አብራኩ የተከፈሉ፣ የገዛራሱን ልጆች፣ ለጋጠ-ወጥ የባዕድን ባሕል መጫወቻ አሻንጉሊት አያደርግም። ይህ አሳዛኝ ሁኔታ ግን፣ ምንም ያህል የተጠላም ቢሆን፣ ባሳዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ላይ፣ በዘመናችን ተፈጽሟል። ይች አጭር ታሪክ፣ የዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ምሥክራዊ ሥንክሳር ናት።

እዚች መጪረሻ ነጥብ ላይ፣ ላስታውሳችሁና ላስገነዝባችሁ የምፈልገው፣ "መጪረሻው-አያምር" እንደሚሉት ሆኖ እንጅ፣ በበኩሌ ታላቁ ታጋይ የዚያ ሀገር መሪ፣ የነብረ-ጊዮርጊስን ግዳጃዊ ምክር ተቀብለው እንዲያ ያለውን አስተዛዛቢ ድርጊት ፈጽመው ይሆናል እንጂ፣ በፊተኛው ዘመናቸው፣ ከእንደዚህ ዐይነቱ ድክመታቸው ባሻገር፣ ጉረቤታቸው ላይ የሚንጐማለለውን፣ የዘመናችንን ጭራቅ ኢምፔሪያሊዝም ገድግደው ያቆሙ፣ ታላቅ ጀግና በመሆናቸው፣ አድናቆቴ ፅንፍ የለውም።





"... እንጀራውስ ይቅር፣ ወጡ የታለ ?" አለች ሰመነ በስተጒኒ ግራና ቀኝ ማዕድ ላይ የቀረቡትን ጓደኞቿን እየጐሸመችና በሹክሹክታ እየጠየቀች።

"ዝም ብለሽ ብትበዩ ይሻልሻል ! አለበለዚያ እዚያ ግድግዳ ላይ የተሠቀሉት፣ ጭራቅ ከነነፍስሽ ይውጡሻል !" አለ በማስፈራራት፣ ከበስተቀኟ የተቀመጠው፣ ካብሮ ዘመት ጓደኞቿ ሁሉ ተንኰለኛውና ቀበጡ ኪሩቤል።

"ውነቱን ነው፤ ትላንትና ሞግዚታችን፣ ባለጌ የሆናችሁትን ልጆች ሁሉ እኛ የግድግዳው ላይ አስፈሪ ሰውዬ ይቀጣችኋል ብለን የለ !" አለች ሶስና፣ ጓደኛቸው ኪሩቤል ላቀረበው የማስጠንቀቅያ ምክር ድጋፍ እየሰጠች።

"የቀረበልሽን ዝም ብለሽ ብትጠርጊ ይሻልሻል" አለ ኪሩቤል፣ እያስጠነቀቀ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴ ምን ማለታችሁ ነው ! እኔኮ ወጥኮ በጣም ነው የሚጣፍጠኝ ! በተለይ ያኔ እማማ በእንቁጣጣሽ ዕለት የምትሠራው ወጥኮ፣ ከኮረሜላም ሆነ ከቸኮላታ ይብልጥ ያጓጓኛል ! ሲጣፍጥ ሌላ ነው ! እጅ ያስመጥጣል።" አለች ሰመነ፣ የናትዋ ጣፋጭ ወጥ ትዝ ብሏት እንባዎቿ በሁለት ዓይነቿ ዳር ዳር ቅዝዝ እያሉ።

"ጠብቂ ! እናትሽ ወጥ ታመጣልሻለች !" አለ ያ አብረው ከዘመቱት ወጣቶች ውስጥ፣ ሞላጫውና አሻፊው ኪሩቤል።

"እዚህ ሀገር እኮ፣ እንኳን ወጥ ሊሠሩ ቀርቶ፣ ራሱ ወጥ የሚለውን ቃል አያውቁትም። ሰመነ ! እባክሽን እኛ ሁላችንም ብንሆን ወጥ ብናገኝ ጠልተን አይደለም። ግን ባገሩ ውስጥ፣ በጭያሽ ስለማይገኝ ነው፣ አለፍላጉታችን ይህን ፓስታና ሩዝ ከመኩሮኒ ጋር የምንውጠው !" አለች ሶስና የሰመነን ፊት በማሐረቧ እያባበሰች።

"ሌላ ቀን እሺ፣ የዘወትር ቀን ስለሆነ፣ ማንኛውንም የሚያቀርቡልንን እንብላ ! ዛሬኮ የዕንቁጣጣሽ በዓል ነው ! ሌላው እንኳ ባይገኝ፣ እንዴት ያ የሚጣፍጠኝ ወጥ ይጥፋ ! እማማኮ ትዝ እያለች እያለች ... እያያለለችኝኝ..." ሰመነ፣ የናቷ ትዝታ፣ በዕንቁጣጣሹ በዓል ወጥ ምክንያት ተቀስቅሶበት እየተሠቀሰቀች ልቅሶዋን ታስነካው ጀመር።

"ኮምፓኜሮ ! ኮምፓኜሮ ! ምን ሆንሽ !" አለ ከበስተፊቷ ከጠረጴዛው ማዶ የተቀመጠው ሌላ ወጣት፣ የቀዘዘው እንባዋ፣ እየተንሰቀሰቀች ስታለቅስ በፊትዋ ላይ ሸረር እያለ ሲወርድ አይቶ።

"እሷ እባክህ፣ ወጥ ከአዲስ አበባ ካልመጣ ነው የምትለው !" አለ ያ ተንኮለኛው ኪሩቤል፣ እየሣቀ።

"እዚህም አንዷ የንጀራን ያለህ እያለች ትንሾኳሾክ ነበር !" አለ የበስተፊታቸው ልጅ።

"አብሲቱ ተጥሏል፣ ሲደርስ ይመጣልሻል፣ አትላትም" አለ ያ ኪሩቤል።

"ቀልዱን ተውና፣ ዛሬ መነጫነጫቸው ይገባቸዋል። እንዴት በዕንቁጣጣሽ ዕለት፣ በአዲስ ዓመት፣ ዓመት በዓል ምድር፣ ሌላው ቢቀር እንኳ፣ ወጥ አያዘጋጁልንም !

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህስ ጉዳይ እነሱን ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ደብሮናል !" አለ ከበስተፊታቸው ተቀምጦ ያለው ጓደኛቸው፣ የኪሩቤልን ቀልድ እያክቸለቸለ።

"አንተም ለካ አልጫ መረቅና ደሮ ወጥ፣ በዓይንህ ላይ ብዥ ብሎብህ ነሯል !" አለ ኪሩቤል፣ መልሶ በጓደኛው ላይ እያሾፈ።

"ሁላችሁም ድብርታሞች ናችሁ ! መቀለጃ ብታጡ፣ በጓደኞቻችሁ ታላግጣላችሁ ! አንድ እንኳ ጤነኛ ልጅ ከማሐላችን ላይገኝ ነው !" አለች ሶስና እየተቸች።

"አንቺን ደግሞ ምን ትዝ ብሎሽ ይሆን ? ቆሎ ወይስ አሹቅ ! ቀራረሬ ወይስ አረራ ?" ኪሩቤል ሶስናን ማሸሚጠጡ ነው።

"እኔስ !" አለች ሶስና እንደመቆጣት እየቃጣት፣ "እኔስ የናፈቀኝ፣ የናቴ ወጥና እንጀራ፣ ወይም አንተ እንደምትለው፣ ቆሎና አሹቅ ወይም ቀራረሬና አረራ ሳይሆን፣ ራስዋ እናቴ ናት !" አለች።

"ጠብቂ፣ ከሰማይ ትወርድልሻለች !" አለ ያ ኪሩቤል ይብልጥ እያበሸቃት።

ማዕድ ላይ ተቀምጠው፣ እንዲህ እንዲህ ያለውን ትዝታ እያነሱ ሲበሻሸቁ፣ የሰመነ የነፈረ ናፍቆት ገንፍሎ፣ ልቅሰዋን ቀጥላ ኖሮ፣ ያ ከበስተፊቷ የተቀመጠው ልጅ፣ ሞግዚታቸውን ካሉበት ክፍል ጠርቶ፣ ስለ ሰመነ ሁኔታ ይነግርና ሞግዚቷ



ይመጣሉ። ማልቀስ የተከለከለ ስለሆነና፣ ከዲስፕሊን ጉድለቶች እንደከፍተኛም

ስለሚቀጠር፣ ሞገዚቷ ወዲያው አጣድፈው ሰመነን ቢሮአቸው ይወስዷታል። ከሩብ ሰዓት ቆይታ በኋላ፣ ይዘዋት ይመለሱና ከነበረችበት የማዕድ ወንበሯ ላይ ካስቀመጧት በኋላ፣ የቀረበላትን መመገብ ስትጀምር አይተው፣ ተመልሰው ወደ ቢሮአቸው ይሔዳሉ። ሰመነም፣ ውስጥ ውስጡን እየተንሠቀሠቀች፣ የቀረበላትን ያለ ምንም ቅሬታ መጥረግ ጀመረች።

"ኻያ ወይስ አሥር ፣" አላት ያ ተንኰለኛው ኪሩቤል፣ ገና ተቀምጣ መብላት እንደ ጀመረች፤ ሞገዚታቸውም ካካቢያቸው እንደ ሔዱ አይቶ።

"ኻያ ይሆናል እንጅ ፣ መዳፍን አታየውም ፣ ፍም መስሏል ፣" አለች ሶስናን፤ እንደ ማስተዛዘንም፣ ደግሞም ምክሯን ስላልተቀበለቻት እንደ ማቋጪትም እየቃጣት፣

"ወጡን ወይስ እንጀራውን የሰጧት ፣" አለ ያ ኪሩቤል እየሳቀ።

ሲወረውረውም ሆነ ሲያነሳው አልታየም፤ ያ ከበስተፊታቸውም ያለው ልጅ፣ በኪሩቤል ቀልድ ተናዶ፣ ይበላው የነበረውን ገንፎ መሰል ሾርባ፣ ከነሣህኑ አንስቶ ከኪሩቤል ፊት ላይ ሲለድፍበት ብቻ፣ መላው ማዕድ ላይ የነበረ ወጣት በሁኔታው ይረበሻል። ደግነቱ ሣህኑ ከፕላስቲክ የተሠራ መሆኑ በጀ እንጂ፣ ከኒኬል ወይም ከመስተዋት የተሠራ ቢሆን ኖሮ፣ የኪሩቤልን መላ ገፅታ ወዲያው ባጪራመመው ነበር። በዚያ ግርግር አብዛኛዎቹ ደንግጠው፣ ግማሹ ሹካና ማንካውን ከወለሉ ላይ ሲጥል፣ የቀረው ደግሞ የሚመገቡትን ጠረጴዛ አናግተውት ኖሮ፣ ላጭርም ጊዜ ቢሆን፣ ቀበሮ ከመሐላቸው የገባችባቸው የበግ መንጋ መስለው ነበር።

"እኔ ሞገዚቷን መጥራቴ፣ ብሶቷን እንዲያበርዱላት፣ የለቅሶዋንም መነሾ ተረድተው፣ መፍትሔ እንዲፈልጉላት ነበር እንጂ፣ አንጠረኛ ያቀረበው የጋለ ብረት ይመስል፣ እጇን ፍም እስኪሆን እንዲቀጠቅጡላት አልነበረም አለ" ያ ከበስተፊታቸው የነበረ ልጅ፣ የለበሰውን ሸሚዝ እጅጌ ወደ ላይ እየጠቀለለ፣ ድብድብ የሚፈልግ ቢኖር እየተዘጋጀ። ምግብ አሰላፊዎቻቸው፣ አለወትሮአቸው፣ በውጥቱ እንደዚያ መሆን ተደናግጠው፣ የሚይዙትና የሚጥሉት ጠፋባቸው። የምግቡን አዳራሽ፣ ቱማታ ዋጠው። ከጥቂት፣ ዳር ላይ ካሉ ልጆች በስተቀር፣

t.me/OLDBOOKSPDF

በመላው ከመቀመጫቸው ተደናግጠው በመነሳት፣ ሁኔታውን ለማየት ይጣደፋሉ። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ሞገዚቶቻቸውም አልመጡም ነበር። ብቻ ያ ኪሩቤል፣ ፊቱ ላይ የተለጠፈበትን ገንፎ መሰል ሾርባ፣ በዐሥር ጣቶቹ ይቧጥጣል። ከመቀመጫውም አልተነሣም ነበር። በጣም የሚገርመው ደግሞ፣ እንደዚያም ያለ ሁኔታ ገጥሞት፣ መቀለዱን አላቆመም ነበር። ልጆቹን ሁሉ ያሣቃችው "[illegible] ... ሀገራችን ብንሆን ኖሮ፣ በዛሬው ቀን አባባዬ ሆይ ወይም ሆያ ሆዬ እንጪዋት ነበር ፤ ይኸ አሁን የምታዩት ድርጊትም፣ የእንቁጣጣሽ በዓል መስተናገጃ፣ የዚህ ያለንበት ሀገራችን ያበባዬ ሆይ ጪዋታችን መሆኑ ነው ፣" ያለው ፌዝ ነው። መጋቢዎቻቸው፣ ሞገዚቶቻቸውን ሊጠሩ ሔዶው ኖሮ፣ አምስቱም ሞገዚቶቻቸው ከተፍ አሉ። ወዲያው፣ የዕለቱ የምግብ ፕሮግራም ሰዓት የተፈፀም መሆኑን፣ ለሁሉም ልጆች ነግረው፣ ወደ የመኝታ ቤታቸው ሲበትኑ፣ ለዕለቱ ረብሻ ምክንያት የሆኑትን፣ አምስት ልጆች መርጠው የምርመራና የጠባይ ማረሚያ ብለው ወደ ሰየሙት፣ አንዲት ጠባብ ክፍል ወስደው ያሽጓቸዋል። ሰመነ፣ ሶስናና ኪሩቤል፣ ከቀሩት ሁለት ጓደኞቻቸው ጋር፣ በዚያች ክፍል ብቻቸውን በነበሩበት ወቅት፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው፣ ሞገዚቶቻቸውን የሚመክቱበትን መከላከያ ሐሳብ ይመሣጠራሉ። ያዘጋጁትም ዘዴ፣ "አንዱ መጋቢያችን ነው፣ ኪሩቤል ላይ ሾርባውን አውቆ ከነ ሣህኑ የለጠፈውና፣ እዚህ ሀገር መኖር አንፈልግም ፣ ለቅጣትም ሆነ ለሌላ፣ ሀገራችን እንድ ትመልሱን እንጠይቃለን" የሚል ነበር። "ሀገራችን መልሱን ከሚለው ርእሰ-ሐሳብ ላይ ለመነሳት፣ አሳማኝ የሆኑ ምክንያቶችን መደርደር ነበረባቸው። ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ፣ ያጋጠማቸውን ልዩ ልዩ ችግሮችና ብሶቶች፣ በየመልካቸው መወያየትና መተንተን ነበረባቸው። ለዚህ ዐይነቱ ዝግጅት፣ ያምስቱ ጓደኖሞች ጥፋተኞች መባልና በተወሰነች ትንሽ ክፍል ውስጥ መገለል፣ ጥሩ እጋጣሚና ምቹ ቦታ ሆኖላቸዋል። ለሁለት ዓዐመታት ጊዜ፣ በሕፃንነት ላጋ ዕድሜያቸው፣ ያለ ውዴታቸው ሲያመነዥኩ የኖሩትን የስቃይ ማዕድ ሁሉ፣ እንደገና ተንትነው በማየት፣ ማመስኳት የጀመሩት በዚያ ወቅት ነው። ቀደም ሲል

ግን፣ የሚፈፀምባቸውን በደል መተንፈሻ ቀዳዳ ባገኙ ቁጥር፣ በያጋጣሚው ለማጋለጥና፣ በትንሹም አቅማቸው ከማመጽ አልተቆጠቡም። ወላጅ አባቶቻቸው፣ የፋሽስት መንግሥት በፈጠረው ለራስመዳኛ ተብለው በተፈጠሩ፣ ምክንያት–የለሽ ጦርነቶች፣ በጦርነት ሜዳው በመውደቃቸው፣ የካሣን ይሉ የማባረርያ፣ ተብሎ በተዘየደ ጥበብ፣ ከአንድ የወላጅ ሀገር መናገሻ ከተማ ከሆነው ውስጥ፣ እየተማሩ እንዲያድጉ፣ የተበየነባቸው አሳዛኝ ወጣቶች ናቸው። ገና ዓላማው ተወጥኖ፣ ሐሳቡ ለወላጅ እናቶች፣ አንዳንድ ልጆቻቸውን፣ ለጉዞው እንዲያዘጋጁ ሲነገር፤ ባሎቻቸውን አለአግባብ ላጡት ወላጅ እናቶች፣ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖባቸው፣ ለወር ጊዜ ያህል፣ ለቅሶ በለቅሶ፣ እንባ በእንባ ሆነው፣ የወላጅ አንጀታቸው፣ እርር ትክን ሲል ሰንብቶ ነበር። ሕፃናቱቹም ቢሆኑ፣ ባጡአቸው አባቶቻቸው፣ የደረሰባቸው ሐዘን ገና እንፋሎቱ ሳይከስም፣ ከወላጅ እናቶቻችሁ ተለዩና፣ ባዕድ ሀገር ሒዱ፣ የሚል አስደንጋጭ መዓት ሲመጣባቸው፣ ሊደርስባቸው የሚችለውን፣ ሠቀቃውና ሆደ ባሻነት፣ ማንም ሰው ሊረዳው ይችላል።

ወደዱም ጠሉም፣ እናቶቻቸውንም ሆነ ሀገራቸውን፣ ከባሕላቸው ጋር ጥለው የመሔዱ ጉዳይ፣ ከላይ በጫና የወረደ፣ ፋሽስታዊ ትእዛዝ በመሆኑ፣ ዝም ብሎ ከመንጉድ በስተቀር፣ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። የህን ትእዛዝ ለመጣስ የሞኩሩ፣ ባለአንድዬ ልጅ የሆኑ እናቶች፣ አንድ ልጃችንን አንሰጥም በማለት፣ በማንገራገራቸው ብቻ፣ እውስጥ ይሆን ስመጥ፣ የት እንደደረሱ አይታወቅም። ከያሉበት ተሰባስበው፣ አዲስ አበባ ካለ አንድ የጉዞአቸው መዛጋጃ ሥፍራ በነበሩበት ወቅት፤ አለመጠን አግቶ ከነበረው፣ ከያንዳንዱ ተጓዥ ወጣት፣ በየቀኑ ይታለብ የነበረው የዕንባ ፍሳሽ፣ ከጋሎኖች አልፎ በርሜሎችን ሊያጥለቀልቅ ይችል ነበር። እንግዴን ከትብቱ በመቀሥ ተጉመዱትን ያህል ነው፣ እናቶችንም ሆነ ተጓዥ ልጆቻቸውን የተሰማቸው። አንዳንዶቹን እናቶችማ፣ ልባቸውን እንደመንካት አድርጓቸው፤

"ሞትና መለየት ምን አንድ አደረገው፣

t.me/OLDBOOKSPDF



እትብቱ ተቆርጦ፣ ከራቀ ከናቱ፣
ምኑን ሰው ይሆናል፣ የሰው ልጅነቱ!

ሞት ይሻል የለም ወይ ቁርጡ የታወቀው !" የሚለውን ዘፈን እያዜሙ፣ የለቅሶ ያህል ተጠቅመውብታል። "የልጆቻችን ሞግዚቶች እንሁን የሚሉትንም እንደ ሆነ፣ እዚሁ ሃገራችን መጥተው፣ ምን ዐይነት ሰዎች እንደሆኑ አይተናቸዋል። እነዚህን እምቦቃቅላ፣ ሕፃናት ከነዚያ ሕዝቦች ሀገር ወስዶ ማስተማሩ፣ የወደፊት ጥፋታቸው እንጂ፣ ልማታቸው አይታየንም።" በማለት፣ ቅን ሀሳባቸውን የሠነዘሩ ሰዎች ሁሉ፣ ሞተዋል ወይም እሥር ቤት ናቸው። ሕፃናቱ ሀገራቸውን ለቀው ለመሔድ ከየናቶቻቸው እየነጠቁ ሲያመጡ፣ የነበረውን ግዜያዊ ትርሢት ለመግለፅ፣ የየትኛውም ቋንቋ ቃላት ቢሆኑ ዐቅም አይኖራቸውም። በእንደዚያ አሸባሪ ግዴታ ተወስደው፣ ከሞግዚት ሀገር ከተማ ከደረሱ በኋላ፣ የመጀመርያውን ዓመት ጊዜ እንዴት እንዳሳለፉት መግለፁ፣ ቋንቋን አያስጠቅስምና፣ ዝም ማለቱ ይበጃል። የሕፃናቱ የመከራ ስንክሳር ይከፈትም ከተባለ፣ ራሳቸው በሦስተኛ ዐመቱ፣ የእንቁጣጣሽ በዓል ዕለት፣ የጀመሩትን የዐመፅ ዝግጅት ሲተነትኑ በነበሩበት ወቅት፣ የሆነውን ራሳቸው ይናገሩ።

"ጠባሳዬ ዛሬም እያመረቀዘ ነው ! ተመልከቱ !" አለች ሰመነ፣ የክንዷን እጅጌ ወደ ላይ እየጠቀለለች፣ የእንቅልፍ መርፌ እያሉ፣ ለዓመት ያህል ሲጠቀጥቋት የነበረውን ክንዷን እያሳየች፤ በዚያች ጠባብ የመቅጫ ክፍል ውስጥ እንዳሉ።

"ማን ያልቀመሰ አለ ብለሽ ነው፣ ለኛ የምታሳዪን ! ይልቁንስ እንዴት ባለ አቀራረብ ብንፅፈው ነው፣ ብሶታቸንን በጉልህ ሊያሳይልን የሚችል ?" አለች ሶስና፣ አቤቱታቸውን ለማቅረብ በሥውር እያዘጋጁ ነው።

"ለመጻፉ ችግር የለም ! ግን ቅደም ተከተሉን ማስተካከል ይኖርብናል !" አለ ያ ኪሩቤል በጸሐፊነት የተመረጠው እሱ ነበርና።

"ቅደም ተከተል፣ ስትል ምን ለማለት ፈልገህ ነው ?" አለ ያ ፊቱ ላይ፣ ሾርባ የቸለሰበት ጓደኛው።

"ቅደም ተከተል ስል፣ ያኔ ገና ወደ እዚህ አገር ልንመጣ ስንዘጋጅ፣ እናቶቻችን የሆኑትን መሆን፣ እኛን ከነሱ ላለመነጠል፣ ያደረጉትን የተቃውሞ ተጋድሎ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህም መነሻ የደረሰባቸውን ፍዳና ግፍ፣ ኋላም እኛ በዚህ በባዕድ ሀገር፣ እናቶቻችንም በሀገራችን ሆነው፣ የሚሰማንና የሚሰማቸውን የናፍቆት ሰቀቀን፣ እንደ ፋብሪካ እቃ የራሳቸው ሥራ አርገው ለማውጣት፣ በየዕለቱም ስለሚጫወቱብን ድርጊት፣ ..." ማለቴ ነዋ !

"እሱማ ምን ይቀራል ! የእኔ እናት፣ አንድ የነበርኩ ልጂ፣ እኔ ያለፍላጐቷ፣ እዚህ ተገድጄ በመምጣቴ ያለቀሰችብት ሁሉት ዐይኗ ጠፍቶ፣ እውር መሆኗን፣ አንድ ጓደኛዬ በተዘዋዋሪ ፅፎልኝ፣ ደብዳቤዋ ደርሶኛል።" አለ 5ኛው፣

"እኔ ከተለየኋት ጀምሮ፣ ከአልጋ ላይ ሳትወርድ፣ እንደማቀቀች ያለች መሆኑን፣ በየጊዜው በመስማቴና የናቴም ጤንነት፣ እንደወትሮ ሊሆን የሚችለው፣ እኔን ስታገኝ ብቻ መሆኑን ስለእማውቅ፣ ለዚህ ግብ መታገል እንዳለብኝ የናንተን ምኞትና ሐሳብ አላውቅም እንጅ፣ የኔ የግሌ ምኞቴና እዚህም እስካለሁ ድረስ፣ የማንቀሳቅሰው መፈክሬ ነው !" አለች ሰመነ፤ ለዚህም አባባሏ፣ ባንድነት "እናቱን የሚጠላ ማን አለ !" አሏት፣

"እኔ ብዙ ጊዜ እንደማስበው ከሆነ፣ ተቃውሞአችን መልክ እንዲይዝና ክብደትም እንዲኖረው ከፈለግን፣ እንደ ጥራቅ ማሰፈራርያ የሆነብንን፣ የዚህን የግድግዳ ላይ ሥዕል፣ ከክፍላችን፣ ከምግብ ቤታችን፣ ከመኝታ ቤታችንና እኛ ከምናይበት ቦታዎች ሁሉ እንዲነሳልን እንጠይቅ። አቅማችን የማይፈቅድልንም ቢሆን፣ ቀራጥነታችን በሚያስገኝልን ጉልበት ተደፋፍረን፣ በሕግና በሥርዓት እንዲያነሱልን የጠየቅነውን ባይፈፅሙ፣ በተባበረ ዐመፅ ተነሳስተን ፎቶግራፉ፣ ከተሰቀለበት ቦታ ሁሉ እያወረድን፣ እንክትክቱን እናውጣ። ምናልባት ይኸ ተግባራችን ብቻ ወደ ሀገራችን ለመመለስ የሚረዳን፣ ዐይነተኛ ምክንያት ባይሆንም እንኳ፣ ለጀመርነው ተቃውሞ ጥሩ መነሻ ምክንያት ሊሆን ይችላል እላለሁ" አለ፣ በኪሩቤል ላይ ሾርባ ቸላሹ ወጣት፣ በተግባር እንጅ በጽሑፍ አቤቱታ አለማመን እየገለጠ።

"ምንም ሕፃናት ብንሆንም ቅሉ፣ የደረስብን ችግርና መከራ፣ ያጉላመሰን መሆኑ፣ ሁላችንም የተሰማን ይመስለኛል ! አሁን እሱ ያለው ጥሩ ነው። ግን ሰዎቹ

ሞኞች ስላይደሉ፣ ዐመፃችንን ለማብረድ፣ በጥያቄችን መሠረት፣ የመሪውን ፎቶ አንስተው የኛን "ሀገር መሪ" ይቱኩ ይሆናል። የኛ ዐመጽ ግብ ግን፣ ሀገራችን መመለስ ነው። ታድያ በፎቶው መለወጥ ሊሸነግሉን ቢፈልጉስ ?" አለች ሰመነ።

"እዚህ አምጥቶ፣ መከራችንን እንድንጠብስ ያደረገው ዋናው እሱ አይደለ እንዴ ? የሱንማ ፎቶ ቢተኩ፣ ጭራሽ ከተሰቀለበት አለማውረድ ነው። እዚያው እንዳለ መስተዋቱን እያንከታከቱ በፎቶው ላይ ቀለም መቸለስና፣ የሆነ ያልሆነ ነገር እየፃፉ ማብሸቅ ነው !" አለች ሶስና።

"የራሱን ልጆች ሞስኮ ኤምባሲ ልኮ ያቀማጥላል። እኛን ግን እዚህ አምጥቶ፣ በባይተዋርነት በባቢሎን ከተማ፣ የቸነፈር እሳት ያቃጥላል ---የምትሉት፣ ለመሆኑ እናንተም እንደሱ ልጆች፣ በአምባሳደር የኑሮ ደረጃ፣ ከልዩ ወጭ ጋር ለመንቀባረር ትፈልጋላችሁ እንዴ ?" ያ ነገረኛ ኪሩቤል፣ ከጥቂት ጋብታ በኋላ፣ የተለመደ አሽሙሩን ሲጀምር የተናገረው ነው።

"በላ አንተ ደግሞ፣ እንደቀሩት ቁርጠኛ ደጋፊዎቹ ተከላከልለታ ! እኛ ግን በምንችለው ሁሉ፣ ተቃውሞ ፈጥረን አገራችን የምንመለስበትን መንገድ፣ ከማዘጋጀት ወደ ኋላ አንልም። ሶስናም ያለችው ወርቅ ነው። የሱን ፎቶ መተካታቸው አይቀርም። እንዳለችው መስተዋቱን እየሰባበርን፣ ፎቶው ላይ፤

"ትልቁ ጆኮር፣ ትላንት ቢጠፋ፣

ትንሹ ጆኮር፣ ዛሬ ተሰፋፋ !"....እያልን፣ እንለጥፍበታለን" አለ፣ ያ ኪሩቤል ፊት ላይ ሾርባ የቸለሰው ልጅ።

"ይልቁንስ ሌላውን ተውና፣ የተቃውሞ አቤቱታችንን በምን መነሻ ላይ ብናደርገው ይሻላል። እዚህ ላሉትም ጥቂት ደጋፊዎቻቸው አብሮ ዘመቶች፣ ቢቻል ልናሳምናቸው እንሞክራለን፣ አለያም ምሳቸውን እንሰጣቸዋለን" አለች ሰመነ።

"እንግዲያውስ፣ መጀመር ያለብን፣ መሠረታውያን በሆኑ ነገሮች ላይ በመነሳት ነው። ይኸውም፣ "ሰው የአካባቢው ውጤት ነው።" የሚለውን ትልቅ ሀሳብ፣ በተለይ እኛን በሕፃንነት እድሜያችን፣ ከሀገራችን አስወጥቶ፣ በሌላ ሕዝብ አከባቢ ተወስደን፣ እንድንማር መደረጉ፣ ትክክል አይደለም፣ የሚለውን

t.me/OLDBOOKSPDF

መነሻ ይዘን፣ ከዚያ በማከታተል የደረሰብንን፣ መከራና ሥቃይ፣ በደልና ፍዳ፣ ግፍና ጭቆና መዘርዘር ይኖርብናል። ያቤቱታችንንም ትክክል ግልባጭ፣ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሳይቀር መላክ አለብን !" አለች ሶስና፣ የአቤቱታቸውን ከፍተኛነት እያማሚቀች "ኮፒውንስ ለሰው መብት ጠባቂ ለተባሉ ዓለም-አቀፍ ድርጅቶችና ለአፍሪቃ አንድነት ድርጅት፣ ለገለልተኞች ማኅበርና፣ ለቀሩትም ሁሉ እናሠራጫለን !" አለ አምስተኛው፣ ዝምተኛ መሳይ ልጅ።

"በተለይ፣ እርስ በርስ የሚጋጩ ባሕሎች ካሉበት ሀገር፣ እኛን መሳይ ሎጋ ሕፃናት መላክ፣ ወንጀል መሆኑን ካነጠርን፣ አቤቱታችን የሚያስቀጣ ጭምር እንደሚሆን መጠራጠር የለብንም። ምክንያቱም፣ በዚህ እድሜያችን፣ ስንት ዐይነት ቅጠ-ቢስና ጋጠወጥ ዜጋ ካለበት ሀገር፣ "ተማሩ" ብሎ መላኩ፣ ምን ለመማር እንደሆነ፣ የትምህርቱ ይዘት መጋለጥ አለበት" አለች ሶስና።

"በዚያ ሰሞን፣ ሞግዚት እናቴ፣ ቤቷ ይዛኝ ስትሔድ፣ ሁለት ጠና ጠና ያሉ ሴቶች፣ መንገድ ላይ አግኝተውን፣ "የየት ሀገር ልጅ ናት ?" ብለው ጠየቁና፣ ዜግነቴን ከተረዱ በኋላ፣ ሁለቱም፤ "ልጆቻችንን ወስዳችሁ፣ በጦርነት ማጥ ውስጥ አስውጣችኋቸው ቀሩ-የትም ወድቀው ! ደግሞ ይቺ እዚህ ምን ልታደርግ መጣች ብለው !" ተንደርድረው እንዴ በጥፊ ቢወለውሉኝ፣ ምድር ሰማዩ ዞሮብኝ፣ የተፈጠርኩበትን ቀን ሳይሆን፣ እዚህ ሀገር የመጣሁበትን ቀን ረገምኩ ! ይህ፣ ውጣ ባልን ቁጥር የሚያጋጥመን ነው። እንዲህ ያለው ሁሉ፣ አቤቱታችን ውስጥ መጠቀስ አለበት።" አለች ሰመነ በየጊዜው የተፈፀመባትን ትልልቅ በደል እያስታወሰች።

"በዚህ ዐይነት አያያዛችን፣ ምንም መጻፍ እንደማንችል ተረዱ ! ሁላችሁም ብልጭ የሚልባችሁን በደል ብቻ ሰትዘበዝቡ፣ በሥርአት አጠናቅረን፣ አቤቱታውን ማቀናጀትና መጻፍ የሚሆንልን አይመስለኝም !" አለ ኪሩቤል ከየአቅጣጫው እየተዝረከረከ የሚቀርበውን ብትን ሐሳብ፣ በመልክ በመልኩ አድርገው ማቅረብ እንዳለባቸው ጓደኞቹን እየመከረ። ይህን ምክሩን ተናግሮ ሊጨርስ ሲል፣ ሁሉቱ ሞግዚቶቻቸው፣ አለወትሮአቸው በጣም ማልደው፣ ወዳሉበት ክፍል በመምጣት፣ ድንገት በሩን ከፍተው ከቸች አሉ። መጨረሻ ላይ

ይናገር በነበረው ኪሩቤል ላይ፣ አጉርጠው አፈጠጡበት። ደግነቱ፣ አቤቱታቸውን ባቀረቡት ወረቀት ላይ አላሠፈሩም እንጅ፣ ጽፈውት እንዳለ ደርሰውብት ቢሆን ኖሮ፣ የሚደርስባቸው ቅጣት ሌላ ይሆን ነበር። አምስቱ ሕፃናት ሌሊቱን ሙሉ፣ ችግራቸውን ሲያወጡና ሲያወርዱ እንቅልፍ የሚሉ ባይናቸው አልዞረ ኖሮ፣ የሁሉም ዐይኖች ቀልተዋል። ነገር ሲጐነጉኑ እንዳደሩ፣ ሁለቱም ሞግዚቶች ጠርጥረው፣

"ተመልከቺው ያ ተንኩለኛ፣ ዐይኑ የጦጣ ዐይን መስሏል ፣" አለች አንዷ ሞግዚት፣ ለሌላዋ።

"ማ እኔ ፣ የኔ ዐይን ነው የጦጣ የመሰለው ?" ኪሩቤል ይጠይቃል፣ ለማረጋገጥና መልስ ለመስጠት እያሰላሰለ።

"አዎ፣ ያንተ ነው ፣" አለች፣ ሞግዚቷ እየተቆጣች።

"በጦጣ ዐይንሽ አይተሽኝ ይሆናል ፣" አለ፣ኪሩቤል የመጣው ቢመጣ እንደቆረጠ ለማሳየት። ገና እንደገባች የተተናኮለችው ሞግዚት፣ ተንደርድራ ኪሩቤልን አጮለችው። የመገላገያ ዜዴ ያገኘች መስሏት፣ ድንገት የመጣላትን ሐሳብ ተጣድፋ እያቀረበች፣

"እኔ ሌሊቱን ታምሜ ሳቃስት በማደሬ እንቅልፍ ሊወስዳቸው ባለመቻሉ ነው፣ ዐይናቸው የቀላው ፣" አለች ሰመነ ዶክተር ለማየት መፈለጓን፣ ለሞግዚቶቹ እየገለፀች። በዚያች የማረሚያ ጣብያ በሆነች ጠባብ ክፍል ውስጥ፣ ጠባያቸውን እንዲያርቁ ተብሎ፣ ያለፍርድ ከተወሰነባቸው አንድ ሳምንት አልፏቸዋል። የሞግዚቶቹና ያምስቱ ሕፃናት የማለዳ ግብግብ፣ ገና በአፈናው ላይ እንዳለ፣ ሁለት የኤምባሲ ባለሥልጣኖች ከውጭ ይገባሉ። ሰላምታ ከሁሉም ጋር ከተለዋወጡ በኋላ፣ ዲፕሎማቶቹ፣ ስለችግሮቻቸው ሕፃናቱን ይጠይቃሉ።

"በርግጥ አእምሮ ያላቸው ወገኖች ብትሆኑ ኖሮ፣ እዚህ እንዲህ ስንሠቃይ እየሰማችሁ ባላስቻላችሁ ነበር ፣" አለች ሰመነ፣ የኤምባሲ ባለሥልጣኖችን እየነካካችና እየወቀሰች።

"አእምሮማ አላቸው። የሚጠቀምቡት ግን፣ ለእንደዚህ ዐይነቱ ድሪጊት ማራመጃ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብቻ ነው ፣" አለ ኪሩቤል፣ የኤምባሲዎቹ ሰዎች፣ በዚያች ጠባብ የጠባይ ማረሚያ ክፍል መገኘታቸው፣ የልብ ልብ ሰጥቶት።

"ታዲያ ይህን መሣሪን አእምሮ፣ ምን አእምሮ ትለዋለህ ፣ ብሶት የሚያራምድ አእምሮ፣ አእምሮ አይባልም ፣" አለ ያ ኪሩቤልን፣ የሾርባ ዱላ ያቀመሰው ልጅ። ለካስ አእምሮ፣ አእምሮ፣ እያሉ ደጋግመው ያነሱት አለምክንያት አልነበረም። በዚያ ቀን ማለዳ ከመጡት፣ ሁለት ዲፕሎማቶች ውስጥ አንደኛው፣ አምባሣደሩና የሚጠሩበትም ስማቸው፣ "ሳሊና" የሚባል ኖሯል። እሳቸውም፣ በልጆቹ ድፍረትና የዕብሪት አነጋገር እንደመብሸቅ በለው፤

"ስንት ጪዋ ልጆች አገር ቤት እያሉ፣ እናንተ እዚህ መምጣታችሁ ነው፣ ትልቁ ጥፋት። የምትሠሩትን ጥፋት ሁሉ፣ በየጊዜው ተከታትለን ደርሰንበታል። ይህን ሁሉ የውርጋጥ ጠባያችሁን፣ ለምን እንደምታስፋፉ፣ ዓላማችሁ ግብተናል። ወልጋዳ ባሕርያችሁ፣ እዚሁ ሀገር ውስጥ እንዲታረቅ ይደረጋል እንጅ፣ ሀገር ቤት እንድትመለሱ አይረዳችሁም። የናንተ የጥቂቶቹ ተንኩልና ሤራ፣ መላውን ሕፃናት፣ ለጊዜው ማሳደም ቢቻልም፣ አድማው ጊዜያዊ ነው። እያደር ይሠክናል። አሁንም ደጋግሜ የምነግራችሁ፣ በእንደዚህ ዐይነቱ የሤራ ሙከራ፣ አገር ቤት የመመለስ እቅዳችሁና ምኞታችሁ፣ በጭራሽ ሊሳካ እንደማይችል ነው..." አሉ አምባሣደር ሳሊና፣ እነኪሩቤልን እያስፈራሩ።

"ማነው ሀገራችን ካልገባን ያላችሁ ፣" አለች ሰመነ፣ ምሥጢራቸው እንዴት እንደወጣ ለማወቅ እየጓጓች።

"ለምን ትዋሺያለሽ ፣ ይኸ የማነው ድምፅ ፣" አለ፣ አምባሣደሩን አጅቦ የመጣው፣ ሁለተኛው ዲፕሎማት፣ ከወደ ብብቱ ስር የወሸቃትን፣ ብልቃጥ የምታህል ድምፀ-መቅርፅ አውጥቶ፣ "ሀገራችን መመለስ አለብን ፣" የሚለውን የራሷን ድምፅ በጉልህ እያሰማ።

"ለሁሉም" አሉ አምባሣደር ሳሊና "ለሁሉም፣ ሊቀመንበር ስሞኑን ለጉብኝት ስለሚመጡ፣ በዚያን ቀን የወደፊት ሁኔታችሁ ይወሰናል ፣" ብለው፣ ደኅና ሁኑም ሳይሉ፣ ጭልጥ አሉ። የመጡትም ቢሆን፣ አምስቱን የታሠሩ ሕፃናት ለማየት

ሳይሆን፣ በነሱ ምክንያት፣ ትምህርት አንማርም ብለው፣ ከሁለት ቀናት በፊት አድማ የመቱትን፣ ጓደኞቻቸውን ለማነጋገር ነበር።

"አመፅ ብቻውን፣ ሀገራችን ይመልሰናል !" ደጎና ይሁኑ እንደማለት፣ አምባሣደሩ ሲመለሱ፣ አምስቱም ሕፃናት ያሰሟቸው ድምፅ ነበር። አምባሣደሩም፣ ሌላ መልስ ሳይሰጡ፣ ሽምጥጠው ሲሔዱ፣ ተከትሎአቸው የመጣው ዲፕሎማት፣ እነዚያን ሁለት ሞግዚቶች፣ አምባሣደሩ ሊያነጋግሯአቸው እንደሚፈልጉ ገልጾ፣ ይዟቸው ወጣ። ሞግዚቶቹም፣ በሩን ከርችመው ከወጡ በኋላ፣ እስከቀኑ የምሣ ስዓት ድረስ፣ ወደ ታሠሩት ሕፃናት አልተመለሱም። ምሳ ሰዓት ላይ፣ አምስቱም ሞግዚቶች፣ ከት/ቤቱ አስተዳዳሪ እመቤት ጋር ሆነው፣ እነሰመነን ለማነጋገር ሲመለሱ፤ እንደወትሮው ለዱላ ሳይሆን፣ አዲስ ዜናና፣ ልዩ ማስጠንቀቂያ ለመንገር ነበር። መላው የት/ቤት ሕፃናት፣ እነሰመነ ከታሠሩበት ነፃ እንዲወጡ፣ ለሁለት ቀናት ያደረጉት የትምህርት ማቆም አድማ፣ ተሰሚነት አግኝቶ ኖሮ፣ ይኸንንው ለመንገር ነበር። ይሁን እንጅ፣ አምስቱ ልጆች ነፃ የሚወጡት፣ በገደብና በልዩ ማስጠንቀቂያ ነበር።

"ዛሬ በነፃ የተለቀቃችሁት፣ የትምህርት ቤቱን አስተዳደርና፣ የመምህራን ጉባኤ፣ አምባሣደራችሁ ይቅርታ እንዲ ደረግላችሁ በመጠየቃቸው ብቻ ሲሆን፣ ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት፣ ጠበያችሁን ባታሻሽሉና እንዳለፈው ጊዜ ተመሳሳይ ድርጊት በነጠላም ሆነ በቡድን ስትፈጽሙ ብትገኙ፣ ከፍ ያለ ቅጣት እንሰሚጠብቃችሁ ተወስኗል። በተለይም፣ ሰመነና ኪሩቤል፣ ከዚህ በፊት በየጊዜው ለተጣሩ አለመግባባቶች ሁሉ፣ መነሻ ክብሪቶች መሆናችሁ ስለተረጋገጠ፣ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባችሁ ተወስኗል። ለሚቀጥሉት ሦስት ቀናት እረፍት የተሰጣችሁ በመሆኑ፣ ክፍል ባትገቡም አትገደዱም። መልካም ዕድልና የጠባይ መሻሻል እመኝላችኋለሁ !" ይህን ቃል ያሰሚቸው፣ በአምስቱ ሞግዚቶቻቸው ምሥክርነት፣ የት/ቤታቸው አስተዳዳሪ እመቤት ናቸው።

ከዚያች ማፈኛ ክፍላቸው እንደወጡም፣ አድማ ለሁለት ቀናት የመቱላቸው፣ መላው አብሮ-ዘመት ጓደኞቻቸው፣ በሩቅ አዩአቸውና፣ እንደንብ እየሮጡ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከበቧቸው። ከዚያም፣ ሆ ! እያሉ፣ አምስቱንም ተሸክመው ወደ መሰብሰቢያቸው አደራሽ ከወሰዷቸው በኋላ፣ በመላው ተማሪዎቹ ስም፣ አንድ ወጣት "እንኳን ነፃ ወጣችሁ !" የሚል አጭር ንግግር በማድረግ፣ የመላው ተማሪ መተባበርና አድማ መምታት፣ ነፃ ሊያስወጣቸው እንደቻለ ገልጾ፤ ከታሠሩ ቀን ጀምሮ፣ መላው አብሮ-ዘመት ጓደኛ፣ በሐሳብ አብሮአቸው እንደከረመ አስረድቶ፣ ጭብጨባው ቀለጠ። ለተደረገላቸው ድጋፍና አቀባበል፣ ባምስቱ ወጣቶች ስም፣ ኪሩቤል የሚከተለውን አጭር መልስ ሰጠ።

"ስላደረጋችሁልን ድጋፍና አድማ፣ ባለውለታዎቻችሁ ነን። ነገር ግን፣ ነፃ ወጣችሁ የምትሉንን ጉዳይ ፈፅሞ አንቀበልም። ባሳለፍናት አንድ ሣምንት የመራራ ጊዜያችን ወቅት፣ ለሁላችሁም የሚስማማ አንድ መፈክር አዘጋጅተናል። ይኸውም "ሀገራችን መመለስ አለብን !" የሚለው ነው። ይህ መፈክር ተሚልቶ፣ ሀገራችን እስካልገባን ድረስ፣ እዚህ ሀገር እያለን፣ ነፃ ወጣችሁ ብትሉን፣ አይገባንም !" ብሎ ሲጨርስ፣ የቀሩት አራቱ ያፈና ቤት ጓደኞቹ፣ ከተቀመጡበት ተነስተው፣ ጮክ ብለው በመናገር ባንድነት ድምፅ፣

"ቃላችን ነው" አሉ። ከዛ ወቅት ጀምሮ ነበር፣ የደጋፊዎችና የተቃዋሚዎች የድንበር መስመር በጉልህ የለየው።

"ሀገራችን መመለስ አለብን !" በሚለው መፈክር ያልተስማሙቱ ወገኖች፣ አንድ አንድ እያሉ አዳራሹን እየለቀቁ ወጡ። የመፈክሩን ስንኩልነት ለማስረዳትም፣ ጥቂቶች ሽንጣቸውን ገትረው ተሚገቱ።

"ለመሆኑ እዚህ በመምጣታችሁ፣ ምን ተበደልን ነው የምትሉት ?" የክርክሩ እንብርት ይህ ነበር።

"ያለንበት ሀገር፣ ምን ዐይነት ጎብረተ-ሰብአዊ ሥርዓት ያለበት ሀገር ነው ? ይህ ጥያቄ፣ እዚህ በመምጣታችን ምን ተበደልን ነው የምትሉት ? ለሚለው ጥያቄ፣ መስቀልያና አጠቃላይ መልስ ሊሰጥ ይችላል !!" የሚል መልስ ነበር፣ ከመፈክሩ ደጋፊዎች የቀረበ አስተያየት።

"ይህች ሀገር፣ የጎብረተ-ሰብዓዊ ሥርዓት የሠፈነበት ሀገር ከመሆኗም በላይ፣

ብዙ የትግል ልምድ ያፈራችና በተለይም ሀገራቸውን፣ ከኋላ ቀር የአስተዳደር ቁራኛና ከኢምፔሪያሊስቶች ቀንበር ለማላቀቅ፣ የቅርብ ረዳት የሆነች ሀገር ናት" የሚል መልስ፣ ከመፈክሩ ተቃራኒዎች ቀረበ።

"አይደለችም !" አሉ የመፈክሩ ባለቤቶች።

"ናት !" አሉ መፈክሩን የሚፃረሩ ወገኖች።

"አለመሆኗን እናስረዳ !" አሉ ባለመፈክሮቹ።

"ከሆነላችሁማ ደስ ይለናል !" አሉ ተቃዋሚዎች። በዚያ ጊቢያቸው ውስጥ፣ በዚያ ረዥም የሁለት ዓመታት ጊዜያቸው፣ ነፃ ሐሳባቸውን፣ ባደባባይ ሲገልጹ፣ የመጀመሪያ ጊዜያቸው በመሆኑ፣ ባጋጣሚው ያልተደነቀ የለም።

"ከስር እንጀምር !" አሉ ባለመፈክሮቹ "አንድ ሀገር፣ ወይም አንድ ሕዝብ፣ የምርት ምንጮችን በቁጥጥሩ ስር ማድረጉ ብቻ ኅብረተ-ሰብአዊ ሥርዓትን አስፍኗል ማለት አይቻልም። ዋናው ቁም ነገር ግን፣ የዚያ ኅብረተ-ሰብአዊ ሕዝብ፣ ቁጥጥር ላይ በዋሉት የምርት ምንጮች፣ ምን ያህል ተጠቃሚነትና አዛዥነት አለው ? የሚለው ጉዳይ ነው። ሕዝብ በሚለው ምትክ፣ የዚያ ኅብረተ-ሰብ፣ ላባ-አደር የሆነው ሠራተኛው መደብ፣ ብንል ይሰምራልና፣ የሀገሩ ሠራተኛው መደብ፣ በነዛ የምርት ምንጮች ላይ ምን ያህል የወሳኝነት ሥልጣን አለው? ብትባሉና መልስ ብትጠየቁ፣ ማዕከላዊ ኮሚቴ፣ ኮንግረስ፣ የሠራተኛው ፓርቲ... ምንትስ፣ ምንትስ የሚወስነው ስለሆነ፣ የሠራተኛው መደብ ተጠሪዎች ናቸውና፣ ላባ-አደሩ ቁጥተኛ የሆነ፣ በምርት ምንጮች ላይ የማዘዝና የማስተናበር ሥልጣን አለው፣ ልትሉን ይሆናል። ይህን፣ በጭራሽ አንቀበልም። ሀገራቸው፣ በተወሰኑ የከሊክ ቁንጮዎች የምተመራ፣ እነዚህም እፍኝ የማይሞሉ ኢዲሞክራታዊ ባለሥልጣኖች፣ ለሀገሪቱ የምርት ምንጮች ፈላጭና ቆራጭ፣ አዛዥና ናዛዥ፣ የአዲሱ ኢምፔሪያሊዝም ገባሮች፣ እጅ ከጓንት ብቻ ሳይሆን፣ ጥርስና ከንፈር ጭምር ሆነው፣ ከሶቭየት ኅብረት ጋር፣ ባንድነት የምትራመድ ሀገር ናት። በዘመናችን፣ በየትኛውም ክፍለ-ዓለም፣ ራሻውያን ከንፈሮች፣ ለብዝበዛ መጠጣ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተሰማርተው በገለፈጡ ቁጥር፣ የዚህ ሀገር ሰዎች ጥርሶች ወለል ብለው ይታያሉ። ይህም የምዝበራ ዘመቻቸው፣ በዝርዝር ሲተነተን፣ የሚከተለውን ያንፀባርቃሉ።

-- በደካማ ሀገሮች ውስጥ ጣልቃ ባመግባትና፣ የሀገሩን ሥልጣን ከሀገሩ መሪዎች ጋር በሽርክና ተዳብሎ በመያዝ፣ የራሳቸውን ዓላማዎች ለመቀየስና ግቡን ለመትለም፣ ሲያስገድዱ ወይም በራሳቸው የወታደር ኃይል በመጠቀም፣ የቀድሞውን መሪ ከሥልጣን በማውረድ፣ በምትኩ ብጤያቸውን ፑፔት ሲተኩ ታይተዋል። ሶቭየቶች ባፍጋኒስታን፣ ባንጐላና በሀገራችን፣ ይህ ተግባራቸው ተከናውኖ በማየታቸው ተደስተው፣ እስክስታ ሲመቱ፣ የዚህ ሀገር ሰዎች፣ አጨብጫቢዎቻቸው ነበሩ።

-- ከባድ የወታደር ትጥቅና ሠራዊት በማዘጋጀት፣ የቀረውን ዓለም በመርዛማና በአቶሚክ የጥፋት መሣሪያዎቻቸው ያሸብራሉ። በሌሎች ደካማ ሀገሮች ወታደራዊ ምሽጐችን ለወረራ ያዘጋጃሉ። የጋራ ወታደራዊ ስምምነቶች በሚል ሽፋን፣ የደካማ መንግሥታትን ወታደራዊ ኃይል፣ በራሳቸው ቁጥጥር ውስጥ እንዲውል አርገዋል።

-- የወታደርና የሲቪል አማካሪ-ሠራዊት በየሀገሩ በማሠራጨት፣ በባሕል፣ በፓለቲካና በትምህርት ተቋሞች ውስጥ ሠርገው በመግባት ሥር ሰደው፣ የራሳቸውን ጥቅም የሚያስጠብቅ መመሪያ በማውጣት፣ ያን ደካማ ሕዝብ ይመርዛሉ፤

-- አንድ ወጥ የሆነ፣ የፋብሪካ እድገት ብቻ እንዲስፋፋ በመገፋፋት፣ ለዚያ ፋብሪካ የሚያስፈልጉትን እቃዎች፣ ከራሳቸው መንግሥት ብቻ ሁልጊዜ ተመፅዋቾችና ገበያተኞች እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል-ዝርዝር ውስጥ እየገባን፣ የኛን አባቶች የበላ፣ የጦር መሣርያ፣ በሶማሌያ በኩል ሆነ በሌላው፣ ከየት የተገኘ መሆኑን አለመግለፃችን፣ ታውቋት ይሆናል በሚል ግምት ነው።

-- ያልተመጣጠነ የንግድ አቋም ስምምነት በመዋዋልና በመደራደር፣ የራሳቸውን፣ ከጥቅም ውጭ የዋለ ሽቀጣ ሽቀጣቸውን፣ ደካማዎቹ ሀገሮች፣ በውድ ዋጋ እንዲገዙና፣ በምትኩም፣ የነሱን ጥሬ እቃ እንዲሸጡ በመገፋፋት፣ የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ሲያዳብሩ ይታያሉ።

-- ከፍተኛ ወለድ ያለው ብድር በመስጠትና፣ ያንንም ያበደሩትን ገንዘብ፣ ከዚያው ካበዳሪው መንግሥታቸው ብቻ የሚገኘውን ሽቀጥ እንዲገዙበት፣ በተለዩ የውል ስምምነቶች በመቸንከርና፣ ብድሩም የሚከፈለው፣ በየጊዜው በሚሰጥ ጥሬ እቃ እንዲሆን ያስገድዷቸውና፣ ሲዘርፉ ይኖራሉ፤

-- በተለይም የሦስተኛ ዓለም ሀገሮችን፣ ያረጁባቸውንና ጊዜ የከዳቸውን የጦር መሣሪያዎች እንዲገዙ በመስበክና በማባበል፣ የረከሠ ሽቀጥ መጣያ ያደርጓቸውና፣ ይህም የድራ ገበያቸው እንዳይቋረጥ፣ መለዋወጫ እቃዎቹን ከነሱው ብቻ የሚገኙ በመሆናቸው፣ ከነሱው በስተቀር ወደ ሌላ ገበያ ውልፍት እንዳይሉ በተጠቀሰው የመለዋወጫ እቃዎች እግረ-መቅ ከርችመዋቸው፣ ከነሱ ዘንድ በስተቀር እንዳይንቀሳቀሱ አስረዋቸዋል።

-- ከራሳቸው ሀገር ይልቅ፣ ገና ድንግል ከሆኑት፣ የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች የተፈጥሮ ሀብት ላይ በመጣበቅ፣ እነዚህንም ያልተበጠቦጡ ሀገሮች፣ ለጥሬ እቃዎች ፍላጐታቸው ምንጭ በማድረግና፣ በኃይልም ሆነ በዘዴ፣ ወይም በአጋርነት በመጠጋት፣ ፍፁም ጥገኛቸው ያደርጓቸዋል።

-- በኤኮኖሚ ለበለፀጉ ሀገሮች ጥቅምና፣ ለራሳቸውም የዚህ ጥቅም ስውር ሽርክና ሲሉ፣ የኢምፐሪያሊስት ግብረ-አበሮቻቸውን፣ የገንዘብ ዋጋ ከፍ ያደርጉታል።

-- የራሳቸውን ኢምፔሪያሊስታዊ የውጭ ጉዳይ መመሪያዎች፣ ጥገኛ ላደረጓቸው ታናናሽ ሀገሮች ሁሉ፣ በግድም ሆነ በውድ እንዲከተሉ፣ በውል ሳይቀር ያስገድዷቸዋል። ብሬዝኔቭ፣ ወይም፣ ሌላ ሶሻሊስት ነኝ ባይ መሪ የተነፈሰውን የፖሊሲ ድምፅ፣ የሀገራችን አምባገነን ወዲያው ተቀብሎ ሲያላዝንበት የሚከርመው፣ ወዶ ሳይሆን፣ የዚህ የገባበት ውል ግዴታ እንደሆነ ማንም የሚያውቀው ነው።

-- ያንድ ሀገር መሪ፣ የሕዝቡ ቅን አገልጋይ መሆን ብቻ ሲገባው፣ እንደ አማልክት መመለኩ፣ ለዝናውና ለስሙ ብቻ መጠበቂያ እየተባለ የሚፈሰው ገንዘብ፣ በሀገሩ ውስጥ ስንቱን የተራብ አንጀት ማራስ ሲችል፣ ስንቱን ሥራ አጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወገን፣ ሥራ ሊፈጥርለት ሲችል በከንቱ መባከኑ፣ የነዚህ በስም ሶሻሊስት የሆኑ ሀገሮች፣ መንግሥት አንቀሳቃሽ የሆኑ የጥቂት ቡድን (ክሊክ) ቁንጮዎች፣ መመዘኛ የሚሆን ሌላው ጠባያቸው ነው።

"እንግዲህ ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው፣ ጉልሆቹ የኢምፔሪያሊስትነት መንፀባረቂያ ባሕርያት ናቸው። ይህች ሀገር፣ እናንተ እንደምትሉት፣ ሶሻሊስት ሀገር ሳትሆን፣ የነዚህ ኢምፔሪያሊስታዊ ባሕርያት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሠረፀባት የመጣች ሀገር ናት። በስመ-ሶሻሊስትነት ካልሆነ በቀር፣ ዘመኑ በሚጠይቀው የኢምፔሪያሊስነት ታክቲክ ከመጠቀሚ በስተቀር፣ በዓለም ኢምፔሪያሊስትነቱ ከለየለት፣ ከአሜሪካ መንግሥት፣ በምንም ዐይነት የምትለይ አይደለችም። ስለዚህም፣ በኢምፔሪያሊስት ቁጥጥር ስር በወደቀ ሀገር፣ የሚገኙ የዋሃንና ለጋ ሕፃናት፣ ምንም ዓይነት ችግር የለባቸውም የምትሉን፣ በጭራሽ አይገባንም። ሊገባንም አይችልም..." በማለት ሰፊና አጠቃላይ የሆነ መልስ፣ ለተቃዋሚዎቻቸው አቀረቡ።

"ምን ይቸግረናል ?" የሚል ጥያቄ ያቀረቡላቸው፣ ተቃዋሚዎቻቸውም፣ ወዲያው በማከታተል፤

"ብዙ በማታውቁት፣ የፖለቲካ ማጥ ውስጥ ገብታችሁ ዳክረልን አላልናችሁም ነበር። በጣም የተጠቃለለ ዲስኩራችሁ ውስጥ ከመግባት ይልቅ፣ እዚህ ሀገር ሳላችሁ፣ ምን የከፋ ችግር አጋጥሟችኋል ? ነበር፣ ጥያቄያችን። ደግሞስ፣ ሀገራችን እንመለስ የሚል ጥያቄ እስከማቅረብ፣ የሚያደርስ ምን በደል ተፈፅሞባችኋል ? ነበር እንድታስረዱን የፈለግነው..." አሉ፣ ተቃዋሚዎች፣ የሰጧቸውን መሠረታዊ መልስ በማቃለል።

"ሌላውን እንተውና፣ ለዚህም ጨቅላ ጥያቄያችሁ፣ መልስ እንስጥ ! መልሳችንም ጥያቄ ይሆናል። ከሀገራችን ወደዚህ ሀገር ስንመጣ፣ ለመምጣት ምክንያት የሆነው መሠረታዊ ዓላማ ምን ነበርን ?" አሉ የመፈክሩ ደጋፊዎች።

"ትምህርት !" አሉ፣ ተቃዋሚዎቻቸው በጣም ተጣድፈው።

"ጥሩ ! ትምህርት ነው። ትምህርት በበኩሉ፣ የጎብረተ-ሰቡ ሥርዓታዊ ይዘትና

የኢኩኖሚው ነፀብራቅ ነው። እፍኝ የማይሞሉ የክሊክ አባሎቻቸውና ቁንጮው፣ በፈለጉት ሚና ለሚረጩት የኤኩኖሚ ሀብት፣ እንደፈለጉ ለሚያዙበት የምርት ምንጭ፣ በፈለጉት አቅጣጫ ለሚነዱት ያስተዳደር ሠረገዳ፣ እንደሞኖታቸው ለሚዳኙበት መቅጫ ሕግ... ዐይነተኛ ዋና መሣሪያቸውና መገልገያቸው፣ ትምህርት ነው። በዚህ ዐይነቱ የትምህርት ፋብሪካዎቻቸው ውስጥ፣ እንደናንተ ያሉትን ደጋፊ ዎቻቸውን፣ በሚፈልጉት የባሕርይ ቅርፅ ዐይነት፣ አቅልጠው፣ ጨፍልቀው፣ አድቦልቡለው ወቅረው፣ በመጪረሻም ላይ፣ አጥበውና ቀብተው፣ ወልውለው ያወጣሉ። ይህ ዐይነቱም ሰው—ሠራሽ ሰው፣ ሞቱን ሳይቀር የማይፈራ አገልጋያቸው ይሆናል። ይህ ዐይነቱ ትምህርት፣ ከሚሰጥበት የትምህርት ፋብሪካዎቻቸው መገኘታችን፣ ራሱ የበደል በደል ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ነን። ባሕላችንም ሆነ ኢትዮጵያዊ ሰብዕናችን፣ በረጋ—ሠራሽ የጭንቅላት አጣቢዎች፣ መታጠብ የለበትም። ሀገራችንም እንመለስ የምንለው፣ ከዚህ ነጥብ ላይ በመነሳት ነው። ...” አሉ።

“ባሕላችን የምትሉት፣ የቱን ባሕል ነው ? የፊውዳሉን ወይም የግማሽ ከበርቴውን ባህል ነው !...” አሉ ተቃዋሚዎች፣ መከራከሪያ ነጥብ ያገኙ መስሏቸው።

“ከቤተ—ሰብ ያስተዳደግ ሥርዓት አንስቶ፣ በሕይወት ጉዞአችን ውስጥ የምንጠቀምባቸው፣ ምግባችን፣ የየብሔረ—ሰቡ ቋንቋችን፣ ሕዝባዊ በዓላችን ሐቀኞች አንጋፋዎችን ማክበራችን፣ ብሔር ወጥ ልብሳችን ...ሁሉ፣ ከትውልድ የተላለፉልን፣ በሔራዊ ቅርሶቻቸን ናቸው። ሰፋ ባለ አመለካከት ብትመረምሯቸው፣ እናንተ ሳትጠመቁ ከምታምኑበት፣ ከዚህ ሀገር ረጋ—ሠራሽ የሶሻሊስት ባሕል መቶ በመቶ ይብልጣል !” አሉ።

“ስንኩል መልሶቻችሁን ማዳመጡ ቢሰለችንም፣ ድምር ትችታዊ መልስ መስጠቱ ይሻላልና፣ ዓለም—አቀፍ ይዘት ስላለው፣ እዚህ ስለምንማረውስ ትምህርት ምን ትላላችሁ !”

“የምናጠናው ጆኦግራፊ ሳይቀር፣ የኢትዮጵያን ዐባይ፣ ራስ ዳሽን፣ጣና ሳይሆን፣

t.me/OLDBOOKSPDF

እትብቴ አሻራ !

ሥጋ ለብሶ ያለ ባለንበት ምድር፤
ጭራሽ አላየሁም፣ እንብርት የለሽ ፍጡር፣
አሻራ ማኅተም ምንጭ እሚመዘር።
እትብት ነው ስሙ እናት ልጅ አሳሪ፣
ተፈጥሮ ያተመው፣ ያንድነት አብሣሪ፤
ግዴታ እንኳ ሆኖ፣ ቢቆረጥም ቅሉ፣
አብረው እንዲኖሩ አብረው የበቀሉ፣
እትብት ማሰሪያ ነው፣ ከሌላውም ሁሉ።
ተወላጅ ከወላጅ ተራርቆ እንዳይኖር
እትብት ማሰሪያ ነው የተፈጥሮ ምሥጢር፤
አብረው እንዲኖሩ ሰዎች የሚመክር።
ናሽናሊስት ሁሉ፣ ጉጠት ያለም ሥርዓት፣
ተለውጦ ቢሆን ኢንተርናሽናሊስት
የሰው እኩል መሆን ጉጠትና አምኖበት፣
ማነው ከቶ በምድር ተደስቶ እማይሞት!!
ይህንን ለማድረግ የዘየዱት ሥርዓት፣
ትክክል አይደለም፣ ያንዳንዶች መንግሥታት፣
የተጠቀሙበት የዘዴያቸው ዓይነት።
ሆያ ሆዬ ባቱን፣ ያልባለቀ ሕፃን፣
ገና በለጋነት፣ ሲቦርቅ ያለውን፣
ከወላጅ ከሀገር፣ ነጥቆ ወስዶ በግድ፣
በባዕዳን ምግዚት፣ እንዲያድግ ማስገደድ፣
በወላጁም ሆነ ያለራሱም ፈቃድ፣
ትክክል አይደለም፣ ያድራጎቱ ሥራት፣
ካልሆነ በስተቀር፣ በሕፃን መጫወት፣
ባሕር ማዶ ወስዶ፣ ማስጨነቅ ሕፃናት፣
አሳልፎ መስጠት ለባዕድ ምግዚትነት።
ጓላም ከውጭ አድገው፣ በሌሎች ባሕል ውስጥ፣
አጠራጣሪ ነው ጠባያቸው በርግጥ፣
ይሆናል ግለቱ፣ መሰል እንዳገር ወጥ።
በግሉ መወሰን፣ የማይችልን ሕፃን፣
ለምግዚት መስጠቱ፣ ያውም ለባዕዳን፣
ከወንጀል አያንስም፣ ቢታይ በፍትህ ሥልጣን።
ለጋ ሕፃን ሁሉ፣ ቢወድም ባይወድም፣
ግዴታ ይሻለዋል፣ እናት ሀገሩ ዓለም፣
ወጡ እንደሆነው፣ ሆኖ ለዘለዓለም፣
አፈር ቅሞም ቢሆን፣ ቢያጋመው ሌላም፣
ለየትኛውም ልጅ፣ ሀገሩ ናት ጣዕም፣
ባሕሉን ይዞ እንዲያድግ፣ ሌላ እማራጭ የለም
ነውና እትብቱ፣ አሻራው ማኅተም፤

የዚህን ሀገርና የሩስያን ወንዞች፣ ተራሮች፣ ባሕሮች ነው። የራሳችንን ቋንቋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየረሳን፣ በነሱው ቋንቋ እየተካን ነው። በለጋ እድሜያችን ላይ፣ ካገር የወጣን በመሆናችን፣ ስናጠነጥን የቆየነው የአእምሮችን ዕውቀታዊ ክር፣ ጠንካራ ባለመሆኑ፣ በቀላሉ ሊተረተር ከመቻሉም በላይ፣ የዚህ ሀገር መሪዎች በትምህርት ስም አስታከው የሚያቀርቡልንን፣ ብሔራዊ ፍላጉትና ምኞት መከላከልም ሆነ መመከት አልቻልንም። ከተወሰነልን ጊዜ በኋላ፣ ሀገራችን የመመለስ ዕድል እንኳ ቢገጥመን፣ እናቶቻችንንም ሆነ፣ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን፣ ብምን ቋንቋ ማነጋገር እንደምንችል አናውቅም። በተለይም ይበልጥ እየገፋፋ ለአመፅ የሚያዘጋጀን፣ ትምህርት ተብሎ ከሚቀርብልን፣ ሦስት አራተኛውን እጅ የሚሸፍነው፣ ሙዚቃ፣ ቲአትርና መዝሙር ነው። ጭቁን ሕዝባችንን በሚመለከት ይዘት ላይ ያተኰረ ቢሆን እንኳ፣ ብንማርም ምንም አልነበረም። የሚያሳዝነው ግን፣ ያ ሁሉ የሙዚቃ፣ የቲአትርና የመዝሙር ዝግንትል፣ ውዳሴ የኢ.ና ያለንበት ሀገር መሪዎች ብቻ መሆኑ ነው። ላንቃችን እስኪደርቅ ድረስ መሸቶ በነጋ ቁጥር "ውዳሴ-ከንቱ" ሲያስጮሁን ይውላሉ። ይህ ዐይነቱ ትምህርት፣ ለኢትዮጵያ ዐብዮትም ሆነ፣ ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ፣ ምንም ዓይነት አስተዋፅኦ ሊያበረክት እንደማይችል፣ ከገባን ቆይቷል። ይህ ሁሉ ብሶት ተጠራቅሞ ነው፣ ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ እዚህ ተሰብስበን ለመወያየት ያበቃን !" አሉ፣ የመፈክሩ ደጋፊ ዎች።

"አሁን ፍጆታው የኛ ነው ! ለቀባጠራችሁት ምላሽና፣ ላነገባችሁት ሰንካላ መፈክር፣ ትክክለኛውን አስተያየታችንን እንሰጣለን። በተቀዳሚ ልትረዱልን የምንፈልገው፣ የዓለም-አቀፍ ወንድማማችነት መንፈስ ተጀምሮ እስኪጨረስ ያልሠረፀባችሁ መሆናችሁን ነው። ይህ መንፈስ ቢኖራችሁ ግን፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ፣ ባሕላችን፣ እያላችሁ በውሱን ናሽናሊስትነት ባላናፋችሁም ነበር። ግን ወደዳችሁም ጠላችሁም፣ ያለማችን ባሕልም ሆነ የተራማጆች ኪደት፣ የሚያመራው፣ ወደዚሁ እናንተ ወደ ጠላችሁት ግብ ነው። ዓለም-አቀፋዊነት ዳብሮ በሚጐለብትበት ጊዜ፣ ሀገራችን እያላችሁ ያቅነዘነዛችሁ፣ ኢትዮጵያ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚለው ሥያሜ ሳይቀር ተውጦ፣ የሚጠፋበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። የዚህ ትግል አርበኞችም እነብሬዝኔቭ፣ የሀገራችሁና የዚህ ሀገር መሪዎች ናቸው። የኛም በዚህ ተራማጅ ሀገር መገኘት፣ የነሱ ትግል ያስገኘው ፍሬ ነው። የወዳሴ መዝሙር እንዳላችሁትም ብንዘምርላቸው፣ ቢያንሳቸው እንጅ አይበዛባቸውም። የዚህን ሀገር መሪ እንኳ ትተን፣ የሀገራችሁን መሪ፣ በሀገራችሁ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ ረሀብ፣ሥራ አጥነት፣ ድንቁርና፣ በሽታ፣ ድራሽ አባታችው ጠፍቶ፣ ለምልክት ያህል እንኳ አይገኙም። ከሀገር ቤት ተርፎ፣ ይኸው እኛንና እናንተን ተቃዋሚዎቹን ጭምር እዚህ ሀገር ድረስ እንድትመጡ አስደርጎ፣ ይኸው ተንቀባራችሁ እስክታስችግሩ ድረስ አብቅቷችኋል። ደግሞም..." ብሎ የተቃዋሚዎች ተጠሪ ወኪል፣ ንግግሩን ሳይጨርስ፣ ቀደም ብለው አዳራሹን ለቀው በወጡ የተቃዋሚ ወገኖች ጠቋሚነትና መሪነት፣ ተራ ልብስ በለበሱ ፖሊሶች፣ አዳራሹ ተወረረ። ከዚያም የመፈክር ደጋፊዎችና የመፈክር ተቃዋሚዎች፣ ሁለት ስዓት በፊጀ ጊዜ ውስጥ ተበጥሮ ተለየና፣ የመፈክር ተቃዋሚዎች ከሌሎቹ እንዲገለሉና እንዲዝናኑም ታስቦ፣ ልዩ መኪና ቀርቦላቸው፣ ወደ ኤምባሲ ሲወሰዱ፣ የቀሩት የመፈክር ደጋፊዎች ግን፣ እንደ ወንጀለኞች ተቆጥረው፣ ቅጣትና ምርመራ ለማድረግ፣ ሁለት ሁለት አርገው እያጣመሩ፣ ወደ አልታወቀ ቦታ ተወሰዱ። በአፈሣው ግርግር ጊዜ፣ ያ የመፈክር ተቃዋሚዎች ተጠሪ ሆኖ፣ ንግግር ያደረገውና አጠገቡ የነበረ ጓደኛው ብቻ፣ የፊት ጥርሶቻቸውን፣ በተሠነዝሩ የተቃዋሚዎቻቸው ቡጢዎች ሲያጡ፣ ሌላ ኮሽ ያለ ነገር አልነበረም። ከዚያ ቀን ጀምሮ፣ ያ በሕፃናት ሁካታ ሲምቢች የነበረ የት/ቤታቸው ግቢ፣ ለወር ጊዜ ያህል ጭር ብሎ ሰነበተ። የመፈክር ተቃዋሚዎች ሲዝናኑ፣ የመፈክር ደጋፊዎችም ሲሠቃዩ፣ ከከረሙባቸው ቦታዎች፣ በአንድ ቀን ውስጥ ወደ ት/ቤታቸው ተመለሱ። ተዝናኚዎቹም ረክተው፣ ተሠቃይዎችም መሮአቸው ሳይሆን፣ ወደ ት/ቤት የተመለሱት፣ የሀገራቸው መሪ የመጎብኛ ጊዜ የተቃረበ በመሆኑና፣ ከመጡ ጀምረው ሲያጠኑ የኖሩትን፣ ሙዚቃ፣ ቲአትር፣መዝሙር፣ እንደገና እየከለሱ እንዲያዘጋጁ ታስቦ ነው።

ሁለቱ የለየላቸው ተቃራኒ ወገኖች፣ በየቀኑ የጉሪጥ እየተያዩ፣ ዝግጅቱ ሲደረግ ሰነበተ። ከዚህ በፊት ለአምባሣደሩ ቃል በገቡላቸው መሠረት፣ የመፈክሩ ባለቤቶች፣ በልመና ሳይሆን በአመፅ፣ መፈክራቸው በሀገራቸው መሪ የጉብኝት ጊዜ እንዲፀድቅ ለማስደረግ፣ ልዩ የሆነ የስውር ዝግጅት ማቀናበር ጀመሩ። በዚህ ዝግጅታቸው ውስጥ፣ የራሳቸውን መፈክር የሚመለከት፣ ልዩ መዝሙር ይገኛል። እንደተባለውም፣ "የሀገራቸው መሪ" ለአሥር ቀናት ኦፊሲያል ጉብኝት ለማድረግ ካሉበት ሀገር ገባ። ከነዚህ ቀናት ውስጥ፣ የአንደኛው ዕለት ፕሮግራም "የታዳጊ ተራማጅ ኢትዮጵያውን ተማሪዎች ጉብኝት" የሚል ነበር።

ገና ስምንት ቀን ሲቀረው፣ ያገር ሠራተኛ ተሰብስቦ፣ የት/ቤቱ በርና መስኮት ሣንቃዎች፣ ልዩ ልዩ ቀለሞች ተቀቡ። ወሃ ነክቶአቸው የማያውቁ የወለል እንጨቶች በናፍታና በዘይት ተወለወሉ። ሣር እንኳ ተጉዝጉዞባቸው የማያውቁ የሲሚንቶ ወለሎች፣ ቀይ ግምጃ በመሰለም ንጣፍ ተሸፈኑ። በመኝታ ቤቶችም ውስጥ፣ እየተንጣጣ እንቅልፍ አላስወስድ ብሎ የከረመ፣ የእንጨት አልጋ ሁሉ፣ በሚያረገርጉ የሽቦ አልጋዎች ተተኩ። ለወራት ሳይቀየርና ውሃ ሳይነካው የነበረ አንሶላና ብርድ ልብስ ዝተት፣ በወርጀናሌ መብረቅና በሱፍ ብርድልብስ ተቀየረ። የሽንት ቤቶች አሸንዳዎች ሳይቀሩ፣ ተረስተውና ዝገው ሲኖሩ፣ ባዳዲስ ተተኩ። መጋ ለብሶ፣ የቢንቢና የትንኝ መፈንጫ የነበረው የኳስ መጫወቻው ሜዳ፣ ከስታዲየሞች አንዱን ይመስል ያህል አማረበት።

ጫማ ተነፍጓቸው የከረሙ፣ የሕፃናት ሻካራ እግሮች ሁሉ፣ በካልሲ ሳይቀር ተዋቡ። በዚያ ከተማ ታይቶ የማይታወቅ ዩኒፎርምም ስለተሰጣቸው፣ እላያቸው ላይ አልቆ የነበረው ቡትቶ ልብሳቸው፣ መጣል ብቻ ሳይሆን ተቃጠለ። ዘይት ያላየው ሾርባቸው፣ በቅቤና በሥጋ ሳይቀር ተዝናና። ውሃ መጠጫቸው ብርጭቆ ሳይቀር ተለወጠ። የፍራ ፍረ ጭማቂ መጠጦች፣ በምግብ ቤት ቧምቧዎቻቸው ሁሉ፣ እንደውሃ ፈሰሱ። እንዲያ እንዲያ ተደረገና፣ የት/ቤታቸው ሁለንተና ሲያሸበርቅ፣ የተባለው የሀገራቸው መሪ፣ ከክብር እጃቢዎቹ ጋር፣ በአንደኛው ሰንበት ከቸች አለ። አበባው ባንገታቸው ሳይቀር ተጠለቀ። ዙሪያውን ጉብኙ፣ ማሸብረቁን


t.me/OLDBOOKSPDF

ዐይተው፣ በልጆቹ እድለኛነት ቀኑ። ቅልጥ ያለ የምሣ ድግስ ተበላ። የሀገሩ መሪና የሀገራቸውም ከተማ ገዥ ንግግር አደረጉ። ተጨበጨበ። የመጨረሻው ፕሮግራም፣ በተማሪዎቹ የሚቀርበው፣ የሙዚቃ፣ የቲአትርና፣ የመዝሙር ዝግጅት ስለነበር፣ ልዩ ልዩ የውዳሴ ዝማሬ ፈሰሰ። አባባ መሪ፣ እማማ ገዥ ተባሉ። ሊያልቅ አሥር ደቂቃዎች ሲቀር፣ ነገር መጣ። እነዚያ "አገራችን መልሱን" የሚሉት ወገኖች፣ የሚከተለውን ልዩ መዝሙር ይዘው አናወጡት ።

<u>ሰው ባገሩ ፣</u>

"አዕላፍ ነው ክብሩ ፣
ሰው ባገሩ ፣ ሰው ባገሩ፣ ሰው ባገሩ ፣
አዝማች፡– ከውድ ሀገራችን፣
አትሔዱም ብትለን፣
ባመፅ እንገባለን ፣
ቢበላ ሣር፣
ምናምንቴ ቢማር፣
ቢበላ መቅመቆ፣
ቢማር ከጪለንቆ፣
እየዋጠ ዶኬ፣
እየሳለ ቀኬ፣
ይከበር የለም ወይ፣ ሰው መሆኑ ታወቆ፣
በባዕዳን ሀገር፣ ከሚኖር ወላልቆ።
ለያይቶ ከናቶች፣
ለጋ ሕፃናቶች።
ሆነ ማሠቃየት፣
ምልክት የፋሽስት ፣

መልሰኝ ብያለሁ ከሀገሬ፣
ከዚህ ሀገር ትምህርት፣ ይሻል መደንቀሬ።
የቀረጠ አንጀት፣ እንደተክሌች ቅጠል፣
አያቆጠቁጥም ምንጊዜም ቢቀጠል ።። ...”



በዚህ፣ ዜማው ከይዘቱ በተዋጣለት፣ ከተቀመጡበት በሚያስነሳ መዝሙር፣የነበሩበትን አዳራሽ ብቻ ሳይሆን፣ የት/ቤቱን ጊቢ ሳይቀር አናጉት። አብሮ የነዘረ ልብ ቢኖር፣ የሀገራቸው ገዥ ጭምር ነው። ከተተረጉመ በኋላማ ያሉበትንም ሀገር መሪ ቆሽት አደረቀው። ይሉኝታም ይሁን ሀፍረት አይታወቅም፣ ቀራጮቹ ሕፃናት ያን ፀረ-ፋሽስት የሆነ መዝሙራቸውን ይዘው ሲደልቁት አስተናጋጁም የሀገሩ መሪ ሆነ፣ እንግዳው ያገራቸው አምባ-ገነን፣ ትንፋሽም አልወጣቸው። ምድረ-አንጋች ሁሉ ሲቅበጠበጥ፣ አጃቢዎቹ ተከታዮች በሙሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሽምቅቅ ብለዋል። ያ እንደ ማዕበል ሞገድ፣ አዳራሹንና ጊቢውን ያናወጠው መዝሙር በሚዘመርበት ወቅት፣ በተሰጣት መምሪያ መሠረት፣ ሰመነ ከመሐላቸው ወደ መድረኩ ጫፍ ብቅ እያለች፣

“አመፅ ብቻውን ሀገራችን ይመልሰናል !”

የሚለውን መፈክራቸውን፣ ጣልቃ እያስገባች፣ ጮክ እያለች ታሰማ ነበር። የሀገራቸውም አምባገነን ገዥ፣ ያልጠበቁት አባዜ መጨረሻ ላይ ገጥሚቸው፣ የሚያደርጉት ጠፍቷቸው ዝምታ ውጧቸዋል። አምባሣዳሩ እንኳ፣ መዝሙሩን አቁሙ ለማለት አስቦ፣ ያሉትን የውጭ እንግዶችና ዲፕሎማቶች፣ የበስተኋላ ትችት የፈራ ይመስላል፣ አልደፈረም። ውጣቶቹ ራሳቸው መዝሙሩን አሉት፣ አሉትና ሲበቃቸው፣ መጨረሻ ላይ “በትዕግሥት ስላዳመጣችሁን እናመሠግናለን !” በሚል የተባበረ አንድነት ድምፅ ተናገሩና እንግዶቹን አሰናበቱ።

“ከመሔዳችን በፊት ስላቀረባችሁት አሳብም ሆነ ሌላ ነገር እናነጋግራችኋለን!” የምትለውን ዐረፍተ-ሐሳብ ብቻ፣ እንደምንም ተንፍሰው ሲመጡ የተደሰቱትን ያህል፣ ሲመለሱ በሽቀው ጭልጥ አሉ። ምድረ-አጃቢ ሁሉ በሆዱ ጉድ እያለ፣ እንግዳውን አምባገነን ተከትሎ ሸመጠጠ። የበዓሉ ዝግጅት በዚህ ሁኔታ ከተፈፀመ በኋላ፣ ለዕለቱ ሁሉም ተማሪዎች፣ የቀሩትን ተጨማሪ ሰዓቶች፣ እንደፍላጐታቸው እንዲዝናኑበት ተፈቀደላቸው።

በዚህ በዓል ላይ፣ ለሕፃናቱ በበጐ ፈቃድ የተመደቡ፣ ያሉበት ሀገር ቤተሰቦች ጥሪ ተደርጐላቸው መጥተው ስለነበር፣ ለሰመነ የተሰጡትም የሀገሩ ቤተሰቦች ተገኝተው ነበር። የፕሮግራሙ ዝግጅት እንዳበቃ፣ ሁሉም ቤተ-ሰቦች ምድብ ልጆቻቸውን እየተሰናበቱ፣ ወደየቤታቸው ሲሔዱ፣ የሰመነ ቤተሰቦች ግን በተለይም የዚያ ሀገር ሞግዚታዊ እናቷ፣ በጣም ስለሚወዷት፣ በዚያንም ወቅት ረዘም ላለ ጊዜ እቤታቸው ያልሔደች መሆኗን፣ ለአንድ ለሚያውቋት ሞግዚቷ ነግረው ወደ ቤታቸው ይዘዋት ይሔዳሉ። የሰመነ ቤተ-ሰብ የሚጨነቁላት፣ በተለይ ስለወላጅ እናቷ የሚሰማትን ጭንቀት ስለሚያውቁ ነው። እነሱም ቢሆኑ ደስ ብሏቸው የሚኖሩ ሰዎች አይደሉም። በተለይ ባለየው በፖለቲካ ግፊት ምክንያት፣


እንደታሠረና እንደተፈታ የኖረ ነው። ያ ትልቅ በዓል፣ በነሰመነ ት/ቤት ከተከናወነ በኋላ፣ በማግሥቱ አንድ ትንግርት ተፈጠረ። ሰመነ ለአንድ ቀን ዕረፍት፣ ከሀገሩ ሞግዚታዊ ቤተሰቦቿ ጋር ለመቆየት፣ አብራቸው ከሔደች በኋላ እንደገና አልተመለሰችም። በጣም የሚደንቀው ደግሞ፣ እሷ ብቻ ሳትሆን የጠፋችው፣ ሁለቱ ቤተሰቦቿ ባልና ሚስት ጭምር ናቸው። የቀሩት የሰመነ ጓደኞች ሁሉ፣ የሷ መጥፋት ከታወቀ በኋላ፣ ብረት በያዙ ወታደሮች መጠበቅ ተጀመረ። ካሉበት ክፍልም፣ ደጋፊዎች ሳይቀሩ፣ ወደ ውጭ መውጣት ተከለከሉ።

በዓሉ በተከናወነ በአራተኛው ቀን፣ የሀገሩ መሪና እንግዳው አምባገነን ወደ ትምህርት ቤቱ ተመልሰው መጡ። አመጣጣቸው ሌላ በዓል ለማክበር አልነበረም። በቀረበላቸው የምርመራ ውጤት መሠረት፣ በት/ቤቱ አስተዳዳሪ ወይዘሮ አማካይነት፣ ሕፃናቱን ለማነጋገርና፣ ፍርድ ለመስጠት ነበር። ግን በተማሪዎቹ አድማ ምክንያት፣መልስ የሰጣቸው አንድም አልነበረም። የሀገራቸው እንግዳ አምባገነን፣ "ውስጄ ሀገሬ ፍርድ ልስጥ" ሲሉ፣ ያገሩ መሪ ደግሞ "እድሜያቸው አይፈቅድም" ሲሉ፣ አምባገነኑ እንግዳ "ባገራችን፣ ወንጀለኛ ፍርድ አያስፈልገውም !" ሲሉ፣ ክርክር ገጥመው ከቆዩ በኋላ፣ እዚያው ባሉበት ከተማ እንዲቀጡ ተብይኖ፣ ዛሬም ሕፃናቱ ቅጣት ላይ ይገኛሉ። ሰመነ ግን፣ ከሀገሩ ሞግዚቷ የመረራቸው ቤተሰቦቿ ጋር፣ በዚያ ሰሞኑ የጀልባዎች ጉዞ፣ ወደ ጎረቤት ሀገር ከተሰደደች በኋላ፣ አሁን አውሮፓ ትገኛለች። የምትናፍቅ እናቷን ግን ዛሬም አላገኘችም !

---

t.me/OLDBOOKSPDF

እናቴን ለመቅበር



አንድን ሕዝብ ለመግዛት፣ ዓይነተኛው ጥበብ፣
"መበተን ፣ግራራት ፣ ግንኙቱን ግጥበብ!"
ነው አሉ ሲታውንት ፣ ያጠኑ ሥነ-ሕዝብ።

ከፋፍሎ ለመግዛት፣ ለገዥ እንዲያመች፣
ዕድሞ፣ ወሰን ፣አጥር፣ ያበጃል ሳደለች።

እናትን ከልጅዋ፣ሳትወድ ይነጥላል፣
አንድ ላይ ካሉማ፣ራሱም ይደግል!


ሰለዚህኮ ነው ፣ይሰፍ ረታድ ጠፍቶ፣
የማያረናፍን ፣የውስጥ ደንብ ሠርቶ፣
ከርችሞ ወጥሮ ፣ በርቄን ዘጋግቶ፣
ፋሽስት የሚያሰጨንቅ፣ሕዝቦችን በሳልቶ!

እንደታሠረና እንደተፈታ የኖረ ነው። ያ ትልቅ በዓል፣ በነሰመነ ት/ቤት ከተከናወነ በኋላ፣ በማግሥቱ አንድ ትንግርት ተፈጠረ። ሰመነ ለአንድ ቀን ዕረፍት፣ ከሀገሩ ሞግዚታዊ ቤተሰቦቿ ጋር ለመቆየት፣ አብራቸው ከሔደች በኋላ እንደገና አልተመለሰችም። በጣም የሚደንቀው ደግሞ፣ እሷ ብቻ ሳትሆን የጠፋችው፣ ሁለቱ ቤተሰቦቿ ባልና ሚስት ጭምር ናቸው። የቀሩት የሰመነ ጓደኞች ሁሉ፣ የሷ መጥፋት ከታወቀ በኋላ፣ ብረት በያዙ ወታደሮች መጠበቅ ተጀመረ። ካሉበት ክፍልም፣ ደጋፊዎች ሳይቀሩ፣ ወደ ውጭ መውጣት ተከለከሉ።

በዓሉ በተከናወነ በአራተኛው ቀን፣ የሀገሩ መሪና እንግዳው አምባገነን ወደ ትምህርት ቤቱ ተመልሰው መጡ። አመጣጣቸው ሌላ በዓል ለማክበር አልነበረም። በቀረበላቸው የምርመራ ውጤት መሠረት፣ በት/ቤቱ አስተዳዳሪ ወይዘሮ አማካይነት፣ ሕፃናቱን ለማነጋገርና፣ ፍርድ ለመስጠት ነበር። ግን በተማሪዎቹ አድማ ምክንያት፣መልስ የሰጣቸው አንድም አልነበረም። የሀገራቸው እንግዳ አምባገነን፣ "ውሕጄ ሀገሬ ፍርድ ልስጥ" ሲሉ፣ ያገሩ መሪ ደግሞ "እድሜያቸው አይፈቅድም" ሲሉ፣ አምባገነኑ እንግዳ "ባገራችን፣ ወንጀለኛ ፍርድ አያስፈልገውም !" ሲሉ፣ ክርክር ገጥመው ከቆዩ በኋላ፣ እዚያው ባሉበት ከተማ እንዲቀጡ ተበይኖ፣ ዛሬም ሕፃናቱ ቅጣት ላይ ይገኛሉ። ሰመነ ግን፣ ከሀገሩ ሞግዚቷ የመረራቸው ቤተሰቦቿ ጋር፣ በዚያ ሰሞኑ የጀልባዎች ጉዞ፣ ወደ ጎረቤት ሀገር ከተሰደደች በኋላ፣ አሁን አውሮፓ ትገኛለች። የምትናፍቅ እናቷን ግን ዛሬም አላገኘችም !

----------***----------

እናቴን ለመቅበር



አንድን ሕዝብ ለመግዛት፣ ዓይነተኛው ጥበብ፣
"መበተን ፣ግራራት ፣ ግንኙቱን ማጥበብ!"
ነው አሉ ሊቃውንት ፣ ያጠኑ ሥነ-ሕዝብ።
ከፋፍሎ ለመግዛት፣ ለገዥ እንዲያመች፣
ዕድሞ፣ ወሰን ፣ አጥር፣ ያበጃል ሳይለሰች።
እናትን ከልጅዋ፣ ሳትወድ ይነጥላል፣
አንድ ላይ ካሉማ፣ራሱም ይደግል!
ስለዚህኮ ነው ፣ ይለፍ ሬቃድ ጠፍቶ፣
የግያሩናዥን ፣ የውስጥ ደንብ ሠርቶ፣
ከርችሞ ወጥር ፣ በርቼን ዘጋግቶ፣
ፋሽስት ሮሚያሰጨንት፣ ሕዝቦችን በላልቶ!

t.me/OLDBOOKSPDF

መንደርደርያ

ማንኛውም የሰው ልጅ እንዲሁ እምሳበ–አልቦ፣ ከሰማያት በርቆ የተገኘ አይደለም። በጥምር ወላጆቹ አማካይነት፣ በሕገ–ተፈጥሮ የተወለደ ነው። በመሆኑም፣ የተወለደበት ሀገሩ፣ አፅመ–ርስቱና መብታዊ ቤቱ ነው። ግላዊ መናኸሪያው እስከሆነም ድረስ፣ የሌሎችን መብት ሳይጨነቁር እንደፈለገው የመኖርና የመዝናናት መብት አለው። በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ፣ የሚደክም እግሩ ይጭነቀው እንጅ፣ የመንቀሳቀስና የመጓዝ ነፃነት አለው። በሀገሩ ላይ በፈለገው ጊዜና ቦታ የመዘዋወር መብቱንና ነፃነቱን ምንም ዐይነት ምድራዊ ኃይል ሊያግርበትና ሊከረችምበትም አይገባም። የዚያ ሀገር ሰው ሆኖ የተገኘ ለታ፣ የተሰጠው የተፈጥሮ ልደታዊ ነፃነቱ ነውና ።

ታዲያንን፣ አለመታደል ሆኖ፣ አንዳንድ ጋጠ–ወጥ የዘመናችን የገዥ ቁንጮዎች የራሳቸውን ክብርና ገናናነት ያስከበሩና፣ የሕዝባችንንም የሕልውና መብትና ነፃነት እንደግል ችግሮታቸው የሚለግሡ እየመሰላቸው፣ በፈለጋቸው ሚና የሚነዱትን ሕዝብ፣ በገዛ ምድሩና በገዛ ሀገሩ ውስጥ፣ ከቦታ ወደቦታ በፈለገው ጊዜ እንዳይንቀሳቃስ አገረውት ይገኛል። ይህንንም ኢሰብዓዊ እገዳቸውን፣ በአዋጅና በልዩ ልዩ ኢሕጋዊ ትዕዛዛቸው በማጠናከር መዝናናት የተፈጥሮ ስጦታው የሆነውን ሕዝባችንን፣ እንዳይንቀሣቀስ አፍነውት እያወራጩት ነው።

በራሳቸው እምነት የሌላቸው፣ እሊህ ጭብጥ የማይሞሉ የገዥ ቡድናዊ መደቦች አካል፣ በዚያ ሕዝብ መሠረታዊ የመንቀሳቀስ ፍላጎቱ ላይ ሲያሾፍና

t.me/OLDBOOKSPDF

ትንግርት የሚታይበት፣ የሚጎበኝ ቦታ ነው። ለእንደዚህ ዐይነቱ የመጎብኘት ፍላጐት፣ የመንቀሳቀስ ነፃነት መኖሩ ተቀዳሚና ወሣኝም ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ በየዘመኑ በተፈፀሙ፣ የጦርነት፣ የመፍለስ፣ የጋብቻ፣ የሥራ ዝውውሮች፣ ... የተነሳ ብዙ የማኅበረ-ሰቡ አባሎች፣ በተለያዩ ክፍለ-ሀገሮች፣ እንደጪው ተበትነው ይገኛሉ። ሌላው ቀርቶ የአንድ ቤተሰብ አባሎች እንኳ፣ በየምክንያቱ፣ በየቦታው ተሠራጭተው ይኖራሉ። በቆየው የሀገራችን ልምድ መሠረት የቤተ-ዘመድና የወዳጆች ተዘዋውሮ መጠያየቅ ነባር ባሕል ስለሆነ ተገናኝቶ መጪዋወት፣ ፍላጐቱም፣ ግዴታውም፣ ምኞቱም ጭምር ነው። ባሕል ባስገኛቸው የጋብቻ፣ የልደት፣ የተዝካርና፣ በሌሎቹም የሐዘንና የደስታ ዝግጅቶች ከያሉበት ተሰባስቦ መገናኘት የነበረና ያለ ነው።

ይሁን እንጅ፣ ከድኅረ-የካቲት ጀምሮ በዐብዮት ስም፣ የጥቂት ገዥ ቡድኖችን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል፣ የተለያዩ ቤተሰቦችም ሆኑ ወዳጆች እንዳይገናኙ በአዋጅ ተደንግጎ እንደተነጣጠሉ ቀርተዋል። "ነጣጥለህና ከፋፍለህ ግዛ" በዚህ መልኩ በድርጊት ሲገለፅ ቆይቷል። ናፍቆት ሲያቃጥለው ይኖራታል እንጅ፣ ፍቅረኛም ጓደኛውን፣ ልጅም እናቱን ... የማየት እድላቸው የመነመነ ነው። በእገራው ፀጥታ ውስጥ የገዥ መደቡ እንደፈለገው ይፈልላል፣ እስረሽ ምቺውንም እንዳጦፈው አለ። በአዲስ አባባ እንኳ የስዓት እላፊው አዋጅ ባስከተለው ጦስ፣ ከቀበሌ እሥር ቤቶች ቦታ ጠቧቸው በሠንዳፋና በከርቸሌ ታጭቀዋል። ...

በተፈጥሮው ነፃ ባሕርይ ያለው የሰው ልጅ፣ አንድ ቦታ ብቻ ታፍኖና ታጅሎ መኖር አይዋጥለትም። ይህ ዐይነቱ እገራም፣ ሰብዓዊ የመንቀሳቀስ መብቱን ይፃረርበታል። አካላዊ መዋቅሩ ሳይቀር የመንቀሳቀስ ባሕል ያለውና ሆነኝም ተብሎ የተሠራ ነው። ተጓዥ (ሎኮሞቲብ) ነው። ታዲያንን ሁልጊዜ ተለጉሞ መቀመጥ አይሆንለትም ከድኅረ-የካቲት ጀምሮ የምናየው ያገራችን አገዛዝ ግን፣ በተቃራኒው፣ ከስፍራ ወደ ስፍራ "ልውሽ፣ ድርሽ፣ ፈቀቅ፣ ንቅንቅ..." የለም የሚል ነው። የዚች አጭር ልቦለድ ጭብጥ ይህን አሠቃቂ የሰው ልጅ መብት ረገጣ አሰመልክታ፣ በገጠር የሞቱ እናቱን ለመቅበር አንድ ከተማ የሚኖር

ሲቀልድ፣ ነበረም አለም። ይህ "የአትንቀሣቀስ" እገራ፣ ከድኅረ-የካቲት ጀምሮ በኢትዮጵያውያን ላይ፣ ከወረዱት መዓቶች ውስጥ አንደኛው ነው። ነጋዴው ተዘዋውሮ እንዳይነግድ፣ ሞፈር ዘመቱ ገብሬ ተዘዋውሮ እንዳያርስ፣ ሕዝቡ ተዘዋውሮ ከወገኑም ሆነ ከዘመዱ ተገናኝቶ እንዳይወያይ፣ ... በማያፈናፍን አዋጅ ከርቸሞ፣ ሲያስጨንቀው ኖሯል፣ አለም። ይህች አጭር ልቦለድ ታሪክ፣ ይህን አፈና በማስመልከት የተነደፈችና ታሪካዊ ብልጭታነቷም ይህን አሠቀቂ፣ የሰብዓዊ መብቶች አንዱ የሆነውን ክፍል፣ ረገጣና አፈና የምታንፀባርቅ ጭላንጭል ናት።

ከነፃነት ዘርፎች አንዱ፣ ከቦታ ወደ ቦታ፣ ያለአንዳች ሐሳብ፣ ቀልብ ሳይሠቅሉ፣ እንደልብ መዘዋወር መቻል ነው። በተለይም በገዛ ሀገር ውስጥ በራስ ምድር ላይ፣ የመጓጓዣውን ብርና የእግር ጣመን ይጭነቀው እንጅ ከፈለጉበት መካን፣ አምባ፣ ደብር፣ መንደር ግዛት ... መሔድ፣ ማደር፣ መንሻርሸር፣ የየአካባቢውን ነፃና ትኩስ ዓየር መተንፈስ፣ ተፈጥሮንም ተዘዋውሮ አይቶ ማድነቅ ... ትልቁ፣ ሰው የመሆን ነፃነት ነው። በተለይም የተለያየ መልክአ-ምድር ያላት ሀገራችን፣ በደጋ፣ በወይና አደጋ፣ በቆላ፣ በበረሐ፣ በባሕረ-ሽሽ ... የተከፋፈለች እንደመሆኒ መጠን ተዘዋውሮ ለመጎብኘት ማነኛውንም ኢትዮጵያዊ ያጓጓል። "የሚበላው ዳቦ የሌለው" አትበሉኝ እንጅ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሞኙቱ አንባር፣ እንዲያ እንዲያ ነው። በተለይም ደግሞ፣ የታሪክ ቅርሶቻችን የሚገኙባቸው ሥፍራዎች በተለያዩ ክፍለ-ሀገሮች በመሆናቸው፣ "የእገራው አዋጅ" በመንቀሳቀስ እገዳው አንባር ያለውንም ሌላኛ ተልእኮ ይጠቁማል። እነአኩስም፣ ላሊበላ፣ ጉንደር፣ ደብረ-ዳሞ፣ ደብረ-ቢዘን፣ ግሸን፣ መቅደላ፣ አንኰበር፣ አደረ ጢቆ፣ ኑራ ሁሴን ... እዩን እዩን በሚሉበት ዘመን፣ "እትንቀሳቀሱ" ን፣ ምን እንዳመጣው ከሌላ ጉዳይ ጋር ማገናዘቡ ቀላልና አስቸጋሪም አይደለም።

በተፈጥሮ ታሪካዊ ትርዒቱም፣ የነአባይ፣ የነግቤ፣ የነኦሞ፣ የነዋቢ ሸበሌ፣ ...ገጽታ እጅግ የሚስብ መሆኑን የሚያውቅ ሁሉ ያውቀዋል። እንደገሙ ጎፋ ያለው "የእግዜር ድልድይም"፣ ሌላው እውቀትና ደስታ የሚያስገኝ የተፈጥሮ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኢትዮጵያዊ፣ ሐዶ ለመቅበር የደረሰበትን ጣጣ ፈንጣጣ በጨረፍታ ታትታለች። ይህን ኢሰብአዊ እፈና በሽንቁር ጭላንጭል ለማሳየት በመሞከሯ፣ ትልቁን የሰው ልጆች የመንቀሳቀስ መብት መደፈር የምታሳይ "የብልጭታ ነፀብራቅ" ናት መባሏም በዚሁ ባሕርይዋ ነው። ይቻትላችሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እናቴን ለመቅበር

"... ራሴን ከራሴ የበለጠ የሚያውቅ ሌላ ሰው እንደሌለ እምናለሁ። እኔ ራሴ እኔነቴን ለማወቅ ብዙ ዘመን እንደፈጀብኝ ተረድቻለሁ። የገዛ ራሴን ባሕርይና ዝንባሌ፣ የእኔነቴንም ጠባይ ለመመርመር ምን ያህል ጉልበትና ትዕግሥት እንዳስፈለገኝ ከኔ ውጭ የሚያውቅ የለም። አካባቢ ኃይሎች የነደፉብኝን ሥዕሎች ሳንፀባርቅ መኖሬ ግን፣ ካቅሜ በላይ በግዳጅ የፈፀምኩት እንጅ፣ በውዴታዬ እንዳይደለ አውቃለሁ። ብሎም አካባቢዬን በሙሉ በነፀብራቄ አልቀዳሁም። አለያማ፣ በሠካራም ኅብረተ-ሰብ መካከል አድጌ፣ ጥሩ ጠጭ በወጣኝ ነበር። በቅንዝረኛና በዘማዊ ኅብረተ-ሰብ ጭን ስር ተመንድጌ፣ የወጣልኝ ቅንዝረኛ በሆንኩ ነበር። በሌባና በቀማኛ ኅብረተ-ሰብ አካባቢ ጉልብቼ፣ ካራዳዎቹ ወይም ከካቤኖዎቹ ወይም ከደርጉቹ ጩልሌዎች የበለጥኩ መንታፊ በወጣኝ ነበር።

የራሴን ግላዊ ድክመቶች በሚገባ ባውቃቸውም፣ ድክመቶቼ ሁሉ እንዲያ እንዲያ የመሳሰሉት አልነበሩም አይደሉም፣ አይሆኑምም። የነቃሁ፣ የጠራሁ፣ ሙሉ ጨዋ ባልሆንም፣ የለየልኝ፣ የወጣልኝ ሙሉ ባለጌ እንዳልሆንኩ አውቃለሁ። ራሴን በራሴ የማውቀው፣ እዚህ ድረስ ቢሆንም፣ ሌሎች ስለኔ በሚሠነዝሩት አስተያየት እገረማለሁ። ደግነቱ የሚያሥቀኝ እንጅ፣ የሚያሰከፋኝ አለመሆኑ ነው። የፈለገውን ያሰተያየት ገመድ ቢተበትብ፣ እኔን ሊሸብበኝ እንደማይችል አውቃለሁ። የፈለጋቸውን የመሠናክል ወጥመድ ቢኰለኩሉ፣ እኔን እንደማያደናቅፈኝ አምናለሁ።

አንዳንዴም ከንቱ ሙከራቸው ሁሉ ሲታሰብኝ፣ ስለራሴ ሳይሆን፣ ስለራሳቸው እዝናለሁ። እንዲህ ዐይነቶቹ ሰዎች፣ እነዚያን መሰል አስተያየቶች ሲሠነዝሩ፣

የራሳቸው መነሻና የግላቸው አመለካከት አስገድዷቸው እንደሆነ ይታየኛል። ከምን ላይ ተነስተው፣ በምንስ አመለካከት፣ የሚለውን ሐተታዊ ጥያቄ ግን፣ ማንሳትና መተንተን ማንነታቸውንና ምንነታቸውን ለመረዳት ያስችላል። ኧረ ለመሆኑ፣ እንዲህ፣ የወለደችኝን እናቴን፣ ቢቻል አስታምሜ ባይቻልም ለመቅበር፣ የሚከለክሉ ጉዶች ከምን የፈሉ መዓቶች ናቸው? ...” እያለ ልቡን እንደሳተና አእምሮውን ነካ እንዳደረገው ሰው፣ እቤቱ የናቱን መርዶ ስምቶ፣ ከጥቂት ጓደኞቹ ጋር ተቀምጦ በእንቡዘ–ልብ የሚያነበንበው ትዝታ ነው።

እድሜው አቅመ–አዳም ቢደርስም፣ አልተዳረም። “ሚስትና ጉንፋን” እንዲሉ፣ አጣማጁን ማግኘት ተስኖት ሳይሆን፣ በየሰበብ አስባቡ ዘግይቶ ነው። ተምሮ፣ ሥራ አግኝቶ ቤት ሠርቶ፣ ቆሳቁሶች ተሟልተውለት፣ ለትዳር ዝግጅት ላይ ነበር። በተለይም፣ “ሠርግህን ሳላይ እንዳልሞት” እያሉ፣ ያስጠነቅቁት የነበሩ እናቱ፣ የዩኒቬርሲቲውን ትምህርት እስኪጨርስ እንዲታገሡት ብዙ ጊዜ ይማጠናቸዉ ነበር። ኋላም ትንሽ ጥሪት ልያዝ፣ ጉጆ ልቀልስ፣ እያለ፣ የናቱን ጥያቄ ሳይመልስ ብዙ ጊዜ ቆይቶ ነበር። ወላጅ አባቱ፣ ገና እሱ በሕፃንነቱ እንዳለ፣ ከዓለሙ በሞት ስለተለዩ፤ እንድ እናቱ፣ እንደ አባትም፣ እንደ እናትም ሆነው ስላሳደጉት፣ የናቱ ውለታ፤ የሰማዩን ያህል እንደሚከብደው ዘወትር ይሰማዋል። ስለዚህም ነበር፣ ትዳር መሥርቶ፣ ወላጅ እናቱንም ካሉበት ክፍለ ሀገር፣ አዲስ አበባ በማስመጣት ከቤተ–ሰቡ ጋር ባንድነት ለማኖር በማሰብ ላይ እንዳለ፣ ድንገት የናቱን መርዶ የሰማው።

ይህ አሳዛኝ ወጣት፣ አኖሬዎስ ይባላል። ይህን ስም ያወጡለት ወላጅ አባቱ ናቸው። ምን ማለት እንደሆነና ለምንስ በዚህ ሥያሜ እንደጠሩት፣ እናቱም ይሁኑ ራሱ የሰሙ ባለቤት አያውቁም። ከትምህርት ቤቶችና ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መዝገቦች ላይ ሳይቀር፣ በደፋ ተመዝግቦ ሲጠራበት፣ ከሠላሳ ዓመታት በላይ አልፈዋል። የሚሠራው በተመረቀበት የንግድ ሙያ ተመድቦ፣ ከአዲስ አባበ ንግድ ምክር ቤት ነው። መኖሪያው ግን፣ በጭስኝነት ተመርቶ፣ በብድር ከሠራው፣ ከኰተቤ አካባቢ ነው። በዶሞዝ ሰሞን ብቻ የሚያመጣት አንዲት

t.me/OLDBOOKSPDF

ከርካሣ ቮክስ አለችው። ያውም ቢሆን፣ በጣም ሲነሽጠው እንጅ፣ በብዙ የደሞዝ ወቅቶችም ያላወጣበት ጊዜ አለ። ወረት ለሚፈጥሩ ብርቅዬ ነገሮች፣ በጣም ቁጥብ ነው። ባለባበሱም ሆነ ባኗኗሩ ግድየለሽ ነው። የፀደይ ልብስ የበጋ ልብስ...የሚሉ የየወቅቱ ልብሳዊ ዘዬዎች ትዝም አይሉት። ለወረት ተብሎ የሚደረግ ነገር ሁሉ፣ በሽታው ነው። ለጤናው በማሰብ እንጅ፣ ለውብት ሲል ፀጉሩን ያስተካከለበትም ሆነ ያበጠረበት ወቅት፣ ትዝም አይለው። ለናዜራ ስሜቶቹ የተንበረከከባቸው ጊዜዎች፣ በጣም ውሱን ናቸው። ተንኰል የሚባል ነገር፣ ሊያደርገው ቀርቶ ሌሎች ሲፈፅሙ ሲያይ፣ እጅግ ያዝናል። ከየዋህነቱ የተነሣ፣ ባልንጀሮቹ ሁሉ “በጉ” የሚል ሥያሜ ሰጥተውታል። የዋህ ይሁን እንጅ፣ የዋህነቱ ድንበር አለው። ጌታ በሎሌው ላይ ሲፈነጭበት፣ ሀብታም በደሀው ላይ ሲያፈጥበት ብልጡ በሞኙ ላይ ሲያሾፈበት፣ ከበርቴው በላብ አደሩ ላይ ሲጋልብበት፣ ጉልተኛው በገባሩ ላይ ሲሸናበት ... አጋጥሞት ባየ ቁጥር፣ ዛር የሠፈረበት ባለአዶ ከብረሮ ይመስል፣ በንዴት ያንቀጠቀጠዋል። አንዳንዴም ሁኔታው አላስችል ብሎት ቡራከረዩ በማለቱ፣ ባለጉልበተኞች ይዘው “ቸብቸብ” የተደረገበት ወቅት ነበር።

ወጣት አኖሬዎስ፣ በበጉ ምግባሩና በሽጋ ባሕርዩ፣ የማያውቀው የጐረቤት ሰው የለም። ቅንነቱና የተገራ ጠባዩ ያለአባት ያደገ፣ አያስመስለውም። በወላጅ እናቱ ግለኛ ርዳታ ያደገ ቢሆንም፣ “ሴት ያሳደገው !” የሚያሰኝ ባሕርይም ሆነ ዝንባሌ አልነበረውም። ወላጅ እናቱም፣ አካባቢው ካስገኘላቸው ሥርዓት፣ በጐውን እየመረጡ ተጪንቀውና ተጠበው ነው፣ በእንክብካቤ ያሳደጉት።

“የእንጀራ አባት” ተግሣፅና በትር እንዳይደርስበትም በማሰብ፣ ሌላ ወንድ ሳያውቁ በብቸኝነት የኖሩትም ለአኖሬዎስ ልጃቸው ሲሉ ነው። ገና ሕፃን ሆኖ በባላገር ሳለ፣ ለእረኝነት ተግባሩ ወደተሠማራበት መስክ ድረስ በመሔድ፣ ምግብ ሲያቀርቡለትና መንፈስ–ጠንካራ እንዲሆን የሚያስችሉትን፣ የተለያዩ ተግባራዊ ምክሮችን ሲለግሡት ያያቸው ሰው ሁሉ፣ ላንድዬ ልጃቸው ምን ያህል እንደሚንሠፈሠፉለት ያውቅ ነበር። የሚች አባቱ ታናሽ ወንድም የነበሩ አጐቱ፣

የሚኖሩት ከመናገሻው ከተማ ስለነበር፣ አዲስ አበባ በጉልማሳነቱ ወራት አምጥተው ያስተምሩት ነበር። አጉቱም ቢሆኑ፣ እንደ ወላጅ አባቱ፣ በአፍላ ዘመናቸው በድንገተኛ አደጋ ስለሞቱበት፣ አኖሬዎስ አብዛኛውን የትምህርት ዘመኑን ሊቋቋምና ሊገፋ የቻለው፣ ልዩ ልዩ የጉልበት ሥራዎችን በመሥራትና ራሱን ያለንዳች ረዳት በራሱ ጥረት ብቻ በመደገፍ ነበር። በዚያ ረዥም ዘመናት ውስጥ፣ ለተወሰኑ ጊዚያቶች ብቻ ዕድል አግኝቶ፣ እናቱ ከሚኖሩበት የትውልድ ቦታው፣ ወለንጭቲ ብቅ ብሎ ጠይቋቸዋል። ትልቁ ዓላማው ግን ትምህርቱን ጨርሶ ሥራ እንደያዘ፣ ወላጅ እናቱን አዲስ አበባ አምጥቶ፣ ከሚበላው እያበላ፣ ከሚለብሰው እያለበሰ ለመጦር ነበር። ግን ታመው ሞቱ።

የወላጅ እናቱን ሞት መርዶ ሰምቶ፣ ሀዘን ላይ መቀመጡን ያወቁ፣ የወላጅ እናቱ የድሮ ጓደኛ የነበሩ አንዲት ጠጅ ነጋዴ እመቤት፣ ከሀዘኑ ተከፋይ ለመሆንና ለማፅናናት፣ ከሚኖሩበት ሠፈር፣ ከጉለሌ ይመጣሉ። ወትሮም ቢሆን የናቱ አደራ ስላለባቸው፣ አልፎ አልፎ ብቅ እያሉ ይጠይቁት የነበሩ ናቸው። አኖሬዎስ ከመኖሪያ ቤቱ፣ ከጥቂት ጓደኞች ጋር ተቀምጦ በሐዘን ላይ እንዳለ እኝህ እመቤት፣ "እህቴ እህቴ ምን አገኘዎ ፣" እያሉ ደረታቸውን እየመቱና እያለቀሱ ይገባሉ። ያገር ደንብ ነውና፣ እቤቱ ውስጥ ያለው ሁሉ ልቅሶውን ተቀብሎ ካለቀሰ በኋላ፤ ለሴትዮዩቱ የሚያርፉበት መቀመጫ ይሰጣቸዋል። እመቤቲቱም ልቅሶአቸው ጋብ ካለ በኋላ፤

"አንተዬ አኖሬዎስ ፣ እኔን አፈር ይብላኝና፣ እንዲያ ሲንሰፈሰፉልህ ሞተው ይረፉ፣"

"አዎን፣ ይኸውልዎ፣ አንድ እጅ ብቻ ነበረኝ፣ እሱንም ተቆረጥሁ"

"ለመሆኑ መቸ ነው ያረፉት ፣"

"ትላንትና ሣምንቷ አለፈ ፣"

"እንዴ ቆይቷልና ፣"

"አዎ ዘጠኝ ቀናት ሆነ ፣

"ለመሆኑ አንተ የሰማኸው መቸ ነበር ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ገና በጠና ታማ ለመሞት ስታጣጥር ሳለች ነበር ፣"

"ታድያ ሔደህ አየኻቸው እንዴ ?"

"ሞክረ አልተሣካልኝም ፣"

"ድራሼ በጠፋ፣ መሔድ አልቻልክም ?"

"እኔማ ምኞቴና ሐሳቤ፣ ሌላው ቢቀር፣ ማለቴ በክብር መጦሩ እንኳ ቢቀር፣ እዚሁ እኔውጋ አምጥቼ ለማስታመም ነበር ፣ አልሆነልኝም አልዎታለሁ ፣"

"ለመሆኑ ምን ዐይነት ዘመን ላይ ደረስን ይሆን ? ሰው ወላጅ እናቱን እንኳ ለማስታመም ያልቻለበት ቀውጢ ዘመን ፣ ኧረ ለመሆኑ የመሔጃ ፈቃድ ለማግኘት አመልክተህ ነበር?"

"እንዴታ ፣ እግረ ብቻ ሳይሆን ጉረርዬ ጭምር እስኪነቃ ድረስ ነበራ ፣"

"ምን መልስ ሰጡህ ?"

"ማዕከላዊው አመራር ውስጥ ጥያቄህ እየተጠና ነው"የሚል ነው ፣

"ጥያቄህ እንደተሠቀለ ሣለ ነዋ፣ እናትህ የሞቱት ፣"

"አዎን ፣ ያረፈችው ማመልከቻዬ ተንጠልጥሎ እንዳለ ነው ፣"

"እኔኮ በጣም የሚገርመኝ፣ ያሠራራቸው የጅራፍ ቁግ ያን ያህል ረዝሞ፣ መንዛዛቱና መንጦልጀሉ ብቻ ነው ፣"

"አዬ ይተውኝ እባክዎ፣እንደፈለጉ መጓዝ፣ በተመኙት አከባቢ ተንቀሣቅሶ መዝናናትም ሆነ፣ ጉዳይን ማከናወን ቀደም ቀረ ፣"

"ውነትህን ነው ፣ መላወስኮ አልቻልንም ፣ ድሮኮ ማር እንኳን ለመግዛት፣ በመርሐ ቤቴ ቆላና በጉጃም ገጠር ሳይቀር፣ በየሣምንቱ እየተመላለስንበት ነበር! ዛሬ እዚሁ ከተማችን ውስጥ እንኳ፣ የቦሌው እንጠጦ፣ የገፈርሳው ኩተቤ መዘዋወር አልሆነለትም ፣ ያሳዝናል ፣"

"በተለይማ፣ ይህ እኔ የምኖርበት ቀጠናና ቀበሌ፣ እንደ አንዳንዶቹ ቀበሌዎች፣ ያድኃርያን ቀበሌ የሚል ስም ስለተሰጠው፣ ያለው ቁጥጥርና ክትትል፣ በጣም ጥብቅ ነው። የቀበሌዎቹ ሹሞችና ዐብዮት ጠባቂዎች ጭምር በአድኃርያን መልክ

ስለሚታዩ፣ የቀበሌው ነዋሪ ለሚያቀርበው ማመልከቻ ሁሉ፣ ውሣኔውን የሚያገኘው፣ ከሌላ የተራማጅ ቀበሌ በሚመጡ ሹማምንት ነው።"

"ምን የናንተ ቀበሌ ብቻ ! የየትኛውም ተመሳሳይ ነው። በየምሽቱ እኔጋ የሚመጡ፣ የየቀበሌው ሰዎች ሁሉ ሲያማርሩ ሰምቻለሁ !"

"ምን ማለትዎ ነው ! ማን ያልተቸገረና ግራ ያልገባው አለ ብለው ነው ? የማያፈናፍኑ ድርጊቶች እየደረጁና እያደጉ በመምጣት ላይ ናቸው።"

"ምን በመምጣት ላይ ናቸው ትላለህ ! መጥተዋል እንጅ ! ወላጅን ከልጁ፣ ሚስትን ከባሏ፣ ዘመድን ካዝማዱ ሲያራርቀውና ሲለያየው እያየን ! እንዲያማ ባይሆን ኖሮ፣ እንድ ወላጅ እናትህን መቅበር፣ መች ያቅተህ ነበር ! ምን አንተ ብቻ ! እኛ ሁላችንም ተገኝተን፣ በሥርዓት በሸኘናቸው ነበር !"

"እዬ ይተውኝ፣ አንጀቴኮ ነው የተቃጠለው !"

"እንተ እንኳ፣ ክፋት የማታውቅ፣ ተንኮል የሌለብህ ሰው ነበርክ ! እንዴት ሊከለክሉህ እንደቻሉ ገርሞኛል !"

"ምን መከልከል ብቻ፣ አንከራተቱኝ እንጅ ! እዚህ፣ አንዴ ቀጠና ሹምጋ፣ አንዴ ቀበሌ ሹም ዘንድ፣ አንዴ ዐብዮት ጠባቂዎችጋ፣ ከዚያ ደግሞ ከፍተኛ ዘንድ የተንገላታሁባቸው ሰዓቶች ጥቂት አልነበሩም። ከዚህ እንዳለቀልኝ፣ ደረቅ ጣብያ በማበል ከታወቀው የትውልድ ቦታዬ ለመድረስ፣ በየጣ ቢያው ያልደርሰብኝ ፈተና የለም። ከአቃቂ ጀምሮ እስከ ናዝሬት ለመድረስ አራት ቀናት ፈጅቶብኛል።

አንዴ የመታወቅያ ወረቀቴ በቂ አይደለም ስባል፣ አንዴ፣ ለማስተላለፍ የበላይ ትዕዛዝ እንጠብቃለን ስባል፣ የኋላ ኋላ መጨረሻ ላይ፣ በናዝሬቱ ከተማ የፓሊስ አባሎች፣ ወደ ወለንጪቲ የምጓዝበት ጉዳይ የሚያስጠረጥር መሆኑ ተነግሮኝ፣ በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ እንድመለስ ተደረገ። የትውልድ ቦታዬ፣ ወለንጪቲ መሆኑ እየታወቀ ወላጅ እናቴ በዚያ መኖሯ እየተረጋገጠ፣ በተለይም በአሐዜ ዓለም ተይዛ ለሞት በማጣጣር ላይ በመሆኗ፣ ያስቸኳይ መልእክት ማስተላለፍ እየታወቀ፤ "የወለንጪቲ ጉዞህ ያስጠረጥራል ..." ሲባል፣ የተሰማኝ ንዴትና ብሽቀት መግለጫ አላገኝለትም። ደግነቱ፣ ብሽቀቴ ለተወሰኑ ደቂቃዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

ያህል ሲያርበተብተኝ ከቆየሁ በኋላ፣ ቀኑን ሙሉ ደብቶኝ መዋሉ ብቻ በጀኝ እንጅ፣ ጤናማና ንቁ ብሆን ኖሮ፣ በራሴም ላይ ሆነ በሌላ ሰው ላይ፣ የከፋ እርምጃ ከመውሰድ ወደ ኋላ አልልም ነበር ??

"አይ ልጄ ! መታገሥ ነው እንጅ፣ መናደዱማ ምን እርባና ይኖረዋል ብለህ ነው ?"

"ኧረ ይተውኝ ! በናት ሞት ላይ የሚደረግ ትዕግስት፣ ምን ረብህ አለው ብለው ነው ? የኔ ጅልነት ማርኩኝ፣ ወይም ለመኖር ያለኝ ፍላጉት አሸንፎኝ፣ ይሆናል እንጅ፣ በገዛ ሀገሩ፣ በገዛ ወገኑ፣ በገዛ ምድሩ ... ለሚኖር ዜጋ፣ ብሔራዊ ክብሩን ተገፎና፣ ሰብአዊ ነፃነቱን ተነፍጉ፣ እየተሸማቀቁ ከመኖር የበለጠ፣ ምን የከፋ ሌላ ውርደት ሊያጋጥመው ይችላል ? በዚህ ዓይነቱ ህላዌ ሲንገላጀጁና ሲያደዘድዙ ከመኖር ይልቅ፣ አለመኖር ይመረጣል። በሕይወት መጨማለቁ፣ በተፈጥሮው ክቡር ለሆነ ሰው፣ ምርጫው አይደለም። የሚቻል ከሆነ፣ ሊለወጥ የሚችልበትን ዘዴ መሞከሩ ያዋጣል። አለያም፣ አንዳንድ ቆራጥ ወገኖቻችን ያሳዩንን አርአያነት፣ መከተል ይኖርብናል። የነ አቶ ዘካርያስ ጉዳና፣ አማራጭ የሌለው ጥርጊያ መንገድ ነው። በተጓዘበት መንገድ መከተል፣ በውርደት ከመኖር ይልቅ፣ በክብር መሞትን ያስገኛል ! በርግጥ ከነአቶ ዘካርያስ ቆራጥነት፣ መማር ይኖርብናል። አይመስላችሁም እንዴ ወንድሞቼ ?" ሊያስተዛዝኑት የተቀመጡቱን ጓደኞቹን ይጠይቃል።

"እነ አንተዬ፣ አቶ ዘካርያስ ደግሞ ማን ነው ?" አሉ እንግዳዋ ወይዘሮ።

"እዚሁ ኩተቤ የሚኖር ጉረቤታችን ነበር !" አለ ከጓደኞቹ እንዱ !።

"ምን ያጋጠመው ይሆን ? ያልሰማነው ትንግርት በየሠፈሩ ሞልቷልእኮ !"

"በደረሰበት ችግር ተበሳጭቶ፣ ያበሳጨትን ይዞ ያለፈ ነው !"

"መቸ ይሆን ይህ ደግሞ የተፈፀመው ?"

"ሦስት ወራት ያህል አልፎታል !"

"የማይደረግ ነገር የለም፣ ምን ነበር የተፈፀመበት ?"

"እዬ፣ የሱማ ሁኔታና የተፈፀመበት ግፍ ያሳዝናል !"

"ምን የማይፈፀም ግፍ አለ ብላችሁ ነው !"

"በሱ ላይ የደረሰው የተለየ ነው። ... በዚያ፣ አዋጅ በየቀኑ ይፈስ በነበረበት ወቅት ነው። የሚሠራው ትልቅ ኃላፊነት ያለበት የኢንጅነርነት ሥራ ነበር። ምድብ ሥራው ዐየር መነገድ ነው። ቦሌ ! እሱ መብረር ይችላል ብሎ ውሣኔውን በፊርማው ያላፀደቀለት ጄት አሮፕላን ሁሉ፣ ከቦታው መንቀሣቀስ አይችልም። ታዲያ በዚያ ሰሞን በአንድ የተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ፣ ሁለት የተለያዩና እርስበርሳቸውም የሚቃረኑ ተፀራርያን አዋጆች ይወጡ ነበር።

አንድ ዕለት ቀኑን ሙሉ "የየትኛውም መሥሪያ ቤት ሠራተኞች፣ በምድብ የሥራ ጊዜያቸው ወቅት፣ በምድብ ሥራቸው ላይ የማይገኙ ቢሆን፣ እንደ አድኃርያንና እንደ ፀረ-ዐብዮተኞች ተቆጥረው፣ ከፍተኛ ዐብዮታዊ እርምጃ ይወሰድባቸዋል" የሚል አዋጃዊ ማስጠንቀቂያ ሲነገር ይውላል። በዚያኑው ዕለት፣ ማታውን ደግሞ "ፀረ-ዐብዮተኞች፣ የፖለቲካ አሻጥር ለመፈፀም ስለተደረሰባቸው፣ በቁጥጥር ሥር ለማዋል፣ በሚወሰደው እርምጃ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፣ ነገ ማንኛውም ተሸከርካሪ ካለበት ቦታ እንዳይንቀሳቀስ !" የሚል ሌላ አዋጅ ይወጣል። አቶ ዘካርያስ ከዚህ ከኰተቤ መኖሪያ ቤቱ፣ ለሚመለከተው የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ፣ ስለሁኔታው በተቀዳሚ በስልክ ከነገረ በኋላ፣ መኪናውን ከቤቱ አስቀምጦ ረዥም ጉዞውን በእግሩ ይይዘዋል።

የዕለቱ በራሪ ጄት አውሮፕላኖች ሁሉ፣ አቶ ዘካርያስ፣ ቦሌ እስኪደርስ ድረስ፣ መጠበቅ ነበረባቸው። ልዩ የመጓጓዝ ፈቃድ የነበራቸው የውጭ ሀገር መንገደኞችም፣ ያለውዴታቸው፣ ያቶ ዘካርያስን መድረስ መጠበቅ ነበረባቸው። በእግር መጓዝ ልምድ ያልነበረው አቶ ዘካርያስ፣ የሁለት ሰዓት ጊዜ ያህል፣ ከምድብ የሥራ ሰዓት ጊዜው ዘግይቶ ይደርሳል። የሚጠበቅበትን ተግባር አከናውኖ፣ የዕለቱ መንገደኞች ጉዞአቸውን ከቀጠሉ በኋላ፣ አቶ ዘካርያስ፣ በምድብ የሥራ ሰዓት ጊዜው፣ በወቅቱ አለመገኘቱ፣ ሌላ አሻጥር ሲያከናውን ነው፣ በሚል ግምት አስጠርጥሮት፣ ወዲያው ለምርመራ፣ ወዳልታወቀ የቀበሌ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከፍተኛ እሥር ቤት ይወሰዳል። ከዚያም ቀን ጀምሮ ለአንድ ወር ያህል፣ የት እንደደረሰ የሚያውቅ ሰው አልነበረም።

ወሩን ጨርሶ እንደተለቀቀ፣ ስምንት ቀን ባልሞላው ጊዜ ውስጥ፣ አስፈላጊውን ግላዊ ዝግጅት አድርጉ፣ አንድ ወር ታስሮ ሲማቅቅ ወደ ነበረበት አካባቢ ሔዶ፣ በጊዜው የነበሩትን የቀበሌውን ባለሥልጣኖች ከረፈረፈ በኋላ በመጪረሻ ላይ፣ በያዘው መሣሪያው ራሱን ያጠናቅቃል። እንዴውም በሠፈራችን ዘካርያስ የሚለው ሥያሜ ተረስቶ "ሣልሳይ ቴዎድሮስ" ነው የሚባለው !"

"በቃህ ! በቃህ ! ልጄ። ብሶት ለያዘው ሰው፣ ማጭድ አታውሰው ! አኖሬዎስ ወጣት ልጅ ነህ። ተድረህ፣ ተኩለህ፣ ገና ዓለምህን አላየህም። በስንት ሥቃይ ስትማር ኖረህ፣ ገና አሁን ሥራ መጀመርህ ነው። ሁኔታው ቢያሳዝንም የሞቱትን እናትህን እንደገና በሕይወት ማግኘት አትችልም። ህዘንህን ዋጥ አርገህ፣ ኑሮህን መመሥረት ይኖርብሃል። በወረደብን መዓት፣ በየቤቱ ያልቀሰለና ያልነደደ ሰው አይገኝም። ርግጥ ፍቃድ አግኝተህ፣ እናትህ ካሉበት ሔዲህ አስታመህ ብትቀብራቸው ኖሮ፣ ህዘንህ በመጠኑም ቢሆን ይከፈልልህ ነበር ! ይኸ መቸም ቀላል ሠቀቀን አይደለም ! ግን ምን ያረጓል ! እናንተም ጓደኞቹ ምከሩት ! አፅናኑት ! የፈሠሰ ውሃ አይታፈስም !!

"ሌላው ቢቀር፣ አስከሬኗ የወደቀበትን መቃብሯን፣ ሔጄ ማየት አለብኝ !"

"እሱማ ያደርሰሃል፣ ቀስ ብለህ እንደገና አለስልስህ መጠየቅ ትችላለህ። ማመልከቻህን ስትፅፍም የልመና ቃና ያቤቱታ ሽታ፣ አክልበት። እንዴው በደረቁ፣ እንድሔድ ይፈቀድልኝ ብቻ ብትላቸው፣ ደስ የሚላቸው አይደሉም። ስምተኸኛል ?"

"አዩ ! እርስዎ ቢቸግርዎና ቢጨንቅዎ ነው እንዲህ የሚሉኝ ! እሪ እኔ በመለማመጥ ነበር፣ ፊትም የደፍኩላቸው ! አያምኑኝ ይሆናል ! ማመልከቻዬን፣ አሁንም ቢሆን አልጣልኩትም ! ይኸውልህ ! እስቲ ይስሙት አንብላቸው ! (አጠገቡ ላለ ጓደኛው ወረቀቱን ይሰጣል)

"እኔ አምንሐለሁ። እነሱ የሚፈልጉትን ዝንባሌ ለመግለጥ ያህል ነው። በደንብ አውቃቸዋለሁ። በየምሽቱ እኔ መጠጥ ቤት ይመጡ የለም ! የየትኛውም ቀበሌ ቢሆኑ፣ ጠባያቸው አንድ-ወጥ ነው !

"ላንብልዎ ! የፃፈው ማመልከቻ እንዲህ የሚል ነበር !"

... ለኰተቤ ቀበሌ ሊቀ መንበር፣

የተለመደው ዐብዮታዊ ሰላምታዬ ይቀርባል።

ጓድ ሊቀ መንበር እንደሚያውቁትና እንደሚያምኑበት ሁሉ፣ ለማንኛውም ሰው፣ ከዐብዮትና ከሕዝብ ቀጥሎ የወላጅ እናት ፍቅር ይኖረዋል። በተለይ እኔ፣ በወላጅ እናቴ ላይ ያለኝ ፍቅር፣ እጥፍ ድርብ ነው። ሌላውን መዘርዘር ባያስፈልግም፣ ያለአባት ያሳደገችኝ እናቴ፣ ልዩ ፍቅር ልታሳድርብኝ የበቃች፣ ባለውለታዬ ናት። ከዛሬ ነገ ተሚልቶልኝ፣ እጠራታለሁ እያልኩ ስመኝ፣ ካለፈው ወር ጀምሮ፣ በጠና ህመም ላይ መገኘቷንና፣ ብዙም ቀን ልትቆይ፣ አቅም የማይኖራት መሆኗን በመግለጽ፣ መልእክት አስተላልፋልኛለች። ጓድ ሊቀ መንበር የሚያውቁኝን ያህል፣ በአብዮታችን ላይ፣ ምንም ዓይነት ደባ ያልፈጸምኩ፣ ነፃ ሰው መሆኔ ተገልጾ፣ እናቴ በሕመም ላይ ከምትገኝበት፣ የትውልድ ቦታዬ ሔጄ እንድጠይቃት፣ አስፈላጊው ፈቃድ እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ። ..." የሚል ነው።

"እናት፣ ሀገር እንጅ፣ ወላጅ አይደለችም ብለውህ ይሆናላ !"

"ይቆዩኝ ! ይኸውልዎ፣ ለማመልከቻዬ የተሰጠኝ ምላሽ! አንብላቸው።"

"እባክህን የሚሰጡትን መልስ አውቀዋለሁ ! ከማር የጣፈጠ መሆን አለበት ! ችግሩ ግን ማስፈጸሙ ላይ ነው !"

"የተጻፈለት የፈቃድ ደብዳቤ የሚከተለው ነበር።" አለ ጓደኛው እያነበበ ...

ለሚመለከተው ሁሉ

በያሉበት፣

ለብዙ ዘመናት የደለበን ነባር አስተሳሰብ፣ በአንድ ውሱን ጊዜ ውስጥ ለማስወገድ እንደማይቻል ሁሉ፣ አንዳንድ ግለ-ሰቦች የሚያንፀባርቁትን፣

t.me/OLDBOOKSPDF

የኋላ ቀር ባሕልና የመንፈስ ዝንባሌ ለመቆጣጠር፣ ጊዜ እንደሚያስፈልግ የታወቀ ነው። በቀበሌያችን የዐብዮት ተግባራዊ ሥምሪታችን ላይ፣ የጊዜው አስቸጋሪ የአሠራር መሠናክል እየሆኑ ከሚያጋጥሙን ነገሮች ውስጥ፣ ሠርግ አለብኝ፣ ተዝካር ላውጣ፣ ዘመዴን ልጠይቅ፣ ... እያሉ፣ ከቦታ ወደ ቦታ ለመዘዋወር፣ በየጊዜው በማመልከቻ የሚጠይቁን ግለ- ሰቦች ሁኔታ ይገኝበታል። ዐብዮታችን እየተጧጧፈ በመጣበት በአሁኑ ወቅት፣ ፀረ-ዐብዮተኞችና አድኃርያን፣ እንዲህ ያለውን ጥያቄ መከታ በማድረግ፣ ልዩ ልዩ አሻጥሮችን መሥራታቸውም አይዘነጋም። በዘመነ-ዐብዮትም፣ የዘመድ ጥየቃና የመሳሰለው ተግባር ሁሉ፣ ተቀዳሚነት የሚሰጠው ጥያቄ አለመሆኑ ግልጽ ነው። ሆኖም የቀበሌያችን ነዋሪ የሆነው አቶ አኖሬዎስ፣ የናቱን መታመም በማስረጃ ጭምር ስላቀረበና፣ ከዚህ ቀደምም በቀበሌያችን የፈፀመው ምንም ዐይነት ወንጀል ያልተመዘገበና፣ ፀረ-ዐብዮት ድርጊት ያልሠራ ስለሆነ፣ በሽዋ ክፍለ ሀገር፣ በየረርና ከረዩ አውራጃ፣ በወለንጭቲ ወረዳ፣ በቀበሌ ሦስት የሚገኙትን እናቱን፣ ለተወሰነ ጊዜ ጠይቋቸው እንዲመጣ፣ አስፈላጊው የመተላለፍ አብዮታዊ ትብብር እንዲደረግለት እንጠይቃለን። ሆኖም ፀረ-ዐብዮተኞች ሁሉ፣ እውነተኛ ገፀ-ባሕርያቸው እስካልተከሠተ ድረስ፣ ሥውር መሆኑ እውቅ ነውና፣ ይህ የቀበሌያችን ነዋሪ በሚዘዋወርበት ሁሉ፣ አስፈላጊው ቁጥጥር ላልቶ፣ የሚፈፅመው ወንጀል ቢኖር፣ ኃላፊነቱ የማይመለከተን መሆኑን፣ በበኩላችን አስቀድመን እንገልፃለን።

ከዐብዮታዊ ሠላምታ ጋር ፣

"አላልኳችሁም ! እንዲዘዋወር ፈቅደንለታል ካሉ በኋላ፣ ለሚፈፅመው ሌላ ወንጀል፣ ኃላፊነቱ አይመለከተንም የሚለውን ሐሳብ ምን አመጣው ! የሌሎቹስ ቀበሌዎች ሹሞች፣ ምናቸው ሞኝ ነው ! በበኩላቸው እነሱም መዘዋወሩን ቢከለክሉት፣ ጥፋታቸው ከምን ላይ ነው ? "ሥጋውን ሰጥተው፣ ቢላዋውን ከለከሉት" እንደሚባለው አይደለም እንዴ አሠራራቸው !! እንዴው አያድርስ

ብቻ ! አያጋልጥ ማለት ይሻላል እንጅ፣ ውልፍት ከማያስኝ ዘመን ላይ ነው የደረስነው !

እኔ እዚያ ጠጅ ቤቴ ሆኜ፣ በየቀኑ የማልሰማው የብሶት ዐይነት የለም። ግማሹ ከከተማ ባላገር ሔዶ፣ ግማሹ ደግሞ ከባላገር ወደ ከተማ መጥቶ፣ የቀረውም ካንዱ ቀበሌ ወደ ሌላ ቀበሌ ሔዶ፣ ያልደረሰበትና ያላጋጠመው ትንግርት አይገኝም። የዘመድ መጠየቁን ጉዳይ ትተን፣ በሥራ ምክንያት እንኳ፣ የሚዘዋወሩ ሰዎች የሚደርስባቸው ፍዳ፣ የቱን ያህል የሚያሠቅቅ ነው።

ትዝ ይለኛል፣ በዚያ ሰሞን፣ አንድ ከጉንደር የመጡ አረጋዊ አዛውንት፣ ቤቴ ጠጅ ሊጠጡ መጥተው፣ እንደ ሕፃን ልጅ እያለቀሱ ያጫወቱኝ ብሶት፣ አንጀቴን ነበር የበላው። ያንድ አውራጃ ዳኛ ናቸው። እዚህ ካለው የፍርድ ሚኒስቴር የሚያስመጣ፣ የሥራ ጉዳይ አጋጥሚቸው፣ አስፈላጊውን ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር የሚያስችሉ ማስረጃዎች ይዘው፣ አዲስ አበባ ይመጣሉ። ብታዩዋቸውእኮ፣ ለዓይን የሚከብዱ አዛውንት ናቸው። ታዲያንን አዲስ አበባ እንደደረሱ፣ የሚያርፉበት ሆቴል ይፈልጉና፣ መርካቶ ውስጥ ያገኛሉ። ማንነታቸውን ማረጋገጥና ስለ እንግዳውም ለቀበሌው ሹም መግለጫ መስጠት ግዴታው ስለሆነ፣ የሆቴሉ ባለንብረት ለቀበሌው ይነግራል። ራታቸውን በልተው ሊተኙ ሲዘጋጁ፣ የቀበሌ የዐብዮት ጠባቂዎች ይደርሱና፣ አዛውንቱ መታወቂያቸውን እንዲያሳዩ ይጠይቃሉ። ከትንሽ ቆይታ በኋላ፣ የመ/ቤትዎ መታወቂያ፣ ከቢሮ ሰዎች ጋር በመመሣጠር የተገኘ ይመስላልና፣ የሚኖሩበትን የቀበሌ መታወቂያ እንፈልጋለን ይሏቸዋል። አዛውንቱ ዳኛ ግን፣ የመ/ቤታቸው መታወቂያ ብቻ በቂ መስሏቸው፣ የቀበሌያቸውን የነዋሪነት መታወቂያ አልያዙም ነበርና፣ በቀጥታ ወደ ቀበሌው እሥር ቤት ይወስዷቸዋል።

ጉንደር ያለው ቤተሰባቸው፣ አዲስ አበባ ናቸው ይላል። ያዲስ አበባው ዋና መ/ቤታቸው፣ ጉንደር ናቸው ብሎ ያስባል። አዛውንቱ ዳኛ ግን በመሐል የት እንዳሉ ሳይታወቅ፣ ለ40 ቀኖች ያላስታዋሽ በቀበሌ መህኒ ቤት ይማቅቃሉ። የኋላ ኋላ፣ አብሯቸው ታስሮ የነበር ሰው፣ ከቀበሌው ሲለቀቅ፣ ፍርድ ሚኒስቴር

t.me/OLDBOOKSPDF

ሔዶ፣ ስለሁኔታቸው በመንገሩ ብቻ፣ ሊፈቱ መቻላቸውን፣ እንባ እየተናነቃቸው አጫውተውኛል። ታዲያ ይኸንን ምን ትሉታላችሁ ? አያድርስ ! አያጋልጥ ነው እንጅ! አሉ ወይዘሮ በረዥሙ እየተነፈሱ።

"ፈረንጆች ፓሊስ-ስቴት" ነው ብለው የሚጠሩት፣ እንዲህ ያለውን፣ የዜጐችን ነፃነት የሚነፍግ፣ ዜጐችን የማያላውስና የማያፈናፍን ሥርዓት ያለበትን ሀገር ሁሉ። የኛም እንደዚያው መሆኑ ነው። ይሁን እንጅ፣ በተፈጥሮው ነፃ የሆነን የሰው ልጅ፣ በተወሰነ ቦታ ብቻ ከርችሞ ለማቆየት መጣር፣ ዘለቄታ የሌለው ሙከራ ነው ! ..." አለ ከአኖሬዎስ ጓደኞች አንዱ

" አዬ እሱማ ! የታፈነ ሁሉ መፈንዳቱ፣ ተራ የተፈጥሮ ሕግ አይደለም እንዴ !" ይላል ሌላኛው ጓደኛ፣ ድጋፉን በመስጠት።

"ልክ ናችሁ። ግንኮ የታፈነው እስኪፈነዳ ድረስ፣ ብዙ ሰው ማቀቀ ! የኔም እናትኮ፣ ከማሕፀኒ የተገኘው ልጇ እንኳ፣ ላንድ ቀን እድሜ ሳያስታምማት፣ በባዶ ቤት ብቻዋን ማቅቃ ሞተችኮ ..." ይልና አኖሬዎስ ለቅሶውን ያቀልጠዋል፣ የወላጅ እናቱ ትዝታ አንጀቱን እያቃጠለው።

"ልጄ ታገስ ! ልቅሶውም ይበቃኻል ! ባፈናው ምክንያት፣ የቅርብ ረዳታቸው ሳይደርስላቸው የሞቱት፣ ያንተ እናት ብቻ አይደሉም ! በየቦታው ብዙ ባይተዋር እናቶችም እንደሚሞቱ፣ ማዘከር ይኖርብሃል። ራስህን በራስህ አፅናንተህ ለመኖር መሞከር ይኖርብሃል። የናትህን ሞት እያስብክ፣ ሆድ እንዲባባህ ማድረግ የለብህም። ወጣት ስለሆንክ፣ ገና የትዳር አለም ይጠብቅሐል። ተበረታተህ መቋቋም ግዴታህ ነው !!" እያሉ የሚች እናቱ ጓደኛ በመምከር ላይ እንዳሉ፣ ከውጭ ሁለት ሰዎች ይገባሉ። መቀመጫ ተሰጥቷቸው እንደተቀመጡ የተለመዱ የሀዘን ቤት ጥያቄዎች ይደረድራሉ።

"ብዙ ታመው ነበርን ? ምን ሕመም ነበር ? እድሜያቸው ገፍቶ ነበር ?" አስፈላጊውን ምላሾች ከሀዘንተኛው አኖሬዎስ ካገኙ በኋላ፣ ትችት ይጀምራሉ።

"መቸም አቶ አኖሬዎስ፣ እንደምታውቀው ሁሉ፣ በዐብዮት ላይ የሚገኝ ሕዝብ፣ እንዳለፈ የጉልተኛና የከበርቴ ዘመን፣ ለልቅሶና ለሀዘን ሥርዓት ጊዜ አይኖረውም። ዓላማውም ሆነ ግቡ፣ ካለው ሁኔታ ላይ ተነስቶ እውነታን በመጪበጥ፣ ትግል ያከናውናል እንጅ፣ ባለፉ ነገሮች ላይ ሙጥኝ ብሎ፣ ጊዜ ማጥፋት አይኖርበትም። ደግሞም እንግዳ ዐብዮታችንን፣ በሚገባ ለማስተናገድ እንጅንችል፣ ከስሜት ጋር የተያያዙ ትንንሽ ነገሮችን መርሳት ይኖርብናል። ዐብዮት እስካለ ድረስ፣ ያለና የሚኖር ነገር ሁሉ፣ ሕያውነቱ ዋስትና አለው። ስለዚህም ሙታንን መርሳት ይኖርብናል ..." ብሎ አንደኛው ሊያስተዛዝን የመጣ እንግዳ ሲያበቃ፤

"እናቴን አልረሳም!" ብሎ ለመናገር አኖሬዎስ ብልጭ ብሎበት ነበር። እነዚህ አስተዛዛኞች እነማን እንደሆኑ ስለሚያውቅ፣ እየተፈላሰፉ የተለፋዱዱበት ምክር ማርኰት ሳይሆን፣ ስላለፉ ነገሮች ማዘን አለማስፈለግ፣እውነተኛው ትርጉምና ፅንስ-ሐሳብ ተሰምቶት፣ ሊያወጣው የነበረውን የተቃርኖ ምላሽ፣ እንደምንም ውጦ፣ ዝም አለ። እነዚያም ሁለት የቀበሌ የዐብዮት ነፍጠኞች፣ አኖሬዎስን ለማስተዛዘን ብቻ ሳይሆን፣ ከላይ የተጠቀሰውን መለእክት ለማስተላለፍ ሲሉ፣ የተወሰኑ ደቂቃዎች ከተቀመጡ በኋላ "በሀዘን የሚፀፀት ልብን፣ በዐብዮት መንፈስ ማደንደን ነው!" የሚል "ፅናቱን ይስጥህ" እንደማለት ያለ የመስናበቻ ቃል ወርውረው ይወጣሉ። ገና እግራቸው የበሩን ዳኛፍ ረግጦ እንደወጣ፣ ድምፃቸውን አጥፍተው፣ ጭጭ ብለው የነበሩት፣ እኛ ሴት ወይዘሮ፤

"እነዚህ እንግዲህ፣ የቀበሌያችሁ ሹሞች መሆናቸው ነው!" አሉ።

"እዎ የበታች የቀበሌ ሹሞች ናቸው!" አለ አንዱ ያኖሬዎስ ጓደኛ።

"አሁንኮ የነሱ እናት ቀርቶ፣ ውሽማቸው እንኳ ብትሞት፣ ድንኳኑ ሳይቀር ተጥሎ፣ ስምንት ቀን ሙሉኮ ነው፣ ድግስ ቤት ይመስል ሽብ ረብ ሲሉ የሚከርሙት!" አሉ ተቆጭተው።

"የዘመናችን የቀበሌ ደጃዝማቾች አይደሉ ብለው!" አለ እያሽሚጠጣቸው።

"ታዲያ እነሱ የማያደርጉትን፣ ለምን ለሌላ ያስተምራሉ?" አሉ ሴትዮዋ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"የራስና የሌላ የሆኑ ነገሮች ሁሉ፣ ለየቅላቸው አይደሉ ብለው ?" አለ እንደኛው ጓደኛ።

"በጣምኮ የሚገርሙ ትንግርቶች ናቸው ! አላጪወትኳችሁምኮ መሰለኝ ! ያ የኔ ጠጅ ቤት ያላሳየኝ ጉድ የለምኮ ! እንደምታውቁት፣ በሥራ ሰዓት መጠጥ ቤቶች ዝግ ናቸው። ታዲያንን፣ እነሱ ሹልክ ብለው በአሳቻ ሰዓት በጓሮ በር ገብተው፣ ሲጠጡ ነው የሚውሉት።

"ታዲያ አንዳንድ ቀን፣ የጉረቤት አንዳንድ አዛውንቶች፣ በተለይም ጡረታ የወጡ አዛውንቶች ቀኑ እየረዘመ ሲያሰለቻቸው፣ እንደነሱው ተደብቀው መጥተው ሲጠጡ ይውላሉ። የሚገርመው፣ እነዚህን አዛውንቶች እነሱ ራሳቸው ተደብቀው ለመጠጣት ሲመጡ ያገኟቸው እንደሆነ፣ ወዲያው አቻኩለው፣ ፎቶግራፍ አንሺ ያስመጡና፣ ጠጅ በጠርሙስ ሙሉ ይሉንና፣ የጠርሙሱን ጠጅ ራሳቸው ላይ አስቀምጠው ፎቶግራፍ እያነሱ፣ በጋዜጣና በቴሌቪዢን ለሕዝብ እንዲታዩ ያደርጓቸዋል። ማዋረድ ያሉት ነው። በዚህ ድርጊታቸው ስንቱን አዛውንት እንደ አሻንጉሊት እያደረጉ ተጫውተውብታል ! እነሱ ግን ከዕለት ዕለት፣ በግላጭ እየመጡ፣ በጠራራ ፀሐይ ሲጠጡ ሲውሉ፣ ሌላው ቀርቶ የጠጡበትን ገንዘብ እንኳ የማይከፍሉበት ጊዜ አለ። ታዲያ እኔ የሚገርመኝ፣ ራሳቸው የማያደርጉትን፣ ለምን ለሌላ ያስተምራሉ !" ሴትዮዋ ራሳቸውን ነቀነቁ።

"ጪዋታን ጪዋታ ያነሰዋል" አለ ካኖሬዎስ ጓደኞች አንዱ፣ "በዚያ ሰሞን ነው፣ አንድ የኔ የሥራ ጓደኛ እህት፣ ልትጠይቀው ከደሴ ትመጣለች። አስፈላጊዎቹ የመጓጓዣ ሠንዶች ሁሉ አላት። እንዳጋጣሚ፣ የሚኖርበት ቀበሌ ሹሞች አንዱ፣ ጉረቤት ነበርና፣ ይህችን እህቱን ሻንጣዋን ይዛ ከወንድሟ ቤት ስትገባ አይቷታል። ወይዘሮዋ እንዝርት የመሰለች ደማም ናት። ቀኑን ሙሉ አድፍጦ ያመሸና፣ ማታው ገዳማ ላይ፣ ካንድ የሥራ ጓደኛው ጋር፣ ይህችን እንግዳ ለመጥለፍ፣ ወደ ጓደኛዬ ቤት ሲያመሩ፤ ጓደኛዬ ደግሞ በአዲሱ ደንብ መሠረት፣ ከቤት እንግዳ መምጣቱን ለማስገንዘብና ለማስመዝገብ፣ ወደ ቀበሌ ጣቢያ ለመሔድ ሲነሳ፣ ከበሩ ላይ እነዚህን የቀበሌ ሰዎች ያገኛቸዋል። እንግዲህ ተመልከቱ፣ ይቺ እህቱ

የወለደች፣ የከበደች፣ የሞቀ ትዳር ያላት፣ የቤት እመቤት ናት። ስለሁኔታው እዚያው እበሩ ላይ ለሁለቱም የቀበሌ ሹሞች ይነግርና፣ "እንዲውም ቀበሌው ጣቢያ ከመሔድ ዳንኩ፣ እናንተው መዝግቡና ፍቃዱን እዚሁ ስጡኝ !" ይላቸዋል። እነሱም፣ "እኛ ዛሬ ተረኞች አይደለንም ተረኞቹ እዚያው ቀበሌ ጣቢያ ይገኛሉና ሔደህ አስመዝግብ !" ይሉታል። እሱም መስሎት፣ ሊያስመዘግብ ሲሔድ፣ እነሱ ክቤቱ ገብተው፣ እንግዳዋን፣ "ያለፈቃድ ነው የመጣሽውና ለጥያቄ ትፈለጊያለሽ" ብለው በመውሰድ፣ ላልተወሰነ ጊዜ፣ ባልታወቀ ቦታ ሞሽረዋት ይባጃሉ።

"ያ መንድሚ፣ ያን ዕለት ማታ፣ ቀበሌ ካገኛቸው ሌሎች ሹማምንቶች ጋር ተነጋግሮ፣ አስፈላጊውን የእንግድነት ፈቃድ አግኝቶ፣ እቤቱ ሲመለስ ካጣት ጀምሮ፤ ሰማይ ቢቧጥጥ፣ ጮቤ ቢረግጥ፣ ለሣምንት ቆይታ ሊያገኛት አልቻለም። እየተፈራረቁ ስምንት ቀን ሙሉ፣ ውልቅልቋን ካወጡ በኋላ፣ ተጠርጥራ ምርመራ ላይ መቆየቷን በመግለጽ፣ ከሣምንት በኋላ አምጥተው ያስረክቡታል። እሱም ለጊዜው የሚያደርገው ተደናግሮት፣ እህቱን እንዳገኘ ለወጉ ያህል እንኳ ሳያስተናግዳት፣ ሳትውል ሳታድር፣ ባስቸኳይ ወደ ደሴ ይልካታል። በእህቱ ውርደት ቂም መያዙን የተረዱ፣ እነዚህ አለሌ የቀበሌ ሹሞች፣ በዚያ ጓደኛዬ ላይ የሆነ ያልሆነ ወንጀል ፈጥረው፣ ውህኒ ካስገቡት፣ ይኸው እዚያ ሆኖ ሲማቅቅ፣ አራተኛ ወሩን ይዟል።"

"አይደረግም አይባልም" አሉ ሴትዮዋ፣ አፋቸውን ከፍተው ሲያዳምጡ ቆይተው።

"እያዩዋቸው ! ይኸው እናንተ ለጥቂት ስዓቶች ለማፅናናት መጥታችሁ፣ እዚህ መገኘታችሁን አውቀው አይደል፤ እንዳያችሁት፣ "እናትህን መርሳት ይኖርብሃል"፣ ብለው ሲለፋደዱ ቆይተው የሔዱት ! እኔ እንደነሱ፣ ድንኳን አስተክዬ፣ ደርዘኖች መጠጦች አስደርድሬ፣ ደረት ምቱልኝ አላልኩ! ያለጠባዬ ጠባይ ፈጥረው፣ እንዳልቀብራት አረጉኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF


"አዩ ልጄ፣ አኖሬዎስ ! እነዚህን ርሳቸው ! ታግሰህ ትዳርህን መመሥረት ይሻላል" አሉ ----

"ጉረቤቴ ኢንጂነር ዘካርያስ የሰጠን ትምህርት፣ አማራጭ የማይገኝለት የዘመናችን ሐቀኛ ርምጃና ውሣኔ ነው። ሁኔታዎች እስኪያመቹልኝ ድረስ እዘገይ ይሆናል እንጅ፣ ቆራጡ ዘካርያስ የቀደደልን አውራ ጉዳና፣ ለኔም መጓዣ መሆን ያለበት፣ ጥርጊያ መንገዴ እንደሆነ ወስኛለሁ። መሠናክል በሌለበት ትክክለኛ ጉደና ላይ ለመጓዝ፣ የማይመርጥ ማን አለ።

------❋▲❋▲❋❋❋ ------



ብድር በምድር !



ኦራ-ፋርስን ቢነክሰ፣ከደሲ ተንኮለኛ!
ሰምች ተግፀነች፣ብታገኘ መጻኛ።
ሙጥኝታዋም ቢሆን፣ምላሹን አግኝቶ፣
ከከደሲ መንጋጋ፣አላቋታል ዋቶ።
ሰዚያ ሰፈፀመው፣የሰው ልጅ ውሰታ፣
ከሩቅ ሀገር ሔዳ፣ተንገላታ ለምጥታ፣
"ወይኔን እንካ!"ብላ፣ከፍላለች ወሮታ!
ያ ወይኒ ነው አሱ፣እስከ ዛሬ ድረስ፣
ሰውን እያረካ፣በተሰየ መንፈስ፣
አንጻንጾችን ሲያሥቅ፣ሌሎች ሮሚያስለቅስ!

t.me/OLDBOOKSPDF

ም ራ ቂ

ይቺን ቍንጽል ድርሣን የተረጐምኳት፣ በቻይንኛ ከተፃፈ የምድረ-ፋርስ ትንግርታዊ መጽሐፈ-ታሪክ ውስጥ ነው። ለሃገሬ ኢትዮጵያ አንባብያን እንደሚጥም አድርጌ ማቅ ረቤን፣ አንባቢ ሁሉ እንደሚረዳልኝ አምናለሁ። በመሠረቱ "መተርጐም" ማለት *"A translation is not just a simple substituition of words. It involves the transfer of a massage from one culture to another in such a way that the readers can understand exactly what the writer intended to communicate. Two countries are not alike. Differences in landscape, climate. history, politics and tradition produce different cultures; the very same cultures which inturn shape people and society in this modern day."* ስለሆነ፣ ትረጉም ሁለንተና ባሕርያቱን ማቀፍ ይኖርበታል። ይህችን መሰል ትርጉመ-ታሪኮች በብዛት ስላሉኝ፣ የአንባብያንን የፍላ ጐት መጠነ-ትርታ እየተከታተልኩ፣ በየጊዜው ላሳትማቸው ተዘጋጅቼአለሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ብድር በምድር !

ከምድረ ፋርስ ብርቅ
ታሪኮች አንዱ

የወይን ጠጅ
ቅድመ ታሪክ

ሐራት፤ በምድረ-ፋርስ የምትገኝ አንዲት ደማቅ መን ደር ነች። አያሌ ታሪኮችን አሳልፋ፤ ዛሬም አለች። ለህላዌዋ ምክንያት የሆኖት አንድ የፋርስ ንጉሥ ነበር። ዝናውና ገና ናነቱ የጊዜውን የጐረቤት ሀገሮች ሁሉ ያሸብር ነበር። ይህ ኃይለኛ ንጉሥ ሻሚራን ይባላል። የጦር ሠራዊቱ ብዛት፤ ለቀጥጥር ያስቸግር ነበር። የመንግሥቱ ሀብትና ንብረት ይህ ነው አይባልም። ንጉሡን በዘመኑ ዝና ያተረፈለት፤ ኃያልነቱ ብቻ ሳይሆን፤ ብልጽግናው ጭምር ነው። ሠራዊቱም ሆነ ሕዝቡ ተንደላቆ ይኖር ነበር። በዚያ ጥንታዊ ዘመን ውስጥ መንግሥታዊ መዋቅሩ ተሳክቶለት፤ ሕዝባዊ አስተዳደሩ ተደላ ድሎለት የሚኖር ንጉሥ፤ እንደ ሻሚራን ያለ አልነበረም። ይበልጥ ደግሞ ተሟልቶለታል ያሰኘው፤ በችሎታውም ሆነ በጉልበቱ ይህ ቀረው የማይባል መሰል ልጅ የነበረው መሆኑ ነው። በአልጋ ወራሽነት የታጨው ይህ ልጅ፤ ተኮሶ የማይ ስት፤ ተናግሮ የማይሳሳት፤ ጠላት ይዞ የሚወቃ፤ ተቃራኒውን ሁሉ የሚደቃ፤ መሆኑን በየዕለት ድርጊቱ ያሥመሰከረ ነበር። ንጉሥ ሻሚራን ባድሐም ከሚባለው ተኮሶ ከማይስት ልጁ ጋር በተድላ ደስታ፤ በባዝግናና በእንቍ ተንቆጥቁጦ በተሠ ራው ቤተ-መንሥት ባንድነት ይኖሩ ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዘመናት በአንደኛው ቀን፤ ንጉሥ ሻሚራን ከሚወ
ደው የቤተ-መንግሥቱ ባልኮኒ ላይ ዙፋኑን አዘርግቶ ታላቅ
ግብጣ ያደርጋል። በዚሁ ዕለት ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ
ሌላ፤ የቅርብ ባለሟሎች የሆኑት ሁሉ ከበረንዳው ሥር በተን
ጣለለው ፀአዳና ማራኪ መስክ ላይ፤ የዚህ ታላቅ ፈንጠዝያ
ግብር ተካፋይ በመሆን ተገኝተዋል።

ያለወትሮው፤ በዚያን ቀን የተተከለ ድንኳን ወይም
የተጣለ ዳስ አልነበረም። የቀኑ ፀሐይ ፈንጥቃ፤ ወደ ማለዳው
ላይ ነበር። በቤተ-መንግሥቱ አድማሚዊ ዙርያ ገረገንብ
ባለው ያታክልት መስክ ላይ የተሠተሩት ተክሎችና ጽጌያት፤
አዕይ ንትን ከመማረክ አልፈው፤ የያንዳንዱን ተጋባዥ
አፍንጫዎች ሁሉ በመዓዛቸው አሥክረውታል። በቅይር ቅርፅ
ከተኰለ ኰሉት የግብር መቀመጫዎችና ጠረጴዛዎች ሌላ፤
ሰፊው መስክ፤ ብዙ እንግዶችን በመድረክነት ጭምር ለማገ
ልገል ይሆነኝ ብሎ የተሠራ ነው። ከመስኩ ምሥራቃዊ
ጠርዝ ላይ፤ ገብታችሁ ተንቦራጨቁብኝ እያለች የምትጋብዝ
መሳይ መጠነኛ ኩሬ፤ በአርምሞ ለጥ ብላ ትታያለች። ከበስ
ተዳርቻዋ እየተንጠራዋዙ የሚዝለገለጉ ሐምራዊ ሐረጎች፤
ረባዳውን ቦታ እየፈለጉ ተሸሎክልከው በመጓዝ፤ በቤተ
-መንሥቱ የጀርባ ሕንፃ ላይ ተሠይመዋል። ውበታቸውን
ያየ፤ እህል ውሃ አያሰኘውም። ለኬክሮስ ቆይታ ያህል
እያረፉ፤ ወደላይ እንደ ርችት የሚተኮሱ ምንጮች ከሐይቁ
እንብርት ላይ፤ ሿ ተምቧ እያሉ፤ በሕብረ ቀለማት አሸብ
ርቀው፤ ልዩ ትርዒት ከመስጠታቸውም በላይ፤ ከዕዝልና
አራራይ በተቀመረ ፀዋትወ-ዜማ ስልት ልዩ ጣዕመ-ሙዚቃ
ይለግሳሉ። በዚያች አነስተኛ ኩሬ ላይ እንደመኖርያ ገዳማቸው
አርገው የሚንሳፈፉትን ልዩ ልዩ ዓሣዎችና አዕዋፋት መመል

t.me/OLDBOOKSPDF

ከት፤ ታይቶ የማይጠግቡት ትርዒት ነው። የዕለቱ ግብር ተከና
ውኖ፤ በዚያች ውብ መስክ ላይ የባሕሉ ሙዚቃና ጭፈራ
ሊጀመር ሲል፤ ከዚህ ቀደም በዚያ ታላቅ ቤተ-መንግሥት
የመስክ መድረክ ላይ፤ በዚያ ሁሉ መኳንንትና ሠራዊት ፊት፤
ንጉሡ ከነቤተሰቦቹ በዙፋኑ ላይ እንዳለ፤ ተደርጐም ሆነ
ተሰምቶ የማያውቅ፤ አንድ አስደናቂ ድርጊት ተፈፀመ።

ከዚህ መጣች የማይሏት አንዲት በውበቷ የምታባባና
የምታሳዝን ፎኔክስ ከወደሰማይ ተምዘግዝጋ ንጉሡ ከተቀመ
ጠበት ባልኮኒ (በረንዳ) እጅታ ላይ ታርፋለች። ወርቅማ ላባ
ዎቿ ከሰማያት የወረደች አስመስለዋታል። በደረቷና በአክ
ናፎቿ ላይ የተነደፈው ሽልምልሞቿ ምድራዊ እንዳልሆነች
ይመሰክራል። በበረንዳው ላይ ብዙ ሳትቆይ፤ ፈጥና ለባሕላዊ
ዝግጅት ወደተሠናዳው የመስክ መድረክ ላይ ከማዕከሉ ታር
ፋለች። ይህችን ፎኔክስ አስቀድሞ ከዚያ ሁሉ ሠራዊት ያየ
ንጉሡ ነበረ። ለህያውነትና ለዘለዓለማዊነት ምልክት በመሆን
የታወቀችው ያቺ ፎኔክስ፤ በዚያ የቤተ-መንግሥት አደባባይ
ላይ መገኘቷ አለብርቱ ምክንያት አልነበረም። የተራበ እባብ
በመላ አካላቷ ላይ ተጠምጥሞ፤ ሊገድላትና ሊመገባት ይታ
ገላት ኖሯል። ከይሲው ባስከተለው ትንቅንቅ ሳቢያ፤ የፎኔክሷ
ላባዎች በመጠኑ መነቀልና መነጨት ደርሶባቸዋል። በዚያን
ወቅት “ ክንፌ አውጭኝ! ” በማለት፤ ከንፋ ባደባባዩ መገ
ኘቷ፤ “ ሙጥኝ፤ አድኑኝ፤ ” ለማለት ነበር። ያ ሁሉ ሠራ
ዊት፤ ሳያስበውና ሳይጠብቀው፤ ያ አሳዛኝ ትርዒት ድንገት
ሲያጋጥመው፤ የሚይዘውና የሚሠራው ጠፍቶት ተሸበረ።
አስቀድሞ አይቶ የነበረው ያ ንጉሥ ግን፤ ለጠቅላላ ሠራዊቱ

እንዲረጋጋና በያለበት እንዲቀመጥ ትዕዛዝ ካስተላለፈ በኋላ፣ በተኳሽነት ለታወቀው ልጁ ፈጥኖ እንዲህ አለ።

“ ልጄ ባድሀም! ዛሬ የሙያህ መፈተኛ ቀን ነው። የተቸገረ ሰው ሳይሆን፣ በሥቃይ የተያዘች ፎኔክስ የኛን ርዳታ ለማግኘት መጥታለች። ምናልባትም ይህን ርዳታ ለማግኘት ብዙ ርቀት ተጉዛ ይሆናል የመጣችው። በዚያ ሁሉ ጉዞዋ፣ የሚረዳት ሰው ሳይኖር ቀርቶ አይደለም። እንግዲህ እመረኝ። ከዚሁ ከበረንዳው እንዳለህ፣ የከይሲውን መርዘኛ ጭንቅላት አነጣጥርና ቀንጥሰህ ጣልልኝ!! እኛን መርጣ፣ ሙጥኝ ለማለት የመጣችዋን ይህችን የዋህ ፎኔክስ ከጭንቀቷ ገላግላት! እግረ መንገዱንም፣ ይህንን አጋጣሚ ተአምር ለማየት የታደለው ሠራዊታችንና መኳንንታችን፣ ግብሩን እየበላ ታሪኩን ይመዝ ግብ” አለና ከወርቅ የተሠራ የገዛ ራሱን ሽጉጥ ከትጥቁ ፈትቶ ሰጠው። ባድሀምም አፍታም አልቆየ፣ ያባቱን ሽጉጥ ተቀብሎ ከመቅጽበት አቀባብሎ ወደ ፎኔክሴዱቱ አቅጣጫ ደገነ!!

“ አደራህ ልጄ! ምናልባት ስተህ፣ ከእባቡ ይልቅ ፎኔክሷን እንዳትገድልብኝ!” በማለት ንጉሡ እንደገና አስጠነቀቀው። የፎኔክሷ አሳዛኝነት ያባባው ሆኑ አላስችል ብሎት።

“ አባባ በኔ ይሁንብህ! ይህ ላንተ ብቻ የቀረበ ፈተና ሳይሆን፣ ለታሪክም የተላከ መፈታተኛ ነው!” ሲል መለሰ። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ፎኔክሷ ከእባቡ ጋር ትታገላለች። እባቡ ጡንቻዎቹን ባኰማተረውና ባጠዘው ቍጥር፣ ፎኔክሷ አቅም እየተሳናት ከቆመችበት ለመውደቅ ትንገዳገዳለች። ይህም ሁኔታዋ፣ ለባድሀም ኢላማ ማነጣጠር መለስተኛ ችግር ሆኖበት ከቆየ በኋላ፣ በዚያው ወቅት እባቡ ራሱን ወደ ፎኔክሷ ጭን ቅላት ለማምራት ሲንጠራራ፣ ቃታውን ሳበ። የባቡ ጭንቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ላት ተቀንጥሶ በመስኩ ላይ ሲወራጭ ከታየ በኋላ ነበር፣ የተ ኰሰው ጥይት ጩኸት እንኳ የተሰማው። ቀሪውን የእባብ ዐካል በኩንቢዋ ካላቀቀችና፣ በመስኩ ላይ ከጣለች በኋላ፣ ተጨብጦ የቆየውን ዐከሏን ለማንቀሳቀስ ያህል ክንፎቿን አራገበች፣ ለምስጋና ያረገችው ይመስላል፣ ሦስት ጊዜ ያህል ንጉሡ የነበረበትን ዙፋን ዞራ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ከነ ፈች። አራግፋው ከነበረው ላባዋ ለማግኘት፣ በቤተ- መንግ ሥቱ አደባባይ የነበረው ሠራዊት ሁሉ ተሻማ!! ንጉሡም፣ በሕዝቡ መሐል ለነፍጠኛ ልጁ ምሥጋና ካቀረበ በኋላ፣ የዕ ለቱ የሙዚቃ ድርጅት እንዲቀጥል አዘዘ። ያን አስደናቂ የፎኔ ክስ ትንግርት በአንክሮ ሲመለከት የቆየው ሠራዊት፣ የፎኔክሷ ሥቃይ ከፈጠረበት ጭንቀቱ እፎይ ብሎ፣ በቤተ-መንግሥቱ ዘማርያን የቀረበለትን የሙዚቃ ድግስ ይከሠክስ ጀመር። የጭ ንቀቱን ያህል፣ በሙዚቃው ርካታ ተዝናንቶ፣ ከዝግጅቱ ፍፃሜ በኋላ በደስታ ወደየቤቱ ተሠማራ።

እንስሳትና አእዋፋትም እንደባለኅሊናው ሰው የዘመን መሥፈርያና ካላንደር ያላቸው ይመስላል፣ ያቺ ውለታ የተደረገላት ፎኔክስ ወሮታዋን ለመክፈል ያቀደች ይመስላል፣ ርዳታ በተሰጣት ልክ በዓመቱ፣ በዚያው ሰዓትና ቦታ ከተፍ አለች። በዚያን ዕለት፣ ከወትሮዋ አምሮባት ወፍራና አሸብርቃ ነበር። ወርቅማና ሽልምልሙ ላባዋ በውበቱ ያየውን ዐይን ሁሉ ይገላምጥ ነበር። ዐይኖቿ የፀሓየ ብርሃን ፀዳል ያህል ያንፀባርቃሉ። ፀዳል ይረጫሉ። ንጉሡ በበረንዳው ዙፋን ላይ የተሠየመ ቢሆንም ብርሃነ-ፀዳል ሲፈነጥቁ፣ የደስታ ብሥራት እንደነበር ያሳያሉ። የተጋበዘው መኳንንትና ሠራዊት ገና ውጭ ነበር። ያቺ ፎኔክስ፣ በንጉሡ ዙፋን አናት ላይ ሦስት ጊዜ ያህል በዝግታ ፍጥነት ከዞረች በኋላ፣ ያ

ጠላቷ እባብ ከተገደለበት ቦታ ላይ ሔዳ አረፈች። ቀን ቆጥራ በመምጣቷ፣ ንጉሡና ባለሟሎቹ ተጠንቅቀው የምታደርገውን ሁሉ በውል ይከታተሉ ጀመር። አስቀድማ በሁለት እግሮቿ ጥፍሮች መሬቱን ከኰደፈረች በኋላ፣ ከአንገቷ ቀና ጐንበስ በማለት ለንጉሡ እያመ ለከተች፣ ሦሥት ነጫጭ ፍሬዎችን ካፏ አውጥታ፣ ከቆፈረችው መሬት ላይ አስቀምጣ አፈር አለበሰችው። ይህን ካደረገች በኋላ፣ ንጉሡ ወደ ተቀመጠበት ዙፋን ተጠግታ የሚስረቀረቅ ድምፂን ካሰማች በኋላ፣ እንደለመደችው ሦሥት ጊዜ ዞራ፣ ወደመጣችበት ሄደች። ንጉሡም ወዲያው ፈጥኖ ሦስት ባለሟሎቹን፣ ያመጣችውን ሦስት ፍሬዎች ከቀበረችበት አምጥተው እንዲሰጡት ትዕዛዝ ሰጠ። ወዲያው ቀርቦለት ቢያይ፣ ከዚህ ቀደም አይቶ የማያውቀው የፍሬ ዐይነት መሆኑን ተረዳ። ለጊዜው ባካባቢው ካሉት ባለሟሎች ውስጥ፣ የየትኛው ተክለ-ዘር ወይም የየትኛው ዕፅ ፍሬ እንደሆነ ሊያውቅ የሚችል ሰው ባለመኖሩ፣ በሃገሩ የሚገኙትን የሥነ ዕፀዋት ሊቃውንት እንዲመጡለት ጥሪ አደረገ። ይህ በሆነ በሣልስቱ፣ የሀገሩ ሊቃውንት በጥሪው መሠረት ከቤተ መንግሥት መጡ።

ጉባዔ ሊቃውንቱ በተከፈተበት ወቅት፣ ንጉሡ የሚከተለውን መግለጫ አሰማ።

" እነዚህ ጠንካራ ፍሬዎች በስጦታ የቀረበልን ከወዳጅ ወፍ ነው። ከዚህ በፊት ለፈፀምንላት ውለታ፣ ወሮታ እንዲሆንላት የሰጠችን መሆኑን እንገምታለን። ዝርዝር ታሪኩን ወደፊት ትረዱታላችሁ። አሁን ግን የምትረዱን ፍሬነቱ የምን ተክል እንደሆነ እንድትገልጡልን ነው። ምንስ ሆኖ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲጠቅመን ያበረከተችበትን ግልጋሎት ብትገልፁልን ደስ ታውን አንችልም " በማለት ሦስቱን ፍሬዎች አቀረበላቸው።

ሊቃውንቱ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት፣ የፍሬውን ምንነት ለማወቅ ብዙ የምርመራ ሙከራዎች አደረጉ። ምንነቱን ግን በማየት ብቻ መረዳት እንደማይችሉ አረጋገጡ። በመጨረሻም ላይ፣ የተሰበሰቡት ሊቃውንተ-ቦታኒ በሙሉ (ሊቃነ-ዕፀዋት)፣ ፍሬዎቹ ተተክለው፣ በብርቱ እንክብካቤና ጥበቃ ካደጉ በኋላ፣ ቅጠላቸውን በማየት ምንነቱን መወሰን እንደሚቻል ለንጉሡ ተናግረው ተበተኑ። ንጉሡም በሊቃውንቱ ሐሳብ ተስማምቶ፣ በቤተ-መንግሥቱ ለታወቁ አትክልተኞች በአደራ ጭምር ተክለው እንዲያበቅሉ ፍሬዎቹን ሰጣቸው። ፍሬዎቹን በሰጠበት ወቅት፣ የሚከተለውን አደራ ጭምር ነግሮአቸው ነበር።

" በዚሁ በግቢው ውስጥ በአንደኛው ያትክልት ቦታ ጥጋት ላይ ትከሏቸው። እንስሳም ሆነ ሰው እንዳያጠፋቸው፣ የተተከሉበትን ቦታ በጥንቃቄ እጠሩት። ባካባቢውም ወፎች እንዳይጠጉ በጥንቃቄ ተከላከሉ። ስለ እድገታቸውም በየጊዜው አስፈላጊውን ዘገባ አቅርቡልኝ። በትልቅ ተስፋ የምንጠብቀው፣ የፎኔክስ ልዩ ስጦታ ነው። አደራ! "

የቤተ መንግሥቱ አትክልተኞች በተጣለባቸው አደራ መሠረት፣ ጠዋት ማታ ፍሬያቱን ሳይለዩ፣ በማጠጣትና በመኰትኰት ፍግ በመስጠት፣ በሚገባ ተከባከቡ። ብዙም አልቆየ፣ የተተከሉት ፍሬዎች እንቡጥ አፅቅ አቆጥቁጠው ብቅ አሉ። ይህ እንደሆነም፣ ተክለኞቹ ተፋጥነው ለንጉሡ አበሠሩት። ንጉሡም እንደሰማ፣ ሊቃውንቱን ባስቸኳይ ጠርቶ እንዲመረ

ምሩ አደረገ። ሊቃውንቱም ተሰብስበው ቆጽሉን ካዩ በኋላ፤ “እንዲህ ያለ ተክልም ሆነ ቅጠል ከዚህ ቀደም አይተንም ሆነ አጋጥሞን አናውቅም ” በማለት፤ ወደየቤታቸው ተመለሱ።

ከፍተኛ እንክብካቤ እየተደረገላቸው እድገታቸውን የወጠኑት እነዚያ ሦስት ፍሬዎች፤ ፈጣን የሆነ ለውጥ ማሳየት ጀመሩ። አደራ የተጣለባቸውም አትክልተኞች፤ ከመቸውም ይልቅ ንጉሡን ለማስደሰት ሲሉ፤ ተክሎቹ የሚያስፈልጋ ቸውን ውሃ፤ ሙቀት ግፍና ሌላም አልሚ ምግበ ተክሎች እጥፍ እያደረጉ እንክብካቢያቸውን ቀጠሉ። የሚለገሣቸውን ስጦታ ሁሉ በከንቱ ያላስቀሩት እነዚያ ስሉሥ ፍሬዎች፤ ባል ተጠበቁበት ሰዓት፤ ቆፅላቸውን አቆጥቁጠው ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። የበቀሉት ቀንበጦች መጠናቸው የበዛ፤ ተክላዊ ዐይና ቸው ያጐረጠ፤ ዳጉሣ መሳዩ ለጋ ቅርንጫፋቸው ያንፈራጠጠ ሆኖ ተገኘ። ይህን የተስፋ ምጣት የተመለከቱ ተክለኞች፤ ሁኔ ታው አላስችል ብሏቸው፤ ስለ ፍሬዎቹ ማቆጥቆጥ ለማብሠር ወደ ንጉሡ ሔዱ። ንጉሡም ዘንድ እንደቀረቡ፤

“ በቤተ መንግሥቱ ጊቢ ውስጥ የማይገኙ የዕፀዋት ዐይነቶች አልነበሩም። በምድር ላይ የበቀሉ የዕፀዋት ዐይነቶች ሁሉ ከዚህ ቀደም አላመለጡንም። የተለያዩ ውብ ተክሎች በማስተናገዳችን ኩራት ይሰማን ነበር። ይሁን እንጅ፤ በትዕ ዛዝም መሠረት የተተከሉት እነዚያ ሦስት ፍሬዎች፤ ሌላ ውብ ትና ተፈጥሮ ያላቸው ሆነው ማቆጥቆጥ ጀምረዋል። ገና በእ ንቡጥነታቸው፤ ለጊቢውና ለሌሎቹ አትክልቶችም ግርማ ሞገስ በመሆን ልዩ ድምቀት እየፈነጠቁ ነው። እንኰራባቸው የነበሩትን የፋርስ ጽጌያት ሳይቀር እያስናቋቸው ነው። ለውበ

t.me/OLDBOOKSPDF

ታቸውም ሆነ ለዕድገት ፍጥነታቸው ምንም ዐይነት እንከን አይወጣላቸውም። ”

ንጉሡም ወዲያው እነዚያን ጠበብተ-ዕፀዋት አስጠ ርቶ ይዟቸው፤ ዕፀዋቱ ወደ ሚገኙበት ወሰዳቸው። ንጉሡም ሆነ ሊቃውንቱ ታዳጊዎቹን ዕፀዋት እንዳዩ ካድናቆት በስተ ቀር፤ በሕይወታቸው ዐይተውት የማያውቁት ተክል እንደሆነ ተናገሩ። ንጉሡም “ ምናልባት ያቺ ባለውለታ ፎኔክስ፤ ከም ድር ዳርቻ ያመጣችው ልዩ ስጦታዋ ይሆናል። ሁላችንም በትዕግሥት መጠበቅ ይኖርብናል። ተክሎቹ ለዓቅመ-ፍሬ ደር ሰው፤ ውጤቱን ካየን በኋላ ነው፤ የተክሉን ምንነት መለየት የምንችለው ” በማለት ተናገረና ሊቃውንቱን አሰናበተ።

የተወለደ ማደጉ፤ የተዘራ መብቀሉ፤ የተተከለ መፅደቁ የማይቀር የተፈጥሮ ሕግ ነውና፤ እነዚያ ሥሉስ የፎኔክስ ስጦታ ፍሬዎች በቀሉ፤ አደጉ። አንጓቸው ሳይቀር አውቀው እንደ መዘዙት ያህል እያደር ተመነደገ። ቆፅሎቹ በየቀንበ ጣቸው ላይ አበቡ። ገና አበባቸው ታይቶ ሳይጠገብ፤ እምቡጥ ነታቸውን አልፈው ፍሬያቸውን አሳዩ። እያደር ጐመሩ እንጅ፤ ጅማሬያቸው ላይ ሐምራዊነት የሚፈነጥቅ ቀለም ነበራቸው። ውስጠ ውሃቸው፤ ይሆነኝ ብለው የቀመሙትና የጠመቁት ይመስል፤ አተኩሮ ላያቸው ሲላወሱና እርስ-በርስ ሲዋሀዱ በግልፅ ይታይ ነበር። ቀስ በቀስም ውህደታቸው ሠምሮ፤ ወፍራምና የረጋ ደም መሰል ፈሳሽ ይታይባቸው ጀመር። የእሸትነት አፍላ ዕድሜያቸውን እንዳገባደዱም፤ መጐምራታቸውን ለማሳየት፤ ፍፁም ጥቁር እርጎ መሰሉ። የተመለከታቸውን ሁሉ ቢያስጐመዥም፤ ቀጥፎ ሊበላቸው የደ

ፈረ አንድም ሰው አልነበረም። አንዱ ፍራቻ ምንነታቸው ያልታወቁ መሆናቸው ነበር። በመዓዛቸው ግን ሰዎቹ ብቻ ሳይሆኑ፤ መላው የቤተ መንግሥቱ ጊቢ ረክቷል።

ፍሬዎቹ በሙሉ ዕድገት በጐመሩበት ጊዜ፤ ወርኃ ዓመቱ በልግ ነበር። በዚያ በቤተ መንሥስቱ ቅጥር ጊቢ የሚ ገኙ ተክለ-ፍሬዎች ሁሉ የዐመቱን በረከት ያሚያበረክቱበት ወቅት በመሆኑ፤ ሁሉም አኵርተዋል። በትረሎሚው፤ ፖፖ ዬው፤ ብርቱኳኑ፤ ትርንጐው ወዘተ... ግሽጣውም በየበኩላ ቸው አፍርተው ከምግብነታቸው ሌላ ለሚመለከታቸውን አዕይ ንት ርካታ ይሰጡ ነበር። ጊቢውን የሚያውደው መዓዛቸው፤ ሌላ ሕይወት ይሰጣል። ይህ መዓዛና ትርዒት የማረካቸው አእዋፋት ሁሉ፤ በቤተ መንግሥቱ አናት ላይ ሲያንጐብቡ፤ ይውላሉ። የሚያስጠጋቸው ግን አልነበረም።

በከፍተኛ ጉጉት ሲጠባበቅ የከረመው ንጉሥ፤ ፍሬ ዎቹ ለመከር መድረሳቸው እንደተነገረው፤ በአንደኛው ቀን ከነአጀቡ ወደ ተክሎቹ ሔደ። ዘለላዎቹ ፍሬዎች ከመጐ ምራታቸው ብዛት የተነሳ ሙክክ ብለው በመብሰላቸው፤ አንዳ ንዶቹ አርግዘው የያዙት ፈሳሽ እየወጠራቸው ጧ ብለው ይፈ ነዱ ነበር። አሁንም ፍሳሻቸውን በማየት ይጐምጁ እንጂ ደፍሮ የቀመሳቸው አልነበረም። ንጉሡን አጅበው የተገኙት ሊቃውንትም፤ ያ ፍሬ የተክሉ ፍሬ መሆኑና በመጨረሻ የብስ ለት ደረጃው ላይም እንዳለ አረጋገጡ። ከመሐላቸው ምንነ ቱን ያወቀ ባይኖርም፤ ቀምሶ ለመረዳት የሞከረም ሆነ የደፈረ አልነበረም። ንጉሡ ግን በበኩሉ ያዘጋጀው እቅድ ስለ ነበ ረው፤ የደረሰ የደረሰውን ዘለላ፤ በዋድያት አጠራቅመው፤

t.me/OLDBOOKSPDF

እስኪኰመጥጥለት ድረስ በጥንቃቄ እንዲያስቀምጡ ላትክል ተኞችና ለቤተ መንግሥቱ መጋቢ አለቃ ትዕዛዝ ሰጠ። ይህን ልዩ ትዕዛዝ ባስተላለፈ በሁለተኛው ወር ላይ፤ በዋድያት ከተቀ መጠው ውስጥ የመፍላት ድምፅ በመሰማቱ፤ ለንጉሡ ተነገ ረው። ንጉሡም ወዲያው፤ ሞት ተፈርዶባቸው፤ ዕለተሞታ ቸውን ከሚጠብቁ ወንጀለኞች ውስጥ አንዱን ከእስር ቤት አስመጥቶ፤ ራሱ ንጉሡ ባለበት እንዲጠጣ ተደረገ። ያ ፍሬ መርዝነት ቢኖረውና ጠጭውን ቢገለውም፤ የሞት ፍርደኛ መመረጡ፤ በዚያው አድዮስ ቢልም ዋጋው እንጅ በደል እንደማይሆን ታስቦ የተደረገ ዘዴ ነበር። ያ እሥረኛ ግን፤ የመጀመሪያ ዋንጫውን እንደጠጣ፤ ኰሶ የጠጣ ያህል ፊቱን አኰማተረ። ጐምዛዛው የፍሬ ወሃ ጐመዘዘው፤ መረረው። ጕሮሮውን፤ ላንቃውን፤ ትናጋውን፤ ከንፈሩንና ምላሱን ጭምር አንጣጣው። በዚህ ምሬት ያልተበገረው ያ ሸካራ ጥርሱ ብቻ ነበር። የጕሮሮውን ቁልቁለት ወርዶ ከሆድ ባሕሩ ሲገባ ግን፤ ሌላ ስሜት ነበር የሰጠው። ወንጀለኛው በመ ጠጡ ጣዕም የተሰማው ስሜት በገፅታው ላይ ልዩ ሁኔታ ይነበ ብበት እንጅ፤ ሆዱን አልቄረጠውም፤ ወይም አልፈለ ጠውም። ይህን ሁኔታ በአንክሮ ይመለከት የነበረው ንጉሥ፤ ሁለተኛ ዋንጫ ይፈልግ እንደሆነ እሥረኛውን ጠየቀው። ቆራጡ እሥረኛ ግን፤ መፈተኛ መሆኑን ባይረዳም፤-

" ታድዬ! አግኝቼ ነው እንዴ! " ሲል መለሰ። ንጉሡም ድግሙት አለና፤ ሌላ ኣንድ ዋንጫ ሙሉ ተሰ ጠው። አፍታም ሳይቆይ ዋንጫውን አፈፍ አርጐ እንደተቀ በለ፤ ወዲያው ባንድ ትንፋሽ ጭውውው አርጐ ጨለጠው።

ከሆዱ መጠጡ እንደደረሰ፤ ድል ያለው ግዛት አሰማና “ እሠይ! ” አለ። ወዲይው ከተቀመጠበት አፈፍ ብሎ በመነ ሳት፤ ንጉሡን የዝንብ ያህል ሳይቆጥር፤ ይዘፍን፤ ይዘምር፤ ያቅራራ ይጨፍር ገባ። በሕይወቱ አጋጥሞት የማያውቅ ደስታ ጠቅላላ ሰውነቱን ወረረው። በፍፁም ደስታ ሰጠመ። ከተሠረገበት ዕለት ይልቅ ያ ወቅት አስፈነደቀው። ዘለለ ፈነ ጠዘ። አውታረ ሰውነቱ በተድላ ሲነዝሩ ተሰማው። ሕዋሶቹ ማሲንቆኣቸውን ሲከረክሩ፤ ክራራቸውን ሲያከሩ፤ ከበሮ አቸውን ሲደልቁ ተሰማው። ሕዋሳቱ በመላእክት እንዚራ ታጅበው በሕዋ ላይ ሲንሳፈፉና ሲከንፉ ታየው። እነኣርያም እነራማ ተበርግገው ወለል ብለው በራዕዩ ሳይሆን በውኑ ተከሠቱለት። የሚያየው ሁሉ ብርሃን የተጐናፀፈ፤ ፀጋ የለበሰ መሰለው። ባጠቃላይ ሰው ከመሆኑ ክልል የወጣ ልዩና ሌላ ፍጡር የሆነ ያህል መሰለው። የሚናገረው ጣመለት፤ የዘመ ረው ተሰማለት፤ ያደረገው ሁሉ ተደነቀለት። ያልነበረው ጉል በት ተሰማው። የመጀመሪያው ዋንጫ ቅምሻ ፊቴን በምሬቱ ያኰማተረበትን ያህል፤ ሁለተኛው ዋንጫ፤ ገፁን ብቻ ሳይ ሆን መላ ዐካሉን አቀላለት። ያጋሙት ፍም መሰለ። ገዳይነቱን ቀርቶ ወንጀለኛነቱንአስረሳው። እሰይ! እልል አለ....

ያን አስደናቂ ሁኔታ ያየ ንጉሥ፤ አላስችል ብሎት፤ እንደገና ለሦስተኛ ጊዜ አንድ ዋንጫ እንዲጨመርለት ለማ ዘዝ ሲዘጋጅ፤ ከንጉሡ ቀድሞ እሥረኛው እንዲጨመርለት ንጉሡን እንዲህ በማለት ተማጠነ። “ በወለደችህ እናት! ሌላ አላስቸግርህም። ሌላ አንድ ዋንጫ እንዲሰጠኝ እለምናለሁ። የመጨረሻዬ ይሆናል። ከዚያ በኋላ የፈለጋችሁን ለማድረግ


t.me/OLDBOOKSPDF

ትችላላችሁ፡--- ብታርዱኝም ብትሠቅሉኝም እንደ ፈለጋችሁ! በሰው ልጅነቴ፤ መሞቴን በመወለዴ አውቀዋለሁ! መዋቲነቴን ልደቴ አስቀድሞ አስተምሮኛል-- ብቻ አንዲት የመጨረሻዋን ፅዋ አትንፈጉኝ! ”

ለመፈተኛ የተዘጋጀ መሆኑን ንጉሡ ያውቃልና፤ እሥረኛው የሚሆነውን ሁኔታ ሳይሆን፤ መጠጡ የሚያደ ርገውን ውጤት ለማየት ሲል፤ በእሥረኛው ጥያቄ መሠረት ሦስተኛው ፅዋ ተፈቀደለት። የመጨረሻውን ሦስተኛ ዋንጫ እንደጠጣ፤ ሆዱን ሳይሆን ራሱን ከበደው። ብዙም አልቆየም ወደቀ። ከወደቀበት ወዲያው እንቅልፍ ይዞት ጭልጥ አለ። ከዚያ እንቅልፉ የነቃው በሁለተኛው ቀን ማለዳ ላይ ነበር። ጠባቂዎቹ ባለሟሎች በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት፤ እንደ ነቃ፤ ሲጠብቀው ወደ ነበረው ንጉሥ ዘንድ ወስደው አቀ ረቡት።

“ ትናንትና ምን ጠጥተህ ነበር ? ምንስ ዐይነት ስሜት ተሰማህ ? ” ስለነዚያ የፎኔክስ ፍሬዎች ውጤት ለማወቅ፤ በጉጉት የቆየው ንጉሥ፤ ለዚያ እሥረኛ ያቀረበለት፤ የመጀመሪያ ጥያቄ ነበር።

“ ምን ዐይነት መጠጥ እንደጠጣሁ አላውቅም። ግን በሕይወቴ ያላጋጠመኝ ከፍተኛ ጥሩ ስሜት ነበር የሰጠኝ። አርኪ ነበር!” በማለት ባጭሩ መለሰ። የመጠጡ ስሜት ገና አልለቀቀውም ነበር። ያለወትሮው ባንድ ቀን ውስጥ ሴለ-ደሞቹ አብበውና ለምልመው ማደራቸው፤ በዚያ ወቅትም ይሰማው ነበር። ሰውነቱ ሳይቀር ልዩ መዓዛ ይረጭ ነበር።




ላለም ወይን መገኘት፣ መነሻው ምክንያት፣
ያ ከደሲ ከሆነ፣ ከሳችው መሠረት፣
ይወጣው ይሆናል፣ ጠቃሚ መድኃኒት፤
በዘዴ ጨብጦ፣ በጥበብ ቢጨምቁት!

t.me/OLDBOOKSPDF


“ ንጉሥ ሆይ፤ ፈቃድም ቢሆንልኝ፤ ዛሬም ቢለገሠኝ ምኞቴ ነው! የመጀመሪያዋን ፅዋ ስቀምስ፤ የአሲድ ጣዕም ያህል ምሬቱ ጐምዝዞኝ ነበር። ባሕረ ሆዴ በደረሰ ጊዜ ግን እንድደግም አሰኘኝ። ሁለተኛው ጽዋ ሲደገመኝ፤ ተዝናና ዝፈን ጨፍር የሚል ስሜት አሳደረብኝ። አብሮኝ የኖረው አፋርታምነቴ፤ ዐይነ ጥላዬ ለቆኝ ሲሄድ ታየኝ። ያን ጊዜ ነበር፤ ይህ ዐለም ለሰው ልጆች መደሰቻና መፈንጠዝያ ልዩ ሠገነት ሆኖ ያገኘሁት። ይህን ዕድል ሳላገኝና ጠበሉንም ሳልቀምስ ብሞት ኖሮ ምንኛ በቆጨኝ ነበር!! ” በማለት አድና ቆቱን ካንጀቱ ገለጠ።

ንጉሥ ሻሚራንም፤ በዚያ እሥረኛ ናሙናነት፤ የዚያችን ባለውለታ ፎኔክስ ወሮታዊ ስጦታ ምንነት መረዳት ብቻ ሳይሆን፤ “ መጠጥ ” ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ ተማረ። ይህ በተገለፀለት በሣምንቱ፤ ከዚያ በፊት ተደርጐ ያማያውቅ ከፍተኛ የፌስታ ድግስ አርጐ፤ መሳፍንቱንና መኳንንቱን በዚያ የወይን ጠጅ አሰከረው። እሱማ የሚነቃበት ጊዜ እስኪጠፋበት ድረስ በየቀኑ ይጐነጭ ጀመር። “ ወይን ያስተፈስህ ልበ ሰብ ” የሚለውን የመኢጠማ እውቅ መፈክር (መርሖ) በመቀየር “ ወይን ያስተፈስህ ሴለ-ሰብ ” ያለው ይኸው ንጉሥ ሳይሆን አልቀረም። ታዲያንን፤ ከዚያ ሁሉ የፌስታ ግርግርታና፤ ያጋጣሚ ትንግርት ውስጥ በጣም የሚገርመው፤ በዚያ ታላቅ የወይን ጠጅ በዓል ላይ፤ አስገኝዋ ፎኔክስ፤ ሽልማቱና ሌላው እንኳ ቢቀርባትም ቅሉ፤ በእንግድነት ወይም በተጋባዥነት አለመገኘቷ ነበር!!




ቤተ-መንግሥት ይሏል ፤ እንደዚህ ነው እንጅ
ወይንን ያስመረተ ፤ ለ " ሴል " የሚበጅ !

t.me/OLDBOOKSPDF



እንዳትሙ ጠጥቶ፣ እንዲረካ ባለም!
እኔ ብለግሠው ፣ ወይን ያለው ልዩ ጣዕም!
ሰክሮ ይረብሻል ፣ አንዳንዱ ድንባጓም!

t.me/OLDBOOKSPDF



ክንፍማ ቢኖረኝ

ክንፍ የለሽ ሆኜ እንጅ ፣ክንፍማ ቢኖረኝ
መቶ ያስችለኝ ነበር ፣ እኔ አንቺን ሳልጐበኝ??
መቶ ያስችለኝ ነበር ፣ እስከ ዛሬ ድረስ፣
ያችን ውብ ሀገሬን ፣ ላላይና ሳልደርስ!
ከምድር ጥጋት ሆኖ ፣ ያለሁበት ጋጣ፣
ርቀት ድል መታኝ ፣ ስታገል ልመጣ!
ተቸግሬ እንጅ ነው ፣ ሱንጎው እግሬ ቦያጥር ፣
አለያማ በርግጥ ፣ እጐበኝሽ ነበር።
እንደ ወፎችማ ፣ ኖሮኝ ቢሆን ያ ክንፍ!
ባልዘገየሁ ነበር ፣ እዚህ ሰንከረፍፍ!
በርሬ አያት ነበር ፣ ምን ዚት እንደሞጣት
ጉስቁሏን ሀገሬን ፣ እርግብግቧን እናት!
ተባራሪ ወሬ ፣ ከሚያላግጥብኝ ፣
ክንፌ አያት ነበር ፣ ክንፍማ ቢኖረኝ!!
ሸረ አፅዋፋት ፣ ክንፋችሁን ልዋስ ፣
ሀገሬን አይቼ ፣ ደርሼ እስክመለስ።
ንጋንግ ሆኜ ፣ ብገባ ከሀገር!
የናቱን ተባዮች ፣ በጠዘጠዝኩ ነበር!

t.me/OLDBOOKSPDF